

# ግራጫ ቃጭሎች

አዳም ረታ

የቴሌግራም ቻናላችንን
በመቀላቀል
ሌሎች
አማርኛ ና እንግሊዝኛ ልብወለድ
ትረካዎች
ያግኙ

ይሄን ይጫኑ

ወይም

@amharicbooks24

# እንደ መግቢያ

ልብ ወለድ የቀለጠ `ፋንታሲ´ም ቢሆን *(ከመ ስብሐት ለአብ ገብረ እግዚአብሄር (ስምንተኛው ጋጋታ/ ኢጋፋሪ እንደሻው)* ከመ የይሁን እንደሻው ቀልደኛ ወዳጅ አባ ገድል *(አምራው ሼህ)* ማሕበራዊ መነሾ አለው:: ቢያንስ መጠቀሚያ ቋንቋው በመዝገበ ቃላት ስርዓት የታሰረ ነው:: እዚህ ፈጠራ ውስጥ የተፃፈው ታሪክ በሙሉ ከላይ እስከ ታች "መዝገቡ ዱባለ" ይመስገንና ቅጥፈት ነው:: በተአማኒ ቅጥፈት ውስጥ ዕውነትን ለመንገር::

የመጀመሪያዬ ረዥምም ልብወለድ ነው:: ይህን መግቢያ የመፃፍ ዓላማ ያሳደረብኝ ዋና ጉዳይ ከዚህ በታች ስላሉት ሦስት ነጥቦች በአጭሩ የመናገር ሽታ ነው.......

## እንጀራ፣ እንጆሪና ሕፅን:

***እንጀራ:*** *("በቁሙ ሴቶች በምጣድ ላይ አስፍተው የሚጋግሩት የሰው ሁሉ መኖ፣ ባለ ብዙ ዐይን::"* ዐዲስ የማርኛ መዝገበ ቃላት: ከደስታ ተክለ ወልድ)

ሴቶች ብቻ ሳይሆን ወንዶችም ይጋግሩታል፤ በተለይ በዘመኑ የውጭ አገር ስደት ላይ:: ምንም እንኳ ሸውራራ አይኖች ቢሆኑም የዚህ መጽሐፍ ደራሲም ጥቂት እንጀራዎች አዙሯል::

***እንጆሪ (እንጌራዊ):*** *("ፍሬው የሚበላ እሾሃም ዐረግ::"* ዐዲስ የማርኛ መዝገበ ቃላት: ከደስታ ተክለወልድ)

የጹር ፍሬ ነው፤ ገና 'ያልሰለጠነ' ወይም ለመሰልጠን ቢጠብቅ ችል የተባለ:: ዐረግ የመሰለ ዛፍ ላይ ይበቅላል:: ፍሬው በጥሬነቱ መሐከለኛ ጠጣርነት አለው:: ሲበስል ቀይና በጣም ሲበስል ደግሞ ያሞከሞከ ጥቁር ጣፋጭ ፍሬ ይሆናል:: አንዱ ዘለላ ልክ እንደ ወይን ፍሬ ከደቃቃ ኳስ መሰሎች የተሰራ ነው--ቢያንስ የሜጢ (ከአዲስ አባ በስተ ምዕራብ ያለ ሠፈር--ከዚህ አጠገቤ ካለው የእንጆሪ ዐይነት ልነሳ ስላልኩ):: ቢተልቁ ቢተልቁ በአብዛኛው ከአውራ ጣት አይተልቁም::



@BOOKALEM

ሌላ ዐይነት እንጀሪዎች ቢኖሩም ኳሶቹ በጠቃጠቆ ይተካሉ:: የተለያዩ ዝርያዎች ቢኖሩም እኔ ላነሳው የፈለግሁትን ጉዳይ አይረብሹትም::

***ወሽመጥ:*** *("የሱሪ ወንበርና የጥብቆ የእጀ ጠባብ ሠላጤ፣ ሕፅን፣ የጠበበ ልብስ ማስፈያ::" ዐዲስ የማርኛ መዝገበ ቃላት ከደስታ ተክለወልደ)*

ወሽመጥ ብዙ ጊዜ በስፌትና በስፌት መሃል የሚገባ ነው:: መዝገበ ቃላቱ ግን አይጠቅስም:: እንደ መዝገበ ቃላቱ ልቅ ትርጉም ማስፈያው የትም ሊገባ ይችላል:: ብዙ ጊዜ በጠበቡ የሱሪ እግሮች መሃል:: በብብት:: በወገብ:: የእጀታ ማርዘሚያ:: የወሽመጥ ሰው ባልሆንም ልጅ እያለሁ ጥቂት ያህል ሳላስገባ አልቀርም፤ በተለይ ያኔ ጠባብ ሱሪ 'ፋሽን' ሆኖ አባት ግን 'ፋሽነብል' ሳይሆን:: ......አባት ታዲያ እንዲህ ይል ነበር:

"ምን የሚሉት ነው ተጣብቆ ፊንር ፊንር ማለት:: ጉድ! ቁም ነገር ተኘቶ ተሞቷል:: ሳይንሱን ማጥናታችሁ ነው? በል ወሽመጥ አስገባበት!"

ወይም፤

***ሕፅን :*** *(1: "ሁለትና ሦስት ራስ፣ እግር ባላቸው ፊደሎች በየቅርሣቸው መካከል ያለው ክፍቱ፣ ባዶው:: ትርጓሜው አጠገብ ማለት ነው፣ ውስጥንም ያስተረጉማል::*

*2: "የጥብቆ የእጀ ጠባብ ሠላጤ ወሽመጥ::" ዐዲስ የማርኛ መዝገበ ቃላት ከደስታ ተክለወልደ::)*

እንጆሪ፣ ሕፅን/ወሽመጥና እንጀራ ከዚህ ልብ ወለድ ጋር ምን አገናኛቸው?

'እንጀራ' እንጀራ የተባለበት ምክንያት የዓይኖቹ ጠቃጠቆ የእንጆሪ ፍሬ ስለሚያስመስለው ነው የሚሉ አሉ:: እንጆሪ ሞላሌ ገላው ከትንንሽ ቀዳዶች (ጠቃጠቆዎች) (ኳሶች) የተሰራ ወይም ያሉበት ፍሬ ነው:: የዚህን መፅሐፍ የአፃፃፍ ቅርፁን የተዋስኩት ከእንጀራ ቅርፅ ነው:: በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት ምዕራፎች ከእንጆሪው ጠቃጠቆ (ንዑስ ፍሬዎች) ጋር ወይም ከእንጀራው ዓይኖች ጋር እንዲማሰሉ ሆነው ነው የቀረቡት (አንድ ዐይን/ጠቃጠቆ እንደ አንድ ምዕራፍ):: ታዲያ በአሰያየም ውስጥ ከእንጆሪ ወደ እንጀራ ከመጣን ለምን ከእንጀራ ወደ እንጆሪ



@BOOKALEM

እንሄድም? ከዚያ ወደዚህ የወሰደን መንገድ አይመልሰንም ማን አለ? ወደ መነሻው ሄድኩና ለዚህ ልብወለድ ቅርፅ እንጀራ የተሰኘ ስያሜ ሰጠሁት ወይም መረጥኩ።

**ተጨማሪ ማብራሪያ:**

ጥሩ ሆኖ የወጣ እንጀራ በዐይኖች የተሸፈነ ነው። ከእንጀራው መጋገር እንነሳ። ምቹ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በጋለ ምጣድ ላይ ሊጡ መዞሩን ሳያቆም እንጀራው ቀዳዳ ማውጣት ይጀምራል። ቀዳዳዎቹ በሊጡ ገፅ ላይ በተለያየ ዕርቀትና ጊዜ ይፈላሉ። የተለመደ ተራ የለውም። አንዱ ዐይን ከሌላው ዐይን ያለው ቅርበትና ዕርቀት የተሰላ ጂኦሜትሪ የለውም፤ ማለት ዐይኖቹ እርስ በእርሳቸው በዚህን ያህል ሚሊ ወይም ሳንቲ ሜትር ይራራቃሉ ብለን መወሰን አንችልም። በጆሜትሪ የተደረደሩ የእንጀራ ዓይኖች (ማለት አንዱ ዐይን ከሌላው ዐይን ወይም አጠገቡ ካለው ዐይን በሁለት ሚሊ ወይም ሳንቲ ሜትር ያህል ወይም በሌላ መሰል የታቀደ ስልት የተራራቁ) ቢፈሉ ሳይዞርብን፤ ሳያስደነግጠን አይቀርም። (ምናልባት እንዲህ ዓይነቱን እንጀራ፡ "ይሄ የፈረንጅ እንጀራ ነው" ሳንል እንቀራለን?) (ከት ከት ከት)።

እንጀራው ሲጋገር ከሁለት ሁኔታዎች ጋር እንገጣጠማለን፡ ጊዜ እና ቦታ (በስነፅሑፍ ቴክኒክዊ ቃል "መቼት")። ጊዜ ስል ዐይኖቹ በተከታታይነት (በአናሳ የጊዜ ክፍፍልም ቢሆን) መፈጠራቸው፤ ቦታ ስል ዐይኖቹ ከሌላው ዐይን ጋር ያላቸው መቀራረብና መራራቅ። እዚህ መግቢያ ላይ ጉዳያችን ከዐይኖቹ ብቻ ነው። ይሄ ሞዴልም በአንድ ጊዜ የሚፈሉትን ዐይኖች ሳይስት ነው። እዚህ የሚያጋጥመን እያንዳንዱ ምዕራፍ በአብዛኛው ከአንድ የስሜት አካል (መመልከት) የተገነባ ነው። እያንዳንዱ ምዕራፍ ከሌሎች ምዕራፎች ጋር አስፈላጊ ወይም አላስፈላጊ ግኙኝነት ሊኖረው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ መቼቱ ግልፅ ያልሆነ "ነፃ ገፅ" ያጋጥመናል—ከሌሎች ምዕራፎች ጋር የረባ ግኙኝነት የሌለው። እንዲህ መሆኑ አባቢ አይደለም። አጠቃላይ ፕሮጀክቱን አያጠፋውም። እንደውም ለአጠቃላይ ግብሩ ተሻራኪ ድባብ ይሆነዋል። ይሄ ዐይነቱ ምዕራፍ በወሰድነው የእንጀራ ተምሳሌት በግራ ወይም በቀኝ በኩል ያፈጠጠ ("በልጠጥ ያለ ዐይን" ያለው) "ዋና" ካልሆነው ምዕራፍ ፈንገጥ ያለ የመሰለ ግን እንደ "ዐቢይ" ዐይኖች ውጥ የሚቀበል ዐይን ነው። አጠቃላይ የድርሰቱን ንቅናቄ የማይገታ ምዕራፍ ነው። ቢያንስ ቢያንስ ስለተራኪውና ስለ ተራኪው አካባቢ ማወቅ እንችላለን።



@BOOKALEM

## ስለ ተለጣጭ ወይም ተስፋፊ ልብወለድ፡

እንደዚህ ዐይነት ምዕራፎች መጠነኛ ማዕከልነት ተሰጥቷቸው ከመፅሐፉ ጀርባ እንደ ሕዳግ ማስታወሻ ይቀርባሉ:: ያን ጊዜ ሕፅን ወይም ወሽመጥ እላቸዋለሁ:: ሕፅኖች መረጃ ወይም ማስታወሻ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን የቻሉ ታሪክ ሊሆኑ ይችላሉ:: አንዳንድ ሰው 'ለምን ከታሪኩ ጋር ተወስውሰው አይሰሩም' ነበር? ብሉ ሊጠይቅ ይችላል:: ውስወሳ 'ዕውነታ' ያጥረዋል:: ሕይወት እንደዛ አይደለም:: ውስወሳ ምሕንድስና ነው:: ከፍተኛ የሆነ ደራሲው ራሱን የዶለበት ግንባታ እንዳለ ያሳያል:: ሕፅኖች ከዚህ በሆነ ደረጃ (ከፍ ዝቅ ቢሉም) ያላቅቁናል:: ይሄም ትረካችንን ቢያንስ መጠነኛ ግብታዊነት ይሰጠዋል:: ትንሽ ነፃነት:: ከምትሃት ውስጥ ሌላ ምትሃት ለመፈልቀቅ እንዲያመች አድርጎ:: በዚህ አባባል 'በመገሸሻቸው' ሕፅኖች ምሳሌ በጉያቸው ሸውከዋል ማለቴም አይደለም:: ወደዚያ የሚንጠራሩ ቢኖሩም ልዩ ማስጢርና ተዓብ አልያዙም::

ስለ ሕፅን ትንሽ ልጨምር:: ማንኛውም ልብወለድ አያልቅም:: ማለቁ ምትሃት ነው (ምሉዕ አይደለም):: የመስፋፋት ድብቅ ሐይል (ፖቴንሽያል) አለው:: ይሄ እኔ የምጠቅሰው መስፋፋት ግን በመለጠጥ የሚመጣ አይደለም፣ ቢያንስ በእኔ የግል ትውፊት:: መለጠጥ ግራና ቀኝን ያሳያል እንበል–ከመጀመሪያውና ከመጨረሻው ይዞ (ልክ እንደ ላስቲክ) በመጎተት ማስፋት:: እኔ የምለው መስፋፋት ግን ከመሃል ልክ እንደ ወሽመጦች (ሕፅኖች) ዐቢይ ምዕራፎች በማስገባት 'ያመለጡ' አዳዲስ የእንጀራ/እንጆሪ ዐይኖችን (ታሪኮችንና መረጃዎችን) በማስገባት መስራት ማለቴ ነው:: እንደገናም ለእነዚህም ዐቢይ ምዕራፎች ሌሎች ሕፅኖች በመፍጠር ማለት ነው:: ስለዚህ እኔ ስለሚስፋፋው ልብወለድ ሳወራ ስለስግሲጋ ማለቴ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ወሽመጦች ተዋረድ ሳይጠብቁ ከተጠቀሱበት ምዕራፍ ወጥተው የበላይ ነን ሊሉ ይጥራሉ:: ሊሆኑ ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ የተረሳ ነገር ከምናስታውሰው የበለጠ የበላይነት ሊኖረው ይችላል:: ሕፅን ከዝንጉነት መውጫ መሳሪያ ልትሆን ትችላለች:: መኖር መዘንጋትም (ደረሳል እንጂ) ነው::

አንዳንድ ሰዎች ሕፅን መስራቴን 'መንዛዛት' ነው ሊሉ ይችላሉ:: ምነው ጃን የዘነጉትን ነገር ቢያስታውሱ መንዛዛት ነው? ለምሳሌ አንድ ሰው ሊያወራ የጀመረውን



@BOOKALEM

ነገር አርግቶ፣ አንጠልጥሎ አርዕስት ቢለውጥና ሌላ ታካኪ ትረካ (በእኔ ወሽመጥ) ቢጀምር በነገሩ ተበሳጭተው (የሚያበሳጭ ጉዳይ ባይሆንም) "መጀመሪያ የጀመርከውን ጨርስ" ቢሉት ትንሽ የአተራረክ ቁንጥ ወይም ቃና ያሚያናጋ አይመስልዎትም? ብዙ ጊዜስ ዋና አንገብጋቢ ጉዳይ ረስቶ አንዳንድ ሕብረተሰብ ወሽመጥ ጉዳዮች ላይ ሲያፈጥ ይውል የለ:: ግን በአብይ ትረካውና በሕፅኖች መካከል ተዋረድ አለ:: ዐቢይ ትረካው ያለ ወሽመጥ ዕድሜ ሊኖረው ይችላል:: ወሽመጥ ለብቻው ግን ጥያቄዎች እንድንጠይቅ ያደርገናል:: ወይም "ከየት መጣ ይሄ ታሪክ" ያሰኛል:: ዓለም ተዋረድ እንዳላት ትረካስ ቢኖረው እንግዳ ነው? ዝንጀሮ "መጀመሪያ የመቀመጫዬን" ስትል ቅደም ተከተል (ፕሪዮሪቲ) ማውጣቷ አልነበረም እንዴ::

ይሄ ልብ ወለድ በሌላ ጊዜና ቦታ እጥፍ ድርብ ሊሰፋ ይችላል–እንዳያሰለች ከተደረገ:: ተዋረዱስ ቢፈርስና ጥያቄ ውስጥ ቢገባ ማን ይጎዳል? ሁሉስ ልብወለድ አይደሉ::

*የከረመ ሒስና እንጀራያዊ ቅርፅ:*

ድርሰቱ በመጀመሪያ የተፃፈው በአንደኛ ነጠላ ተውላጠ ሥም ልክ ከላይ እንዳልኩት *በፍፁም* እንጀራ ስልት ነበር:: እያንዳንዱን ምዕራፍ ከሌላ ምዕራፍ የሚያያይዘው የተባ ሴራ አልነበረም:: እያንዳንዱ ምዕራፍ ከሞላ ጎደል ራሱን ያገለለና ራሱን የቻለ ነበር:: *ጥያቄ:* ምስሉ ከእንጀራ ዐይኖች ከተወሰደ እኮ የእንጀራ ዐይኖች ስር ለስር ይገናኛሉ፣ ለዚህም ነው ወጥ የሚያርሳቸው:: *መልስ:* አስፍተን ብንቀርብስ......የሚገናኝም የማይገናኝም አለ ብለን:: ከተገናኘ ልቅ ትርጉም፣ ካልተገናኘ ተምሳሊታዊ ትርጉም ወስደን ወይም የተገላቢጦ::

ይሄ አቀራረፅ ስለባይተዋርነት ብዙ ያወራናል:: በምሳሌ ላድርገው:: በ35 ዓመቱ ይህን መፅሐፍ የሚያነብ ሰው ዕድሜው ከ1 እስከ 10 በነበረበት ወቅት የሚያውቃቸውን ሰዎች በሙሉ ዛሬ ያውቃቸዋል? ሁለተኛ ደረጃ ሲማር ከሚያውቃቸው ልጆች ዛሬ ኮሌጅ ጨርሶ ለሥራ ከው ከው ሲል ስንቱን ጎዳና ላይ ቢያያቸው ያውቃቸዋል? ወይም ስንቶቹ በሕሊናው ውስጥ ብቅ ይላሉ? በጊዜና በቦታ አይገናኙም:: 'መራራቅ' የቦታም ብቻ ሳይሆን የጊዜም ነው በተጨማሪም የመንፈስም ነው:: ያዝ ያዝ የለም:: መታደል ካለ ያዝ ለቀቅ እርግማኑ ሲመጣ ደሞ ለቅቅ ነው



@BOOKALEM

ያለው:: በአብዛኛው የሚቀረው ትዝታ እያመነዠከ ብቻ ሳይሆን ያልተጠናቀቀ ትዝታ መሆኑም ነው:: ትውስታም ትከሳለች:: "ነበር" እንደፈለገው ተረጋግቶ አይሰበስብትም:: በዚህ ልቦለድ ውስጥ የመርሳት ኪነት ለመፍጠርም የመሞከር ነው:: 'ያልተባለውን' አንባቢ በነፃ በምናቡ እንዲገምት......

......ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ ግን ቢያንስ ለንባብ ርትዕ እንዲሆን በብዛት በወሽመጥ የሚነቃነቀውን ልብወለድ በመጠኑ ቀጥተኛነት ልሰጠው ሞከርኩ:: ወሽመጦችን "ከውስጥ"ና "ከውጭ" በማከማተር ግን ሳልተዋቸው ልብወለዱን "በዐቢይ ምዕራፎች" "ምሉዕ" ሳደርገው ጣርኩ:: ክለሳው የተሞከረው ከ"ኢምፐረሺንዝም" በላይ ለመሄድ ጥረት የማድረግ ልፋት ነበር......ከንድፍ(?) እስር ለመላቀቅ:: ግን ለመዝገቡ ዱባለ ሕይወት የንድፎች(?) ድምር ነው:: ነገሮች ቢያያዙበት እንኳን ሳያቅዳቸው በገጠመኝ ነው:: በዚህ ድርጊት ውስጥ ከወሽመጥነት ወደ ዐቢይነት የተሸጋገሩ ነበሩ (በመጠነኛ ለውጥ):: ይሄ የከረመ ግለ-ሒስ የተዋጣ ሆኖ እንደሆነ ፈታሹና ፈራጁ አንባቢ ነው::

እነዚህን ሕፅኖች ወይም ወሽመጦች ከሕዳግ ማስታወሻ የሚለያቸው ምንድነው? "ለአሮጌ ነገር አዲስ ስም በመስጠት ለመሸወድና የተለየ ለመምሰል ካልሆነ በስተቀር" ብሎ አንድ ሰው ሊከራከር ይችላል:: "የተለመደው" የሕዳግ ማስታወሻ ግዴታ ነው:: ሳይንስ ነው:: የምናውቀው የሕዳግ ማስታወሻ አይኳሽም:: ቀጥተኛ ነው:: ማለት ከዋናው የምርምር ወረቀት ጋር የጋለ ሽርክና አለው:: እስከ ዛሬ ሕዝብ ያነበባቸው የሕዳግ ማስታወሻዎች ከፖለቲካና ከታሪክ ምርምርና መጣጥፎች ጋር የተያያዙ ነበሩ:: እዚያ ሕፅኖች ዋቤ መጻሕፍት ማጣቀሻ ናቸው:: እዚህ ድርሰት ውስጥ የሚጣቀሰው ግን የሰፈር ወሬና ትውስታ (የባለታሪኩ ብቻ ሳይሆን የሌላም ሰው ትውስታ) ነው:: በኢትዮጵያ ዐይነት ሕብረተሰብ ውስጥ የብዙዎቻችን ዕምነት (ርዕዮተ–ዓለም) የሚፈጠረውና የሚከረው በአብዛኛው በመንደር ወሬ ነው:: ያ ታላቁ መፅሐፋችን ነው:: ስናወራ የምናጣቅሰው በምርምር ወይም በተጨባጭ መረጃ የበለፀገ አካባቢ ሳይሆን ዕውነት ይሁን ውሸት እንደሆነ የማይታወቅ "በመተማመን" የጠጣነው የወሬ "ኢንሳይክሎፔድያ" ነው:: "የግራጫ ቃጭሎች" ሕፅኖች ሰፈራቸው ኪነት ነው:: እንዲያም ሆኖ መፅሐፉን በሴራ (ፕሎት) ወደፊት አይገፉትም:: አንዳንዶቹ እንደውም በትውስታ ውስጥ የመጡ ትውስታዎች ናቸው:: ትውስታ እንደ ሳይንሳዊ እውነት ፍፁም አይደለም:: በዚህ ፍፁም ባለመሆኑ ውስጥ ጨዋታ የማምጣት ነው:: ሕይወትም 'ዐቢይ'ና 'ሕዳግ' አላት:: ትረካው ከሁለቱ የትኛው እንደሆነ ወሳኙ ባለቤቱ ነው እንጂ:: ከባለቤቱ ያወቀ ማነው? ተንታኝ? ደራሲ? ቡዳ? ሠላይ?



@BOOKALEM

አንድ ፅንሱ-ሐሳብ ከሌላ ፅንሱ-ሐሳብ በትንሽ ነገር እንኳን ቢለይ አዲስ ስያሜ የማውጣት መብት አለኝ። ማንኛውም ሰው አለው። ለምሰራቸው የፈጠራ ስራዎች በቅርፅ የራሳቸውን ባሕርይ ልሰጣቸው እሞክራለሁ። አዲስ ጉዳይ ቅርፅ ነው። ለአስተማሪነት ቀበቶዬን አጥብቄ አላውቅም። የማን ወገብ ከማን ይበልጣል? የማንስ ድግ? እዚህ ድርሰት ውስጥ የአዳም ድምፅ የለም። ስራዬ በገለልተኛ ንቅናቄ መስታወቱን የመገለባበጥ ነው። ተዳፋቱን እዚያና እዚህ በማድረግ ያመለጠን እውነታ ከፍርድ ሳይጠጉ ለአንባቢ ዐይን ማብቃት ነው። ድርሰት ኮስታራነት ብቻ ሳይሆን ጨዋታም ነው። እዚያ ድረስ ጎዳናው የእኔ ብቻ ነው። ከዚያ ወዲያ መዝለቅ ለዝናናነት ወይ ለአንጀባ መልፋት።

***እየቀላ ሒደ፡***

ሕፅኖቹ ወደ ጀርባ ሲገፉ በዕርግጥ ዝቅተኛ ቦታ አላቸው ማለት አይደለም። ማድፈጣቸው ነው። ሕፅኖቹ በመፅሐፉ ውስጥ ለአንባቢው የሚጠቀሱት በቀይ ቀለም ኩለት ነው። በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ገድል (በሌላም?) አፃፃፍ ዋና "ባሕርያት" (ቅዱሳን፣ መላዕክትና እግዚአብሄር) የሚወከሉባቸው ቃላት የሚፃፉት በቀይ ቀለም ነው። በዓለማዊ ፅሁፍ ውስጥ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድሕን በሼክስፒር የሐምሌት ትርጉሙ (ማክቤዝ?) ውስጥ የገፀ-ባሕርያቱን ስሞች (በግራ ረድፍ ሲፃፉ) በሙሉ ቀይ ቀልሚቸው እንደነበረ ትዝ ይለኛል (ካነበብኩት ጥንድ አስርታት አልፈዋል)። ፀጋዬ ይሄን ለምን እንደሠራ ለመገመት አልፈልግም። እሱም የሚነግረን አይመስለኝም። ገፀ-ባሕርያቱም የእግዜር ወይም የመላዕክት እኩያ አይደሉ—ምንም እንኳ ሼክስፒር ቢፅፋቸው። ቀይ መሆኑም ትኩረት ከመሳቡ ውጭ ሌላ የድራማው ወይም የድርሰቱ ቀኖና አይደለም—ሲመስለኝ። እዚህ ውስጥ የባለታሪኩ ዓላማ ቀይ የተቀለመው ቃል/ሐረግ ሕፅን/ወሽመጥ መሆኑን ሊያመለክተን ነው። ትኩረትን ስቦ ነገርዬው ላይ (እንደ ገድሎቹ) እንድትተክዙ አይደለም። እንደ ጎዳና ነው። ጎዳና ላይ እንዳሉ አካፋይ መስመሮችና የትራፊክ መብራቶች ነው። እዚህች መጋቢ መንገድ ገብታችሁ ተመለሱ ወይም እዚህ አካባቢ የሚጎላ ነገር አለ ልል ነው። ትንሽ የትረካ ትርንጓፍ አለ ብዬ ልጠቁም ነው። ብርገ ሲቀዳ፣ ተቀድቶም ሞሰቡ መሐል አይቀመጥም፣ እንዲህ ወደ ጎን ወጣ ብሎ ነው። ትንሽ ማማግ መልካም ነው። አንዳንዴ ሕፅኖቹን ማንበብ ግዴታ ነው። አንዳንዴ ብንዘላቸው የሚጎል ነገር የለም።



@BOOKALEM

በእኔ ሕልዮ ሕይወታችን በአብዛኛው ከመዘንጋት የተዋቀረ ነው። በቸልተኛነትም የተዋቀረ ነው።

ይህ መፅሐፍ ሁለት ክፍሎች አሉት። በዐቢይ ምዕራፎቹ ውስጥ አንባቢ በቀይ የተቀለሙ ቃላትና ሃረጎች ያጋጥሙታል። እናም በእያንዳንዱ የክፍል መጨረሻ ላይ የሕፅኖቹ ማውጫ አለ። እነሱን ለማንበብ የሚወክላቸውን ጠቋሚ ቁጥር መከተል ነው።

መስከረም 1 , 2013 ተለቀቀ
ቡክዓለም በቴሌግራም ያቀረበው መጽሐፍ
@BOOKALEM
መልካም አዲስ ዓመት

*አዳም ረታ*

*ሆላንድ ፡ 1983 ዓም*



@BOOKALEM

# ክፍል አንድ

@BOOKALEM

## 1ቃ

ቤቴ አልጋዬ ላይ እንደተቀመጥኩ የሚናፍቀኝ በመስኮት የማያቸው ከፊት ለፊቴ የተዘረጉት የሸንኩርትና የአበባ መደቦች ሳይሆኑ ዐይነ-ሕሊናዬ ውስጥ እንደ ክር ተተብትበው በጠዋቱ አመዳይ ስር የሚናውዙት የሰፈሬና የከተማዬ መንገዶች(1) ነበሩ::

በተለይ ጠዋት:: ከጠዋቶች በተለይ ደግሞ እሁድ ጠዋት:: እሁድ ጠዋት በተለይ የሠፈር ሰው ከእንቅልፉ ሳይነሳ፣ ግራጫው(2) የመድሐኒዓለም ደወል ሳይመታ፣ ጤዛው ፏ እንዳለ......የሰው ኮቴ ሳያደፈርሰው......ሣር ላይ ያንቀላፋውን የጠል መስታወት ጉሮሮአቸውን በማህሌት የሣሉ ወፎች ሳይቀምሱት::

ያን ጊዜ እወጣለሁ......

:: :: :: ::

ብዙ ሰዎች የፀሐይን መውጣት ቤታቸው ውስጥ ሆነው ይጠብቃሉ: በአልጋዎቻቸው አፎት ውስጥ እንደ ሰይፍ ተወሽቀው ዐይኖቻቸውን የንጋት ውጋጋን ውስጥ በልጥጠው በሙቀት የሚሟሟ ቆዳቸውን እየዳበሱ፣ ወይም የሚስለመለሙ ዐይኖቻቸውን ጨምድደው ገላቸውን በእርካታ እያከኩ፣ በእነሱ እምነት በመኖር ፍትወት ታስረው......የእንቅልፍ ሰንሰለታቸውን ሰብረው ለመነሳት በሰመመን ሲንደፋደፉ::

እኔ እጅግ በጠዋት አንድ ሰድሜ ያነገላት የካኪ ጃኬቴን ደርቤ ከተማዬ መሃል አለች እንዲት ትንሽ ጉብታ ላይ እተተከለች ስልክ እንጨት ስር ሔጄ እቀመጣለሁ:: ግራና ቀኝ ዓይኖቼ ብብት አተር የሚያካክሉ ዐይን አሮች፣ ከአንደኛው የአፌ ጥግ ምናልባት የቀኜ (ፊቴን ወደ መስኮት አዙሬ በቀኝ ጎኔ ስለምተኛ) ወደ ተዘጋው–ብዙ ነገር መስማት ወዳላማረው ጆሮዬ የሚቃጣ የልጋግ ሰንበር:: ሰፍሳፉ የጠዋት እግሮቼ ሁሉን ነገር በቀስታና በፍርሐት ይረግጣሉ:: አልጋዬ ውስጥ በብልኮ የተሚሚቀችውም ቂጤ እዚያ እርጥብና ቀዝቃዛ ሳርና አፈር ላይ ስታርፍ ጮቄው የሚፈጥረው ውጋት በአሰርሳሪዬ አልፎ ማጅራቴን ያለማኛል:: ግን ግድ ሰጥቶኝ አያውቅም:: መጠበቅ እፈልጋለሁ:: ፀሐይ ስትወጣ ፀዳሏን ማየት እፈልጋለሁ::

:: :: :: ::

ዙሪያዬን የአቧራና የድንጋይ ሜዳ ነበር:: የሚዳውን ከፊፍ ከተወለድኩ ጀምሮ ትልቅ እስከሆን ድረስ ምናቸውም ያልተለወጠ የቆሻሻ ጭቃ ቤቶች ሰልፍ ይዞሩታል:: በአራት ግዛን ከትር የተለያዩ ዐይነት ሱቆች፣ መጠጥ ቤቶችና መኖሪያ ቤቶች ተደርድረዋል:: በሮቻቸው ሁሉ ወደ መሃል ያፈጠጡ ናቸው:: በግራ በኩል ያሉት ብዙዎቹ የእህል



@BOOKALEM

መሸጫዎች ናቸው:: ከየመሃሉ መደርደሪያቸው በከፊል የተራቆተ ግን የሚሸጡት የማያጡ ሱቆች አሉ:: በስተላይ ቀጭን ምንገድ ነበረች ወደ ሰሜን ሆቴል የምትወስድ:: መታጠፊያውም ላይ የእንጢቆ ዙፋን መኖርያ ከተማው የሚጥልባትን የተረት አመድ ለብሳ:: ማታ ማታ ቤቴ ለመሄድ ከመነሳቴ በፊት ጊዜውን እንደ ሰዓት የሚነግረኝ የእሱ አሳዛኝ ጥቁር ፉጨት ነበር:: በታች በኩል የሙስጠፋ ሻይ ቤትና በወረቀት የተሞሉ ሁለት የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ጥቂት የእህል መሸጫዎች ነበሩ:: እነዚህ ሁሉ የከበቡት የአቧራና የጠጠር ካሬ በትክክል መሃል ከመሃል በኮረኮንች ጎዳና ይቀደዳል:: ፊቱን ወደ ሙስጠፋ ሻይ ቤት ሳዞረ ከአውራጃው ከተማ ወደዚህች ወረዳ ከተማ ለሚመጣ መግቢያው በስተግራ ይሆናል:: ወደ ጉና ተራራ የሚያወጣው ደሞ በስተቀኝ ተዘርግቷል:: ከቤቶቹ በላይ ወዲያ ወዲህ የሚተሳለፉ ጥቂት የኤሌክትሪክ ገመዶች አሉ:: ከነዚህ በላይ በተለይ በጋ በጋ መፀው መፀው ሳንፔር የሚያስቀና ሰማይ:: ይህን ሰማይ ዘውትር ቀልቃላ ወፎች እንደሚወረወር ፈንጣጣ ይሸፍኑታል:: ከበስተሁዋላዬም ቅርብም ሆነ ሩቅ እንደዚሁ ነው:: የካሬው የላይኛው ክፍል ሁልጊዜ የማልታጣበት ስርፋ ነበር:: እዚያ ስርፋ መሀል ላይ እኔ የምቀመጥባት ጉብታ ናት:: ለምን ይህቺ ቦታ መልፅልት ሆና እንደቀረች ምክንያቱ አይገባኝም:: በሐሜት የማዘጋጃ ቤቱ ሐሳፊ አቶ እንግዳ(3) "ነካ" ያደርጋቸዋል ሲባል እሰማ ነበር::

ለምንድን ነበር የምጠብቀው? መጠበቅን ማን አስተማረኝ? መጠበቅ ምንድን ነው? አንድ ሰው አንድን ነገር መጠበቅ ፈልጎ ሌላውን ነገር መጠበቅ ለምን አይፈልግም? ይሄን እንደኔ ዐይነት የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ሊመልሰው የሚችል ጥያቄ አልነበረም:: የራበው ለመመገብ ይጠብቅ:: የታረዘ ለመልበስ ይጠብቅ......እኔን ግን በዚያ ጠዋት ጉብታ ላይ ጉልቶ ወደ ምሥራቅ እንዳፈጥ ያደረገኝ ምንድን ነበር......?

:: :: :: ::

ጠዋት እስከ አራት ሰዓት ያህል ድረስ እቆይና ከተማው ሞቆ ጩኸት በርትቶ......ሁሉ በየጉዳዩ ሲሔድ ወይም ጉዳይ ሳይኖረው......በየበረንዳው ቆሞ ጉያውን እያከከ፣ ትንባሆውን እያንፎለፎለ፣ ወሬውን እየቀደደ ወደ ከተማዋ መሐል ሲያፈጥ ቁርሴን ለመብላት ወደ ቤቴ እመለሳለሁ::

አንዳንድ ጊዜ ፀሐይዋ ባትመጣስ ኖሮ? እላለሁ:: ምን ይውጠኛል? እንዲያ ተቀምጬ የጠዋቱን ብርድ ጠጥቼ ቂጤን አደንዝዤ፣ ከፀሐይዋ ጋር መቼም በግል አልተነጋገርንምና፣ ቀጠሮ የለንምና፣ ወደ ጎን ሸርተት ብላ ዐይኖቼ ወደማይደርሱበት ዓለም ብትሔድስ?

ማን እጠብቃት ነበር::

:: :: :: ::



@BOOKALEM

ግን ስፋ አድርጌ ካየሁት የምጠብቀው የፀሐይን መውጣት ብቻ አልነበረም:: የመጣን እንግዳ ካልሸኙት ምን ይሠራል? እንደገና ከአሥራ አንድ ሰዓት በሁዋላ ቀስ ብዬ ከቤቴ እወጣና......እዚያችው ጉብታዬ ላይ እቀመጣለሁ:: አንዳንዴ ይህቺ ጉብታዬ እላይዋ ላይ ሰው ፊሶ ያጋጥመኛል:: ብዙ ጊዜ በተለይ እነኚህ የከተማ ዱርዬዎች ሌላ ቦታ ማድረግ የሚችሉትን ነገር እዚያች 'እኔ' ቦታ ላይ በመስራት የስሜቴን ካብ ከላዬ ላይ ሊያወርዱ ይተናነቁኛል:: ሌላ ቦታ ማድረግ የሚችሉት ነገር እንደሆነ ቢያውቁም እዚያች ቦታ ካልፈጠሙት የልባቸው አይደርስም ነበር:: ቁም ነገር ሳይሆን ቁማር ጨዋታ:: ጉብታ ነው ቦታው እንግዲህ:: እዚያች ጉብታ ደረት ላይ ትናንሽ ጉድጓዶች ይሰሩና ሁለት ሜትር ከማይደርስ ርቀት እነዚያ ጉድጓዶች ሆድቃ ውስጥ ሳንቲም ማስገባት ይጫወታሉ:: የትም ቦታ ሄደው ሊጫወቱት ይችላሉ:: በመብሸቅ የማደርገው ሌላ ነገር ስለሌለኝ አጠገባቸው መጥቼ እቀመጥና ቂልነታቸውን አጠናለሁ:: ወይም ሌላ ሌላ እያየሁ እቆማለሁ::

"አትጫወቺም!" ይሉኛል::

"በምኔ" እላለሁ::

"ከአባትህ አትዘርፍም.......አባትህ ዱባለ ጨው አለው......" ይሉኛል::

አልሰማም::

ግን ደስ የሚለኝ ነገር ደ'ሞ እዚያ ዳገት ላይ ማንም እኔ ምን እንደምሰራ አለማወቁ ነበር:: የፀሐይን መጥለቅ ሌላ ጉዳይ ሌላ ጨዋታ የማይ መስዬ ነበር የምመለከተው:: በትንሹ ግን እፈራለሁ:: ለሰዎች እዚያ ምን እንደምሰራ ብነግራቸው በተለይ ለእነዚህ ዱርዬዎች ፀሐይዋን በማይበት አቅጣጫ ሕዋው ላይ፣ አየሩ ላይ ጉድጓድ ሰርተው ቁማር መጫወት ይጀምሩ ይሆናል ብዬ::

:: :: :: ::

......ከ11 ሰዓት ቀደም እልና ፀሐይዋን ስታቆለቁል ጀምራ አያታለሁ:: ቢጫ ሆና ከዛ ደብዛዛ ቀይ ስትሆን......ጠርዟ እንደተሰመረ ነገር......እንደተቀፈፈ ሆኖ......ስለራሷ......ታሳዝነኛለች:: አንዳንዴ ተመልሳ የምትመጣ ይመስለኛል...... እፈራለሁ......:: ታዲያ መመለሷን ለማረጋገጥ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት መምጣት አለብኝ:: በፊት በፊት......የበለጠ ልጅ እያለሁ... ያቺ ትንሽ ደረቴ ስር የምትፈራገጠው ልቤ ፍርሃት እድትሞሟት እዚያው እተቀመጥኩባት ነው'ዝ ይጥለኝ ነበር::

ከዚያ ምሽቱ ይመጣል:: የዚያ ከተማ ምሽት ደ'ሞ እንደ ናና ከረሜላ ጣዕም ነበር:: ትልቅ ሐብት የተደበቀበት ዋሻ ውስጥ እንደመግባትም ነበር:: የተሽሞነሞነ ሚስጢርነቱ



@BOOKALEM

እያታለለ ይጋፋል፣ እየተጋፋ ያታልላል። ያ ሐብት ግን የትኛው የቆሻ ክፍል ውስጥ እንዳለ የሚያውቅ አልነበረም። ሁሉ ሕዝብ በዚያ ቆሻ ውስጥ ይኖራል። እኔም አንዱ ነበርኩ። የምሽቱ ፀጥታም ይገርመኛል። ይሄ ሁሉ ሕዝብ የዚቺን ፀሐይ አወራረድ ሳያይ በየቤቱ ሲገባ ቅር አይለውምን? እላለሁ። በየቤታቸውስ ምን ይሰራሉ? እላለሁ። የሚሰሩትን አስቤ አስቤ ከጥቂት ነገሮች የበለጠ መዘርዘር አልቻልኩም። ይሔ ሁሉ ሕዝብ እነዚህን ትንሽ ትንሽ የመሰሉ ነገሮች ይሠራል......

ራት ይበላሉ (ካልበሉ ስለሚራቡ)

ይጠጣሉ (ካልጠጡ ስለሚደርቁ)

ይጫወታሉ (ካልተጫወቱ ስለሚያብዱ)

ይተኛሉ (ካልተኙ ስለሚደክማቸው)

ያወራሉ (?)

እኔ በማትደክም ቂጤ ተቀምጬአለሁ፣ በማይደክሙ ዐይኖቼ ዙሪያ ገባዬን እያለሁ፣ እዚያው እንደተቀመጥኩ ይመሻል። ጥቁሩን ሰማይ ማጥናቴን እቀጥላለሁ። ከዋክብት እቆጥራለሁ። ሁልጊዜ ከዋክብት ለመቁጠር እሞክራለሁ። መጀመሪያ ጎልተው የሚያበሩትን ከዋክብት እቆጥራለሁ። በፀሀይ መውጫ ያሉትን። ብዙ ጊዜ አንዲት ብሩህ ኮከብ አያለሁ......የበሰለ ኮሽም የመሰለች። አንዳንዴ ሰማይ ውስጥ ጨረቃ ትገባባታለች......ጨረቃ ትመጣና ለጋ ደመና ሁሉ ይመጣል......ከዚያ......ሲያልፍ ሲያገድም ሲተላለፍ ጨረቃን የጋረደበትን ጊዜ እቆጥራለሁ፡ '......1 2 3 4 5 6 7......አ! ሊሸፍናት ነው ሊሸፍናት ነው......ሸፈናት......' አንዳንዴ አውራጃ የሚያክል ጥቁር ደመና እነዚያን የብር ቀዳዳዎች የመሰሉ ከዋክብት ለረጅም ጊዜ ይደፍናቸውና የመቁጠር ተስፋዬን ቆርጬ እቀመጣለሁ።

:: :: :: ::

በየቤታቸው ያሉትን ሰዎች ከኔ የሚለያቸው አንድ ትልቅ ጉዳይ ከሌሎች ሰዎች ጋር መሆናቸው ነበር። እኔ እዚያች መልዕልት ላይ ብቻዬን ነበርኩ። ከቤቴ ደግሞ ተጨንቆ ራት እንድበላ የሚጠራኝ ማንም የለም። ሁለመናዬ እንደሌሎች ቢሆንም። የምቀርበው የማፈቅረው የማምነው ሕፃን ጓደኛ አልነበረኝም። ለምን እንደሆነ አላውቅም። ከመጫወት፣ እየተንጫጫሁ ከመዝለል ወይም እየዘለልኩ ከመንጫጫት ቁጭ ብሎ መታዘብ ነበር የምወደው። በዚህ ከፀሐይ ጋር እንቀራረብም። ከጨረቃ ጋር እንቀራረብም። ከደመናዎች ጋር እንቀራረብም። ከአንድ ቀን ሌላ ቀን የምሰራው ነገር ቢኖር መቀመጥ ከሆነ የምመስለው ዛፍ ነው።

እግዜር ፍጡርን እዚህ ምድር ሲያመጣ ጀምሮ......ትልቁ ያስቸገረው ነገር ለፍጡራን እጋር የመስራት ነበር (ሄዋንን ለመፍጠር ታዲያ ለምን ዘገየ? እጋር መቀመሩ ከብዶት



@BOOKALEM

ይሆን?)። ለወንድ ሴት፣ ለሴት ወንድ አለው። ለልጅ አባት አለው......ያለ አጋር እግዚአብሄር ምንም ነገር አልሰራም......እሱም ነገሩ ገብቶት ነው መሰለኝ (ቢከብደውም)—ለእኔም አጋር ሰጥቶኛል......

አንድ ብቻ ሳይሆን.......

አባቴ ለእኔ አባት መሆን አልቻለም። እናቴ ዕድሜዬ ሦስት እያለ ነበር የሞተችብኝ። ከእንጀራ እናቴ(እእ) ጋር ቅቤና የውሻ ሆድ ነበርን። እኔ "ቅቤ ነኝ" እላለሁ። እሷ ደግሞ እኔን "እሱ ውሻ ነው" ትላለች። እኔ ጮክ ብዬ ባልናገረውም ከእሷ በመሸሼ......እንዳልዋጥ የፈራሁ ዐይነት ይሰራኛል። እግዜር ግን የሰው ፍጡር ባይሆንም እንኳን አጋር ሰጥቶኛል። ያቺ ሚና በሁለመናዋ አጋሬ ነበረች። ልቁጠራቸው: እዚያች ጉብታ መሐል ላይ ከተማችን የምትኩራባት የኤሌክትሪክ ምሰሶ አለች—አንድ። ከቁንጮዋ ከብ ጠፍጣፋ የቆርቆሮ ባርኔጣ ከዶፍና ከፀሐይ ሞገድ የጋረዳት። ከኤሌክትሪክ ምሰሶዋ አናት ትንሽ ዝቅ ብሎ ደሞ ሻማዋ ከባድ ያልሆነ አምፖል አለች—ሁለት። ያቺ አምፖል ሁልጊዜ ማታ ማታ እንደበራች ነበር። ከተማው ውስጥ ያለችው የምንገድ መብራት እሷ ብቻ ናት። በየሱቁ በረንዳ፣ በየመጋዘኑ በረንዳ፣ በየቡና፣ ጠላ ቤቱ በረንዳ አምፖል አለ......ከተከፈቱ ቤቶች የሚወጣ ብርሐን አለ......ይህች መብራት ግን ልዩ የሚያደርጋት ሁል ጊዜ የምትበራው ከእኔ ጭንቅላት በላይ መሆኑ ነበር። በድፍን የጨለማ ድድ ላይ የተንጠለጠለች አንዲት የፊት ጥርስ ናት። አትሞቅም። ግን ለእኔ የምትሞቅ ይመስለኛል። ብዙ አታሳይም ግን መብራት ከጀመረች ጀምሮ (ከምሽቱ 12 ሰዓት) አብሬአት ስለምሆን ለእኔ ወጋገን ነበረች።

ለመሆኑ ቤተሰብ አለኝ?

አዎ ቤተሰቤ ከሦስት ሰዎች የተገነባ ነበር። አባቴ፣ ሚስቱ እና የሚስቱ ልጅ። አባቴና ሚስቱን አላከብራቸውም፣ ስለማላከብራቸው አልፈራቸውም። የእንጀራ እናቴን ልጅ ግን ደግ ትመስለኝ ስለነበር በመጠኑ እቀርባታለሁ። ብዙ ጊዜ ስለማመሽና አምሽቼ ስለምመጣ ቤቱን ይዘጉትና የክፍሌን መስኮት ብቻ ክፍት አድርገውት ይተኛሉ። የተራረፈ እራት ካለ (እህቴ ናት ብዙ ጊዜ የምታስቀምጥልኝ) በትንሽ ሳህን መኝታ ቤቴ ውስጥ አገኝና በልቼ እተኛለሁ። ብዙ ጊዜ ግን አያስገኝም። ጠዋት፣ ከሰዓት፣ ማታ......ከሰኞ እስከ እሁድ......ሽሮ መብላት የሚወድ አለ? ይሰለቸኛል። አንዳንድ ጊዜ አባቴና እንጀራ እናቴ መኝታ ቤት ውስጥ ትልቅ የሽሮ እርሻ ያለ ይመስለኛል። የሆነ የሽሮ ሰቲት ሁመራ።

የእኔ አጋሮች እንግዲህ ጉብታዋ፣ አምፖሉና የአምፖሉ የቅርብ አካባቢ ብቻ አልነበሩም። ሲመሽና አምፖሏ ስትበራ ብርሀን እየሳባቸው ወደዚህች መብራት የማይመጡ የፍሳት ዐይነቶች አልነበሩም። ከነዚህ ነፍሳቶች አንዳንዶቹ ታዲያ አምፖሏ ዙሪያ መብረር



@BOOKALEM

ከብደቻቸው ይሁን......ትናንሽ ክንፎቻቸው በኤሌክትሪክ ግለት ተቃጥለውባቸው......አንዳንድ ጊዜ እላዬ ላይ ይወድቃሉ......እግሮቼ ስር ይወድቃሉ።

ምን አደርጋቸው ነበር?

እነሱ ክንፍ ስላላቸው አየር ላይ መቆየት ቻሉ እንጂ እንደ እኔ ስዱድ ናቸው። ታዲያ ሲወድቁ አነሳቸውና ወደ ሰማይ እወረውራቸዋለሁ። አንዳንድ አሪፎች ይበራሉ። አንዳንዶቹ ተመልሰው......ሳር መሃል፣ አፈር መሀል ይጠፋሉ። መልሼ አግኝቼ ብወረውራቸውም መብረር አይችሉብትም። እዚያች አምፖል ስር ከተለማመድኳቸው ችሎታዎቼ አንዱ የወደቀ በራሪ ነገር ከመሬት አንስቶ እንዲበር የመገፋፋት ነበር። ብዙ ሰው የሚሆንለት አይመስለኝም። ብዙ ሰው 'ሞተዋል' ብሎ የማያልፋቸውን የእሳት እራቶች ተንከባክቤ ወደሚመኙት አየር ውስጥ አስገባቸዋለሁ። ተስፋ የሚቆርጡ ያጋጥሙኛል......እጄ መሐል አስቀምጬ ስነካካቸው ዝም ብለው ይተኛሉ......ወይም......በእጄ ላይ በቀስታ እየሮጡ ሔደው......ወደ መሬት ይወድቁና ሰፋፊ ዐይኖቻቸውን በሳርና በአፈር ኩረት ጠልለው ያናውዛሉ......እነዚህን ብዙ ጊዜ ጠዋት ላይ ስመለስ አላገኛቸውም። በሕሊናዬ......ትላንት ማታ ከእጆቼ ላይ ወድቀው ወይ አምልጠውኝ የጠፉት በራሪዎች በዚያ የከተማዋ አደባባይ ላይ የሚገዛው እንደጠፋው ወይ ዋጋ እንደተወደደበት ገበያተኛ ሲንከራተቱ የሚውሉ እየመሰለኝ አዝናለሁ።

......ቤቴ በመስኮት ዘልዬ እገባና......ልብሴንም ሳላወልቅ እተኛለሁ። አልጋዬ ያረጀች ሽቦ ነበረች። መሐሏ ዘቅጦ አንዳንዴ የቅብጠት ስዘልባት መሬት ትነካለች......ሽቦውን ሞጭሮጮ የያዘውም ብረት በቁንጫ ዐይነ-ምድር ቡናማ ቀለም የተነሰነሰበት የመሰለ ነበር። የገዛችው እንጀራ እናቴ (እእ) ናት። ከዚህ በፊት የምተኛው መሬት ነበር። አባቴ አዲስ ምቹ የሆነ አልጋ ሊገዛልኝ ሲል (የቦንዳ) "ምን የመሰለ ሽቦ አልጋ አግኝቼሊታለሁ" ብላ አስር ሳንቲም በተከፈለው ኩሊ (ያኔ ኩሊ ነበር የሚባለው) ያን የዛገ ነገር አሸክማ አመጣች። እኔ ደሞ አልተነጫነጭኩም (ማን ሊሰማ)። አልጋውን ሣሎን ዘርግታ አፏን እየዳበሰች ከንፈሮቿን እየነከሰች በአድናቆት ስታወራ ዝም ብዬ አይ ነበር—አፏን፣ ፊቷን፣ አልጋውን። አባቴ ሴትዮዋን ለምን እንደሚያምናት አይገባኝም።

እንጀራ እህቴ ግን የምትተኛው በጣም በሚመች አልጋ ላይ ነበር። አልቀናሁባትም።



@BOOKALEM

# ስምፖኋን የመመልከት ዘዴዎች

አንድ ሰው ስለአንድ ነገር ብዙ ካወቀ ብዙ ከተረዳ ባለሙያ ይባላል። እኔም ሙያ አለኝ። ይሄ ሙያዬ ግን ተቀምጦ የማየት ነበር። ተቀምጬ ከማያቸው ነገሮች አንደኛው የሚበራ አምፖል ነው። አምፖል ከመስታወት የተሠራ እንደሻማ፣ ፋኖስ፣ ማሾ የሚያበራ ነገር ነው። ግን እንደሻማ ንፋስ አያጠፋውም፣ እንደፋኖስ በገመድ፣ እንደማሾ በአየር አይሰራም። ነገርየው ትንሽ ረቀቅ የሚል መሰለኝ። የማወራው ትክክለኛ ሙያዬ ስለሆነው መቶ ሻማ አምፖል ስለመመልከት ጉዳይ እንጂ ስለ አምፖሎች አሠራር አይደለም።

አምፖልን ስትበራ እያዩ ለመደሰት በቀጥታ ማየት አያስፈልግም......የሆነ መጠነኛ የዐይን ቅኔ ያስፈልጋል። በቀጥታ ካዩ የብርሐን ጨረር በብሌን ሰተት ብሎ ስለሚገባ ያጥበረብራል......ዐይንንም ሊጎዳ ይችላል። ከአምፖሉ አቅጣጫ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ወደ ላይ ወይም ወደታች ቢበዛ ሁለት ሳንቲ ሜትር ራቅ ማድረግ ነው......የዐይንን የትኩረት አቅጣጫ......ብቻ እንደ የሰው ፀባይ ሊለያይ ይችላል። ብርሐኑን አይተው ለመደሰት የሚመጡ ትንኞችና በራሪዎች ዝብርቅ አድርገው ውጋጋን ውስጥ እየዋኙ......ከአምፖሉ ጋር ሲጋጬ የሚያይ ሰው መሳቅ የለበትም። እኛም ከንፍ ኖሮን ከመሬት ብንነሳና ኑሯችን እንደ እሳት እራት ቢሆን ሊደርስብን የሚችል አደጋ ይመስለኛል።

አምፖሉን በማየት የተሰላቸ ወይም የተዳከመ ዐይኖቹን ማሳረፍ ወይም ማዝናናት ቢፈልግ ዐይኖቹን በፍጥነት ወደ ጨለማው ማዞር የለበትም። አምፖሏ በጨረሯ የራሷን ደሴት ፈጥራለች......ይሄ ፍጥረቷ ግን ቅልብጭ ያለ አወራረድ የለውም። ፍፁም ብርሃን ሆኖ ፍፁም ጨለማ የለም። እስከ አምፖሏ ዕምብርት ድረስ በብሌኖቻችን ለቅመን ማውጣት የማክብድ ደካማ ግራጫ ከወዲያ እስተዚህ ተወስውሶአል። ደረጃ ነው ያለው። ከስልክ እንጨቷ በራቅን ቁጥር የብርሐኑ ሐይል እየቀነሰ፣ እየቀነሰ ይሔድና ጨለማ ይሆናል። ከአምፖሉ የብርሃን ቀጠና ውጭ ወደ አምፖሉ ለሚመጣ ሰው የብርሃኑ መጠን እንዲሁ በየደረጃ እያደገ እያደገ ይሔዳል። ስለዚህ ዐይኖቻችንም በዚህ አሰራር እንዲሳተፉ ማድረግ ነው......ማላመድ.......። ማንኛውም አምፖል የሚሰራው በዚህ መርሆ ነው።

ይሔ ጉዳይ ከሕይወቴ ጋር ምን ያገናኘዋል.......?

ስለማየት።

እኔ የማወራው ስለማየት ነው። አንድ ነገር ወይም ብዙ ነገሮችን ስለማየት። መሆን የምመኛቸው ግን መሆን የማልችላቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ። ዕድሜዬ ልጅ ነው ታዲያ ሚስት



@BOOKALEM

ማግባት እችላለሁ? አልችልም:: ስለዚህ ሚስቶችን አያለሁ:: ፀሐይን መሆን እችላለሁ? አልችልም:: ስለዚህ ፀሐይን አያለሁ:: የእንጀራ እናቴን መሆን አልችልም? አልችልም:: ስለዚህ አያታለሁ::

ግን ማየት ብልሐት አለው:: የማወራው ስለብልሃቱ ነው::



@BOOKALEM

# መዝገቡ

"ሲወለድ የተረገመ ነው" ሲሉኝ እሰማ ነበር:: ታዲያ አንድ ጊዜ ጭል ያለ ሜዳ ላይ የራሴን ስም ከፍ አድርጌ ጠራሁ:: "መዝገቡ!! መዝገቡ!"

"መ! ዝ! ገ! ቡ!" የሚገርም ስም ነው:: *መዝ*......መዘዝ ሊሆን ይችላል:: መዘዘኛ ለማለት:: *ገ*......ገማባ:: *ቡ*......ቡቃያ:: ሲጠቃለል: *መዘዘኛ የሆነ ገና ከአሁኑ የተገመበ ቡቃያ::* ካልጠፋ *ሥም* ይሔን ይሰጡኛል? ሌላ ሌላ ጠፋ እንዴ!? ለምን "እግዚሀር" ብለው አይጠሩኝም ነበር? እሱ እንደ እኔ ተቀምጦ ከማየት ሌላ ምን ሠራ? ወይ ካደግሁ በሁዋላ ለምን የራስህን *ሥም* አውጣ አይሉኝም ነበር? ስሜ የሚያስታውሰኝ አተር እርሻ ውስጥ የሚያጋጥሙኝና የማያቸውን አንዳንድ ጮርቃ የአተር ተክሎችን ነበር:: እነዚህ ጮርቃ ተክሎች ቅጠሎቻቸው በተባይ ይጠቁና የተለያየ ደብዛዛ የድምቀት ደረጃ ያላቸው ሐመልማል ይሆናሉ:: እጄ መሐል አድርጌ ሳጤናቸው በዐይን ለማየት በሚከብዱ ዕንቁላል መሰል ፍጡራን ተበልተው ወይም ተልሰው የተቀደዱ ወይም የለሰለሱ ነበሩ:: ካልተቀደዱ ደግሞ ቢያንስ በውስጣቸው አሳልፎ ማየት የሚያስችሉ መስታወት የመሰሉ ጠባሳዎች ይሆናሉ:: እነዚህ ቅጠሎች የተገጠቡ ናቸው:: እነዚህ ጮርቃ ቅጠሎች የተገጠቡ ናቸው:: እነዚህን ጮርቃ ቅጠሎች ከእኔ የሚለያቸው ነገር ቢኖር የሚገጠቡት በተባዮች እንጂ በሌሎች እነሱን በሚመስሉ የአተር ችግኞች አለመሆኑ ነበር::

ሳስበው ታዲያ ስሜ ትክክል መሰለኝ::

ትንሽ ያልገባኝ መዘዘኛነቴ ነበር::

ቆይቶ ሳስበው ግን ልክ ነው:: መዘዘኛነቴን ልክ ሆኖ አገኘሁት::

እንጀራ እናቴ(እእ) ሲያል ስትወርድ......እግዜር በእኔ ነገር ክስ ያቀርብባታል......ታዲያ እሳት ውስጥ ቆማ......"ያ መዘዘኛ ልጅ ነው......እዚህ የነዳኝ" ማለቷ አይቀርም (ማላከክ ትወዳለች):: "መዘዘኛው መዝገቡ ነው" ማለቷ አይቀርም:: ስሜን ሁልጊዜ ስትጠራው ተነጫንጫ ነበር:: እግዜር ግን ስሜን ሲጠራው ቀስ ብሎ ነው: "መ ::: ዝ ::: ገ ::: ቡ:::" ብሎ ነው:: *መ*–መይሳው ማለት ይሆናል:: *መ*–መከረኛው ሊሆንም ይችላል:: *ዝ*–ዝምተኛው:: *ገ*–ገሳፊዬ:: *ቡ*–ቡቃያው:: ታዲያ እግዜር በሚያበሩ እጆቹ ይነካካኝና የጣቶቼን ጥፍሮች መላእክት እንዲቆርጡልኝ ያዛል:: እንክብካቤ ቢጤ::

የአባቴ *ሥም* ግን እራሴኑ ያስቀኝ ነበር:: ስለሚያስቀኝ ልጠራው አልፈልግም:: የዚያን ዐይነት *ሥም* ቢኖረኝ በእግሬ ካርቱም ወይም ወደ ሌላ የሚቀርበኝ ቦታ እሰደድ ነበር::



@BOOKALEM

በየቀኑ ለሥራ እየወጣ ሲገባ፣ ሳያንገራግር (ወይስ በሆዱ ይብሳጫል?) በዝምታ ሲበላ ሳየው ስሙ እንዴት እንዳላማረረው እየገረመኝ በእሱ ምትክ እኔ እተክዛለሁ። በተለይ አንዳንድ ቀን ለብቻዬ ሆኜ ድምፄን ዝቅ አድርጌ ስሙን እየደጋገምኩ ስጠራው መጀመሪያ እንደቀልድ ያስቀኝና እየቆየ ደሞ ጣዕም የሌለው የሲጋቱራ ዶፍ ይሆንብኛል። በስተመጨረሻ ላይ ባዶ ነገር—ልክ አንብቤ የጨረስኩት የጋዜጣ ቅዳጅ በድንገት ከእጄ አምልጦ መሬት ሲወድቅ የሚሰጠው ዐይነት ስሜት.......

ዱባለ። ዱ.......ባ.......ለ።

ለምሳሌ ደሞ ያቺ ቆንጆ ልጅ 'ወሰን' የሚሏት ሙሉ ሥሟ 'ወሰን የለሽ' ነበር። 'የለሽ'ን ለምን አጥፍተው እንደሚጠሯት አላውቅም። ቀንተው ይሆናል። ወሰን ከማይኖራት ወሰን ይኑራት ብለው። ሙሉ ስሟ ደስ ይል የለ? ባሌ ትሆናለህ ባትለኝ እንኳን ከእህቴ ጋር የምታወራውን ያህል ብታዋራኝ፣ ብትሳፋኝ፣ ብትስቅልኝ ደስ ይለኝ ነበር። ወሰን ስሟ ቢያምረኝም ንፍገት ይመስለኛል። ወርደ—ሰፊ ውብት አላት ቀላዋጭ የሚጠራ፣ ግን ኑፉገ ናት። ንፉግ ነበረች። ሳቅ እንኳን አትስቅልኝም። ብዙ ጊዜ ንፍገቷን በግድ ለመስበር ሞክሬአለሁ። 'ብልጥ' የሚሏት ነበረች። ገና ከሩቅ ስታየኝ ከምንገድ ጥምዝዝ ብላ ትሸሸኛለች።

የእኔ ስም ግን ከባድ ይመስለኝ ነበር.......ከባድነቱን እየዞርኩ ባላወራውም። ምንም ብንገላታ። ብንገላታ እንኳን። ምክንያቱም መዝጋቢ ነኝ ማለት ነው። መዝጋቢ—ፀሐፊ ትዕዛዝ ማለት ነው። ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ማለት ነው። የአማርኛ አስተማሪያችንን አንድ ጊዜ ጠይቄአቸው "ፀሐፊ ትዕዛዝ ማለት በንጉሡ ታዞ የሚፅፍ ማለት ነው" አሉኝ። ግን በንጉሥ ታዞ የሚፅፍ አደገኛ አይደለም። እኔ ታዝዤ አልፅፍም። መመዝገብ ትርጉሙ ማየት፣ መስማት፣ ማሽተት ማለት ነው። ለምሳሌ የከተማችንን የንፋስ መውጫን ጠረን በትንሽ ብልቃጥ ማስቀመጥ ይቻላል ቢባል እኔ ነበርኩ አቀናባሪ የማደርገው። የኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ ጠረን በብልቃጥ ተደርጎ ቢመጣልኝ የንፋስ መውጫን ሽታ በቀላሉ መርጬ ማውጣት እችላለሁ። የንፋስ መውጫ ጠረን የንፋስ፣ የሰንሰል፣ የዕድ፣ የአፈር፣ የጠላ፣ የፋንድያ፣ የአሰታ፣ የሰንዴ ቆሎ፣ የግብጦ የፈረጠ ዕንቡዋይ የተቀላቀለበት፣ እነዚህ ሁሉ የተመሳጠሩበት ነበር። የልደታ የልደታ ዕለት ግን በየቤቱ ብዙ ቡና ስለሚፈላ ከጅማ ከተማ ጠረን ያምታታ ይሆናል።

ታዲያ መመዝገብ፣ መመዝገብ፣ መመዝገብ።

ለምሳሌ የሐይለኛውንና የርብቃን ግንኙነት የማውቀው እኔ ብቻ ነበርኩ። ብልጥ የተባሉት እንኳን አያውቁም። ሥራዬ ስሜ ውስጥ ነበር። የምንጩን ሽጥ ተሻግሮ ዘማሪ



@BOOKALEM

ርብቃና ቲቸር ሐይለኛው ያደረጉትን ነገር ያየሁ እኔ ብቻ ነበርኩ። እንዳየሁዋቸውም የሚያውቁት እነሱ ብቻ ናቸው። የትልቅ ሴት ጭን እንደዚያ የሚያምር አይመስለኝም ነበር። ያስፈራል ግን። ጭን እንደዚያ በጣም ትልቅ ሲሆን ያስፈራኝ ነበር ግን። ይሄን ሁሉ መዝግቤአለሁ።

ታዲያ እግዚያብሔር ወደዚህ ምድር ሲመጣ የንፋስ መውጫያ ሕዝብ ለፍርድ ሲቀርብ ለምስክርነት የምጠራው እኔ ነኝ። የእግዜር መዝገቡ እኔ ነኝ። የተጎዳሁትም የመዘገብኩትም እኔ ነኝ። ለምሳሌ ርብቃ "ቤትህ እመጣለሁ" ብላ እንደፎከረችው አልመጣችም። ያደረገችውን ስላየሁ አፍራኛለች። ሐይለኛው ሲጃራ እንድገዛለት ልኮኝ (ሲልኩኝ ባልወድም) የሣንቲም መልሱን ስሰጠው እንድወስደው ነገረኝ። እንዲህ ባያደ ግልኝም አላወራብትም። በሚስጥር ግን የሚፈሩኝ ሰዎች እንዳሉ ሳውቅ ገረመኝ። ይገርማል። ይሔ መዝጋቢ ሰው ይገርማል። ተማሪዎች ሲያወሩ ድሮ ርብቃና ሐይለኛው ወዳጆች እንደነበሩ ሰማሁ። የከንፈር ወዳጆች። ሐይለኛው ከሌላ ሴት ጋር ይሔድና ተጣሉ አሉ። ከተጣሉ በሁዋላ ርብቃ ሸዋ ወርዳ ዘመዷ ዘንድ ሚሽን ሆና መጣች። "አሁን ጨዋ ሆናለች" ይባላል። እኔ ሳላወራ ሳልቀባጥር ጨዋ አለመሆኗን መዝግቤ ቁጭ ብያለሁ። እንደ በሰለ ሾላ የቀላ ጭን ነበራት። (ንፋስ መውጫ መስከረም ላይ የሾላ ጠረን ታወጣለች። የሾላው ዛፎች የበቀሉት ግን ጉና ላይ ነበር። ከዚያ ዘንድ ጠረኑን የሚያመጣው ንፋስ ይሁን ወይ በየገበያው ቀን ወደ ከተማዋ እየተግተለተለ የሚመጣው የገበሬ ጋቢ እርግጠኛ አይደለሁም) የወሰን አባት ልጃቸውን ሚሽኖች ቤተክርስቲያን ድረስ ሔደው ፀጉሯን እየጎተቱ ሲመልሷት ሳይ እንዳትባልግ አስበው መስሎኝ ነበር። በሁዋላ እህቴ ስትነግረኝ እንዳትከተልክ ብለው ነው አሉ።

ርብቃና ሐይለኛው ያደረጉትን ባለጌ ጉዳይ የሚያውቅ ሰው አልነበረም። እኔ ግን ወሰንን አንድ ቀን "ሚስቴ ነሽ" ብዬ በተናገርኩ ቀንና ማታ ይተረትብኝ ነበር። የከተማዬ መዝጋቢዎች ቀሽሞች ነበሩ። መጀመሪያ ብሌናቸው የተደፈነ፣ ሁለተኛ አንድ ቀን ያዩትን መቶ ቀን የሚያወሩ ዓይነቶች ነበሩ። ርብቃና ሐይለኛው ተጣልተው ቢሆንስ ኖሮ?......የእኔ ምዝገባ በየቀኑ ነበር። አዲስ ነው። "መዝገቡ" ሲባል እንኳን የንፋስ መውጫ የአገሪቷ ፀሐፊ ትዕዛዛት ሁሉ መድረሻ ይጠፉቸዋል......

......ክርስቶስ ጥፍሮቼን ያስቆርጥልኝና ትልቅ ሰገነት ላይ አስተኝቶ ወይን እየጠጣሁ እና ሥጋ እየበላሁ ሲወብቀኝም መላእክት ከበው በክንፋቸው እያራገቡልኝ ይጠይቀኛል:

"ድንቅ ነው። መዝገቡ ድንቅ ነው። ርብቃን ከምንጩ ሌላ ቦታ አይተሃታል?"



@BOOKALEM

"እዎ...... አንድ ቀን ማታ ወደ እሱ ቤት ማለቴ ወደ ሐይለኛው ቤት በጧሮ ሹክክ ብላ ስትገባ"

"ሹክክ አልክ? አትርሳ.......ከወይኑ እየጠጣህ"

"እዎ.......ቀስ ብላ፣ ኀብጥ ብላ፣ ግራና ቀኝ እያየች በወላለቀ አጥርና አሜሜር የዳማ ከሴ ተክሎች መሐል......."

"በቃ.......?"

"እንዴ! እሱ ብቻውን ነበር የሚኖረው......አንድ ሰዓት ላይ ገብታ እኩለ ሌሊት አካባቢ ወጣች"

"አይ የእኔ መዝገቡ......እንኳን እናትህን ገደልኩብህ" ይለኛል።



@BOOKALEM

# ተጓዥ ዝንቦች

ተቀምጬ ስመለከትና ስገነዘብ ሌላ ምን ምን ነገሮች አይ ነበር? ብዙ:: ብዙ:: ለምሳሌ ዝንቦች::

እዚያ ንፋስ መውጫ ብዛት ካላቸው እንስሳት (ንፍሳት) የመጀመሪያዎቹ ዝንቦች ናቸው:: እኔ ምንገድ ዳር አደባባይ መሐል ተቀምጬ በመዋሌ የማያማኝ ግን አልነበረም:: ማንንም ሰው ግን አልጉዳሁም:: ትንሽ ቁራጭ መሬት ላይ......ትንሽ የከሳች፣ የተበደለች ቂጤን አስቀምጬ......የልጅነት ዐይኖቼን ባንከባለልኩ:: እኒህ ዐይኖቼ ግን ብዙ ነገር ይለቅማሉ:: እንደካሜራ ናቸው:: የእኔ ዐይኖች ያዩትን ነገር በደንብ ይከታተሉታል፣ የአቅማቸውን ያህልም ያጤኑታል::

በጋ በጋ ከተማችን እሳት መሀል እንደተጣለች ሁሉ ትግላለች:: አየሩ ይርገበገባል:: ጠራራም ቢሆን ኮቴን አውልቄ ራሴ ላይ አድርጌ ከጉብታዋ አልሔድም:: ያን ጊዜ ከተማዋ ውስጥ ከሰው ይልቅ በዝቶ የማየው ዝንብ ነበር:: ለጫወታ ፍጡር የለበትም ብዬ በጠረጠርኩበት አቅጣጫ ድንጋይ አንስቼ ስወረውር ድንጋዩ ከወደቀበት ቦታ ዝንብ ኸው ብሎ ይነሳል:: በተለይ የሳምንት ገበያ ቅዳሜ ሆኖ......እሁድ ዕለት ቀትር ላይ ከተማው ዝንብ ብቻ ነው:: በዚያ በምታነድ ፀሐይ ጋቢውን የተከናነበ ሰው......ሳያቋርጥ ባሕር ውስጥ እንደተጣለ ግን ዋና እንደማያውቅ እጆቹን እያወናጨፈ ይሄዳል (ስለምንስ በዚያ የሚያስጮህ ግለት ቦርጫም ጋቢ ለብሶ ወዲያ ወዲህ ይላል?):: ቃሪያ እንደቆረጠሙ ሁሉ ሳያቋርጡ ፊታቸውን በእጆቻቸው የሚያራግቡ አሉ:: ጉልበቶቹ የቆሰሉ ልጅ ጥቋቁር የዝንብ ኩኩቦች እንደ ጌጥ ተሸክሞ በቀስታ ይቀዝፋል (ምን አንቀራፈፈው? የተሸከማቸው ዝንቦች ከበዱትን?):: ሌላ ንፍጡን ያልሰበሰበ ብላቴና ገፁ ላይ የዝንብ እግረኛ፣ ገፁ ዙሪያ አየር ውስጥ ሌላው ተረኛ:: በየገበያው ውስጥ በቀስታ መሬት እያየሁ ስሔድ......ዕርጥበት አገኛለሁ......ይሔ እርጥበት ምራቅ ነው:: ብዙ ጊዜ እዚህ እርጥበት መሐል......ወይ ከእርጥበቱ ትንሽ ሳንቲ ሜትር ፈቀቅ ብሎ በአቧራ የተለወሰች እግሮቿ ተሳስረው......ክንፎቿ ረጥበው መብረር አቅቷት የምትንገዳገድ ዝንብ አትጠፋም......አንዳንዴ ከወደቁበት አንስቼ ሳያቸው......የሚያጋጥሙኝ በሆነ ምንገድ አካለ ስንኩላን ሆነው ነው:: አልፎ አልፎ ያሳዝኑኛል...... የመብረር ታላቅ ስጦታቸውን ተነፍገው......በሰው የሳል ቃጭል ታጅበው ጀርባቸው በባልጩት ድንጋይ ተሰብሮ (የሚተፋ [ተፊ] ቦታ አይመርጥምና) በምራቅ አሲድ ሲቃጠሉ ላይ.......



@BOOKALEM

አንድ ዕለት እዚያችው ጉብታዬ ላይ ተቀምጬ ስመለከት......ዝንቦች ከጠዋቱ ወረራቸውን መጀመራቸው ገባኝ:: ጥያቄዎች መጠየቅ ጀመርኩ:: እነዚህ ዝንቦች ከየት መጡ? እዚህ ምን ይሰራሉ? ሌሎች ከተሞችስ ላይ እንደዚህ ዐይነት የዝንብ ወረራ ይካሄዳልን? እስፈላጊ ግን ቾል የተባሉ ጥያቄዎች ነበሩ::

ጥያቄዎችን መመለስ አልቻልኩም:: እኔ ቢሆን ቢሆን የአምፖል እንጂ የዝንብ ባለሙያ አይደለሁ:: ሰዎች ወዲያና ወዲህ ይላሉ:: ማርያምና መድሃኒያለም ደርሰው የሚመለሱ ሴቶች ነጠላዎቻቸው በዝንብ ነጠብጣብ ተሸፍነው ይመጣሉ:: ምናልባት ሰዎች ወደ ከተማዋ እንደ ዕቃ በልብሶቻቸውና በገላዎቻቸው ተሸክመው እያስገቧቸው ይሆናል:: እንዲሁ እየታዘብኩ ሆዴንም ረሀብ እያስጮኸው እስከ አምስት ሰዓት ቆይቼ ልነሳ ስል አንድ ነጭ በነጭ የለበሰ ብቸኛ ሰው ከበስተግራ ከተማውን በቀስታ እያቋረጠ ሲመጣ አየሁት:: ከአካሔዱ ዘላቂ የሚመስል፣ ቁመናው ቀጥ ያለ፣ አለባበሱ ዜንጠኛ ነበር:: የሆነ ከተሜኛ የተዘየነ:: ግራና ቀኝ አያይም:: ቢመቸው......ከተማዋን እንደ ንፍሮ ዘግኖ ኪሱ የሚከት ይመስላል:: ፈራሁት:: ዝንብ እንደሌሉች አያባርርም:: እየቀረበኝ መጣ:: ከዚያ ጠራራ... ከጠለለችኝ ጃኬቴ ስር አጮልቄ እያየሁ ጠበቅሁት:: የጫማዎቹ አፍንጫዎች ድንቡልቂኝ ይንኩቸው እንጂ (እንደው በጥንቃቄ የተልባ ወጥ እንደላሱ ሁሉ) የሚያበሩ ጥቁሮች ነበሩ:: ድምፅም አላቸው ልበል? እንደዘፈን:: እኔን አለፍ እንዳለኝ ግን ይሄ ተንኘ ሌላ ሰው ሆነ:: ጀርባው......ከማጅራቱ ጀምሮ እስከ ቂጡ በዝንቦች እንደ ተሸፈነ አየሁ:: የሚያስፈራ ንጣት የነበረው ኮቱ በድንገት አስደንጋጭነቱንና ግርማውን አጣ:: ከዝንብ የበለጠ ብልጥ አለ? ፊት ሊፈቱ ያያቸዋል:: ካያቸው ያባርራቸዋል:: ሰውዬው ማባረር ከጀመረ አደገኛ ነው......ዝንብ ይገድላል:: ስለዚህ በእኔ ግምት ከዘሉትና ከሦስቴ ፍተሻ በሁዋላ አደገኛነቱን ተገንዝበው ዝንቦቹ ከሁዋላው ሰፈሩ:: ሰውዬው ሰፊ ጀርባ ላይ ጥቁር ቁራጭ ጨርቅ የተለጠፈ ይመስላል:: በአፍታ ስለ ሰውዬው የነበረኝ አመለካከት ተለወጠ......የመጥላት ወይም የመናቅ ሳይሆን እንደሌሎች እዚያ አብረውኝ እንደሚኖሩት ሰዎች ተራ ሆኖ ታየኝ......

......ከጉብታዬ ተነስቼ ልከተለው ፈለግሁ:: ጃኬቴን ለበስኩና ሳብ ችፍ ያለበትን ግንባሬን እየጠረኩ ከሁዋላው ከሁዋላው:: ሰውዬው ትንሽ ከእኔ መቅደሙ ብቻ ሳይሆን ሲራመድ በረኀኝነትም ነበር:: ሊጠጋውና ሊይዘው የሚፈልገው ነጥብ እንዳይሸሸው የፈራ ይመስላል:: ተከተልኩት:: በከፊል ሩጫ በከፊል ሶምሶማ:: እንዲታወቅብኝ አልፈለኩም:: ይኼ ከተማው ሥራ የፈቱ ብዙ ዐይኖች አሉት......ሁልጊዜም ነበሩት:: "ያ ጉብታ ላይ የሚቀመጠው መዝገቡ የፀሐር አስተካካዩ የዱባለ ልጅ የሆነ ሰው ይከተላል......ምን ሊያደርገው ነው?" የመሳሰሉ ነገሮች ማለታቸው አይቀርም ነበር:: (ምን ማድረግ እችላለሁ? ምንስ አቅም አለኝ?):: ስለዚህ በተመጠነ እርቀት ሳላስበላ ሰውዬውን መከተል ቀጠልኩ::



@BOOKALEM

ዝንቦቹ ከዜንጠኛው ጆርባ አልተነሱም:: ምናልባት ጠዋት ላይ እዚያች ቦታ ከመምጣቴ በፊት ሽንኩራ የበላች ሐፃን ልጅ አገሉ ይሆናል:: ከሰውዬው ሁዋላ ከዞብት የመሰልኩ ልጅ ስንጦለጠጦል......ዝንቦች እያዩ ዝም የሚሉ አልመሰለኝም:: እንጀራ እናቴ እንደምትለኝ ከሆነ ገና ቤቴ ሳልጠጋ በግምቴ (ወይስ በጠረኔ?) መምጣቴን ታውቃለች:: ገላዬን የታጠብኩበትን ቀን አላስታውስም......ድሮ፣ ድሮ ልጅ እያለሁ ይሆናል:: ዝንቦቹ የሊፍት ዐይነት መምረጣቸው ከሆነስ? ከእኛ የማይሻሉ ገበሬት ላይ ተሳፍረን ከምንሄድ......ንፁህ ነጭጭ ጨርቅ ለምን አንመርጥም ብለው......በመጠኑ የተናቅሁ መሰለኝ:: በዚያች ከተማችን ግን ይሄ ሰው እንግዳ ይመስል ነበር......ከዚህ በፊት ከተማችን ውስጥ አይቸው አላውቅም:: የከተማዋን ጠባይ ስላልለመደው ነው:: የለመደ......የጠረጠረ......የባሕር ዛፍ ዝንጣፊ ይዞ ጆርባውን ይገርፍ ነበር::

ሰውዬው አቧራው ውስጥ ሰንበሩ ያልደበዘዘ የአዲስ ጫማውን ማሕተም እየተወ (በአንዳንድ ሜትር ዕርቀት) ቶሎቶሎ ይጓዛል:: ተከተልኩት:: ባለጫማ ስላልሆንኩ ጠጠር፣ ግርድፍ አፈር፣ አሸዋ፣ ሣርና አመድ ለውስጥ እግሮቼ የተለያዩ የምቾት ደረጃ አላቸው:: ካልቸገረኝ፣ መረማመጃ ካልጠፋ በኮርኮንች አልሄድም:: የከተማዋ አደባባይ ግን ብዙው ጠጠርና ግርድፍ አፈር ነበር (ከተማዋ ከመቆርቆሯ በፊት ከብት የሚሰማራበት ዘንባባ የሸፈነው ለምለም ቦታ ነበር ይባላል) ስለዚህ የሰውዬው መኖር ለእኔ ተመችቶኛል:: በጠጠሮች ላይ ሲሄድ በጫማው ያስተካክላል......በግርድፍ አፈሩ ላይ ሲራመድ ግርድፍ አፈሩን ያልመዋል......ታዲያ እኔ እንደጫዋታም እያደረግሁ እሱ የረገጠውን እየረገጥኩ እሔዳለሁ......

......ሰውዬው ከከተማው ጥቂት ወጣ እንዳለ በስተቀኝ ወደ ጠላ ሻጯ አስካለ ቤት ቀርቦ በር አንኳኳ:: ቤቷ አጥር አልነበራትም:: ዋናውን ምንገድና ቤቷን የሚለያቸው ሠፊ ቦይ ነው:: ይኼ ቦይ ድልድይ የለውም:: ከመሐሉ ብቻ ትላልቅ ድንጋዮች ለዝናብ ቀን መረማማጃ ተብሎ ("እዚህ ጋ!! እዚያ ጋ!!" እየተባለ) ተንጥፈውበታል:: በመጠኑ ዘመም ያለች የቤቷ አንዲት መስኮት ክፍት ናት:: የቆሸሸች ባለ አበባ መጋረጃ ተገለጠችና አስካለ ጥቁር ሻሽ ጠምጥማ ሞላላ ፊቷን ብቅ አድርጋ "መጣህ ጋሼ?!" አለች:: ሁለቱም ዐይኖቻቸውን ለቅፅበት ወደ እኔ አቅጣጫ ወረወሩ......የነበርኩ፣ እዚህ ፕላኔት ላይ የተፈጠርኩ አልመሰላቸውም......(*እያዩ አለማየት ሆነና ነገሩ፣ ያደግንበት ቦታ ጠፋና መንደሩ—እለ ዘፋኝ*):: ሰውዬው ከጥቂት ሰኮንዶች በሁዋላ በር ተከፍቶለት ገባ:: ሳልፍ ሳገድም የማየው ቤት ነበር:: ብዙ ጊዜ ሳልፍ ሳገድም የማየው ግድግዳ የተደገፉ አግዳሚ ወንበሮች:: ሰውዬው ሲገባ ዝንቦቹ ከጆርባው አልተነሱም:: በሩ እንደተከፈተ ቆየ:: ድምፅ ለመስማት እፈልግ ነበር:: የቤቷ ወንበሮች ግድግዳ ተንተርሰው ስለተደረደሩ ሰውዬው ሲቀመጥ በጆርባው ወደ ሁዋላ



@BOOKALEM

መደገፉ ስለማይቀር ዝንቦቹ በጆርባውና በግድግዳው መሃል ላለመጣበቅ ሲሸሹና ሲነሱ 'እው' የሚሏል ድምፅ ለመስማት ጠበቅሁ:: አልነበረም:: የሰውዬው ነጭ ቅርፅ የቤቷ ግራጫ ውስጥ ሲቀመጥ አየዋለሁ:: ከዚያ አንጀቴ እስኪፈርስ መሐል ጎዳና ላይ በሳቅ ፍንድት አልኩ......

ከዚያ በሁዋላ......

እንደ እልግጫ መሆኑ ነው......ልክ እንደ ሰውዬው እየተራመድኩ ከተማው መሐል ወደአለችው ጉብታዬ ተመለስኩ......ተቀምጬ፣ ቦታዬ ተመቻችቼ......በእጄ ጆርባዬን ስመታ......የዝንብ ድምፅ አልሰማሁም::

ያች ቀትር ላይ ከሳቅሁዋት ሳቅ......ረቂቅ ቅባቷን እስኪመሽ አፌ ዙሪያ.......በስሱ......ውርጭ እንደ መከላከያ ቫዝሊን ተቀብቼአት ቆየሁ::



@BOOKALEM

# ከሬቫቱ

ፊት ለፊቴ መጥተው ሠርገኞች ከሁለት መኪናዎች ወረዱና የማይገባኝ የሥነሥርዐት ወሬ አወሩ:: የሠርግ ነገር ሁልጊዜ ይዞርብኛል:: ልጅ እያለሁ 'ሚዜ' ና 'ሙሽራ' የተባሉ ቃላቶች ይምታቱብኝ ነበር:: 'ሚዜ' የሚለው ቃል 'ሙሽራ' ከሚለው የሚከብድ እየመሰለኝ:: እና ሚዜው ከሙሽራዋ የሚጋባ::

ቀትር ላይ ብዙ ጊዜ ምሳ አልቆ ቤቴ ስለምደርስ፣ እእ: "ና የእኔ እምቦሳ......ናልኝ ምንም እኮ የምሳ ጊዜ ጠብቀህ አትመጣም" ትለኝና አፏን እንደማባበልም አሞጥሙጣ......ገና ከምጣዱ የወጣ......ትኩስ ሽንብራ በሱሪዬ ኮሮጆ አሲዛ ታባርረኛለች::

ውጪው ፀሐይ ነበር እንግዲህ......ውጪው ቃጠሎ ነው......የቁምጣዬ ኪስ ደ'ሞ ቆሎው ይገባበትና እንደ ፍም ያደርጋታል፣ እንደ ጨርቅ የእሳት ነበልባል ይሰራታል:: ከዚህ ቢታደገኝ ብዬ ቆሎ የከተትኩባትን የኪሴን አንድ ጠርዝ ጭኔን እንዳይነካ እንደቆሻሻ ዕቃ በአውራጣቴና በአመልካች ጣቶቼ ከፍ አድርጌ እይዝና ጉብታዬ እወጣለሁ:: እስከዛሬ ሽምብራ አልወድም......የሽንብራ ቂጣ፣ የሽንብራ ሽሮ ሲባል ጠር መምዘዝ ነው የሚቀረኝ:: ታዲያ 'ሙሽራ' የሚለው ቃል 'ሽንብራ' ከሚለው ቃል ጋር ጆሮዬ ውስጥ ተመሳሳይ ቅላፄ ይሰጠኝ ነበር::

እንደ አጋጣሚ ሆኖ......በሕይወቴ ለመጀመሪያ ቀን ያየሁት ሙሽራ......በጣም ትንሽ፣ አጭር ሰው ነበረ:: 'ሽምብራ የሚያክለውን ታግባ!?' እየተባለ ሲወራም ሰምቻለሁ::

ሠርገኛው እየተንጋጋ ከመጣበት ሶስት ግልጥ መኪናዎች (ፒካፖች) መካከል የሁዋለኛው ሙሽራው ያለበት ነበር:: መገመት ቀላል ነው:: የሙሽራው ፒካፕ ንፁህ ነው:: ከዚያም በላይ በብዙ የጽድ፣ የዘንባባ፣ የአበባና የባሕር ዛፍ ቅጠል ዝንጣፊዎች ዙሪያውን የታጠረ ነበር:: ወደ መኪናው ውስጥም ሳይ ነጭ ልብስ ይበዛል......የቬሎ ከፊልም......በወዲያኛው መስኮት በኩል ከትንሽ ባሊ ገንፍሎ የወጣ ንጹህ ጋቢ የተዘፈዘፈበት አረፋ መስሎ ወጥቷል:: ዣንጥላ የያዘ ሰው ከሌላው ቆሸሽ ያለ ፒካፕ ላይ ወርዶ መጣና ሙሽራዋን ከነበረችበት መኪና ውስጥ በከፊል እያቀፈ በከፊል እየጎተተ አወጣት:: ሙሽራው ተከተለ:: ሴትዬዋ ረዥም ነበረች:: የተቀመጥኩበትን ቦታዬን መተው ባልፈልግም ለወሬ ጓጉቼ ወደ መኪናዎቹ ተነስቼ ሔድኩ:: የሙሽራው ፒካፕ መኪና የሁዋላ ጐማ ፈንድቷል:: "በአንድ ጊዜ ሁለት ጣጣ" ይላል አንዱ ሚዜ (ሁለተኛው ጣጣ አልገባኝም):: ሙሽራው ሊረዳ መጣ:: የሙሽራው ቁመና አጭር ነበር (ያየሁት ሙሽራ ሁሉ አጭር ነው?) ጠቅላላ አቋሙን ሳየው ቆየሁ:: ጥቁር ኮትና ሱሪ ለብሷል:: እና በጣም ነጭ ሸሚዝ:: ጫማዎቹ ደ'ሞ ረዥም



@BOOKALEM

መፍረም ፣ ተረክዞ ነበራቸው:: እየተንገዳገደ የሚራመድ ይመስላል:: ዐይኖቼ እቋሙግ ሲያበጥሩት ቆዩና ክራቫቱ ላይ አረፉ:: ክራቫቱ ረኝርምና ሰፊ ነበር:: እንደቀለጠ ላስቲክ የተኰመጣተረ:: ከክራቫቱ ሽምቀቆ ጀምራ ትንሽ አረንጓዋዴ ዝንብ በክራቫቱ ሰረሰር ላይ ያለፍርሃት ትመላለሳለች:: ይኼን የክራቫት ጨምዳዳ ሳይ፡ አረፉ የመሰለው ቪሎ፣ መኪናዎቹና ጥቁሩ ሰፍ ልብስ ዋጋ አጡብኝ:: በፒካፕ መኪና መዳር በገጠር ኩተማ እጅግ ክብር ነው:: ለመሆኑ ለሙሽራው ፒካፑ ይበልጥበታል ወይስ አንገቱ ዙሪያ የሚያጠልቀው ንፁህ ክራቫት? ከባለቤቱ ያፀቀ ቡዳ ነው እንዳልባል እንጂ:: መሳቅ ቃጣኝ:: ከሠርገኞቹ አንደኛው እንድረዳው ሊጠራኝ ነበር መሰል ሲጋራ ከሸሚዙ ደረት ኪስ አውጥቶ ከንፈሮቹ መሃል ሰካና ፊቱን ወደ እኔ አዞረ:: እንዳላየሁ ወደ ጉብታዬ አቀናሁ:: ሳቄን አምቄ ይዤ......በሁዋላ ተረጋግቼና አግሬን ዘርግቼ ጉብታዬ ላይ ለብቻዬ ልስቃት (ይሄ ድርጊቴ ተንክል ነውን?) ለብቻ እንደመሳቅ ደስ የሚል ነገር አለ? ብቻን ሲሳቅ የሚጠይቅ የለም (የሚከለክሉ የሳቅ ዐይነቶች እንዳሉ የሚያውቅ ጥቂት ሰው ነው):: ራሴን ተቸቼ ብጠይቀው እንኳን ክርሜ ክርሜ ሳረጅ ነው:: ወይ በጉልምስና ዘመኔ በትዝታ ወደ ሁዋላ ስንሸራተት ("ለምን ያን ጊዜ በሙሽሮቹ ሳቅህ? ደግ አልነበረም" ብዬ......ራሴን)::

ያቺን የሾረች፣ በጉድፍ የምታብራ ክራቫት ግን አልረሳትም::

ለክራቫቱ ለክራቫቱ አባቴም ክራቫቶች ነበሩት:: ሁለት:: አንደኛው ሌሊዘን ሁለተኛው ለልዩ ቀን:: ሲሰይማቸው ነው የሰማሁት:: አንዳንድ ቀን ካስቀመጠበት ቦታ ያወጣቸውና አንዱን በግራ እጁ ሌላውን በቀኝ ይዞ......እያነጣጠረ ያይና......'ጥቁሩን እወዳለሁ' ይላል:: ለብሶት አይቸው ግን አላውቅም:: እኔ ስሞት ያደርገው ይሆናል::

እኔ ደ'ሞ በቅርብ የምሞት ይመስለኛል::

ምክንያቱም ጤነኛ ሰው፣ ጤነኛ ልጅ ስልክ እንጨት ስር ተጉልቶ አይውልም::

ምክንያቱም ጤነኛ ልጅ በሳምንት ሰባት ቀን ምሳውን የተንገረገበ ወይም የተቆላ ሽንብራ (ለዐይነት መሆኑ ነበርን?) አይበላም::

ምክንያቱም ጤነኛ ልጅ ከሰው ሁዋላ እየተከተለ ጀርባ ላይ ያረፈ ዝንብ አያጤንም::

ምክንያቱም ጤነኛ ልጅ ብቻውን አይስቅም::

ምክንያቱም ጤነኛ ልጅ ክራቫትን እንደቁም ነገር ወስዶ አያስበውም::

ታዲያ ግን......ሁሉ ያማረበት ጤነኛ የተባለ ሠርገኛ ጨምዳዳ ክራቫት ለምን አሰረ......?



@BOOKALEM

# መጠጣት

አንድ ዕለት ማታ ሁለት ሰዓት አካባቢ በዝግታ እያሰበ የሚራመድ ሰው ወደ ተቀመጥኩባት ስልክ እንጨትና አምፖሉ ጋ......ብርሃን አምሮት ነው መሰለኝ-ሲጃራ እየጠጣ መጣ:: የትምህርት ቤታችን አስተማሪ ጋሼ ሐይለኛው እንደሆነ አውቃለሁ:: ምን እንደሚያስተምር ግን አላውቅም:: ምክንያቱም አያገባኝም:: አስተማሪን ቢያውቁት ምን ይጠቅማል:: አስተማሪ የሚያውቁት ወንዶች ልጆች ቢበዛ የሚያገኙት ጥቅም-ጥቅም ከተባለ "መላክ" ነበር:: ሴቶቹ ደሞ አንዳንዶቹ የጭን ገረድ ይሆናሉ፣ አንዳንዶቹ ቀንቷቸው ይሁን ተረግመው ሚስት ይሆናሉ፣ አንዳንዶቹ ወሬ አመላላሽ ይሆናሉ:: የአንዳንድ ተማሪዎች ጉራ ግን ይገርመኛል:: እንደ አሽከርና ገረድ በተላኩ እንደ ሽርሙጣ በተተኙ ጉራቸው ይገርመኛል::

"ሽንኩርት ግዙ"

"ኩካኩላ ግዛልን"

"ጠላ አምጣልን"

እንዲህ ያለ ነገር አልወድም:: አስተማሪ ሐይለኛው ሲጠጋኝ አንገቴን ወደ መሬት ደፋሁ:: ጀርባውን ለእኔ ሰጥቶ ሲያጨስ ቆየና የሲጃራዋን እሳት ሳያጠፋ አፒራ ላይ ወረወራት:: ከዚያ ዞር ብሎም ሳያይ የመልስ መንገዱን ጀመረ:: ሰውዬው ራቅ እንዳለ ሲጃራዋን ከወደቀችበት ፈልጌ አነሳሁዋት:: እሳቷ አልጠፋም ነበር:: ቁሩዋን በቀኝ እጄ ደብቄ ጉብታዬ ላይ ይገኛት ተመለስኩ:: ፍሟን ስስ አመድ ጋርዷታል:: አመዷን ለማራገፍ ስሞክር ሲጃራዋ ከማጠሯ የተነሳ ከጣቶቼ መሐል አመለጠችኝ:: ዙሪያዬን ተገላምጬ አይቼ ከወደቀችበት እንደገና አነሳሁዋት:: የመጀመሪያ ሲጃራዬን ጠጣሁ:: ጠረኑ አፍንጫ ይበጥሳል:: ደገኛ አይደለሁ:: በጠራ አየር አድጌ:: ጉብታዬ ላይ ተኮፍሼ አንድ ኩርማን ኒያላ:: ሲጃራው ቡሽ ሲቀረው ቀድሞ ወድቆበት ወደነበረበት ቦታ ወርውሬ መለስኩት::

ለመሆን ሳል ሳልኩ?

እንክት አድርጌ::

እሪታ ሊሆን ጥቂት የቀረው::



@BOOKALEM

## ከቆንጆ ልጅ ጋር መደነስ ሳይጣፍጥ አይቀርም

ይህቺን ዓለም እግዜር ያለአጋር አላዋቀራትም፣ አልሰራትም:: ለጨለማ ብርሐን፣ ለውሐ እሳት፣ ለነጭ ጥቁር፣ ለሴት ወንድ እያደረገ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ሰው ራሱ የለመደው በእግዜር የተሰጠው አጋር ይሰለቸውና የራሱን አጋር ይፈራጥል:: ወይም ቀድሞ የራሱን አጋር ይፈጥርና ዘግይቶ እግዜር ወደ ሰራለት ይመለሳል:: አንዳንድ ጊዜ እኔም እንደሌላው የሕይወት ምንገደኛ ጉብታዬን ገና ሳያት ትሰለቸኝ ነበር:: ጠዋትና ማታ እንደ መጥፎ እህል እያቃሩኝ በዝምታ የማልፋቸው የትምህርት ቤት ጓደኞቼ ራሴን እስኪገርመኝ ድረስ ይናፍቁኛል:: አንዳንዴ የትምህርቱ ክፍለ-ጊዜ ረዝሞ ገጣጣው የሳይንስ አስተማሪያችን ጃለታ በአፋ ንፋስ እያስገባ ለሁለት ሰዓታት ማስተማሩን ቢቀጥል እወዳለሁ:: ሁሉን ሰው መሳም እፈልጋለሁ......እየሮጥኩ ሔጄ አንገታቸው ላይ ተጠምጥሜ በየተራ......ቢቻል አንገታቸው አንድ ሆኖልኝ፣ ጉንጫቸው አንድ ሆኖልኝ:: እምጳ እምጳ በአደርጋቸው:: ይሔ ግን ጥልቅ ቢሆንም የቅፅበት ስሜት ነበር:: ባልታወቀ ምክንያት ከአፍንጫ ስር ውልብ ብሎ የሚጠፋ ዐይነት ሁድ:: ስሜቱ እራሱ ጥንት ጥንት የሰረፀብኝ ዐይነት መስሎ በበነጋታው እንደ ረቀቀ ተራ ትዝታ የሚታወሰኝ::

ማታ አባቴ አዲስ ቶንዶስ እንዳመጣለት ወደ ቤት ልኩኝ ስመለስ ወሰንን አገኘሁዋት:: ወሰን የለሽ ማለት ዝነኛ ናት:: ወሰኔ ማለት 'ከወለዱ ላይቀር እንደሷ መውለድ ነው' የሚባልላት ቆንጆ ናት:: ሴት ስትወለድ ካማረች 'እንደወሰኔ ናት' የሚባልላት ናት......እኔ ግን ቀለም አልነበረኝም:: ቢብስ 'ያ አቧራ እየጠጣ አደባባይ ላይ የሚቀመጥ ከንታዋ' ብባል ነው:: የእኔ ዝና ዱርዬነት ነበር:: የእኔ ዝና ስራፈትነት ነበር......'ያ እንደተሸካሚ እዚያ ተጉልቶ የሚውል' የምባል ነኝ:: አላፍርበትም:: ከዚያ በላይ መሆን አልችልም::

ቶንዶሱን በአንድ እጄ ይዤአለሁ......ወሰን የለሽ ነጠላ ጫማዎቿን እያንጣጣች ከፊት ለፊቴ ትመጣለች:: ቀኑ ዝብያ ነበር:: ባጠገቤ ስታልፍ ዞር ብዬም የማላያት ያኔ ወደድኳት::

"ወሰን" እልኳት::

ግራ ገብቷት አየችኝ::

ስጠጋት አይኖቿ እየፈሩ ጠበቀችኝ:: ግራ እጇን ልይዛት ስል (ለምን ግን ግራ እጇን? የተገኘውን መያዜ ነበር) ወደሁዋላ አፈገፈገች::

"ነይ እንደንስ!" አልኳት::

"እንዴ! አበደ እንዴ ልጁ"



@BOOKALEM

አልፋኝ ለመሔድ ስትፈልግ መንገዱን ዘጋሁባት።

"ዞር ካላልክ እጮሃለሁ" አለችኝ።

በመድሐኒያለም ነው የምለው ጠላሁዋት። ደ'ሞ ብልሐቷ፣ ተንኩሏ ገረመኝ። ከእኔ የምታንስ ናት።

"ምንድነኝ ነው የምትይው?"አልኳት

"ምንስ ብሆን?"

"እንደንስ" ከልቤ አልነበረም።

እንደ መናቅ አድርጋ በቀስታ ገፍታኝ አለፈች።

*(የማንም ወገኛ መንደር ያደነቃት*
*ታገነግናለች እንላምሽ ስንላት*
*ባል ባል አታርጊን እንቺ ባለ ሱሪ*
*እንዳታፈጭብን ሲደርስን ሉተሪ*
......**የንፋስ መውጫ አዝማሪ**)

ጩኸት ይጠቅማል እንዴ?።

እጮሃለሁ  ባትለኝ እጇን ይዤ ልሽከረከር ነበር። ዳንስ ደሞ ጉብዝ ነኝ። ማታ ማታ ጉብታዬ ላይ እንዳንዴ ከተማው መሃል ካሉ ሶስቱ ሻይ ቤቶች በመስኮትና በበር እያመለጠ የሚመጣ ስደተኛ ሙዚቃ እምቀመጥበት ቦታ ሲደርሰኝ በትራፊው እለማመዳለሁ። ለጥምቀት ለጥምቀት ዘመድ ለመጠየቅ ከዋናው ከተማ የሚመጡ አንዳንድ በዓለኞች በፈረንጅኛ እስክስታ ሲደልቁ ትንሽ ኮርጄአለሁ። ግን ከቆንጆ ጋር ገና ልጅ እያሉ ቢደንሱ እስኪሞቱ አይረሳም። በተለይ እንደወሰን ካለች ልጅ ጋር።

ከእሷ ሁለት እርምጃ እንደራቅሁ......ጭልም አለብኝና የሚታየኝ ነገር ቢኖር ጉብታዬ ብቻ...... 'ጀሃነም ግቢ' አልኩ በልቤ። የሚያምር ስም ብቻ......መልክ ጥፉን በስም ይደግፉ።

እንግዲህ ተንቀልቅዬ አጋር አግኝቼ ሙቼ በግ ያለብኝን ስሜት በዳንስ ላብርድ አልኩና ወሰንየለሽን ብጠጋት.......ፎረሸ።



@BOOKALEM

# ከቴም

ማታ ላይ ገበያው ተበትኖ ሸቃይና ሸማች ወደ መጣበት ሲመለስ እኔ ግን ከገበያው ዕምብርት ብዙም ሳልርቅ ያቺ ጉብታዬ ላይ ስልክ እንጨት ተደግፌ የለመድኳትን ናና ከረሜላ በፍቅር እየመጠጥኩ። ......ከሰዓት በሁዋላ ዝናብ ጥሎ ስለነበረ ቦታው ርጥብና ቀዝቃዛ ስለሆነብኝ መቀመጥ አልቻልኩም። አፌ ውስጥ ያለችው ናና ከረሜላ ሦስተኛዬ ነበረች።

በቀኝ የካኪ ኮት ኪሴ የአፈር ብናኝና የሳር ስብርባሪ (እንዴት እንደገቡ ብዙ ጊዜ ራሴን እየጠየቅሁ መልስ ማግኘት አልችልም) በየጥጓ የደበቀች ኪሴ ውስጥ ከደብተር በተገነጠለ ወረቀት አምስት ናና ከረሜላዎች ተጠቅለው ተቀምጠዋል። እነዚህን ኮሜጭ በሆነ ቅመም ውስጥ የተነከሩ የስኳር ብስኩቶች ስቆረጥም፣ ስመጥ ዐይኖቼ ይከፈታሉ፤ መከፈት ብቻ ሳይሆን ጥራታቸው የጨመረ ይመስለኛል። የሰራ ገላዬም ይረጋጋል፣ ይዝናናል። የሆነ ሚስጥራዊ ሐይል በደም ስሮቼና በጡንቻዎቼ ውስጥ ይወራጫል።

ጉልቶች ሁሉ ተነቃቅለው ነጋዴዎች በድንጋይ ኮረት ያጠሯቸው ትንንሽ አራት ማዕዘን ዕርስቶቻቸው በተራቆተ አፈራቸው የከተማውን ታች ከፊል ጉርብጥብጥ አስመስለውታል። አያ ፀጥታ ባስለመዱት ቀጠሮ አደባባዩ መሃል እንደ ግራጫ ብርድልብስ መውደቅ ሲጀምር አንድ ሐይለኛ ቀጭን ድምፅ ከበስተላይ እንጢቆ ዙሩን ከሚኖርበት አቅጣጫ ደም እንደተነከረ ጨቤ እየተወረወረ መጣ። ለአፍታ ከረሜላ መምጠጤን አቆምኩ። ድምፁ ከዚያ አቅጣጫ ይምጣ እንጂ ከማን እንደሚወጣ መለየት ከበደኝ። ያለኝ አማራጭ እዚያ አካባቢ ከነበሩ ጥቂት ሰዎች በጋራ ወደሚያዩበት በኩል ዐይኖቼን ማዞር ነበር። ሴትዮ ናቸው። ስማቸው አፌ ላይ አይመጣልኝም። ቀላል ስም ነበር ግን አይያዝልኝም። ምናልባት ከልጅነቴም ጀምሬ የምሰማው "የፀሐይ እናት" እየተባሉ ሲጠሩ ስለሆነ ስማቸውን የማወቅ ግዴታ ስላልተጣለብኝ ይሆናል። የፀሐይ እናት ጀርባቸው ወደ እኔ በኩል ነበር። ሽሮ የመሰለ ነጠላቸውን (ከእኔ በስተግራ ያለው የነጠላቸው ጫፍ ቀጭን አረንጓዴ ጥለቱ ተቀዶ ድንጋይ እየመታ ለብቻው መሬት ያብሳል) ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው እጆቻቸውን ዳሌዎቻቸው ላይ አስደግፈዋል። ታዲያ መብረር የሻቱ የሉስ ያስመስላቸዋል። እኔ እያየሁዋቸው ፀጥ ብለው ነበር—ወደ ላይ እያዩ—ለእኔ ወደማይታየኝ አቅጣጫ:

"ኩቴም ተዳደርን! ኩቴም ተዳደርን! መጫወቻ ሆንኩ እኔ ልጅት *(ፊታቸውን ወደ ታች አዞሩ)* ይሁና! ይሁና! ይሁና! *(እንገታቸውን ሰበር አድርገው ወደ መሬት፣ ለመሬት)* መውለድ ምን ረባ። አልረባም እኮ! ምን ረባ *(ፊታቸውን ወደ ላይ አነሱ፣ ወደ ጎን አዞሩ)* ማን ነኝ ነው የሚለው ለመሆኑ? እ!? እ!? *(ፊታቸውን ወደ ሰማይ አንጋጠጡ)* እሱም ችላ



@BOOKALEM

አለ ምነው ጉልበተኛ ሲጨፍርብን:: ሴት ሳይማ ትበረታላችሁ:: የምትችሉት እሱ ነው:: ሽርሙጣ:: ዘረ–ሽርሙጣ ሁሉ:: በየት እንጀራችንን በልተን እንደር:: ይህቺም ማደር ተሁና:: ሚስት አለው! ትልቅ ልጅ ያደረሰ ነው! ምን ዐይነት ሰይጣን ቢያድርበት ነው ክብር የሚገፈው:: *(ወደ ታች መንዝ ጀመሩ:: በእግራቸው አውቀው ይሁን ሳያውቁ ድንጋይና ጠጠር ይመታሉ:: ጫማ ያድርጉ ኣያድርጉ እርግጠኛ አልነበርኩም:: ወደ እኔ ፊታቸውን አዞሩ)* ጉድ ነው! ጉድ ነው! መድሐኒያለም ይሄን ጉድ እይ:: *(እኔን ያዩኝ አይመስልም:: ወደ ውስጣቸው ነው የሚያዩት)* ቆዳው ጨዋ:: *(ፊታቸውን ከእኔ መልሰው ኩታቸውን ለመሰብሰብ ሞከሩና ተዉት:: የደከማቸው ወይም የሰለቹ ይመስላሉ)* ከቴም አስተዳዳሪ ተባለልኝ:: ከቴም ተዳደረ:: ትምህርት ቤቱን ስትከፍተው ነው? ጤናችንን ስታስተካክል ነው? ስታኻሽሉን ነው? እንዳችሁ አስረግዛችሁ ትሄዳላችሁ፣ እንዳችሁ ሰናሳድግ ታዩናላችሁ፣ እንዳችሁ ደሞ ያሳደግናትን ትደፍራላችሁ:: ሌላ ቁም ነገር የታለሽና:: አወቅንሽ አዳሜ:: ወስላታ ሁሉ:: *(ምራቃቸውን ተፉ:: ፀጉሩ በትንሹ ያደገውን አናታቸውን በስሜት አከኩ:: ከጀርባቸው የማከካቸው እርካታ የታች ገላቸው ረግቶ በመቆሙ ይታወቃል)* ከቴም! ከቴም ወንድ ተሆን! አበላሺ ሁሉ:: እርጉም ሁሉ:: ጦር ሰብቀሽ ማሸነፍሽ ነው! እግዜር ጠርጎ የሚወስድ ነገር ይላክልኝ:: እኔ ይህቺ ነገር ፍጣሜ ሳታገኝ አለቅህ:: ንጉሥ ዙፋን እቀርባለሁ:: ንጉሡ ዙፋን ቀርቤ አንድ የንፋስ መውጫ ወደላ አቅሙን ተጠቅሞ የሴት ልጅ ደፈረ ብዬ:: አለቅህ:: እኔም አልወለድኩም:: አንተም አላበላሽህም:: ከቴም አክብሩኝ:: አክብረናችሁ ስንሰግድ ቀና ከማለታችን ሴት ልጆቻችንን ትነጥቃላችሁ:: ክብርናቸውን ትወስዳላችሁ:: የልጄን ክብር በጉቦ ልስጥ?? 'ዝም ካልሽ አስተዳድርሻለሁ' ይለኛል::"

ሴትዮዋ መንገዳቸውን በቀስታ ቀጠሉ:: እየኑ መቀዝቀዝ ጀምሮ ሳይሆን አይቀርም በሐይል አነጠሱ:: ፊታቸው ሲዝረከረክ አያለሁ:: ፊታቸውን እንዳለ በኩታቸው አበሱና–ገና እጃቸው ከፊታቸው ላይ ሳይነሳ:

"ጉድ እቴ! ተዳደርና ተዳደርን:: መሰልጠኑ ነው:: አንዲት ፍሬ ልጅ ምኗ ውስጥ ምን ይገባል? ምኗ ደርሶ ነው:: ምኗ አብቦ ነው:: ወይ ሆዳሜ የኔ ሆዳም:: በእኩያዎችዋ ወንዶች ቀናህ:: ግማታም የገማ::: *(ፊታቸውን እንደገና ጠረጉ:: ገና እንደተዝረከረኩ ማሰኳቸዋል ወይም ተጠራጥረዋል)* ምን ታዩኛላችሁ ነግ በኔ ነው:: ነግ በኔ ነው:: ደሞ 'ደብቂ':: ከቴም ተደበቀ ከቴም ተደበቀ:: ዝንጀሮ የቂጡን መላጣ እንዴት ይደብቃል? ተቀምጦ ሊኖር? ተቀምጦ ይኑራ ምን አገባኝ:: ከቴም! ከቴም አስተዳዳሪ!"

ለአፍታ ዞር ብለው አዩኝ:: ፊቴን ወደ ሌላ አቅጣጫ መለስኩ:: ያን ሁሉ ሲያወሩ የሴትዮዋ አላማ አልገባኝም ነበር:: ትንሽ ቶሎ ቶሎ ሄዱና ቁጭ አሉ:: ይሄን ቁጭ አውቀዋለሁ:: በየቦታው ከጠዋት እስከ ማታ የማየው የሴቶች ቁጭ ነው:: በእጆቻቸው መሃል



@BOOKALEM

ፊታቸውን አስደግፈው የሚተክዙ መሰሉ (ፊታቸውንም ያካሉ ልበል? መነሳታቸውን ረሱት መሰለኝ ብዙ ቆዩ:: ከላይ በዐይን ይከታተሏቸው የነበሩ ሰዎች ንግግር ይለዋወጣሉ:: ይህቺ ሁኔታ በዚህች ሌሊት ለሁሉም ተዳርሳ......)

"ኩቴም ኩቴም ተኖረ!" (ጥቂት ወደ ፊት ተራምደው ወደ ሁዋላቸው መሬት ላይ አዩ:: ውሐ የጠገበው መሬት ላይ ትንሽ ጣና ሐይቅ የተሰጣ ይመስላል–ያውም ባለአረፋ:: ኩታቸውን ከተንጀላጀለበት ሰብስበው ተከናነቡ:: ከዚያ ያውሩ አያውሩ ይጩሁ አይጩሁ ልሰማቸው አልቻልኩም::) ጉጉት አደረብኝ:: የፀሐይ እናት እንዲህ የሆነብትን ምክንያት ለማወቅ ጉጉት አደረብኝ:: ሌላ ናና ከረሜላ በጉንጩ ያዝኩ:: ቀድሞ አፌ የገባችው በምላሴ ለዝባ የምትሰጠኝ ደስታ እየጠፋ ነበር::

ፀሐይ በዕድሜ ከእኔ ቢያንስ ሦስት አመት የምትበልጥ፣ ሁለት ክፍል ቀድማኝ የምትማር ልጅ ነበረች:: ሁሉም የሚያውቃት ወንዳ ወንድ ቀልቃላ በመሆኗ ነበር:: እኚህ እናቷ የጉሬዛ ቆዳና ማገዶ ከከተማ ውጭ እያመጡ ለገበያና ለባዛን ቀን ይሸጣሉ:: ፀሐይ ከወንዳ ወንድነቷ ሌላ በከተማው የምትታወቀው እንደ እናቷ ከትምህርቷ ቀን ውጭ ከሙስጠፋ ሱቅ በስተግራ ያለው መተላለፊያ መንገድ ላይ ተጠቅለው በገመድ የታሰሩ (ብዙ ጊዜ ሦስት ወይም አራት የሚሆኑ) የጉሬዛ ቆዳዎች ስለምትሸጥ ነበር:: በከተማው ቤቶችና ሆቴሎች ያሉት ብዙ ወንበሮችና መደቦች ላይ የሚጣሉት የጉሬዛ አጎዛዎች ከእሷ የተገዙ ነበሩ::

ጉጉቴ ሳይውል ሳያድር የረካው የፀሓይ እናት ሲጮሁ የነበረበትን ምክንያት ወሬውን ከቤት ስሰማ ነበር:: እእ የምትሰራው ጠፍቷት ደረሰኩ:: የምትሰራው ስራ ሁሉ ሲያበሳጫት፣ ሲያሳክካት.......ነገር እንደ ተበላሸ ገብቶኛል:: የተበላሸው ምን እንደሆነ ግን አልገባኝም ነበር:: አባቴ ያለጠባዩ ከስራው ወደ ቤት ቶሎ መጣ:: ኀንጥላውን እንኳን በስርዓት አላስቀመጠም::

"ምንድን ነው እሱ ያቺ ዕብድ ምን ሆነች? ሰማሽ?"

እእ ከጓዳ ወጣች:: ፊቷ ጭር ብሷል:: ስለ ፀሐይ እናት ማውራት እንደጀመሩ ገባኝ::

"ምን ትሰራለህ ትልቅ ሰው ወሬ መሃል... ከዚህ ውጣ " አለች:: (ፊቴ ላይ ደስታ አየች እንዴ?)

ጦል ጦል ብዬ መኝታ ቤቴ ገባሁ:: መኝታ ቤቴ የአንድ ሰው አልጋ ብቻ የምታስነጥፍ ጠባብ ቦታ ነበረች:: ውስጧ አልጋ፣ አልጋ እንደገና ያው አንዱ አልጋ ብቻ:: በር የላትም:: ለበር ማስገቢያ ከተሰራው ቀዳዳ ፊት ለፊት ግን የፊት መስታወት የምታክል መስኮት:: ታዲያ በትክክል ወደ ክፍሌ ስገባ እንዳልገባሁም ይቆጠራል:: እና በር ላይ ቆሜ ሰማሁዋቸው.......



@BOOKALEM

"ከአንቺ ጋር ምን አገናኛቸው?" አለ ዱባለ።

"እኔ ነኝ የመከርኳት። እሳዛ ስትሸጥ አግኝቻት ተፍ ተፍ ያልሽ ልጅ ስለሆንሽ ደህና ሰው ቤት ብትሰሪ ገንዘብ ታገኛለሽ። እሷን ጠርቀምቀም አድርገሽ እዚህ ውጭ ከምትጎለቺ ሱቅ ቢጤ ትገዥያለሽ አልኳት። የከፋት አልነበረም።"

"ምኑ መጥፎ ነው ይሄ ምክር?" አለ አባቴ በጎርናና ድምፁ።

"ስትሰድበኝ ነበር አሉ ስሜን እየጠራች።"

"ይገርማል የአበራን ልጅ ሳስተካክል እኮ ነው ማነው ያ የእንትና አበልጅ ስሙ ጠፋኝ ኢድያ-መጥቶ የነገረኝ።"

"ልጅቷ ራሷ ቀልቃላ ናት። አቶ እንግዳ ይህቺን አንዲት ፍሬ ልጅ እንዲህ ያደርጋሉ አልልም።"

"ሰውዬው እንኳን ባለጌ ነው። ስንት ሰራተኛ እያባለገና እያስረገዘ አባሯል። እሱ እንኳን ቢያጋጥመው የሚምር አይመስለኝም። ይሄን አታውቂምና ነው? የተረገዘው የእሱ ነው ወይስ የሌላ ነው ጥያቄው።"

"ምን እኔ ወሬ የት ይደርሰኛል።"

"በይ አትዋሺኝ። አሁን ዋሸሽ።"

"እኔስ እሺ። እንግዳን እንዲህ የምትላከፈው ለምንድነው? አንድ ነገር ቢያደርጋትስ? ይሄ የምትሰበስበው ጉሬዛ ሕጉ-ወጥ ነው ብሎ እንጀራዋን ቢዘጋውስ። አለአቅሟ አፏን የምትከፍተው።"

"የትም አትደርስ። ልጅቷን ለመሆኑ አይተሻታል?"

"ከሳምንት በፊት እንግዳ ቤት ሄጄ ነበር።"

"ደርሳለች?"

"የሚታይ ነገር የለም። አምሮባታል። እሱ ቤት ጥሩ ብትበላ እኮኳ ይራገፍላታል አልኩ እንጂ ለእኔ ራስ ምታት ትሆንብኛለች ብዬም አላሰብኩ።"

"ልጅቷ ዕድሜዋ ስንት ይሆናል?"

"አይ አንተ። እሷስ ደርሳለች። ማርገዟ ዕውነት ከሆነም ፈልጋ ነው። ቀልቃላ። የቀልቃላ ልጅ። ያለአቅሟ ተንጠራርታ ነው። ሒሳቧን ስታገኝ ደነገጠች እንጂ።"



@BOOKALEM

"የሆነውን አናውቅም:: ካሣ ገንዘብ ፈልጋ ቢሆን ነው እናቷ:: ለሌላ መሰለኝ:: ራት አምጭልኝ ርቦኛል:: እንርሳው::"

"እዚያ ሻይ ቤቱ ጎን ቆዳ ንግዷን ረስታ እኮ ነው ከጎረምሳ ጋር ስታሽቃብጥ የምትውለው"

ከመሃል እህቴ ስትገባ ሰማሁ::

እእ:–"የት ጠፋሽ ስፈልግሽ? ይሄ በየሰፈሩ መዞር ምን ለመፍጠር ነው? ለመሆኑ ጭቃው አዞረሽ:: እይማ ጫማዋን::"

የእህቴ ኮቴ አልፎአቸው ወደ ማድቤት ዘለቀ::

"በይ ነገ ሄደሽ ሁሉን ነገር ጠይቂ" አለ አባቴ::

"ልሄድ ነበር፤ እንደው ምንገድ ላይ ብታጋጥመኝ በስድብ ታዋርደኛለች ብዬ ነው:: ዕብድና ዘመናይ......::"

"ዕብድና ዘመናይ" አለ አባቴ አባባሏን እየደገመ::

"የትም አትደርስ:: ዲቃላ ትልቅ ጉዳይ ሆኖ ነው? ቢመረመር ስንት ዲቃላ አለ በየቤቱ:: ውስጡን ለቄስ አሉ:: "

"ሰማሽ እመቤት! ራት አቅርቢ" አለች እእ::

"ነገ በጠዋት እንግዳ ከቤቱ ሳይወጣ ድረሺበትና አጫውቺው" አለ አባቴ::

"እማዬ ጭልፋው የት አለ? "

"ደሞ ጭልፋው ጠፋሽ:: ከእንስራው ሁዋላ ወድቆ ይሆናል"

ምን ያደርጋል ጭልፋ ከእንስራ ጀርባ?

አልጋዬ ላይ ወጣሁ:: በወዲያ በኩል ከበሩ ጎን ያለው ግድግዳ ላይ ከጭቃ የተሰራች መቅረዝ ነበረች:: እፍኟ ውስጥ ኩራዝ እንደ ወዳጇ አቅፋ ይዛ......የኩራዟ ቀንጮ እንደ ጥቁር ምላስ ተጎልጉሎ......በምላሱ አቅጣጫ እስከግድግዳው አጋማሽ የጥላሸት ሰንበር ያለማፈር ቆሞ......ቅርፅ የጠር:: እሱ ላይ ሳፈጥ እንቅልፍ ሸለብ አደረገኝ:: ደክሞኛል:: የምሽቱ ቅዝቃዜ ተሻርኮ ከቦኛል:: በሆዴ ተገልብጬ ተኛሁ:: የካሊሚ አመድማ ጠረን እንደወዳጇ ቀርቦኛል:: ከውጭ ኮቴ እሰማ ነበር:: ሁልጊዜም እሰማ ነበር......የማን እንደሆነ የማላውቀው ድፍ ድፍ ድፍ ተፍ ተፍ ተፍ ወይ ግም ግም ግም እንደ ሕልም:: ያን ማታ ግን አቶ እንግዳ እንደሆኑ አወቅሁ:: ኮቴያቸውን ተከትሎ የሰማሁት የእሳቸውን ንግግር ነበር:: ድምፃቸው ድንክ ሰው



@BOOKALEM

ይመስላል:: *ስለምን ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ያወራሉ?* እላለሁ:: ለመነሳት እስባለሁ:: ሰመመኔ ጣፋጭ ነበር:: ዕንቅልፍ አባብሎ ሊወስደኝ ሲል......አፌ ውስጥ ልሸሸው የማልፈልግ ስኳር አለ:: ቀን ባጋጠመኝ ነገር በውስጤ ፈገግ እላለሁ:: ሁሉም ጉድ አለው እላለሁ:: ሁሉ ዝንጀሮ ከአቅሙ በላይ ዛፍ ላይ የወጣ ዕለት ቀና ብሎ የማየው የነደደ ሬብ መዓት እላለሁ::

የጎረቤታችን ሴትዮ ውሻ ታላዝናለች::

ስባንን ጠዋት ነበር::

ጠዋት:: ልክ እንደዚህ::

ደፋ ብዬ ቀና ስል ጠዋት::

ዳመናው ያጋተ......ረሃቤም ከባድ ነበር::

*(ይሄ ምዕራፍ በ1984 ዓም የተጨመረ ነው)*



@BOOKALEM

# "ስስኪ ስታደፈርሺብኝ"

አንድ ሰው ሰልካካ አፍንጫ ስለሌለው መጥላት ጥሩ ነው? አንዲት ሴት ፀጉሯ ዞማ ስላልሆነ ብንጠላትና ብናንቋሽሻት እግዜር ይወደዋል? አንድን ሰው አንካሳ ነው በማለት ከእኛ ልናርቀው ይገባናል? እኔ አይመስለኝም:: ለእኔ አፍንጫ ደፍጣጣ ባይ፣ ፀጉር ቁጭራ ባይ፣ አንካሳ ቢያጋጥመኝ ግድ አይሰጠኝም:: ምክንያቱም የራሳቸው ጉዳይ ነው:: ደፍጣጣነቱ አይጋባብኝ፣ ቁጭራነቷ አይጋባብኝ፣ አንካሳነቱ አይጋባብኝ::

ወይስ ይጋባል?

ግን አንዳንድ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ለማሳደድ ሲፈልጉ በመጀመሪያ ምክንያት መፍጠር አለባቸው:: አለበለዚያ ቅዱስ መፅሐፍ ጠቅሶ "ምነው እናንተዬ እግዜር ወይም አላህ ይኼን ነገር ይወደዋል?......ምን አደረጋችሁ?" የሚል ይመጣ ይሆናል:: ስለዚህ ጠቃሚ ሰበብ ቀድሞ መፈጠር አለበት:: ቢቻል ሰበቡን በጣም ቀደም አድርጐ ማውራትና በተከታይ ተወዳጅ ማድረግ ያስፈልጋል:: ተቺ ለማላመድ:: የሚቀናቀን ለመቀነስ::

እእ ስትቀጣኝ በሁለት ዐይነት የአመታት ስልቶች ነበር:: ጠርታኝ ተጠንቅቃ የምትመታኝና፣ ሳልጠነቀቅ የምትመታኝ:: ጠርታኝ ስትመታኝ በጥፊ ነው:: በቀኝ እጇ ግራ ጆሮዬ ላይ:: በእሷ ጥፊ ሰበብ መሰለኝ ይኼ ግራ ጆሮዬ ከቀኝ ጆሮዬ ይልቅ ማርያምን ከርፈፍ ያለ ነው:: አስጠንቅቃ ስትመታኝ ግን በኩርኩም ነው:: ኩርኩሟ እንደመድፍ ነው:: 'ኀጭ' ስታደርገኝ የበላሁት ቆሎ ሆድ እቃዬ ውስጥ እንደ ጽናጽል ይንሿሿል::

እኔን የመምታት ወስፋት ማን እንደሰጣት፣ ከየት እንዳገኘችው እስከዛሬ አላውቅም:: ሳያት እርበደበድ ነበር:: ሥራዬ ከእሷ መራቅ ብቻ አልነበረም:: ከእሷ የሚያገናኙኝ ነገር የሚከሰውን ከመሰለኝ የመፍጠር ችሎታዬ መሸሺያ ይፈለስማል:: ከእሷ የሚያገናኙኝ የማላመልጠው አጋጣሚ ከተፈጠረ ደሞ የምሰራው ነገር ውስጥ ሁልጊዜ ስህተት አይጠፋም:: ታዲያ ጉብታዬ ላይ መዋል ስለጀመርኩ እኔን የምታገኝበት ምንገድ ጠፋት:: ሥራዬ መሰወር ሆነ:: ሙሉቀን ጠፍቼ ማታ እመጣለሁ:: ዕድሜ ለመልዕልቴ ገዳም::

ብዙ ጊዜ ግን ሰው ሳይሆን በዳዩ እግዜር ሳይሆን አይቀርም::

አፍንጫ ፎናና ይፈጥራል፣ ፀጉሬ ከርዳዳ ይፈጥራል፣ የሰው እግር ይቆርጣል:: ካላጣው አፍንጫ፣ ካላጣው ፀጉር፣ ካልጠፋ እግር:: በዓለም ላይ ከሚሰሩ ወንጀሎች አብዛኛውን በእግዚአብሔር ማመካኘት ይቻላል::



@BOOKALEM

በሽታ ነበረብኝ:: ለእኔ በሽታ ነው የምለው:: ይኼ በሽታ ሌሊት ከአልጋዬ ተነስቼ በዕንቅልፌ ልቤ የመዞር ነው:: እግዜር እንደፈጠረኝ እራቁቴን ከአልጋዬ እነሳና ከቤት እወጣለሁ:: የግቢያችን አጥር በር መቀርቀሪያው ለቁመቴ ስለሚረዝምብኝ ወደ ውጭ መውጣት አልችልም ነበር:: ስለዚህ ግቢው ውስጥ እንከራተት እንከራተትና ተመልሼ ገብቼ እተኛለሁ:: ተመልሼ ስተኛ ደ'ሞ ያጋጠመኝ ቦታ ነበር:: ቤቱ ፊት ለፊት፣ ሣር ውስጥ፣ ወንበር ላይ፣ ማድቤት መሐል፣ ወዘተርፈ::

በዕንቅልፍ ልቤ መጓዜ የታወቀው አንድ ቀን ማታ አባቴና እንጀራ እናቴ አምሽተው ሲያወሩ በመሐላቸው እንደዋናተኛ ራቁቴን ስጓዝ አይተውኝ ነው:: ያን ዕለት ምናልባት ሁለቱም ተደናግጠው ይሆናል (ይሔ ግምት እንጂ ከፉንታቸውን አበዛዛባቸው እንዳልባል በይሉኝታ ያሰብኩት ይሆናል):: ሁለት ቀኖች ያህል ወደ ቤት ጐትተው እንዳስገቡኝ ትዝ ይለኛል:: ብዙ ጊዜ የምነቃው ግን የተከፈተ በር ስር ተኝቼ ነበር......እንደ ውሻ::

(እንካ ሰላንታ)

በመደሻ

(ልጅም አለኝ የማይጦረኝ የማይሆነኝ መሸሻ

መዝገቡ የሚባል ደንቃራ የሚሰራው እንደ ውሻ:: ......**አባቴ ዱባለ**)

(እንካ ሰላንታ)

በእፍታ

(እናት አምጣ ብትወልድ ደም የመታት ዕለት ማታ

የማያበላኝ፣ የማያጠጣኝ፣ የማያስተምረኝ ወሸከታ ......**ልጅ መዝገቡ**)

ብዙ ጊዜ ከእንቅልፌ እባንን ነበር:: ብዙ ጊዜ ዕንቅፋት ስለሚመታኝ:: ዛሬ ብዙዎቹ የቀኝ እግሬ ጥፍሮች ጠማማ ናቸው::

መጀመሪያ ይኼ ሕመም አለ:: ይኼ ሕመም ደ'ሞ ከሆነ አጋጣሚ ጋር ያሴርና ሲያል ይሆናል:: ሕመሙንም፣ አጋጣሚውንም የሚፈጥረው ያው እግዚአብሔር ነው:: ከእሱ ቂም አለኝ:: እንደ ኢዮብ:: አንድ ቀን በእንቅልፌ ተጉዤ የእህቴ የዕጌሬዳ አትክልት ውስጥ ተቀመጥሁና ብተኛ ደህና፣ ተቀምጬ በተከደኑ ዐይኖቼ ባፈጥ ደህና:: ግን አትክልቱ መሐል ተቀምጬ አበቦቹን እንደ ፍራፍሬ እየቀነጠስኩ መብላት ጀመርኩ:: እየቀነጠስኩም መጣል ጀመርኩ:: ያው አጋጣሚ ሆነና (እግዚአብሔር አይደለ) እህቴ ሽንቷን ልትሸና ትወጣለች:: ከአታክልቶቿ ብዙም ሳትርቅ ቂጥጥ ብላ ስትሸና......



@BOOKALEM

(ወንዙን ከላይ ገደብነው፣
ምንጩንም ወትፈን አቆምነው፣
ዝናቡን በድግምት ሰማይ አስቀረነው፤
የሴቱ ነገር ነው እኛን እምቢ ያለን፣
ተስማምተው ቢሸኑ አጥለቀለቀን።
......የንፋስ መውጫ አዝማሪ )

እኔ እሸት መሐል እንደ ሰፈረ እረኛ ውድ ተከሎቿን ስበጠቡጥ ታያለች። "ብሎ ብሎ እዚህ መጣ" ትልና (ያኔ አልሰማሁዋትም። አሁን ያን ጊዜ ልትናገር የምትችለውን ነገር ስገምት) ሽቅማጥዋን ቆርጣ ጉትታ ታወጣኛለች። ትወዘውዘኝና ትቀሰቅሰኛለች። ማጅራቴን ይዛ ቤት ታስገባኛለች......"አበባዎቼን ብጥስጥስ አድርጎ ጨረሰው" ብላ ትጮሃለች። (ይሔን ስትናገር ሰምቻታለሁ)

ሲነጋ ታዲያ እንጀራ እናቴ "ቀን ቀን ያሰበውን ነገር እኮ ነው የሚሰራው። ዕውነት እኮ ነው። በሕልም ታዲያ ምን ብሎ ይመጣል እንዲህ እንዲህ ዐይነት ነገር። ቢቀናባት ነው በልጇ። ምን የተለየ አግኝታ ነው እሷ......አባታቸው አንዱን አብልጦ አንዱን አያሳንስ፣ እኔም እንዲሁ......" አለች።

የዕውነት ግን የአበባ ቦታዋ ብዙም አልተጐዳም። እህቴ ግን ነገሩን ረሳችው። አሁን ስገምት ከአበባዋ ይልቅ አጠገቤ መጥታ ስትሸና ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እያየሁዋት ዝም ማለቴ አበሳጭቷት ይሆናል። (ያየሁዋት መስሏት። በሁዋላ በሁዋላ የረሳችውም በዕንቅልፉ የሚሄዝ ሰው ማየት እንደማይችል ተነግሯት ሳይሆን አይቀርም) እንጀራ እናቴ ግን ሰበብ አገኘች። ጅብ በግን በግድ 'እስኪ አታደፍርሺብኝ ያላት ነገር መጣ። ይሔ ተረትና ምሳሌ ማለቴ የጅቧና የበጉ የገባኝ ድሮ ነበር። ተረቱን ሰምተው የክፍሌ ተማሪዎች ሲስቁ ነበር። ስላልኖሩት ስላልገባቸው አይወጋቸው።

ታዲያ እንጀራ እናቴ......ዘረ-ቀላጥቤ ይሄን የአበባ ነገር በተገኘው አጋጣሚ ታነሳው ነበር። በዐል ሲኖርና ቢጋው በዝቶ ውርጩ ሰፍቶ ውሃ አጥሮ እንቡጥ አላኮረኩር ብሎ አበባ ካጣች: "ምን አበባ አለና ተጨፍጭፎ!" ትላለች። እኔ ታዲያ ቶሎ መሸሽ። ኩርኩሟ እንደላውንቸር ሳይወረወርብኝ።

"ቢወቀጥስ እሱ። ሰው ነው!? አበባ የማይምር"

"እሱ ልጂ ልቡም አይታወቅ። ቅናቱ። አይጣል ቅናቱ"



@BOOKALEM

ከምንም ነገር ተነስታ ርዕዮተ–ዓለሟን ፈጠረች። ቀድሞ ጥላቻ ቢኖራትም እጅ ከፍንጅ መወንጀያ ምክንያት አልነበራትም። አሁን ተረጋጋች። ኩርኩሟ ባለፉጨት፣ ጥፊዋ ባለንፋስ ሆነ። ቆሎዬም ይንሿሿል። ጆሮዬም ይሰፋል።



@BOOKALEM

# እሬ!!

የወሰን ነገር ይገርመኛል......ሁልጊዜም ይገርመኝ ነበር......

ልጅ እያለሁ ያንድን ሰው ነፍስ አንድ ሰው ብቻ ሊያጠፋት የሚችል አይመስለኝም ነበር። ይህ፣ ነፍስ የምትባል ነገር እንደ አየር ሳይሆን እንደ አቧራ እየመሰለችኝ። እንደ አቧራ፣ እንደ ዱቄት፣ እንደ አመድ። ታዲያ አንድ ሰው እንዲሞት ለማድረግ ከገላው የሚወጡት ያቧራ ቅንጣቶች ሁሉ መጥፋት ያለባቸው ይመስለኝ ነበር......ቀስ በቀስ።

ግን ነፍስ......እግዜር የፈረደባት ነፍስ በእሪታ ትድናለች?

ነፍሴ እንደ አቧራ ቦና ከማለቋ በፊት በእሪታ ብከልላት?......

ማታ በካሊማ ተጠቅልዬ......ያልታጠቡ ቆሻሻ እንደ ቆዳ የለበሱ እግሮቼን ሳክ ወሰን አንድ ቀን የተናገረችኝ ነገር ትዝ ብሎኝ ገረመኝ። ጩኸቷ ሰው እንደሚጠራ ተማምና የሚመጣውም ሰው እንደሚረዳት ገብቷት "ዞር ካላልክ እጮሃለሁ" ያለችኝ። በጣም ብልጥ ናት......እንዲህ እንደሚቻል አላውቅም ነበር። እኔ ጮኼ አላውቅማ። እንጀራ እናቴ እንደ ከበሮ ስትጠልዘኝ የመጣ አልነበረም። ስላልጮህኩ ይሆናል። እየተደበደብኩ እኮራለሁ። ወሰንም ልጅ እኔም ልጅ ምናልባት ቀኑም ይሆናል። እንጀራ እናቴ ለምሳሌ የምትመታኝ አባቴ በሌለበት ቀን ነበር (አባቴን ፈርታ ሳይሆን ድርሻዋን ነጠል አድርጋ ልትዝናናብኝ ይሆናል እንጂ)። ብዙ ጊዜ ሐሙስና ቅዳሜ። ሐሙስና ቅዳሜ ገበያ ነው። ወሰን ይሔ ገብቷት ይሆናል። ያ ዕለት ሐሙስ ነበር።

ተስፋዋስ? ብትጮህ እንደሚደርስላት ተስፋዋ። መስኮቱን ከፈትኩና ወደ ውጪ አየሁ። እንደ ሕፃን የምታምር ጨረቃ ጥቁር ሰማይ ላይ ትንሳፈፋለች። ኩንስንስ ጅብታ ነበር። ጢንዚዛ ሲተነፍስ መስማት ይቻላል። ጉሮሮዬን አፀዳሁና አንድ ጊዜ ለፍተሻ አምርሬ 'እሪ!' አልኩ።

በእኔ ዕድሜ ቀላል ድምፅ ቀላል ጩኸት አልነበረም። አሥር የወሰን ጉሮሮዎች፣ 2000 የወሰን ምላሶች፣ 1000 የወሰን እንጥሎች፣ ያለፍላጎቷ የምትሰረር አንበሳ ተደምረው ሊያወጡት ከሚችሉት ዐይነት ድምፅ በላይ ነበር። ቀይ እሪታ። ዐይኖቼን ስጨፍን ያወጣሁት፣ ከጉሮሮዬ የወለድኩት ዕራት የከሰል ፍም የመሰለ ቀለም ያለው መሰለኝ። እርግጠኛም ነበርኩ የብዙ እንቅልፋሞች ጆሮ አቃጥሎ እንደሚቀሰቅስ። ለብቻዬ ሳቅሁ። አባቴ ሲስል ሰማሁት። በቃ። ፀጥታው የውጪም የቤቱ አልተረበሸም።



@BOOKALEM

የጠየቀ፣ የመጣ አልነበረም። ጩኸቴን 'እሪታዬን' ሰው ቢሰማውም ባይሰማውም ቢያንስ መጮህ ችዬአለሁ አልኩ። እንግዳ የእርካታ ስሜት ተሰማኝ።

በዕርዳታ ተስፋው ሳይሆን በጥሬ አካላዊ ድርጊቴ።



@BOOKALEM

# አረንጓዴ ቢጫ፣ አረንጓዴ ቢጫ

ጉብታዬ ላይ ስሆን ወደቀኝ በስተደቡብ በስተግራዬ በስተሰሜን ተራሮች አሉ። የእነዚህ ተራሮች ሥራ ሁለት ዐይነት ነበር። ከጉብታዬ ሆኜ ሳይ ነው እንግዲህ። ክረምት ክረምት አረንጓዴ......በጋ በጋ ቢጫ ይሆናሉ። ያንን የሚያካክሉ ተራሮች ከዚህ የበለጠ አይሆኑም? እነዚህ ሁለቱ አፋፍ ላይ ተዘርግተው የማያቸው ቀለሞች ይሆናሉ። ምናልባት ቀያቴው ሸጥ ውስጥ ነው። መተንፈስ ያቃተው። ምናልባት ቀይ ቀዩ እኔ የማሳድበት ገደል ስር ይሆናል። ግን ያን የሚያካክሉ ተራሮች፣ ልብ የሚሰልቡ ገመገሞች ከዚህ የበለጠ አይሆኑም?



@BOOKALEM

# የቤቢቱ ትንፋሽ

ከጉና ተራራ የሚመጣው ንፋስ የአወራረዱ ቅጥ ይሁን ወይ በዚያ ሰዓት የአየር ፀባይ ለውጥ ተፈጥሮ እዚያች ከተማ ውስጥ በብዙ ሰዎች የሚከበር የሌሊት ድምፅ ነበር:: ወሩ ደግሞ አሁን ትዝ አይለኝም እንጂ ስገምት ከእንቁጣጣሽ በሁዋላ ቢሆን ነው:: መስከረም ሲያልቅ ጥቅምት ወር ሲጀምር ሊሆን ይችላል:: ሐይለኛ ንፋስ ይመጣና የከተማዋን ቤቶች ጣሪያ ይነቀንቃል:: ስለ ሌሎች ቤቶች ግን ሌሎች ሲያወሩ ነው የሰማሁት:: የእኛን ቤት ግን ለአጭር ጊዜ (አምስት ሰከንዶች......በግምት) ይሄ ንፋስ ይመታትና ከስሯ ትነቃነቃለች:: በደካማ የባሕር ዛፍ ወራጅ እንጨቶችና በቆርቆሮ የተሰራው ጣሪያዋ ተገልቦ የሔደ ይመስላል:: ከዚያ ለአፍታ ፀጥታ ይሆንና የመጀመሪያው ፍርሀት ሳይለቀን 'እእእፍፍፍ' የሚል ከደከመ ሰው አፍ የሚወጣ ትንፋሽና ድምፅ በከተማዋ ገላ ውስጥ ያልፋል:: ይሔ በዓመት በዓመት ለአንድ ቀን ሌሊት ብቻ ስለሚመጣ በበኋታው ጠዋት ከተማዋ ስለዚህ የተለመደ ጉድ ስታወራ ታረፍዳለች:: ይሔ ድምፅ ታዲያ ስሙ 'የገብሩ ትንፋሽ' ይባላል::

ገብሩ እራሳቸውን ደጃዝማች ያደረጉ የጣሊያን ጊዜ አርበኛ ነበሩ:: ንጉሥ ተፈሪን ይረብሻሉ ስለሚባል ሰው ይወዳቸው ነበር:: ጣሊያን ሊወጣ ሲል ውጊያ ላይ ከፉኛ ይቆስሉና በዚህም መነሻ ታመው ብዙ ዘመን ቤታቸው ወንበር ላይ ተቀምጠው ከጉና ተራራ ወደታች ወደ ንፋስ መውጫ የተዋጉበትንና የተዋጉለትን አገር ሲያዩ ይውሉ ነበር:: እንዲህ ታመው እንኳዋን ነገራቸው መሬት አይወድቅም እየተባሉ ማንም ይፈራቸዋል:: እስኪሞቱ ንጉሡ ላይ ሲዝቱ ነበር አሉ "ንጋሽ እኔ ነኝ" አሉ ሲል ከፈሉ ሰው፡ በመጣሁበት እግርህ ካልወረድክዘ መጣውልህ ብለዋል ይላል ከፊሉ፡ ከፊሉ ሌላም አይደለ ይሄ ጉደኛ ተፈሪ ነበር የሚሉት ይላል):: ሐይለሥላሴ ያን ጊዜ ምን እንደሚሰማቸው አላውቅም እንጂ እኛ ከተማ ውስጥ በዚህ አባባላቸውና ምኞታቸው ደጃዝማች ገብሩ የተከበሩና የተፈሩ ነበሩ:: ይቀናባቸዋልም:: ታዲያ ሲሞቱ 'ሥጋዬ ቢያልፍ ትንፋሼ አያልፍም' ብለዋል ይላሉ:: እና ሲሞቱ ከአፋቸው ጠረኑ አንዳንዴ እጋም እጋም፣ አንዳንዴ ቀጋ ቀጋ አንዳንዴ ዘቢብ ዘቢብ የሚል ሰፎይታ ወጣ ይባላል:: እንደሚወራው እንደሚባለው ያ 'ሰፎይታ' ጉና ተራራ ላይ እያንገበበ ይከርምና መስከረም መጨረሻ ወይም ጥቅምት መግቢያ ላይ ወደ ከተማዋ ይነፍሳል:: የኔ ቤታችን ይንቀጠቀጣል......ሲነጋ ወሬ ይወራል:: በረቀቀ፣ እንደ እኔ ዐይነት ተራ ልጆች ሊቀርቡን በማይከብደን መልክ የሚቀኑም ትልልቅ ሰዎች ነበሩ:: የጉና ደገኞች ሰፎይታውን ወደ እናንተ ሲመጣ አይተነዋል ይላሉ 'እንደ ትልቅ የጭስ ፋኒላን':: 'ሰፎይታ' መታየቱን እንጃ እንጂ እፎይታው ነጭ እንሽልፋ ጉም መስሎ ከተራራዋ ተነስቶ እንደሚበር አከንባሉ ሆኖ



@BOOKALEM

ወደ ከተማዋ ይወርድና ነፋስ መውጫ ላይ ይከደናል ይላሉ የጉና ሰዎች። ታዲያ የእኛ ከተማ እኩያዎቻቸውን በመቀለድ "ተጋግራችሁ አደራችሁ?" ይሉዋቸዋል–የሚቀጥለው ዕለት ዝበያ ሆኖ ከተገናኙ።

ዘፈንም አላቸው የአዝማቹ ግጥም ሁለቱ ስንኞች እንዲህ የሚሉ፡

*"ነፋስ መውጫ ቂጣው ነጣ ነጣ አለብኝ*
*ገብሩ አስከንባሉ ሰለቸው መሰለኝ"*

ለምሳሌ ፀጉር አስተካካዩ አባቴ ይበሳጭ ነበር። "አንድ ሽባ ሰው ይሄን ሁሉ ጉድ አንበጠበጡት" ይላል። 'አንበጠበጡት'. ምን ማለት እንደሆነ አይገባኝም። 'አስፈሩት' ማለቱ ነበር? ሊሆን ይችላል። አያገባኝም። አባቴ "አበሳጨኝ" እንጂ "አስፈራኝ" ሲል አልሰማሁትም። እሱማ ከኔ በስተቀር ሌላ ሰው ይሔን የገብሩ ንፋስ የሚፈራ ያለ አይመስለኝም ነበር። አባቴ ጦርነት ቀምነገር እንዳልሆነ ነጋ ጠባ ያወራል። "ከሁሉ የበለጠ ቁም ነገር 'ሥራ' ነው" ይላል። የእሱ ቁም ነገር ከጦርነት እንደሚበልጥ ያወራል። ጦርነት ሰው እንደሚገድል ሰው እንደሚያጠፋ ሥራ ግን ለሰውና ለሰውነቱ ጥሩ እንደሆነ ያወራል። በገብሩ ግን ይቀናል። እኔ እንደሚመስለኝ እሱ ጦርነት የሚፈራው እንዳለው ሰው ስለሚገል ነው......ሰዎች ደ'ሞ ሲሞቱ ጭንቅላታቸውና የጭንቅላት ፀጉራቸው አብሮ ይቀበራል። ፀጉር ከተቀበረ ደሞ የሚስተካከል ሰው አይኖርም። የሚያበሳጨው ይሄ ይመስለኝ ነበር። አንዳንዴ ሳስበውማ ሳንቲም የሞላ የሻማ ካርቱን እያንቿቿ ወደ መንግሥት ሔዶ "ሰው ግደሉ ግን ፀጉራም ፀጉራሞቹን ለእኔ ስትሉ ተውአቸው......አደራ" ብሎ የሚደራደር ይመስለኛል።

የሚገርመኝ የቅናቱ ነገር ነበር። አንዳንዴም አተኩሬ ሳስብ እንደውም አባቴ ልክ እንደ ገብሩ ደፋር ሆኖ የሰውን ልጅ ከላይ እስከ ታች ማስፈራራት፣ በጦርና በጉም ማንቀጥቀጥ ቢችል የሚወድ ይመስለኛል። ብዙ 'ትላልቅ' የተባሉት ወንዶች የሚቀኑትም በዚህ ይመስለኝ ነበር። ገብሩ ተንፍሰው ያደሩ ዕለት በበነጋታው ብዙዎች ተበሳጭተው አያቸዋለሁ፣ ወዲያ ወዲህ እያሉም እንዲህ ይላሉ፡...... "እንደው የእኛ ሰው አይገርምም? ጉም......ሽረ እንደው ይኼ ጉም ምኑ ያን የዞረበት ሽባ ይመስላል? ሰው ጠፋና" ሲሉ እሰማቸው ነበር።

ሲመስለኝ የገብሩን ትንፋሽ አባቴ የሚጠላው ስለሚፈራው ነበር። የሚፈራው የገብሩን ሥራ ስለሚያውቅ ነው። የሚያውቀው ደ'ሞ ፈሪ ስለሆነ ነው። የራስን አባት 'ፈሪ' ማለት ጥሩ አይደለም ይባላል። ምን አለበት ግን ያሳፍራል እንዴ? ክርስቶስ ከመስቀሉ በፊት ፍርሃት ነበረበት ይባል የለ። ጌቴሴማኒ እኮ የተንቀጥቃጮች ቦታ ነው።

"ኡፍፍፍፍፍፍ" እኔ ብልስ?



@BOOKALEM

ለማንቀጥቀጥ ብመኝ ኖሮ።

ብመኝ ኖሮ።

ብመኝ።

# ዘቢብ

በሕይወቴ ሌላው ይቅርና በበዐል ቀን እንኳን እናትና አባቴ ጠርተውኝ ከረሜላና ሸንኮራ ግዛ ብለው ሣንቲም የሰጡኝ ጊዜ አልነበረም። አባቴ 'እናትህ ትስጥህ' ይላል። እንጀራ እናቴ 'አባትህ ይስጥህ' ትላለች። ከመሐል በላተኛ እየየሁ ዝም ነው። ከረሜላና ብስኩት ቀረ ብዬ አላከርፍም። እዚያች ከተማ የሚሸጡትን ከረሜላና ብስኩት ወድጄአቸው አላውቅም። ከናናዬ በስተቀር። ብስኩቱን ስበላው ከረሜላውን የበላሁ ይመስለኛል......ከረሜላውን ስበላው ብስኩቱን የበላሁ ይመስለኛል። ብስኩቶቹ እርስ በራሳቸው መመሳሰል ብቻ ሳይሆን የዚር ጉድባ ዘለው ከከረሜላዎች ጋር ይሻረካሉ። ታዲያ ናና ያሰኘኝ ሰለት አባቴ ሱቅ ፀጉር መቁረጫው ቦታ እሔድና ግድ የለሽ የሆነበትን ጊዜ እጠብቃለሁ። በእሱና ገንዘብ በሚያስቀምጥበት ጠረጴዛ መሐል ያለውን ዕርቀትና የቸልታውን ጥልቀት አይቼ አሥር ሣንቲም ሰርቄ እወጣለሁ። ሁል ጊዜ አሥር ሣንቲም ነው። እሱ መኸገር አይደል ይህቺም እንደጠፋች ያውቃል። ማን እንደወሰደበት ማወቅ መቻሉን ግን እንጃ። ፀጉር መቁረጫው መስታወቱ አጠገብ በስተቀኝ ሁልጊዜ ሥራ ሲጀምር ነጭ ወረቀት ይሰቅላል። ታዲያ ፀጉር ቆርጦ በጨረሰ ቁጥር ምልክት ያደርጋል። '/' የዚህ ዐይነት ምልክት አንድ ሰው ተቆረጠ ማለት ነው። '0' ማለት ደሞ አንድ ሰው ተቆርጧል ግን አልከፈለም ዱቤ ነው ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ሳንቲሙን የሚያስቀምጠው ጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ ነበር። አንዳንዴ መሳቢያ መጎተትና መግፋት ሲደክመው ወይም ሲሰለቸው (የትኛው እንደሆነ ጠይቄው አላውቅም እሱም ሲናገር አልሰማሁትም) እኪሱ ያስገባል።

ቤተሰቦቼን አንደ 'ልጅ' አስቸግሬ አላውቅም። (በላሁትም አልበላሁትም ነፍስና ስጋዬን የትም እንደማያደርሳቸው ገብቶኝ ይሆናል) እንግዲህ ሱሪዬ ለምሳሌ ቂጡ ተቀዶ መቀመጫዬ መታየት ከጀመረ ረጅም ጊዜው ነው ልበል። እና ከሰሩ እስር እሮጌ ቁምጣዎቼን ደራርቤ ደራርቤ ባደርጋቸውም ያው በተመሳሳይ መልክ ስለተቀደዱ መራቆቴን አይጋርዱልኝም። እኔ ደሞ አልናገርም። ዐይናቸው ስር ወዲያ ወዲህ ስል አመዳም ቡናማ ቂጤን እንደ ሲኒማ ያዩት አልነበረም? አንዳንዴ (አንዳንድ ጊዜ) ጉብታው ላይ ተቀምጬ ስነሳ የቂጤን ሲጋና የቂጤን አጥንት በነርስ መርፌ ስጠቀጠቅ እንደዋልኩ ሁሉ ያመኛል። ምናልባት ከዕለታት አንድ ቀን ቆዳዬ እንደ ቃጫ ጆንያ ተቀዶ አጥንቴ፣ ሥጋና ደሜ እንደ ቁሳቁስ ወደ ውጭ ይዘረገፉ ይሆናል እያልኩ እፈራ ነበር።

አንድ ዕለት የዓመቱ ማሪያም ሆና ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ሰዎች በዓልዋን ሊያከብሩ ነፋስ መውጫ ከተማ ውስጥ ተሰብስበው ነበር። ሰው ከላይ እስከ ታች ጢም ነበር ያለው—መኪቃንቂያ እስኪቸግረን። እኔ ጉብታዬ ላይ ነኝ። ብቻዬን እንኳን ሳልሆን፣ የቦታው



@BOOKALEM

ከፍታ ቁመት ስለሚጨምር የጂሙን ትርምስ ለማየት የፈለጉ (የሚዘፍኑትን፣ የሚጠጡትን ለማየት......በቅሰል ስማቸው "ድድ" የተባሉ—"ድፍድፍ ድፉ" እንደማለት፣ የደረሱ ልጃገረዶችን ቂጥና ጡት በዐይኖቻቸው ለመመዘን፣ የማይፈልጉትን ሰው ላለማግኘት ጠዝተ......) ሌሎችም ሰዎች እዚያ አብረውኝ ተገትረዋል:: በየቦታው አጠገቤ አፍንጫዬም ስር እንደ ማንቆላለጥ እየደረጉ ግንድ የሚያክል ሸንኮራ እየላጡ የሚበሉ ምላሳቸውን የሚመጡ ነበሩ:: ለመብላት እሻፍዳለሁ:: አንዳንዱ ሕፃን ፊቱን ወደ እኔ አዙሮ የለሐፈጩ ፍንጣሪ ፊቴን እስኪመታኝ ድረስ አፉን ከፍቶ ያላምጣል:: ቀዝቀዝ ብዬ አየዋለሁ:: ያልጎመጀ መሰዬ:: አንዳንዱ ሊያስጎመጅ ይበላል:: ዐይኖቻችን እስኪደክሙ እንተያያለን:: እኔ እንዳልጐመጀሁ ላረጋግጥ አፌን ገጥሜ በትዝብት እንደሚመለከት:: በዚህም ሁኔታዬ ያሸነፍኩት ጉብል ካለ ይበሽቅና ጓደኛውን ጐሽሞ ወደ እኔ ያሳየዋል:: ያሳየውና: "እንዴት ይቀላውጣል በማርያም!"-......ማረጋገጫ ሲያጡ ሊፈታተኑኝ ከያዙት ለሐጫቸውን ነስነሱት ሸንኮራ ብጣሽ እንዱን ይጋብዙኛል:: እንደ ፕሬዝዳንት፣ እንደ ትልቅ ሰው ጭንቅላቴን ግራና ቀኝ በቀስታ በጣም በቀስታ በአሉታ እነቀንቃለሁ:: ከአጠገቤ ይጠፋሉ:: ምናልባት በእኔ መረጋጋት ተረብሸው ሸንኮራ መብላታቸው ያስጠላቸው ይሆናል እያልኩ እጠረጥር ነበር:: *እንዲህ የናቀውን እንዴት እኛ ልባችን እስኪጠፋ እንብላው?*

ቅድም እንዳልኩት እግዚያብሔር ሰውን ያለ አጋር አልፈጠረውም:: ያን ቀን ሳነጋግረው ያልፈለኩት ልጅ አጠገቤ አለ:: ከአለባበሱ ከሁኔታው እንደ እኔ የግዱን ደሐ የመሰለ:: እዚያ ዐውድ ላይ አይቸው አላውቅም:: ምናልባት የልብሱን ቀዳዳ፣ ኩቱ እጅጌታ ላይ የተለጠፈውን የንፍጥ ዳጥ ሰዎች እንዳያዩበት አፍር ይሆናል እዚያ ለመደበቅ የመጣው:: ጉብታ ላይ ያሉ ሰዎች ብዙ ጊዜ አጠገባቸው ያለውን አካባቢ አያዩም:: ወደ ሌላው ነው......ወደ ወዲያ......ቢኖሩም እንኳን......የቆሙበትን አካባቢ የሚመለከቱ ዐይኖች ብዛት ጥቂት ነው:: ልጁ መሬት ይቆረቁራል:: እዚህም እዚያም አያይም:: መሬት የሚቆረቁረው አፈር የሚጐለጉለው በዳንቴል መሥሪያ ሽቦ ነው:: ሽቦው መሬት ውስጥ እስከ ወገቡ ሰምጦ ይቸገና ይመለሳል:: የልጁ ጥንካሬ ገረመኝ:: ወይም ተናዶ ነበር::

"ዘቢብ ትወዳለህ?" አለኝ በድንገት::

እዛኝነት ያለበት ይመስላል ድምፁ:: ሰድሜው ከእሥር ሳይበልጥ አይቀርም::

"ምነው?" አልኩት::

"በዚህ ዓመት ዘቢብ ተወደደ:: ባለፈው ዓመት በመለኪያ ሁለት ነበር:: በአሥር ሳንቲም አሁን አንድ ብቻ ነው::"

አልገባኝም:: ስገምት ሳንቲም ኖሮት እንደሚገዛ ግን ዝቢያው ስለተወደደበት የተበሳጨ ይመስል ነበር::

"አምስት ሳንቲም አለህ?" አለኝ እንደገና።

በአሉታ ራሴን ነቀነቅሁ። አምስት ሳንቲም ቢኖረኝ ኡሪ አጋሬ ሆይ ለፓርላማ እወዳደር ነበር አልኩ በልቤ።

ከተቀመጠበት ተነስቶ 'ወደ ታች' ወረደ። ከተማውን ከሁለት የከፈለው ምንገድ ላይ ግራና ቀኝ ጧፍ፣ ዣንጥላ፣ እጣን፣ ዘቢብ፣ ብርቱካን ወዘተርፈ ሻጮች ተደርድረዋል። ብዙዎቹ ሴቶች ናቸው። ከመሐል ያለው ምንገድ በሰው ጉርፍ ጢቅ ብሏል። ልጁ እዚህ ጉርፍ መሐል ገባ። ከአካሄዱ ፍጥነት ወዲያ ጥግ ፀሐይ ጉልት ጉሬዛ ተራ ይዘልቃል መስሎኝ ነበር። ብዙ ሳይቆይ ጩኸት ተጀመረ።

"ሌባ! ሌባ! ያዘው ሌባ!"

በነጬና በግራጫው......የሕዝብ ጉርፍ ውስጥ እግር ያለው ትልቅ የጭቃ ኳስ የሰው እጆች እየሸወደ ሲሮጥ አያለሁ። በመጀመሪያ ራሴ መስሎኝ ነበር። የሯጩ ገላ ከእኔ ገላ ጋር ያለው ተመሳሳይነት። ሳይረፍድ ግን አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው ልጅ መሆኑን አወቅሁ። ከሰው እምልጦ ሲሮጥ ሌሎች ትላልቅ ልጆች እየጮሁ ያባርሩታል። በእጁ የሆነ ነገር ይዟል። በግራ እጁ። ግራ'ጁ አልተዘረጋም ስለዚህ የሆነ ነገር ይዟል። የሚከተሉት ሁለት ልጆች የተዳከሙ ይመስላሉ። ከተቀመጥኩበት ተመድርፌ ተነሳሁና ልጁ ወደ ሚከንፍበት አቅጣጫ ሮጥኩ። ያሯሯጠ አማራጭነት በልጁና በሚያባርሩት ሁለት ሰዎች መሐል አመጣኝ። ቁና ቁና እየተነፈስኩ ቆምኩና አንዱን ሰው "ጋሺ ጋሼ......እኔ ልጁን ይገዬ አመጣዋለሁ" አልኩት።

"የዱባለ ልጅ ነህ አይደለም?"

"አዎ......ይገዬ አመጣዋለሁ" አልኳቸው።

ሰዎቹ አውቀውም ይሁን ተዳክመው ቆሙ። እኔ ልጁ በሮጠበት አቅጣጫ ተከተልኩት። ከተማውን ዘልቆ ወጥቶ ምንገድ ላይ የሰው ሰልፍ የቀጠነበት አካባቢ ወዲያና ወዲህ እያለ አገኘሁት እንደሚሸልል፣ እንደሚያቅራራ። እኔ ስጠጋው አልፈራኝም። ወደ ሁዋላ ተገላምጮ አየሁ። ሰዎቹ አልመጡም።

"ምን ሰረቅህ?" አልኩት።

"ዘቢብ"

ከነመለኪያው ነው የሰረቀው። የቆርቆሮ መለኪያዋን አፍ በመዳፉ አፍኗታል። አሮጌ ቆርቆሮ ነበረች። የዘቢብ መለኪያዎች ሁሉ አሮጌ ቆርቆሮዎች ናቸው። ዘቢብ ሻጭ ሴቶች በሙሉ አሮጊቶች ናቸው። በስተግራችን ከዕለታት አንድ ቀን ዝንብ ተሸክሞ የመጣው ዜንጠኛ ሲገዛ ያየሁበት ቤት ነበር። መስኮት ክፍት ስለነበር ሚስጥራችንን ማውራት



@BOOKALEM

ስላልፈለግን በቀስታ እየተራመድን ከከተማው ራቅን:: የማንተዋወቅም ይመስላል:: ዘቢቡና የዘቢቡ ጣሳ በልጁ እጅ መዳፍ ውስጥ ናቸው:: የልጁ ዐይኖች የማያርፉ ከንፍንፍ ያሉ:: አፋ ዙሪያና ዓይኖቹ ውስጥ ሊጋገር የደረሰ ቀዝቃዛ ሀፍረት በኩቶ ይታያል:: ጠቅላላ ሁኔታው ያሳዝን ነበር::

"ለምን አንበላውም?" አልኩት::

እንደመሳቅ ሞከረ:: ለመናገረ ሞከረ:: አልቻለም::

"ና" አለኝና በጥቅሻ ዛፍ ፈልገን ከስሩ ቁጭ አልን......

እንደ ሁለት ሀብታሞች እግሮቻችንን ዘርግተን:: ቀዝቃዛ ዛፍ ጥላ ስር ቆርቆሮዋን ከመሐላችን አስቀምጠን እየቆነጠርን መብላት ጀመርን:: መቆንጠር እንዴት እንደቻልን ይገርመኛል:: እንዴት እንደሰረቀውም ሊነግረኝ አልፈለገም:: ልጠይቀውም አልፈለኩም:: አቀማመጣችንና ዝምታችን አብረን ያለን አያስመስሉንም:: የልጁ ፊት ላይ ያየሁት ጭንቀት ቀስ በቀስ ጠፋ:: ሰዎች፣ የጭነት መኪናዎች፣ ፈረሶች፣ በቅሎዎች በአጠገባችን ያልፋሉ:: እንደ ሐብታም ነበርን:: በዚያች ሰዓት እንደ እኛ ተዝናንቶ የሚበላ ማነው? ረጋ ብለን እንደ ዲታ......ዘቢብ እያፈረጥን:: አልፎ አልፎ እየተያየን:: ከከተማው መሀል የሚመጣው ታቦት ማስገቢያው እልልታ ለእኛ ሆድ የተሰራ እየመሰለ......

*አላት አላት ዘቢብ*
*አላት አላት ዘቢብ.......*

ይኼን ልጅ ከዚህ በፊት አይቸው አላውቅም::

ከዚያም በሁዋላ አይቸው አላውቅም::

ምን አልባት ቢያገጣጥመን......የሚታወሰኝ ቢኖር የዘቢቡ ነገር ነው::



@BOOKALEM

# ደፍደፍ

ለመወለድ አልለመንኩም:: ማንም ሰው አለመነም:: ብዙ ጊዜ ግን ሰዎች ተለማምጧን ወይም በፈቃደኝነት እዚህች ምድር እንደመጣን አድርገው ያስተናግዱናል::

"ባትወለድስ......." ተብዬአለሁ::

"አንተን የወለደ......." ተብያለሁ::

"አንተን ከመውለድ......." ብለውኝ ነበር ያማጡም ያላማጡም:: አለመወለድን እኔም እነሱም እንደምናቃት ሁሉ:: አለመወለድ አገር የምታወሬር ጥቅም አለች ቢባል እነሱ ተጋፍተው ይሁን ኢታለው ቀድመውኝ እንደማይደርሱ ሁሉ......

መቼም አንድን ሰው ለመጉዳት ወይ ለመቅጣት ሲፈለግ ምቹውና የሚቀለው ነገር ምንድን ነው? ከቅጣቱ በፊትም ይሁን በሁዋላ ሰለባ የሆነው እኔ እንደ ጥፋተኛ በሌሎች እንዲታይ ከተቻለ ደሞ እራሱን እንዲያይ ማድረግ ነው......ቀድሞ ብዬዋለሁ......

አባቴና እንጀራ እናቴ ለእኔ ምግብ፣ ልብስና፣ ትምህርት ከመጨነቅ ይልቅ የሚረብሻቸው ነገር የራሳቸው ትንሽ ምቾት መውገርገር ነበር:: አባቴ ምግብ ሲበላ ውሐ ጠጥቶ አያውቅም:: ጠላ (ሳቅ ሳቅ እያለ "ቅራሪ ቢኖር" ይላል...... "ጠላ" ብሎ ካለ ስካራም እንዳያስብለው) ወይም ጠጅ ("ብርዝ እስኪ ካለሽ" ይላል......ጠጅ ከጠየቀ ያው "ሰካራም" ስለሚያስብለው) ማግኘት ነበረበት:: ታዲያ ብልጥ ሚስቱ ኪሴን ውሃ በሚያዝረበርብ የባቄላ በቆልት ሞልታ ጋን የሚያህል ማንቆርቆሪያ እሲዛ ጠላ ወይም ጠጅ እንድገዛ ትልከኛለች:: በተለይ የምሳና የእራት ጊዜዬን በአጋጣሚ አክብሬ ከመጣሁ እኔን ከድግሱ ለማራቅ ወይም ከድግሱ የሚያምር ትርፍራፊ ለማሸሽ ማንቆርቆሪያ አስይዛ ትልከኛለች:: የምትመርጠው ጠላ ቤት ሩቅ ያለውን ነበር:: እንዲያዘገዩኝ፣ እንዲያደክሙኝ:: እንደመጣች ሰምን እያመነኳት ሩቅ ሄጄ ጠላ አመጣላት ነበር:: ተንኮሏ ሲገባኝ ግን መዋሸት ጀመርኩ:: ይኼ ዐይነት አስተዳደጌ የለገሰኝ አንድ ባሕርይ ቢኖር ይክፋኝ፣ ደስ ይበለኝ፣ ውሸት ልናገር ዕውነት ልናገር አለመታወቁ ነበር:: ታዲያ ይሔ ጠባዬ የአባቴን ሚስት ያስፈራታል:: ይነጫነጯል እንዳትል አልነጫነጭም:: ደስ ብሎታል እንዳትል አልሳቅሁም:: ስለዚህ ብዙ ጊዜ የምትናገረኝ ነገር እራሷ ካጋጠማት ሁኔታ ይነሳ ነበር:: ደስ ያላት ቀን አሽኩራማ ትናገረኛለች:: የከፋት ለት ተቆጥታ ትናገረኛለች:: ደስ ያላት ቀን ታሰማምረኛለች:: የከፋት ለት ትረግመኛለች:: ደስ ቢላትም ባይላትም ግን ዋናው የሕይወቴ የጋራ አካፋይ መታሸት ላይቀርልኝ::



@BOOKALEM

ማታ ርቦኝ መጥቼ ስጋና ነፍሴ እህል ሲቋምጥ ማንቆርቆሪያ አሲይዛ ጨለማ ውስጥ ሰደደችኝ:: ተብሳጨሁ:: ደከሞኛል፣ እርቦኛል:: ያኔ 'ደክሞኛል' እንኳን ብዬ መናገር እፈራለሁ......በልቤ አስበዋለሁ እንጂ:: "ደክሞኛል" ማለት የተከለከለ ነበር......በዚህ መልስ አድጌ፦"ምን ሰርተህ ነው የደከመህ? "...... "እፈራለሁ...... ጨለማ ነው" ማለት አልችልም ነበር:: እሱም ተከልክሎ......ደሄ መልስ ጆሮዬ ላይ እየተወረወረ፦"ምን ብሎ ነው የሚበላህ? ካልነኩት አይነካ የዚህ አገር ጅብ":: ብሶቴ ደግሞ ትንሽ ገላዬን እየበላ የበለጠ ያዳክማታል:: ማንቆርቆሪያውን ተሸክሜ ጠጅ ቤት ሔድኩ......

አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጬ ሻጯ እስካለ ጠጁን ከብርሌ ወደ ማንቆርቆሪያ እየለካች ስትገለብጥ ሳይ እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ጠጅ አመላልሳለሁ እንጂ ጠጥቼ እንደማላውቅ ተገለፀልኝ:: ሒሳቤን ከፍዬ ከወጣሁ በሁዋላ ከምንገድ ሽሽት ብዬ ጠጁን ለመሞከር ፈለግሁ:: በመጀመሪያ ቆም ብዬ በማንቆረቆሪያው አፍንጫ አንድ ጉንጭ ጠጅ ሳብኩ:: ይቀዘቅዝ ነበር:: ከኢጋም አጥር ላይ አረቄን የተላተምኩ መሰለኝ:: ዐይኖቼ ብርት ሲሉ ይታወቀኛል:: ጭንቅላቴን እንደ ረጠበ ውሻ አራገፍኩና ፈገግ አልኩ:: ለማንኛውም ባጠፋም ባላጠፋም ያቺ እንጀራ እናት የምትባል ነገር እኔን መደብደቧ ስለማይቀር የግርፊያ አደጋውን በመቀበል ማንቆርቆሪያዬን ይዤ ከመንገዱ ሳልርቅ አንድ ግራር ስር አረፍኩ:: ይኼ ግራር ከዚያ እንግዳ ልጅ ጋር የሰረቀውን ዘቢብ ተቀምጠን የበላንበት ነበር:: ጨርሰን የወረወርናት የዘቢቦቹ መስፈሪያ ጣሳ አፈርና ጠጠር ሞልቷት ድቅድቅ ጥላ ስር በጎኗ ወድቃለች:: እስኪበቃት ዝጋለች:: የፍርድ ቀን ሲመጣ እግዜር በሚንቦገቦግ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ሰውን ወደ መንግስተ ሰማያትና ወደ ገሐነም ሲልክ በእኔና ዘቢቡን በሰረቀው ልጅ ተራ ያቺ ጣሳ መረጃ ሆና ትቀርባለች:: እኔም ደግሜ በሰማይ ቤት ይሔን ቀዝቃዛ ማንቆርቆሪያ እያለሁ:: እግዜርን ግን አልፈራውም:: ፈርቼው አላውቅም:: ምኑ ያስፈራል:: እንጀራ እናቴን፣ አባቴን፣ ረሐብን ፣ ዘቢብን ማንቆርቆርያን የፈጠረ ምኑ ያስፈራል::

ዛፏ ስር ተቀምጬ መጀመሪያ በማንቆርቆሪያው አፍንጫ ጠጅ እንደ ሲጃራ ስስብ ቆይቼ፣ ሞቅ ሲለኝ ሲጀምር በአፌ በቅጡ ማንቆርቆር ጀመርኩ:: ይጣፍጣል:: ሆዴ በኮስታራ ፈሳሽ ከረሜላ የሚሞላ ይመስለኛል:: ብቻዬን መሳቅ ጀመርኩ:: ሁሉ ነገር ያስቀኛል:: በተለይ እንጀራ እናቴ ታስቀኛለች:: አፏ ያስቃል፣ ብልጥ የሆነች ሲመስላትና እኔ ግን ሳውቅባት ግን የማውቀውን ሳልነግራት ይኼ ያስቀኛል አባቴ ከኑቶንዶሉ ከነሻማ ጨርቅ ካፖርቱ ያስቀኛል ዛፍ ስር የበላሁት ዘቢብ ትዝ ሲለኝ ያስቀኛል:: የእሁቴ ወፍራም ፊትና ቂጣም ጆሮባ ያስቀኛል በአጠገቤ በዚያ ጨለማ ሳያዩኝ የሚያልፉ ሰዎች ያስቁኛል...ሳቁ ደ'ሞ ድምፅ የለውም:: እንዳረጀ ወይ ሳንባው በወረርሽኝ በሽታ እንደተበለሻሸ ጉብል ነበር የምስቀው...ለራሴ በግድ የሚሰማኝ ጉሳቱ ከአገጬ የማያልፍ ሳቅ ነበር የምስቀው::



@BOOKALEM

ማንቁርቁሪያው ያስቀኛል... ከሞቀ ቤት አውጥቼ እንቁራሪቶች የሞቱበት መሬት ላይ አስቀምጬ እንደ እናቴ ጡት ስጠባው እንደ ወንዝ ድንጋይ ሳይነቃነቅ ዘርፈጥ ብሎ.......እየደከመኝ.......መጠጣቴን ሳላቆም .......

ባንክ:: ጠዋት ነበር:: በምንገድ ሰዎች ያልፋሉ:: ጥቂት ሰዎች:: አያዩኝም:: ማንቁርቁሪያውን እንደተኛሁ በእግሬ መትቼው ነበር መሰለኝ ተገልብጦአል:: ብርድ ያንዘረዝረኛል:: ዐይኖቼን ማግለጥ ከብዶኛል:: ቁጌ ስር ጠጅ የገዛሁበት ሳንቲም መልስ ተዘርግፎአል:: በጠይሙ መሬት ንቃቃት ሾልከው የገቡ ሳንቲሞች ይኖሩ ይሆናል:: ልብሴ በጤዛ እረጥቦአል:: ታጥፎ ያደረ ጉልበቴን ማዘርጋት አልቻልኩም:: ብርድ እንደመታኝ ስረዳ መንዘርዘር ጀመርኩ:: ጥርሶቼ ይንቀጫቀጫሉ:: እግሮቼ ከእኔ ቁጥጥር ውጪ ይርገፈገፋሉ:: የፊቴ ቆዳ ጠንካራ የማይታጠፍ ክርታስ ሆኖአል:: የፀሐይን ከፍታ ለመለካት ቀና አልኩ ጨረሮቹ እንደ ደመኛ ይዋጋሉ:: ከዐይኖቼ መጀመሪያ እንደ ጠብታ ቀጥሎ እንደ ወንዝ ዕንባ መውረድ ጀመረ:: እነበርክሁበት ተቀመጥሁ:: ጠጅ ቤቱ ከዚህ ይታየኛል:: አስካለ የእንጨት ዘንግና የማይታይ ነገር በጉያዋ ይዛ ወጣች:: እንጨቱን መሬት ውስጥ ሰክታ ካቢቃች በሁዋላ ከብብትዋ ደግሞ የማንቁርቁሪያውን ዐይነት ቀለም ያለው (ብርማ) ባለሰንበር ጣሳ አውጥታ ሰቀለች:: ዐይኖቿ በእኔ አቅጣጫ ወረወረችና ጭንቅላቷን ነቅንቃ ወደ ቤቷ ተመለሰች......የሚያቅፈኝ ሰው ፈለግሁ:: ጉልበቴን አቅፌ ኩምትር ብዬ ተቀመጥሁ::

የሚያቅፈኝ የለም?

ማነው የሚያቅፈኝ? አልኩ::

አሥር ድርድርብ ያለው ጋቢ የለበሰ ወይም ጉፈሩ ባላለቀ የደብረ ብርሐን ብርድ ልብስ አቅፎ የሚያስተኛኝ ማነው? እንደተከናነብኩ ጉንጬን እየነካካች ጉንጬን እየዳበሰች ስኳር የበዛው ሻይ የምታጠጣኝ እናት ማናት? ረሐብ ደኅሞ አለ:: ትላንት ቁርሴን አንድ ፍሪት ዳቦ በአንድ ጥፊ ውጥ የበላሁ ነኝ ትናንት ቀትር በቀዳዳ ኪሴ በእፍኝ የተሰፈረ ቆሎ የበላሁ ነኝ ማታ ድንቅ ነገር ሲበላ እንዳላይ በብልሐት በእርጥብ አሹቅ ታፍኜ የተባረርኩ ነኝ:: አምላክ ደኅሞ ሕይወቴን ተንብዮ ያለሆድ አልፈጠረኝም::

መሮጥህ ፈለግሁ:: ሰው ቢመጣ ምን እላለሁ ግን? "በጥጋቡ ነው" እባላለሁ:: "በጥጋቡ" ...ችግሬን መስማት ሲጠሉ "በጥጋቡ ነው" ይሉኛል.......:: አልሮጥሁም:: ዕንባዬ ግን ይወርዳል:: የእግሮቼ ጣቶች ደንዝዘዋል ጥፍሮቼ የእጄም የእግሬም ያቃጥሉኛል:: ሰው እንዳያየኝ ከመንገዱ ወደ ዛፉ ሸሸት ብዬ ፀሐይ ሙቀት ውስጥ ተኛሁ:: ብርድ ከሚገርፈው ቆዳዬ ስር የምታለቅስ ነፍሴ ውስጥ በዚያ ልጅነት የሚገርም ጉድ ተሰማኝ:: እንደወይን ዘር እንደወይን ሰንደ ተጠቅላ......በተሰፋ የሞቀች አንዲት ፍሬ ሣቅ፣ የሆነች ወዛም ሉዛ ተኝታ



@BOOKALEM

ነበር......እዚያ ውስጥ የተፈጠረችበት ምክንያት እዚያ ውስጥ ያስገባት ምክንያት ምን እንደሆነ ግን አላውቅም። ግን እሰማት ነበር።

እንዴለች እሰማት ነበር.......

መቼ እንደምስቃት ያልተረዳሁዋት።

እቤት ውስጥ አራት ነበርን። እኔ ከተቆጠርኩ። ተቆጥሬ የማውቅ አይመስለኝም። ቁጥር እኔ ዘንድ ሲደርስ መሥራት ያቆማል። አንድ ሁለት ሦስት...... እእእም......። ቡና ተፈልቶ ትኩሳታቸው በየቦታው የሚሰራጭ ረከቦት፣ ስኒዎችና አንድ ጀበና እንደየወንያቸው ተቀምጠዋል። (እእ ግራኝ ስለሆነች ጀበና የምታስቀምጠው በግራዋ በኩል ነበር)። የወሰን እናት በሹራብ ነበሩ። "ፍጭጭ" ያለ አረንጓዴ ሹራብ ለብሰው። ጫማቸው የታጠቡ ሽራዎች ናቸው (አሁን ሳስተውል የወየዘሩ ሴት ነበሩ እላለሁ) ትልቅ አርቴፊሻል የወርቅ ሎቲ ጆሮዎቻቸው ከንፍ ላይ አድርገዋል። ሰንዘር የሚያህል የብር መስቀል ትላልቅ ጡቶቻቸው መሐል ተጋድሞአል። ቀሚሳቸው ነጭ ቴትሮን ነው አርጅቶ የበረካ ቡና የመሰለ

ጠላ ሻጯ ዐይን የሚያደነቁር ብርቱካናማ ቀለም ያለው ሻሽ ጋን የሚያክል አናትዋ ላይ ጠምጥማለች። ከግራ ጆሮዋ ከፍ ብሎ የሻሺ እስር ላልቶ እንደ አንዳንድ ወታደሮች ቆብ በትንሹ ወደ ጉን ዘንበል ብሎአል። ግራ ጆሮ ግንዷ ታኳለች።

እእ ያለነጠላ ነበረች። ጭንቅላቷ በጉንጉን ተሸፍኖአል። አንገቷ ላይ ሁለት ሀብሎች አሉ ጆሮዎችዋ በትናንሽ ወርቅ ካሶች አጊጠዋል። ቤት ውስጥ ስትንጐራደድ እንደ ዳንስ ነው። የውስጥ ልብሷ ጠርዝ ከቀሚሷ እረዝሞ ይታያል......አውቃም ሊሆን ይችላል......ስለውስጥ ልብሷ ውድ መሆን ብዙ ጊዜ ስታወራ እሰማት ነበር። ጉልበቷ ሳታጥፍ ስለምታጎነብስ ከማጠፊያዋ በላይ ያለው ጭና እያለሁ። የባዕድ ጭን ነበር።

እኔ ትንሽ ሰካር አዙሮኝ ገላዬ በብርድ ኩፍ ብሎ ተቀምጬአለሁ። ስለ እኔ ትንሽ ካወራሩ በሁዋላ እእ ቁርሴን ይዛ መጣች......ከዚያ በፊት ግን ወደ ጓዳዋ ሳትገባ ይኼን ተናገረች፡

"ቢፈርድብኝ ሥራዬ የዱርዬ ሆድ መሙላት ሆነ"

ይሔን እንደተናገረች አራት ሰከንዶች በሚሞላ ጊዜ ውስጥ የሁለቱ ሴቶች ፊት ላይ፣ ሴሐን የያዘችው እእ ላይ እና ራሴን አየሁ። እነዚያ አራት ሰኩንዶች ግን ለመጨረሻ ጊዜ ልቤን ሰበሩት። (በስንጠረዥ የሚከተለውን ይመስላል)



@BOOKALEM

በአራቱ ሰከንዶች ውስጥ «የፈሰሱት» ድርጊቶች ከአደራረገው ጋር ተያይዘው የሚገለጡበት ሰንጠረዥ

| | የወሰን እናት | ጠጅ ሻጯ | እኔ | እእ |
|---|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ሰከንድ** | ሻሻቸውን አመቻቹ... ዐይኖቻቸውን በልጠጥ አድርገው የተገረሙ መሰሉ..... | ግራ ጆሮ ግንዳች ውን ያካሉ.. .. | በከፊል የወሰንን እናት፣ በሩብ የጠላ ሻጧን ጆሮ ግንድና ጥቁር ጣቶች እያለሁ.... | ከሳህኑ ላይ ውሐ ይንጠባጠባል.... ታራግፋለች...ቀኝ ዐይኗን ታካለች... |
| **ሁለተኛው ሰከንድ** | እግራቸውን አነቃንቁና "ጥጋብ እኮ ነው" አሉ:: | "እም" አለች | ዐያለሁ....ጥፍሮቼ በቆሻሻ ሞልተዋል... የወሰን እናት እንገታቸውን በቁጣ ይሰብቃሉ... ጆሮዬ ጠጅ ሻጧን ይሰማል... | የድስት ክዳን ይንኳኳል... |
| **ሦስተኛው ሰከንድ** | በል ጅብ መችም ከመብላት ሌላ ነገር አያውቅም..... | "ምዕ" | ከአውራ ጣት ጥፍሬ ቆሻሻ ለማውጣት እሞክራለሁ... | "ተሞላቀ ተሞላቀ ሲሰለቸው ይተወዋል".... የእግሮቿ ዱካ ይሰማኛል.. |
| **አራተኛው ሰከንድ** | "አይቆነጠጥም እንዴ?"...... | ግራ ጆሮ ግንዳች ውን ያካሉ... | ከግራ አውራ ጣት፣ ቆሻሻ ፈልቅቄ አወጣሁ...በሌላ እጄ አመልካች ጣቴ ጥፍር ደንግጬ ቀና እላለሁ... | "በል ጅብ መቼም ከመብላት ሌላ ነገር አያውቅም"..... |



@BOOKALEM

# ወፍራም እህት

የጠጁ ጉዳይ በሠላም ታለፈ?

በፍፁም:: ሊሆን አይችልም:: የቤታችን ሥነ ሥርዐት፣ የአባቴ ቤት ሥነሥርዐት ይሔን አይፈቀድም (የየትኛውም ቤት ሥነሥርዐት):: ያጠፋ መቀጣት አለበት:: አንዳንድ አካባቢ እንደውም (ዱባለ ቤት) ባያጠፋ እንኳን እንዲያጠፋ ተደርጎ ወደ ስህተት መገፋፋት ነበረበት:: ተገፋፍቶ በሰራው ጥፋት ሙሉ ሐላፊነቱን እንዲወስድ አድርጎ ለመቅጣት:: የተገፋፋ ጥፋት ከአጥፊው ነፍስ እንደማትመጣ መቸም ሁሉም ያውቃል:: ሰው ሰራሽ ናትና:: የዚያች ዐይነት ጥፋት ደሞ ጥልቀት አይኖራትም:: ረባሽነቷ አርኪ አይደለም:: እንደውም ዋናው ዓላማ ወደ ፊት ሊመጡ የሚችሉ ሌሎች ተከታታይ ስህተቶች ካሉ "ልማዱ ነው" ብሎ መንሻቸውንና የአጨራረስ ትርጉማቸውን እንደ አሻ በመተርጎም ቅጣት ለመሰንዘሪያና የተፈፀመ ቅጣትን ለመደጋገፊያ መሳሪያነት መገልገያ ነው::

የሱሪዬ ኪስ በመቀደዱ ብዙ ቅጣት ደርሶብኛል:: የሱሪዬን ኪስ ግን እኔ አልቀደድኩም:: የኪሱን ጨርቅ ነጥዬ ፈልጌ ሥሩን በምላጭ አልቀደድኩም:: በመጀመሪያ የሸንብራው አፍንጮች ሐላፊነት አለባቸው:: ከእነሱ ቀድሞ ደ'ሞ ካልጠፋ አጉል እህል ሽንብራ የሚሰጡኝ ሰዎች ሐላፊነት አለባቸው:: አርፌ ቤት ውስጥ ተቀምጬ ከቁና እየዘገንኩ እንዳልበላ ዓይኖቿን እያጉረጠረጠች አገር ዘርፌ እንደምበላ የምታየኝ እእ ሐላፊነት አለባት:: ታዲያ የሱሪዬ ኪስ ቢቀደድ እኔ ምን ተዳዬ? ይኼ የኪስ ጉዳይ ለማንኛውም ሰውይገባዋል:: የተወነጀልኩት ግን «ቀደድከው» ተብዬ ነበር:: እኔ ደ'ሞ ተቀዶ ሳይ ዝም አላልኩም:: በሚቻለኝ መልክ በአቅሜ ኪሴ እንዳያሾልክ አድርጌ ቀዳዳው ላይ ወረቀት አነጠፍኩበት:: ቢሆንም ይሄ ራሱ እንደ ምክንያት ተጠቅሶ ተመታሁ:: "ለምን መቀደዱን አልነገርከኝም" ተብዬ......በእእ::

የኪሱ ነገር እንዴት ታወቀ?

ጠዋት ላይ ማንቆርቆርያውን ወደ ቤት ስመልስ እቤታችን ውስጥ ሰው ተሰብስቦ ደረስኩ:: ከሳንቲሙ መልስ አሥራ አምሥት ሳንቲም ጠፍቷል:: እንደጠረጠርኩት በነቃቃ መሬት ሾልኮ:: ምንም ሳልፈራ ግን ማንቆርቆሪያዬን እያወዛወዝኩ ገባሁ::

ማን ማን ነበር?

መጀመሪያ ያየሁዋቸው የወሰንን እናት ነበር:: ቀጥሎ ጠጅ ሻጯን፣ ከዚያ በሁዋላ እናቴን:: አባቴ ፀጉር አጨዳ ሔዷል::



@BOOKALEM

ምን አሉ?

የወሰን እናት ሳቃቸው እንደመጣ ሁሉ አፋቸውን ያዙ። ምን እንዳሳቀቸው አላውቅም ስለ እኔ ሜዳ ላይ መተኛት ጠጅ ሻጯ ሳትናገር አትቀርም።

እእስ?

ማንቆርቆርያውን እግሯ ስር አስቀምጪ የመልሱን ሳንቲሞች ሰጠሁዋት። ሳትናገር ቆጠረችና:

"አስራ አምሥት ሳንቲም የታለ?" አለችኝ።

"ጠፋ" አልኳት።

"በል በሁዋላ እንነጋገራለን" አለችና ሔደች።

ወዴት ሔደች?

ሁለት ሳህኖች ይዛ ስትመጣ ማድ ቤት ሔዳ እንደነበረች አወቅሁ። ቁርሴን እንድበላ ሁለቱን ሣሕኖች ፊቴ አምጥታ አስቀመጠች። አላመንኩም። ለእኔ የቀረቡ አልመሰለኝም ነበር።

ስለምን?

"በል ብላ!" አለችኝ እእ።

ከአፏ ዉድ የሚተን ይመስላል፡ ትችልበታለች እንዴ እንዲህ ማለትና ማድረግ?

በግራ በኩል ያለው ሳህን በመዐት የእንቁላል ፍርፍር የተሞላ ነበር። በስተቀኝ የአስኳል ቀለም ያለው ቅንጬ ነው። ከየት እንደምጀምር አላወቅሁም። ሆዴ የጮኸው ጩኸት የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ድረስ ሳይሰማ አይቀርም። ተራሮች ላይ ያሉ ፍጡራን ሳይሰሙት አይቀሩም......ደገኞች 'ዝናብ ሊመጣ ነው' ሳይሉ አይቀሩም። እንደዚያ ዐይነት ሳህኖች እቤታችን ውስጥ ያሉ አይመስለኝም ነበር። ኑጭና ንፁህ ነበሩ። በጣም በጣም ኑጭና ንፁህ ነበሩ......

*አለው አለው ዕንቁላል*
*አለው ዕንቁላል*

ሣሁን ምግቡን ሁሉንም መብላት ፈለግሁ።

ሣሁን ምግቡን የጠረጴዛውንም ልብስ መብላት ፈለግሁ።

ሣሁን ምግቡን የጠረጴዛውን ልብስና ጠረጴዛውን መብላት ፈለግሁ።



@BOOKALEM

ሣሁኑን ምግቡን የጠረጴዛውን ልብስ፣ ጠረጴዛውንና ምግብ የተሰራብትን ማድ ቤት መብላት ፈለግሁ።

ሣሁኑን፣ ምግቡን፣ የጠረጴዛውን ልብስ፣ ጠረጴዛውን፣ ማድ ቤቱንና ምግብ የሰሩትን እጆች መብላት (ካከሽ) ፈለግሁ።

ድምፅ እያበዛሁ......ጪ፣ ጢ፣ ፍጢ፣ ጭርጢ፣ ግርጫጫ፣ ፍጫ፣ ፍጫጫ ስበላ እእናቴ ታወራለች......እኔ ታዲያ በወፍራሙ ዋጥ።

"ጥጋብ......ጥጋብ......አባቱ ትቶታል። እኔ ብመታው ያልወለደ አንጀት ተብዬ ያሳማኛል። ነፃነቱ በዝቶበታል። እዚያ ታዩት የለም......ተጉልቶ ሲውል። ይሔ የጤና ይመስሎታል?......የጥጋብ......"

የተሰበሰቡት ሁሉ ይደጋገፋሉ። አያውቁም መሐይም ናቸው። እንቁላል ፍርፍር...... አደይ የመሰለ ቅንጬ ስበላ የመጀመሪያዬ እንደሆነ አያውቁም። እነሱ ወደየቤታቸው ከተመለሱ በሁዋላ "ዱርዬው ተገኘ" እያሉ ሲያወሩ......ይሔ እህል ሆዴ ውስጥ ገና ሳይረጋ ምን እንደሚጠብቀኝ አያውቁም ነበር።

እህቴ በዚያች ሰዓት ለምን ወፍራም እንደሆነች ገባኝ። የሚዳላት አይመስለኝም ነበር። በልጅ መሐል የሚዳላ አይመስለኝም ነበር። እንደ እኔው የምትበላ ይመስለኝ ነበር። ምክንያቱም ስትበላ ዐይቻት አላውቅም። ሳስብ ስትበላ አይቻት አላውቅም። እህቴ አለ ነገር አልወፈረችም። ወፍራም ነበረች። እህቴ ወፍራም ናት፥ ወፍራም እህት ነበረኝ። ሁለመናዋ ወፍራም ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ለቅጣት ከቤቱ ጀርባ ያለውን ሳር እጨድ ተብዬ በትልቅ ገንዳ ውስጥ ገብታ ገላዋን ስትታጠብ አይቻታለሁ። ጡቶቿ ሁሉ ወፋፍራሞች ነበሩ። ሰውነቷን ለማዳረቅ ስትነሳ እግሮቿን ሳያቸው ትላልቅና ወፍራም ነበሩ። ሁለመናዋ ወፍራም ነበር። ጠላሁዋት። ምንም ሳታደርገኝ ጠላሁዋት። በመወፈሯ ጠላሁዋት። ከሳንባ ገደል እኩል ብንወረወር እሷ ቀድማ የምትወድቅ ይመስለኝ ነበር። ወፍራም ሚስት የምትፈልጉ ወደ ነፋስ መውጫ ተጉዛችሁ አግቧት። የሚጠላውን የሚያቃጥር አጋጥምዎት ያውቃል?

ታዲያ ወጣ እንዳሉ......የወሰን እናትና ጠጅ ሻጯ......በዚያ ታላቅ ቁርስ ተመቻችቼ የሆዴን ድንጋጤ ሳዳምጥ......እንጀራ እናቴ ከወደ ጏዳ ረዥም ማማሰያ ይዛ (ምሰሶ ነበርን?) እሩጬ እንዳላመልጣት ፈርታ ይሁን አላውቅም እየበረረች መጥታ አንገቴን ያዘችኝ። በድንጋጤ ሆዴ ተገላብጦ የቀጠነ ቅንጬ ወደ አፌ ሲመጣ ይታወቀኛል። ስትገፈትረኝ የጉሮሮዬ አሰራር የተለየ ነው መሰለኝ አፌ ውስጥ በመውጣት ላይ የነበረው ቅንጬ ወደመጣበት ተመለሰ። አፍጥጬ አየሁዋት......አፌን ከፍቼ አየሁዋት......

"በል አንተ ሌባ የተላከውን ማድረስህ ቀርቶ ሳንቲም መስረቅ ጀመርክ!"



@BOOKALEM

"ጠፋብኝ"

"ምኑ ይጠፋብሃል?"

"ኪሴ ተቀዶ" ይኼ ምክንያት ከምላሴ እንደ ቅርፊት ተገፎ ወጣ:: እራሴም የጠበቅሁት መልስ አልነበረም::

የመቀጣቴን ምክንያት ለሦስት ከፈለችው:

(1) የተላከውን ያልፈፀመ

(2) ሣንቲም የሰረቀ

(3) ኪሱን የቀደደ

ስትገርፈኝ ታዲያ እነዚህን ሦስቱን በየተራ እየጠቀሰች ነበር:: ከአለንጋው የበለጠ ታዲያ የፈራሁዋቸው ቃሎች መላክ፣ ሳንቲምና ኪስ የተባሉትን ነበር:: ከአለንጋው ይልቅ የፈራሁት ቃሎቹን ነበር::

ያው መችም እኔን የሚፈልገኝ አይኖርም ታዲያ ጊዜ ካላችሁ ንፋስ መውጫ ኑና ወፍራም ሚስት ከፈለጋችሁ እህቴን አግቧት......እል ነበር በነገርና በልምጭ ስቃጠል::




@BOOKALEM

# በስበት መጫወት

ይኼን የሚጠራጠር ማን ነው?

አንድ ዕለት ከትምህርት ቤት ለዕረፍት ተለቀን እያለ፣ ብዙ ጫጫቴ ባለብርንን ለኳስ ጨዋታ ሜዳ ውስጥ ሲቀር እግሮቼ አላርፍ ብለውኝ በውሐ መጠማት አሳብቤ ወደ ወንዝ ወረድኩ። ለከተማዋ የሚያገለግለው ቧንቧ ገና በመሰራት ላይ ነበር። ተሰርቶ ቢያልቅ እንኳን ትምህርት ቤታችን ውስጥ መቸ እንደሚገባ አላውቅም (ስለቧንቧው ግን ምን አገባኝ)። ታዲያ ወንዝ ወርጄ አንድ ጣቢያ ላይ ቆሜ ለጫወታ ድንጋይ እየወረወርኩ ያን የጠራ የውሃ ደረት በድንጋይ ስጨፈጭፍ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ እጄ አንድ በጣም ጠፍጣፋና ለስላሳ ድንጋይ ከመሬት አነሳ። ድንጋይዋን ወርውሬ የውሐውን ጠለል ለመምታት በጣቶቼ ለመያዝ ሳመቻቻት ውበቷ በቅፅበት ዐይኖቼን ሳቡዋቸው። ድንጋይዋ በጣም ስስ፣ በጣም ለስላሳና በጣም ነጭ ነበረች። ከመሐሏ በትክክል የተቃኘ ጉድጉድ ያለ ሰንበር ወርዶባታል። በጠራቢ የተሰመረ ይመስላል። እጄ መዳፍ መሐል ሳገላብጣት፣ ስደነቅባት ከቆየሁ በሁዋላ



(ከወንዝ ያገኘሁዋት ድንጋይ ይህን ትመስል ነበር)

እየወረወርኩ መቅለብ ጀመርኩ። ለእጄ መሐል (ለመዳፌ) ክብደቷ እስተዚህም አይሰማም። "ገላዋ" በሚያብረቀርቁ በጣም ትናንሽ ወርቅ፣ መስታወት፣ አሸዋ በመሳሰሉ ነገሮች ተሸፍኗል ። ወደ ሰማይ ታዲያ ስወረውራት የፀሐይ ጨረር ያርፍባትና በትንሹ በጣም በትንሹ ያፈረች ብልጭልጭ ጌጥ ትመስላለች። በጣቶቼ ስዳብሳት ነጭ ላባ እንደ



@BOOKALEM

ለበሰች ጫጩት የምትለሰልስ ነበረች። ያኔውኑ ፍቅር ነገር ከእሷ ይዞኝ በውሐ አጣጠብኳት። ብዙ ጉድፍ፣ ጭቃ አልነበራትም።

የዕረፍት ጊዜ ማለቁን ገምቼ ድንጋይዋን እየወረወርኩ እየቀለብኩ ወደ ትምህርት ቤት ስመለስ ለቅፅበት የያዝኳት ድንጋይ በድሮ ጊዜ ወፍ የነበረች ግን ሞታ ወደ ድንጋይ የተለወጠችና ልስላሴና ቅርጿ ብቻ ተርፎ......በወረወርኳት ቁጥር ግን እንደመብረርና እንደማምለጥ ተመልሳ ወደ መዳፌ ማዕከል የምትመጣ......

በልጅነት ምናቤ ተደልዬ ምናልባት ራቅ አድርጌ ብወረውራት ትበር ይሆናል በማለት ከፍ እያደረኩ ማጉኔን ቀጠልኩ። ተመልሳ ትመጣለች። ስወረውራት ተመልሳ ትመጣለች። ሳይንስ ውስጥ ስበት ስለሚባል ነገር ተምሬአለሁ። እንስሳት፣ በተለይ ወፎችን የመሳሰሉ በተለያየ መልክ ስበትን እንዳሸነፉ ሰምቻለሁ። የማሸነፍ ሐይል አላቸው ተብዬ።

ተማሪዎች ክፍል ገብተው ደረስኩ። ሜዳው የታጠበ አረንጓዴ ሸሚዝ ይመስላል......የኳስ ሜዳው የጉል እንጨቶች ሰው መስቀያ ይመስላሉ። ሺህ ዐይኖች አውቃለሁ ወደዚህ እንደሚያዩ። የእርሻ አስተማሪያችን "ምን ትሰራለህ? አትገባም?" ብለው ሲጮሁ ሰማኋቸው። ከየት ብቅ እንዳሉ አላየሁዋቸውም። የእርሻ አስተማሪያችን ምናልባት ከጉመን ቅጠሎች መሐል መደበቅ ይችሉ ይሆናል።......እንግዲህ የጉሉን እንጨት ዐይቼ......የበሰበሰ፣ ሰው መስቀያ የሚመስል መሆኑንና......ሰው ሲሰቀል......ብዙ ሺህ ተመልካች ያለ ቀጠሮ እዚያ መገኘት እንደሚችል ሳስብ......ነገሩ ኩስኩሶኝ ነው መሰል ድንጋይዋን ወደ ሰማይ በብስጭት ወረወርኳት። ያኔ እኚህ ጎመን መሐል፣ የሆነ ቅጠላቅጠል ስር ተደብቀው የነበሩ የእርሻ አስተማሪ......

"ምን ትሰራለህ? አትገባም?" አሉ።

ይሔን ጊዜ ነበር ደንግጬ ዞር ያልኩ።

ይሔን ጊዜ ነበር ድንጋይዋ እጄን ስታ እንደጠፋች ያወቅሁት።

እጄ ላይ የለችም፣ ሰማይ ላይ የለችም። ያስተማሪዬን ጥሪ ችላ ብዬ መሬት ላይ እፈልጋት ጀመር። አላገኘሁዋትም። ከእኔ ዕርቃ ወድቃ ነው እንዳልል ምናልባት በእኔ በልጅነት እግሮቼ ተለክቶ በዚያን ጊዜ አስር እርምጃዎች ያህል ወደ ሰማይ ባጉናት ነው ("ሰማይ" ከተባለ)። አስተማሪዬ እየጠሩኝ በወረወርኩበት ጊዜና በደነገጥኩበት ጊዜ መሐል በመሬት ላይ የሔድኩት እርቀት ከሁለት እርምጃዎች አይበልጥም ነበር። ስለዚህ ድንጋይዋ ከመሬት ዘጠኝ ሜትሮች ከፍታ (የእኔን ቁመት ጨምሮ፥ ድንጋይዋን የማጉናት እጄን



@BOOKALEM

በወገቤ አቅጣጫ አድርጌ ነው) መሬት ላይ ደ'ሞ ሁለት ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ውስጥ መውደቅ እንዳለባት ገምቼ፣ ብፈልግ ብፈልግ ላገኛት አልቻልኩም::

እኒያ የእርሻ አስተማሪ የሚታዘዝ ሰው አለቀባቸው መሰል ደጋግመው ይጠሩኛል:: እኝኝኝኝ:: በሽቄ እክፍሌ እንደገባሁና በሌላ አስተማሪ እንደተገላመጥኩ አንድ ሐሳብ ብልጭ አለልኝ......ይህቺ ድንጋይ ወደ አየር ውስጥ እንደወፍ በራ እንደሆነስ?......እየቆየ ወደ ሰማይ፣ በጣም ወደ ሰማይ አለማየቴ ቆጨኝ::

ግን የተወረወረ ነገር ተመልሶ ይወድቃል......ስበት:: ከሰውና ከእንስሳት ቀድሞ የተፈጠረው ስበት አይደል......ከአውሬውም ከምኑም ማለት ከተንቀሳቃሹም:: ድንጋይዋ ወደ መሬት ተመልሳ ሳር ውስጥ ጠፍታ ይሆናል:: መሆንም ነበረበት::

መማሪያ ክፍል ገብቼ ስቀመጥ የሚያስተምሩኝን የእንግሊዘኛ አስተማሪ አልወደድኳቸውም::

" He is working "  present continious tense

"He was working"  past continious tense

ይሉሃሉ::

ሳያቋርጥ የገረመኝ የድንጋይዋ ነገር ነበር:: የት ናት? የት ነበረች?

ይሄንንስ ደጋግሜ ብናገረው የሚጠራጠር ማነው?



@BOOKALEM

# በመጀመሪያ ጥንቸል ነበር

ገበያ ሲደራ እወድ ነበር። በየሳምንቱ ቅዳሜ። ቅዳሜ ለእኔ ድንቅ ቀን ነበር። በእነዚህ የዐይኖቼ የጥቁር ኳሶች አዳሜንና ሔዋኔን ፎቶግራፍ ሳነሳ። ስራዬ ከረሜላዬን (ናናዬን) መምጠጥና ጉያዬን እንደ ውሻ ማከክ ነበር። አራት ናናዎች ገዝቼ እነሱን በአጭር ጊዜ ውስጥ መጥጬና ቆርጥሜ ጨረስኩ። ሌላ ተጨማሪ አምሮኝ ለመሸመት ከተቀመጥኩበት ጉብታ ወረድኩና ታች ሱቅ ለመሄድ ቆሜ ተንጠራራሁ። ናና የሚሸጠው ከልብስና ብትን ጣቃ ጉልቶች ጀርባ ካሉት ሱቆች ከመሃከለኛው ነው።

ባለ ሱቁ ለምዶኝ ገና ሲያየኝ፡

"ስንት ትፈልጋለህ?" ይለኝ ነበር።

የነገርኩትን ቁጥር ያህል በቆሸሸ እጁ ይቆጥርና (በርበሬ፣ ሽሮ፣ ሳሙና፣ ጥራጥሬ የመሳሰለ በነካበት እና ሳንቲምና ብር በቆጠረበት) (ነጋ ጠባ ነጭ ዐይን ዐር እንደ ሎቲ እንደጎለተ ነበር) ዘይት በጠጣ ጋዜጣ ጠቅሎ ይሰጠኛል። ለዚህም እንደ ባለውለታዬ ሊሰራው ይፈልጋል።

ከሱቁ በር በስተግራ በኩል ሁለት ጠፍጣፋ ከቆርቆሮ የተሰሩ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች አሉ። ከግድግዳ ጋር ከሰው ቁመት ከፍ ብሎ በሰባት ስምንት ምስማሮች ላይና ታች ሆነው ተመትዋል። እየሳቁና እየተንተከተከቱ ፋንታና ኮካኮላ የሚጠጡ የሦስት ፈረንጆች (አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች) ፎቶዎች ይታያሉ። እኔ ሁለቱንም ዐይነት ለስላሳ መጠጦች ቀምሼ ጥርሴ ሳይሆን በሳቅ የተነፋው ሆዴ ነበር—ቁንጣን በመሰለ ነገር......የውሃ ቁንጣን ካለው። እዚህ ሱቅ ከመግባቴ አንድ እርምጃ ቀደም ብሎ ሁልጊዜ የሚሸተኝ ሳምባ ነበር።

ከጉብታዬ ወርጄ መንገዱን ልሻገር ስል አንድ ሎንቺና ፊቴ መጥቶ ተገተረ። ሁሉ ባለ መኪና እንደ ልቡ ነበር የሚሰራው። በደንቡ መቆም የነበረበት ከገበያው ክልል ውጭ ከቅመም ተራ ፈቀቅ ብሎ ነበር። እዚያ አካባቢ ታዲያ ሁልጊዜ ሞተር እንደተንዛዛ፣ ጤስ እንደ ጤሰ (ከትንባሆም ሊሆን ይችላል......ትንባሆ የማይጠጣ ሾፌርና አውታንቲ ነበር እንዴ?) ነበር። እንዲህ እንደገዛው መሬት የገበያተኛ ምንገድ ዘግቶ የቆመው ሎንቺና ከላይ እስከ ታች የዛገ ነበር። ቆሞ መሄዱ ያስገርማል። እሱን አልፌ መንገዱን ተሻግሬ እንደ ሄድኩ ፍራፍሬ ተራ ገባሁ። ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ትርንጎ፣ አናናስ፣ ታንጀሪና፣ ኮሽምና ሎሚ ይሸጣል። ብዙው ሎሚ ነው። የሎሚው ጠረን አየር ውስጥ ይተማል። እህል ተራ ስገባ ከወዲያ ፀሐይ ከዞሲ ላይ ተቀምጣ ንፁሕ አሮጌ ጨርቅ ፊት ለፊቷ አንጥፋ እዚያም ላይ የጉሬዛ አካዎች ዘርግታ መፅሐፍ እያነበበች ተቀምጣለች። ገበያ መሃል ምን የሚያስነብብ ነገር አለ? አልኩ



@BOOKALEM

በልቤ:: ከጀርባዋ አንድ ሜትር ያህል ፈቀቅ ብሎ ዝበያተኛ የሚመላለስበት ቀጭን የእግር ምንገድ አለች:: ከዚህ የእግር ምንገድ ቀጥሎ የአንድ ጠጅ ቤት በረንዳ ነበር:: ከዚህ በረንዳ ላይ የጠጅ ሽታ (ጌሾና ማር) የጠጪ ጩኸትና ያላባቸው ዝበሬዎች ጠረን እየጎረፈ ይመጣል::

እና የፀሐይ ማንበብ ግራ አጋባኝ::

ዮማ ፀጉሯ ተጎንጉኗል:: እጥፋቱ እጥፋቱ ላይ ያብለጨልጫል:: ከምታነብበት ቀና ብላ ገገር ስታጤን የገፅዋ ቆዳ ልስላሴ ይወጣል:: የፀሐይዋ ብርሐን ቢጫ ስለነበረ ይሆን? ቀይ ዳማ ወንዳወንድ:: ከምታነብበት ቀና ብላ ባጋጣሚ ዐየችኝ:: ፀባዩ እንዳላማራት ሰው በተኮሳተረ ግንባሯ አብጠለጠለችኝና ወደ መፅሐፍዋ አጎነበሰች:: "ወንዲላ" አልኩ በልቤ:: እንዲያ እንድታየኝ አልፈለግሁም:: የተማሪ ጎረምሳ ተዳራትና የእኔ ሒሳብ ግልምጫ ነው እንዴ? ከንዷ ዓምድ ያክላል:: ትኩስ የተላጠ ግንድ::

እሷን በቀኝ ትቼ በጉልቶች መሐል እየተጥመዘመዝኩ ስሄድ ከላይ በኩል ሁካታ ሰማሁ::

ዞር እያልኩ እያየሁ፣ ዞር እያልኩ እያየሁ ወደ ሱቆቹ በረንዳ ወጣሁ:: እላይ ሎንቺናው አጠገብ ሰዎች እየተጯጯሁ ይተራመሳሉ:: አጠገቤ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ጆሯቸው ቆመ:: ዐይኖቻቸውን ሁሉም ወደ ሎንቺናው አካባቢ ተከሉ:: ጩኸቱና ትርምሱ የምቀመጥባትን ጉብታ ተጠምዞ በቀኝ በኩል አልፎአት ሔደ:: እንዲህ ሲሆን የጉልት ነጋዴዎች ከተቀመጡበት በብዛት ይነሳሉ:: የሆነ ጠመዝማዛ መስመር ተከትሎ ሰው ከተቀመጠበት ይነሳል:: እንደሚከላከል ወደ መሬት እያየ እጆቹን ያነሳል:: እንጣጥም ይላል:: ቃጠሎ የሴት ድምፆች እንደ ቃሪያ ምንጭ ከየቦታው ተነስተው ትርምሱን ያደምቃሉ:: የሁካታውን ድምቀት፣ ችኩልነትና አደገኛነት ያሳያሉ::

እዚያም እቀምከዝበት ሰው ይቁነጠነጣል::

"እባብ ነው:: ይሄ እባብ ነው" አለ አጠገቤ የቆመ የጢሙ ቁጭራ ጠጉር ገጡ ላይ እንደ ችፍርግ የተፈታተለ ሰው::

"ያበደ ውሻስ" አለ ሌላ አትክልተ ነኝ ባይ::

እያወካ ከተቀመጠበት የሚነሳው ሽቃይና ዝበያተኛ እየበዛ እትጣጫው ወደ ግራ ዞረ......ከበስተላይ ወደ ዙፋን ቤት መሄጃ:: እንደገና የትርምሱ መስመር ግራውን እንደያዘ ወደታች ወረደ:: እዚህ ጩኸቱ ልዩ ነገር እንደተፈጠረ ሁሉ የበለጠ ጎላ:: ትርምሱ ዋናውን ምንገድ ቆርጦ እኛ ወዳለንበት መጣ:: ፀሐይ ከተቀመጠችበት ቀና ብላ አየች:: አፏን ይዛ



@BOOKALEM

ከተቀመጠችበት በፍጥነት ተነስታ በፍርሃት ወደ እኛ በኩል ሸሸት አለች፡፡ ከጥቂት ሰከንዶች በዞዋላ ሕልም የመሰለ ነገር አየሁ፡፡

እግረኛ በሚተላለፍበት የተተመተመ የአፈር ምንገድ ላይ እየነጠረች የምትንከባለል፣ እየተንከባለለች የምትነጥር፣ የምትጮህና የምትሮጥ ጥንቸል ብቅ አለች፡፡ የጥንቸሏ የጀርባዋ ጠጉር እንደ ምድጃ ይጤሳል፡፡ ከላይ አንድ ሰው በትልቅ ጣሳ ይዞት የሚሮጠው ውሃ እየተደፋበት ጥንቸሏ ላይ ሊደርስባት ይሞክራል፡፡ ጥንቸሏ እየጤሰችና እየተገለባበጠች ምንገድ ተከትላ ወደ መድሐኒያለም ቤተክርስቲያን ወረደች፡፡ ጥቂት ልጆችና ውሐ በጣሳ የያዘው ሰው ተከትለዋት ወረዱ፡፡ ይሄን እያየ የቆመውና የተቀመጠው ሰው ሁሉ በመገረም ይተያያል፡፡

"ምን ሆነች?"

"ምን ሆነች ይላል??! የሆነውን እያየህ!!"

"እሱማ እየነደደች ነው፡፡ በየት ኢጋጠማት? ቡና ሲታፈላ?"

"ቀልደህ ሞተሃል፡፡ ሚስትህ እሳት ጭራባት ይሆናል"

"እውነቴን ነው"

ይሄ የተረብ ልውውጥ ሳያቆም ሁለት ትልልቅ የትምህርት ቤታችን ልጆች ፀሐይ ተቀምጣበት ወደ ነበረችበት በሕብረት ራሳቸውን እየነቀነቁ መጡ፡፡

አንደኛው ጮክ ብሎ፡ "ምን ትሰራለች ጥንቸል እዚህ ገበያ መሃል? ጉድ አያልቅ" አለ፡፡

አብሮት ያለው በግራ እጁ የያዘውን የተጠበሰ ቡራቡሬ የቡቆሎ እሸት እየጋጠ ይስቃል፡፡

ምን የሚያስቅ ነገር አለው? ጥንቸሏ የእሳትና የጢስ ኳስ ሆና ነበር፡፡ ያስቃል?

ፀሐይ ወደ እነሱ ዞራ ስትናገር አልሰማሁዋቸውም፡፡ ከበረንዳዬ ወርጄ ወደ ልጆቹ ሔድኩ፡፡ እዛው አካባቢ የነበሩት ሰዎች ለመስማት ከበቧቸው፡፡

"እዚህ ሎንቺና ጋ ቤንዚን ፈሰስባት መሰለኝ፡፡ እና በዚያ ዞራ ስትመጣ ሰው ሲጮህባት ተደናገጠራት መሰለኝ በበቆሎ መጥበሻው በኩል ስታልፍ የከሰል ምድጃ ደፋችና እሳት ወደቀባት መሰለኝ፡፡ እሳት እላይዋ ላይ ነዶ ነበር፡፡ ጉድ ነው፡፡ ምን አመጣት በገበያ መሃል?"

"ቢፈርድባት" አለች አንዷ ጥብቆ ሻጭ ራቅ ካለ መደብ (አስገራሚ ጆሮ አላት)፡፡



@BOOKALEM

"መጀመሪያ ከወዲያ በዡል እያለች በቅመም ተራ ብትወጣ ይሄ ሁሉ አይደርስባትም"

"ሰው አዋክቧት ነው" አልኩ እኔ::

ፀሐይና ልጆቹ አዩኝ:: ዐይኖቻቸው በንቀት ይሸሹኛል::

"እያየች ለምን እዚህ ትገባለች" አለ አንዱ በእሽት እኛኪ የተመረገ ዝንጉርጉር ጥርሱን ያለአፍረት እያሳየ:: ለእኔ ሳይሆን እኩያዬ ለሚላቸው:: ከብዙ ትልልቅ ሰዎች ጋር ሲጨባበጥ አየዋለሁ:: አበባሉ ግን ከእኔ አይሻልም::

ትቼአቸው ልሄድ  ስል አንድ ሃሳብ መጣልኝ::

"ነፋስ መውጫ ከመቆርቆሯ በፊት ዘመዶቿ እዚህ ይኖሩ ከነበረስ:: ቦታው ሲጀመር የእሷ ከሆነስ?" አልኩ ጮክ ብዬ:: አየሁዋቸው:: ያኔ ብዙ ሰዎች አዩኝ:: ፊታቸው ላይ መገረም ይነበባል::

ገና ደስታ ሳይጀምረኝ: "እስኪ ቀም ነገር ቀም ነገር" አለች ፀሐይ::

በማፈር አንገቴን ደፋሁ:: በዐይኖቼ ቂጥ አባባሏ ሌሎችን ቅር እንዳላሰኘ አየሁ:: በወሬ ሲጠመዱ ድምፄን አጥፍቼ ጉች ካለው ስብሰባቸው ተነጠልኩ::

ግን ልክ ከሆንኩስ? ጥንቸሏ የለመደችው ነገር ካላትስ:: ለመሞት ሆን ብላ ጥንቸሏ የደራ ገበያ መሃል ትገባለች? የሳባት ግዴታ ይኖር ይሆናል:: ወደ እነ ፀሐይ ተመልሼ ሐሳቤን ለመግለጥ ፈለግሁ:: ግን አፍሬአለሁ:: ገና ፊቴ ላይ ቡን ቡን ብሎ የወጣው እመዶ በነፋስ አልፀዳም::

ቢሆንስ?

እግዚአብሄር በመጀመሪያ የፈጠረው መሬትን ነው:: ጉና ተራራ ላይ ሆኖ ንፋስ መውጫን ሲያይ ተደሰተ:: በራሱ ጥበብ ተደሰተ:: ዘንባባውን፣ ኢጋሙን፣ ሾላውን፣ እንጆሪውን፣ እንክዩን፣ ቀጋውን፣ እንደ ጠበል የሚያደርገውን ምንጭና ወንዝ ሲያይ:

"ለምን አንድ በዚህ መሃል የሚሽሎኮሎክ በሲሳዬ የሚደሰት ፍጡር አልሰራም" ብሎ ጭቃ አድቦለቦለና እፍ ሲለው ጥንቸል ሆነ:: የነፋስ መውጫ የመጀመሪያው ፍጡር ጥንቸል ነበር:: ሰውን የሰራው በመጨረሻ ነው:: ደክሞት ዞር እንዳለበት:: የነበረበትን ሁኔታ ረስቶ ጭቃ አድቦለቦለና: "እምሳሌ ሁን" አለው:: የዞረበት ሰው ተፈጠረ::

ታዲያ ግን የመቅደም የመቅደም ቦታው የጥንቸል አይሆንም? ስለ ጥንቸልም ይሁን ስለ ሌላ ብዙ ነገር ባላውቅም (እንኳን ስለጥንቸል ስለአሳደጉኝ ዝንቦች የረባ ነገር አውቅ ነበርን?) ጥያቄዬ ቢሰማ ብዙ ነበር:: ግን ይሰማልና::



@BOOKALEM

በፀሐይ ነገር ተበሳጭቼ ናና ከረሜላ ልገዛ ወደ በረንዳው ተመለስኩ:: ሱቅ ስገባ ነጋዴው እንደለመደው የናና ቁጥር አልጠየቀኝም:: ስለጥንቸሏ ጉድ ያወራል::

"የምትነድ ጥንቸል? የማያሳየን ነገር የለም"

"አበሳጭተናት ነው" አልኩኝ::

"የዱባለ ልጅ አይደለህ:: እንደ አባትህ ወሬ ታውቃለህ:: ለትምህርትህ በርታ ብትል አንተ ጉደኛ ነበር የሚወጣህ" አለ ወደ ናናው ከረሜላ የላስቲክ ቀረጢት እያመራ::

ከጀርባው ሳየው የተቆጣጠረ ሳሁጫ ፀጉሩን ከዮት እንደፈለሱ ባልታወቁ የአቧራ ብናኞች ሞልቶ........ያቺ ሴት ልጁን ያቺ ሊባኖስን አስተምራታለሁ ይላል እንጂ የጫጉላዋን ፈተና እንደማታልፍ ያልተረዳ መሆኑን ሳውቅ......አሳዘነኝ:: ይለፋል እንጂ ደሞም እንደ ልጅ አድርጎኝ ሲቃለደኝ የእሱ ሕይወት በጥቂት የተሰረቁ ሳንቲሞች በዚያች ስከንድ ከምገዛቸው ናና ከረሜላዎች እንደማይበልጥ ሳውቅ አሳዘነኝ:: ኮረዳ ሊባኖስም ተማሪ ከአስተማሪ ሲቀባበላት ከአንዱ ጠፍር አልጋ ወደ ሌላው ጠፍር አልጋ ስትወድቅ ሳንቲሜን ሊቀበል የዘረጋው እጁ መሐል ለዚህ ለአባቷ የሚቀርለት ለፍቶ ያተረፋቸው ሳንቲሞቹና እነሱን ከቧቸው የተቀመጠው ንፁሕ የነፋስ መውጫ አየር እንደሆነ አያውቅም:: ሒያጅ ሊባኖስ እግሯ በተቀደደ መነጥርዋ የምታየው ሰላ እምሮት የሚያለክልክ ወንድ እንጂ ዕውቀት፣ ንግድ፣ ሥራና ስልጣኔ አለመሆኑን ሲያውቀው.......ያኔ ይሄ የተጠቀለለ አመድ የታጨቀበት አሻራ ፀጉሩን ይነጫል::

እስከዚያ ካልረገፈ::

ጆሮ ለባለቤቱ ይርቃል እንጂ እኔ ባቀርብለት ኖሮ: "ስማ! ጋሼ ሰማህ? ጥንቸሏን ለቀቅ ሊባኖስን ጠበቅ" እለው ነበር::

አንድ ናና እደረቀ አፌ አስገብቼ ከሱቅ ስወጣ እነዚያ ሁለት ጎረምሶችና ፀሐይ ሲላፉ አየሁ:: ገበያ መሃል ዐይን አውጥተው ይላፋሉ:: እሷ ጀንዲዎቿ ዙሪያ ስትዞር አንዱ ጅል ጎረምሳ ማኅበሱ ሳይሆን ይቀራል ቀሰስተኛ ቂጧ ላይ አፍጦ አፉን ከፍቶ ይከተላታል:: ሁለተኛው ጎረምሳ ያላለቀ ቦቆሉ እሸቱን እየነጨ ፀሐይ ኩርሲ ላይ ተቀምጧል::

በዚያ ባሉበት በኩል ማለፍ ስጀምር ተቀማጩ ጎረምሳ: "ዕውነት እናትሽ ጉራዛ የሚያድኑት በወንጭፍ ነው?" አለና ጠየቃት::

ልትመልስለት ስትቆም እየተከተላት ይሮጥ የነበረው ልጅ የውሸቱን ተላተማትና ተበተነበሱ መቆም እንዳልቻለ ሁሉ እንደ ጅል እየሳቀ አረግራጊ ስጋዋን ተደገፋት:: እኔስ ነጥሮ ጉና የሚገባ መሰሉኝ ነበር:: ዞር ብላ ከደረቷ ልታርቀው ገፋችው:: ጠበብ ባለ ቀሚስ የተያዙት ታላላቅ ጡቶቿ ተሰብስበው ወደ አገጯ ተጠጉ:: አየር የተሞሉ ፓስቴዎች



@BOOKALEM

ይመስላሉ:: የጉልት ሴቶች በማፈር አፎቻቸውን ይይዛሉ:: ልጁ ለእሱ በረቀቀ (ተመልካቾች ግን ነጥሮ በገባን ግብብ) ሰፊ ወገቧ ሊያቅፈው ያጣጥር ነበር::

ከልጁ ልፊያ ለመሸሽ እየታገለች: "በደንብ ነዋ" አለች::

"ይሆቺ ባል እንደሌላት ከአሁኑ ተረጋግጧል" አለ በአጠገቤ ቀስ እያለ የሚራመድ ጠላ የሚተነፍስ አንድ አዳናቂ:: አለፍኩት::

የፀሐይ እናት በወንጭፍ አደን ማደን ገረመኝ::

በወንጭፍ? አስገራሚ ነው::

ራቅ ካልኩ በሁዋላ ፀሐይን ከእነ ጉዋደኞቿ ዞር ብዬ አየሁዋቸው::

ሁሉም የሚያስፈራ፤ እኔን ያልገባኝ ቅልጥፍና ያላቸው መሰለኝ::

የጥንቸሏን ነገር ግን እኔ ልክ ነበርኩ::

በመጀመሪያ እሷ ነበረች::



@BOOKALEM

# ዝንቦች ያነጥሳሉ?

ስለ ነፍሳት ሳይንስ ስንማር አስተማሪያችን ጋሼ ዳንኤል ትልቅ የዝንብ ስዕል ግድግዳ ላይ ለጥፎ በእንጨት እየጠቆመ ስለአካሏ ሲያወራን ሲያስረዳን የሰማሁት ዝርዝር ተሰባስቦ ለጥቂት ሰከንዶች ዝንቦች ሰው መሰል ፍጡራን መሰሉኝ:: ከመሐል ገብቶን እንደሆን ሊፈትሽን አስተማሪያችን መጠቆሚያ ዘንጉን ሲሰበስብ እጄን ወደ ላይ ሰቀልኩና እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት:

"ጋሼ ዳንኤል ዝንቦች ያነጥሳሉ?"



@BOOKALEM

# እንጢቅ ዙፋን

እንዳንድ ጊዜ ከጉብኝታዬ ወደ ቤቴ ስመለስ ወደ ምዕራብ የሚያቀናውን ዋናውን ምንገድ ይዤ እለፍ እልና ወደ ቀኝ ከመታጠፍ ይልቅ፡ እዚያው ገቢያው መሃል ከላይ የእንጢቆ ፉጨት በሚፈልቅበት በኩል እወጣና ትንሽ ሄጄ ወደ ግራ እታጠፋለሁ:: የቤቴ (?) አቀማመጥ (4) ከተለያየ አቅጣጫ በተመሳሳይ የጊዜ ዕርቀት ላይ ስላለ ዘግይቶ መድረስ አያስፈራኝም (እስጨንቆኝ እንደሚያውቅ ሁሉ):: ከዚያ በሁዋላ ቤቴ ለመድረስ ቢወስድብኝ አምስት ደቂቃ ነበር:: በጣም በሚያማምሩ የምሽት ቀናት፣ ማንም እንዲያ እንደሆን በሚገባው ዕለት፣ በተለይ ሰማይ እንደ ኑግ ጠቁሮ ከዋክብት እንደ ሱፍ ተረጭተውበት በጠራ አየር ተሽሞንሙኜ፣ ባዶ እግሮቼም ከቀኑ በተረፈው ሙቀት ለስ ያሉ ድንጋዮች እየረገጡ ሲያልፉ፡ እንደ ቀጠሮ ሁሉ የእንጢቆ ዙፋን ፉጨት ከክለል ቤቱ በረንዳ ላይ፣ በሱቆች በረንዳ ላይ፣ በገበያው ባዶ ስፍራ ላይ እንደ ገሞራ እሳት እየፈሰሰ ይመጣ ነበር:: የእንጢቆ ዙፋን ስም *ዙፋን* ነው:: ስለእሱ አስቂኝ ነው የተባለ ነገር ይወራ ነበር:: ዙፋን የመጣው ከላይ ወረዳ ነበር ጎለልታ(5) ከተባለ ተራራ ስር:: የዚህ ሰው ታሪክ እንደ ሰማሁት እንዲህ ነው:......ከአንዲት ጋለሞታ ፍቅር ይይዘዋል:: ባለትዳር ቢሆንም እንኳን ዐይኖቹን በጨው አጥቦ (ይሄ አባባል አባቴ ከሚናገረው የወሰድኩት ነው) ነጋ ጠባ እየተመላለሰ አስቸገራት:: ሚስቱ በዚህ ነገር ሠላም ብታጣ ጋለሞታዋን ፊት ለፊት ሄዳ፡ "ባሌን ማባለግ ካላቆምሽ በሕይወትሽ እንደፈረድሽ ቁጠሪው" ብላ ታስፈራራታለች::

ከዕለታት አንድ ቀን ዙፋን ወደ አፈቀራት ጋለሞታ ተመልሶ ሲመጣ ጊዜውን አጥንታ ከሌላ ተፎካካሪ ወንድ ጋር ቤትዋ ተቀምጣ ጠበቀችው:: ግራ መጋባቱ ቢያሳዝናትም ሚስቱ እንዳስፈራራቻት ሳትነግረው ወደ ጓሮ ጎትታ ትወስደውና እንዲህ ትለዋለች፡

"ስማህ ዙፋን አሁን ሌላ ወዳጅ አለኝ:: አንተ ጥሩ ሰው ነህ:: ካለህ ሁሉ እያካፈልከኝ ሚስትህን እንኳን ዘንግተህ አብረኸኝ ብዙ ጊዜ ተጫዋወትን:: አሁን ታዲያ ምን ልበልህ የምወደው ሰው አለኝ:: የምወደው ሰው ደሞ መልካም የጥርስ ፍንጭት ያለው ነው:: የጥርስ ፍንጭት አንጀቴ የሚገባ ነገር ነው:: መልካም ጥርስ ቢኖርህም የኔ ወለላ ፍንጭት የለህም:: ፍንጭት ነው አንጀቴ የሚገባው:: ልቤ የሚፈርሰው ለፍንጭት ነው"

ዙፋን ተብሰጭቶ እቆመኝበት ትቷት ይሄዳል:: ጥቂት ቀናት እንደ ቆየ ከቤትዮዋ መለያየቱ እየከበደው መጣና መላ ፈለገ:: አሰበ አሰበና ሰው ጠያየቆ አዲስአባ ወጣ:: ከአዲስአባ ሲመለስ ፍንጭት ነበር:: ሲስቅ ከርቀት ወፍራም የኑግ ዘር መስሉ የሚታይ አገር የመሰከረለት ፍንጭት ሆነ:: ሲባል:: ግን እሱ ያሰበው አልሆነም:: እሱ ከአዲስአባ ሲመለስ



@BOOKALEM

ጋለሞታዋ አግብታ ያገባችውም ወንድ ፍንጭት የሚባል ነገር እንደሌለው አዩ:: ሁሉ ነገር የተገለጠለት እሱን ለመሸሽ ጋለሞታዋ የሰራችው ተንኮል በመንደሩ ሲነዛና በድብቅ መሳቂያ መሆኑን ሲያውቀው ነበር:: መጃጃሉን እንደ ውርደት ቆጥሮት ከብቱንና መሬቱን ሸጦ ቀበሌውን ለቆ ወደ ንፋስ መውጫ ተሰደደ:: ንፋስ መውጫ ገብቶ ብዙ ሳይቆይ አንጉል የተቀደደው ጥርሱ ንፋስ እያስገባ ጉሮሮውና ዕንጥሉ በሽተኛ ሆነ:: እነዚህን የአንገት ብልቶቹን ከቀዝቃዛ ንፋስና ከምች ለመጋረድ እስከ አፍንጫው ድልድይ ድረስ ጋቢውን መከናነብ ጀመረ ይላሉ::

ከርሞ ከርሞ ከተማው መሃል ትንሽ ቤት ተከራይቶ የከሰል ንግድ ጀመረ:: ይሄ ስራው መጠበቂያ ይመስለኝ ነበር......የሚያልፍ ዝናብ እንዳይመታው......ጥቂትም ልክ ነበርኩ:: እኔም ይሁን ሌላ ሰው ፊቱን አይቼአለሁ ብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገር የለም:: አንዲትም ቀን ጋቢውን ከዐይኑ ስር ዝቅ ያደረገበት ጊዜ የለም ይባላል:: በፊት በፊት አጥር ስር በጨለማ ተጋርጄ ተሰርቄ ለማየት የሞከርኩበት ጊዜ ነበር:: አልቀናኝም:: ከሰል ለማክሰል መጥረቢያውንና ዶማውን በትከሻው ይዞ ወደ ቆላ ሲወርድ ፊቱ ላይ ካሉት ብልቶቹ የሚታዩት ዐይኖቹ ብቻ ነበሩ:: ብዙ ጊዜ ግራ የሚገባኝ ግን ይሄን የመሰለ ፍንጭት ያለው ሰው እንዲህ የሚያምር ፉጨት ማውጣቱ ነበር:: የሚገርመውም ሲያፏጭ ጋቢውን ከፊቱ ላይ ለአመል እንኳን ወደ ታች ሸርተት አያደርግም:: የመጣ ሰሞን የገበያ የገበያ ዕለት በየጠላ ቤት ተሽፋፍኖ እየዞረ በዚያ በትልቅ ፍንጭቱ ቀዳዳ የተደነቁ እረኞችን ዋሽንት የሚያስቀና የፉጨት ድምፅ እያወጣ ሰውን ያስደምመው ነበር:: ይሄን ሲያደርግ ባላየውም ሰምቻዋለሁ:: ዐይኖቹ ብቻ እየታዩ መልካም ዜማ ማውጣቱ አያስገርምምን? ከዚያ በፊት ዋናው ከተማ እያለ መጠጥ ቤትና ገበያ መሃል ምራቁን ጢቅ ማድረግ ትርዕይት ያሳይ ነበር አሉ:: «እንጢቆ» ያሉት በዚህ ምክንያት ነበር:: ይሄን የመጠጥ ቤትና የገበያ ትዕይንት ግን አላየሁም:: ካልሆነ ታዲያ «እንጢቆ ዙፋን!» ሲባል ለምን «አቤት!» ይላል? እየተኀተተ እዚያች ከተማ ገብቶ ጢቅ ሲያደርግ ባላየውም ብዙዎች ያዩት ሰዎች በጣም አስገራሚ እንደሆነ ያስወራሉ:: ተክለወልድ የተባለ እዚያ ላይኛው ቡና ቤት አልቤርጎ ውስጥ የሚሰራ አልጋ አከራይ ወዲያ ወዲህ ከሚልበት የሆቴሉ ከፍታ ወደ ታች ወደ ከሰሉ ቤት ሲያይ ዙፋን ግራና ቀኝ ተገላምጦ ጢቅ አርጎ የተፋውን አይቼአለሁ ይል ነበር:: (ዙፋን ምን አገላመጠው?) ይሄም የሆነው እንደ ተክለወልድ አባባል ከምሽቱ አስራሁለት ሰዓት አካባቢ ነበር::

"እንዴት ይታይሃል ከዚያ ዕርቀት? ደሞ ማታ" ሲሉት::

"ያላየ የጥሀ" አለና ለነሙስጠፋ ቡጢውን አሳያቸውና "ይሄን የሚያክል ምራቅ አይታይም እንዴ? ታዲያ ጋቢውን ከአፉ ላይ ሸተት አደረገና......መጀመሪያ ዞር ዞር ብሎ

ዐይቶ ወደ ላይ እንጋጦ ቢለቀው መድሃኒያለምን ደነገጥሁ። ትራስ የሚያክል ምራቅ ካፉ እንዴት አዳልጦ እንደወጣለት እግዜር ይወቅ እንጋጦ ወደ ፀሓይ መውጫ ቢተፋ፣ ምንገድ አልፎ የአቶ መርሳት ቤት ግድግዳ ላይ እንደ ነጭ ጭቃ ተም ብሎ ሲመረግ እሰማዋለሁ። ሰው ለሴት ብሎ እንዲህ የሚያደርግ ጉድ ውስጥ ይገባል?" አለ።

አንዳንዴ ወደ ቤት መሄድ ካላሰኘኝና ከዘገየሁ በተቀማጠለው ከፊይ በመሰለው ምሽት ለመደሰት እጉብታዬ ላይ መረጋጋትን ተከናንቤ እቀመጣለሁ። የዙፋን ፉጨት ከከሰል ቤቱ ለስስ ባለ ምት ይመጣል። ዳበሳ ነገር ነበር። ከዚህ ድምፅ ዝርባ የሆነ መውጫ የምትፈልግ ነፍስ ያለች ይመስል ነበር። ቀስ በቀስ እየጎላች፣ የመስሚያዋ ከፈፍ እየሰፋ፣ ጉልህነትዋ ሲጨምር ዙፋን ያቺን ፉጨት ፊት ፊቱ እየነዳ ከቤቱ ይወጣና የማይቀየር ኩታውን እስከ አፍንጫው ተከናንቦ በቀስታ እያዘገመ የከተማውን ዋናውን ምንገድ ተከትሎ ያቺ አስደናቂ ፉጨቱን እያንከለከለ ወደ ምስራቅ ይወጣል። እያዜመ ሲያልፈኝ በእኔ አቅጣጫ ገልመጥ ብሎ ያየኝና ፉጨቱን ላፍታ ውጦ:

"እጅሬው!!" ይለኛል። እጅሬው።

'መሽቷል አትገባም? ቤትም የለህ?' ብሎ እንደ ሌሎች ሎሌዎች(6) የውሽት አሳቢነት ወርውሮልኝ አያውቅም። ታዲያ ወደሚሄድበት ሄዶ እኩል ሰዓት ቆይቶ ይመለሳል።

ስለ ጥርሱ ለማወቅ የምታሳክክ ጉጉት ገፋፍታኝ በቤቱ ደጃፍ ሁለት ሦስት ቀን እንደ ባለጉዳይ አልፈአለሁ። በቤቱ በር ግራና ቀኝ ከውጭ በኩል ባሪያ ድረስ የሚደርሱ ከሰል የተሞሉ ጆንያዎች ነበሩ። እውስጥ አግዳሚ ወንበር ላይ እስከ አፍንጫው ተከናንቦ በከሰል የቆሸሹ እጆቹን አንቀርፎ በር ገርበብ አድርጎ አይቼዋለሁ። አዲስ የተቆላ ቡና ሽቶኛል። ተራነቱ ሚስጢር ይመስለኝ ነበር። እንደዚያ ከቆሸሸ የእንገት ልብስ ጀርባ ከማይታዩ ከንፈሮችና ጥርሶች አስገራሚ ፉጨት ቢወጣም ሁኔታው ሁሉ እንደ ማንም ሰው ነበር። ሁለቱንም ቀን እሱን ለማየት ስሄድ የሸተተኝ ትኩስ ቡና ነበር።

ትፋት ግን አላየሁም።

አልቀናኝ ይሆን እንደ አልጋ እንጣፊው?

# ሥራ

'እናቴ' አንድ ቀን የሰጠችኝ ዕንቁላል ፍርፍርና ቅንጬ በየሄድኩበት የሚከተለኝ ጣፋጭ ትዝታ ሆነ:: ያረከሰው ዱላም አብሮት ቢመጣም የማስበው የማልመው ነገር ሁሉ በትልቅ ቁና የተሰራ ዕንቁላል ፍርፍር ውስጥ አፌን በልቅጬ እንደዋናተኛ መግባት ነበር::

ዕንቁላል ፍርፍሮች ከየት ይመጣሉ?

ከዕንቁላል ፍርፍር በፊት ዕንቁላል አለ:: እንቁላሎች የሚገኙት ደ'ሞ ከዶሮዎች ነው:: ጉብታዬ ላይ ተቀምጬ ቀድሞ እየተንጕራደዱ ከገበያ የተረፈ ጥሬ የሚለቅሙ ዶሮዎችን አላይም ነበር:: ባያቸውም ልብ አልላቸውም ነበር:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ግን ረቂቅ እንስሳት ሆነው ታዩኝ:: በነዚህ ላባ በተሸፈኑ ገላቸው ውስጥ ፍርፍር የሚሆኑ ትናንሽ እንቁላሎች ተሸክመው እንደሚዞሩ ሳውቅ ታላቅ ሆነው ታዩኝ:: ከአንበሳ የበለጠ ታላቅ፣ ከአውራሪስ የበለጠ ታላቅ ፣ ከዝሆን የበለጠ ታላቅ፣ ከንጉሣችን የበለጠ ታላቅ:: ግን እንዲህ ቀን ተለቀው የሚዞሩ ዶሮዎች ማታ የሚገቡበት አለ:: በእያንዳንዱ ዶሮ ኩታት ላይ በማይታይ ቀለም የባለቤቶቻቸው ስሞች ተፅፈዋል:: እያንዳንዱ ዶሮ ባለቤት አለው::

ባለዶሮዎቹ እንዴት ባለ ዶሮ ሆኑ?

ስለገዙት:: ዶሮ ይገዛል ገበያ ውስጥ ይገዛል......ገበሬዎች ዘንድ ይገዛል በየቦታው የሚጣፍጥ እንቁላል የሚወልዱ ዶሮዎች ይሸጣሉ:: እነዚህን አስደናቂ በራሪ እንስሳት ለመግዛት ግን ገንዘብ ያስፈልጋል:: ገንዘብ እኔ ሳልሆን አባቴ ነበር ያለው::

አባቴ እንዴት ገንዘብ ያገኛል?

ስለሚሰራ:: የማይረባ ሥራ ቢሆንም ይሰራል:: አሥር ሳንቲም፣ አሥራ አምስት ሳንቲም፣ ሥሙኒ ብር ሰብስቦ ቤቱ ይገባና ሚስቱን ዶሮና እንቁላል እንድትገዛ ይነግራታል:: ዶሮዎችን ወደ ዶሮ ወጥ ለውጣ ዕንቁላሎቹን ፍርፍር አድርጋ ትሰጠዋለች::

ከዚያስ?

ከዚያ ገንዘቡ ስለሚያልቅ ለእኔ የሚደርሰኝ አንዳንዴ የተቆላ ደረቅ ሽንብራ፣ አንዳንዴ በውሐና በጨው የተነፈረ ባቄላ::

አልፎ አልፎ የዕንቁላል ፍርፍርና የቅንጬ ጉዳይ ትዝ ይለኝና ሲመሽ ጉብታዬ ላይ ተቀምጬ ሰላ እንዳቃጠለው ተኩላ ወደ ጨረቃ አንጋጥጥና የዚያን ቀን የፍርፍርና የቅንጬ ትዝታ በአፍንጫዬ በምላሴ ልጠራ እፈልግ ነበር:: ዕንቁላሎች ሻይ ቤት ውስጥ ሲሸጡ አይቻለሁ:: የተቀቀሉ ናቸው:: የተቀቀሉ ዕንቁላሎች እስከረካ ባይሆንም ብዙ ጊዜ በልቻለሁ::



@BOOKALEM

የተፈረፈረ ግን አንድ ቀን ነበር:: እንጀራ እናቴ ቲያትር የሰራችብኝ ለት:: ከዚያ በሁዋላ አይቼ አላውቅም::

ከዚያች ቀን ወዲህ ከመሸ በሁዋላ ጠጅ ለመግዛት መላኩን ስላልታመንኩ ብዙ ጊዜ ገና ጀምበር ሲታዘቀዝቅ የምትላከው እህቴ ናት:: የጠፋው ሳንቲም ቢረሳም (በተረታቸው ሳልረሳ) የሰመጠዘበት ቀዳዳ ሐጂ ቆፍሬ ልወስዳቸው ብሞክር አልቻልኩም:: መቸም ካልቀና አልቀናም ነው::

ከመሐል የዕንቁላል ፍርፍሬን አምሮት ለማርካት ሥራ መያዝ ፈለግሁ:: ሳስበው የቀረኝ እሱ ብቻ ይመስለኛል:: ዕንቁላል ፍርፍር መብላት የሚችሉት ሥራ የያዙ ብቻ ናቸው:: የትምህርቱ ነገር አልሆነልኝም:: ያለዞብትን ክፍል ደግሜ ወድቄአለሁ:: "ለምን ወደቅህ?" ብሎ የጠየቀኝ አልነበረም:: ብዙ ጊዜ አባቴ ለምን እንደ ወለደኝ ማሰቤ አልቀረም:: ብዙ ጊዜ ማታ ሬዲዮ ከፍቶ ከሚስቱ ጋር እያወራ ምን አልባት ጠርቶኝ እግሩ መሐል ይዞኝ እራሴን እየዳበሰ 'ትምህርቱስ?' ቢለኝ እወድ ነበር:: ያለሁ ግን አይመስለውም:: አንዳንዴ ለሜወታ የሚስቱን ቂጥ በአልኮላም እጁ ጆፍ ሲያደርግ ምን አለበት የእኔን እጅ ይዞ ተም ተም ባደረገኝ እላለሁ:: ያለሁ ግን አይመስለውም::

ወፍራም እእ አለኝ::

ዕድሜዋ 44 የሆነ ወፍራም የእንጀራ እናት አለኝ::

በምቾት ጉንጮቿ ዕጌሬዳ የሚመስሉ::

ውሽማ የሚፈልጉ የትኞቹ ወንዳወንዶች ናቸው ተንጎራደው መጥተው ከአባቴ የሚያፋቱልኝ.......ከዕንቁላል ፍርፍር እኩል ነፍሴን የከደከዳት ሌላው ምኞት.......

አንድ ቀን ማታ ከጉብታዬ ተነሳሁና ፊት ለፊቴ ሁለቱንም በሮች ግራና ቀኝ ከፍቶ ወደ ቆመው ሻይ ቤት ሄድኩ (ለምን ሁለቱንም በሮች ግራና ቀኝ ይከፍታሉ? ወፍራሞች እንኳን አይደለን፣ ግራና ቀኝ ሦስት ሆነን እጅ ለእጅ ተያይዘን ነበር የምንገባው?):: በሩ ደፍ ላይ ቆምኩና ግራ ቀኝ ውስጥ ማን እንዳለ አየሁ:: ለቅፅበት ሰዎች ቤታቸው ውስጥ ባስቴ ይሰራሉ እንዴ? ብዬ እራሴን ጠየቅሁ:: ባስቴና ዳቦ ማጉሪያ ቁምሳጥኑን ተደግፎ ሙስጠፋ ጥርሱን እየፋቀ ቆሞአል:: ሙስጠፋ የሚያስፈራ ልጅ አይደለም:: ጥርሶቹ ነጫጭ ነበሩ:: መልከም ሳቂ ነበር::

ጠጋ አልኩና በጏጏ እናም ጉጉቱ ባፈጠነው ስሜት

"ሙስጠፋ! *ሥራ መሥራት* እፈልጋለሁ" አልኩት::

መጀመሪያ በደንብ አልሰማኝም መሰለኝ ጥርሱን እየፋቀ ወደ ውጭ አየና፦

"ምን?" አለኝ



@BOOKALEM

"ለመስራት እፈልጋለሁ ተቀጥሬ ሥራ መሥራት እፈልጋለሁ" አልኩት።

"ምን ጐደለብህ?" አለኝ እንደ ቀላል ነገር።

"ምን?" አልኩት

"ምን ጐደለብህ?......አባትህ ሰው እየመሰጠ ካሽ አለው መአት አለው"

"የራሱ ገንዘብ ነው የእኔ አይደለም"

ወደቆምኩበት መጥቶ ትከሻዬን ያዘና "ለአንተ እዚህ ሥራ ብሰጥህ ዱባለ ይለቀኛል መሰለህ?"

የአባቴ ስም ድሮ በጣም ድሮ ቤታችን ለአንድ ቀን ብቻ ደርሶ፣ ተመልሶ ግን እንዳልመጣ የዘመድ ሥም ሰማሁት። ተበሳጨሁ።

"እኔ ገንዘብ እፈልጋለሁ"

"ለምን እኩ? ቤተሰብህ ጋ ትኖራለህ ልጅ ነህ"

የግል ሚስጢሬን ልነግረው ፈለግሁ።

"የሚሠራ ሥራ አለህ ግን?"

"ሰው እፈልጋለሁ አንድ አሳላፊ እፈልጋለሁ የማያታልል አራዳ የሆነ ግን አንተ ልጅ ነህ ከአባትህ ጋር መጣላት አልፈልግም። ነገረኛ ነው። በተረቡ ይውረድብኝ?"

"እርሳው"

"ምኑን?"

"አባቴን እርሳው"

"እዚህ ስትሰራ ቢያይህ ምን ይላል?"

"ምን አገባው" አልኩት።

"ዝም የሚል ሰው እኮ ነገረኛ ነው...የሚያስበው አይታወቅም።"

"ጣ" አልኩ በምላሴ......"ጣ!" ማድረግ ደስ ይለኛል። የአራዶች ነበር። በተለይ ሲበሽቁ የሚያደርጉት።

"ሰው ማስቀየም አላውቅም......የደበቅኸኝ ነገር አለ...... ዕውነቱን ንገረኝ የደበቅኸኝ ነገር አለ"

ምክንያቴን ሌላ ሰው ቢሰማው የሚያስቅ መሰለኝ። ቢሆንም ሙስጠፋ ጥሩ ልጅ ነበር። ለምሳሌ ደንበኞቹ መግተ ካጡ እንዳይራቡ ብሎ በነፃ ወይ በዱቤ የሚሰጥ ነበር። ሁሉ ሰው



@BOOKALEM

'ሙስጤ ሙስጤ' ይለዋል:: እኔም እንደ ትልልቆቹ «ሙስጤ» ልለው ፈለግሁ:: ሙስጤ ሚስጥሬን እንደምነግረው አውቋል መሰለኝ ወደ እሱ ጐተት አድርጐ ግራ ጆሮውን ወደ እኔ አቀረበ:: አራት ቃላቶች ከአፌ ውስጥ እንደ ቅቤ ብዦች እየተንከባለሉ ወጡ (እነዚህ አራት ቃላቶች "እንቆላል ፍርፍር መብላት እፈልጋለሁ" የተባሉት ነበሩ):: አንዳንዴ ለመናገር ያሰብነው ነገር የአካላችንን ፈቃድ ሳይጠይቅ እራሱን ወደ ፊደል፣ ወደ ድምፅ ለውጦ በራሱ ፈቃድ ፊታችን ላይ ባለ ቀዳዳ (ያ «አፍ» በተባለ) እንደሚወጣ:: ራቢ አስጠሳኝ::

ሙስጠፋ መጀመሪያ ፊቱ የተገረመ መሰለና ቶሎ ብሎ......"ቀላል ነገር ነው ይኼ.......ቀላል ነው" አለ::

ፊቴ በራ:: ሥራውን ያገኘሁ መሰለኝ::

ቀጠለ ሙስጤ: "እኔ ዛሬ ፍርፍር እሰጥሃለሁ አንድ ነገር ታደርግልኛለህ...ሥራ ግን ልቀጥርህ አልችልም...አባትህ እ አባትህ ፀጉሬን የምስተካከለው እሱ ዘንድ ነው አባትህ የሚያስተካክል መስሎ በቂም ጆሮዬን ቢቆርጠኝስ...አያስቅም ተክለ ወልድ ቤት ሥራ አለልህ...ገብረ ሚካኤል ቤት አሳላፊ ይፈልጋሉ የሆነ ትንንሽ ነገር የሚሰራ"

ሁሉን ነገር አልወደድኩትም:: ንግግራችን ከማለቁ በፊት እኔ ምን ለማድረግ እንደምፈልግ ልጠይቀው አሰብኩ:: ብድሬን ለመመለስ:: እጆቼን ከኪሴ አላወጣሁም

"ምን ላደርግልህ ትፈልጋለህ?" አልኩት::

"ጠጋ በል ያቺ ወፍራም ልጅ እህትህ ናት አይደል? እ"

በአሉታ ራሴን ነቀነቅሁ::

"ማለቴ ግማሽ እህትህ"

ራሴን ነቀነቅሁ

"አይደለችም እንዴ? እንጀራ እህትህ ይባላል?"

ራሴን በአዎንታ ነቀነቅሁ:: ወደ ዋናው ጉዳይ ለመምጣት ምን እንዳስፈራው አላውቅም::

"ቆንጆ ናት"

"ወፍራም ናት" አልኩት

"ወፍራም ቆንጆ ናት...አንድ መልዕክት ትሰጥልኛለህ?"

"እንተስ?"

"እንቁላል ፍርፍር የፈለከውን ያህል ትበላለህ...አዝልሃለሁ"



@BOOKALEM

"ሽንኩርት ያለው እንቁላል"

"ከፈለግህ በዘይት ከፈለግህ በቅቤ በሽንኩርት፣ በቃሪያ፣ በቲማቲም በፈለከው ዐይነት"

"በቅቤ አድርገው" አልኩ::

ይኼ ሁሉ አለ እንዴ? አልኩ በልቤ:: ትቶኝ ማድ ቤት ገባ::

"አሰፋ የአራት ዕንቁላል ፍርፍር በቅቤ...ሽንኩርቱ የበሰለ" ዞር ብሎ እያየ ጠቀሰኝ:: እጄን ከኪሴ ሳላወጣ ፈገግ አልኩ::

ይህን ሳደርግ ከእግዚያብሔር ጀምሮ የሚያነበውን ሰው ጨምሮ ሊገርማቸው ይችላል:: የሚያስገርም አይደለም:: እንደ ንግድ ነው:: ገበያ ሔደን ሳንቲም ሰጥተን ጌሾ እንደምንቀበል ዐይነት ነው:: ማንም ዘራፊ አይደለም:: የለም:: ሙስጠፋ ነው:: ሙስጠፋ ለእኔ የሻይ ቤት ባለቤት ብቻ ሳይሆን የአራዳ ልጅ ነበር:: ሙስጠፋ አራዳ ነው:: አንድ ሰው እሥላም ሆኖ ክርስቲያን ሴት ቢወድ ምን ማድረግ ይችላል? ተማሪ ቢሆን ኖሮ ልጅቷ ትምህርት ቤት ሰው ሊገባውና፣ ሊያውቅ በማይችልበት መልክ አብሮአት የሚያጠናና የሚማር እየመሰለ ሊጠብሳት ይችል ነበር፡ ግን ሻይ ቤት ንግድ ሥራው ላይ እየዋለ እንዴት ሊያገኛት ይችላል? ቢያገኛትስ አያስጠረጥረውም? እሱም እሷም የወሬና የቅጣት አደጋ አያጋጥማቸውም? እሱ ሊረዳኝ እንደሞከረ እኔም ልረዳው ብሞክር መጥፎ አልነበረም::

እሱ ባንኩኒው ጀርባ ሆኖ ደብዳቤ ሲጭር ለእኔ ሰሐን የሞላ ፍርፍርና ዳቦ መጥቶልኝ መብላት ጀመርኩ:: እግዜአብሔር ቤት ገነት ዝቡ ሲባል እንቁላል ፍርፍር እንደመብላት ነው:: ገነት ሰዎች ሲገቡ እንደ አዲስ ሆነው መቀበያ የሚዘጋጅላቸው ምግብ እንቁላል ፍርፍር በነጭ ዳቦ ይመስለኝ ነበር::

"መዝገብ ሻይ ትፈልጊያለሽ ወይስ ዕርጎ" አለኝ ሙስጠፋ:: ሙስጤ አራዳ ነው:: አራዳ ሲሰጥ እንደ ልምድ ነው:: አራዳ አይግደረደርም::

"ዕርጎ" አልኩ::

ጨዋ ልጅነት ያልገዛውን እንጀራ ባለጌነት እያንጋጋ ያመጣዋል ብሎ የሚያስብ አይጠፋም:: ማንም እንዲህ ማሰብ የለበትም:: ሰዎች ማሪያምን ለመማጠን ዕጣንና፣ ጧፍ እንደሚሰጡ ሙስጠፋም ለእኔ ዕንቁላል ፍርፍር ቢሰጠኝ ስለቱ ተደርጉ ይቆጠርለት:: እኔ በወፍራሟ እህቴና በሙስጤ ለማኑ መሐል ያለሁ መልአክ ነኝ እጅ መንሻ ያስፈልገኛል::

ሙስጠፋ ደብዳቤውን በፖስታ አድርጉ አመጣና ወጣን:: ጃኬቴ ውስጥ አስገባውና "ለእሷ በእጇ እንድትሰጣት ማንም መስማት የለበትም" አለኝ::

በመስማማት ራሴን ነቀነቅሁ::



@BOOKALEM

"ቆይ" ብሎኝ ተመልሶ ገባና ባንኩኒው ላይ ከተቀመጡ የተቀቀሉ እንቁላሎች እንዷን ወረወረልኝ። ቀለብኳት። ጠቀሰኝ። ሲጠቅስ ይችልበታል። ቤቴ እስከደርስ ድረስ እንደሱ ለመጥቀስ ስለማመድ ነበር። ዐይኔን በዐይኔ ፊቴን በዐይኖቼ ማየት ስለሚያቅተኝ ግን ምን ያህል ትክክል እንደሆንኩ ማወቅ አልቻልኩም። እህቴ እንዳጋጣሚ ከሁለት የጐረቤት ልጃገረዶች ጋር ዳማ ስትጫወት አገኘሁዋት። ሦስቱም ሴቶች እንደ እንግዳ እንደወራሪ አዩኝ። እጄን ከኪሴ ሳላወጣ እህቴን እንደምፈልጋት ነገርኳት። ከሴቶቹ አንዷ ወሰን ነበረች። አቋቋሟ እንደሚያረካት ይገባኛል። የሙስጠፋን ጥቅሻ አንድ ሰጠሁዋት። በዳማ ጠጠር አፏን ዘግታ አንገቷን ሰበረች። የሚያስጠላኝ ሳቅ ተያይዘው ይስቃሉ። ቡፍ። ቡፍ።

'ቡፍ' ሳቅ ነው? ከሳቁ መሳቅ፣ ካልሳቁ ዝም ማለት። ቡፍ ሳቅ አይደለም። አንዳንዴ ጥሩ የሚያስደስት ስሜት የሌላ ተቃራኒ ግን ብዙ አቅም የሌላቸው ስሜቶች እንደማፈር፣ ትዝብት የመሳሰለ ይደረቱበትና 'ቡፍ' ይሆናል። ቡፍ። ያቺን የመሰለች ልጅ......ቡፍ። እህቴ ግን አላለችም። እህቴ ፊቷ ሁልጊዜ ሳቅ ነበር። ጉንጫም ነበረች። እስኪፈነዳ የበላ ፊት። ቡፍ ባትልም ያለች ነበር የምትመስለው። በግራ ኪሴ ውስጥ በምትሞቅ ቅቅል እንቁላል እጫወታለሁ። በቀኝ ኪሴ የያዝኩትን ደብዳቤ እክፍሷ ገብቼ ሰጠሁዋት። ስሜቷን ማየት አልፈለኩም። ምን አገባኝ። ምናልባት መልስ እንዳላት ብዬ ውጭ እጠብቃታለሁ። ዕንቁላሌን እየወረወርኩ እየቀለብኩ።

"በዕንቁላል ትጫወታለህ......ቢፈርጥስ?" አለች ወሰን።

"ተቀቅሏል" አልኩ።

መናገር አልፈለኩም ነበር። አንዳንድ ሴቶች ሲያናግሯቸው ልዩ የሆኑ ይመስላቸዋል። እህቴ ከነደብዳቤዋ መጥታ መጮሁ ጀመረች። ወሰን 'እጮኸለሁ' ብላ ለማስፈራራት መሞከሯን አልረሳም። ይሄ መጮህ ከባድ መሳሪያ ለመሆኑ ሌላ ማረጋገጫ ነበር።

"አንተ ምንድነህ? አቃጣሪ ነህ ምንድነህ?"

ቀና ብዬ አየሁዋት።

"አንተን እኩ ነው እኔ እኔ ሸርሙጣ አይደለሁም መልስለት" ብላ ወረቀቱን ወደእኔ ወረወረች።

ጓደኞቿ በሕብረት አፍጠው ያያሉ። ብዙ ሳልናገር ወረቀቴን ከወደቀበት አንስቼ ዕንቁላሌን እየቀለብኩ ከግቢ ወጣሁ። ሴቶች ጓደኞቿ አፎቻቸውን ገጥመው አንገቶቻቸውን የበለጠ ሰብረው ሲቀመጡ አየሁ። አዘንኩ። እውነቴን ነው አዘንኩ። ደብዳቤ ደረሳትና ምኗ ሸርሙጣ ሆነ። ብዙ ነገሮች አይገቡኝም። ይሆቺ ቂጣም ትርቡት የእንጀራ እህቴ የሰራችው



@BOOKALEM

ነገር ልክ አልነበረም። ሙስጠፋ እንደ ማርያም የብርሃን ውጋጋን እንድታወጣ ጠብቋት ነበር? ጫጫታ በጫጫታ ሆነች። ቢያንስ ዝም አትልም? የሙስጠፋ አባት ሐጂ ናቸው ይባላል። መካ ደርሰው የመጡ። ይኼን እንዳደረገ ቢሰሙና ቢገሉትስ፣ ወይ ሰቀን ቢቀሙትስ ወይም ደስ የማይል የሚያስከፋው ነገር ቢያደርጉት?

መሂጃ ባጣና የማደርገው ነገር ስላሌለኝ ብቻ ከሰው ገለል ብዬ በቸልታ፣ ያለፍላጐቴ እጄ ውስጥ ብቻ ስላለ ደበዳቤውን አነበብኩት።

ለውድ እመቤቴ

ዐይኖቼ ዕንቺን ካዩ ጀምሮ ዕንቅልፍ ዕይወስደኝም። ያማረ ገላሽን ካየሁ ጀምሮ ደኼው እስከ ዛሬ በፍቅርሽ ተነድፌ ዕንቅልፍ ሁሉ ዕንቢ ብሉኛል። ስበላ ስጠጣ የማስበው ዕንቺን ነው። ከንፈሮችሽ ዕንደሳምኢቸው ሁሉ ደናፍቀኛል። ነገ ት/ቤት በረፍ ላይ ሥሩዶን ተቹ ዕጠብቅሻለሁ። ዕንድ ጊዜ ሳቂልኝና ዕነዚህን ዕንቁ ጥርሶችሽን ልያቸው

በፍቅርሽ ያበደው

ሙስጠፋ ስሲ

ፊርማ

(ምን አስፈረመው እስኪ?)

ደብዳቤውን ካነበብኩት በሁዋላ ሙስጠፋን የከዳሁት መሰለኝ። ገላውን ቀዳድጄ እንደትል ልቡ ውስጥ የሰፈርኩ መሰለኝ። በሌላ በኩል ደ'ሞ ደብዳቤው የቂል ይመስላል። እንዳላበደ እርግጠኛ ነበርኩ። የእህቴ ጥርስ ዕንቁ እንዳልሆነ አውቃለሁ። ዕንቁ ውድ ነገር ነው። እንደ ወርቅ ያለ ነገር ነው። የእህቴ ጥርስ ዕንቁ ቢሆን ኖሮ ወይ አባቴ ወይ እንጀራ እናቴ እየነቀሉ ይሸጡበት ነበር።

በመጣሁብት እግሬ ወደ ሙስጠፋ ተመለስኩ። ሻይ ቤቱ በር ስደርስ መግባት ፈራሁ። ገና ያልበላሁትን እንቁላል እንዲነጥቀኝ ስላልፈለግሁ (ሊናደድ ስለሚችል) ኪሴ ውስጥ እንዳለ የዕንቁላሉን ቅርፊት ሰበርኩት። እኔን ገና ሲያየኝ ፊቱ ተለዋወጠ። እየጉተተ ወደ ጓዳ አስገባኝ።

"ምነው?" አለኝ በጉጉት።

የሆነውን ሁሉ ቀለል አድርጌ ነገርኩት።

የሚያምነኝ ሰው ግን የለም። አራዳው ሙስጤ እዚያው ፊት ለፊቴ በልቅሶ ተተረተረ።



@BOOKALEM

# አንዳንድ ዐጀገሬዶች በብርሐን የተከበቡ ናቸው

አንድ ሰው ሌላውን ሰው ለምን ይወዳል?

አንድ ብላቴና አንዲትን ኮረዳ የሚወዳት ለምንድን ነው?

ስለሌሎች ሰዎች አላውቅም:: እኔ ግን ወሰንን የወደድኳት በብርሐን ተከባ ስላየሁዋት ነበር:: ሰዎች ሊያምኑኝ አይችሉም:: ግን በብርሐን ተከባ ስላየሁዋት ነው::

ለመስቀል ለመስቀል የከተማችን ሕዝብ በጠቅላላ ተሰብስቦ ዳመራ የሚያቀጣጥልበት ጉብታ ከከተማው ወጣ ብሎ አለው:: እስላሙ የሙስጠፋ አባት እንኳን ከነቤተሰባቸው ለወሬ ብለው ይመጣሉ:: ሲመሽ አንድና ሁለት ሰዓት ገደማ ሕዝቡ ዳቦቱን ይዞ ከየቤቱ ሲወጣ የንፋስ መውጪያ ከተማ ከሰማይ የወረደ የኮከብ ስብርባሪ ትመስል ነበር:: ዕውነቴን ነው ያን ዕለት ማታ ከሰማይ የወረደች ትመስል ነበር:: አሳዳጅ ጥላሞቷ ሁሉ ስለሚጋረድ እንኳን ንፋስ መውጪያ ተወለድኩ ያሰኛል:: የዳመራው እርጥብ እንጨት በእሳት ተበልቶ ሳያልቅ፣ ሰዎች ሁሉ ፊታቸው በፈገግታ እንደ ተከፋፈተ፣ አባት የልጁን እጅ ይዞ ወደ ዳመራው ቦታ እየመራው በየጓዳቸው እንጉሮጉባሽ እየመረቀ...ፊራ ተባ የሚለው ጨለማ ከተማዋ ሰማይ ላይ እንደረጋ የችቦዎቹ ብርሐን እንዳፈጠጠ......ንፋስ መውጪያ እንዲያ እንዳማረባት ብትኖር እወድ ነበር::

የዚህ የደመራ ማንደጃ ኩረብታ ዙሪያው ሙልጮ ነው......የመላጣ ሰው ጭንቅላት ይመስል ነበር:: ደመራውን ቀን በብርሃን በተለይ ከመሃል የሚቆመውን ቃወት አዛውንቶች ይገዝቡትና ማታ ችቦ ይዘን መጥተን እንለኩሰዋለን......ከፊሉ የደመራው ግድግዳ ላይ የሚነድ ችቦ እንደ ጦር ወርውሮ ይሰካል.....ከፊሉ እንደመፋቂያ ወስዶ ይሸጉጣል.....ከፊሉ እቃ እንደሚጥል አድርጉ ይወረውራል.....ታዲያ ሁሉ ፊት ላይ ደስታ አያለሁ:: የሚገርመኝ ነገር የዕውነት ሳቅ አይ ነበር ሁሉ ከየቤታቸው እየተኩረኩሩ የመጡ ይመስላል::

ታዲያ ደመራው በየቤታችን በችቦ ተሸክመን ባመጣነው እሳት ይለኩስና ይቀጣጠላል:: ሲቀጣጠል ሰዎች ዙሪያውን ከበው ይዘፍናሉ.....'ኢዮሐ አበባዬ!' ... "ሎጋው ሽቦዬ" ይላሉ:: ሌላ ሌላ ሁሉ ዐይነት ዘፈንም ይዘፍናሉ:: ብዙ ጊዜም ደመራው ከሚነድበት ምንአልባት ሁለት ኪሎሜትር የምትርቀውን የአድባር ዛፍ(7) ነኩቶ የመመለስ ሩጫ ውድድር ይደረጋል:: የመጀመሪያው ሦስቱ አሸናፊዎች ያማረ ጠላ በቀንድ (ቀንድ?) ዋንጫ ይሰጣቸዋል:: ጉራቸው ማነሩ ነበር:: በዚህ ሁሉ መሃል መጠጥ ይቀዳል:: ድፎ ዳቦ ይቆረሳል::

የተከመረው የሚቃጠል እንጨት በእሳቱ እየተናደ፣ ቁመቱ እያጠረ፣ ፍምና አመድ እየሆነ የዘፋኙና የጨፋሪው ድምፅ እንደ ትራሪ መቅጠን ሲጀምር ሰዎች ወደየቤታቸው



@BOOKALEM

ይብታተናሉ። ልጆች ግን 'ብዙ አታምሹ' ተብሉ እንመከርና ወደ ሁዋላ እንቀራለን (እኔን ማለቴ አይደለም).....እንደ እናት ውተት የሚሞቅ እሳት ዙሪያ እንደ ዝባ ጣጦር ተደርድረን።

ወሰን የለሽን ያየሁዋት ይሔን ጊዜ ነበር። ሰዎች ወደ የቤታቸው ለመሔድ ማብተን ሲጀምሩ ወደ እሳቱ ተጠግታ ተቀመጠች። ብን ያለች ኑሮ ኩታ ለብሳለች። አንዳንዴ ወንዝ የማያቸውን ትናንሽ እግረ-ቀጫጭን ወፎች ትመስል ነበር። ቅጥነቷ ደሞ የሆነች ዝዠ። እንግዲህ እሳቱ አጠገብ መጥታ ስትቀመጥ የእሳቱ ወጋገን የሚያበራብት ፊቷ በእኔ በኩል ይሆናል። ታዲያ ያምራል። የእውነቴን ነው ያምራል። ለምን እንደሆነ አላውቅም ያምራል። በተጨማሪ ጉኗ ቆመው የነበሩ ሰዎች ገለል ገለል ብለው ከእሳቱ ራቅ ብለው ወሬ ጀመሩ። ከሁዋላዋ የአገር ልብስ የለበሱ ሴቶች የኖራ ግድግዳ መስለው ቆመው ነበር። የወሰን ፊት ፀጥ ያለ ነበር። ሠላም ያለበት ይመስላል። አልፎ አልፎ ምክንያቱን ባላውቅም በትንሹ ፈገግ ትላለች። አፌን ከፍቼ አያታለሁ።

ከበስተ ሁዋላዋ የቆመው ከነጠላና ከጋቢ የተሰራው የሰው ግድግዳ ሲፈርስ ተአምር ተፈጠረ። ያ የኖራ አገር ባሕል ልብስ ግድግዳ ሰማይ ላይ የምትፎልል ድፍን ጨረቃ ከልሎ ኖሮአል። ታዲያ ጠቆር ያለው የወሰን ጭንቅላት ድፍኗ ጨረቃ መሐል ላይ የተቀመጠ መሰለ። አቅጣጫው። ጨረቃዋ ቢጫ ናት። የጨረቃዋ ማድያት የለም። ታዲያ ወሰን በስዕል ላይ የማያትን ትንሽ ማሪያም መሰለችኝ። አፌን በለጠጥኩ። ትንፋሽ አጠረኝ። የደመራውን እሳት ትቼ እሷ ላይ ዐይኖቼን እንደመኻገር አጣበቅሁ። ወሰን በቀስታ ብትንቃንቅም ጭንቅላቷ ከጨረቃዋ ክብ አልወጣም። ብዙ ሳይቆይ እስኪበቃኝ ሳላያት ያ የኖራ፣ የአገር ልብስ ግድግዳ ቀድሞ እነበረበት ተመለሰ።

ወሰን እንደ አጋጣሚ ዞር ብላ አየችኝ። ያውም ያን የተረገመ አፌን እንደከፈትኩ። እጅ ከፍንጅ። አልሮጥ ነገር። እሳት ውስጥ ዘልዬ አልገባ ነገር። ታዲያ ከዛን ቀን ጀምሮ የወሰን ያቺ ምስሏ አንጀቴ ውስጥ ገብታ ከሌሎች ሰዎች ያልተለየች መሆኗን ብረዳም ምክንያቱን ልገልጠው በማልችልበት ሁኔታ ልዩ አድርጋ አሳቀለችኝ።

አንዳንድ ሴቶች አንደበታቸው ብቻ ያምራል፣ አንዳንድ ልጃገረዶች ፊቶቻቸው ብቻ ያምራሉ፣ አንዳንድ ሴቶች ቂጣቸው ብቻ ያምራል፣ አንዳንድ ልጃገረዶች አለባበሳቸው ብቻ ያምራል.....በብርሐን የሚከበቡ ግን ከወሰን ሌላ ያሉ አልመሰለኝም።



@BOOKALEM

# ስባቴ ወፍራም ስጆች ነበሩት

ሥራ ልፈልግ ወጥቼ ያላሰብኩት ደረሰ:: ጉዳዩ ያኔውኑ ቀን እንደተወለደ ያኔውኑ ቀን ቢሞት ደግ:: ነገር እየተያያዘ፣ በወሬ እየተራባ ሙስጠፋ ለእህቴ ለአመቤት ደብዳቤ መፃፉ በሰፈርና በትምህርት ቤት ተወራ:: እንግዲህ ትልቅ አንቀፅ መሆኑ ነው:: ያልሰማ የለም:: ጣሰን፣ የወሰን ጓደኞች፣ ሙስጠፋ፣ እኔ፣ በቀለ፣ ቤዛ መዓት መዓት ሰው::

አንዳንድ ደረቆችም አይጠፉም::

ይጠጉኝና: "የፃፈው ደብዳቤ ምን ምን ይላል?" ይሉኛል::

መልስ አልሰጥም:: ያስጠሉኛል:: እጆቼን ኪሶቼ እንደከተትኩ ትልቅ ምሬት መሬት ላይ እተፋለሁ:: ሙስጠፋን ማንም እንዲነካው አልፈልግም:: ዕንቁላል ስለሰጠኝ አልነበረም......በመጨረሻ የጉድ ጉድ አባቱ ሐጂ(8) ሰሙ:: ሙስጠፋ ከሱቁ ጠፋ::

ማታ ላይ አባቴ እህቴን ልኮ ከጉብታዬ ላይ አስጠራኝ:: ከቢሮዬ አስጠራኝ:: እቤት ውስጥ እሱና እናቴ ነበሩ:: እጆቼን ከኪሴ አላወጣሁም:: ጠጋ ብዬ አየሁት:: ተቆጥቶአል::

"እጅህን አውጣ" አለኝ

ቀስ ብዬ አወጣሁ::

"ጠዝበ አይደለም!......ተቀመጥ አሁን፤ በትክክል ትመልስልኛለህ"

አየሁት:: ሴትዮዋ ወይም ሚስቱ ወገቧን ይዛ ቆማለች.....ሚስጢራዊ ሳቅ በጥርሶቿ ነክሳ::

"ይኼ ቤትህ እንደሆነ ታውቃለህ?"

ዝም::

"አትሰማም?"

ዝም::

"ና ጠጋ በል......ና እዚህ"

ተጠጋሁት:: አልኮል አልኮል ይሸታል::

"አንተን ደብዳቤ አመላላሽ፣ አቃጣሪ አድርጉ የሾመህ ማነው?"

ዝም::



@BOOKALEM

"ይህ ልጅ ጤነኛ አይደለም" አለ ወደ ሚስቱ ዞሮ።

ትዕግስቱ ያለቀ መሰለኝ። አሊጋ በሚያከል እጁ ፊቴ ላይ በጥፊ መታኝ። እጆቼን ከሰ ውስጥ መቼ መልሺ እንደከተትኩ ትዝ አይለኝም። ግን.....ያለ እጆቼ እንደጉራዳ ለረዥም ጊዜ ስንገዳገድ ቆይቼ ውሐ የተጣደበት የከሰል ማንደጃ ላይ በቁመቴ ወደቅሁ። ውሐው የፈላ ነበር። እግዚአብሔር ያሁን ማርያም ጠብቀውኝ ውሐው እንዳለ ሳይደፋብኝ ቀረ። ምናልባት ቢሰፈር አንድ ወይ ሁለት ብርጭቆ የሚሆን ትከሻዬ ላይ ፈሰሰ።

ውሐው የፈላ ነበር?

አዎ። እሳት ሆኗል። የሚፈላ እሳት ሆኗል።

ምን ሆንኩ?

የትከሻዬና በከፊል የአንገቴ ቆዳ ተገፈፈ።

ምን አደረኩ?

ጮህኩ።

አባትህ ምን አደረገ?

አላየኝም። የፈሰሰብኝ ይምሰለው አይምሰለው አላውቅም። የጥፊው ህመም ያስጮኸኝም መስሎት ይሆናል። ወደ መኝታ ቤቴ በር ጉትቶ ወስዶ......በጉብታው ቅምጥ ተተምትሞ ያለቀ ቂጤ ላይ በካልቾ ጠልዞ ወደ ክፍሌ አስገባኝ።

ከዚያስ የአንገትህ ነገር እንዴት ሆነ?

ቁስሉ ከርሞ ከርሞ ራሱ ዳነ።

የዚያን ማታ የገረመኝ ግን የአባቴ እጅ ነበር። የአባቴ እጅ ትልቅ ባለጡንቻና ባለሰንበር ነበር። በጥፊ ሲመታኝ 25 ጣቶች ያሉት ይመስላል። ትልቅ ነበር። እጁ ትልቅና የቅባት ጠረን ነበረው። የፀጉር ቅባት ጠረን ነበረው። ፊቴ ላይ ሲያርፍ ለአጭር ጊዜ በሚያቃጥል ጨለማ የተሸፈንኩ መሰለኝ። ጨለማው በቅፅበት አልፎ ቀያይ ከዋክብት አየሁ፣ ቢጫ ከዋክብትም አየሁ.....ሐምራዊም አየሁ።

እንደዚያ ያወፈረው ምናልባት ቆንዶሱ ይሆን?



@BOOKALEM

# የማደንቀው ሰው

ሰድሜው አስራ አምስት የማይሞላ ልጅ ቅርቡ ካሉት ሰዎች የበለጠ የሚያውቃቸው ብዙ ሌሎች ሰዎች አይኖሩም:: የሉም:: ቢኖሩም እንደው ጥቂት ቢሆኑ ነው:: በዐይን የማውቃቸውና በትኩረቴ ታክኪአቸው የማልፋቸው ብዙ ነበሩ:: "በጣም" ከሚቀርቡኝ ጥቂት ሰዎች አንደኛዋ እንጀራ–እሁቴ ነበረች:; ቀድሞ እወዳት ነበር:: ሙስጠፋን ያደረገችውን ነገር ሳይና ስሰማ ግን አስከፋችኝ::

*(በመለማመጤ አትበይ ኩራ ኩራ*
*ቀድሞም አጥፍቼአለሁ መሄዴ ጋን ተራ......* **ሙስጠፋ አሊ**)

ይኼም ስለገባት ነው መሰለኝ ሳመሽ የማገኘውን የራቴን ድርጐ ማምጣት አቆመች:: አቆማለች:: ሙስጠፋ ለእሷ የሚያንሳት ልጅ አልነበረም:: የአራዳ ልጅ ለማን ያንሣል? አቦ ሰው እኮ ይገርማል:: አባቴ ግራ ያጋባኝ ነበር:: የቀድሞ ችሎታው አለማወቅ ይመስለኝ ነበር:: ያን ጥፊ ከቀመሰኩና የትከሻ መሳጣ ካገኘሁ ጀምሮ ግን ከልቤ ወቷል:: ሲልከኝ ሲጠራኝ መጥፎ ነህ አልባልና ባዕረ ሞት ሠይፋን ይዞ ወርዶ ነፍሱን ቢወስዳት አልጠላም ነበር:: እንዲህ ከሆን ደ'ሞ እናት የለኝ፣ አባት የለኝ:: ግን ፀጉር አስተካካዮች የሚሞቱ አይመስሉም:: ፀጉር አስተካካዮች ነፍሳቸው ረዥም ሳትሆን አትቀርም::

*ማንን ልውደድ ታዲያ?*

ሙስጠፋን አደንቀው ነበር:: የሰንቁላል ፍርፍር ጋብዞኝ ደብዳቤውን ለእሁቴ ሰጥቶ መልሱን እስካመጣለት ድረስ አደንቀው ነበር:: ምናልባት እወደውም ነበር:: የሚያለቅስ ሰው እጠላለሁ:: የሚያለቅስ ወንድ ያስጠላኛል:: ውሐ ከሰማይ ወይ ከወንዝና ከምንጭ እንጂ ከዐይን መውጣት የለበትም:: ለሙስጠፋ ያለኝ አክብሮት ሲያለቅስ ካየሁት ጀምሮ ጠፋ:: አራዳ እንደሆነ ይገባኛል:: የዚያን ዕለት ምን እንደነካው ግን አላውቅም:: እሁቴ ደ'ሞ እንዲህ ሰው የሚያብድላት አይመስለኝም::

*ታዲያ ማንን ነበር የምወደው?*

ብዙ ሰው ሊገርመው ይችላል:: እኔ የምወደውና የማደንቀው ሰው አበበ ቢቂላ ነበር:: ለምሳሌ አባቴ ፀጉር አስተካካይ ነበር:: እኔ ሳውቀው ጀምሮ ፀጉር ያስተካክላል:: አባቴ ለፍቶ አዳሪ ቢሆንም በዚህም ቢደነቅም ለዘመናት ፀጉር ቆርጦ የሚያውቃቸው የአቆራረጥ ጥበቦች ሁለት ዓይነቶች ነበሩ: «ሙልጭ» የሚባለውና «ስፖርት» የሚባለው:: ብዙ ሌሎች የሰፈሬ አባቶችን ይመስላል(.....ሌሎች አባቶች ቢያንስ ስላልወለዱኝ አይደበድቡኝም እንጂ)



@BOOKALEM

ባልወለደው ርቆኝ ልምጨው ባይደርሰው
በነገር በስድብ ለነዘር ላሽከመው:: ...ያልወለደኝ የገጠመው:: ነፋስ መጫ
ቅጻሜ ማታ:: ለአዝማሪ የተወረወረ::

ልጅም አልነበርኩ፣ የእንግዴም ልጅ አልነበርኩ፣ በቃ በሸዋርኒ የምታይ ነኝ:: እንደሰማሁትና እንዳነበብኩት አበበ በቂላ ትንሽ መንደር ውስጥ እረኛና ገበሬ ሆኖ ያደገ ነበር:: ክብር ዘበኛ ሆኖ ሲኖር ጥሩ መሮጥ በመቻሉ ተመርጦ ወደ ዓለም ተላከ፡፡ ወደ አፍሪካም አይደለም:: ወደ ዓለም ተላከ:: አሸነፈ:: አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁለት ጊዜ አሸነፈ::

ከስፖርቶች ሁሉ የማራቶን ሩጫ የሚያስገርም ነው:: ቀላል ተራ ነገር መስሎ ከባድ ነው:: የማራቶን ርቀት ከ40 ኪሎ ሜትር ይረዝማል ይባላል:: ይኼን ለመሮጥና ዓለምን ለማሸነፍ እንግዲህ አንድ ሰው ታላቅ መሆን አለበት:: ብችልም ባልችልም እንደ አበበ ቢቂላ መሆን እመኛለሁ:: እንደአባቴ ፀጉር ማስተካከል ቀላል ይመስለኛል:: እጅግ ልጅ እያለሁ የአባቴ ስራ ከባድ ይመስለኝ ነበር:: ለምሳሌ እኔን ሲያስተካክል ብዙ ጊዜ አይወስድበትም ነበር:: መጀመሪያ የአንገት ሽርጥ ያለብሰኛል:: ቀጥሎ ያደገ ፀጉሬን በሙሉ በቶንዶስ ይገፈኛል......ሙልጭ ይለራኛል:: በመጨረሻ ጭንቆቿ ረግፈው ያለቀ ጨብራራ ብሩሽ የሳሙና ውሐ ውስጥ ነክሮ (ይቀዘቅዛል) ከቀባኝ በሁዋላ የፀጉሬን ዕንፍ (ማጅራቴንና ጆሮ ግንዴን) በምላጭ ጠርጎቹን ይከረክማል:: የጋረደበትን ሽርጥ ከአንገቴ ይፈታና ከአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት እንደዘለለ አየር ወለድ ተንፍሶ 'በል በቃህ' ይለኛል::

እንዲህ ማስተካከል ይከብዳል?

እግዜር ሁለት እጆቹን ወስዶ በመለኮታዊ ጥበቡ (ጥንቸልንና እንጀራ እህቴን የፈጠረ አይደል) ደባልቆ ቢጠፈጥፋቸው አንድ ከግማሽ የሚሆን አበበ ቢቂላ አይወጣቸውም ነበር?

አበበ ቢቂላ ያደረገውን ግን ማንም በዓለም ላይ አላደረገውም::

አንድ ጊዜ ቢሆን አጋጣሚ ነው ወይም ዕድል ነው ይባላል.....ሁለት ጊዜ ነው:: ደስ አይልም?

የምወደው ሰው አበበ ቢቂላን ነበር:: አበበ ቢቂላን በጣም እወደው አደንቀው ነበር:: እኔ ስሜ መዝገቡ ነው እና ልጅ ብወልድ አበበ ቢቂላ መዝገቡ እለዋለሁ ብዬ እል ነበር:: ቢከለከል እንኳን እለዋለሁ እል ነበር::

የሚያሳስበኝ አንዱ ነገር ስለ አበበ ቢቂላ ብዙ ነገር አውቄ የተወለደበትን ወርና ቀን የሚነግረኝ ማጣቴ ነበር::

# የበጋ ዝናብ

ዝናብ ማለት ከሰማይ የሚመጣ ውሐ ማለት ነው:: ግን ዐይነት ዐይነት አለው:: ከሰማይ የሚመጣ ዝናብ ሁሉ አያምርም:: እንደ ሐምሌ ዝናብ የሚንጫንጭ ዋሊያት አልወድም:: እንዲህ ዐይነት ዝናብ የሚወድ የለም.....ከገበሬ በስተቀር:: ገበሬዎች እያረሱ፣ እያረሙ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ "እንኳን ይሔን የሐምሌ ነጭናጫ ዝናብ ሳከው" ብለው:: የገበሬዎችን ልብ የሚሰውረው ሞዛዛ ዝናብ ነው ይባላል:: ለእኔ የሚያምረኝ ዝናብ ግን የበጋ ነበር:: ዐሐይ ቦግ ብላ ወጥታ ዝናብ ሲጥል በውበቱ የሚያስደንግጥ ሰዎች የሚያወሩለት ይሆናል:: "ጅብ ወለደች" ይባላል:: ሴት ጅብን ያን ጊዜ አደንቃታለሁ:: ወቅትና ጊዜ ጠብቃ ልጆቿን በዚያ የበለጨ ቀን በመውለዷ:: የሚገርመኝ የጅቢቷ ስሌት ነው:: በሌሊት የሰላ(9) ወረራ በጥብጣን እንዲህ በረቂቅ ቀን ስትወልድ:: ሰዎች በዚህ ዐይነት ዝናብ ሳለመመታት ሲሸሹ እኔ ጉብታዬ ላይ የቆሸሸ እናቴን እያከክሁ ጥርሶቼን ገሽልጬ ለአላፊ አግዳሚ እያሳየሁ እቀመጣለሁ::

ጥርሶቼን ሰው አውልቆልኝ አያውቅም:: ሰድሜዬ በጨመረ ቁጥር ራሲ ነኝ የምነቅላቸው:: ሁለት ጥርሶች ጉብታዬ ላይ እንደቀበርኩ ትዝ ይለኛል:: በክር እያሰርኩ ነው የቀበርኳቸው:: ለምን እንደሚወልቁ አላውቅም ነበር:: ጥርሶቼን በሙሉ ሳወልቃቸው ደም የሚባል አልወጣኝም:: ካወለቅሁዋቸው በሁዋላ ውስጣቸውን ሳይ በመጠኑ ቀላ ያለ ሚጢጢ የሊሐጭ ሐይቅ በየጉድጓዳቸው ከትረው ያጋጥመኛል:: አንድ ሁለቱን በኪሴ ይዤአቸው ነው የጠፉብኝ:: ምናልባት ዶሮዎች ለቅመው በልተዋቸው ይሆናል:: እዚያ ጉብታ ላይ እኔ በማልኖርበት ጊዜ ለመጫር የሚመጡ ለቃቃሚ ዶሮዎች ነበሩ:: ዶሮዎቹ ለሆን በዓል ታርደው ይሆናል:: በየሰፈሩ የእኔ ጥርስ ቅመም ያለበት ዕንቁላል የበላ ሰው አይጠፋም.....ወይም ዕንቁላሉ ወደ ሌላ ከተማ ተጭኖ ሔዶ እኔን የማያውቀኝ ሰው በልቷቸው ይሆናል......

ወደ ዋናው ከተማ ዘልቀው ይሆናል::

ወደ ዋናው ከተማ ዘልቀው ለንጉሠነገሥቱ ቁርስ ቀርበው ይሆናል::

አንዱ ሚርተኛ ዶሮዋን ገሎ ጠላቱ አጥር ላይ ሰቅሏት ይሆናል::

አንዳንዴ ስለ ጥርሴ ሳስብ ነገሩ እየሰፋ፣ እየሰፋ ያስፈራኝ ነበር......ምናልባት ደሞ እንቁላሉን እርጉዝ በልታው ከሆነ.......

ያን በመሰለ ውብ የበጋ ዝናብ ግን እኔ ተወልጄ ነበር መሰለኝ። እኔ የተወለድኩበት ቀን ይመስለኝ ነበር። የተወለድኩበትን ቀን ባላውቀውም የተወለድኩት በዚህ ቀን ይመስለኛል። ሳላቋርጥ ጥርሶቼን እንቅላለሁ እንጂ የተወለድኩበትን ቀን አላውቅም ነበር።



@BOOKALEM

# ወሬሪ

ማንም ሰው ከቤቱ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ በሮቹና መስኮቶቹ ቦታቸው ተለዋውጠ እንዲያጋጥመው አይፈልግም። ወይም ሌላ የማያውቀው እንግዳ ሰው ቤቱ ገብቶ እሱ የሚያርፍበት ወንበርና አልጋ ላይ ተቀምጦ ወይ ተጋድሞ እንዲያገኘው አይፈልግም። ሰዎች እቤታቸው ውስጥ ካለው እያንዳንዱ ዕቃ ጋር በረዥም ጊዜ ውስጥ ሊክዱት የማይችሉት የስሜት ትስስር ፈጥረዋል።

አንድ ቀን ጠዋት ወደ ጉብታዬ ስሔድ ልክ እኔ የምቀመጥበት ቦታ ላይ አንድ ጎረምሳ ልጅ ሠፍሮ አገኘሁ። ደነገጥኩ፣ ተበሳጨሁ። 'ተነሣልኝ እንዳልለው የገዛሁት ቦታ አይደለም። ዝም እንዳልለው ሐብቴ በቀሲታ፣ በዝምታ ገና ከመንጋቱ ከዐይኖቼ ስር ከእግሮቼ ስር በፀጉረ-ልውጥ እየተዘረፈ ነበር። ራሴን እያከኩ ልጁን ተጠጋሁት። በጉን አይቶኝ መሬት መቆርቆር ጀመረ። የጠዋት ፀሐይ ፊቱ ላይ ስለምታብራ ዐይኖቹ ሁለት መስመሮች ሆነዋል። ጢም ማብቀል ጀምሯል። በግራ እጁ ገና የተለኮሰ ሲጃራ ይዟል። ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ነበር። በዚያ ቀንና ሰዓት የሳምንቱ ገበያም አልተዘረጋ። ምናልባት የትምህርት ቀን ነበር። እኔ ተዳፋቱ ላይ በመቀመጤ ቀድሞ ይሰማኝ የነበረውን የማየት የበላይነት በጉልበተኛ ጉረምሳ ተነጥቄአለሁ። ይኼን ወራሪ ልጅ የተለየ የሚያደርገው የእኔን ስፍራ መድፈሩ ሳይሆን እንግዳ መሆኑ ነበር። ከዚህ በፊት እዚያ ከተማ ፈፅሞ አይቸው አላውቅም። እተቀመጥኩበት ሆኜ ባስብ፣ ባስብ በፍጹም ልጁን ከከተማው ከየት አቅጣጫ እንደመጣ መገመት እንኳን አልቻልኩም። ከወንዙ ቢታች ያሉት የዛንጢ ልጆች ረባሾች ናቸው ይባላል። ልጠይቀው ፈለግሁ። ጠየቅሁት፡

"ሠፈርህ የት ነው?"

ዞር ብሎ አይቶኝ አልመለሰልኝም። 'ኧረ ምናባቱን' አልኩ በልቤ። የማን ነኝ ነው። ሲጃራ አጤሰና የእኔ ቦታ ላይ ተቀመጠና እኩ እኔን መናቅ አለበት ማለት አይደለም። ደሜ ፈላ።

እንደገና ጠየቅሁት። እኔን እያየኝ ሲጃራውን ሳበና በእኔ አቅጣጫ ጭሱን ረጨና እንደ መሳቅ ነገር አፉን ጠመም አድርጎ ነጫጭ ጥርሶቹን አሳየኝ። የሰማኝም ያልሰማኝም ይመስላል። ጫማዎቹ ትልልቅ የቆዳ ቦቶች ነበሩ። ትልልቅ የደረቀ የጭቃ ድግ ዙሪያቸውን ተሸክመዋል። እስከ ምሳ ሰዓት ድረስ ለፉክክር አብሬው ተቀመጥሁ። አልተነሣም። የሚገርም ነበር። የጉብታዋ መቀመጫ ፀባይዋ ሌሊቱን ተለውጦ አድሮ እንደሆን ከልጁ ቂጥ ስር አጉንብሼ አየሁ። ምናልባት ወደሚመች ትራስ ተለውጣ አድራ እንደሆን ብዬ። እኔ ብዙ ጊዜ



@BOOKALEM

አንድ ሰዓት ከተቀመጥኩ በሁዋላ እቆምና በአንድ እጄ ስልክ እንጨት ተደግፌ እግሮቼን አፍታታለሁ፣ ትንሽ ራሴን እዘረጋጋለሁ:: በነዚያ ጥቂት ሰዓቶች ውስጥ እንኳን አምስት ስድስት ጊዜ ደጋግሜ ተነስቻለሁ::

የምሰራው ስላልነበረኝ ወደ ቤቴ ሔድኩ፣ የሚወዱት ቦታ ተቀምጦ ዓለምን ማዮት ሥራ ቢሆንም:: የአገር ገዢዎች ከዚህ የበለጠ ምን ይሰራሉ? ጥሩ ምሣ እቤቴ አጋጠመኝ:: ከአባቴ የተረፈ:: በውጥ የራስ ለምለም እንጀራ:: እና አንድ ብርጭቆ ጠላ (ጌሾ ሊያንቀኝ ነበር)

*(መባላሽቱ በአንተ*
*በወለድከኝ ሰው እንዳይመሃኝ*
*ጠላ መጠጣት አላምደኝና*
*ስካሩ በላው አሰኘኝ......***መዝገቡ ዱባለ***)*

ወደ ጉብታዬ ስመለስ ልጁ እንደተቀመጠ ነበር:: አቀማመጡን እኔን ሲያዮኝ ጊዜ ነው መሰለኝ ለውጦ በጀርባው ተጋደመ:: በዐይኖቹ ፀሐይን የሚከተል ይመስላል:: ጥላቻዬ ቀነሰ:: እኔን የመሰለ ሌላ አንድ ሰው ያገኘሁ መሰለኝ:: ልረብሸው አልፈለኩም:: የምሔድበት ቦታ ስላልነበረኝ እግሬ እንዳመጣልኝ ስጓዝ አባቴ ፀጉር የሚቆርጥበት ቤት ደረስኩ:: ፀጉር የሚቆርጠው ያለ ሸርጡ ነበር:: አንደኛው መስኮት ላይ የደጃዝማች ጥላሁን ልጅ መስፍን መነፅሩን እየጠረገ ቆሟል:: ሁልጊዜ መነፅር እንዳደረገ ነበር:: ሁልጊዜ ባርኔጣ እንዳጠለቀ ነበር:: መዓት ጊዜ ከሴቶች ጋር ወንዝ ሲወርድ አየዋለሁ......

*(ዝናቡም አባርሏል፣ ዣንጥላውን አምጡ*
*ፀሐይዋም ደሀና ናት፣ ስሟችሁን አስጡ*
*ወንዙ በሴት ሙሉ*
*ወንዙ በሴት ሙሉ*
*ተጣጥቦ ወረደ መስፍን ሴት አውሉ::*
*የተባለለት......***የንፋስ መውጫ አዝማሪ***)*

እንድመጣ በእጁ ጠራኝ:: አባቴ አንገቱን መዘዝ አድርጐ በበሩ በኩል አየኝ:: የአባቴ ጆሮ ትልቅ መሆኑን ልብ አልኩ:: ሁለቱ ጆሮዎቹ ተደምረው ፊቱን ሳያክሉ አይቀሩም::

"ይኼ ልጅ አደገ አይደለም?" አለ መስፍን::

"ሐሳብ የለበት:: ትምህርቱን ሁሉ ትቶታል......ዛሬ ትምህርት የለም እንዴ አንተ?"

አንገቴን ደፋሁ::



@BOOKALEM

"ዝም ትለዋለህ እንዴ?" አለው አባቴን::

"እሱ ካላለበት......እምቢ አለ እኮ......"

"ዕድሜው ስንት ሆኗል?"

የሚቆረጡት ሰውዬ ሽማግሌ ነበሩ:: ፀጉራቸው አጭር ነው ግን ይስተካከላላቸዋል:: እኔ ፀጉሬ አድጉ አፍሮ እንዲሆንልኝ እወዳለሁ::

"ስንት ዓመትህ እንደሆን ታውቃለህ?" አለኝ አባቴ::

ትከሻዬን በመሐይምነት ነቀነቅሁ::

"ስንት እንደሆነ አልነግርህም፤ በየትም ብለህ ዕወቃት" አለ አባቴ ቁጣ ቁጣ ብሎት::

ትከሻዬን ነቀነቅሁ::

"ምን ዐይነት ውሐ ቢጠጣ ነው እንዲህ ያደገው?" አለ የደጃዝማች ጥላሁን ልጅ::

"ጠጅ" አለ አባቴ ወደ እኔ እያየ::

ሽሙጡ ገብቶኛል:: እንዳልገባው አንገቴን ደፍቼ ለመውጣት ወደ በሩ ዞርኩ:: ቀጫጫና ረዥም ልጅ ነበርኩ:: የማያረዝመኝ ዕድሜዬ፣ የማያቀጥነኝ ምግቤና ነገር ነው:: ብዙ በልቼ ነበር መሰለኝ እንቅልፍ እንቅልፍ ይለኛል:: ወደ መሐል ከተማው ሳልመለስ የሰፈራችን ትልቁ ጫካ ሔድኩ:: እስከ ዛሬ እንዲህ ያለ ጫካ አላየሁም:: አደገኛ ቦታ ነበር ይባላል:: ብቻውን በውስጡ ደፍሮ የሚሔድ ልጅ የለም:: አዋቂዎች ይሔዳሉ:: ልጆች ግን ሾላ ለመብላት ከፈለጉ ተሰባስበው ይሔዳሉ:: እዚያ ጫካ ብዙ ልጃገረዶች ተደፍረዋል ይባላል:: "መደፈር" ምን እንደሆነ ዘልቄ የማውቀው ቃል ባይሆንም አስፈሪ ነገር ነበረው:: ከሲታ ስለሆንኩ አውሬ ቢያየኝ ንቆ ተጋፍቶ ያልፈኛል እንጂ......ብሞትስ?......ብሞት ማን ይጨነቃል? ቁምጣው የተቀደደ፣ በባዶ እግሩ እሾህና ኮርች የሚፈጭ፣ የቀጠነ፣ በዐይን-አሩ የታፈነ፣ አደባባይ መሐል በተከፈተ አፉ ዝንብ ሲያስገባና ሲያስወጣ የሚውል፣ በጠጅ ሰክሮ ዛፍ ስር እንደ ዝሉ የሚተኛ፣ እናቱ የሞተችበት፣ አባቱ የገፋው ልጅ ቢሞት ማን ግድ አለው? አውሬ እንኳ ቢያጋጥመው፦ "ኢድያ እቴ ምን ይበላል ይሄ ልለፍበት እስኪ" ብሎ ነበር ተጋፍቶ የሚሄደው::

ሙት እናቴ ከዚያ ከበበኝ ደን ውስጥ ቅጠል ተመስላ እንድትመጣ ፈለግሁ:: እነዚያ ቅርንጫፎች እንደ ክንድ ሆነው እንዲያቅፉኝ ፈለግሁ (ባይወልዱኝም አላደገዙኝ የለ? አየርና ጥላ ሰጥተው፣ እንደ ዝልተኛ ውስጣቸው ደጋግሜ ለምረሳው አፍታ ሸሽገውኝ) በረደኝ መሰል ያኔ:: ሬሳዬ በአውሬ ተበጣጥሶ ከዚያም ተሰብስቦ በሳጥን ሲቀመጥ አባቴ ስለእኔ

ከማልቀስ ይልቅ የሚስቱን ቂጥ ቸብ ቸብ ያደርጋል፣ እህቴ በእኔ መሞት ከማልቀስ ይልቅ መኝታ ቤቷ ሚሉን ትመጣለች፡፡ የማደንቀው የምወደው አበበ ቢቂላ እንኳን ግድ አይሰጠውም፡፡ አያውቀኝም፡፡

ማልቀስ ፈለግሁ፡፡

ደኑ ውስጥ ብዙ ርቄ መንገዝ አልቻልኩም፡፡ የማውቃቸው **የክረምት ድምፆች(10)**፣ የለመድኳቸው፣ የጎጋና የነዛክ ፊጩኸቶች እንደ ልዩ አውሬ ድምፅ አስፈሩኝ፡፡ እግሮቼም ደከሙ፡፡ እንደ ሕመምተኛ እተነፍሳለሁ፡፡ እንደ ዛፍ ተደግፌ ለመጀመሪያ ጊዜ አለቀስኩ፡፡ በዛፉ ግርድፍድፍ ቅርፊት ላይ የዝናብ ውሃ እንደ መጠን የለሽ ዕንባ ይወርዳል......የምሽቱ ሰማይ እንደ እኔ የተዋከበ ነበር፡፡ በስሮች ላይ መዝሊያ ያጡ እግሮቼ የረገፈ ቅጠልና ተዘንጥፎ የወደቀ ጭራሮ እየመቱ ልብ ባልላቸውም ይጫወታሉ፡፡ ሰልፉ ያማረ ዐምባ ግራጫውን ሰማይ እየተመተመ ሲያልፍ ተደብቄ አየሁ......ደኑ ውስጥ ብዙ ጊዜ ቆይቼ ፀሐይ አዘቅዝቃ መብረድ ሲጀምር ተመልሼ ወጣሁ፡፡ ጆሮ ከሚያደነቁረው የደኑ ፀጥታ ጀርባ ከሩቅ ጅብ ሲጮህ እሰማለሁ፡፡ ወደ ከተማው መሐል ስመለስ በድህረ–ዕርበት ጨለማ ውስጥ እዚያ ጉብታዩ ላይ የቅድሙ ልጅ ተቀምጦ አየሁት፡፡ ባልቀረብሁም ከሲጃራ አጢያጢያሱ፣ ከአቀማመጡ፣ ከቅርጹ እሱ መሆኑን አወቅሁ፡፡

ታላቁ ተቀማጭ እንደመጣ ገባኝ፡፡ እንደ እኔ በዝናባማ ፀሓይ ቀን የተወለደ የተቀማጮች ንጉሥ እንደመጣ ገባኝ፡፡ ከዚያ በሁዋላ ሐዘን አልተሰማኝም ነበር፡፡



@BOOKALEM

## ፋሲካ

ብዙ ሕዝብ ከማርያም ቤተክርስቲያን አስቀድሶ ሲመጣ አየሁ:: ከተማው እርጉ የፈሰሰበት መሰለ:: የሚያማምሩ የሐገር ልብሶች.....ከተዘረጋው እርጉ ጥቂቶቹ ተቆርጠው በሠፈራችን አቅጣጫ በፈታውራሪነት ሲሔዱ አየሁ:: ወሰን ከመሃል ነበረች:: ይኼ ቀራጭ ከሞናው ወራሪ ከመሰለው ክምችት ተነጥሎ እንዳይሔድ ለማያያዝ የምትሞክር የጥጥ ጓል ሆና:: አልቻለችም፤ በሩጫ ትንሹን የኩታ እርጉ ተቀላቅላ መሔድ ጀመረች:: እየተንሳፈፈች::

እንጀራ እናቴ፣ አባቴ፣ የወሰን አባት አቶ ገ/መንፈስ ቅደስ (11)፣ የወሰን እናት፣ የጤናው ጥበቃው ሐላፊ (ጉረኛ ቢጤ ነበር) የአባቴና የእናቴ ንስሓ አባት (12) እና ሌሎች የተከናነቡ ሁለት ሰዎች ደጋጉች ይመስላሉ:: አስቀድሰው ነጭ ለብሰው ሲጓዙ ደጋጉች ይመስላሉ:: እኔ ጉብታዬ ላይ ባደፈ ልብሴ ተጠቅልዬ የራሴን ላብ እያሸተትኩ እታዘባለሁ:: ትንሽም እቀናለሁ:: በወሰን ትንሽ እቀናለሁ:: የእናቷን የጥጥ ቀሚስ ተጠግታ ፃዳነቱን እያሸተተችና እየተጫወተች ስትሔድ እቀናለሁ:: ፋሲካ ለእኔ መቸ ደግ እንደምትሆን አላውቅም::

ቂል ነበርኩን?

ወሰን ብልጥ ሆና ነበረችን?

አባቴም እናቴም ብልጥ ናቸውን? ብዙዎች እግዚአብሔርን እንኳን መሸወድ ችለዋል አልኩ በልቤ::

እኔ ላቤን እያሸተትኩ በማያዝያ ፀሐይ ውስጥ ስቀላላ::



@BOOKALEM

# ምንቸት ስብሽ

አንድ የፋሲካ በዓል ዕለት እነ ወሰንየለሽ ቤት ተልኬ መልዕክቱን ካደረስኩ በኋላ እንድቀመጥ ተነገረኝና ከዋናው በር ጎን ያጋጠመኝ የጉሬዛ አጎዛ የለበሰ የሳጠራ ወንበር ላይ ኩስስ ብዬ ቁጭ አልኩ:: (መንኪስሴ ለራሴ ይታወቀኛል) ብዙም ሳይቆይ እንዲህ ሆነ........

ነጭ የላስቲክ ሳህን ፊት ለፊቴ ተቀምጧል:: በስተግራዬ ወሰን የለሽ ትንሽ ራቅ ብላ ግድግዳ ተደግፋ ቆማለች:: እኔ በጉሬዛ አጎዛ የተሟሟቀ የሚመች አሮጌ ወንበር ላይ ተቀምጬአለሁ:: የላስቲኩ ሳህን ትሪ ላይ ፊት ለፊቴ በትንሹ የሚንገዳገድ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጧል (ለምን እንደሚንገዳገድ በዚያን ወቅት እራሴን አልጠይቅም:: የሚንገዳገድ ወንበር ላይ መቀመጥ ምኑ ለእኔ እንግዳ ሆኖስ ነው?):: ከትሪው ላይ ከሳህኑ ጉን ጠይም ድፍን ዝቡቅቡቅ እንጀራ እንደ ቱባ ተጠቅልሎ ተጋድሟል:: የወሰን እናት ከጓዳ ባለ አበባ ጉድጓዳ ሳህን ይዘው መጡና ለወሰን አቀበሏት:: ወሰን ቂብ ቂብ እያለች መጣች:: ጉድጓዳው ሰሀን በአበባ ስዕል ባሸበረቀ እፊያ ተከድኗል፡፡ በእፊያውና በሳህኑ ከንፈሮች መሐል ብር የመሰለ የሚያብራ ጭልፋ ወደ አየር ውስጥ ተዘርግቷል:: ወሰን እፊያውን ስትከፍተው ዐይኖቼን ወደ ጉድጓዳው ሣህን ሆድ ዕቃ ወረወርኩ:: ታላቅ ቀይ ወጥ አየሁ:: ንጉሠነገሥት ሐይለሥላሴ፣ ደጃዝማች ከፍሉም፣ አፈንጉሥ ዘለቀ፣ አባ ጆቢር አባ ጅፋሮ የሚባሉት የሚበሉት ዐይነት ቀይ ወጥ:: የተጌጠ ጠይም ደም ይመስላል:: በቅባት የሰከረ:: ከዚህም ስካራም ወጥ ደካማ ጢስ ቀስ እያለ ወደ ላይ ይነሳል (ምን አድርጌው ነው እንዲህ በቀስታ የሚነሳው? ልቤን ሊሰልበው ነበርን?)::

ከዚያ በጭልፋው ተረበሸ:: እና ውፍረቱ:: ወሰን መሰል መሰል መሰልሰል አደረገችው፣ በቀስታ ከውስጡ የአልማዝ ቀለበት ለማውጣት እንደምትፈልግ:: ከዚያ በጭልፋው እፍኝ ያህል አውጥታ ነጩ ሴሐን መሐል 'ጣል' አደረገችው:: የሚፈስ አይመስልም:: እና ጣል:: መረቁ ከደቀቀው ሥጋ ጋር በማር የተያያዘ ይመስል ነበር:: የነጩ ሰሀንና የወጡ ቀለም ግጭት ከላይ እስከ ታች በጠበጠኝ:: ከዚያ በጠረኑ፣ በዚያ የተስፋ ጣዕሙ ምክንያት ከጉሮሮዬ እስከ ዕምብርቴ ስር ቀላል ነጉድጓድ ሰማሁ:: ቶሎ እንድትሄድልኝ ፈለግሁ:: የመኩራረያ ጊዜ አልሰጠችኝም:: በሆድ ነገር ኩርቼ አላውቅም:: ወሰን ስቃዬ ስላልገባት፣ እኔንም ለማስደሰት፣ ሁለተኛ ጊዜ ከወጡ ጨልፋ ሴሐኑ ላይ አደረገች:: "ብላ እንጂ" አለች:: ረሳሁዋት:: ጠቅላላ ገላዬ ዐይን እጅ አፍ ሆድ ሆነ.....ከዚያ ከጠይሙ እንጀራ ስቀድ.....በመቅደዴና ወጡ ውስጥ በመንከሬ መሐል ያለው ጊዜ የሰማ በረሐን እንደማቋረጥ ሥቃይ በሚንቀጠቀጡ ጣቶቼ ከደቀቀው ሥጋ በእንጀራው አፍኜ ዘገንኩ:: የወጡ ለዘዝ ያለ



@BOOKALEM

ሙቀት (በምን ለኩት እቴ:: አንዷ ሴት የማትሰራው ታብ የለ) ጣቶቼ ጥፍር ውስጥ ሁሉ ይሰማኛል:: ስጎርሰው እጅግ በፍጥነት ነበር......ሮጦ ወይም በሮ እንደሚያመልጠኝ:: አፍ ውስጥ ደሞ ይለሰልሳል:: ትናንሾቹ የስጋ ጥንጎች ጥርሶቼ መሐል ሲፈንዱ መጠው የያዙትን ቅባትና የበሰለ ውሐ ወደ ጉሮሮዬ ሲደፉ....... እመቤቴ ማርያም ሆይ በመላኩ በቅዱስ ገብርኤል ሠላምታ ሠላም እልሻለሁ ሠክርኩ:: አፌ ውስጥ ውብት ብቻ:: ከአፌ እስከ ሆዴ የተዘሩት ትናንሽ የትቦዎቼ በሮች በስስት ተብልቅጠው እንጀራው ተላምጦ በውስጣቸው ሲያልፍ ለማየት በጉጉት የሚጠባበቁ መሰሉ:: ሾልኮ በታች እንዳይወጣ እስክፈራ:: ትንፋሼን እስማዋለሁ:: ከርቀትም እነዚህ አስደናቂ ነገሮች ጠረጴዛው፣ ሣህኑ፣ ሣፋው እንጀራው እግር አብቅለው እየሮጡ የሚጠፉ እስኪመስለኝ:: ሲከፉም ቤቱ እኔን ውልቅ አድርጉ ከትቅያሪ ድስቱ ከትቅያሪ ሞሰቡ ትተውኝ የሚሔዱ:: ሆዴም የሚከዳኝ፣ እየተሸንቆረ፣ አልይዝም እያለ..... ከመሐል ዞር ብዬ አየሁ:: ወደ ቀኝ:: ወሰንና እናቷ ቆመው ይመለከቱኝ እንደነበር ተገነዘብኩ:: መጀመሪያ እናቷ ፊታቸውን መለስ አድርገው ወደ ጓዳ፣ ቀጥላ ወሰን አፏን እንደሚስቅ በእጇ አፍና ይዛ ወደ ጨለማ ውስጥ አለፍ አሉ:: መሳሳቴን አላወቅሁም:: መሳሳቴ አልገባኝም:: መሳሳቴ የገባኝ፣ ያወቅሁት ስጠግብ ነበር:: እንጀራው አልቆ ትንሽ የወጥ ደሴት ከጠፍጣፋው ሰሀን ጥግ የተረፈው ከፊል ጎንዋ ፈጥኖ በሚያቀዋሽ እንጀራ ተቆርጦ ሳይ የስስቴን፣ የገብጋባነቴን ጥልቀት ተረዳሁ:: አፈርኩ:: እንደገና ማፈሬን ስርገኤ ምን ያሳፍራል? ብዬ እራሴን ጠየቅሁ:: አያሳፍርም:: አሳፋሪስ ቢሆን?:: እንደውም በመንገብገቤ ስስታም አባቴን ሰው ፊት አሳጣውና፣ እንጀራ እናቴን አሳማና፣ እግዜርን አይፈሩም መቸም ሐሜት ያንበጠብጥልኛል:: (ሰውን በእግዜር ሳይሆን ሰውን በሰው ነው እኩ የሚባለው::) ዞር ብዬ አይቼ እምስቱንም ጣቶቼን ጠባሁ:: በየተራ:: ሲጀመር እንዳልታጠብኩ ትዝ አለኝ:: ቀደም ብዬ ካላጣሁት ጨዋታ በጉብታዬ አጠገብ የሚያልፍ ልጅ ኳስ እንዳጫውተው ጠይቆኝ ስሯሯጥ ስወድቅና ስነሳ ኳስም እየያዝኩ ስጥል ነበር:: ወሰንና እናትዋ አያውቁም:: ብጠባቸውስ ጣቶቼን? ጣት ጠብተን ነው የምናድገው:: እኔ ከእናቴ ጡት የበለጠ ጣቶቼን ሳልጠባ አልቀርም:: ከሚከዳ ጡት......የምንቸት አብሽ ቅባት የነካው አዋዝ አውራጣት የበለጠ ሸርክ ሳይሆነኝ ይቀራል?

ይሂን ላብራራ? ሳይፈረድብኝ በፊት:: "ሆዳም" ሳልባል ቀድሜ::

እነ ወሰን ቤት የሔድኩት ለፋብሪካ ቅርጫ የተጣለ የበሬ ሥጋ ሒሳብ ለመቀበል ነበር:: አባቴ ሁልጊዜ ሁለት መደብ ነበር የሚገዛው:: ተሸክሜ የምገባው እኔ ነበርኩ:: ከዚያ ሁሉ ከምሸከመው ለእኔ የሚሰጠኝ የሁለቱም መደብ ጨጓራ፣ ዐይነቡ የሆነ ስሙን የማላውቀው የሥጋ ስብስብ ነገር ነበር:: ካንገራገርኩ "ይኼም የቸገረው አለ......በአገሩ ረሀብ እንደገባ አልሰማህም?" እባላለሁ::



@BOOKALEM

በዚህ የተነሳ በሬና በግ እጠላለሁ:: ቆሜ ሳያቸው አንዳንዴ የሁዋላ እግሮቻቸው፣ የፊት እግሮቻቸው፣ ፊታቸው፣ ሻኛቸው፣ ፍሪምባቸው፣ ላታቸው፣ አንጀትና ጨጓራ ይመስለኝ ነበር:: የሥጋ እጥረት የበሬና የበግ እጥረት አገሪቷ ላይ ቢመጣ ለእኔ ቢቻል የእንስሶቹን መፈጠር እንዳልረሳ አበት ተጋግሮ በጠጥ ተቀልቶ ሳይሰጠኝ አይቀርም:: አንዳንዴ ጉና ተራራ ላይ እወጣና (ስድስት ሰዓት ያህል ተጉዤ) ዙሪያ ገባ ያለውን ጠፍጣፋ አገር ላይ "አሁን ይኼ ሁሉ ቦታ ለእኔ የምትሆን የአንድ ጠቦት እግር ያጣል?" እል ነበር:: የመብላት ጉጉት አይደለም ያለኝ፣ የነበረኝ......የመካፈል ጉጉት ነው:: መካፈል ማንን ገደለ? ስስት አበት እጅ ድረስ ከገባ......ታዲያ ጉና ተራራ ላይ እወጣና እንደ መልዓክ መሆን እመኛለሁ:: በመጀመሪያ የምኖርበትን አውራጃ እጥረዋለሁ:: ሰው አይገባም፣ ሰው አይወጣም:: ከዚያ ወንዙን ምንቸት አብሽ፣ ድንጋዩን ዳቦ፣ ቅጠሉን እንጀራ፣ ጠጠሩን ክክ ግንዱን ሥጋ የለበሰ አጥንት አደርግላቸዋለሁ:: ይውጣላቸው:: ከዚያ አይደርሱብኝ ነገር ሳንሳ ገደል (13) ላይ ችፍርግ ቢጥወጣ እወጣና እስታ ጥላ ስር ቁጭ ብዬ ወደ ታች እያየሁ መሳቅ ነው:: መቸም ይሔን ተአምር መስራት የሚከብደው መልአክ ብሆን አንድ ነገር ግን አያቅተኝም:: የአገሩን ሰው ጭንቅላት ጠቅላላ ፀጉር የማይበቅልበት መላጣ ማድረግ::

ከዚያ በሁዋላ አንዳንድ ጊዜ የወሰንን እናት ሳያቸው ትንሽ አፍር ነበር ደሞ አይችሉብትም የሚያምር አንገታቸውን ሰበር አድርገው "ደህና ነህ መዝገቡ?" ይሉኛል:: ትልቅ ወንድ ብሆን ጠልፌ እወስዳቸው ነበር:: ወሰን ታዲያ ለምን አትመር:: እቧን ሳይ ደሞ እቅም የሌለው ዐይን-አውጣነቴ ይበረታል:: ፍጥጥ አድርጌ እያታለሁ:: ትስቃለች:: ማርኪያት አልነበረም:: ማርኪያት ሳይሆን የዚያን ሰለቱ አበባሌ ትዝ እያላት መሰለኝ:: እንዲህ ስትስቅብኝ ብዙው እንደሚባለው "ያንሳሽ" "አትደጊ" "ያሳጥርሽ" አልላትም ነበር:: ትልቁ አኑጣጣሪው እርግማን "እንደኔ ያርግሽ" ነው::

መንሳቱ፣ አለማደጉ፣ ማጠሩ በቀላሉ ይመጣል::



@BOOKALEM

## የቁም ህልም ብሉ ዝም

በእኔ ዕድሜ ክልል የነበረ ሕፃን ብዙ ጊዜ ምን እንደሚያስብ አንዳንድ ሰዎች ቢጠየቁ......"ሕፃን ደሞ ቢያስብ ሆዱንና ጨዋታውን ነው" ማለታቸው አይቀርም። አንዳንዶቹም፡ "ጥሩ ከበላ፣ ጥሩ ከጠጣ፣ ጥሩ ሙዚቃና ማራኪ ዘፈን ከሰማ ሕፃን ምን ሕፃን ነው" ማለታቸው አይቀርም ነበር። የሚያምነኝ አይገኝም እንጂ እኔ ከማስባቸው ብዙ ነገሮች ሁለቱ ስለነፃነትና ስለፍቅር ነበር። ብዙ ሰዎች ግን ሁሉ ነገር እንደራሳቸው ይመስላቸዋል። እንዲህ ስናገር የሐሳቤ ታላቅነት ያስቀናቸው ወይም በእጅ አዙር ትንሽ መሆናቸውን የጠቆማቸው ምን ይሉ ነበር? "ይህቺ ሕፃን ማንኝ ብላ ነው ስለ ነፃነት የምታስበው? ማናትና ነው ስለፍቅር የምታስበው? ወገኛ! ጉድ እኮ ነው። ዘፈን ምርጫ ቅዳሜ ቅዳሜ ዛፍ ስር ተቀምጦ ከሰማ አይበቃውም። ባለጌ ጥጋበኛ" ማለታቸው አይቀርም።

ወገኛ እንኳን እኔ ሳልሆን ሌላ ነበር።

ስለነፃነትና ስለ ፍቅር አስቤ አስቤ ሲምታታብኝ ወደሚቀለኝ ሌላ የቀን ሕልም ሽርተት እል ነበር። እንደ አልቂት አእምሮዬ ላይ ተጣብቆ የሚዞረው አንደኛው የቀን ሕልሜ 'ባልተወለድኩ' የሚለው ነው። ባልወለድ መብቴ መገፈፉን አላይም ነበር። እሺ ልወለድ ግን ለምን ከዚህ አባቴ ከዱባለ ተወለድኩ? እንደገና እሺ ተወለድኩ ግን ከተወለድኩ በሁዋላ ለምን እውነተኛዋ እናቴ ሞተች? በዓለም ላይ......ዓለም ላይ ምን አስኬደኝ እዚያ ጉረቤታችን አንዲት ያለ ልጅ ሊጣቸውን የሚኖሩ በክብት እርባታ የሚተዳደሩ ሴትዮ ነበሩ። ለምን እሳቸው በእናቴ ምትክ አይሞቱም ነበር?

እሺ እናቴ ትሙት መቸም እግዚአብሔርን ማስቆም አይቻልም.....ከእሱ በላይ ማን አለ? የረባች የእንጀራ እናት ለምን አልተካልኝም? እኔ ብዙ አብሉኝ፣ ቀንጣን አስይዙኝ አላልኩም። በቁም ሕልሜ የምመኘው ጠርታኝ እግሯ መሐል አስቀምጣ ፀጉሬን የምትዳብሰኝ......ወይም ጉንጮቼን የምትስመኝ አንዳንዴ እኔ ብችልበትም ልታቀናጣኝ ፀጉሬን የምታጣብኝ እናት ነበር። እሳህ ታዲያ ሲረግመኝ ፎክሮ ነበር መሰል......

*ዘራፍ......ዘራፍ*
*የሰማይና የምድር ጌታ*
*ባገኘው ብትር ሰው የሚማታ*

እያለ......



@BOOKALEM

እሺ......እንጀራ እናት ዕድሌ ይስጠኝ፣ ሌላው ሰው የገባሁበትን ጣጣ ማየት አይችልም? ዐይኖቻቸው ጠጠሮች ናቸውን? ብልሀ፣ ብልጥ፣ ጮሌ፣ እሳት የሚባለው ሁሉ የእንጀራ እናቴን ጅብነት ሳይሆን የሚያየው የእኔን ስህተት ነበር:: በቁሜ የማልመው ታዲያ እንጀራ እናቴ ደግ ሆናልኝ፣ ነፍሴ ቁስሏ ተጠግኖ የከተማው ሺህ ሕዝብ ፈገግ ብሎ ሲያየኝ ነበር (ጥርሱ ይርገፍና)::

የቀን ሕልም ግን እግዚያብሔርን አያባባም:: የእሱ አንጀት አይደርስም::......ጨኸቴ እዚያች ንፋስ መውጫ ሰማይ ላይ እንደ ዕጣን ጠረን ሲንሳፈፍ ይኖራል (ፎነኔ ሁሉ መች ያሸትና)::

እሺ ሰዎች ሁሉ ግን ይጥሉኝ ወሰን የለሽ ግን ለምን? ወሰን የለሽ ጎረቤቴ ብቻ ሳትሆን ቤተሰቦቿ ከዱባለና ከእእ ጋር ሽርክ ነበሩ:: ቤተሰቦቿ እኔ ላይ የሚደርስብኝን በቅርብ ሆነው ማየት ይችላሉ:: እሷም ማየት ትችላለች:: ግን ታዲያ ሲያምር እንደ ወንድሟ፣ ሲከፋ እንደ ዱርዬ ለምን አየችኝ?:: እሷ ብታርቀኝም ታዲያ ከቀን ሕልሜ አንዷ ነበረች:: እንደ እሷ ደ'ሞ የቀን ሕልሜን የሚቆጣጠር አልነበረም:: ቢሆንም አልለማመጣትም:: ብወዳትም አልለማመጣትም::

አልፈራማ::

ለምን እፈራለሁ?

እኔ ከእነሱ የምኞት ስጦታ አልጠብቅም:: ምኞት ብጠብቅ ኖሮ እሱን እንዳላጣ በማለት የማይፈልጉትን ነገር አልሰራም:: ወሰን የለሽ ከወላጆቿ ብቻ ሳይሆን ከእእ ጥሩ ጥሩ ነገሮች ትጠብቃለች::

(1) መደነቅ ('አንቺ የኔ ቆንጆ' መባል)

(2) መጋበዝ ('ወሰን እስኪ ይህቺን እርጐ ሞክሪያት')

(3) ንፁሕ ልብስ ማግኘት ('ለጥምቀት የተገዛላት እኩ ጠቧታል:: ይህቺ ልጅ ቶሎ ቶሎ እኮ ነው የምታድገው' ይሏታል) (ማርያምን ግን አንዲት ሳንቲ አላደገችም)

ይሔ ይሔ እንዲቀርባት አትፈልግም ነበር::

እንደገና ትገርመኛለች......ወሰን:: የደመራው ዕለት በጨረቃ ብርሐን ተከባ ሳያት በልቤ ያ ብርሐን ከእሷ እንዳልወጣ ከጨረቃዋ እንደመጣ አውቅ ነበር:: ታዲያ ከፋት ባልሰራትም ትርቀኛለች:: እና አንዳንድ ጊዜ ምን ይመስለኛል ያቺ ደመራው ላይ ከቦት



@BOOKALEM

የነበረችው ጨረቃ የጠፋች:: የተሰወረች ሳይሆን ተዳክማ ጠርዟ አለ አይደል የጨረቃዋ ጠርዝ......ዘመናት እንዳገለገለ ከሰሌን እንደተሰራ የከሰል መራገቢያ ተተልትሎ ያለቀባት::

ታዲያ ያለ ክፋት በንጹህ ልቤ ስቀርባት ለምን ራቀች? ውሻ የሚበላውን ቀድሞ በምላሱ እንደሚፈትሽ እኔንም በሸራፋ ጨረቃዋ ነካክታ፣ እኔን ከወደደች ሌሎች እንደማይወዷት አውቃ እንደሆነስ.....ወይም ያየሁዋት የተንተራሰቻት ጨረቃ የምትፈነዳ ፈኛ እንደሆነችስ?

እንደ አስገራሚ ዐይነት ውሸት......

ወይም የእሷ ብርሐን ከብዙ ቢራቢሮዎች የክንፍ ውጋጋን የተሰራ ይሆናል.....ዕድሜዋ ሲረዝም፣ መረቋ ሲያልቅ፣ በደም ስሯ ተንከኩልና አገር አቀፍ ብልጠት ሰርፆ ልቧ አድርቆት ቢራቢሮዎቹም የሚቀሰሙት አጥተው አንድ በአንድ በመጠማታቸው እየለቀቋት......ወይም መዓዛዋ ተለውጠ፣ የልጅነቷ ናና ከብብቶቿ፣ ከፀጉሯ፣ ከጆሮ ግንዶቿ፣ ከትናንሽ ጭኖቿ ....... አረቲዋ ቀርንቶ፣ ጭንቅላቷ ዙሪያ ከብ የሠሩት ቢራቢሮዎች......በመሰላቸት እየተሰደዱ......እያነጠሱ፣ እየባሉ......እሷን ትተዋት......ጋና ዋና ከተማ አክራ አዲስ የተወለደ አጁኩ የተባለ ሕፃን ጭንቅላት ዙሪያ ይሰበሰቡ ይሆናል......

ቢሆንም ብዙ ቢገባኝም......የሚያቀያይም......ወሰንን አልጠላትም ነበር::

ተማሪ ቤት ጆግራፊ ስንማር አንዳንድ አገሮች ስማቸው ሲጠራና ሲዘረዘር አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደጋግሜ እነዚያ አይቼአቸው የማላውቃቸው ቦታዎች መሔድ እፈልጋለሁ:: ስለብራዚል ስሰማ ብራዚል መሔድ እፈልጋለሁ፤ ስለአውስትራሊያ ስሰማ አውስትራሊያ መሔድ እፈልጋለሁ፤ ስለደቡብ አፍሪካ ስሰማ ደቡብ አፍሪካ መሔድ እፈልጋለሁ፤ ስለአሜሪካ ሲወራ አሜሪካ መሄድ እፈልጋለሁ:: ግን መሔድ አልችልም:: የሚኬደው በአይሮፕላን ነው:: አንዳንድ ጊዜ በሐሳቤ ትልቁ ወንዛችን እገባና ተሸክሞ ወስዶ ዐባይ ይጨምረኛል:: በዐባይ ወንዝ ውስጥ አሳ፣ አፈር፣ ኩረትና ጠጠር መስዬ በሱዳን በኩል በግብፅ አድርጌ ሜድትራኒያን ባሕር እገባለሁ:: ከዚያ ጀልባ አግኝቼ ነፃነት ወዳለበት አገር እሔዳለሁ:: ብቻ ከዚህ ልራቅ እያልኩ::

አንዳንድ ጊዜ ደ'ሞ የፀሐይን መግቢያ ተከትዬ ደክሞኝ እስከወድቅ መጓዝ እፈልጋለሁ:: እኔ እቀድማታለሁ:: እንዲያ የፀሐይ መግቢያ ደጃፍ አንድ እናት ተቀምጣ የአሳፈ አገዳሚ ሕፃናት ጭንቅላት እየዳበሰች ቆንዳላ ትሰራለች ቢባል......ፀሐይን ቀድሜአት እሮጣለሁ:: አፈራ ነበር ግን......እግዚያብሔር ሰውን እንደ ስፌት አመሳስሎ ፈጥሮት እንደሆነ ብዬ::



@BOOKALEM

አንዳንዴ በቀን ሕልሜ ጉንዳን መሆን እፈልጋለሁ:: ስቀናባቸው:: ትናንሽ ሜር፣ ትናንሽ ስንዴ ተሸክመው ያለ ረብሻ በሠልፍ ጉድጓዶቻቸው ሲገቡ፣ የቆሰለ ዘመዶቻቸውን አዝለው ወደ ሐኪም ቤታቸው ሲሮጡ......የሚገቡበት ጉድጓድና የመሬት ውስጥ ለውስጥ ቤታቸውን ሙቀትና ምቾት እያሰብኩ ጉንዳን በሆንኩ እላለሁ:: ብዙ ጊዜ በልቤ ደጋግሜ

"አንተ እግዚያብሔር ጉንዳን አድርገኝ"

"አንተ እግዚያብሔር ጉንዳን አድርገኝ" ወዘተ......ብዬ እላለሁ:: አልሆንም::

ክረምት ሆኖ የሚያስተክዝ ብርድና ዝናብ ሲመጣ፣ ሰው በየቤቱ ገብቶ እሳት ሲሞቅ፣ ቡና ሲጠጣ፣ ቆሎ ሲቆረጥም፣ አሹቅ ሲቅም ብቻዬን እኩተማ እወጣለሁ:: ጭር ይላል:: ሁሉ በየቤቱ ነበር:: በስክርክር የቦይ ወበላ ስጫወት እቆይና ተዳክሜ ወንዝ ዳር እየተንዘፈዘፍኩ እቆማለሁ:: ብርዱ ውስጤ ነበር:: እውነቴን ነው ውስጤ ነበር:: እንደኳስ ተድበልብሉ የተቀመጠ ብርድ ነው:: ታዲያ ወደ ሞላው ወንዝ ጉሮሮዬ እስኪበጠስ እጮሃለሁ.....ምናልባት የውስጤ ቅዝቃዜ እንደ ትውከት ተወርውሮ ቢወጣ ብዬ:: ተጣብቆ ይቀመጣል:: ብርዱ አንጀቴ ላይ እንደኖረ፣ ጎጆውንም በሲሚንቶ እንደቀለሰ ኩሶ ተጣብቆ ይቀመጣል ከዚያ የቀን ሕልሜን እጀምራለሁ...

ወሰንየለሽ ጉኗ ብታስቀምጠኝ እያልኩ:: በትንሽ ነጠላዋ ከእሷ ሙቀት በትንሹ......እያጠባችኝ......በቀኝ ክንዷ አንገቴን አቅፋ......ቀይ ዳማ ፊቷ ከፊቴ ስንዝር ርቀት ያህል እየተንሳፈፈ......ትኩስ አጇ በማንኪያ እያጠጣችኝ::

ብትስመኝ......

ብትስመኝ ምን ይጐልባታል? ጉንጩ ላይ በሚያማምሩ ከንፈሮቿ ብትስመኝ......መሬት ይንቀጠቀጣል? ዓለም ይናወጣል? ትሞታለች? ከብቶች ወተት መስጠት ያቆማሉ? እህል ማብቀል ያቆማል? ፀሐይ ደም ትመስላለች?

አልነበረም::

እሷ ትናደዳለች:: እሷ ብቻ ሳትሆን ብዙ ብዙ ሰዎች ይናደዳሉ:: አባቴ ይናደዳል፣ እናቷ ይናደዳሉ፣ አባቷ ይናደዳሉ ከዚያ እሷ ጥቅሟ ስለሚቀርባት እጇን ከእኔ ላይ ታነሳለች፣ ነጠላዋን ከእኔ ላይ ታነሳለች፣ ዐይኖቿን ከእኔ ዞር ታደርጋለች፣ እቃዎችዋን ታነሳሳና.....ራቅ ብላ ትቀመጣለች::

ይሔ ሁሉ ስለነፃነትና ስለፍቅር የማስበው ነበር::



@BOOKALEM

# ከተማና ሬድዮ

አንድ ሰሞን ኣፋስ መውጫ ሬድዮ የማይሰማ አልነበረም:: በአገሪቷ ዋና ከተማና በአስመራ ወታደሮች ረብሸዋል ተብሏል:: እኔ የሚገርመኝ ወታደሮች መረበሻቸው ሳይሆን የሬዲዮው መብዛት ነበር:: ምን አልባት ድሮ እዳሪ ስለማሳያቸው ይሆናል:: አባቴ ፀጉር ማስተካከያ ቤቱ የሚያስቀምጣትን ትንሽ ራድዮ ቤቱ ባለው ትልቅ ናሽናል ራዲዮ ተክቷታል:: ማታ ታዲያ እዚያ አካባቢ "የጀርመን ራዲዮ" እንስማ እያሉ የማይሰበሰቡ ሰዎች አልነበሩም:: ድሮ ሲመሽ በአንድ እጃቸው በግ እየጐተቱ በሌላው የሚናፈጡ አዛውንቶች ያን ሰሞን በአንድ እጃቸው ሬዲዮ አንጠልጥለው በሌላው እጃቸው በግ እየጎተቱ ይሔዳሉ:: (ብዙ አዛውንቶች የሚናፈጡት በግራ እጆቻቸው ነበርን?) ወይም ትከሻቸው ላይ እንደ ትንሽ ጭንት......ትንሽ ራዲዮ::

"የጀርመን ራድዮ" ሲባል የአባቴ ራድዮ ጀርመን አገር የተሰራ ይመስለኝ ነበር:: አባቴ ቤት ሲመጣ ለእናቴ ሲቀልድ እሰማለሁ "ረብሻ ቢሆን የሰው ፀጉር ማደጉን አያቆም" እያለ:: የእኔ ረብሻ ከሁለት ሣምንት በፊት ተጀምሮ ከሁለት ሳምንት በፊት አልቋል:: ጉብታዬን የወረሰኝን ጮሌ ደግሜ አላየሁትም:: ተመልሶም አልመጣም::

አባቴ ከአወራሩ ንጉሠነገሥት ሐይለሥላሤን በጣም ይወዳል:: በጣም ነበር የሚወዳቸው:: እኔ ምንም አይገባኝም:: ዜና–እኔ የማደንቀው ዜና የስፖርት ብቻ ነበር፣ ያውም የአበበ ቢቂላ:: ያውም የማራቶን:: ሬድዮኖች ቢበዙ ባይበዙ ለምን ግድ ይሰጠኛል? የገረመኝ በድንገት፣ እንደአሸን መፍላታቸው ነበር::



@BOOKALEM

# የስበበ ቢቂላ ፎቶ

አባቴ አንድ የጃንሆይ ፎቶ ነበረው:: ቤታችን የሚገባ ሰው መጀመሪያ የሚያጋጥመው ስዕል አባቴ እእን አቅፎ የግቢውን የኢጋምና የቀጨሞ አጥር ከጀርባው አድርጎ የተነሳው ፎቶ ግራፍ ሳይሆን የጃንሆይ ጥቁርና ነጭ ጉርድ ፎቶግራፍ ነበር:: የአባቴና የእንጀራ እናቴ ፎቶግራፍ በስተግራ ሞሰብ ወርቅ ተደግፎ ተቀምጦአል:: ምሳ ወይም እራት ተጋብዞ የሚበላውን ወይም ቡና የሚጠጣውን ጥቁር እንግዳ በአራት ዐይኖቻቸው እንደ ሠላይ ይዘውት::

እኔስ?

እኔ ፎቶግራፍ ሳይሆን የነበረኝ ስም ነው:: "እሱ" የተባለ......ያውም ስም ያልሞላ:: ይሄም ቀለምና መርቀቅ ሲሆን......"ያ ወመኔ":: ከምላሳቸው የበለጠ ካሜራ መች ነበራቸውና? አንዳንዴ እኔን መሰደቢያ ቃላቶቻቸውን ከሬድዮ የሚቀዱ ይመስለኝ ነበር::

መማሪያ ክፍላችን ውስጥ ከእኔ መቀመጫ በስተቀኝ መገርሳ የሚባል ልጅ ነበር:: ስፖርት ይወዳል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ስፖርት ሁኔታ በተለይ ስለ እግር ኳስ የማያውቀው ነገር አልነበረም:: የጊዮርጊስ ተጫዋቾችን በሙሉ ያውቃል፣ ስለመንግስቱ ወርቁ ሲያወራ ጓደኛው እንደነበር አድርጉ ነው:: የማያመጣው ዐይነት የስፖርት መፅሔትና ጋዜጣ አልነበረም:: የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ደጋፊ በመሆኑ የደብተሩ ሽፋን ላይ የ 'V' ምልክት አይጠፋም:: የሚያደንቃቸው ተጫዋቾች መንግስቱ ወርቁ፣ አበበ ጉርሙ፣ ጌታቸው ተካ እና ሌሎች......ጎበደ መታፈሪያ የሚባል ሁሉ:: ግን በዐይኑ-ሥጋ ማንንም ዐይቶ አያውቅም:: የእሱ ታላቅ ምኞት አዲስ አበባ ተጉዞ የስታድየም ጨዋታ ማየት ነበር:: የሰበሰባቸው ፎቶግራፎች ደብተር መያዣ ኮሮጆውን ሞልተውታል:: ታዲያ አንድ ዕለት ፎቶ የሚለጥፍበትን ደብተር አውጥቶ ለልጆች ሲያሳይ አንድ አስተማሪያችን ለጉዳይ ጠርተውት ወደ ውጭ ወጣ:: እኔ የምሰራው ስላልነበረኝ ደብተሩን ወደ ዴስኪ ወስጀ ሳገላብጥ ትልቅ ከጋዜጣ የተቀደደ የአበበ ቢቂላን ፎቶግራፍ አገኘሁ:: ደነገጥሁ:: ወርቅ እንዳገኘ ገብጋባ ደነገጥኩ:: እጆቼ ተንቀጠቀጡ:: ለመስረቅ እንደፈለኩ ገባኝ:: ግራና ቀኝ ፎቶውን ከተጣበቀበት ሙጫ አላቅቄ በኪሴ አስገባሁትና ደብተሩን እቦታው መለስኩ:: መገርሳ ተመልሶ ሲመጣ ያደረኩትን አልጠረጠረም:: እንዴት ይጠረጥራል? የስፖርተኞችን ፎቶግራፍ የሚያዩ አይተውም የሚደሰቱ ብዙ ልጆች ክፍላችን ውስጥ አልነበሩም:: እኔም በዱርዬነቴ እንጂ በስፖርት ወዳጅነቴ የታወቅሁ አይደለሁም:: ምንም ሳይጠረጥር መገርሳ ደብተሩን ሰብስቦ ኮሮጆው ከተተ:: በሕሊናዬ የሰረቅሁዋትን ፎቶግራፍ ከፍሊ ውስጥ የትኛው ግድግዳ ላይ

እንደምለጥፋት እያሰላሰልኩ ነበር። የትም ግድግዳ ላይ ይሁን የትም ለዐይኖቼ ቅርብ የሆነ ቦታ......

ስዕሉ ላይ አበበ ቢቂላ ብቻውን ነው። የካናቴራው ቁጥር አስራ አንድ ነበር። ከቅርብ ርቀት 185 ቁጥር የለበሰ ፈረንጅ ይከተለዋል። በባዶ እግሩ ነበር። አቤ የእኔ እናት በባዶ እግሩ ነበር። አፉን ከፈት አድርጓል። የሚያስብ ይመስላል። ሐይማኖተኛ ይመስለኛል። የምንከሰና ልብሱን አውልቀው ለሩጫ የላኩት አበምኔት ይመስላል። ፊቱ ሠላም በሠላም የሞላ። የትኛው ሯጭ ነው ፊቱ እንዲህ ሠላም የሰፈነበት? የተባረከ ካልሆነ። ከፎቶው ስር "አቤ በሮም ሲመራ" የሚል ተፅፎአል።

እቁነጠንጣለሁ። ገላዬን ሁሉ በላኝ። በፀጉሯ የተቀመጡት የልብሴ ጉድፎች በላቤ ተቀስቅሰው ከካልሲዬ እስከ ሸሚዜ ክሳድ ድረስ የሚጣፍጥ እከክ ነገር በላኝ። ትምህርት አልቆ ስንዘገታተን ድሮ እጄን ኪሴ ከትቼ ደብተሬን አጣጥፌ ጉያዬ ሸጉጬ ወደ መሐል ከተማ በቀስታ የምራመደው ሰው በሩጫ ወደ ቤቴ......መኝታ ክፍሌ ገብቼ የአበበን ፎቶ በስንደዶ በሰቼ የጭቃ ግድግዳዬን ጉርጉሬ ስሰቅላት በሕይወቴ ትልቅ ለውጥ የመጣ መሰለኝ። ደስ አለኝ። በጣም ደስ አለኝ። ደሞ ወረቀቷን ከታች በኩል ከግድግዳ ጋር ስላላስያዝኳት በመስኮት የሚገባ ንፋስ በቀስታ እያርገበገባት አበበ ቢቂላን ክፍሌ ውስጥ የሚሮጥ ታስመስለዋለች። እግሮቹ ቀጫጭን ናቸው። ያሳዝናሉ። ምናልባት እንደ እኔ በእንጀራ እናት አድጉ ይሆናል። የባላገር እንጀራ እናት ልጇን ብዙ ብዙ ነገር ታስለፋውና አልደከምላት ሲል በሬ ታሸከመው ይሆናል።

አቤ ግን እንጀራ እናቱንና ዓለምን በሩጫ አሸነፋቸው።



@BOOKALEM

## ካልሲዬ (2)♣

አንድ ዕለት ጫማዬ ውስጥ ጠጠር ገብቶ ለማውጣት ሳወልቀው የካልሲዎቼን ቀዳዳ የተጋገረባቸውን ቆሻሻ አንድ ልጅ አይቶ በሳቅ ሊሞት ነበር::

ምን አደረኩት? ምን መለስኩለት?

ምንም:: ዝም ብዬ አየሁት:: ቤተሰቡ ከእኔ የባሰ ደሐ ነው:: አባቱን ልኳንዳ ውስጥ ርካሽ ተቀቅሎ የሚበላ ቁርጥራጭ ቆርንጮ እንደ ማስቲካ የሚሳብ የበሬ ስጋና ቅልጥም ሲለበስብ አይቼዋለሁ:: ልጁን ሲስቅ ያየሁት ፊቱን ሳይሆን ሽግናም ጥርሶቹን ብቻ ነበር:: አባቱ የሚለበስባቸውን አጥንቶች ይመስላሉ፣ ግን ትናንሾች ናቸው:: ልነግረው አልፈለኩም:: «ጥርሶችህ ተግጦ ያለቀ የቆሸሸ የበግ አጥንት ይመስላሉ» ልለው ፈለጌ:: የራሱ ጉዳይ ነው ግን:: በብስጭት ሳስብ ሳስብ ሁለተኛ ቢስቅ አጥንት የጋጠበት አርኩዋታ ጥርሱን በከተማዋ መንገዶች ላይ ነው የምዘራው ብዬ:: አልደፍርም ግን መድፈር አልችልም ነበር ግን:: ትኩር አድርጌ ለረዥም ጊዜ ሳየው ሳቁን አቆመ:: እራዳ መማታት የለበትም:: እራዳ እንደገባው ማሳየት ነው ያለበት:: ጀጋ የዛገ ጥርሱን በገለፈጠ ቁጥር እራዳ መደንበር የለበትም:: እራዳ ዘና ብሎ ያያል:: ደሞ እኮ የእግሮቹ ጣቶች በሞያሌ(14) ተጠቅተው ወደ ዝንጅብል የተለወጡ ነበሩ::

---

(ካልሲዬ (1) በአርታዒው ተቀንሷል::)



@BOOKALEM

# ባሰ መስቲካ

ጫጫጫጫ ያደርጉታል:: በሰልፍ ሆነው ነው ታዲያ:: ጎጆአቸው ተቀምጠው ገና መብረር እንዳልቻሉ ወፎች አፋቸውን ከፍቲው እናታቸው ከአየር ላይ አዘቅዝቃ:: ጫአጭ.....ከዚያ ይነፉትና ብፍ.....ብፍ.....ዱሽ.....ብፍ:: ሦስት ልጃገረዶች:: አስደነቁኝ:: ከአንዷ በተቀር የቀሩት ካዲስ አባ የመጡ ነበሩ::

በምንገድ ሲሔድ አገኘሁዋቸው:: ላቆማቸው ፈለግሁ:: እና አስቆምኩዋቸው::

"ምነው?" አለች አንዷ ቀልቃላ::

"አንቺን የጠየቀሽ የለም" አልኩ::

"እንለፍበት" አለች::

ሁለቱ አመለጡኝ:: አንዷን ሻሽዋን ይዤ አስቀረሁ ::

"ለምን ለመሸሽ ፈለግሽ?"

"ልቀቀኝ......"

"ምንድነው የምትበይው?"

"መስቲካ ነዎ ሌላ ምንድን ነው?"

"ልየው እስኪ"

"መስቲካ አታውቅም?"

"እንደዚህ የሚነፉ......?"

"ለመንፋት ልምምድ ያስፈልጋል......"

"እስኪ አንዴ አድርጊው"

ነፍታ አፈንድታ አሳየችኝ......ጮሌ ናት:: ፍርሐቷ ጠፍቶ እንደ ጓደኛዋ ነበር ያጋገረችኝ::

"እኔ እንደዚያ ማድረግ እችላለሁ?" አልኳት

"ሞክር"

"መስቲካ የለኝም"

"ግዛ"



@BOOKALEM

"መግገሮ የለኝም"

በጥርሷ የምትጫወትበትን መስቲካ አየሁ። ሮዝ መልክ ነበረው። ወይስ ምላሷ ነበር? የምታምር ልጅ ነበረች። ወደድኳት። አትፈራም።

"የእኔን ላካፍልህ?" አለችኝ።

እቀፉት፣ እቀፉት አለኝ። ስሟን ልጠይቃት ፈለግሁና እንዲያ እንዲያ ዐይነቱ ነገር የጎረምሳ ስራ ነው ብዬ ተውኩት። ከጓደኞቿ አንዷ......የሆነች የታች ሰፈር ሙጢ ጠራቻት።

"ዘነበች አትመጪም......እሱ ዱርዬ ነው" አለቻት።

ከመሐል ዘነቡ (ዘነበች) ከመስቲካዋ ቆርሳ ሰጠችኝ። ያኔውኑ በሩጫ ትታኝ ሔደች። መስቲካውን በጣቶቼ እየፈተሽኩ ስትሮጥ ንፋስ ቡፍ የሚያደርገውን ቴትሮን ቀሚሷን አያለሁ። ዞር እያለች እየሳቀች። መስቲካውን በአፌ አስገባሁ። ሙቅ፣ ስርጥብ የሚያዳልጥ ነበር። እንደ ሽቶ ነበር ጠረኑ። ዘነበችን የበላሁዋት መሰለኝ። ፀጉሯን፣ እግሮቿን፣ ማተቧን፣ ቀሚሷን፣ ጫማዋን፣ ሁለመናዋን በአፌ አስገብቼ የማላምጣት መሰለኝ (ዛሬ ዘነበች የተባለ ስም ስሰማ ሮዝ ቀለም ያለው መስቲካ ይሸተኛል፣ ሮዝ ቀለም ያለው መስቲካ ሳይ ዘነቡ ትዝ ትለኛለች)። ልጃገረዶቹ ታጥፈው ከመሰወራቸው በፊት ኪሴ ውስጥ የከረመ ያላበው አንድ እጄን በፍጥነት አውጥቼ ሠላምታ ሰጠሁ።

መስቲካውን እያላመጥኩ ለመንፋት፣ ለማጮህ ብሞክር አልቻልኩም......ጉብታዬ ላይ ተቀምጬ ጥርሴን እስከሚደክመኝ ባላምጥ በተለያየ ምንገድ ፊኛ ልሰራ ብተነፍስ ባኝክ ባኝክ ፊኛ የለም፣ ቀጭቀጭ የለም። በሸቅሁ። ቤቴ ስመለስ እህቴ ሳታየኝ ገባሁና አንድ የለመደችው ቦታ አስቀመጥኩላት። እህቴ ብዙ ጊዜ አላምጣ ያደከሚችን መስቲካዎች ለበቀል ይሁን ለቁጠባ ልብስ መደርደሪያዋ ጣራ ላይ ከውስጥ ትለጥፋቸዋለች። ይሄም የሚደረገው በስልት ነበር። አራት ቦታ መስቲካዎች ተለጥፈዋል። የከረመ የልዩ ፍጡር ንፍጥ ይመስላሉ። ከአሊጋው ራቅ ብሎ የነበረው አራተኛው በቅርብ የተለጠፈ ነው። አዲስ ነው። ከጐኑ የእኔን አምስተኛ ለጥፌላት ወጣሁ። ከዚህ እየወሰደች እንደምታላምጥ አውቃለሁ። ጠዋት ቁርሷን ከበላች በሁዋላ ወይም ባልተጠበቀ አሳቻ ቀን ነጭ ጠፍጣፋ ነገር ከሁላችን ለመደበቅ እየጣረች ወደ አፏ ታስገባለች። ካየሁዋት እያፈረች።

መኝታ ክፍሌ ገብቼ በረዥም ብጫኛ ወረቀት ላይ "አበበ ቢቂላ የማራቶን ንጉሥ" ብዬ በድርብ ፅሑፍ ግድግዳዬ ላይ የሰቀልኩት ስዕል ስር ዓፍኩና በስንደዶ ምስማር ከግድግዳው ምርግ ጋር አብሬው አልጋዬ ላይ በጀርባዬ ተጋደምኩ ጭንቅላቴን እጆቼ ላይ አድርጌ።

አቤን፣ ፀሐፊን ላይ ቆየሁ—በዕርካታ።



@BOOKALEM

## ሠልፍ

በከተማችን ያሉት የሦስቱም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በሕብረት በዝሆው መሐል ተሰለፉ:: እኔ ጉብታዬ ላይ ነበርኩ:: ይዘምራሉ:: አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮች ይሰነዝራሉ በጩኸት:: ከርታስና ጣውላ ላይ ብዙ የተፃፉ ነገሮች አሉ:: (የፊውዳል አገዛዝ ይውደም) (አቆርቋዥ ይውደም) (መሬት ላራሹ) (የታሰሩ ተማሪዎች ይፈቱ) (ኢትዮጵያ ትቅደም አቆርቋዥ ይውደም):: ሠልፉ ብዙ መጓዝ አይችልም:: ብዙ ከተጓዘ ከተማዋ ጠባብ ስለሆነች ዝብሬ ማሕበር ይገባል:: ዝሆው ደሞ ተነጥፎአል:: የከተማው ሁለት ፖሊሶች የበረንዳ ምሠሦዎች ተደግፈው ቆመዋል:: አንዱ ጉሬዛ ሲጃራውን ያጤሳል (በዚህ ፖሊስ አጠገብ ሳልፍ ሁልጊዜም የሚሸተኝ ትንባሆ ነበር)፣ ሌላው ባንድ እጁ ባርኔጣውን ይዞ በሌላ እጁ ማጅራቱን ያካል:: ብዙ ጊዜ ፖሊሶችን ሳያቸው ባርኔጣቸውን አውልቀው ማጅራታቸውን ሲያኩ ነበር:: ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ስለሆኑ የተሰለፉት ማሳደድና ማሰር አልፈለጉም:: ሰልፉ እዚያው ከተማ መሐል እዚያው በዚያው ሲጠቀለል እንደ ቆየ ተማሪው መሰላቸት ጀመረ መሰል......ረብሻ ተነሳ:: በሁዋላ ስሰማ የሆነ ሰው "ልጅ የጋገረው ለራት አይበቃም" ብሎ ጮሆ እየረጋገጡ ከመሃላቸው ሲያስወጡት ነው አሉ:: ፖሊሶች ሰልፉ መሐል ገቡ::

ተማሪው ከተረጋጋ በሁዋላ ለመጨረሻ ጊዜ ከዝሆው መሐል ተሰልፈው ሲወጡ ሠልፉ ፊት ለፊት በረዥም ጣውላ ላይ ያን ወራሪ ልጅ መፈክር ተሸክሞ አየሁት:: በጉብታዋ በኩል ሲያልፍ ቀና ብሎ አየኝ:: ይስቃል:: ምን ያስቀዋል? ሠልፉ ያስቃል? የሚያስደስት ነገር አለው? የሰልፍ ቋንጆ አለው? ሰልፉን ለምሳሌ "እንደ ወሰን የለሽ ቋንጆ ነው" ማለት እንችላለን?

ሠልፉ ላይ ያልመጣ አልነበረም:: ወሰን እንኳን አለች::

ወራሪው ለሠላምታ እጁን አነሳልኝ.....ዝም አልኩት......እንድመጣ በእጁ ጠራኝ:: አልሔድኩም:: ተቀምጬ እንደማላይ ሆኜ እየዋለሁ:: ትምህርት ቤት መሔድ የምጠላበት ምክንያት አንዱና ዋነኛው ሰልፍ ስለሚመስለኝ ነበር:: ምናልባት ብቻዬን መማር ብችል ጥሩ ተማሪ እሆን ነበር:: ወራሪውን አልጠላውም፣ ግን እዚያ ጫጫታ ውስጥ ስላየሁት ብቻ በልቤ አስገራሚ ብላሽ አልኩ:: ስዘጋው እየጮኸ ሔደ:: ሠልፉን እየጐተተ ከዝሆ መሐል ወጣ:: እንዲያ ይሻላል:: ዝሆው እንዲያ ሲከፈት ያምራል:: ሁሉን ጥርት አድርጎ ማየት ይቻላል:: ብርቱካኖቹ ከምራቸው ላይ በነቂስ የሚቆጠሩ ይመስላል:: አረንጓዴና ቢጫ ናቸው::

ለመሆኑ ለሰልፈኞቹ ባንዲራ ማን ነበር የሰጣቸው?



@BOOKALEM

# ቅንጀ .

ልብሶቼና ጫማዬ በእርጅና ተበጣጥሰው የመጨረሻ ደረጃ በመድረሳቸው እንቁጣጣሽም በመቃረቡ መሰለኝ አባቴ አዲስ ልብስና ጫማ ገዛልኝ:: ያን ያረጀ ልብስ በነሐሴ ዝናብና ንፋስ ለብሼው ብወጣ ከላዬ እንደ ጉም እየተገፈፈ እንደሚጠፋ እርግጠኛ ነበርኩ::

የተገዛችልኝ ሸሚዝ ቀለም የበዛት ሹራብ ነበረች:: ጃኬቴ እንደ ራንግለር ዐይነት:: ትዝ ሱሪዬ ደሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በሳሌ:: ትዝ ራንግለር አይደለም እንደ ራንግለር ዐይነት ነበር:: ሱሪዬ ደሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በሳሌ:: ትዝ ይለኛል ልብሶቼ እንዴት እንደሚሞቁ ልፈትሽ ሌሊት ከአልጋዬ ተነስቼ በብርድ ወደ ውጭ እንደ ወጣሁ:: ሸራ ጫማዬም የማያጅብበት ካልሲ ተገዝቶላት ነበር:: ካልሲ በጫማ በጣም ይመቻል:: መሬት ላይ ቆሜ የምሔድ አልመሰለኝም:: ካልሲዎቹ ብዙ ብዙ ቀለም አረንጓዴ፣ ቀይ፣ ሰማያዊ (የተለያየ ዐይነት ሰማያዊ) ቡና ዐይነት እና ግራና ቀኝ ቁርጭምጭምቶቼ ላይ ደግሞ ቢራቢሮ የመሰሉ የጥልፍ ምልክቶች ነበሩባቸው::

ቀን ከተማ ውዬ ስመለስ ከምንገድ አባቴ አስጠራኝና የሚሰራብት ቦታ ሔድኩ:: ለምን እንደፈለገኝ አላወቅሁም:: ምክንያቱም ስደርስ ምንም ያዘዘኝ ነገር አልነበረም:: እውስጥ ሦስት ሰዎች ነበሩ:: ሦስቱንም በዐይን አውቃቸዋለሁ:: ከከተማ አይጠፉም:: አንደኛው እንደውም የሙስጠፋ ጓደኛ ነበር:: ሁለተኛው ሰው በመስኮት ወደ ውጭ እያየ በትኩረት ነጭ ጥርሶቹን ይፍቃል:: ሦስተኛውን ሰው አላውቀውም:: እየቆጠቆጠ የሚያሳክከኝ የጃኬቴን ኮሌታ ወደ ሁዋላዬ እየሳብኩ ቆምኩ::

ሦስትኛው እንግዳ ከላይ እስከታች አየኝና "ይኼ ልጅህ ነው?" አለው አባቴን::

"ታዲያስ እኔን አይመስልም?"

"ቆንጆ ልጅ አድርሰህ የለም" አለ ሰውዬው::

"አንተ ጎረምሳ እያለሁ ምን የመሰልኩ ነበርኩ" አለ አባቴ::

አባቴ ፀጉር ማስተካከሉን ቀጠለ:: መቀሱ በጣም ይርመሻል::

"ቤት እንድትገባ ልነግርህ ነው የጠራሁህ:: ጠብቀኝ:: የምነግርህ ነገር አለ" አለኝ::

ገራ ግብትብት አለኝ:: አባቴ እኔን ጠርቶ እቤቴ እንድገባ የነገረኝ ምናልባት ከሦስትና አራት አመታት በፊት ነበር:: ጊዜው በትክክል ትዝ አይለኝም:: ይኼን ብሎኝ አቶ የለመደውን እንደተናገረ ሁሉ የተስተካከለ ጠጉር ማስተካከል ቀጠለ:: ወጣሁ:: ምናልባት ልጁን እንዴት እንደሚለብሰው አዩ ሊል ይሆናል:: እግዜር አባት መፍጠሩን አባቶች ደሞ

ተንከል መቀመጣቸውን አይተውም:: ከሁሉ የደነቀኝ ቃል ግን 'ቆንጆ' የምትለዋ ነበረች:: ምንድነው ቆንጆ? ቆንጆ ማለት እንደወሰን ነው:: ሲያዩት ደስ የሚል:: ለዐይን ለልብ የሚጣፍጥ:: እኔ እንደ ወሰን አምራለሁ ማለት ነበርን? በቀጥታ ወደ ቤት ሔጄ የእንጀራ እናቴን መስታወት ተሸክሜ ክፍሌ ይገናው ገባሁ......

......የሰውዬው አባባል አባቴ ቆንጆ እንዳልሆነ ይጠቅሳል:: ስለዚህ አባቴን አልመስልም ማለት ነው:: የምመስለው እናቴን ነው:: ወይስ ሌላ የማላውቀውን ሰው? የዐይኖቼ ብሌን ቀለም ጥቁር ነው:: ጆሮዎቼ ግራና ቀኝ የወጡ ነበሩ:: እንደ አባቴ:: ሌላውን ፊቴን ልሰይመው አልቻልኩም:: ዐይን ትልቅ ነው ሲባል ይለካል? በምን ይለካል? ፀጉሬ ቀይ ነበር:: ቡናማ ቀይ ነበር:: ጥቁር አይደለም:: የአባቴ ፀጉር ጥቁር ነበር:: ጥርሶቼ ትላልቅና ነጫጭ ናቸው:: ታችኛው ጥርሴ በሸግን መበላሸት ጀምሮአል:: አንገቴ ጥቁርና ጭቅቅት የሸፈነው ነበር:: አመልካች ጣቴን በምላሴ አርሼ አንገቴን ስፈትገው መወርወሪያ የሚያክል እድፍ እየተሽመለመለ ወጣ:: መስታወቱን እነበረበት መልሼ ጊዳ ገባሁ:: እናቴና እህቴ ከውጭ ማድቤት አጠገብ ሲሳሳቁ እሰማለሁ:: ጥቂት ሳንጐዳጉድ ቆይቼ የልብስ ሳሙና ይዤ ወጣሁ ....ወደ ወንዝ:: የወንዙ ስም አንድ አይጠጣሽ ይባላል:: ደርቆ የማያውቅ ወንዝ ነበር:: ክረምት ክረምት ሰው፣ ዛፍ፣ ከብት በፈረሰኛው ተሸክሞ ይሔዳል በጋ በጋ ግን ድምፁን አጥፍቶ ጨዋ ግውዝነቱ ውስጥ በውሐው ጥራት፣ በድንጋዮቹ ምቹነት የማይጠራው የማይሰበሰበው ልብስ አጣቢ፣ ዋናተኛ፣ ውሐ ቀጂ አልነበረም:: ሠፍራ ን ንፁህ የውሐ ቧንቧ ከመግባቱ በፊት የሚጠጣ ውሐ ከዚያ ይመጣ እንደነበረ ትዝ ይለኛል:: በዚያ ጊዜ 'የወንዝ ውሐ ንፁህ ነው' ሲባል እሰማ ነበር:: በሁዋላ በሁዋላ 'የወንዝ ውሐ ቆሻሻ ነው' ሲባል ሆነ የምሰማው::

ወንዝ ስደርስ ከብቶችን ውሐ ከሚያጠጡ እረኞች በስተቀር ማንም አልነበረም:: ከመንጋው ከፍ ብዬ ልብሴን አውልቄ ጥልቅ ያልሆነ ቦታ መርጬ እስከ ወገቤ ወንዝ ውስጥ ገብቼ ቆምኩ:: ከእኔ በስተላይ አልፎ አልፎ ወንዙ ሲያቃስትና ሲጉመጠመጥ እሰማዋለሁ:: የዚያ አካባቢ ሰዎች በጥንት ጊዜ ሸግዬ(15) የተባለ ወጣት ወድቆ የጠፋበት ነው ይላሉ:: እኔ ምን ችግሮኝ:: መታጠብ ጀመርኩ:: ከታች የሚጠጡት ከብቶች «ምናባቱን ነው ማነው ከበስተላይ መርገዝ የሚለቅብን» ሳይሉ አይቀርም:: ዕድፌ እንደ ልብስ ይገፈፋል:: ገላዬ ላይ የማሸው የሳሙና አረፋ እየደጋገመ ቡላ ይሆናል:: ከቆዳዬ የሚረግፉት የእድፍ ፈረቃዎች በብርብራ እንደሰከሩ ትናንሽ የወንዝ አሳዎች እያበዱ ይሰርባሉ:: የአምስት ስድስት ዓመት ፍቅረኞቼ ነበሩ:: የእኔ ላብ፣ የሰፈሬ አቧራ:: የሰፈሬ አቧራ- አባቴ፣ እህቴ፣ እናቴ፣ ፈረስ፣ ከብት፣ ሰው ሁሉ ያስነሱትና የረገጡት አቧራ.....አምስት ስድስት ዓመት የተራራ ንፋስ የነፈሰበት.....የተራራ ንፋስ የተሸከመው አቧራ፣ በጋ ከክረምት የነፈሰበት::

በከንፈሮች.....የንፋስ ከንፈሮች.....እየተዳበስኩ በራሴ የላብ ድርቆሽ፣ በራሴ የወዝ ክርታስ እንደ አቾሎኒ ተጠቅልዬ......ጉብታዬ ላይ በገበያ ጠረን፣ በቅመም ተራ ንፋስ፣ በበግ ተራ ንፋስ.....የነዚህም ጠረናቸው እንደ አረፋ ቆዳዬ ላይ ሰፎብኝ፤ አባራውም ሳላውቀው ሳላየው በቆዳዬ.....እዚያ ቆዳዬ ላይ በሙቅ ደለሉ፣ በሙቅ አመዱ ከጥፍሬ እስከ ግንባሬ ሲለስነኝ......ብሌኔም ዙሪያ የቅንድብ ጉፈሬዬ ዙሪያ እንደ ዝምዝማት......

ተጣጥቤ ጨረስኩና አዲስ ቆዳዬንና አዲስ ልብሴን ለብሼ ቤቴ ስገባ ከበው ራት ሊበሉ ደረስኩ:: ሰቡ ያለቀ ሳሙናዬን ሳያዩኝ እነብረብት ጓዳ መልሼ ለእራት እስኪጠሩኝ እውጭ ስብሳብ ስር ተቀምጬ ጠበቅሁ::

መሽቶ መሽቶ እእ እንዲህ አለች:

"አንተ! አንተ! ሳሙናውን አንተ ነበርክ የወሰድከው?"

መልስ አልሰጠሁም::

መኝታ ቤቴ ገባሁ:: መስኮቱን ከፍቼ ወደ ውጭ አየሁ:: መፈክር የምፍከብት ወረቀት ከግራና ቀኝ ተቀንፎ ወደ መሐል ተጠቅሏል:: ጠርዞቹ የተቃጠሉ ይመስላሉ:: የሚያስጠላ ቢጫ ሆኗል:: ለአቤ ፎቶ መስቀያ ነገ ምስማር ማግኘት እንዳለብኝ ወሰንኩ:: ሰማይ ላይ (በመስኮት ፊቴን ወጣ አድርጌ ሳይ) ክዋክብት የውድ ምስማር ቆቦች ይመስላሉ ከብር፣ ከወርቅ፣ ከአልማዝና ከዳንግ የተሰሩ......

ፀጥታ ነበር::

የፌንጣ ጉራ እንኳን አይሰማም::

ቆንጆ::

ጓዴ ቅልል ብሎኝ ነበር::

ምኔን ወንዝ ጥዬው መጣሁ?



@BOOKALEM

# እህቴና የአበበ እጅ

አበበ ስሙ ደስ ይለኝ ነበር:: ረኸርም፣ ትክክሻው ሰፊ የሆነ ልጅ ነበር:: አፉም ሰፊ ነበር:: ሲስቅ ሌላ ወረዳ ይሰማል:: ትምህርት ቤት ውስጥ እሱን የማያውቀው ተማሪ፣ የማያውቀው አስተማሪ አልነበረም:: የማይላፋው ተማሪ የለም:: የማያዘው አስተማሪ የለም:: የማይወደው የለም:: እኔ ሌላውን ባላውቅም በስሙ እቀናለሁ:: ስሙ ለእሱ መሰጠቱ ግን ያበሽቀኛል:: ብዙ ጊዜ ስፖርት ሜዳ የማየው ከሴቶች ጋር ቮሊቮል ሲጫወት ነበር:: ፀሐይን ከመሰሉ የሚንጫጩ፣ የሚበላቀጡ፣ ነጭናጫ፣ ወሬኛ፣ ጮሌ ከሚባሉ ሴቶች ጋር ብዙ ጊዜ ቮሊቮልሲጫወት አየዋለሁ:: ስም ያበላሻል:: ሲሮጥ ግን አይቸው አላውቅም:: ስም ያበላሻል:: አበበ የሚባል ስም ቢኖረኝ በየቀኑ አራት ሰዓት እሮጥ ነበር:: በየቀኑ ላቤ ጠፍ ብሎ እስኪያልቅ እሮጣለሁ:: እግሮቼን ደክሞኝ እስክወድቅ እሮጣለሁ:: እሱ የሚያደርገው ግን ምንድነው?......ከሴቶች ጋር ቮሊቮል መጫወት:: ታዲያ ሴቶች እያቆላመጡ ይጠሩታል:: እበሽቃለሁ:: እያቆላመጡ ይጠሩታል:: አቤ፣ አቢቲ፣ አባዬ፣ አቡ፣ አብ፣ አቢነት፣ እብሽ ሌሎች ብዙ አፈጣጠራቸው የሚያስደንቅ ስሞች:: እበሽቃለሁ:: አበበ ቢቂላን ግን ምናልባት አንዳንዴ 'አቤ' ብንለው ነው:: ከሴቶች ጋር ቮሊቮል ስለተጫወተ፣ ጥሩ ልጅ ስለተባለ ዝነኛ አድርጉ በስምንት በአሥር ሥም ማሞካሸት ከብትነት መሰለኝ::

እኔ ቮሊቮል አልጫወትም ነበር.....እንደ ሴት? ማየት እይ ነበር:: ማየት ምንም አይደለም:: ታዲያ እህቴን አንድ ቀን ከአበበ ጋር አየሁዋት:: አብረው ጐን ለጐን ቢሄዱ ጥሩ:: ግን ያን የማይረባ ቮሊቮል የተጫወተበት እጁን ቂጧ ላይ ሲያስቀምጥ አየሁት:: ቂጧ ላይ ቢያስቀምጥ ምንም አይደለም እንበል፣ ግን ጣቶቹን በቀስታ ያንቃንቃቸዋል:: እጁን አስቀምጦ ጣቶቹን ቢያንቃንቅ ምንም አይደለም እንበል፣ ግን እህቴ ደስ ብሏት በዳሌዋ ነካ ነካ አድርጋው እየተሽኩረመመች በሳቅ ፍርስ አለች:: ምን ያስቃል? አንድ ሴት እጇን ቂጤ ላይ ብታስቀምጥ ተሽኩርምሜ በሳቅ እፈርሳለሁ እንዴ? ወላ ዐይኗን ነበር የማጠፋው:: አበበ ጀጋው የእህቴን ቂጥ እዚያ ሲነካ ወላ እኔ ራቅ ብዬ እያየሁ እበግናለሁ:: ደግሞ ደስ ይላታል:: ደግሞ እሱ በሰው ስም ይነግዳል:: አበበ ቢቂላ የቢቂላ ልጅ ሯጭ እንጂ ሽፋዳ አይደለም:: ይኼኛው አበበ የሚሰራው ትልቅ ነገር ቢኖር የኳስ ከመነዳሪ ማስተንፈስ ነበር:: ለአስተማሪዎች ቶከ ማምጣት ነበር:: ለዳይሬክተሩ ዝያ መላክ ነበር::

ግን በእህቴ ቂጥ ምን አገባኝ:: ቂጧ መአት ነበር:: ቢነካትም የሚሰማት አይመስለኝም:: ቢሰማት እንኳን ዛርብ ነክቷት እንደሆነ ከሁለት ቀናች በሁዋላ እሁድ



@BOOKALEM

ይሆናል:: ከሻማ ጨርቅ የተሰራው የውስጥ ልብሰዋ እንኩዋን መንኩዋኩዋቱ አያሳፍራትም:: ምን አገባኝ:: ግን አበበ በሰው ስም ይነግዳል......

ወዳጄ ዞመዴ አጋሬ ወዜ አበበ ቢቂላ ቢሞት ይሔኛው አበበ በሕይወት ቆሞ የሚያደርገው ነገር ቢኖር በስብ ያበጠ የገብስ እንጀራ በላተኛ ሴቶችን ቂጥ በመጋፊያ እጁ ጨብጦ ለቀቅ ማድረግ ነበር::



@BOOKALEM

# የዱባለ ጃኬት

ፀጉሬን አፍሮ ለማሳደግ ስለምሞክር አባቴ እንዳያየኝ እሱ ያለበት አካባቢ አልቀርብም ነበር። አባቴ ረዥም ፀጉር አይወድም። የንግዱ ፀባይ ሆኖ ሊሆን ይችላል። ፀጉሬ ጉፈር ጉፈር ካለ በምንገድ ስንተላለፍ የሚያደርገው ነገር ምንድነው ጭንቅላቴን ይዞ በፍጥነት ፀጉሬን ስቦ እርዝመቱን መፈተሽ ነበር። የስነስርዐት ፍላጐት አይመስለኝም። በቅርብ ተለውጦዋል። አባቴ በቅርብ ተለውጦአል። በሬዲዮ የሚሰማው ነገር ልዩ ደስታ የሚሰጠው ይመስለኛል። ንጉሠነገሥቱን እወዳለሁ ሲል የነበረው ሰውዬ ፎቶአቸውን አውርዶ ጓዳ አስቀምጦታል። ማለቴ የእኔ የአበበ ቢቂላ ፎቶ እስከ ዘላለም የምትሰቀል ናት። ይመስለኛል።

አበበን ቢሞትም አልረሳውም። አበበ በሕይወት ቢኖርና አበበ አባቴ ቢሆን የፀጉሬን እርዝመት አይለካውም። አንዳንዴ ፎቶውን አይቼ፣ ፊቱንና አሯሯጡን አይቼ መሞቱ ትዝ ሲለኝ አለቅሳለሁ። የዕውነት አለቅሳለሁ። አባቴ ታዲያ ፀጉሬን እየጐተተ ይለካል። ፀጉር ትልቅ ቁም ነገር ነው? ሐይለሥላሤ አፍሮ ይቆረጡ የለ ለምን አይጠላቸውም ነበር? ልቡ ግልፕ አልነበረምና የሚወዳቸውን ሐይለሥላሤ እንኳን አልጋ ስር ደብቆአል። ደ'ሞ "ደርጉ" የሚባል ነገር ስለመጣ ካለሱ የሚያወራው የለም። ይኼ ደርጉ ምን ዐይነት ነገር እንደሆን አይገባኝም። ባይገባኝም ግድ የለኝም። የማውቀው ነገር ግን ስለማራቶን አለመሆኑን ነበር። ስለአበበ ቢቂላ ስለማም ወልዴ አለመሆኑ ነው። ሶሻሊዝም እንግሊዘኛ ነው። የአማርኛው አይያዝልኝም። ትምህርት ቤት ውስጥ ሁልጊዜ የሚወራው ደርጉ ደርጉ ሶሻሊዝም ሶሻሊዝም ነበር። እንዳለለችኝ።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ገጠር ትዘምታላችሁ ተብለው ያቁነጠንጣቸው ነበር። እኔ ወላ የትም መሔድ አልፈልግም። በሕይወት ቢኖር ኖሮና ብችል የአበበ ቢቂላ ጉረቤት ሆኜ ጠዋት ጠዋት ለሩጫ ልምምድ ሲወጣ ባየው እመኛለሁ። ሯጮች አምቦ ውሐ ነው አሉ የሚጠጡት። ለአበበ ቢቂላ በጆርባዬ ሳጥን ሙሉ ተሸክሜ አመጣለት ነበር።

አባቴ ፀጉሬን ለመለካት ሲጐትት ሸርጡን አልለበሰም ነበር። ጃኬቱ አልኩል አልኩል ይሸታል። የደንበኞቹን የማጅራት ፀጉር በምላጭ ከከረከመ በሁዋላ የሚቀባቸውን አልኩል ይሸታል።

አባቴ የአልኩል ሐውልት ነበር። እጁ እግሩ ሁሉ ፊቱ ሁሉ፣ እናም የአባቴ ጃኬት አልኩል አልኩል ይሸት ነበር።

ስለምን እንዲህ ብቻ ይሸታል?



@BOOKALEM

ከእሱ ላብ አልተወለድኩምን?

ከእሱ አብራክ ወዘ አልተቀፈቀፍኩምን?

በቤት ውስጥ ወዲያና ወዲህ ስል የጠረኔን ጉም በገላው ቀዶ አላለፈምን?

አጥንቶቼ ከተዘፈቁበት ደሜ ይልቅ የእሱ አልኮል ጎልቶ ሲሸት አይገርምምን?

ለምን ትንሽ እንኳን እኔን እኔን አይሸትም ነበር?



@BOOKALEM

# ደሂ ምግባስ

በጣም የሚያበሽቀኝ ነገር ጉብታዬ ላይ ሰዎች መሰብሰብ መጀመራቸው ነበር:: ቀንና ማታ ሰው አሳጣም:: ሲሰበሰቡ ደ'ሞ የሚያወሩት ስለ አብዮቱ ነበር:: ተፈሪ ባንቲ ስለሚባል ሰው ያወራሉ:: እነዚህ ሰዎች መርጥ የማይችሉ ከሆነ ግድ አይሰጡኝም:: ኩሉኔልና ጄኔራል ደ'ሞ አይሮጥም:: የሚሮጡ አሥር አለቆች ናቸው:: ተሰብስበው ስለ አበበ ቢቂላ ቢነጋገሩ መልካም:: ስለስራ ማቆም አድማ ያወራሉ:: አባቴ ቢያቆምስ? ቢያቆም ጥሩ ነበር:: ከተማው በሙሉ አፍሮ እንዲሆን:: እኔም «ሰውን ልምሰል» ብዬ አፍሮ እሆን ነበር:: ግን የረባ አያወሩም:: ቢሰበሰቡ ጥሩ......የሚደብት የማይዝ ነገር ነበር ግን የሚያወሩት:: ሲያወሩ ደ'ሞ በስሜት ነበር:: ከጉብታዬ እንዲሔዱ፣ እንዲርቁ እፈልጋለሁ:: ሌላ ቦታ አያወሩም? ድሮ የት ነበር የሚያወሩት? የከተማው ሕዝብ ቁጥሩ ጨምሮ ቦታ ጠበባቸው እንዴ?

ስለዚህ ከሰዎቹ ቀድሜ ወደ ጉብታዬ መሔድ እገደድ ጀመር:: ግን ብዙ ጊዜ የእኔ እዚያ መኖር ግድ የሚሰጠው አልነበረም:: አንዳንዶቹ እንደውም ቀድመውኝ ይደርሳሉ:: በቅርብ ደሞ የለውጥ ሐዋርያ የሚባል ሰው ለከተማው ሕዝብ ንግግር ሊያደርግ ተጠርቶ ካልጠፋ ቦታ የት ይቆማል? ጉብታዬ ላይ:: ሳንድሮቨሩን ጉብታዬ ላይ አውጥቶ እሱ ሳንድሮቨሩ ላይ ቆሞ ብዙ ለፈለፈ:: 'ኢትዮጵያ ትቅደም' ብለው ደሞ ባለዐንድ ዐይን መኪናቸው ላይ ስዕል ስለዋል:: አንድ ዐይን? ለምን ሦስት አይሆንም? ሳንድሮቨራቸው ሰብራ ነበር ማለኝ ኬሔዱ በሁዋላ ጉብታዬ በሙሉ በፍሬን ዘይት፣ በግራሶ፣ በነዳጅና በእኩታ ተበላሽታ መቀመጥ አልቻልኩም::

የለውጥ ሐዋርያ የተባለውን ሰው ሰበካ ያልሰማው ያለ አይመስለኝም:: አባቴ ውጥቆ ሻማ ሸርጡን ወይም ጃኬቱን እያንሿሿ፣ በአልኮልና በጂጉር በናኝ ተከቦ ነበር አፉን ከፍቶ ሲሰማ ያየሁት:: አቶ እንግዳ ሐዋርያው ጎን ቆመው ጭንቅላታቸው እስኪወልቅ ድረስ ላይና ታች እየነቀነቁ በሚባለው ነገር ሲስማሙ ነበር:: እነዚህ ትላልቅ ናቸው የሚባሉት ሰዎች አንዳንድ እንግዳ ነገር ያደርጋሉ:: ዝምተኛ ይመስሉ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ያወሩ ጀምረው ነበር:: ዝም ብሎ ቆይቶ የሚያወራ የሚለፈልፍ ሰው አያስጠላም? ወይስ ድሮ የዝምተኛነት ስሙ ሌላ ነበር? ወገት እያሰጡ ጨዋታ ነው እያሉን:: ወላ ሲሰለቸኝ ወንዝ ወርጄ ታጠብኩ:: ቆንጆ ልጆች መታጠብ አለባቸው:: ስመለስ ታዲያ ጉብታዬ ተበላሽታ፣ መቀመጥ የማልችልባት ቦታ ሆና ሳሯ ተረጋግጦና በከፊል ተመልጣ አገኘሁዋት:: አዋቂ የተባሉ ሰዎች ለምን ማበላሸት እንደሚወዱ አላውቅም::



@BOOKALEM

*(አፍ ያለው ይቆላል ይለኛል አገሬ*
*እኔን የሰለቸኝ ቆሉ ጥራጥሬ*
*መገድልኝ ባለአፍ ጥሬም አይቆላ*
*ሥጋ ቅባቅቤ ጤፍ እንጀራ እንብላ።*
*......**የንፋስ መውጫ አዝማሪ**)*

የምሔድበት ባጣ ሙስጠፋ ቤት ሔድኩ። ሙስጠፋ ሽርኪ በነፃ በራድ ቀዳልኝ። ሙስጠፋ በዕድሜ ብዙ ይበልጠኛል.....ግን ሽርኪ ነበር.....አራዳ በዕድሜው ጉራ አይነፋም። አንዳንድ አዋቂ ነን ባዮች (ምን እንደሚያውቁ ባላውቅም) ግን የሰው መዝናኛ፣ ማረፊያ እያበላሹ አራዳ ነን በስለናል ለማለት ሲሞክሩና ሲሆንላቸው አይቼአለሁ።



@BOOKALEM

## መሳጣ

እንደዚያ ዐይነት መሳጣ ዐይቼ አላውቅም:: የሚያጸልጥ ይመስላል:: ቢቆሙበት የሚጥል:: ከመሳጣው የበለጠ ደ'ሞ ይሔን ዐይነት መመለጥ ሳያጉረመርም የተቀበለው የጭንቅላቱ ባለቤት ይገርመኛል:: ካላጉረመረመው ባለቤቱ የበለጠ የገረመኝ ደ'ሞ የምላጩ ስለት ነበር:: መሳጣውን የሚያይ ሰው እንደ አየር የተባ ምላጭ ትዝ ይለዋል:: በመጀመሪያ ሲጃራውን እያጤሰ መጥቶ ሲቀመጥ መሳጣውን ልጅ የማላውቀው መሰለኝ:: በራዴን በባዶ ሆዴ እየጠጣሁ ነበር:: ወዳጄ ልቤ ሙስጠፋ ከስቶአል:: መክሳት ብቻ ሳይሆን ፀጉሩ አድጐ ግንባሩን ሁሉ ሸፍኖታል:: በራድ በነፃ የሚሰጠኝ ምናአልባት ማልቀሱን ማየቴ ለረዥም ጊዜ አሻርኮን ይሆናል:: በራድ ባይሰጠኝም አልነግርበትም ብዬ ለራሴ ምዬ ነበር—ብልቤ(መቼም እሱ በራድ ለዘለዓለም አይሸጥ እኔም በራድ ለዘለዓለም አልጠጣ):: አንድ የአዲሱ ሠፈር ልጅ የሙስጠፋን ትከሻ በቦክስ እየመታ እየለከፈ ይደንሳል:: እየደነሰ ነው ታዲያ:: የአራዳ ልጅ ይመስላል:: (ዋናው ከተማ ደርሰው ሲመለሱ አንዳንድ ልጆች ይለወጣሉ:: ከእነዚህ አንዱ መሆን አለበት ይሄ.....ያውም ለአንድ ቀን ተንሸራሽሮ የመጣ) እየደነሰ ነው የሚለከፈው:: ሙስጠፋም ሊመታው ይፈልጋል:: ተያይዘው ሲላፉ ቆዩና ተላቀቁ:: ሳቅሁ:: ደስ ብሎኝ:: እነሱ በተላፉ እኔ ደስ ብሎኝ:: ልጁ ከባንኮኒ ላይ ዕንቁላል አንስቶ እየሮጠ ወጣ:: ሙስጠፋ በሽቆ ጮሆ ይናገራል......."ትመጣለህ ቆይ" ውሽቱን:: በበር ወርቅ የመሰለች የፀሐይ ብርሃን ገብታለች:: ዕንቁላል የወሰደው ልጅ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ተመልሶ መጣ:: ከሙስጠፋ ጋር አፍ ለአፍ ገጥመው ማውራት ቀጠሉ::

መሳጣው ሲጃራውን መተርኮሻ ውስጥ ጥሎ በአመልካች ጣቱ እያሸ ሲያጠፋ ከጉን አየሁትና አወቅሁት:: ከጉኑ ሳየው ነበር ያወቅሁት:: ያን ቀን በመጀመሪያም ከቦታዬ ተነስቶልኝ እንደ ሆን ለማየት ስመላለስም ልጁን ያየሁት ከቀኝ ጐኑ ነበር፣ እና ጐኑን ሳይ እሱ መሆኑን አወቅሁ:: (ሰውን በከፊል ጎኑ ማወቅ አይገርምም? ከፊልነቱ ምን ያህል ሰፊ ቢሆን ነው ሁለመናውን የወከለው?)

"ሻይ ትጠጣለህ?" አልኩት

"እሺ" አለኝ

"ሙስጤ አንድ ኩባያ አስኪ" አለ ልጁ

ሙስጠፋ ብርጭቆ ሳከልንና: "ትተዋወቃላችሁ እንዴ?" አለን ከባንኮኒው በጩኸት::

በዝምታ እየሳቅን አየነው:: ወሬውን ከሌላው ልጅ ጋር ቀጠለ::



@BOOKALEM

ለልጁ ስለሩጫ ሳነጋግረው ፈልጌ መጀመሪያ ያነሳሁለት ወሬ "ስፖርት ትወዳለህ?" የሚል ነበር:: ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ::

"ምን?"

"ዋና እወዳለሁ.....ሁልጊዜ ወንዝ እወርዳለሁ"

"ሩጫስ?"

"ሩጫ?"

"እም"

"ሩጫ ስፖርት አይመስለኝም.....አትሌቲክስ አልወድም"

ቀስ በቀስ ስለ ማራቶን አነሳሁለትና ስለ አበበ ቢቂላ ዝርዝር ታሪክ አወራሁለት:: አበበ መቼ እንደተወለደ፣ የት እንደተወለደ:: የቁመቱን ዕርዝመት፣ የልጆቹን ብዛት፣ የባለቤቱን ሥም፣ በሮምና በቶኪዮ የለበሳቸው የሹራብ ቁጥሮች፣ የገባባቸው ሰዐቶች፣ በመጨረሻም እቤቴ ስለ ሰቀልኩት ፎቶ አወራሁት:: በጥሞና ሰማኝ:: እሱ ያወራኝ ነገር የለም:: ዋና እወዳለሁ አለኝ.....ግን ስለዋናተኞች አላወራኝም:: በልጬዋለሁ:: እንደበለጥኩት ይገባዋል:: እንደበለጥኩት አውቃለሁ:: ከመሐል ጥሩ እንደሚዋኝና የሚዋኝበትን ቦታ ማየት እፈልግ እንደሆነ ጠየቀኝ:: በሚቀጥለው ቀን ሊያሳየኝ ተስማማን:: ሁለታችንም ትንሽ ጉራ የነፋን መሰለኝ:: ጉራ ሊሆን ግን አይችልም:: እኔ እውነቱን ነበር የተናገርኩት:: እሱም ዕውነቱን ሊሆን ይችላል:: መዋኘት ባይችል አይጋብዘኝም ነበር::

መመለጡ ግን አብሽቆኛል::

"ለምን ተላጨህ?" አልኩት::

"አጐቴ ላጨኝ" አለ::

"ዝም ትላለህ?"

"የሚያምር አፍሮ ነበር አይደል?"

"አዎ"

"አጐቴ ዱካክ ነገር ነው እንደተኛሁ ከፊት ለፊቴ በመቀስ ቆረጠው" ብሎ በቦክስ ጠረጴዛውን መታ:: ያምራል:: አባቴ ሲናደድ ሁልጊዜ (ትንሽ እንኳን ቁንጡን አይለውጥም ነበር እንዴ?) በቀኝ እግሩ መሬት ይረግጣል:: በእግር መሬት ሲረገጥ ምንም ነገር አይሆንም:: ጠረጴዛ በቡጢ ሲመታ ግን ጠረጴዛው ይነቃነቃል፣ ከፍተኛ ድምፅ



@BOOKALEM

ይወጣል.....ሲኒዎች ተነቃንቀው ሻይ ይፈሳል። በእግር መሬት ሲረገጥ ግን ምንም አይሆን የረጋጮቹ ጉልበት ቢታመም ነው። በእግር መሬት ሲረገጥ ዛፎች አይነቃነቁም።

"ከዚያ ዱባለ ጋ ሔጄ ተጣልሁ.....ሣንቲም ተረፈኝ ለሲጃራ.....አየሽ አንድ ብር ተሰጠኝ በሃያ አምስት ሣንቲም ተጣልሁት"

አባቴ እንዲህ ዐይነት ሥራ ነበር የሚሰራው.....የመልካም ጉረምሶችን ፀጉር የመግፈፍ.....ከአጎት ወደ አባት ከአባት ወደ አባት። እየተቀባበሉ ጨረሱን.....ሴራ ነገር ያለው ይመስል ነበር። ልጁ የማያጨሰውን ሲጃራ እንድወጋው ሰጠኝ። ሙስጠፋ እየሰራ በጉን ያያል። እየተናደደ ያየኛል። ሲጃራውን ተቀብዬ አንድ ሁለቴ ሳብኩና "ቂሟን ስጠኝ" አለና ለመሳጣው መለስኩለት። ሲጃራዋን ምጥጥ አድርጐ እየጠባ በጉን ፈገግ ብሎ አየኝ።

ፈገግ አልኩ።

ከጉብታዬ መበላሸት በስተቀር ያ ቀን ውብ ነበር......

በተለይ የማታ ፀሐይ ወርቃማ ፓስቴዎቹ ላይ እንደ ጨዋታ አድርጋ ስታብራ። እና የሚያስጎመጅ ውጋጋናቸው።



@BOOKALEM

# ቮሊቮልና ቱታ

ከከተማችን አንድ ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ ብሉ ሚሽኖች በሚያምር ቀይ ሸክላና ኑሞ ብሉኬት ውብ ቤተክርስቲያን ሰርተው ቄሶችን፣ ሐጂ አህመድንና ምዕመኑን ግራ አጋቡት:: እንደውም አንድ ቀን ጥቂት ሰዎች እንደ ከተማው ልዑካን ሆነው በዚህ ቤተክርስቲያን መገንባት እንዳልተደሰቱ ለመግለጥ ጠዋት በ3.00 ሰዓት ሔደው የሚደንቅ መልስ ተሰጥቷቸው ከምሽ ሰዓት በሁዋላ ተመለሱ:: ቆይቶ ስንሰማ የከተማው ጉድጓድ ውሐ የተሰራው በዚህ ቤተክርስቲያን ዕርዳታ ነው አሉ:: ይኼን የሰማሁ ዕለት አንጀቴ እስኪቆስል በሳቅ ፈረስኩ:: ምክንያቱም ያ ሁሉ የከተማ ሕዝብ እኔ ላይ አቅም የሌለኝ ስወለድ የተረገምኩ ሰው ላይ ብልጥ ሲሆን ለዘለዓለም የማይሸወድ ይመስል ነበር:: ታዲያ አንድ የቤተክርስቲያን ድርጅት እግራቸው ስር መሬት የተኛ የራሳቸውን ውሐ ቆፍሮ አውጥቶ አጠጥቶ ውሐውን እየጠጣ ሲደሰትና ሰመመን ሲገባ.....ሲራጭ፣ ልብሱን እያጠበ ሲያሽት፣ ከታጠበች ሚስቱ ጋር ሲዳራ.....ቀስ እያሉ በሚገርም መልክ በራሱ በአገሩ አፈር፣ በአገሩ ሸክላ ተወዳዳሪ የሌለው የሚያምር ቤተክርስቲያን ሠርተው ቆጭ አሉ:: በሳቅ ሞትኩ:: ከዚያ ከንቲባችን ወሬ ወረደባቸው:

"እንግዳ እኮ ጉቦ በላ" ተባለ::

"ግንዘብ ሸጉጠውለት ነው" ተባለ::

እሳቸው ደ'ሞ ልክ ልክ ማስወራት ጀመሩ (እንግዲህ ካላረፍክ ልክ ልክህን ነው የምነግርህ አዳሜ'): "እንቁራሪት የሞተበት ውሐ መጠጣት ናፈቃችሁ.....እረኛ ከነከብቱ የዳከረበት ውሐ ጠማችሁ እንዴ?" እያሉ::

አባቴ ራሱ ሔዶ ነበር የፈረንጆችን ፀጉር ብቻ አይቶ የተመለሰ ይመስለኛል ያኔ ዕለት ማታ 'ለመሆኑ እንደው አንዱ ፈረንጅ አስተካክለኝ ቢለኝ እንዴት ነው የማደርገው? ሲል ነበር (የመጡለት ሰዎች ግን አልነበሩም)::

ሚሺኖቹ አራዳ ናቸው:: ከቤተክርስቲያናቸው ጋር.......ግቢያቸው ውስጥ ሁለት የቮሊቮል ሜዳና የአበባ እርሻ ሰርተዋል:: የመሰብሰቢያ አዳራሻቸው ወንበሮች ማማር.....የግድግዳዎቹ ንፅሕና የሚገርም የሚገርም ቄንጥ ነበረው::

እንደተለመደው ጉብታዬ እዚያችው ከተማ መሐል እንደተቀመጥሁ (ብትቆሽሽም አለቀቅሁዋትም) ዋናውን የመሀል ምንገድ ተከትሎ የመዝሙር ድምፅ እንደ ወንዝ እየጎረፈ ሲመጣ ሰማሁ:: እዚያ አካባቢ ድምጹ የተለየ ድምቀት ነበረው:: ከአንድና ከሁለት ኪሎ



@BOOKALEM

ሜትር ዕርቀት ምን ዐይነት ዕንጥሎች ተሻርከው ይኼን ዐይነት የሚያምር ድምፅ እንደ ወለዱ ገረመኝ:: ሳስበውማ ዘማሪዎቹ በሙሉ እያንዳንዳቸው ቱቦ በመሰለ ነገር ውስጥ ይዘምሩና እያንዳንዱ ቱቦ ደሞ ወደ ትልቅ ቱቦ ተያይዞ ይሔም ትልቅ ቱቦ ከሌላ ከሚበልጠው ትልቅ ቱቦ ተያይዞ.....ይሔም ትልቅ ቱቦ የአፉን አቅጣጫ ወደ ከተማው መሐል አድርጎ ዘፈኑን ወደ እኛ የሚልክ ይመስል ነበር:: ከመዝሙሩ መሐል መሐል ደወል ይሰማል:: የቤተክርስቲያናቸው ፊት ለፊት ወደ ላይ ሾጠጥ ብላ የወጣች ዐይነት ናት:: ይህቺ ሾጣጣ ጫፍ ላይ ዕንቁላል የመሰለች ደወል አለች:: የከተማችን የመድሃኒያለም ደወል በብረት ዱላ የሚደበደብ ነበር:: ሲደውል ሲያል ድረስ እንዲሰማ ነው መሰል ግራጫማ ድምፁ አርበትባች ነገር ነበረው:: የሚሽናቹ ደወል ግን የምትሰማው ለሰው ብቻ ይመስላል:: ከዚህ ከሰው ጆሮ አትርቅም::

እንዴት እንደሆነ እንጃ የትምህርት ቤት ተማሪዎች አሁንም አሁንም ስለሚሽኖች ማውራት ጀመሩ:: ስለሁሉ ነገር.....በተለይ ስለአንዲት ከሚሽኖች ጋር ስለምትኖር ርብቃ ስለምትባል ረዥም፣ ዕንግዳ ዐይነት ቀሚስ ስለምትለብስ መልከ መልካም ሴት:: ያው ነበር:: ሁሉ ነገር ያው ነበር:: አንድ ቀን ልቤ ዳድቶ ነበር ሚሺኖቹ ዘንድ ለመሔድ:: እዚህ ከሰለቸኝ ለምን እዚያ አልሔድም ብዬ:: የንፋስ መውጪያ ልጅ አለች ሲባል ግን ከልቤ አወጣሁት:: የማመልጥበት ቦታ ሔደው ልዩ ቀሚስ ለብሰው ንፋስ መውጫዎች እየጠበቁኝ ነው አልኩና::

አንድ ቀን ማታ ርብቃን አየሁዋት:: ትምህርት ቤታችን በር ላይ ቆማ ወደ ቤታቸው ለሚመለሱ ተማሪዎች ወረቀት ስታድል:: በወረቀቱ ፊትና ጀርባ የእግዚያብሔር ቃል ነው አሉ የተፃፈበት:: ሰበካ:: የምታምር ሴትዮ ናት:: በተለይ ስትስቅ የጥርሶቿ ንጣት:: ትልቅ ብሆን ጠልፌ አወስዳት ነበር:: እንቢ አልጠለፍም ካለችም ክርስቶስ አይወደውም ብላ......ጥርሷን ለብቻ አርግፌ በኪሴ እንደ ቆሎ መያዝ:: ወረቀቱን እየሰጠችኝ ፍልቅቅ እያለች "ኢየሱስ ክርስቶስ ካንተ ጋር ይሁን" አለችኝ:: ክርስቶስ ሁልጊዜ ጐኔ እንደቆመ አውቅ ነበር:: ስጠቃ ምንም አይሰራልኝም እንጂ:: ጐኔ ቆሞ ሲከብደኝ ይታወቀኛል:: የተልባ እግር ልብሱ ትንሽ ከከሊታዬ ከፍ ብሎ እንጉቴን ይኮረኩረኛል:: ጥርሷን ከመፋቅ ተቆጥባ አተኩራ በስተግራዬ በኩል ብታይ.....የሆነ ዐይነት ጀለብያ ወይም ጋቢ ለብሶ ጢሙን አንዥርግጎ ከጭንቅላቱ ዙሪያ ቀለበት የመሰለ ፋኖስ እየነደደ.....አንድ እጁን ወደ ላይ ሰቅሎ መዳፉ መሐል ያለውን የምሥማር ብስ ለሚያዩለት እያሳየ:: ለምን ሁለቱን እጆቹን ወደ ላይ አያነሳም? (ስንት ዘመን ያህል አንስቶ አንስቶ ቢደክመው)—አታይም እንጂ:: እኔ ደ'ሞ ያን ቀን የምጠላውን የታሪክ ትምህርት ተምሬ፣ ደብተሬን በቀበቶዬና ˈበሆዴ መሀል ሸጉጬ በስልቾታ ተሰብብሬ እየተጉተትኩ ስወጣ በር ላይ አገኘሁዋት::

"እየሱስ ክርስቶስ ከአንተ ጋር ይሁን" አለችኝ::



@BOOKALEM

እግዜር ከእሷ ጥርስ ጋር ነበር ያለው። ቢባረክ አይደል የነጣው። ታዲያ ወረቀቱን ስትሰጠኝ በቸልታ ተቀበልኩና ምንገዴን ቀጠልኩ። የመጀመሪያው ገፅ ላይ ይሁን የሁለተኛው ገፅ ላይ ትዝ አይለኝም ከአናቱ ላይ ይሔ ተፅፎአል:......

*"ሕፃናትን አትከልክሉአቸው ወደ እኔ ይምጡ መንግስተ ሰማያት የእነሱ ናትና"*

ጨባበጥኩና ወደ መሬት ጣልኩት። ጣልኩና የተድቦለቦለው ወረቀት መሬት እንኳን አልነካም መሰል ዞር ስል ከልጅቷ ጋር ተያየን። ፊቷ ላይ ከባድ ቅሬታ አነበብኩ። ምናልባት የቄስ ልጅ ነው ብላ ትጠረጥር ይሆናል። እንደገና ለመሳቅም ሞከረች። ያማረባት አልመሰለኝም። ፊቴን መልሼ ደብተሬን እንደጠገበ ሰው እያሸሁ መንገዴን ቀጥዬ ዞር ስል ከትምህርት ቤት ግቢ ከሚወጣ አንድ አስተማሪ ጋር ጉንጭ ለጉንጭ ሲሳሳሙ አየሁዋቸው። ይኼ አስተማሪ ከመወለዴ በፊት ሁሉ እዚያ ከተማ ነበር ይባላል። እኔ ነፍስ ሳውቅ ጀምሮ ሲያደርግ የማየው አራት ነገሮች ነበር:— ማስተማር፣ ጠላ መጠጣት፣ ሲጃራ ማጤስና፣ አቅመ ሔዋን የደረሱ ልጃገረዶችን ማስረገዝ። ከተማው ውስጥ የነጋሽ ልጆች የምንላቸው ሦስት ትናንሽ ሕፃናት ሲቶች ነበሩ። ከተለያዩ እናቶች ቢወለዱም መልካቸው ተመሳሳይ ነበር። ቅፅል ሥሙ ለምን እንደሆን አላውቅም "ሐይለኛው" ነበር። እስከዛሬ ድረስ የቅጽል ስሙ አላማ አይገባኝም።

በትምህርት ቤታችን ብዙ ሳይቆይ ሚሽኖች ዝነኛ ሆኑ። የንፋስ መውጫዋ ልጅ የድሮ ስምዋ ዘቢደር ነበር ሲባል ሰማሁ። ሚሽን ከሆነች በሁዋላ ግን ስሟ ርብቃ ሆነ አሉ። ርብቃ ብሉ ሥም ዘቢደርስ ብሉ ሥም። የርብቃንም የዘቢደርንም ትርጉም አላውቅ። ብዙ ሳይቆይ ርብቃና ዘቢደር ላንድሮቨር መኪና እየነዳች ትምህርት ቤት መግቢያና መውጪያ ትቆምና ለፀሎት ወደ ሚሽኑ የሚሔዱ ልጆች መሰብሰብ ጀመረች። ወደ ክርስቶስ ለመቅረብ ሳይሆን በላንድሮቨሩ ለመሣፈር የማይሻማ ተማሪ አልነበረም። በተለይ ቤታቸው ወደ እዚያ አካባቢ የሆነ።

አንድ ቀን ትምህርት ቤት በር ላይ የተለጠፈ ወረቀት *"በንፋስ መውጪያ ሚሲዮን ለድሜያቸው ለጋ ለሆነ ወጣቶች የስፖርት በዓል ስለሚዘጋጅ ፈቃደኛ የሆናችሁ በዛ ተጋብዛችሁዋል። ለስፖርት የሚሆን ቲታና ሌላም አስፈላጊ የሆነ ለስላሳ መጠጥ በሚሽኑ ይታደላል። ፈቃደኛ የሆናችሁ እሁድ ከጠዋቱ 3 ሰዓት ጀምሮ ምዝገባ ስለሚደረግ እንድትመጡ"* ይልና *"ሕፃናትን አትከልክሏቸው ወደ እኔ ይምጡ መንግስተ ሰማያት የእነሱ ናትና"* በሚል ጥቅስ ይዘጋል። መከረኛ ጥቅስ። የመሔድ ጉጉት አደረብኝ። ግን ብዙ ነገር፣ ብዙ ደስታ ያጋጥመኛል ብዬ አልጠበቅሁም። በመጀመሪያ ዘቢደር የሰጠችኝን ወረቀት የጣልኩ ዕለት ስላየችኝና ስለአስከፋሁዋት ቤተክርስቲያን ውስጥ ላታስገባኝ ትችላለች ብዬ ጠረጠርኩ። ለማንኛውም ከዘፍ እኩል ስለምንቃ ነቅቼም የምሰራው ስለሌለኝ ቢኖረኝ



@BOOKALEM

ስለማልፈልግ እሁድ ጠዋት ርብቃ ቤተክርስቲያን ወጣሁ። በምንገድ ብዙ ልጆች አላጋጠሙኝም። የሚገርመው ቤተክርስቲያን ውስጥ ስገባ ከዎት እንደመጡ አላውቅም የትምህርት ቤቱ አንድ አራተኛ የሚሆኑ ሕፃናት ጉረምሳና ኮረዶች ተሰብስበው ነበር። ያውም የተቀመጡት በዕድሜ በዕድሜ፣ በፆታ በፆታ ነበር። ሴት በቀኝ፣ ወንድ በግራ። ሕፃናት በቀኝ ጉረምሳ በግራ። የመስበኪያው ማማ የሚያምር ነበር። የምትሰብከው ርብቃ ነበረች። ስገባ ስታየኝ ሳቅ አለች። የሳቀችው ለእኔም ሳይሆን ለአሰባበኪ ስልት ሊሆን ይችላል። ወይም ሠይጣን ላይ ክርስቲያናዊ ቀልድ ቀልዳ። አጠገቤ ያገኘሁት ወንበር ላይ ተቀመጥኩ። ያው በሕፃናት በኩል። የተቀመጥኩበት አግዳሚ ወንበር ላይ ማንም አልነበረም። ፊት ለፊቴ የተዘራ እሁት ባቄላ የሚያክል ወንድማን አትፋ ተቀምጣለች። የተዘራን እሁት ልዩ የሚያደርጋት ሻሽ አስተሳሰሯ ነበር። ሁልጊዜ በሻሿ ከዙዋላዋ የሚንጀላጀል ነገር ትሰራለች። ምን አልባት ፀጉሯ አልረዘም ቢላት በሻሽ ጨርቅ መተካቷ ይሆናል። ዕርብቃ ትሰብካለች። እኔ ስፖርቱ እንዲጀመር ነበር የምፈልገው። እግዚያብሔርን ከሷ የበለጠ የማውቀው ይመስለኛል። ለምን? አስር ደቂቃ ሳይሞላ በስብከቱ ተሰላቸሁ። ፊት ለፊቴ ወንበሩ መደገፊያ ላይ የተዘራ እሁት ሻሽ ግማሽ ሜትር ያህል ተንጠልጥሎአል። እሱን እንደ ክራር ክር በጣቴ እየመታሁ መጫወት ጀመርኩ። ድምፅ መቸም የለውም። የተዘራ እሁትም የማደርገው አይሰማትም። ሻሿ ንፁሕ ነበር። በጣቶቼ ሻሿን እየኮረኮርኩ እያለሁ የሚያምር ድምፅ ከሰገነቱ መጉረፍ ጀመረ። ርብቃ፣ ሁለት አሮጌ ፈረንጅ ሴቶችና አንድ ቀጫጫ ሀበሻ ሰውዬ ሕብረ–ዝማሬ ያደርጋሉ። አንድ ሌላ ፈረንጅ ከመድረኩ በስተቀኝ ፒያኖ (ያን ጊዜ ፒያኖ መሆኑን አላውቅም) ይጫወታል። ያምራል። የሚያስቅም ነገር አለው። አራቱ ሰዎች በሕብረት አፋቸውን ሲከፍቱና ፊቶቻቸው ላይ ትልልቅ ቀዳዳዎች ሲከፈቱና ሲዘጉ ሳይ የሚያስቅ ነገር ተሰማኝ። የሚያሻማ ስሜት ተሯሯጠብኝ።

*አምላክ እረኛዬ ነው፣*

*አምላክ እረኛዬ ነው፣*

*አምላኬ እረኛዬ ነው......።*

እረኛ የሚለውን ቃል ስሰማ ግን ያኔውኑ ውስጤ የተፈጠረው የስሜት ሽሚያ ፈረሰ። ወደ ግድግዳዎቹ አየሁ። በሚያማምሩ የክርስቶስ ስዕሎች፣ በጥቅስ ሰልፍ ግድግዳዎቹ ተንቆጥቁጥዋል ። እሱ እረኛ ከሆነ እኔ በግ፣ ላም፣ በሬ፣ ፈረስ ወይ አህያ ነኝ ማለት ነው። ስህተቱ እዚህ ያለ ይመስለኛል። ልጅም ሆኜ ብዙም የማይገባኝ ነገር ቢኖር ስህተቱ የሰው ነበር የሚመስለኝ። ልናገረው ባልችልም ይታወቀኛል። እውስጤ ይሰማኛል። እዚህ ብንተሳሰብ ኖሮ ክርስቶስን እረኛ እኛን በሬ አናደርግም ነበር። በሬ ሳልሆን የተበደልኩ ሰው ነኝ። ዘማሪዎች ጨረሱና ሁላችንም አብረን በርብቃ መሪነት እንድንዘምር ቀጫጫው ሰውዬ



@BOOKALEM

ጋበዙን። ተጀመረ። ባይሳካም ብዙ ትርምስ ቢፈጠርም ግማሹ ቢስቅም መዝሙሩን እየተንገዳገዱ ጨረሱት። ርብቃ ግን ዐይኖቿን ከእኔ ላይ አላነሳችም ነበር። እንድንዘምር ስትገፋፋን እኔን አተኩራ እያየች ነበር። እኔ ደ'ሞ ዝም። ጠልቻት አልነበረም። ለምን እጠላታለሁ? ለእኔ ምንም ነገር ማድረግ የምትችል አይመስለኝም። ሁሉ ነገር ያምራል። አዎ። ሁሉ ነገር ንፁሕ ነበር። አዎ። መዝሙር ሁሉ አለ። ፒያኖ ሁሉ አለ። እኔ ነኝ። እውስጤ መዝሙሩ አርፎ የሚበቅልበት አፈር አልነበረም። በንፋስ መውጫ ንፋስ.....በክረምት ዶፍ.....በበጋ ሣር.....በስልቹ ቀን ዕንቅፋት ተጠርጉ ሳያልቅ አይቀርም። ከዚያ በማፈር ያለዞብትን እየረሳሁ መሬት መሬት እያየሁ ሳስብ.....ሁሉ ልጆች ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ ውጭ መውጣት ጀመሩ። 'እንውጣ' ሲባል እንኳን አልሰማሁም። ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላውቅም። ከአዳራሹ ሌሎችን ተከትዬ ወጣሁ። ጥቂት ልጆች ወደ ሜዳው እየሮጡ ገቡ። እነዚህንም የቀረው ተከተላቸው። እኔ ከቤተክርስቲያኑ ደረጃ ወረድ ብዬ በስተግራ በኩል ያሉት ሁለት የቮሊቮል ሜዳዎች ላይ በመሰብሰብ ላይ ያሉትን የትምህርት ቤቱን ልጆች አያለሁ። አበበ አለ። እሱ ለቮሊቮል ጨዋታ ሲል ሌት ተቀን ወደ የትም ይጓዛል። በእሱ መሪነት አራት ቡድኖች ተፈጠሩ።

ብዙ ሳይቆይ ከቤተክርስቲያኑ ጀርባ በትልቅ ካርታስ ዘቢደርና አንዲት ፈረንጅ ጨርቆች ይዘው መጡ። ከዚያ ርብቃ ሁላችንም እንድንሰማት አድርጋ አጨበጨበችና እንዲህ አለች፦ "ጅምናስቲክ ወይም ሰርከስ ለመስራት የምትፈልጉ ቱታ እዚህ ስላለላችሁ እየለካችሁ የሚሆናችሁን ውሰዱ። የማስጠንቀቃችሁ ግን ከተጫወታችሁ በሁዋላ በሥነሥርዐት እዚህ ካርቶን ውስጥ እንድትመልሱ ነው።"

ለግማሽ ሰዓት የካርታሱ ሳጥን ዙሪያ የተሟላ ረብሻ ነበር። መጋፋት፣ ጨርቅ መናጠቅ፣ መሰዳደብ፣ ምራቅ ሁሉ መተፋፋት፣ በቅፅል ስም መጠራራት.....ታዲያ የመንግስት ትምህርት ቤት መሰለ። ርብቃና ፈረንጇ ከዳር ሆነው ያያሉ። ከመሐል ርብቃ በዐይኖቿ አንድ ነገር ስትፈልግ አየሁዋት። ሰው ወይም ዕቃ አልገባኝም.....ፈልጋ ፈልጋ ወደ ቤተክርስቲያኑ መውጪያ ዞር ስትል ብቻዬን ቆሜ አየችኝ። ከዚያ በአንድ እጇ ወገቧን ይዛ በትኩረት አጤነችኝ። ወደ እኔ በቀስታ እየተራመደች መጣች። ያን ጊዜ መሮጥ ብችል ደስ ይለኛል። ግን ደክሞኛል። የደከመኝ ይመስለኛል። ለምን ይደክመኛል? በቀስታ እየተራመደች መጥታ፣ እኔም አንገቴን ሰብሬ (መሬት መሬት እያየሁ) ጠበቅሁዋትና። (ቀስ ብላ አመጣጧ የሆነ እመቤትነት ነበረው። በሁዋላ ጥቂት ወራት ካርሞ እሷ ከስር ሆና፣ ሴት አውሉ ሐይለኛው ደሞ ከላይዋ ሆኖ ታላላቅ ጭኖቿን ያየሁ ዕለት ትዝ ያለኝ.....ያ እ! የእመቤትነት አካሄዷ ነበር። ስትጠጋኝ.....በለሆሳስ ግን እንደ መንፈሳዊ ሴራ ሳሙና በውሃ የሚሸት ቀሚሷን ነበር። ደባደቦ ከንፈሮቿ እየተገናኙ ሲላቀቁ የሚያባብል ቀስስተኛነታቸውን



@BOOKALEM

ነበር። በቀሲታ አወራሯን ነበር፣ የአፍ አከፋፈቷን ነበር። አፏ ትንሽ በርገድ ብትል እሷን እንድጠራጠር ከሚያደርጉኝ ከሰፈሩብኝ ጋኔኖች ጥቂቶች ዘለው የሚገቡባት መስሏት ይሆን? እነዚያ የሚቆሙብትን የተጠራጠሩ የመሰሉ እግሮቿ እሷ ከስር ሐይለኛው ከላይ ሆነው እዛና እዛ ያየሁዋቸው ዕለት አ! እግሮቿ እንዴትስ ዘማሪ የሚመራ እጆች መሰሉ? የትስ ይሄን ድንቅ የመሰለ ሐጢያት ተማረችው? ማን ነገራት ሐይለኛው ጀርባ ላይ እግሮቿን መስቀልኛ ማሳመር እንዳለባት? ያኔስ ከአፏ ሲወጣ የሰማሁት ድምፅ ለምን ከመዝሙር ያማረ መሰለ? ስለምንስ ተረጋግታ ተኝታ እንዳመመው ቃሰተች? ስለምንስ ቀድማ ንፁሕ ነጠላዋን ደርቆ ያልደረቀ መስከረም ሳር ላይ አሰጣች? የእኔ ልጅነት ሐይለኛው ጀርባ ላይ ካየሁት የፀጉር ጉተና ይጎድፋል? ፀሎት ያስፈልገኛልስ? የእግዜር ሚስጥሩ ከባድ ነው።)

"ምነው? ስፖርት አትወድም?" አለችኝ።

ራሴን ነቀነቅሁ።

"ለምን አትወድም?" አለችኝ ሳቅ እያለች።

ትከሻዎቼን አነሳሁ።

"ለሰውነት ጥሩ ነው። ያጠነክራል"

ዝም አልኩ።

"ጥሩ ቱታ እመርጥልህና ትጫወታለህ። የማን ልጅ ነህ?"

መናገር አልፈለኩም።

"መናገር ፈራህ?"

መናገር አልፈለኩም።

"ምነው?" አለችና ራሴን ለመንካት እጅዋን ሰደደች።

ጀዳድ እጅ። ነጫጭ የታጠቡ ጥፍሮች ያለው። አንገቴን ሰብሬ ዐይኖቼን ከደንኩ። ከክርስቶስ የበለጠ የምታምር ትመስል ነበር።

አንድ ሁለቴ ዳበሰችኝና፡ "የማን ልጅ ነህ?" አለች

ዝም አልኩ። ለምን ጉትታ አንስታ በክንዶቿ አታቅፈኝም? ለምን ወደ ሚሞቅ ሰውነቷ አስጠግታ መሐል አናቴን አትስመኝም ነበር። ገላዬ ፈለጋት። መንቀጥቀጥም የጀመረ መሰለኝ። ማልቀስ ፈለግሁ። የማን ልጅ እንደሆንኩ ማወቅ ምን ይሰራላታል? ለሁኔታዬ መልስ ማግኘት እንዳቃታት ሁሉ ከውስጥ ተነፈሰችና፡

"እውስጥ ገብተን እንፀልይ የሚያስጨንቅህ ነገር ካለ?" አለችኝ።



@BOOKALEM

ገዛም አልኩ:: በልቤ እንደገና ንኪኝ አልኩ:: እንደገና ዳብሺኝ አልኩ:: አላደረገችውም:: ዳታዬ አሸንፎአት ወደ ሜዳው ተመለሰች:: ብዙ ሳይቆይ መረብ ያልተዘረጋበት የቮሊቮል መጫወቻ ሜዳ ላይ አምስት የሚደርሱ የአልጋ ፍራሾች በቁመት በቁመታቸው ተጠጋግተው ተደረደሩ::

ያኔውኑ አንድ ልጅ......የትምህርት ቤታችን የእግር ኳስ ቡድን ካፒቴን የነበረው: "ሰርከስ እንድትለማመዱ የተመደባችሁ ወደ እዚህ ኑ" ብሎ ተጣራ::

መቸ እንደተመዳደቡ እግዜር ይወቅ:: ሰርከስ ማለት ምን እንደሆነ እሱንም እግዜር ይወቅ:: ብቻ የሚያምር አረንጓዴ ረዥም ሱሪና ካኔትራ ለብሳ እጆቿን አደራርባ ደረቷን የጋረደችውን ወሰንየለሽን ሳይ ጨዋታውን ለመከታተል ተጠጋሁ::

ርብቃና አበበ ጐን ለጐን ቆመው እኔን እያዩ ያወራሉ:: ወሰን ማንንም ለማየት የፈለገች አትመስልም:: ያፈረች ትመስላለች:: ደረቷ ላይ ትንንሽ ጉብ ጉብ ያሉ ነገሮች አያለሁ:: የምታምር ሳዱላ:: ታምራለች ቢባል አይገርምም:: ታዲያ ካፒቴኑ ከልጆቹ መሐል አንዱን መረጠና:

"እንዴት እንደሚሰራ እሱ ያሳዮናል" በማለት ወደ ፍራሹ አቅጣጫ ገፋው::

ልጁ ዕድሜው ከእኔ የሚያንስ የተነቀለው የፊት ጥርሱ ሁለተኛ ያልበቀለ የከተማችን ነርስ ልጅ ነበር:: ሰውነቱን በቀስታ ሲያሟሙቅ ቆየና በተቀጣጠሉት አምስቱም ፍራሾች ላይ ሳያቋርጥ በእጁ ሔደ:: ከዚያ እንደገና በአየር ላይ አምስት ጊዜ ይሆናል እየተገለባበጠ ጨረሰና ተጨበጨበለት:: ወሰን ልጁን የወደደችው መሰለኝ:: ዐይኖቿ ከእሱ አልተነሱም ነበር:: ወደ ርብቃ አየሁ:: ለአበበ በእጇ ወደ እኔ ጠቆመችው:: ያወራት ጀመር:: ለመራቅ አሰብኩ (ስለ እኔ እንደሚያወሩ ገባኝና) ከእነሱ እየሸሸሁ ከሜዳው ወዲያ በኩል ሔድኩ......ወሰን በቆመችበት:: ወሰንን ስጠጋት እንደ ማፈር አለችና ራቅ አለች:: ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ከዱርዬ ጋር ቆምሽ እንዳይሏት ነበር:: ሰርከስ የተባለውን ነገር ማየት ጀመርኩ:: ተምታታብኝ ግን ሰርከስ ነው? ጅምናስቲክ ነው? አክሮባት ነው? ከዐይኖቼ ስር የሚሰራውን ግን ቆሜ አያለሁ:: ከዚያ ስሜ ሲጠራ ሰማሁ:: እንግዳ ነው:: እንግዳ ስሜት ነበረው:: ስሜ እሰው መሐል ክፍት ሜዳ ላይ በከፍታ ሲጠራ:: አበበ ሜዳውን ዞሮ እየሮጠ መጣና አጠገቤ እየሳቀ ቆመ:: አበበ አጠገብ ያን ያህል ቀርቤ አላውቅም:: ሁለመናው ትልቅ ነበር:: የለበሰው የስፖርት ልብስ ቀለሙ ቢያምርም የጎደለው ነገር ያለ ይመስላል::

"መዝገቡ አክሮባት ትለማመዳለህ ወይስ ቮሊቮል" አለኝ::

"ምንም አልፈልግም"

"እህት ርብቃ ደስ ያላለህ ነገር ያለ መሰላት"



@BOOKALEM

"ደስ ባይለኝ እዚህ አልቆምም" አልኩት::

አበበ እንደገና ሊያዋራኝ የስፖርት ሸሚዙን እጀታ ሲጠቀልል......ደርቱ ላይ የእጅ ስፌት እንዳለው አየሁ::

"ስማ አበበ ልብሳችሁ አዲስ ነው?" አልኩት::

"ታዲያስ.....እይማ የቁጥሩ አፃፃፍ አያምርም? ለአንተ ደስ የሚልህን እመርጥልሀለሁ" አለኝ::

ደግ እንደሆን አውቃለሁ:: የመርፌዋን የእጅ ስፌት ነገር አላየም ነበር:: እነ ርብቃ የነገሩትን አምኗል::

መጫወት አለመፈለጌን ሲያውቅ አበበ በሆዱ በኩል ያለውን የሸሚዙን ጨርቅ ወደ ላይ ቀልብሶ የማንባሩን ላብ እየጠረገ ወደ መጣበት ተመለሰ:: አልቦት እንደነበር አላየሁም:: ፀሐዩ ሞቅ ያለ ነበር:: አምስት ሰዓት አካባቢ ሳይሆን አይቀርም:: ምናልባት ስድስት ሰዓት:: ከጀርባዬ በኩል የዛፍ ችግኞች ብቅ ብቅ ያሉበት የመደብ ሰንጣ አለ:: በጎን በኩል ትልቅ ቦይ እየተቆፈረ ነበር:: አጠገብ ካለው ምንጭ ውሐ በቧንቧ ለማስገባት እያሰቡ እንደሆነ ሰምቸአለሁ:: እነዚህ የፈንዱ የሚያማምሩ አበቦች ከሰማይ የወረዱ የሚመስሉ ናቸው:: የሚጣራ የሚሰበስብ ውበት ነገር ነበራቸው:: እንደ ተዘረጉ እጆችም:: ስፖርቱን ትቼ አበባውን ሳይ ትከሻዬን ሰው ነካኝ:: ዞር ስል ርብቃ ናት:: ገሸሽ አልኩ::

"ምነው?......"

ዝም

"አንተ የሙናዬ ልጅ ነህ?" አለችኝ::

ዝም አልኩ::

"እናትህን አውቃታለሁ እኮ" አለችኝ::

ዝም አልኩ:: መሬት መሬት እያየሁ::

"ስትወለድ አላየሁሀም እንጂ:: እንደተረገዝክ ነው ከንፋስ መውጪያ የሄድኩት:: አባትህ አሉ?"

ዝም::

"ልክ እሷን ነው የምትመስለው:: ሆዴ ጠርጥሮ ነበር" አለች::

ዝም::



@BOOKALEM

"እናትህ ጓደኛዬ ነበረች"

ዝም:: ወሬ ይወዳሉ:: ከምታወራ እጇን ዘርግታ እንድትይዘኝ ፈለግሁ:: ገላዬን አላበኝ:: እጆቼ ይንቀጠቀጣሉ:: ምን እንደሆንኩ አላውቅም:: ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም::

"እድሮው ቤት ነው የምትኖሩት?"

ራቅ አልኳት:: እንድትመጣ አልፈልግም:: እናቴ እንጂ አባቴ ጓደኛዋ አይደለም:: ከዚያ በጀርባዋ በኩል በቀስታ እየተራመድኩ እየራቅሁዋት ሔድኩ:: አፏን ይዛ በመገረም ታየኛለች:: ጠልታኝ ይሁን አላውቅም:: ብትወደኝም፣ ብትጠላኝም የምትለውጠው የለም:: ከዚያ ጠራችኝ:: ሰው እንዲሰማ አድርጋ ጠራችኝ:: መሮጥ ጀመርኩ:: ከቤተክርስቲያኑ ግቢ በሰከንድ ወጣሁ:: ወደ ሁዋላም ዞር ብዬም አላየሁ:: እንዲህ እሮጬ አላውቅም:: በጠቅላላ ገላዬ የታመቀ ለቅሶ ፈንድቶ ሊወጣ ይፈልጋል:: ጥርሴን ነከሻለሁ:: የገላዬ ቃጠሎ ለራሴ ይሰማኛል:: ቀለበቱ የወለቀ እጅ ቦንብ እንደዚያ ሳይሆን ይቀራል? (እጅ ቦንብ ሁለት ጊዜ አይቻለሁ:: አንድ ጊዜ የከተማው ፖሊስ ሲያሳየን:: ሁለተኛ ጊዜ ከሁመራ የመጣ እጅ ቦንብ ዝቢያ ውስጥ ማን እንደጣለው ሳይታወቅ ከወደቀበት ተለቅሞ ሰዎች እያገላበጡ እያዩት ሲያወሩ::) ቀለበቱ የወለቀበት ቦንብ ሆኚያለሁ:: ከተማው ዳር ደርሼ ዞር ብዬ አየሁ:: ለስፖርት የመጡት የሚሺኑ ምዕመናን መግቢያው ላይ እንደ አጥር ተገድግደው ቆመው ያዩኝ ነበር::

አበበ በውራጅ ቱታው ወዲያና ወዲህ እያለ እጁን እያውለበለበ ይጠራኛል:: ለምን እሮጥኩና ለምን እመለሳለሁ:: ታዲያ ቆሜ እያየሁዋቸው ባዕድ አገር ያሉ መሰለኝ:: በእኔና በእነሱ መሐል እኔም ልሻገረው የምፈራ፣ እነሱም ሊሻገሩት የማይችሉት ወንዝ አለ:: "እናትህን አውቃታለሁ" ማለቷ ከእኔ መወዳጅዋ ጥበብ መሆኑ ነበር? እናቴን የማያውቅ ከተማ ውስጥ አልነበረም:: ማወቅ ብቻ ሳይሆን አስታመው ቀብረዋታል:: አርባዋን፣ ሰማንያውን ሙት አመቷን በልተው ይሆናል:: እና ርብቃ መጥታ እንደ አዲስ ነገር ታወራኛለች:: የወሰን እናት እናቴን ያውቋት ነበር:: ጓደኛም ነበሩ መሰለኝ::

ንፋስ ቢለዋውጥ የሚተርፈኝ ምቹ ነው::

ምኝ በዛ::

ያን ቀን የቸገረኝ የቀረውን ጊዜ ግማሹን ፀሃያማ ቀን የት እንደማሳልፍ ነበር::



@BOOKALEM

# ትዕዕቆች ዕጆች ሄደው የቀሩት በጉች ናቸው ደባባዕ

እህቴ እንኳን ዘመቻ ሔዳለች:: "ሕዝብ ልታስተምሩ ነው" ተብላ ሔዳለች:: ማንን ማስተማር እንደምትችል አላውቅም:: የምታውቀው ነገር ቢኖር መብላት ነበር:: ወላ እኔ አውቃታለሁ:: ራሷ አይገባትም እንጂ አቁርቋኘ ናት:: ጠዋት ትበላለች፣ ማታ ትበላለች፣ ከሰዓት ትበላለች:: ከፍሷ ስገባ የሚሸተኝ ትኩስና የበረደ ምግብ ነበር......መቸም አንዳንዴ ቁምሳጥኗ ስር የምታስቀምጣቸው መስቲካዎች ለክፍሏ ጥሩ ጠረን ይሰጡላታል እንጂ::

ዕድገት በሕብረት የሔደች ዕለት እናቷ ያኔውኑ አልጋዋን አንስታ ግድግዳ አስደግፋ አቆመችው:: አንሶላዎቿንና ብርድልብስዋን አጥፋ ደበቀቻቸው:: ከማን እንደምትደብቅ ይገባኛል:: ከመሐል ቁምሳጥኗ ስር መስቲካዎቹን ስፈልግ አጣሁዋቸው:: እህቴ ከጭኮዋ ጋር እንደ ስንቅ ወደ ዘመቻ ይዛቸው ሔዳ ይሆናል አልኩ:: እህቴ እንደ ሻሽ የተለቀ እንደ ሱሪ የሳከረ መሐረብ ነበራት.....የደረቁ መስቲካዎቹን እንደ ሰሙኒዎች ቋጥራቸው አብረዋት ዘምተው ይሆናል::

"እህቴ" ብዬ ስናገር ቅር ይለኛል:: "ዘማች" መባሏ ትልቅ ያደረጋት ይመስላታል፣ ዘማችም ስላት ቅር ይለኛል:: ለእኔ ዘማች ማለት ከአንድ ቦታ ሌላ ሩቅ ቦታ ሔዶ ቁም ነገር የሚሰራ በተለይ ጦርነት የሚውል ነበር:: እህቴ ደሞ ሩቅ አልሔደችም:: ቅርብ አውራጃ ውስጥ ነበር:: ለፋሲካ ዶሮ በአገልግል እልክላታለሁ እያለች እንጀራ እናቴ ስታስወራ ነበር:: አንዳንዱ ይሳካለታል እዚያው እግራቸው ስር አጠገባቸው ተቀምጨ ሳፈጥ ግን የሚሰጠኝ የመነቁቁ እንፍሌ::

እና የከተማው ጎረምሶች ሲቀነሱ ጊዜ መሰለኝ ከተማው ውስጥ በግ በዛ:: ፋሲካም ስለቀረበ ይሆናል:: አባቴ ቀንዳም በግ ይወድ ነበር:: ሁልጊዜ የሚገዛቸው በጎች ቀንዳሞች ነበሩ:: ቀንዳሞች ናቸው:: በጣም ልጅ እያለሁ ደሞ የበግ ቀንዱ የሚበላ ይመስለኝ ነበር:: ታዲያ ካልተበላ ለምን የሚበላ ነገር ላይ ተሰክቶ ተፈጠረ? አባቴ ግን ቀንዱን አጥር ላይ ይሰቅለዋል:: በየዓመቱ ታዲያ በግ ባረደ ቁጥር የቀንዱም ዕይነት ይለዋወጣል:: ቤታችን አጥር ላይ ረዥም ቋሚ እንጨት መርጦ የበጉን ቀንድ ይሰቅለዋል:: ለምን እንደሆነ አላውቅም:: ታዲያ ለአስራ አምስት ቀን ያህል የአጥር በር በተከፈተ፣ በተንኳኳና በተከደነ ቁጥር ከቀንዱ ላይ ዝንቦች ሲቀመጡና ሲነሱ ይውላሉ:: እው እው::

የዚህ ፋሲካ በግ እግረ ረዥም ናት:: የሰው ሴት ትመስላለች:: የፋሲካ ዕለት ንፁህ ሥጋ ከማኖቱ በፊት እእ ጨጋራ በጨው አገንፍላ ሰጠችኝ:: ያጠብኩት እኔ ነኝ:: ሳጥበው ደሞ "አበዛኸው እንደ፣ አትሸው......ምኑን በላነው" ስትለኝ ቆየችና፣ ለእኔ አገንፍላ ሰጠችኝ:: እሱን መኝታ ቤቴ ወስጄ ስሶጭ አንድ ሰዓት ቆየሁ:: አያልቅም:: የኛ ከተማ በጎች ፊታቸው



@BOOKALEM

የበግ ሆኖ ጨጓራቸው የበሬ ይሆናል:: ክፍሌ ጠረኑ እንደ ፈርስ ሆነ:: ሙስጠፋ ቤት ሔጄ ስቀመጥ ለአንድ ሻይ የሚሆን ቦታ አልነበረኝም:: ግና ሻይ ፉት ስል አያገሳኝም! ሲያገሳኝ ታዲያ......አፌ ውስጥ በረት ያለ መሰለኝ:: ከመብሸቅ ይልቅ ነገሩ ገርሞኝ የሞቀ ሻይ ፉት እያልኩ ማግሳት ቀጠልኩ.....ከሆዴ ሳያቋርጥ የእበት ጠረን ይወጣል:: እየቆየ ግን በሸቅሁ:: ጉብታዬን ግራሶ አፍስው አበሳጧዋት፣ ይሄም አንሶ ሆዴን በጨጓራ ሞልተው ሞልተው ግሳቴን የከብት ሽታ አጎናፀፉት::

በምንገድ ላይ ስለሸፈተ ሰው ሰዎች ያወራሉ:: ጨጓራ አብልተውት ስለተናደደ ይሆናል የሸፈተው:: እቤት ስገባ ስለሸፍታ ያወራሉ:: አባቴ በሽፍታው የተናደደ ይመስላል:: ሽፍቶች ፀጉራቸው ረዣዥም ነው ይባላል:: ሽፍቶች ብቻቸውን አይሸፍቱም ይሆናል......ሃያ ሆነው ከሸፈቱ ፀጉሩን የሚስተካከል ሃያ ሰው ከከተማዋ ተቀነሰ ማለት ነው:: አባቴ በዚህ ደስ አይሰኝም::

በትንሽ ድስት እእ መኝታ ቤቴ ድረስ ቀን የተረፈኝን ጨጓራ አመጣች:: በሸቅሁ:: በእግሬ ልረግጠው ፈለግሁ:: አሳሞቀችውም እንኳን:: ስቡ እንደ ዳቦ ፍርፋሪ በየጨጓራው እጥፋት ተጣብቆ ያስጠላል:: አጉንበሼ ሳሸተው ከብት ከብት ይላል:: በጣቴ ከድስቱ መዝዤ አወጣሁትና አመዛውዤ ወደ ድስቱ ውስጥ ወረወርኩት:: መረቁና የስቡ ኩረት ዙሪያዬን ተፈነጣጠቀ::

ግድግዳ ላይ አበበ ቢቂላ መሬት መሬት እያየ ይሮጣል:: እእ ስትስቅ እሰማለሁ:: ድስቱን ተሸክሜ ወደ ጓዳ ገባሁ:: የበጉ የሁዋላ እግር ትራሩ ግድግዳ ላይ የአንሶላ ቁራጭ ተከናንቦ በትልቅ የእንጨት ምሥማር ላይ ተሰቅሏል:: ወደ ጓዳው በር ተመልሼ ትላልቆቹ በወሬአቸው እንደተመሰጡ አይቼ ቢላ ፈለግሁና የተሸፈነበትን አንሦላ ገፍፌ የበጉን ሥጋ አየሁ:: ላቱ የለም:: ከአከርካሪው የተገፈፈ ቀይ የሽንጥ ሥጋ ከበጉ ዳሌ ሳይላቀቅ እንደ እባብ ብዙ ያልተበላለት የበጉ ጭን ላይ ተኝቷል:: ከማማሩ ቆረጥኩና ጃኬት ኪሴ ከተትኩ:: ኪሴ ይጠበዋል:: አንሶላውንና ቢላውን እነበረበት መልሼ በጀርባ በር ወጣሁ::

"የት ነው የምትሔደው አንተ?" አባቴ ጮሆ ጠየቀ

"ከተማ!"

"ተመለስ ረብሻ ነው፣ ጦርነት ነው...አንድ ነገር ብትሆንስ?"

ምን እሆናለሁ:: ብሞት ሽንጥ የሰረቀ ቢሞት ማን ይጐዳል:: የባለ አይሰጥ ቅቅላቸውን ከፋንድያ የሚያፀዳ ሰው ያጡ ይሆናል::

ጥሬ ሽንጥ ሲጋዬን እየነጨሁ ከተማ ገባሁ:: የሰው ጀፌ:: ሥጋው በጣም ይለሰልሳል:: ቀዝቃዛ ነበር:: ሥጋ ሥጋ ይሸታል:: ሰዎች በግ ለገና ቢያርዱ ትክክል ነው:: ምንገድ ላይ ከተማ የሚጠብቁ ሁለቱ ፖሊሶች አገኙኝና ያዙኝ:: የት እንደምሔድ ጠየቁኝና አንደኛው

እንደሚያውቀኝ ተናግሮ በኪሴ ምን እንደያዝኩ ጠየቀኝ:: አልፈራሁትም:: እየሳቅሁ ረዥም የሸንኮ ሥጋ ከኪሴ አውጥሁና አንጠልጥዬ አሳየሁት:: ሥጋው ባትሪ ሲበራበት አውሬ ይመስላል:: እባብ ምናምን:: አንደኛው በባትሪ ስጋውን ነካካና ሳቀ::

"እሳት ጠፋ እንዴ?" አለ::

"ጥሬው ጥሩ ነው" አልኩ::

ጉብታዬ ላይ ሁለት ወታደሮች ቆመው ነበር:: የሙስጠፋ ሻይ ቤት ተዘግቷል:: አንድ ቡና ቤት ብቻ ክፍት ነው:: ጥሬ ሥጋዬን እየነጨሁ ቡና ቤቱ በር ላይ ቆምኩ:: ምሽቱ አይበርድም:: እቡና ቤቱ የአጥር በር አንድ ወፍራም አጭር ዘበኛ ቆሟል:: የቡና ቤቱ ዘበኛ የቡና ቤቱ ዘመድ ነው:: ስለቡና ቤቱ ከባለቤቱ የበለጠ ልጨነቅ ይላል::

"ምን ትሰራለህ እዚህ?" አለኝ::

እንዲህ ዐይነት ጥያቄ ምንድን ነው?

"ለመቆም"

"ቆመህ ምን ትሰራለህ?"

"መቆም ለመቆም መቆም"

"እዚህ የሰብድ መቆሚያ አይደለም"

"ሥጋ ትበላለህ.....እንካ" ከኪሴ የቀረውን ቁራጭ ሰነዘርኩለት......

"በል ዞር በል"

"ለምን?"

"የሰው ቡና ቤት ነው.....ከገባህ ግብተህ ጠጣ.....ካልገባህ ዞር በል ከዚህ"

"ይኼ የመንግሥት መሬት እኮ ነው"

"ግንቡን አትደገፍ እሺ"

"ወላ አቦ ምን ይዘነዝዘኛል.....እተውልሃለሁ"

ቡና ቤቱን ትቼ የዘፋን የከሰል ሱቅ በአበረበት በኩል ፀባዬን ወደሚገባው የከተማው ማዕከል ሔድኩ:: ዘበኛው በተከፈተው ሠፊ የአጥር በር ግራና ቀኝ ይመላለሳል:: ጥላ ሞቱ እንደብቸኛ ብርድ መሬት ላይ ይጉተታል:: ሌላ ቦታ ያለሁ መሰለኝ:: ይኼ ከተማ ሌላ ቦታ መሰለኝ::

ግን በጣ ያዛ አልበዛ......



@BOOKALEM

# ዙፋን የት ነው?

ያ ዙፋን አንድ ቀን ማታ "እጅሬ" ብሎኝ እንዳለፈ ወደ ንፋስ መውጫ ተመልሶ አልመጣም። ምክንያቱን የሚያውቅ ሰው አልነበረም። አንዳንዱ የጥርሱ ነገር አማርሮት ፍንጭቱን ሊያስደፍነው አዲስ አበባ ሄደ ይላል። አንዳንዶቹ ጉና ወጥቶ እርሻ ጀምሮአል ይሉታል። አንዳንዶች ከሰል ሲያወጣ ነበር በላው እና ልብሱንና ስቃውን አንዲት ሴት አግኝታ ገበያ መሃል «የማነው?» ስትል ነበር አሉ (ይሄን አላየሁም) ይላሉ። አንዳንዶቹ ልብስ ሊያጥብ ወንዝ ወርዶ እንደ ሽግዬ ድንገተኛ ጎርፍ ወሰደው ይላሉ። በከሰል እያባበሉ ከሚስጢረኛ ወንድ መዳራት ያማራቸው የቤት እመቤቶች ወጣ ገባ አበዙ ስለተባለና በሃሜትም ስለደረሰው ሸሽቶ ሄደ የሚሉ አሉ። በኑሮው ተማርሮ ሰው እንዳያገኘው አድርጎ የሆነ ቦታ የራሱን ነፍስ አጥፍቷል የሚሉም አልጠፉ። ሚስቱ አማላጅ ስለላከችበት ወደመጣበት ወደ ራሱ አገር ወደ ጎለልታ ተመለሰ የሚሉም አሉ። ከብት ገዝቶ ለማርባት ፎገራ የሚባል ለከብት የተመቸ አገር ወርዷል የሚሉም አሉ። ኪራይ መክፈል ስላልቻለ የሦስት ወር ሒሳብ ይዞ ጠፋ በፖሊስ እየተፈለገ ነው የሚሉ አሉ (ፖሊሶች ደሞ "ማነው የሚቀባጥረው?" ይላሉ).....የማይድን ካንሰር ቢጤ ታሞ የጉሮሮ ምንትስ ነው አሉ ሊታከም አንድ አዋቂ ዘንድ ጎጃም ወርዷል የሚሉም አልጠፉም። ወጣቶች ለዘመቻ ሲሄዱ እኔስ ለምን ይቅርብኝ ብሎ ራሱን ሊያዘምት ሄዶአል የሚሉ ቡዋልተኞች ሁሉ ነበሩ። የሆነች እወዲያ ከተማ የምትኖር ቆጣም ሴት ወዶ እሷ ጋ ሄደ የሚሉም ነበሩ።

ዙፋን ግን "እጅሬ" ሲለኝ ድምፁ ውስጥ አዲስ ነገር አልሰማሁም። ያው የለመድኩት የማይታይ ፈገግታ ነበር ከወደታች ወደ እኔ እየዳኸ የመጣው።

ከዕለታት አንድ ቀን ግን እንዲህ የለመድኳትን ዜማ እያፏዋጨ እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ። ያን ቀን እንደለመደው "እጅሬ!!" ብሎኛል። አይቼዋለሁ የተሰወረበትን ቀን፣ ያለ ልማዱ በጀርባው ቀረጢት አዝሎ በዋሽንት ፉጨቱ ሳይታጀብ እንደ ጥላ መሰስ ብሎ ሲሄድ። ሳላውቀው ታዲያ ያለ እኔ ተቀባይነት በጆሮ ልምድ እንጢቆ ለካስ የጆሮዬ አጋሬ ኖሮ የሚያቃጥል ብቸኝነት እየተሰማኝ የጉብታዬ ዐውድ ትደብተኝ ጀመር። ግን የት እሄዳለሁ? ታዲያ ያን ቀን መሰስ ብሎ ከከተማዋ ሲወጣ እንደ ልማዱ አጉተምትሚ ዝም ከማለት የጠረጠረች ደመ-ነፍሴን አምኜ ምነው ድምፄን ዝቅ አድርጌ ዙፋንን «እንደ ምን አመሸህ ዙፋን?» ብለው ኖሮ እላለሁ። እየገላመጡ የሚያዩኝን፣ የሚያሳድዱኝን ሠላምታ ሲሉኝ ገና ለገና ለቤተሰቦቼ ነግረው ("ይሄ ልጅህ ምነው ዱባለ በማን ወጥቶ ነው ሰው የሚገላምጠው?") ያስጠምዱኛል እያልኩ በፍርሃት ድዴን ከምገሽልጥ። ልክ ብዙ አብሬው እንደ ኖርኩት ወዳጄ.....አብሮኝ እንደዘለለ፣ አብሮኝ በግ እንደጠበቀ፣ አብሮኝ እንደ በላ፣



@BOOKALEM

አብሮኝ እንደ ጠጣ፣ አብሮኝ ቁልቋል እንዳደነ፣ አብሮኝ አጋም እንደ ለቀመ፣ አብሮኝ ሾላ እንደ ወጣ፣ መሬት በውሃ አርሶ ዳጥ ላይ አብሮኝ እንደ ተንሸራተተ፣ በመስቀል ደመራ ስር የእሳት ሙቀት እንደተጋራን ሁሉ፣ የቡሄ ጅራፍ ዷዷታ በለጋ ክንዶቻችን እንደሰራን፣ የአመቷ ማርያም ዘኪ ደጀሠላም ውስጥ እንደተሻማን፣ ፓስቴ ቢጋራ ገዝተን ጉብታዬ ላይ አብረን ተቀምጠን እንደበላን፣ በልተን ባልጠፋ ጉምዠታ የጣቶቻችንን ዘይት በየተራ እየተያየን እንደ ጠባን ሁሉ ዘሩን ውል ይለኛል::

ዘሩን እንደ ተረሳ ትንሽ መልዕክት እዚያው ነበር::

ወደ ጎለሊታም አይደል::

ጎጃም አዋቂ ዘንድም አይደል::

ወደ ሸግዬም ቀዝቃዛ ጉድጓድም አይደል::

ወይም ነብር ደም ስር ውስጥ::

ለብ ያለች አድርባይ ትውስታዬ ውስጥ ነበር::



@BOOKALEM

# ባት

ሰው እንደ በግ ጅራት የለውም። ሰው እንደበግ ጅራትና ላት የለውም። ሰው እንደ በግ ስብ የተሞላ ጅራት የለውም። የሚመሳሰል ነገር ግን አለው። ለምሳሌ ሰው አጉንብሶ የሚሔድ ቢሆን እጆቹ እንደበግ የፊት እግር፣ እግሮቹ እንደበግ የኋዋላ እግር ይቆጠሩና ቂጡ ደ'ሞ እንደ በጉ ላት ይሆናል። የበግ ላት የተለያየ ነው። ቀጭን፣ ሰፊ፣ ረዥም፣ አጭር፣ ወፍራም ዐይነቶች አሉ። የሰውም እንደዚያ ነው ሰው እንደበግ በአራት እግሩ ቢሔድ። ከፋሲካው በግ ብልት ላቱ አልቆ ይሆን ጠፍቶ በማግኘቴ ገርሞኝ ነበር። "ምን የሚያኘማ ነገር አለው?" አልኩ። ምናልባት ሥራ ከያዝኩ የምገዛው በግ ባለ ትልቅ ላት ይሆናል እል ነበር ለራሴ። ላት ተወዶ ሳይሆን አይቀርም እህቴ ከዘመቻ ጣቢያ ተባራ ከተማዋ መጣች። ወሬውን ስሰማ በእህቴ ሁለት ወንዶች ተጣልተውባት ኩተማውን ስለበጠበጡ ነው አሉ። በወሰን ሰዎች ቢጣሉ አይገርመኝም።

ያ አራዳው መላጣ ጓደኛዬ ማን እንደነገረው ወይም የት እንዳያት አላውቅም ሲያወራኝ፡ "እህትህ አሪፍ መቀመጫ አላት" አለኝ። መቀመጫ። በሁዋላ ስለበጉ ላት ሳስብ በእህቴ መጣላታቸው አልገረመኝም።

እቤት ውስጥ የእህቴን ጉራ አልቻልኩትም። ልብሶቿን በቧንቧ ውሓ ነጋ ጠባ እየጨፈጨፈች (በሳምንት ውስጥ ጨርቋ በፍቀት አለማለቁ ይገርመኛል) ተቀምጣ የምታወራው ወንዶች እንዴት እንደተጣሉባት፣ እንደተሻሙባት ነበር። ደስ ይላታል። ሰዎች ቢጣሉ ምን ደስ ይላል? እኔ እሷን ብሆን እንዳይጣሉ ለሁለቱም ቂጤን እንዲነካኩ እፈቅድላቸው ነበር። ዝም ብለው እንዲነካኩኝ.....ሌላ ወሬ እያወሩ......በድብቅ እንዲነካኩኝ። እህቴ ያኔ አራት ፈላጊዎች ነበራት ማለት ነው። አበበ [ሥም አጥፊው]፣ ሙስጠፋ [አሊቃሻው]፣ ሁለት የዘመቻ ልጆች [ተደባዳቢዎች]። ታዲያ የበጉ ላት ቶሎ ማለቁ ይሔን ወሬ ከሰማሁ በሁዋላ አልገረመኝም።

ያ አራዳው ጓደኛዬ ግን ከእህቴ ላት ይልቅ ሌላ ነገር ነበር ደስ የሚለው። ምን እንደሆን አላውቅም። ቀጠሮ ሲያፈርስ ቆይቶ "ነገ ወደ ዋና ሐደን የምነግርህ ነገር አለ" አለኝ። ደስ ይላል። ከአራዳ ጋር ቁም ነገር ማውራትና ሚስጢር መካፈል ደስ ይላል። በተለይ ሰው በማያይበት ወደ መንዝ ወርዶ......የዋኙ እየመሰሉ......።

የዚህ መላጣና አራዳ ጓደኛዬ ስሙ "ኤልያስ" ነበር።



@BOOKALEM

# ቢንቢ፣ ሱብስና የሰው ጠባይ

የቧንቧ ውሐ የገባ ጊዜ 'ከተማችን ዘመነች' ተባለ። ወደ ከተማው አደባባይ መግቢያ ወዲያና ወዲህ ሁለት ጉድጓዶች ተቆፍረው አዳሜ በእንስራ የሚያብረቀርቅ ውሐ ጠጣና ከተማችን ቄንጠኛ ሆነች ይባላል። ሴቶች ደግሞ ውሐቸውን ቀድተው ቤታቸው ቶሎ እንደመመለስ ወገባቸውን ይዘው እዚያው ቆመው ወሬያቸውን ሲቀጩ ይውላሉ። እንኳን ባለ ሚስት አልሆንኩ። ምን እንደሚያወሩ ግን አይገባኝም ነበር። እነዚያ የውሐ ጉድጓዶች ዙሪያ ከሰሊታት እንደ ቀን እሳት አንድደው፣ ጀበና ጥደው ቡና ሳይጠጡም አይቀር። መጀመሪያ ሰሞንማ መዳፋቸው መሃል ቀትረው እንደጠላ የሚቀምሱት ነበሩ። ልጃገረዶች ደግሞ የወተት ቆርቆሮና ትናንሽ ባሊዎች ይዘው መጥተው ውሐ ሲራጩ ይውላሉ። በዚህ ላይ ከጉድጓድ ውሐው መቅጃ እስከተወሰነ እርቀት ሁልጊዜ ጭቃ ነበር። ትንሽ ከርሞ ከተማዋ በዚህ ውሃ ከዘነጠች በሁዋላ እእ ባሊ ገዛች። ካልጠፋ ሰቃ.....ባሊ። ሽሯ ገባኝ። ከዚያም እንደፈረደብኝ ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ውሐ መሸከም ጀመርኩ። ለእኔ እንደ ሥራ ሳይሆን እንደቅጣት ስለምቆጥረው በደስታ አድርጌው አላውቅም። ባሊዬን እያንቀጫቀጭሁ እወጣና ውሐው አካባቢ በፀጥታ ተራዬን እጠብቃለሁ። እሪ ይባላል፣ ይርመሀል፣ ውሐ ይረጫል። ጨዋ የምትመስለው ወሰን እንኳን ከዚያ ጉረቤታቸው ተሰማ ንፍጦ ጋር ቀሚሷን ሰብስባ እየተባረረች ውሐ ትራጫለች። ከተሰማ ንፍጦ ምን አሻረካት? አፍንጫው ስር ሁልጊዜ ሁለት ነጫጭ ቋሚ ሰንበሮች አይጠፉም። የአፍንጫውን ቀዳዳ ተከትለው። በስተግራው ቀዳዳ...ሁልጊዜ በስተግራው ቀዳዳ ጫፉ የሚታይ አድፍጦ የሚጠብቅ ነጭ ሚጢጢ እርጥብ ዘንግ ነበር። ለምን በስተግራ? እንጃ ምናልባት ጭንቅላቱ ሲወለድ ወደ ግራ ዘመም ያለ ይሆናል። ልፊያ ይወዳል።

ውሐዬን ቀድቼ እቤት ከተመለስኩ በሁዋላ የሚደገም እንደሆነ ደግሜ ጉብታዬ እመላለሳለሁ። ከዚያ እግሬን ማከክ ነው። ከባሊው የሚፈሰው ውሐ ቆሻሻ ባቶቼና እግሮቼ ላይ ይፈስና ስፍቅ ስፍቅ ስፍቅ። እግዜር ቸርነቱ አይሸሽ..... ሁልጊዜ የእጄ ጣት ጥፍሮች ረዥምም ነበሩ።

ቧንቧ ከተማው መግባቱ አንድ ትልቅ ለውጥ አመጣ። ሕዝቡ ልብሱን ወንዝ ማጠብ አቆመ። ወሬው በየቦታው፣ በየቤቱ በቧንቧ ውሐ ስለታጠበ ልብስ ሆነ።

"ልብሱ ሲሸትስ ሲያምር"

"ሳሙና ሲይዝ ወንዙ እኮ በሳሙና ገሉናል"

"እንቺ ነጠላሽን ሞክርሽው? ጥለቱ የኔ እንዴት ፏ ብሎልሽ ወረቀት መስሎ ወጣ ማሰልሽ" (ወረቀት ንፁሕ ነው ማን አለ?)



@BOOKALEM

"የጋሼን አጥቤለት ጥቁር ኮት ታውቂው እንደሆነ.....ኑግ መስሎ ወጣልሽ"

"የማይረባ ሳሩ አምጥቶልሽ ያ.....ከአሁኑ ተበሳሽ ተቀደደ"

"ይቅደደውና የሚቀድ.....ምነው ነጋዴው ከፋ"

"ገላሽን ታጥበሽ ሞክርሽው?"

"እንዴ! ሂ ሂ ሂ ሂ አልነገርኩሽ.....ማታ ለአቶዬ ሳልነግረው ታጥቤ ተኛሁልሽና ዛሬ ጠረንሽ ሁሉ ይሰባል አለኝ" (ውሃው ማግኔት ሁሉ ሆነ)

"አለሽ? ሃ ሃ ሃ ወይ አንቺ"

ይታያችሁ በምንገድ ሳልፍ የማንም ሰው ጠረን ስቦኝ አያውቅም:: ምንድነኝና ነው እሰው ብብት ስር እያለከለኩ የማነፈንፍ:: ዛፍ? አዎ:: የመንገዱ አቧራ? አዎ:: ሰው? ሽቶኝ አያውቅም:: ምን አልባት ሰው እራሱ እንደ አቧራና እንደዛፍ ይሆናል የሚሸተው:: ወይ አፍንጫዬ ብላሽ ይሆናል:: ከእእ ጋር በበር ተገፋፍተን ስናልፍ፣ አጠገቤ ስትቆም የሚሸተኝ ትልቅ እግር ያበቀለ ማድ ቤት ነበር:: ውሸቴን አይደለም:: ሰቃ ከማድ ቤት ፈልጎ አምጣ ስባል ካላገኘሁት 'ማድ ቤቱ ጠፋህ?' እባላለሁ:: ታዲያ እግር ያለው ማድ ቤት ትዝ ይለኛል:: ዱርዬ፣ ነፃነት የፈለገ ማድቤት እእ ዞር ስትልለት ጫማውን አጥልቆ ጉና ተራራ የሚጠፋ::

ብቻ ሰው ሸቶኝ አያውቅም::

አንድ ቀን ከተሰማ ሞንጉል ቤት ጀርባ የሚኖሩ አንዲት ሴት ባዶ እንስራቸውን ጀርባቸው ላይ አንከብክበው ሲመጡ ቢንቢውን የከበበው ጭቃ ቦታ ሲደርሱ አዳለጣቸውና ከቁማቸው በቂጣቸው ዘጭ አሉ:: የሰውነታቸው ብዙ ክፍል የተነቃነቀ መሰለኝ:: የገረመኝ የደነቀኝ ግን ቆብ እስክትመስል የጠመጠሚት ሻሽ ከእናታቸው ላይ ተስፈንጥራ ስትወድቅ ነበር::

"እይ እቴ!" አሉ::

'እይ እቴው' ለተሰበረው እንሥራ ይሁን ሰውነታቸው ውስጥ ለተሰማቸው አጋጣሚቸው የማያውቅ የብልት ንቅናቄ ወይ ለሻሻቸው አወዳደቅ አልገባኝም:: እኔን ያስገረመኝ ግን እናታቸው ከመሃል በምላጭ እንደ ተላጩት ሁሉ መላጣ መሆኑ ነበር:: የእናታቸው ዙሪያ ፀጉር ነበር:: ጋሜ ይመስላሉ:: መቸም ሴቶች በ40ና በ50 ዓመታቸው ጋሜ የሚሰሩበት አገር አልተወለድኩም::

የወለቀው ሻሽ ሳይተረተር በጭቃው ላይ እንደ ጎማ እየተንኳለለ እግሬ ስር መጥቶ ቆመ:: የሴትዬዋ መላጣ ገርሞኝ ሕሊናዬ ሸሽቶኝ መካከቶች የሸፈንም ጉማ እያየሁት ሳልይዘው



@BOOKALEM

በቀሴታ እየተንገዳገደ ቆየና ቡላማ ቀለም ያለው የጭቃ ውሐ ውስጥ ከንበል አለ:: ብንን አልኩና ቶሎ አነሳሁት::

"እምጣው!.....እምጣው!.....ቶሎ እምጣው!" አሉኝ ሴትዮዋ::

('አይዞት' 'እኔን' 'እኔ ልውደቅ' 'ደህና ነዎት' ) ብዙ ማፅናኛዎች ይሰማል:: እኔን ግን ዘለው በቀጣ 'እምጣው!'::

መላጣቸው ከመላጨት የመጣ አልነበረም:: ሕመም እንደሆነ ሰማሁ:: ላሽ በልቷቸው ነው አሉ:: የዕውነት ግን ሴትዮዋ ሻሻቸውን አድርገው ሲያዩዋቸው ፀጉራቸው ረግፎ የጠፋ አይመስልም:: ምክንያቱም ከሻሹ ስር ዙሪያውን የሚያምር ለሥላሳ ፀጉር እንዳልተበጠረ ሳዙሜ ጉፈሬ በተለያየ አቅጣጫ እየተጠቀለለ ይወጣል:: ሻሹ ሽፋን መሆኑ የገባኝ ያን ዕለት ነበር:: ከዚህ ቀን ጀምሮ ባለ ሻሽ ብቻ ሳይሆን ባለባርኔጣ ሁሉ ተጠራጠርኩ:: የከተማው ፖሊሶች ሁሉ ባለ ላሽ መሰሉኝ::

ይህቺ መነሻ ሆና ደ'ሞ ከራሴ ጀምሮ ለብሶ የሚሔድ ሰው ፈራሁ:: ማመን ከበደኝ:: እህቴን አንድ ቀን ከወገቤ በላይ ልብሴን አውልቄ ጀርባዬ ላይ ላሽ የሚባል ሕመም ወጥቶብኝ እንደሆነ እንድታይልኝ ጠየቅሁዋት::

"አንቺ እማማ.....ላሽ ጀርባ ላይ ይወጣል?"

"እሱ እብዱ ምላሱ ላይም ይወጣበታል" አለች እእ::

እሷን መች አናገርኳትና::

"የእትዬ አዳስን መላጣ አይቶ እኮ ነው"

"ቁም ነገር መሰለህ?" ተባልኩ::

የሴትየዋን ስም አላውቅም ነበር::

ለምሳሌ የእኔን አለባበስ፣ የምቀመጥበትን ቦታ፣ የምውልበትን አካባቢ የሚያይ ሰው በትክክል የተነገረው ሰው፣ ፎቶ አንስቶኝ ፎቶዬ የተሳከለት ሰው ባለጌ፣ ስድ፣ ወመኔ፣ ልክስክስ፣ ቆሻሻ፣ ሜዳ አደር፣ ዋቶ አደረ፣ ዘራፊ፣ ቀማኛ፣ ዱርዬ፣ ምንገድ አዳሪ፣ እጓለማውታ ኢጋሚዶ ልመስለው እችላለሁ:: ከእነዚህ ሁሉ ግን አንዱም አይደለሁም:: የሀዳስን የላሽ መላጣ፣ መላጣውም የተደበቀበትን ዘዴና ሲወድቁ ሴትየዋ ያደረጉትን የመሸፈን ሙከራ ላይ.....ጠቅላላ የዚህ ከተማ ሕዝብ ላሽ እንኳን ባይኖረው ሌላ ሕፍረቱን ለመሸፈን የሚሞክር መሰለኝ:: ለዚህም ትላልቅ ጋቢ፣ ረዣዥም ኩት፣ ትልልቅ ሪዝ (ፊታቸው ላይ፣ አንገቻቸው ላይ ጠባሳ ከአለ) ቦት (ቁርጭምጭምታቸው ላይ ጠባሳ ካለ ወይም ቅልጥማቸው ላይ) ያደርጋሉ:: ታዲያ እንዲህ ሳስብ ሳስብ አንድ ቀን በከተማ እየዞርኩ የተሰጡ ልብሶችን




@BOOKALEM

በማየት በተለይ ሻሾችን በተለይ ካልሲዎችን በተለይ ውስጥ ሱሪዎችን በመተንተን የሰዎችን ፀባይ ለመገመት ወሰንኩ። የአባቴ የሻማ ጨርቅ ኩት ለምሳሌ የትም ብትሰቀል ትታያለች። ዋናው የክፍለሐገሩ ከተማ ከንቲባ ወይም በዥሮንድ ካለ ደግሞ የጤና ጥበቃ ሹሙ በእኛ ቤት አቅጣጫ በአጋጣሚ እያዩ የአባቴ ነጭ የሻማ ካፖርት ያጥበረብራቸውና፡

"ጓድ ጓድ ያ የሚታየኝ መስታወት ካልተነሳ እስከ እኩለ ቀን ሺህ ሰው ዐይኑ መታወሩ ነው። ንፋስ መውጪያ የፊት መስታወት መስቀል ጀመረ እንዴ?" ማለታቸው አይቀርም። የሓዳስን ሻሽ አልረሳውም። ጉጉቴ ከሁሉ ጉጉቴ የወሰንንና የእናቷን ልብስ ማየት ነበር። በተለይ የወሰንን።

ብዙ ጊዜ ልብስ ቅዳሜ ቅዳሜ ነበር የሚታጠበው። ሌላ ጊዜ ሥራ ስለሚበዛ አይደለም። ወግ መሰለኝ። ቅዳሜን የልብስ ማጠቢያ ቀን የሚያደርጉት ለመዘነጥ ይመስለኛል። አንዳንድ ሰዎች አሉ አይደል "አንተ የዓርብ ጋዜጣ አለህ?" የሚሉ። ሁልጊዜ የዓርብ ጋዜጣ የለም ብንላቸው፣ ሁልጊዜም ያው «ያለውን አምጣው» ማለታቸው አይቀርም። ዓርብን የሚጠሩት ለወግ ነው። ታዲያ ጠዋት ላይ ጀምሮ ቅዳሜ በየቤቱ ግቢ ጨርቅ በየዐይነቱ መንጠልጠል ይጀምራል። ሁሉ በየአቅሙ የተቻለውን ያደርጋል። የሙስጠፋ ሻይ ቤት አሳላፊ እንኳን ወጉን ሊያሳይ ሻይ ቤቱ በረንዳ ላይ የጠረጴዛ መጥረጊያ ፎጣ አጥቦ ሰቅሎ ሕዝቡን ሲያስገርመው ነበር። ፎጣው ቆሻሻና የታጠበበት ውሃ ሲንጠባጠብ ቀለሙ አሳፋሪ ግራጫ ነበር። የጉድጊድ ውሐችንን የቅመም ዐይነት ባናውቅ እንኳን ቀለሙ ግራጫ ግን አልነበረም።

ታዲያ ከጠዋት ጀምሬ ከታች የሳልኩትን ዐይነት የሚመስል ጉዳና በከተማው ውስጥ ተጓዝኩ።






@BOOKALEM

የወሰን የለሽ ግቢ ውስጥ:......የሚያምር ነጠላ የልብስ መስቀያቸውን ግማሽ ይዞታል:: ከዚያ በሁዋላ ጠቅላላው ቀሚስ የውስጥ ልብስና የውስጥ ሱሪ ነበር የተደረደረው:: ነጠላው አመልማሎ መስሎ ንፋስ ውስጥ ይንሳፈፋል:: ከሌሎች ከተሰጡት ጨርቆች ስር ውሐ በቀስታ ይንጠባጠባል:: ቀሚሶቹ ሁለት ናቸው:: የእናቷ ናቸው:: ብዙ ጊዜ የሚለብሷቸው መሆኑን አውቃለሁ:: የውስጥ ልብሶቹን ግን አይቼአቸው አላውቅም:: አንዱ ትንሽ ሌላኛው ትልቅ ነበሩ:: ትንሹ የወሰን መሆን አለበት:: የሚገርመው ቀለማቸው የሁለቱም ሮዝ ነው:: እነዚህን የውስጥ ልብሶች ምንገድ ላይ እግር አብቅለው ሲሔዱ ባያቸው ኖሮ ወሰንና እናቷ ናቸው ማለት አልችልም ነበር:: ማንስ ይችላል? ታዲያ ይሔ ገመድ ላይ አንጠልጥሎ ማስጣት ገመና የሚያወጣ መሰለኝ:: ውስጥ ልብሶቹ ንፁህ ነበሩ:: ከእነሱ ቀጥሎ አንድ ትልቅ ግራ የሚያጋባ ሱሪ ዐይነት ነገር......ከእሱ ቀጥሎ ደሞ የጠጣ ግንባር የሚያካክሉ የውስጥ ሱሪዎች::......እነዚያ ትናንሾቹ የውስጥ ሱሪዎች የወሰን እንደሆኑ ገባኝ:: መጠናቸው ከእኔ ቁምጣ ያንሳል:: ቀለማቸው ዝንጉርጉር የግስላ ቆዳ የመሰለ ነበር:: ቆሜ ፈዝዤ እያየሁ ንፋስ ሲያንጬዋልላቸው ከተሰቀሉበት ሽቦ ተንሸራተው ወድቀው የሚበሩ መሰለኝ:: ወይ እንደ አሞራዎች ከሽቦው ላይ እኩብኩበው ተነስተው ወደ ጉና የሚበሩ:: የሚያማምሩ ልጃገረዶች እንዲህ የሚያማምሩ ሱሪዎች ከቀሚሶቻቸው ስር ያጠልቃሉ ማለት ነበር እንዴ?

እዚያ ከተማ ውስጥ ለዙር እንጂ የተሰጡ ልብሶች እስኪበቃኝ ማየት አልቻልኩም:: እነ ወሰን ቤት ያየሁዋቸው ጨርቆች በተለይ ትናንሾቹ ባልገባኝ ምክንያት እጅግ አዘንተኛ አደረጉኝ:: ልብስ.....የውስጥ ልብስን ሁሉ ጨምሮ የሰው ጠባይ እንደሚሸፍኑ ማሰብ ከጀመርኩ በሁዋላ እየዞርኩ ሌሎችን ማየት ትርጉም አጣብኝ:: ስለምን እያለሁ? ስለምን ሰውን በእርጥብ ጨርቁ እገምተዋለሁ? በዐይኖቼ ጥግ በየአጥሩና በየገመዱ ላይ የተለጠፉ፣ የሚንጨዋለሉ ጨርቆች ባይም ችላ አልኳቸው:: እንጢቆ ቤት የገባው አዲስ ሰው ለመሆኑ ማነው? ጭኑ ላይ ከነጣው ቡናማ ካኪ ሱሪው ስለ እሱ የምማረው ምንድን ነው? ካሰጣው ባለስንበር ሸሚዝ ስለ እሱ ጉረኛነት አውቃለሁ?

እኔ የምደብቀው አልነበረኝም:: ምኔ ይደበቃል? ያልፈለጉት ባልፈለጉት አይጋረድም::

ዐይን በማይስብ ጉድ ዐይን የማይስብ ጉድ ይጋረዳል?



@BOOKALEM

# ወረቀቶቹ

መንዝ ስወርድ: ዝናብ ነበር:: ኤልያስ ለመዋኘት ልብሱን ሲያወልቅ ደረስኩ:: አጠገቡ ስደርስ ፊቱን ወደ እኔ አዙሮ ወደ ሁዋላ ባሕር ውስጥ ዘሎ ገባ:: በጣም ይዋኛል:: እንደ እሱ የሚዋኝ አይቼ አላውቅም:: ከተመረው ልብሱ ስር ወረቀቶች ብቅ ብለው አያለሁ:: ክምር ወረቀቶች አያለሁ::

"ግባ" አለኝ ወደ ውሃው::

"መዋኘት አልችልም"

"አለማምድሃለሁ"

ልብሴን አውልቄ ጥልቅ ባልሆነው በኩል ገባሁ:: እግሮቼ የሚያዳልጥ ድንጋይ ላይ ሲቆሙ ተንሸራትቼ ውሐ ውስጥ ወደቅሁ:: በድንጋጤ እየጮህኩ ተነሳሁ:: ብዙ ውሐ ጠጣሁ:: ኤልያስ ይስቅብኝ ነበር:: አበሸቀኝ:: አሪፍ ሆኖ ማብሸቁ ነው እንዴ? እንደጠጋው ይጠራኛል:: እጆቹን ይዘረጋና እየተለማመጠ ይጠራኛል:: እጆቹ ላይ እየፈራሁ ተጋድሜ እስኪደክመኝ እንቦጫርቃለሁ:: ትቶኝ ወደ ውስጥ ይሰምጣል:: የውስጥ እግሮቹን አያቸዋለሁ:: ብዙ የውሐ ኳሶች ከጥልቀት ወደ ላይ ይመጣሉ:: ኤልያስ ወደ ውስጥ ይጠፋል:: መፍራት ስጀምር ከውስጥ ይወጣል.....እንደ ዘንዶ:: እየሳቀ:: እሱ ሲዋኝና እኔ ስንቦጫረቅ ቆየንና የተቃጠርንበት ምክንያት ትዝ ብሎኝ ጠየቅሁት:

"እነግርሀለሁ ያልከኝ ምንድን ነበር?"

እንዳልሰማኝ የወንዙን ዙሪያ አየና ዳገቱን ሁሉ.....ገደሉን ሁሉ.....ገደልና ዳገት ላይ ምን ያፈጣል? ወደ ውሐው ዳር ወጣን:: ዝናቡ ቢቆምም ብርድ ነበር:: እየተንቀጠቀጥን ልብሳችንን ለበስን:: ወረቀቶቹ ላይ ትልቅ የሰሌን ባርኔጣ ጫነባቸውና እየሳቀ አየኝ:: እናቱን በጣቶቹ እየሳባ ፀጉሩን ሲያዳርቅ ቆየ:: እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ምን እንደሆነ አልጠረጠርኩም:: ወረቀቱን በጉያው ይዞ እንድከተለው ነግሮኝ አንድ ትልቅ ዋርካ ስር ተቀመጥን...ወረቀቱን ከማሀላችን አስቀምጦ የሸፈነበትን የሰሌን ባርኔጣ ገለጠና አሳየኝ::

"ደፋር ነህ?" አለኝ::

"ለምን?"

"አራዳ እንደሆንሽ አውቄአለሁ.....ግን ደፋር ነሽ?"



@BOOKALEM

ደፋር ነኝ:: እስከ እኩለ ሌሊት በጨለማ ብቻዬን የምሔድ፣ ሜዳ ላይ ብቻዬን ያደርኩ ነኝ:: ልነግረው ፈለግሁ::

"ለምን?"

"ይኼን ወረቀት ዘመቻ ጣቢያ መርጨት ፈልጌአለሁ"

"አንተ አትረጭም?"

"እንደ'ሱ አይደለም:: ሔደህ ሰው እያየህ አትበትነውም:: የዘመቻ ጣቢያ ሰዎችን አሳይሃለሁ:: ትተዋወቃቸውና አብረሃቸው ሁለት ቀን ሦስት ቀን ትቆያለህ.....ትለማመዳቸዋለህ.....ከዚያ በሁዋላ እኔ የምሰጥህን ወረቀት መኝታቸው ላይ ታስቀምጣለህ ወይም ሌላ የማትጠረጠርበት ቦታ"

"አንተ አታደርገውም?"

"እኔን ይጠረጥሩኛል:: አንተ ከእኔ ስለምታንስ አይጠረጥሩህም"

"እዚያ ሔጄ አላውቅም"

"ዘመቻ ጣቢያ ሔደህ አታውቅም?"

"በፍፁም"

"አትጓጓም?"

"ይደብቱኛል:: የሆነ ዩኒፎርም ለብሰው የሙስጠፉን ቤት ያጣብባሉ:: ጉረኞች ናቸው"

"በደንብ ስለማታውቃቸው ነው:: ስታውቃቸው ትወዳቸዋለህ:: ዘመቻ ጣቢያቸው ከሄን ጀምሮ ሒድ.....ከትምህርት በሁዋላ ማታ ማታ......እና......ሽርክ ትሆናለህ:: እኔ አስተዋውቅሃለሁ ከፈለግህ......እ......"

"እነዚህ ወረቀቶች ናቸው የምበትናቸው?"

"ሌላ ነው......እነዚህ ደሞ ትምህርት ቤት የምትበትናቸው ናቸው......ትምህርት ቤት ማብተን ቀላል ነው አይደለ እንዴ?......ማስጠንቀቂያ ልስጥህ:: ይኼንን አሁን የምናደርገውን ነገር ለማንም አትነግርም"

"ሰዎች ሳያውቁ ሳያዩ መኝታ ቤታቸው የማስቀምጠው ለምንድነው?"

"ይኼ ወረቀት የማን እንደሆነ ታውቃለህ?"

"አላውቅም"



@BOOKALEM

"የኢሕአፓ ነው"

"ስለኢሕአፓ ስምቻለሁ"

"ከስማህ ኢሕአፓ የደርግ ባለጋራ ነው። ደርግ ፋሺስት ኢሕአፓ ህዝባዊና ለሕዝብ የቆመ ነው። ኢሕአፓ የሚታገለው ሕዝባዊ መንግስት ለማቋቋም ነው። ይሔን ወረቀት እዚያ በማስቀመጥህ ሕዝቡን ነው የምታገለግለው" ቀጠለ– "እዚህ ያለው ዘማች እንቅልፋም ቢጤ ነው......እየበላ፣ እየጠጣ ይተኛል። መቀስቀስ ያስፈልጋል።"

ሁሉ ነገር የሚከብድ ሚስጢር ነበር የሆነብኝ። ልጁ ይሄን ሁሉ ሲነግረኝ ደሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእሱ ያልጠበቅሁት ኩስታራነት አየሁበት። ሚስጢሩ ፍርሃት ፍርሃት የመሰለ ነገር በደም ስር ያንቀረቅራል። ቢሆንም ሁለታችን በሚስጢር የምንጋራው ድርጊት በመኖሩ የኩራት ደስታ ተሰምቶኛል።

ወደ ከተማ ስንመለስ ብዙ የምናወራው ጉዳይ አልነበረንም። ቢያንስ እኔ አልነበረኝም። ከመሃል ፀጥታችን እንዳስፈራው ሁሉ ስለታሰሩና መፈታት ስላለባቸው ተራማጅ ስለተባሉ ዘማቾች ያወራል። የሚያገባኝ ጉዳይ አልነበረም። ምንም እንደማያገባኝ ይታወቀኛል። እንደ እህቴ ያሉ ሴቶች ቢታሰሩ ምንም አይጉልም። ከተማው ውስጥ ያሉትም ጉረኞች ነበሩ። ጉራቸው ደ'ሞ በማንም ይታወቃል።

"አንተ ለምን አልዘመትክም?" አልኩት

"አልፈልግም" አለኝ

"ብትታሰርስ?"

"አያስሩኝም። ፖሊሶቹ የአባቴ ዘመዶች ናቸው። መቶ አለቃን ታውቀዋለህ....እሱ ዘመዳችን ነው"

ተጠግቶ ትከሻዬን አቀፈኝ። ከተማው ውስጥ ካሉት ሁለት ፖሊሶች አንዱ ዘመዱ ነበር። አይ መታደል።

ከተማ ከመግባታችን በፊት ከተማውን እንደፈራ ሁሉ በሌላ ምንገድ ሔደ።

"ብዙ ጊዜ አብረን መታየት የለብንም" አለኝ።

ምን ያስደብቀዋል?

ብቻዬን ስንጎራደድ ጃኬቴ ኪስ አንዲት ወረቀት አገኘሁ። በዝናብ ማንበብ አልችልም። ያቀፈኝ መስሎ ኪስያስ እንዳስቀመጣት ተረዳሁ። ቤቴ ሔጄ የማይገባኝን አራት ገፅ ወረቀት በኩራዝ ዕርዳታ አነበብኩ። ኢምፔሪያሊዝም፣ ንቃት፣ አቀባባይ ከበርቴ፣ ሶሻሊዝም፣

ኮሚኒዝም፣ ትግል፣ ምርጥ መኩንኖች፣ ፋሽስት ኸረ ሌላ ብዙ ብዙ። ጠቅላላው ግን ያስፈራል። በጣም እንግዳ ከሆነ ነገር ጋር እንደተነካካሁ ገባኝ። የሆነ ደስ የሚል አንድ ነገር ግን ነበረው እንዲህ ከእንግዳ ነገር ጋር እንደታከከሁ የሚያውቅ ሰው አለመኖሩ። ለዎች አለማወቃቸው.....አባቴ፣ እእ፣ እህቴ፣ ሌላው ሕዝብ አለማወቁ እርካታ ሰጠኝ። አባቴ እንኳን ገርሞት "ምን ትሰራለህ አንተ ጋዝ የምትጨርሰው?" አለኝ.....ክፍሌ የሚመጣ መስሎኝ ወረቀቱን ደበቅሁ። ወረቀቱን የሳር ፍራሼ ስር ደበቅሁት። ለምን ደበቅሁት? የአበበ ቢቂላን ፎቶ ግድግዳ ላይ ሰቅዬ ይሔንን ለምን ደበቅሁት? ከአበበ ቢቂላና ከዚህ ወረቀት የትኛው ይበልጣል?

ፈራሁ። በጣም ፈራሁ። አበበ የሚታዘበኝ መሰለኝ.....አበበን የከዳሁት መሰለኝ።



@BOOKALEM

## ሁሉ ቦታ ፀጉር

አባቴ ከስራ መጥቶ እቤት የሚቀመጥበት የእንጨት ወንበር ስር ብዙ ጊዜ ጠጋ ብሎ ለሚያይ ደቃቅ ፀጉሮች አያጣም። የቤቱ ወለል ደ'ሞ ቢጫ ሳጠራ ስለሆነ ፀጉሮቹ ቦግ ብለው ይታያሉ። ሥራው ቦታ ቢያራግፋቸውም ያመልጡታል......በሸሚዙ እጀታዎች በሱሪው ላይ......ተጣፍረው አብረውት ቤት ይመጣሉ። ቤቱን ደ'ሞ እእ ማፅዳት ስለሚከብዳት እኔን እንድጠርግ ስለምታዘኝ እነዚህን ፀጉሮች አያቸው ነበር።

ፀጉር ማስተካከያ ቤቶች ውስጥ ብቻ ሳይሆን እውጭም የወደቀ ፀጉር አይጠፋም። በወደቀ ፀጉር ኳስ ሰርተው የሚጫወቱ አጋጥመውኛል። አባቴ የቆረጠውን ፀጉር ሰብስቦ ቦይ ውስጥ ይጥለዋል። ከዚያ ይሔ ፀጉር በቦይ ተጠርጎ እስከሚጠፋ.....በንፋስ እየተገፈፈ እስኪያልቅ ድረስ ማንም ሲያልፍ ሲያገድም ያየዋል። አንዳንዶች ሰብስበው ኳስ ይሰሩበታል።

ፀጉር የሌለው ሰው የለም አናቱ ላይ፣ ቅንድቡ፣ ሽፋሽፍቱ ፊቱ ላይ ጠጋ ብለን ካየን ደሞ በቆዳችን ላይ ሰውነታችን በሙሉ ፀጉር ነው። አንድ ዕለት ወንዝ ገላዬን ስታጠብ ደ'ሞ እግሮቼ መሐል ጭጉኝ አገኘሁ። ቅር ይላል። ድሮ ስታጠብ የማልሸፍነው የዚያን ዕለት ግን መሸፈን ፈለግሁ። ምን ያስሸፍነኛል? ምናልባት የምለምደው ስህተት ይሆናል። ስለምደው ረሳዋለሁ። በምንገድ ሳልፍ ሰዎች እግሮቼ መሐል ፀጉር እንደበቀለ የሚያውቁ ይመስለኛል። ኤልያስ ካስተዋወቀኝ ሰዎች ጋር ስሔድ ዘመቻ ጣቢያ ጉብቼ አጠገባቸው ተቀምጬ ሲያወሩ ስሰማ የሚያውቁብኝ ይመስለኛል.....ምናልባት እነዚህ ዘማኞች ሁሉ እግሮቻቸው መሐል ፀጉር አለ። ሴቶችስ? ሴቶች የሚኖራቸው አይመስለኝም። ሴቶች ብዙ ያወራሉ። ብዙ የሚያወራ ሰው የሚኖረው አይመስለኝም ነበር።

እህቴ ደ'ሞ እኛ ከተማ ውስጥ ዘመቻ ጣቢያ ካለ አንድ ረዥም ልጅ ጋር ሸርከ ሆናለች። አንድ ዕለት ቤታችን መጥቶ ሲጠራት ነበር። ዐይን ዐውጣ ናቸው። አስተምሩ ተብለው ሲላኩ ሌላ ነገር ያደርጋሉ። ይኼ ረዥም ልጅ ደ'ሞ እንድፈራውና እሱ የፈለገውን እንዳደርግ ይጥራል። ባርኔጣውን ኪሱ ከቶ እየተዝናና ሲጃራውን እያጤሰ...... "ሰማሽ ጆ እህትሽ አለች?" ይለኛል። (ምንድነው «ጆ» ብሎ ነገር?) እንደ እኔ እግሮቹ መሐል ፀጉር የሌለው ልጅ ይሆናል። እንደኔ እንደኔ ቢሆን ሰው አላስቸግርም። እኔ እሱን ብሆን ኖሮ እሷ እራሷ እኔን እንድትፈልገኝ ነበር የማደርገው። ደንባዛ ያዲስ አበባ ልጅ ነበር።

አንዱ ዘማች በኩዳ የተቀመጠ ጠጅ 'ውሐ ነው' ብሎ ከሰጠኝ በሁዋላ መጠጣት ስጀምር በሳቅ ፈነዳ። ምን ያስቃል? ይግረመው ብዬ ጨለጥኩለት። ስጨልጥለት ግን

አልሳቀም:: ሙኽ:: "ምናባቱን ጨለጠው" አለ:: እራሳቸውን አረፍ ያደርጋሉ:: አቤት እራሳቸውን አረፍ ለማድረግ ሲለፉ:: እግሮቹ መሐል ፀጉር ያለው ሰው ራሱን አረፍ ለማድረግ አይለፋም አልኩ ለራሴ::



@BOOKALEM

# ዳዊትና ጎልያድ

ሙስጠፋ ሻይ ቤት ፊት ለፊት የበረንዳ ምሰሶ ተደግፌ ናና ከረሜላ እየመጠጥኩ ወደ ላይ ወደ እንጢቆ ዙፋን ቤት አቅጣጫ አያለሁ። በቀኝ እግሬ ጫማ ጫፍ አቧራማ የበረንዳው ወለል ላይ ፊደላት እንዳመጣልኝ እስላለሁ። ቀና እያልኩም አያለሁ። ከተማዋ የሚያስደንቅ እንቅልፍ ተኝታለች። ቀስቃሿን ሁሉ የሚያስጠላት። ማንኮራፋት እንኳን የሌለበት ጥልቅ ሕልም-የለሽ ልሙጥ እንቅልፍ። እንደ ሦስት ድርብርብ ጭገራም ካሊም በላይዋ ላይ የወደቀውን የፀሐይ ሙቀት መሸከም የቻለች አትመስልም። ሁሉ ነገር ማቃተቱን የዋጠ ጭር ርጭ ያለ ነበር። የሙስጠፋ ቤት እንኳን ገብተው ያልወጡ ሰዎች ይበዙታል። እግሮቻችንን ዘርግተን ያወራነውን መልሰን እያወራን ጠላታችን እንደሆን ሁሉ ጊዜን እናነደዋለን። የሲጃራ ጢስ ጎለሊታ ላይ የምናየውን የክረምት ጉም መስሎ ዐይኖቻችን እስኪለበለቡ። ከዚያ ዓላማ ያለው የመሰለ ጭርታ ይወርድብናል። እውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር መፋጠጥ ቢሰለችኝ ነበር የወጣሁት። በየንግድ ቤቱ በራፍ ላይ እንጥል የሚያካክሉ ከሻማ ጨርቅ የተሰሩ የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ተንጠልጥለዋል። እነሱም እንደ እኔ በቀኑ ነገር ተዳክመው የተዝለፈለፉ ይመስላሉ። በተሰላቸ ዐይን ወራጅ ወጪ አያለሁ። በስተቀኜ የእህል በረንዳው ፊት ለፊት ከበሩ ጎን ዶሮዎች በቀስታ እየተረማመዱ ለእኔ የማይታየኝ ነገር ከመሬት ላይ ይቶክትካሉ፤ ጥቂቶች ብብታቸውን እየቆፈሩ ቅንቅን ይዘራሉ። ከታች ሆኜ ሳያቸው አንድ ሱቅ ፊት ለፊት ድመቶች ይጣላሉ። እንደ ተቧጨሩ እገምታለሁ። ዙሪያቸውን ትንሽ የአቧራ ጥገድ ይነሳል። ንጭንጫቸው ግን አይሰማኝም። ድምፃቸው በእኔና በእነሱ መሃል የወደቀውን የርቀትና የሐሩር ግድግዳ ሰብሮ መምጣት አልቻለም።

እዚያች መሬት ላይ ፊደል እየጻፍኩ፣ የድመት ቡጭሪያ እያየሁ፣ የዶሮን አትኩሮት እያጤንኩ ስለማይታይ የቅንቅን ጉም እያሰብኩ ከቆምኩ ሁለት ሰዐቶች ያልፈኛል። ስለራሴ የማወጣው የማወርደው ሕልዮ ሁሉ በተሰፋ መቁረጥ የታጠነ ነበር። እያንዳንድዋ ትንሽ ሓሳብ ታደክመኛለች። ግቢ አይታየኝም። ከአፍንጫዬ ወዲያ ምን እንደሚያጋጥመኝ አንካሳ ግምት መስጠት እንኳዋን አልችልም ነበር። መተኛት ያምረኛል። ተነስቼ ግን ቤቴ መግባት ከብዶኛል። ያደግሁብትና ያሳደገኝ ዕርቀት እንደ እንግዳ ዐይኖቼና አእምሮዬ ላይ ይጮሓል። ዕርቦኛል። ተነስቼ ያገኘሁትን የመብላት ፍላጎት ግን የለኝም። ገላዬ ቆሽሾአል። በሃሳቤ ወንዝ ወርጄ ለመታጠብ ሰሜትና አቅሜን ለማስተባበር ሳሴር በስተቀኝ በኩል የምትጮህ ሴት ድምፅ ሰማሁ። መጀመሪያ በድምፅዋ ልለያት ሞከሬ አልቻልኩም። ወደ ከተማው አደባባይ ስትቀርብና የዋናውን ምንገድ ኩርማን ስትጨርስ የፀሐይ እናት መሆናቸውን አወቅሁ። ከጀርባቸው ቁንጮው እንደ እንጨት የተቀሰረ አንገቱ እንደ ምንገድ የተመዘዘ ሕፃን መሬ



@BOOKALEM

ከማስለ የቆዳ እንቀልባ ውስጥ በዘጠ መስሉ ወጥቶአል። ከላይ በስተግራ ያኔውኑ ጫጫታ መሳል የሰዎች የንግግር ትብብል ሰማሁ። ሀይናቼን ዞር ሳደርግ አቶ እንግዳና ረዳት ዐሐፊያቸውን (ይጠንቀቃል የሚባል ደብተራ) እንድ ሰው አቀዋአቸው ያወራሉ። እሳቸው በቀጣ ያወራሉ፡ የሁተማው እንቅልፍ እንደተረበሽ ገብቶኝ ነቃ አልኩ።

የፀሐይ እናት ይጮሃሉ፡......"ማገኝ ነው እኮ። የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ፡ "ሚስ ባጠልቅ መስጮሀለሁ የምለቅ። ጊዜዬ ደርሶአል። አቆርቋዋገር ይወድማል"

አቶ እንግዳ እጃቸውን እንደ መናቅ አወናጨፉ። ደብተራው ከሁዋላቸው ቆሞ ለእኔ የማይታየኝ ምራቅ ይተፋል። ወይስ አልተፋም? ታዲያ አቱን ምን አሞጣሞጠው? ስለምንስ አንገቱን በፍጥነት አስግጎ ሰበሰበ?

"ማን ሙዋርተኛ ይፈራል አሉሆ? እ? እ? የምትጎትተው ያጠናግርሀ። መድሓኒያለም አለን ለእኛ።"

የፀሐይ እናት ይሄን እንዳሉ በአርጅና ፀኒ የመሰለ ጋቢያቸው ከላያቸው ላይ ሾርተት ብሎ ወደ መሬት ወደቀ። ከዚያ በተቀላጠፈ ፍጥነት የሆነ ነገር ከአናታቸው በላይ ማዞር ጀመሩ። ከወዲያ አቶ እንግዳና ፀሐፊያቸው ወዲያ ወዲህ ተብታተኑ። ደብተራው እጁን እናቱ ላይ አድርጎ ጎዝበስ ብሎ ወደ ሰቆቹ በረንዳ ይሸሻል። በረንዳው ላይ የነበሩ ጥቂት ሰዎች ወደ ውስጥ ገቡ። አቶ እንግዳ ትንሽ ሸሸት ብለው አመልካች ጣታቸውን እየነቀነቁ–

"ተይ አንቺ ሴት ሰበብ አትሁኚ። እረፊ። ደሓ ላይ እንድጨክን ኢታድርጊኝ። ተይ በምትወጂያት ማሪያም። ተይ። አታሳድጂኝ። ቤሕግ ነይ። ሌላ ሐጢያት ቢኖረኝ ያሳደግሁዎትን ልጅ አላበላሽም...... "

ከመሃል የፀሓይ እናት ወንጭፍ ሮጡ። ለጥቂት ሰከንድ ዋኖስ የሚያክል ድንጋይ በአየር ላይ ሲበር አየሁ። አቶ እንግዳ ከሚመጣው መዓት ለመከለል በሁለት እጆቻቸው አናታቸውን ጋርደው ወደ መሬት አጎነበሱ። ድንጋይ ጀርባቸው ላይ ነጥሮ ጥላ የመሰለ አስገራሚ ቅንፍ በአየር ላይ ሰራና በሸሸት በረንዳ ላይ ወደ ተሰበሰቡት ሰዎች እየተንከባለለ ሔደ። አቶ እንግዳ ካጎነበሱበት ወደ መሬት አሸበረኩ። አንገታቸው ወደ መሬት በፍጥነት የተቀነጠሰ መሰለ። የጀርባቸውን ድምታ ተከትሉ ከእሳቸው የማይጠበቅ የማቃሰት ድምፅ ካጎነበሱበት መሬት አነፃጂ ወጣ። ከአፋቸውና ከመሬቱ መሃል ትንሽ የአቡዋራ ጉም ተነሳ።

"ቅማሳ ይቺን!! ቅመሳት!! ሰይጣን ሴሰኛ!! እደግምሃለሁ ቆይ!! ሙላጅ ወዝቢዬ!! የቀናው ይደብ!!"



@BOOKALEM

ወንጭፋቸውን ዘርግተው ድንጋይ ይፈልጋሉ። እየመረጡ ይጥላሉ። ከጀርባቸው አንድ ፖሊስ ይሮጣል። ሊደርስባቸው ሲል ዞር አሉ። ሊጥሉት የነበረውን ድንጋይ በእጃቸው ጨብጠው ፖሊሱን ያስፈራራሉ......

አቶ እንግዳ አወደቁበት ሰዎች እየተሯሯጡ መጡ......

ፖሊሱና የፀሐይ እናት ተፋጠዋል......

ሰዎች አቶ እንግዳን ደጋግፈው አነሱዋቸው......

ፖሊሱ የፀሐይን እናት እጅ ጠምዞ ወንጭፉን ይቀማቸዋል......

"ጠብቅ! ጠብቅ! ጠብቅ!"

ፖሊሱ ጅራፉን ነጥቆ በአንድ እጁ ይዞአል......

"ይሄን ዲቃላ እንዳትገድለው፣ አፍረህበት ሊታስገድለው ነው? ይገባኛል። የመድሐኒያለም ፀይን መነጥር ነው፣ እንክዋን አንተን ጥሬ ሠይጣን ያያል። ምን ለየህ እሱስ። ጠብቅ። ጠብቅ። እኔ ልጅት"

ፖሊሱ ይጎትታቸዋል......

ወደ ትርምሱ ተጠጋሁ......

"ይህቺን እርጉም ያዙልኝ" ይላሉ አቶ እንግዳ እያቃሰቱ።

ፖሊሱ ሊስቅ ይሞክራል። እኔ መቅረቤን ሲያይ ካቶ እንግዳ ጋር ዘመድ እንደሆንን ስለሚያውቅ ሊኮሳተርና ሳቁን ሊውጥ ሞከረ። ሰውዬውን እንደማልወዳቸው አያውቅም። ተንበርክከው እያለ እስከዚያን ዕለት ድረስ አይቻው የማላውቅ ደም ስር ግንባራቸው ላይ በቅሉ አየሁ። በርበሬ በመሰሉ ዐይኖቻቸው ቀና ብለው ዐዩኝ። ከዚያ ጨፈኑ። ዐይኖቻቸውን በቀስታ ጨፈኑ። የሚያሳዝን ጥልቅ ዕፍረት ገላቸውን ሲሰበስበው ተሰማኝ። አንገታቸው ትከሻቸው ውስጥ በቀስታ ተቀበረ፡ ቦታ የማይበቃው የመሰለው ገላቸው በእፍኝ የሚማገን መሰለ። ግራና ቀኝ ሁለት ሰዎች ደግፈው ወደ ሱቆቹ በረንዳ ጥላ ወሰዷቸው። ፖሊሱ እንዲታይ አድርጎ ሴትዮዋን ይገፈታትራቸዋል......

"በጥፊ በላት" ይላል አንድ ሰው......

ፖሊሱ ሴትዮዋን እየጎተተ ወደ አስተዳደር ቢሮ ሊወስዳት ወደዚያ አቅጣጫ ይመራቻዋል። ሴትዮዋ እንግዳ በሆነ መልክ ፀጥ ብለዋል።



@BOOKALEM

"የአገር ሽማግሌ እንዲህ ይመቱታል?" አለ አንድ ድምፅ። ቀደም ሲል የሰማሁት። ሰውዬው አይታይም። ወደ በረንዳው አካባቢ እንደሆነ አውቄአለሁ። ለአፍታ ከአንድ ሱቅ መስኮት ጀርባ የቆመ የሰውዬው ጉርድ ጥላ ውልብ ብሎ ጠፋ።

ወደ ጀርባዬ አየሁ። ሻይ ቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎች በሙሉ ወጥተው ቆመዋል። ሙስጠፋ ሲጀራ በአፉ ነክሶ ሊለኩስ ክብሪት ይደበድባል። ሁለት ሰዎች ይስቃሉ። ከዚያ ስርቆት የጥርሳቸው ንጣት እንደ ወረቀት ነበር። ወደ ሻይ ቤቱ ለመመለስ አሰብኩና በጥያቄ እንደሚያጣድፉኝ ገባኝ፤ እንዲህ የማውራትም ሆነ የማዳመጥ ፍላጎት በሌለኝ ወቅት በማንም መነትረክ ስላልፈለግሁ ዋናውን ምንገድ ተከትዬ ግጭቱን ወደ ላይ ትቼ ትንሽ ሄድኩና ወደ ቀኝ ታጠፍኩ። አንድ መስቀልኛ ምንገድ ደረስኩ። ሌላ ቀኝ ከወሰድኩ ወደ አስተዳደር ቢሮ፣ ግራ ያለውን ከወሰድኩ ደሞ ወደ ቤቴ ይመልሰኛል። በቀጥታ ከሄድኩ ወደ ወንዝ ያገባኛል።

ወንዝ ወረድኩ።

ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ እስከ አንገቴ ገብቼ ያየሁትን ሁሉ ለመርሳት ሞከርኩ። ላም እየሁ የምታምር በራብሬ እዚያ ዳገት ላይ......አቶ እንግዳ በሀይናቻቸው በአፍረት ሲያዩኝ ከዚያ ጀርባ ድምፅ ያሌለው ግን ሐይለኛ መልዕክት ነበር። ከዚያ የቀሉ ሀይናች ጀርባ "ምነው ጃንን?" ነበረበት። ሳያቋርጥ እንደ አኮርድዮን ከሚሰበሰብ ገፃቸው እኔ ብቻ የሰማሁት አራራይ ነበር "ምነው ጃንን? ተዋረድኩ እኮ!!" የሚል ግን በፍጥነት ያልገባኝ። "እንዳንተ ሀይነት ዘመድ እያለኝ ተደፈርኩ እኮ ምን ትሰራለህ?" የሚል እሪታ። ትንሽ አፍሬአለሁ። መደባደቢ አለመደባደቤ ሳይሆን፣ ወገን መምረጥ አለመቻሌ። ለሁላችን እንዲቀለን። እዚህና እዚያ ሲሆን ይቀላል። እኛና እነሱ ሲሆን ይቀላል። ከኚህ ከአባቴ ወዳጅ ጋር ግን የሚያግባቡን ስሁተት አልሰራሁም።

(ምን አለበት ታዲያ እንደ ጲላጦስ ብታጠብ እጆቼን ብቻ ሳይሆን–ጠቅላላ ገላዬን.....ከጣሳ በሚንቆረቆር ማይ ሳይሆን ከወንዝ በሚንገዋገዋቅ?)



@BOOKALEM

## ሰንገተ ዘመሲካም

ብዙ ጊዜ እበሽቅ ነበር። እንደዚያ ቀን ግን በሽቄ አላውቅም። ብዙ ጊዜ አልበሸቅም ግን ያን ቀን በሸቅሁ። ሰው በድሕነቱ ሲበሽቅ እኔ በሰው አፍ ክርፋትና ሰፋት ነበር የምበሸቀው። አንዳንዴ ሳስበው ከተማችን ውስጥ የሚኖሩት ሕዝቦች አፎች ብቻ ይመስሉኛል። ታዲያ እነዚህ አፎች ሥራቸው መብላትና ማውራት ብቻ ነበር። በተለይ ማውራት......

እነዚህ አፎች ግን ታዲያ የሚደግፏቸውና የሚለጠፉበት ፊት አልነበራቸውም። የሚሰለቅጡትን እህል የሚዘረገፉበት ሆድ፣ የሚያንሸራሽሩበት አንጀት አልነበራቸውም፣ ይሄ ሁሉ ጉድ የሚቆምበት አፅምና ሥጋ አልነበራቸውም። እንደ አቧራ አየር ላይ የሚንሳፈፉ የጉን ስንጥቅ ያላቸው ትላልቅ በሮች ናቸው። የሚያቀናብራቸውም የተሰየመ ጭንቅላት አልነበራቸውም። ከቦታ ቦታ ለንጨጭና ለምላሳቸውን እንደክንፍ እያርገበገቡ ይበራሉ። ጭር ባለው አየር የእነዚህ የሲጋዎች ጥፊ ጨዋታ ተመስሎ ይሰማል። ቤት የላቸውም። በበረራ ላይ ሲነካኩ ይንካካሉ፣ ጠባቻቸውን ይዋዋላሉ። በዚህ ይጣላሉ፣ ይወዳጃሉ። እነዚህ አፎች እንደ ሰው ስም አልነበራቸውም......እነዚህ አፎች ታዲያ ማረፍ አይችሉም። እንደተጣሉ ነበር። እነዚህ አፎች ሁልጊዜ እንደተጣሉ ነው......

በቀን ሦስት አራት ሰዎች በነገር ሳይለካከፉ አይውሉም......

ታዲያ በዚያን ቀን ከተማው መሐል የሆነ በዓል አክብረው ከሚመለሱ ሰዎች አንድ ሁለቱ ምንገድ ዳር አገኙኝና በጣም ነበር የበሸቁብኝ ማለቴ ብዙ እንደሚያውቁና ለአገራቸው እንደሚያስቡ። እኔ እጆቼን ሱሪ ኪሶቼ ከትቼ የማርፍበት የሌለኝ ቁራ ጭቃ የተሸከመ ሸራ ጫማዬን እየጐተትኩ ምንገድ ዳር ወዲያና ወዲህ እላለሁ። ዝም ብሉ ወዲያና ወዲህ......

"ምን ትሰራለህ?" ተብዬ ብጠየቅ መልስ አይኖረኝም ነበር።

ታዲያ በዚህ ቀን ሰነቱ ሰዎች በአጠገቤ ሲያልፉ አንደኛው ትክ ብሎ አየኝና አስቆመኝ።

"ስማህ ጉብል አባትህን አይተኸዋል?"

ጭንቅላቴን በአሉታ ነቀነቅሁ

"አትናገርም!?"

"መናገር አልችልም.....መፍራም ኢምፔሪያሊዝም ውጩአለሁ" አልኩት።




@BOOKALEM

ሰዎቹ ከት ብለው ሳቁ።

"እንደ አባቱ ቀልደኛ ነው እባክህ" አለው አንደኛው ሌላውን።

ቀልድ በመቀለዴ ራሴን ጠላሁት። ዓላማዬ ሳስቃቸው ሳይሆን ጠልተውኝ ወይም ፈርተውኝ እንዲሔዱ ነበር። እንደ ጎልያድ ግዙፍ ብቻ ሳይሆኑ በጉያዎቻቸው እንደ ዳዊት ወንጭፍ ደብቀው ይሆናል። አቋቋማቸው ያስጠላል። በሰልፍ ነበር የቆሙት። ምን እንዲህ የሚያስደረድር ነገር አለ? ምርጥ መኮንኖች ለመምሰል?




"እናትህስ?" አለኝ መሐከለኛው

"እናት የለኝም" አልኩት

"እሃ እሃ......ባትወልድህም እንኳን ዘነቡ ጥሩ እናት ናት" አለ በስተግራ ያለው ሰውዬ። የት ያውቃል? ምን ያውቃል? እንዴት አወቀው? ምን አልባት እእ በየመንደሩ እየዞረች እኔን እንደምትወደኝ በቅጠል አፏ እየሰበከቻቸው ይሆናል.....ታዲያ ለምን አመናት? ታዲያ ምን ልመልስ። ደ'ሞ እንደ ጮሌ ነበር የሚናገረው አለ አይደል የሚያመልጠኝ ነገር የለም ሁሉን አውቃለሁ ዐይነት።

ስሟን አልወደውም ነበር። ስሟን ጠራብኝ። ምናልባት አባቴን ከማግባቷ በፊት ይኼ ሰውዬ የዘነብች ውሽማ ነበር።

*"ያደለው ያደለው ጠለፈሽ ከፊቴ*
*ስምሽ አልተዳረ እስኪ ነይ በሞቴ"*

እያለ ለብቻው የዘፈነ ይሆናል። ይሰርቃትም ይሆናል። ሚዳው ሠፊ፣ ተራራው ትልቅ፣ የወንዙም መስከ ለስላሳ ነውና ደኑም ጥልቅ ጥላ አለውና ታዲያ የምፈራው ሌላ ወፍራም ልጅ የመስቲካ ቋንጣ የምታስቀምጥ፣ ቂጣም ሴት ከመሐል ገብቶ እንዳያስወልድና በቤተሰብ ውስጥ አራተኛ ዜጋ እንዳያረገኝ......

"የዛሬ ዘመን ልጅ ጥጋቡ.....አናርኪስት ይሆን ይሆናል" አለ አንዱ።

በቀስታ እየራቅሁዋቸው ሔድኩ።

"እትኩሩ አይዟህ እንገተ-መልካም እናት አለህ" አለ አንዱ ራቅ እንዳሉኝ። ተያይዘው ሳቁ። እንግዲህ ብልጥ ሆኑና ነው የሳቁት። እንግዲህ ብልጥ ሆነው ሞተዋል። እፍ። በቃ እፍ።



@BOOKALEM

ቤቴ ስገባ ማታ ለመጀመሪያ ጊዜ የእእን አንገት አየሁት። እየፈራሁ። ከአባቴና ከእሷ ተርፎ ትሪ መሐል ተሰብስቦ ትኩስ ምስር ወጥ በላዩ የፈሰሰበት ፍርፋሪያቸውን አጠግባቸው ተቀምጬ ስበላ እነሱም ሻይ እየጠጡ ሲያወሩ አንገቷን ለመጀመሪያ ጊዜ አየሁት።

ቆንጆ አንገት ምን እንደሚመስል አላውቅም። ምን መምሰል እንዳለበት አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር ግን ያቺ ሴት ክፉ መሆኗን ነበር። ይህቺ ሴት የምታዳላ መሆኗን ነበር። ያቺ ሴት ሰውን በረሐብ የምትቀጣ መሆንዋን ነበር። ያቺ ሴት ሩህሩህ አለመሆኗን ነበር።

አንገቷ ዙሪያ ሁለት-አንድ ትልቅ፣ አንድ ትንሽ የወርቅ ሐብሎች አሉ። እነዚህ ከሚዳ የተለቀሙ ጌጦች አልነበሩም። አባቴ ሲያመጣት ወርቅ እንዳልነበራት አውቃለሁ። እነዚህ የወርቅ ሐብሎች የእኔ ልጅነቶች ነበሩ። የእኔ ደስታዎች ነበሩ። የእኔ የዋሕነት ነበር። የእኔ ድፍረት ነበር። በዙርኩም በግርፊያ ነበር ከእኔ የወሰደቻቸው። ቁርሴን፣ ምሳዬን፣ ራቴን መንዝራ ነበር።

በዚህች በአንዷ በአባቴ ጎጆ ስር የተቀማማን ነን። አንገቷ የቀማኝ ነኝ። አንገቷ ሌባ ነበር። ግን እነዚያ ሰዎች አፍ ብቻ አይደሉ!......

"አንገተ መልካም እናት አለህ" አሉኝ። አፍ ብቻ ናቸው። አፎች ብቻ ነበሩ።

ያን አንገት ያቀፉ፣

በዚያ አንገት የተጫወቱ፣

ያ አንገት ያጫወታቸው፣

ያ አንገት የዘመረላቸው፣

እዚያ አንገት ላይ የተነፈሱ፣

ያ አንገት የተነፈሰባቸው፣

እነሱ ያን አንገት ያደንቁ።

ለእኔ ያ አንገት የቀጣ ድምፅ ፋብሪካ ነበር። ለእኔ የምቀኝነት ፋብሪካ ነበር። ከሥጋ፣ ከደም፣ ከሁሉ ከአጥንት የተሰራ የአፍ አሽከር ነበር።

አንገቷ የባለጌ አፍዋ አሽከር ነበር።

የፈለገው ዐይነት አንገት ላይ ይሰቀል ሁሉ ዐይነት ሰው አፍ ይፈልጋል፡—የሚማርከ፣ የሚስብ፣ የሚያስደንቅ፣ የሚያስወድድ፣ የሚያስከብር፣ የሚያስመሰግን፣ ጉብዝ



@BOOKALEM

የሚያስኝ.....በሰዎች መሐል የነበረው ልዩነት በእነዚህ ዐይኖቼ እንዳየሁት ከሆነ የአፍ ስፋትና ጥበት ብቻ ይመስለኛል......እኔ የምፈልገው እግሮች ነበር ሁለት እግሮች ሳይሆን ሦስት እግሮች፣ ሦስት እግሮች ሳይሆን አራት እግሮች፣ አራት እግሮች ሳይሆን ብዙ በጣም ብዙ እነዚያ አፎች በልተው ከሚጨርሱኝ በፊት ሮጬ የማመልጥበት።

የቴሌግራም ቻናላችንን በመቀላቀል ሌሎች አማርኛ ና እንግሊዝኛ ልብወለድ ትረካዎች ያግኙ ይሄን ይጫኑ ወይም @amharicbooks24



@BOOKALEM

# ስለባ

ማታ ጉብታዬ ላይ አምሽቼ እቤት ልገባ ስል ወደ ቤቴ የሚወስደው መታጠፊያ ምንገድ ላይ የቀጨሞ ጥላ ስር ሁለት ሰዎች ተቃቅፈው ቆመው ደረስኩ:: እህቴና ዘሪሁን ናቸው:: ደሞ ፊቶቻቸው ተጣብቀዋል:: የእህቴ እጆች አንገቱ የሚባል የዘመቻ ጣቢያ ወዳጇ ዙሪያ ተጠምጥመዋል:: የሚያናድድ ነገር ነበረው:: ሰዎች እንዴት አፋቸውን ያገጣጥሙታል? በልቡ «አንገቷ ፊቱን አንገቷ ውስጥ ቀብሮ ይስማታል፣ እንደ ሚጥላት ሁሉ ይታገላታል:: ከዚያ እንደዚህ ካደረጉ በሁዋላ ምን ያምራል» ይል ይሆናል፤ እናቷን እንደሚያሟት:: ቁምሳጥኗ ስር የደበቀችውን የመስቲካ ይላታል......"እወድሻለሁ".....ምኗን ነው የሚወዳት? ቋንጣ ቢያይ አይወዳትም ነበር:: ምናልባት በዚያች ደቂቃ እየሳማት የምታላምጠው መስቲካ አንድ ዓመት የቆየ ነው:: ከዚያ ይሔን ካላት በሁዋላ እየገፋ..... በገላው እየገፋ ይጢጋታል:: እሷ ደ'ሞ የሆነ የሚያናድድ ድምፅ እያሰማች አሂ ሁዛ አኢ ብቻ እንደዚያ ዐይነት ድምፅ.....ደሜን አፈሉት:: ልተፋ ፈለግሁ:: ግን ይሔ ሚስጥራቸው መሰለኝ:: ማገም የማያየውን በማየት ላይ እንደሆንኩ ገብቶኛል:: ከዚያ እንደገና ፊታቸውን አገናኝተው ደስ የማይል ድምፅ አወጡ:: ምጥዋ! እንቧ ጧ ብርጭቅ ሙስጠፋ እንዲህ ዐይነት ነገር ማድረግ ቢቀርበት አይጉዳም:: እጅ ለእጅ ተያይዘው አይሔዱም?......ወይም ዝም ብለው ተቃቅፈው አይሔዱም?.....ዞር አሉ ወደ እኔ:: ቁጥቋጦ ውስጥ ተደበቅሁ:: ቁጥቋጠው ይሸታል:: ውሻ ሳያራ አልቀረም እዚያ ውስጥ:: ጡቶቿን ይዞ ያሻቸዋል:: እሷ ደሞ ዝም ትላለች:: ከዚያ ከእጆቹ መሐል ወጥታ እየሮጠች ሔደች "ነገ እንገናኝ ደህና እደር" አለችው:: ተበሳጭቶ ጭኖቹን በጥፊ መታ:: በቃ አበደ:: ወደ ጣቢያው ሔዶ አይዘምትም? እንዲያ ሊያደርግ ነበር ጥራልኝ የማለኝ?

ጠዋት ላይ ለኤልያስ ማታ ያጋጠመኝን ልነግረው ፈለኩና የማላውቀው፣ ያልገባኝ ምክንያት አስቆመኝ:: ስለ እነሱ ምን አስወራኝ? ማየት አልነበረብኝም:: ማየት ብቻ ሳይሆን ካየሁ በሁዋላ ለመናገር ማሰብ አልነበረብኝም:: የሰው ሚስጢር ማውጣት መሰለኝ......መሰለል መሰለኝ:: ማውራቴን ተውኩ:: ኤልያስ ደ'ሞ ሌላ አያወራም:: ኤልያስ ከፖለቲካ ውጪ አያወራም:: አሰልችቶ ሊገለኝ ነበር:: እንዳነብ የማያመጣው ወረቀት አልነበረም:: ብዙውን አላነበውም:: ኪሴ ከትቼ ቤቴ አድርሼ እመልሰዋለሁ:: ማንበብ ሳይሆን የምወደው ማየት ነበር:: ይሄ አልገባውም::

ማታ ዘሪሁንን አገኘሁትና ጣቱን እያወዛወዘ ጠራኝ::

"አንተ ትላንት ማታ እየሁሁ--ትሰልላለህ?" አለኝ::



@BOOKALEM

ምን እንዳለ ስለገባኝ አፈርኩ። እንደ ሽርክ ሊያደርገኝ አቀፈኝና ትከሻዬን መታ መታ አደረገኝ። የሚያናድደኝ ነገር ደሞ ትከሻዬን አቅፈው ሲነካኩኝ ነው መታ መታ ሲያደርጉኝ ነው። እሁቴ ላይ የምናገርባት መስሎት ይሆናል። የፈራኝ መሰለኝ። እንዲፈራኝ አልፈለኩም። ትከሻዬንም እንዲመታኝ አልፈለኩም።

ዘመቻ ካምፕ ወስዶ የምሥር ውጥ ጋበዘኝ። ዘማቾች የጠቀሙኝ ነገር ቢኖር ምግባቸውን ያለስስት ያበሉኛል። በፈለኩ ሰዓት ሔጄ የሚበላ ነገር አላጣም ነበር። የአለባበሴ ድህነት ለቅልውጥና እንደመጣሁ እየተናገረብኝ ይሆናል። ወረቀት ለማስቀመጥ እንደምሔድ ግን አያውቁም።

ወረቀት ማስቀመጥ ቀላል ነበር። ሲያዩኝ ችጋራም ነበር የምመስለው። ለመቀላወጥ እንደመጣ ሆኜ እገባለሁ። ለሥራ የሔደ ዘማች ሥም እጠራና እንደሚጠብቅ እቀመጣለሁ። ዘማቾች ቂጣቸው አያርፍም እየተነሱ ሲወጡ ሦስት አራት ወረቀቶች ትራሶቻቸው ስር አስቀምጬ እወጣለሁ። የምሣ ጊዜ ከደረሰ ምንም እንዳላደረገ ሰው አብሬአቸው እበላለሁ።

በጣም የማዝነው ያኔ ነበር። በፍፁም ብልጥ የሆንኩ አይመስለኝም። እምነታቸውን የካድኩ ይመስለኛል። እንዲህ ዐይነት አራዳ መሆን አልፈልግም ነበር። ሰላይ መሆን አልፈልግም ነበር። ኤልያስ ግን ሞራል ይሰጠኝ ነበር።

"አይ አንቺ!" ይለኛል።



@BOOKALEM

# ስምንተኛው ሺህ

በሚሽኑና በከተማው መሐል ሰፊ ሜዳ ነበረ። ለነገሩማ የንፋስ መውጪያ ኩተማ መጀመሪያ በሜዳ ቀጥሎ በተራራ የተከበበች ናት፣ መጀመሪያ የሜዳ ቀጥሎ የተራራ ቀለበት። ይኼኛው ሜዳ ግን በሚሽኑና በከተማው መሐል ያለው ልክ እንደመዳመጫ ለስላሳ ነበር። ለበጋ ለበጋ ጣሩ ወርቅ ይመስላል። ክረምት ክረምት ቀላል ጨፌ ይሆናል። መስከረም ብቅ ሲል ጀምሮ ደሞ አደይ አበባ ይነጠፍበታል። "ወንድ አይወለድብሽ ሜዳ" ወይም በአጭሩ "ወንድ ሜዳ" ይሉታል። ከሜዳው በስተግራ ከከተማው ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ አንድ ብቻውን የተጎለተ ትልቅ፣ ድቡልቡል ጥቁር ድንጋይ ነበር። የሚያምር፣ የሚገርም ቅርፅና ውበት አለው። የዚህ ድንጋይ ስም 'ወንድ አይወለድብሽ' ይባላል በሁዋላ በሁዋላ የበላይ ድንጋይ (16) ተባለ። ታዲያ ሜዳው የድንጋዩን ሥም ተውሶ ወንድ አይወለድብሽ ሜዳ ተባለ አሉ። ሲወራ ነው። የወሬ የወሬ ነገርማ ከሆነ የማይወራ ነገር አልነበረም። እልም ያለ አውላላ ሜዳ ላይ እንዲህ ክብ የሆነ፣ እንዲህ የጠቆረ ድንጋይ መኖሩ የማያስገርመው የለም። አንዳንድ ሰዎች የግራኝ ድንጋይ ነው ይላሉ። እንደሚሉት ንፋስ መውጪያ ድሮ ድሮ በማርያም ስም የሚጠራ ታላቅ መቅደስ ነበራት። እጉና ተራራ ላይ ውጊያ ሆኖ ግራኝ ታች ወርዶ በመዝለቅ የፈለገውን ጥፋት መስራት አለመቻሉ አብሽቆት ያን መቅደስ ለመምታት ድንጋይ አንስቶ ወረወረ ይባላል። መቅደሱን ሳተውና ድንጋዩ እሜዳው ቀረ ይላሉ። ይኼ ግን ውሸት ይመስለኛል። ግራኝ ድንጋዩን ከተማ ሊመታ ከሚወረውረው የሚወጉት ወታደሮች ላይ አይወረውረውም ነበር? ወታደሮቹን ካሸነፈ በሁዋላ ታዲያ ከጉና በግማሽ ቀን ገብቶ ንፋስ መውጪያን እንደፈለገ ሊያደርጋት ይችል አልነበር። ደሞ ለምን ግራኝ ድንጋይ ይወረውራል? ስራ አጣ እንዴ?

እንደሚሉትማ ወንድ አይወለድብሽ ድንጋይ ስምንተኛው ሺህ ሲመጣ ይሰነጠቃል አሉ። ይሰነጠቃል እየተባለ ይጠበቃል። ለማርያም ለማርያም ዓመት ሲነጋ ሲነጋ አካባቢ ጥቂት ሽማግሌዎች ተነስተው ወደ ድንጋዩ ይሔዱና ስንጥቅ ይፈልጋሉ አሉ። ለእኔ ስምንተኛው ሺህ መጣ አልመጣ ግድ አልነበረኝም። የሚጎልብኝ ነገር የለም። ከተማው መሐል ትልቅ ሱቅ ያላቸው አቶ ስለሺ የሚባሉ ሰው ነበሩ። ጠቅላላ መላጣ የሆኑ። የሱሪዎቻቸው ኪሶች አፍ በዘይትና በጉድፍ የሚያብረቀርቅ። ንፋስ መውጫ በውሃ የማይታጠብ ጥቁር የሱፍ ኩት የሚለብሱ። ስለ ስምንተኛው ሺህ ስሰማ የእሳቸው ዘመድ ይመስለኝ ነበር። ወይም የሚተዋወቁ። ስምንተኛው ሺህ ወፍራም ቅልጥም ያለው ረዥም ሰው ይመስለኝ ነበር። እና እሩቅ ሳይሆን ያለው እዚያው ጉና ተራራ ጀርባ ቂጣ እየጋገረ እየበላ ተደብቆ እስኪጠሩት የሚጠብቅ። እየቆየ ስምንተኛው ሺህ የሚጠራበት ሰፊ ስም 'የ ቀን' የተባለውን ስሰማ ስለ ጊዜ የሚነገር መሆኑ ገባኝ ሰለት መሆኑን ተረዳሁ። ታዲያ በዚያ



@BOOKALEM

ምን እንዳለ ስለገባኝ አፈርኩ። እንደ ሽርክ ሊያደርገኝ አቀፈኝና ትከሻዬን መታ መታ አደረገኝ። የሚያናድደኝ ነገር ደ'ሞ ትከሻዬን አቅፈው ሲነካኩኝ ነው መታ መታ ሲያደርጉኝ ነው። እሁቴ ላይ የምናገርባት መስሎት ይሆናል። የፈራኝ መሰለኝ። እንዲፈራኝ አልፈለኩም። ትከሻዬንም እንዲመታኝ አልፈለኩም።

ዘመቻ ካምፕ ወስዶ የምሥር ወጥ ጋበዘኝ። ዘማቾች የጠቀሙኝ ነገር ቢኖር ምግባቸውን ያለስስት ያበሉኛል። በፈለኩ ሰዓት ሒጄ የሚበላ ነገር አላጣም ነበር። የአለባበሴ ደህንት ለቅልውጥና እንደመጣሁ እየተናገረብኝ ይሆናል። ወረቀት ለማስቀመጥ እንደምሔድ ግን አያውቁም።

ወረቀት ማስቀመጥ ቀላል ነበር። ሲያዩኝ ችጋራም ነበር የምመስለው። ለመቀላወጥ እንደመጣ ሆኜ እገባለሁ። ለሥራ የሔደ ዘማች ሥም እጠራና እንደሚጠብቅ እቀመጣለሁ። ዘማቾች ቂጣቸው አያርፍም እየተነሱ ሲወጡ ሦስት አራት ወረቀቶች ትራሶቻቸው ስር አስቀምጬ እወጣለሁ። የምሣ ጊዜ ከደረሰ ምንም እንዳላደረገ ሰው አብሬአቸው እበላለሁ።

በጣም የማዝነው ያኔ ነበር። በፍፁም ብልጥ የሆንኩ አይመስለኝም። እምነታቸውን የካድኩ ይመስለኛል። እንዲህ ዐይነት አራዳ መሆን አልፈልግም ነበር። ሰላይ መሆን አልፈልግም ነበር። ኤልያስ ግን ሞራል ይሰጠኝ ነበር።

"አይ አንቺ!" ይለኛል።



@BOOKALEM

# ስምንተኛው ሺህ

በሚሽኑና በከተማው መሐል ሰፊ ሜዳ ነበረ። ለነገሩማ የንፋስ መውጫያ ከተማ መጀመሪያ በሜዳ ቀጥሎ በተራራ የተከበበች ናት፡ መጀመሪያ የሜዳ ቀጥሎ የተራራ ቀለበት። ይኼኛው ሜዳ ግን በሚሽኑና በከተማው መሐል ያለው ልክ እንደመዶመጫ ለሰላሳ ነበር። ለበጋ ለበጋ ሜሩ ወርቅ ይመስላል። ክረምት ክረምት ቀላል ጨፌ ይሆናል። "ወንድ አይወለድብሽ ሜዳ መስከረም ብቅ ሲል ጀምሮ ደግሞ አደይ አበባ ይነጠፍበታል። "ወንድ አይወለድብሽ ሜዳ ወይም በአጭሩ "ወንድ ሜዳ" ይሉታል። ከሜዳው በስተግራ ከከተማው ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ አንድ ብቻውን የተገለለ ትልቅ፣ ድቡልቡል ጥቁር ድንጋይ ነበር። የሚያምር፣ የሚገርም ቅርፅና ውበት አለው። የዚህ ድንጋይ ስም 'ወንድ አይወለድብሽ ይባላል በዙዋላ በዙዋላ የበላይ ድንጋይ (16) ተባለ። ታዲያ ሜዳው የድንጋዩን ሥም ተውሶ ወንድ አይወለድብሽ ሜዳ ተባለ አሉ። ሲወራ ነው። የወሬ የወሬ ነገርማ ከሆን የማይወራ ነገር አልነበረም። እልም ያለ አውላላ ሜዳ ላይ እንዲህ ክብ የሆነ፣ እንዲህ የጠቆረ ድንጋይ መኖሩ የማያስገርመው የለም። አንዳንድ ሰዎች የግራኝ ድንጋይ ነው ይላሉ። እንደሚሉት ንፋስ መውጫያ ድሮ ድሮ በማርያም ስም የሚጠራ ታላቅ መቅደስ ነበራት። እጉና ተራራ ላይ ውጊያ ሆኖ ግራኝ ታች ወርዶ በመዝለቅ የፈለገውን ጥፋት መስራት አለመቻሉ አብሽቆት ያን መቅደስ ለመምታት ድንጋይ አንስቶ ወረወረ ይባላል። መቅደሱን ሳተውና ድንጋዩ እሜዳው ቀረ ይላሉ። ይኼ ግን ውሸት ይመስለኛል። ግራኝ ድንጋዩን ከተማ ሊመታ ከሚወረውረው የሚወጉት ወታደሮች ላይ አይወረውረውም ነበር? ወታደሮቹን ካሸነፈ በዙዋላ ታዲያ ከጉና በግማሽ ቀን ገብቶ ንፋስ መውጫያን እንደፈለገ ሊያደርጋት ይችል አልነበር። ደግሞ ለምን ግራኝ ድንጋይ ይወረውራል? ስራ አጣ እንዴ?

እንደሚሉትማ ወንድ አይወለድብሽ ድንጋይ ስምንተኛው ሺህ ሲመጣ ይሰነጠቃል አሉ። ይሰነጠቃል እየተባለ ይጠበቃል። ለማርያም ለማርያም ዓመት ሊነጋ ሊነጋ አካባቢ ጥቂት ሽማግሌዎች ተነስተው ወደ ድንጋዩ ይሔዱና ስንጥቅ ይፈልጋሉ አሉ። ለእኔ ስምንተኛው ሺህ መጣ አልመጣ ግድ አልነበረኝም። የሚገልብኝ ነገር የለም። ከተማው መሐል ትልቅ ሱቅ ያላቸው አቶ ስለሺ የሚባሉ ሰው ነበሩ። ጠቅላላ መላጣ የሆኑ። የሱሪዎቻቸው ኪሶች አፍ በዘይትና በጉድፍ የሚያብረቀርቅ። ንፋስ መውጫ በውሃ የማይታጠብ ጥቁር የሱፍ ኮት የሚለብሱ። ስለ ስምንተኛው ሺህ ስሰማ የእሳቸው ዘመድ ይመስለኝ ነበር። ወይም የሚተዋወቁ። ስምንተኛው ሺህ ወፍራም ቅልጥም ያለው ረዥም ሰው ይመስለኝ ነበር። እና እሩቅ ሳይሆን ያለው እዚያው ጉና ተራራ ጀርባ ቂጣ እየጋገረ እየበላ ተደብቆ እስኪጠሩት የሚጠብቅ። እየቆየ ስምንተኛው ሺህ የሚጠራበት ሰፊ ስም 'ያ ቀን' የተባለውን ስሰማ ስለ ጊዜ የሚነገር መሆኑ ገባኝ ስለት መሆኑን ተረዳሁ። ታዲያ በዚያ

ቀን የሚመጣው ቅልጥማም ሰው ሳይሆን ክርስቶስ ነው አሉ። በግርማ ሞገስ። ክርስቶስን በግርማ ሞገስ ወደ ምድር ሲወርድ ማሺኖች ስዕል ላይ አይቼዋለሁ። የሆነ ፈረንጅ ነገር ከሰማይ ይሁን አላውቅም ያው ከሰማይ ነው የሚሆነው በዳመና ተከቦ ትናንሽ ጡሩንባ የያዙ ኪሩቤሎች ጭንቅላቱ ላይ እየነፉበት፣ ብርሐን እያፈናጠቀ፣ ባዶ እግሩን፣ እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ። ታዲያ የሚያስፈራ ቀን አይመስልም። ቢከፋ ቢከፋ የጡሩንባ ሙዚቃ እንሰማለን።

በዚህ ሰሞን ደ'ሞ መንግስት መለወጡ ያስከፋቸው ብዙ ሰዎች በረሐ ሸፍተዋል ተብሎ አድናቆት በአድናቆት ሆነዋል። ጠመንጃ ይዘው ጫካ ይገቡና ይደነቃሉ። ታች ማዶ ሸፈተ የተባለው ሰው የመጨረሻ ጉረኛ ደጃዝማች ነበር። ከተማ ከከተማ እየዞረ ጮማውን ሲቆርጥ ኖሮ ኖሮ ዞር ብሎ ሳያየን እግዜር ዘራፌ ቢልክበት በወንድነት ሊመጣብን። ግን ሽፍታ አድንቄ አላውቅም። ሞኙንም ይፈልግ።

*(ጥንት ነበር እንጂ አስቦ ማካፈል*
*አሁን ምን ያደርጋል ዲሞትፈር ማግተልተል*
*ጥንት ነበር እንጂ አስቦ ሰው መውደድ*
*አሁን ምን ያደርጋል ሽፍቱልኝ ማለት*
*......**የንፋስ መውጫ አዝማሪ)***

ጫካ እየገቡ የፈለጋቸውን ወንድ ቢመስሉ። «ከቴም» አሉ እትዬ አስካለ። እንደሚመስለኝ መወዳደሩ ነበር። ዕድሜዬን ለአንድ ቀን እንኳን ፎክሬ ሳልተኩስ ብሉ። ጥላቻው ከደርጉ ሣይሆን ከወንድ አይወለድብሽ ድንጋይ መሰለኝ። ከበላይ ዘለቀ ትንቢት ሳይሆን አይቀርም። እሱ ወንድ ሊሆን ይሄ ሁሉ ሴራ።

እንዲህ ይላሉ ቋሚዎች፦

*በላይ ዘለቀ ሊሰቀሉ አዲስአባ እሥር እንደተቀመጡ ከሚጠብቃቸው ዘበኛ ጋር ውል ይዋዋላሉ። እንዲህ ይሉታል......"እኔ ወንድ ነኝ። እንኳን ከስደት የተመለሰ ፈርጣጭ ይቅርና ጣሊያን በሩምቢላ አልቻለኝም፣ የሚገርመኝ የዚህ ፈርጣጭ የዚህ ፈሪ ነገር ሳይሆን ደይኑን ሲያይ የአበረ ሕዝቤ ዝም ማለት ነው። ቢቸግረውም ነው። የአገሬ ጀግኖቿ ደም የማንም ዘፋን ማሳደጊያ ከሚሆን እዚህ አገር ላይ ጀግኖች እንዳይወለዱ እፈልጋለሁ። ምን? ቢሉ ትርፉ በከሐዲ መገደል ነዋ። ገባህ? እናልህ ቃል እገባልሀለሁ። አንድ ቦታ ሊጀባህ ትወስደኝና እርግማኔን የምፈጥምበት ቦታ አለ እዚያ......ጠሎቴን አድርጌ ትመልሰኛለህ" ይሉታል። ጠባቂው በጣም ስለሚያከብራቸው "እወስዶታለሁ። ግን ቅርብ ይሁን" አላቸው። እላቸውም "ቅርብ ነው ኸረ ቅርብ ነው" ይሉትና አምኖአቸው ከእስር ቤት ይዞአቸው ይጠፋል። ብዙ ተጓዙ። ብዙ ተጓዙ። "ምነው ቅርብ ነው ብለውኝ አልነበር" ሲላቸው 'ደረስን*



@BOOKALEM

'ኢየሉት:: 'ምነው? ሲሏቸው 'ደረሰኝ ኢየሉት በበዶ እግር ቀንና ሌሊት ተጉዘው ንፋስ መውጪያ:: ንፋስ መውጪያ ሊመሽ ሲል ደረሱ አሉ:: ጠባቂያቸው የሚያምኑት ታቦት ፈልገው አንጥፈው የሚፀልዩ መስሉት ነበር::. ሲያዩ ግን ሜዳ መሐል ወደ ወደቀ ድቡልቡል ድንጋይ እየሮጡ ሔደው......በለስላሳ ገላው ላይ እየቧጠጡ፣ እየተፍጨረጨሩ አናቱ ላይ ቆሙና እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው ትንሽ ፀለዩ:: ጠባቂው እያንጋጠጠ የሚሰሩትን ያያል:: ከዚያ ጉሮሮአቸው እስኪሰነጠቅ......"ወንድ አይወለድብሽ" ብለው ጮሁ:: ከእርሻ መልስ ላይ ያሉ ገበሬዎች ድምፅ የመጣበትን ቀና ብለው ሲያዩ ቀጭን፣ መሐከለኛ ቁመት ያለው፣ ራሰ ከበድ፣ ፊተ ሰልካካ ሰው ድንጋይ ላይ ቆሟል:: ለጥያቄ ጊዜም ሳይሰጡ በላይ ከድንጋይ ላይ ጡብ ብለው ወረዱና ሌላም ወሬ ሳያበዙ "በል ውሰደኝ......መልሰኝ " ይሉታል ጠባቂያቸውን:: ይኼን ጩኸት የሰሙ ገበሬዎች ይሰበሰቡና "የማን ጥጋበኛ ነው እርጉዝ ቀፍድዱት እንጂ" ተባብሉ በላይና ጠባቂያቸው የሚያስጥል ጩኸት የሚጮኸው..... .....ቀፍድዱት እንጂ" ተባብሉ በላይና ጠባቂያቸው ይከበባሉ::

በላይ ዞር ይሉና ገበሬዎችን: "ምነው? ምን ሆናችሁ?" ይላሉ::

"ማነህ አንተ? አንተ ሰው አገር መጥተህ ወንድ ምንትስ እያልክ የምትቀባጥር......"

"በላይ ነኝ"

"የማን በላይ"

"አንድ በላይ ነው ያለ"

"በላይ ዘለቀ?"

"ታዲያማ"

"ምነዋ ታስረሃል አላሉማ"

"እንኳን የተፈራ ሲባን የጥሊያን ታንክ አላሰረኝም"

"ታዲያ ምን ረገምካት"

"ይህቺ አገር ከጦርማ እንጂ ወንድ አያስፈልጋትም ብዬ ነዋ"

"በል እንዳታስጨርሰን:: ሰንቅህን እንስጥህለን ሂድ"

"ምቷን አበላለሁ:: ገበሬ ሁላ" ብለው ከጠባቂያቸው ጋር ጀንበር ስታዘቀዝቅ የተነሱ አዲስ አበ በሁለተኛ ቀን ጀምበር ስታዘቀዝቅ ደረሱ::

ያን ሁሉ.....ያን ሁሉ ምንገድ በበዶ እግር ላፍ አድርገውት ሲመለሱ ያውቀ አልነበረም አሉ:: (የተረት ነገር አይገርምም) (የበላይ የእግር ጥንካሬም) (እሾክ ወጋኝ ብለው አንድም

ጊዜ ወደ ሁዋላ አልቀሩም አሉ) በበነጋታው እንዲሰቀሉ ተወስኖ ነበርና ከእሥር ቤት እየተነዱ ሲወጡ የለበሱት ቀጭን እጀ ጠባብና እንደ ተፈሪ ቅድ ሱሪ። እሱም ያለቀ ያላለቀ። የሚገርመው ግን በእግራቸው የተሸከሙት ጭቃ ነበር አሉ።

ወደ ማስቀያው ሲጠጉ "ጥረጉት እንጂ" ተባሉ። ኩስተር ብለው "አይ እንዴት ተብሎ፣ እንዴት ሆኖ.....ሥልጣኔን ቀማችሁ፣ ሐይሌን ሰበራችሁ፣ ጉልበቴን አደከማችሁ። የቀረችኝ ይህቺ አፈር ናት ፍቅሬን ልትቀሙኝ?" አሉ አሉ።

እንዲህ ሲሉ የሰማ ሁሉ ነበር አሉ የተገረመው: "እንዴ ይኼ ሰው አልቤኑን ብቻ ሳይሆን ምላሱንም ገርቶአል ለካ" ብለው።

ሲቃዮቹ "ኧረ ይሁን ይሁን ተወው.....ለገመዱ ይከብደዋል። ሲሰቀል ለገመዱ ይከብደዋል። ቶሎ ይሊድልን። የፈለገውን ያድርግ።" ይሉና ይስማማሉ። አዲስአባ መሀል የሆነ አደባባይ ነበር አሉ የተሰቀሉት። ታዲያ ተሰቅለው ነፍሳቸው ሲታልፍ እግራቸውን አቅፎ የያዘው ጭቃ ልክ ማስረያው እንደተፈታ ጫማ መሬት ላይ ዱብ አለ አሉ። የዚህ ዱቢታ ድምፅ ከፍተኛ ነበር ይባላል። ዱብታውን የሰማው ግን ጠባቂያቸው ብቻ ነበር። ሰው እየየው እተንጠለጠለው ሬሳ ስር ተጠግቶ ማጉንበስ አሳፋሪ ድርጊት መስሎት ከመሸ በሁዋላ ይመጣና ከበላይ እግር ስር የወለቁትን እነዚያን የጭቃ ጫማዎች ይወስዳል። መቸም ቢጨልምም በአጋጣሚ ያየ ሰው ነበርና ስለ በላይ የጭቃ ጫማ መጥፋትና የጠፋውም በሌሊት እንደ ጅብ እየደባ በመጣ ሌባ ቢጤ ተሰርቆ እንደሆነ ተናገረ። ነገሩም እንዲጋነንለት ሳይሆን አይቀርም ጫማው የጭቃ ይሁን እንጂ በውስጡ እንደመብራት የሚያበሩ ውድ ማዕድናት ዕንቁና ጌጣጌጥ እንደነበረበት አወራ። መንግሥት ግን ቢፈልግ፣ ቢያስፈልግ ዘበኛውን ሊያገኘው አልቻለም። ያ ጠባቂም ነፍሱን ለማዳን ይሁን የዘረፈውን ሐብት ተደብቆ ሊበላ ጠፋ አሉ።

ይኼ የቋሚዎች ወሬ ነበር።

ቋሚ ምላሱ ስላልሞተ ያወራል።

> በሬ እያስወለደ ዝንብ እያሳረረ
> ንፋስ መውጪያ ሳንባው እንደአለት ከረረ

አለነገር አላሉትም ደገኞቹ።

ለዚያም ነበር መሰለኝ ሲጃራ የሚባል ነገር ከተማው ውስጥ ባይሸጥ ባይለወጥ ይሻላል ይሉ የነበረው አንዳንዶች። የሚሰማ ጎረምሳ ቢኖር። ለምን? ቢባል የወሬ ጊዜ ይሻማል ተብሎ ነው አሉ። ከተከፈተው አፋችን ጢስ ይውጣ ወይስ ነገር?

አንድ ግራጫ በመሰለ ጠዋት እንቅልፍ እምቢ ብሎኝ ከአልጋዬ ተነስቼ ለማፏጨት እየሞከርኩ (በስንት ጥረት ትንንሽ ችዬአለሁ) ዋናው ምንገድ ስገባ ከሩቅ ሦስት ሰዎች ወደ በላይ ድንጋይ አቅጣጫ ሲያዘግሙ አየሁ። የአካሄዳቸው ሾካካነትና ጥንቃቄ ጉጉት ፈጠረብኝና የሚያደርጉትን ለማየት መንገዱ ዳር ዳር የበቀሉ ቁጥቋጦዎችን ተገን እያደረግሁ ተከተልኳቸው። አልፎ አልፎ ወደ ሁዋላቸው፣ ወደ ግራና ቀኝ ይመለከታሉ። በቁጥቋጦውና በድንጋዩ መሃል ግን ሰፊ ግልጥ ሜዳ ስለነበር ሳልታይ እነሱን ልቀርብ እንደማልችል ተረድቼ አድብቼ አጤናቸዋለሁ። ሦስቱም ድንጋዩ ጋ እንደደረሱ ግራና ቀኝ ተሰረጫጩና በየፊናቸው ድንጋዩን ተጠግተው በእጆቻቸው መዳበስ ጀመሩ። ዙሪያውን ተራምደው ከጨረሱ በሁዋላ አንዱ ሽማግሌ ድንጋዩን በሁለት እጆቻቸው ተደግፈው ቆሙ። ሁለተኛው ከቆሙት ጀርባ ጎንበስ ብለው በእግሮቻቸውና በእጆቻቸው መሬት ላይ ሆኑ። ረዘም ቀጠን ያሉት ሦስተኛው አዛውንት ያጎነበሱት ሰውዬ ላይ ቆሙና በመጀመሪያው ሽማግሌ ጀርባ ላይ ተረማምደው ድንጋዩ አናት ላይ ወጡ። ይሄን ሁሉ ሲያደርጉ ድምፃቸው አይሰማም (ትንሽ እንኳን አያምጡም? አያቃስቱም? ወይስ አልተሰማኝም?)። ድንጋዩ ላይ የወጡት ሰው ጎንበስ ብለው የሚፈልጉትን መፈለግ ጀመሩ። ትንሽ ቆይተው ራሳቸውን በአሉታ ነቀነቁ። ድንጋዩ አናት ላይ ወዲያ ወዲህ አሉና በወጡበት መልክ ከድንጋዩ ላይ ወረዱ። ልብሳቸውን አረጋገፉና ሦስቱም እንደሚመካከሩ ሁሉ ተጠጋግተው ቆሙ። ምን ይፈልጉ እንደ ነበረ ስላወቅሁ ደስ አለኝ። ከቆሙበት እየተገላመጡ ዙሪያ ገባውን አዩና በመጡበት አኳዋን ወደ ከተማው መመለስ ጀመሩ። ራቅ ብለው እንደሄዱና ሊያዩኝ እንደማይችሉ ስገምት ወደ ድንጋዩ ሮጥኩ። ሽማግሌዎቹ ወደ ሄዱበት አየሁ። ማን እንደጠቆማቸው አላውቅም በከፊል ጨለም ባለው ጠዋት ከተማው ጠርዝ ቆመው አሯሯጤን ሲያዩ አየሁዋቸው። ማን እንደሆንኩ ከዚያ እርቀት የሚያውቁ አልመሰለኝም። ጠምዘዝ ብዬ እንዳያዩኝ ከድንጋዩ ጀርባ ቆምኩ። ድንጋዩ ልጅ በነበርኩ ጊዜ ተራራ የሚያክል ይመስለኝ ነበር። ልክ እንደ ድሮው የሚያብለጨልጭ ጥቁር ነበር። ከድንጋዩ ጀርባ ፊቴን ወጣ አድርጌ አዛውንቶቹ በሄዱበት በኩል አየሁ። ሁለቱ መንገዳቸውን ቀጥለዋል። አንደኛው (ቀጫጫው) ቆመው ያያሉ። እቆሙበት እጆቻቸውን ያፍተለትላሉ። እሳቸውን ተውኩና በማልታይበት በኩል ድንጋዩ ስንጥቅ አውጥቶ እንደሆነ መፈለግ ጀመርኩ። ሩጫዬ ሆዴን በጥብጦት ነበር መሰለኝ ከመሃል መፀዳዳት ፈለግሁ። ከድንጋዩ ሽተት ብዬ ሱሪዬን አውልቄ ቁጢጥ አልኩ። በጠዋት ብርድ ውስጥ ከሦስት የተረገመ ምጥ በሁዋላ እኔ ሳልሆን አንድ ሰው ተናገረ፡



@BOOKALEM

"የዱባለ ልጅ ነህ አይደል?!!" በቁጣ::

"ምነው?" በድንጋጤ ተና አልኩ:: ቀጫጫው ሽማግሌ ናቸው::

"ምነው ይለኛል? ነህ አይደለህም? ምኝታም የለ?" አልፈውኝ ሄዱ።።

ወደ ጀርባዬ ስለሄዱ ቂጤን ከወይኖቻቸው ለመጋረድ እዛው የተቀመጥኩበት ተሽከርክሬ ፊቴን ወደ እሳቸው አዞርኩ::

ለብቻቸው እያወሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ:: የት ነበር የሚሄዱት?

ተፀዳድቼ እንደጨረስኩ ድንጋዩን ከላይ እስከታች ብወጣና ብወርድበትም ስንጥቅ ፈልጌ አጣሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ እድንጋዩ እናት ላይ መቆም የሚያምር ትዕይንት እንደሚለግስ ተገነዘብኩ:: ሰው እንደ ልብ አይታይባትም እንጂ ከጉብታዬ እጅግ የተሻለች ቦታ ነበረች:: የምስራቅ ሰማይ አድማስ እንዲህ በቀላ ጨረር ተኩሎ ዳር እስከ ዳር ያምራል።

ወይስ ቀንቶኝ ነበር?

ከሳምንት በሁዋላ:

"ኸረ የበላይ ድንጋይ አልተሰነጠቀም:: እስኪ በጋው ሲያልቅ በክረምቱ ዝናብ ምክንያት ድንጋዩን የሸፈነው አፈራ ሲታጠብ እናየዋለን ተብሏል አሉ"

"ስንጥቁ? ስንጥቁማ ይኖራል ለምን አይኖርም ዘመኑን አታይም የተገላበጠ ነገር አለ:: ይሄ አፈራና ጭቃ ልጆች እየወጡበት ቆሽሾአል:: እባካችሁ ልጆቻችሁን ከዚያ እንዳይደርሱ ከልክሏቸው:: መጫወቻ አጡ እንዴ? ዝናቡ ሲያጥበው ቀልጭ ብሎ ይወጣል ተብሏል" አሉ::

"ትሄዳለህ እንዴ እዚያ?" አለኝ አባቴ::

"የት?"

"የበላይ ድንጋይ?"

"ምን ተዳዬ" ፊቴን በጮሌነት ከፍቼ::

የማይወዱትን አያምኑትም::

የማያምኑትን አይነግሩትም::



@BOOKALEM

# ዉፎኛ

ኢልያስ ትምህርት እንዳስጠላው ይነግረኝ ነበር:: እየደጋገመ "ከባንዳ ጋር አልማርም" ይለኛል:: የምጠላው ቃል ደ'ሞ 'ባንዳ' የሚባለውን ነበር:: ዘራሁንና እህቴ ያደረጉት ሁሉ የባንዳ ሥራ ይመስለኛል:: ጉብታዬን ያቆሸሹ፣ ጉብታዬ ላይ ያለ እኔ ፈቃድ የሚሰፍሩ ሰዎች ሁሉ ባንዶች ይመስሉኛል:: እየዋኘን ነው 'ትምህርት ያስጠላኛል' የሚለው ኢልያስ:: እኔ ደ'ሞ ዋና ወድጄ ልሞት:: ውሐው ደስ ይላል:: መስከረም ስለነበረ ደ'ሞ ዙሪያችን አረንጓዴና ቢጫ መልካምድር:: እኔ ስዋኝ ኢልያስ ሙታንታውን ብቻ ለብሶ ዋርካ ስር መፅሐፍ ያነባል......

"ምንድነው የምታነበው?" አልኩት

"መፅሐፍ"

"ምን መፅሐፍ?"

"ልብ ወለድ......የአማርኛ ልብ ወለድ"

"ምን የሚባል?"

" 'ጨረቃ ስትወጣ' የሚባል"

አፌ እንዳመጣ "ታውሰኛለህ?" አልኩት

"ጨርሺዋለሁ እየደገምኩት ነው......እንደውም ውሰደው"

ከወንዙ ራቁቴን ወጥቼ ሔድኩ:: የእግሮቼን መሐልም አልጋረድኩ:: መፅሐፉን ተቀበልኩና አየሁት:: ሽፋኑ በትንሹ አርጅቷል:: 'ጨረቃ ስትወጣ' ይላል:: የሽፋኑ ስዕል ላይ የሆኑ ሰዎች ዛፍ ስር የተቀመጡ ይመስላል:: ነጭ ክብ ነገር መፅሐፉ መሐል (ጨረቃ መሆኗ ነው?) ተስላለች:: ጨረቃ ትሆናለች:: ደራሲው ብርሐኑ ዘርይሁን ነው::

ኢልያስ ፀጉሩን ያካል::

"አንተ እዚህ ጋ ፀጉር ገና በደንብ አላበቀልሽም" አለኝ::

አፈርኩ::

"አንተስ......?"

"እሃ! ብዙ ጊዜዬ ነው......ሴት አታውቅም?"

"ምን ማለትህ ነው......ከንፈር ስሚ?" አልኩት:: ራሱ ቃሉ እያስጠላኝ::



@BOOKALEM

"አዎ ወይም ሌላ"

"እንዲህ ያለ ነገር አይወጣኝም" አልኩት

"መጥፎ አኮ አይደለም.....ወዳጅ የለህም?"

"የለኝም አንተ አለህ?" አልኩት

"ሀይነት ነገር"

"ምንድነው ሀይነት ነገር"

"እንትን ናት:: ውሽማዬ ናት"

"የተለያየ ነው እንዴ?"

"ዋናው ከተማ ነው ያለችው:: ደን ልማት መስሪያ ቤት ፀሐፊ ናት"

"አደርቅብሀም?" አልኩት:: ውሽማ እንዳለው መስማቱ ግራ እንዳጋባኝ ሁሉ::

"ሽርክ ሾፌሮች አሉኝ የፈለኩ ቀን እሔዳለሁ"

"እናትና አባትህ አይቆጡህም?"

"የት ያውቃሉ:: ከጓደኞቼ ጋር ያደርኩ ይመስላቸዋል.....አባቴ ቤት የለም"

ለምን እንደተናገርኩ አላውቅም::

"ወዳጅ አለችኝ" አልኩት ውሸቴን::

"ማን?" አለኝ፣ ቀጠለና በችኮላ "ትደብቀኛለህ?" አለ::

"ለመደበቅ ሳይሆን አለ አይደለ"

"ማን ናት?"

"ወሰን"

"ወሰን?" በዐይነ ሕሊናው ይፈልጋል "ያቺ ቀንጆ ልጅ? ገብረ ማነው አባቷ....."

"ታዲያስ" አልኩት::

ዐይኖቹ ተብልጥጠው አየኝ::

"......ወንዷ......እንዴት ነው ስመሃታል?"

"አይደለም አለ አይደለ"

"አሃ ትደብቀኛለህ.....ምን ትደብቀኛለህ? እንትን አላደረግሽም?»



@BOOKALEM

"ወደ ፊት ላገባት ነው የምፈልገው.....እሷም"

እንዲህ ማሰቤና መናገሬ እራሱ አስጠላኝ።

"እንትን ማድረግ ትፈልጊ እንደሆን ዋናው ከተማ እወስድሻለሁ"

"የክፍለ ሐገሩ ዋና ከተማ ከእኛ ከተማ ይበልጣል? ጉራ እኮ ነው ከዚያ የሚመጡትን እናውቃቸዋለን እኮ" አልኩት እየፈራሁ።

"እዚህ ትታያለሃ!"

"እዚህም አውቃለሁ እንዳትለኝ" አልኩት።

"አንድ አሮጊት አለች"

"አሮጊት?"

"አሮጊት ስልህ አሮጊት አይደለችም......ምን አስፈራህ?"

"አልፈልግም ወሬውን ድንገት ወሰን ብትሰማ" አልኩ ፈጥሬ።

ኤልያስ ሳቀ።

እስከዚያ ድረስ ስዋሽ ኤልያስ አልተቀናቀነኝም። ምን አልባት ቢጠይቃትስ? ወሰንን አቁሞ ቢጠይቃትስ? ወይም ወሰንን 'አንቺ......'የሙዘገቡ ወዳጅ' ብሎ ቢጠራትስ? ብዙ ዋሽቻለሁ። ይኼን ውሸት ለማጥፋት ፈለግሁ። ከወንዝ ስንመለስ ቤቴ ሳልገባ እነ ወሰን ቤት አጠገብ ቆሜ ዋልኩ። ወሰንን ደግሞ እናቷ ወደ ውሐ መጠጫ ሸክና ለውጠዋታል መሰል ከቤቷ አልወጣ አለች።

ብትወጣስ?

ብትወጣ ጠጋ እላትና "አንቺ እኮ ወዳጄ ነሽ" ብዬአት እሔዳለሁ።

ወሬኛ ሆንኩ።



@BOOKALEM

# እወድሻለሁ

ጠበቅሁ:: ጠበቅሁ:: ማታ ወሰን ከቤቷ ወጣች:: ወደ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ:: ከ"ጨረቃ ስትወጣ" ልብወለድ ያነበብኩት አንድ ገፅ ብቻ ነበር:: በመጀመሪያ ማንበብ አልቻልም:: ቶሎ ቶሎ ማንበብ አልችልም ነበር:: ሁለተኛ ወሰንን ከቤቷ እስክትወጣ ስጠብቅ የቤታቸው በር በተከፈተ ቁጥር ቀና እላለሁ:: ቀና ስል ያነበብኩትና የቆምኩበት ቦታ ይጠፋኛል::

መጨረሻ ላይ ከማን ጋር ትወጣለች? ከእህቴ ጋር:: በሸቅሁ::

በጉን አይተውኝ ሲያልፉ: "የኛ አንባቢ የኛ ምሁር ታዲያስ" አሉኝ::

ለስድብ ጣቴን አሳየሁዋቸው.....የማንም ቂጣም አይሰድበኝም::

"ባለጌ ስድ አደግ" አለች እህቴ

"ማነው ባለጌ?" አልኳት:: (ከእናቷ የበለጠ ባለጌ እኮ የለም:: እናቷን እንዲህ ሰድባት ታውቃለች?) የሰራችውን ስለምታውቅ ዝም አለች:: ፊቷን አዙራ ምንገዷን ቀጠለች:: ተከተልኳቸው:: ወሰን እህቴን ቤቷ አስገብታ ስትመለስ ፈገግ ብዬ ተጠጋሁዋት:: (ሲሸኛኙ ይውላሉ......አያልቅባቸውም?)

"ምነው?" አለች እየሳቀች

"አንድ ነገር ልንገርሽ" አልኳት::

ሴቶች ወሬ እንደሚወዱ አውቃለሁ:: ቆም አለች:: የሚያስደስት ነገር አላት::

"ምንድነው ተናገራ" አለችኝ::

"ወዳጄ ነሽ አይደለ?" አልኳት::

"እንዴ! የማን ደረቁ ነው" አለችና ልታልፈኝ ስትል ያዝኳት:: ከዚያ በሁዋላ ምን እንደምናገር አላውቅም......

"እኔ እኮ እህትህ ነኝ" አለችኝ::

ደነገጥኩ:: ወሰንን እህቴ ናት ብዬ አስቤአት አላውቅም:: እጇን ለቀቅሁዋት:: ቆይቶ አልፋኝ ሔዳ ቤቷዋ ልትገባ ስትል "ቢሆንስ" አልኩ ለራሴ::

ስላጋጠመኝ ነገር ለኤልያስ ልነግረው እውነቱን ሳወጣና ነፍሴን ሳሳርፋት ብሞክር አልቻልኩም:: ኤልያስን ባላገኘው ኖሮ እንዲህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ አልገባም ነበር:: ጉብታዬ ተቀምጠው አላፊ አግዳሚ ባይ ኖሮ እንዲህ ያለ ሰዳ ውስጥ አልወድቅም ነበር::



@BOOKALEM

ኤሊያስ ስለእኔና ስለ ወሰን ያወቀ እየመሰለኝ ከተማ መውጣት ፈራሁ:: ቤቴ ተጋድሜ ለሁለት ቀኖች ያህል 'ጨረቃ ስትወጣ' ን አነበብኩ:: ያቺን መፅሐፍ የፃፈው ሰው እግዚአብሔር መሰለኝ:: እንብቤ ከጨረስኩ በሁዋላ የሽፋን ስዕሉን ለረዥም ጊዜ አየሁት:: ዛፍ ስር የተቀመጡት ሰዎች እኔና ወሰን መሰሉኝ:: ወሰን ግን የለችም:: እኔ ብቻዬን ጨረቃ ስትወጣ ዛፍ ስር ተቀምጬ አሰባለሁ:: ተሰምቶኝ የማያውቅ ነገር አደረብኝ:: ሴት ጓደኛ ያስፈልገኛል:: ሴት ጓደኛ ግን የለኝም:: ወሰንን እጇን ስይዛት ለአጭር ጊዜ የተሰማኝ ደስታ ብዙ ጊዜ ብይዛት ብዙ ጊዜ እንደሚሰማኝ አወቅሁ:: ወሰን ግን እኔ አስቤ የማላውቀውን 'ወንድሜ ነህ' አለችኝ::

ለኤሊያስ መፅሐፉን ስመልስለት በእኔና በወሰን መሐል ስለደረሰው ችግር አወራሁለት:: ምን አልኩት::......ወሰንና እኔ ዛሬ ጠዋት ተጣልተን በጣም ተኩራርፈን እንደተለያየንና ዝም ብሎ መለያየት ብቻ ሳይሆን ለቅጣት የሚሆን ጥፊ ቀንጆ ፊቷ ላይ እንደሰጠሁዋት......

ኤሊያስ ታዲያ: "ሆሆሆ" ብሎ ሳቀ::

ስቆ ብቻ አላቆመም ቀጠለና ወሰን የምትባል ሴት ጓደኛ እንደሌለችኝና ብትኖርም ምናልባት የአጐቴ ልጅ እንደሆነች......ከባድ ውሸት እንደነገርኩት አውርቶ ቅጥፈቴም ፊቴ ላይ እንደሚነበብብኝ በቆሸሸ ጣቱ ወደ ዐይኖቼ እየጠቆመ ነገረኝ::

"ይልቁን አሮጊቷ ጋር ልውሰድህ" አለኝ::

እፍረት ስለያዘኝ ተከትዬው ወጣሁ::

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት......



@BOOKALEM

# ......ቀይ ወፍራም ሴት

ከዙዋላው እየተከተልኩት ለሩብ ሰዓት ያህል ተጉዘን ከከተማ ወጣን፡፡

ከብዙ ቤቶች ተነጥላ ሜዳ መሃል ከመሬት ለመደባለቅ ሁለት ጫማዎች ከፍታ የቀራት አንዷት ቤት አጠገብ ስንደርስ ኤልያስ ቆመና: "አትፍራ እኔ ገብቼ አናግራትና እመጣለሁ ጠብቀኝ" ብሎ በር አንኳኳ፡፡

የሴት ድምፅ ሰማሁ፡፡ በር ተከፈተ፡፡ ኤልያስ ምንም ሳይናገር ገባ፡፡ በር ተዘጋ፡፡ ፈራሁ፡፡ ትናንት፣ ከትላንት ወዲያ የማውቀው በጨለማ የተሞላው ሰንጣ የሚውጠኝ፣ የቆምኩበት መሬት እንኳን ተንሸራቶ የሚሔድ፣ የማላያቸው ብዙ እጅግ ብዙ ዐይኖች እየታዘቡኝ መሰለኝ፡፡ እዚያ ከገባሁ በሁዋላ ነገም ከነገወዲያም ግንባሬና፣ ጉንጬ ላይ የባለጌ ምልክት ጠባሳ ተፈጥሮ የሰራሁት ነገር ይገለጥብኝ ይሆናል እያልኩ ለራሴ፡፡ መሮጥ ተመኘሁ—ኤልያስ እንዲታዘበኝ ደ'ሞ አልፈለኩም፡፡ ኤልያስ የፈሊጋት ሴት ሞታ ብትገኝ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ኤልያስ ሲወጣ "ያቺ ያልኩህ ሴት ሞታ ስለተገኘች ያልኩህን ነገር ማድረግ አንችልም" ቢለኝ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ብዙ ሳይቆይ ተመልሶ ወጣ፡፡ በሩ እንደተከፈተ ነበር፡፡ በበሩ ቀዳዳ የማየው ደብዛዛ ብርሃን ጉድጓድ መሰለኝ፡፡ ኩራዝ ግድግዳ ላይ ተሰቅሏል፡፡ ሴትዮዋ ጥላ መስላ ትታየኛለች፡፡ አጭር ጥላ፡፡ ኤልያስ ቀረበኝና "አትፍሪ እንኪ ይሔን"፡፡ ዝቅ ብዬ አየሁ፡፡ በእጁ የሆነ ነገር ሊያሲዘኝ ይዳብሰኛል፡፡ ብሮች ነበሩ፡፡ ለምን እንደሆነ ገብቶኝ መቀበል አፈርኩ፡፡ የለመድኩት ጓደኛዬ እራሱ አሣፈረኝ፡፡ ወደ ሴትዮዋ ለመግባት ተስማምቻለሁ፡፡ ወደ ጣር የምሔድ መሰለኝ፡፡ ጥቁር ጣር፡፡ ሴትዮዋን አውቃት ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ከጉብታዬ ላይ ተቀምጬ የማያት፡፡ በጣም ቀይ ሴት ነበረች፡፡ ከእሷ ይልቅ ቅላቷ የሚታይ፡፡ እውስጥ በክፊል ጨለማ ነበር፡፡ የኩራዙ መብራት ባልተስተካከለ መልክ ይበራል፡፡ ደንገዝገዝ ያለ ቦታ መርጬ ሳላስበላ ቆምኩ፡፡ ሴትዮዋ በሩን ዘግታ ወገቧን ይዛ እየሳቀች ታየኛለች፡፡ ፀጉሯ ጀርባዋ ድረስ እንደ ጥቁር ወንዝ ይወርዳል፡፡ ፋርጣ የሆንኩ መሰለኝ፡፡ ፋርጣ ሆንኩ እንጂ፡፡ እጄን ዘርግቼ ብሮቹን (ምን ያህል እንደ ሆኑ አላውቅም) ሰጠሁዋትና ተቀመጥሁ፡፡ ተቀብላኝ ለእኔ የማይታይ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠችው፡፡ የቆሸሸ ወይም ቀለሙ ጥቁር የሆነ ጠረጴዛ ይሆናል፡፡ የብሮቹ ድምፅ የበለጠ ስለ ስህተቴ የሚነገር አሉባልታ መሰለኝ፡፡ መጋረጃ ገለጠችና አልጋ ዳር ቁጭ አለች፡፡ ሰድሜዋ ሰላሳ አይሆንም? ሳቋ ከፊቷ ላይ አልተነሳም፡፡ ምን ያስቃል? እስቅ ነበር?

"አትመጣም እንዴ?"



@BOOKALEM

አንገቴን ደፋሁ:: ስትጠጋኝ እሰማለሁ:: እግሮቿን አያለሁ:: የቀሚሷን ጫፍና እግሮቿን አያለሁ::

የቀሚሷ ጫፍ አሮጌ ቀሚስ እንደለበሰች ይናገርባታል:: እጇን ሰዳ ጭንቅላቴን ያዘችው:: ዳበሰችኝና:

"በጣም ታምራለህ:: የምታምር ልጅ ነህ:: ራቴን ሳብላህ"

ኸረ ኸሮሽን ብይ እቴ:: ምን ልታደርገኝ ነበር:: ሽሽት አልኩ:: ልብሴን ከፊት ለፊት ይዛ ጐተተችኝ:: ፈራሁ:: ልቤ ሲነርት እሰማዋለሁ:: አፌ ደርቋል:: ምንም መናገር አልቻልኩም::

በግድ: "ገንዘቡን ውሰጂው በቃ" አልኩ::

"ለምን ከፈልከኝ?"

"በቃ አልፈልግም"

"ቤት ነህ? የለህም እንዴ?" አለችና እጇን ወደ እግሮቼ መሐል ላከች::

ገፋሁዋት:: ሰውነቷ ለስላሳ፣ ከባድና ሙቅ ነበር::

"እንዴ ምነው ልጅቷ......ተወዋ" አለችና ወደ አልጋዋ ሔደች::

እንደቆምኩ ቀረሁ:: እሷ ተቀመጠች:: እኔን የመሳብ ብልሐቷን ለመለወጥ ነበር መሰለኝ ልብሷን ማውለቅ ጀመረች:: እግዜር እንደፈጠራት ራቁቷን ቆመች:: ዛሬ 'ራቁት' የተባለ ድምፅ ስሰማ ትዝ የሚለኝ የዚህች ሴት ገላ ነው:: ለእኔ ያን ጊዜ ትልቅ ነበረች:: አሁን ትዝ ስትለኝ:: ጢም ያለ፣ ያልራበው፣ ያልጠማው በድሃነቱ ረክቶ የሚኖር ገላ:: እግሮቿ መሐል መአት ፀጉር ነበራት:: መተንፈስ አልቻልኩም:: ከቆምኩበት ተቀመጥሁ:: ቂጥጥ አልኩ:: ዐይኔን አፍጥጬ አያታለሁ:: እዚያ ተቀምጬ ሰውነቷን ማየት ነበር የምፈልገው:: ዐይን ይሞላል:: ሴትዮዋ ትልቅ ናት:: እንደተፋጠጥን በር ተንኳኳና: "አንተ አትወጣም?" አለኝ ኤልያስ......ሴትዮዋ ድምጿን ከፍ አድርጋ በሳቅ መንተክተክ ጀመረች:: ጡቶቿ:: ረግተው የተቀመጡት ጡቶቿ ውሐ እንደሞላው ፊኛ ተወዛወዙ:: በሥጋና በቦርጭ ጢም ብሎ የተሞላው ቆዳዋ በሚንቃነቀው የስብ ጉድ የሚቀደድ መሰለ:: ለመውጣት ወደ በሩ ስሔድ ከሁዋላዬ ያዘችኝ::

"ቆይ ቆይ......" አለች::

"ልሔድበት" አልኳት::



@BOOKALEM

አፌን ዘላ ሳመችኝ። በትክክል አፌን እንኳን ሳይሆን ከፊል ጉንጩን፣ ከፊል ከንፈሬን፣ ከፊል አገጬን፣ ከፊል አፍንጫዬን። አፌን በሙሉ አላገኘችውም። አላማዋ አፌ ነበር። አፌ። አ አፌ። መንጭቄአት በሩን ከፍቼ ወጣሁ። ሳቋ። ሳቋ ከተራቆተ ሰውነቷ እንደጉርፍ ይወጣል። እንደጉርፍ እኮ ነበር። ራቁቷን በር ላይ ቆማ።

ኤልያስ የሆነው ነገር ስለገባው ይስቃል። ይስቃል። አፉን ወደ ሰማይ ከፍቶ። ደ'ሞ እያጉነበሰ፣ እየቆመ። ሆዱ ተወርውሮ ተወርውሮ የሚወጣበት ሀይነት ፈርቶ በሁለት እጆቹ አቅፎ እያቆመው። እያቆመው በሁለት እጆቹ። አፉን ወደ ሰማይ ሰቅሎ እሷም እራቁቷን......አይበርዳትም እንዴ? በር ላይ ቆማ እንደከሰል ቆማ በሰው ቅርፅ ከጨለማ እንደተሰራ ጉድጓድ......ግራ ቀኙ፣ ጀርባና ፊት በሁለት ትላልቅ ሳቅ መሐል ጠምደው ፋራ ነፍሴን አጣብቀው። በሳቅ አጣብቀው ይዘው......

በሁለት እጆቼ ፊቴን በማፈር ሸፈንኩ......

የኤልያስ እጅ ተከሻዬ ላይ ተጋድሟል......ሊያባብለኝ ይፈልጋል። መንጨቅሁት።

አያቆምም። ምኑ ያስቃል? ሳቀ። በጉን ራቁቷን የቆመችውን ሴት እያየ ሳቀ።

"ስማ ይኼ ቀላል ነገር ነው" ይለኛል። ምን አሳቀው ታዲያ። ምን የሚያስቅ ነገር ነበረው።

ሳቁን አቁሞ ከሁዋላዬ እየተከተለኝ ሳንነጋገር ከተማ ገባን። አንድ ወና ቤት (የዚህ ቤት ባለቤት አቶ ዘለቀ የሚባሉ ሰው ነበሩ። ከመሬት አዋጅ በሁዋላ ቤታቸውን ትተው ስለሸፈቱ ቀበሌ ወርሶት ዕህፈት ቤት ሊያደርገው ያስባል ሲባል ሰምቻ ነበር።) ውስጥ ቦታ አመቻችቼ ተኛሁ። ቤቴ መሔድ አልፈለኩም። ሠላሜ እንዲረበሽ አልፈለግሁም ነበር። ከነኩት ዕብት ያዩት ዕብት ይሻላል። ዕንቅልፍ ሳይዘኝ በፊት ኤልያስ የነበርኩበት መጣ። ሁለት ጠርሙሶች በእጁ ይዟል። አጠገቤ ሳጠራ ጠርጉ ተቀመጠና

"ምነው አኩረፍክ?" አለኝ

ዝም አልኩት......

"እርሳው። ትደርስበታለህ"

"ልክ አይደለሁም"

"ስለዚህ ነገር ባናነሳ ጥሩ ነው.....ይሆቺን ጠጪ" አለና በኩካ ጠርሙስ የተሞላ ጠጅ ሰጠኝ። ተቀበልኩት።



@BOOKALeM

ጠጁ ቀዝቃዛ ነበር። አንዴ ስጎነጭ ግፍልፍል ያለችው ነፍሴ እንደ ጥንግ ተጠቅላ ልሰይመው ወደሚያቅተኝ ስፍራ ውስጥ ያረፈች መሰለኝ። ብዙ ሳይቆይ ሲጃራ ለኩሶ ሰጠኝ። ሲጃራውን አየሁት።

"ሮዝማንስ ነው" አለ።

ፀጥ ብለን ብዙ ቆየን። ጠጆቹ አልቀው ሁለተኛ ሲጃራዎቻችንን ለኩሰን ተቀመጥን። ከመሐል ጠጁ ይሁን ወይ በምሽቱ ያሳለፍኩትን የከሸፈ ጀብድ እንደገና በአዲስ ዐይን አይቸው እንደሆን አላውቅም ወይ አደገኛ ልምዶች ነቂሶቹን፣ ዝርዝሮቹን ስናያቸው ስለሚያስቁ 'ቡፍ' አልኩና ሳቄን ጀመርኩ። ያሳለፍነውን ነገር እንደገና እያነሳን ከኢልያስ ጋር እስከ ዕኩለ ሌሊት አሽካካን።



@BOOKALEM

# ብርሐኑ የሚባለው አስማተኛ ሰውዬ

ኤልያስ ዘማቾች፣ አስተማሪዎች፣ ተማሪዎች፣ ብዙ ብዙ ዐይነት ሰዎች ሠላማዊ ሰልፍ ስለሚወጡ እንድገኝ ጠርቶኝ ነበር:: አልሔድኩም:: እኔ በሽቁአለሁ:: የበሸቅሁበት ምክንያት ማዘጋጃ ቤቱ ገበያውን ለማስፋት በሚል መብራት ያለበትን ጉብታዬን ስላፈረሳት ነበር:: ሥልጣኔ አመጣሁላችሁ ሊለን ይሆናል:: አንዳንድ ሹሞች የሚያስገርሙ ፍጡራን ናቸው:: ትንሽ ደብሬን አፍርሰውና የከተማውን ማዕከል ጨለማ ውስጥ ነክረው እነሱ ምን እንደሚያገኙ ከቶ አልገባኝም:: ታርሶ የፈረሰው ቦታ የውስጥ አፈሩ ወጥቶ ጠቁሮ ነበር ያገኘሁት:: መገፈፍ ማለት ይሄ ነው:: መረሬው መሐል ላይ ሔጄ ቆምኩ:: ስልክ እንጨቱ የቆመበት ቀዳዳ እንኳን አልነበረም (ምን ያህል ቢቆፍሩት ነበር ጃን?):: ለእኔ ኢምፔሪያሊዝም፣ ባንዳ፣ አቀባባይ ከበርቴ የሚባሉት እነዚህ ጉብታዬን የሚያፈርሱ ነበሩ:: ያ ጉብታ ተነሳ አልተነሳ የሚጎዳቸው፣ በረባ የሚጠቀማቸው የለም:: ያው አንዳንድ የምርጥ መኩንኖች ወኪሎች ሲመጡ በሜጋፎን ይጮሁበታል እንጂ::

ቢመቻቸው ይሆናል:: አሽከሮቻቸውን ከከፍታ፣ የአድማጮቻቸውን ባይነትም፣ የአፋቸውን አከፋፈትም፣ ፊታቸው ላይ ያሉትን ዝንቦች አስፋፈርና የግፃቸውን አቀማጠንም እየተመለከቱ ደረታቸውን መንፈያ ሳይጠቀሙባቸው ይቀራል? ምናልባት ለራሳቸው ማንም የማይወጣው መድረክ ቢጤ ሊገነቡ አስበውም ይሆናል:: እንዲህ ዐይነት የመንፈስ ጣጣ ውስጥ ሆኜ ኤልያስ ታዲያ ሠላማዊ ሠልፍ ተሰለፍ እያለ ያስቸግረኝ ነበር:: አልፈለግሁምና እዚያ ወና ቤት ሔጄ የብርሐኑ ዘሪሁንን መፅሐፍ ለሦስተኛ ጊዜ አነበብኩት:: ፈጣን አንባቢ ሆኛለሁ:: ይሄ ብርሐኑ የሚባለው ሰው በጣም አስማተኛ ነው:: በጣም የሚጣፍጥ ታሪክ ይፅፋል:: ለራሴ እንዲህ ደስ የሚል መፅሐፍ ካገኘሁ ሁልጊዜ አነባለሁ እል ነበር:: አንድ ጊዜ እንጀራ እናት ስላሰቃየችው አንድ ልጅ አንብቤ መፅሐፉ አስጠልቶኝ ነበር:: እንጀራ እናትየዋ አሪፍ እንጀራ እናት አልነበረችም:: ደራሲው የእኔን ዐይነት የእንጀራ እናት አላየም:: የእኔ የእንጀራ እናት የእንጀራ እናቶች ሁሉ ሊቀመንበር መሆን የምትችል ነበረች:: እንጀራ እናቶች እንደ ኢህአፓ ወይም እንደ ደርግ ዐይነት ማህበር ወይም ፓርቲ ቢያቋቁሙ አርማቸው የእንጀራ እናቴ ፎቶግራፍ ይሆናል እል ነበር:: ብርሐኑ ስለ ፍቅር ነበር የፃፈው:: ያስደስትና ያሳዝናል:: ግን ስለ ፍቅር ነበር::

ማታ ጨረቃ ስትወጣ ለማየት ስጠብቅ አመሸሁ:: አልወጣችም:: ኩተኛሁ በሁዋላ ወጥታ ይሆናል:: ሲነጋ ለኤልያስ መፅሐፉን ሦስቴ እንዳነበብኩት ስነግረው በሳቅ ፈነዳ......ቤቱ ይዞኝ ሔደ:: ቤቱ ሔጄ አላውቅም:: ቤቱ ከወንዙ ከፍ ብሎ ከግንብ የተሰራ በጣም ትልቅ ቤት ነበር:: "የፊታውራሪ ናደው ቤት ነው" ሲባል እሰማለሁ:: ግቢው በፍራፍሬ የተሞላ



@BOOKALEM

ነበር። ፓፓዬ፣ ቡርትካን፣ ሎሚ እና ሙዝ ተተክሎበታል። የሙዝ ዛፍ አይቼ አላውቅም ነበር። እቤት ውስጥ ከሰራተኞቸው በስተቀር ማንም አልነበረም። ትልቁ ክፍላቸው ውስጥ ወስዶ መደርደሪያ የሞሉ መዓት መፃሕፍት አሳየኝ።

"የፈለከውን መርጠህ ውሰድ" አለኝ።

"የት አውቃለሁ አንተ ንገረኝ" አልኩት

"ብርሐኑን ነው የምታነበው?"

"እዎ"

መደርደሪያው ስር አጐንብሶ ሲፈልግ ቆየ። ቤታቸው ያምራል። የእኛ ቤት መዓት መዓት ሽረሪት ነበረው። የእኛ ቤት ሕይወት ያለው ኩርኒስ አለው። የእኔ ክፍልማ ሸረሪት ብቻ ነበር። አንዳንዶቹ የእኛ ቤት ሸረሪቶች አይጥ ያካክላሉ። ጥሩ ጆሮ ያለው እነኚህ እንስሳት ሲሮጡ ዱካቸውን መስማት ይችላል። ሲመስለኝ ሸረሪቶቹ ቦት ሳያጠልቁ አይቀሩም። የእነ ኤልያስ ሶፋ አሮጌ ቢሆንም ደስ ይላል። የቤታቸው መስኩት መስታወት አለው። እቤታችን የነበሩት መስታወቶች ጥቂት ብርጭቆዎችና አንድ የፊት መመልከቻዎች ናቸው። በተጨማሪ እንጀራ እናቴ የመስታወት ማንኪያ ነበራት። ከየት እንዳገኘችው አላውቅም። ደሐ መሆን በሶሻሊዝም ይሁን በካፒታሊዝም መጥፎ ነው። ሁለት አሮጌ መፅሐፍቶች ጠረጴዛ ላይ ወረወረልኝ። የጠረጴዛው ጠለል ደሞ ለስላሳ ነበር......እና መፅሐፍቶች እላዩ ላይ ሲወድቁ እንግዲህ ኤልያስ ከእኔ ራቅ አድርጐ ነበር የወረወራቸው ታዲያ እየተንሸራተቱ አጠገቤ ድረስ መጡ......በትንሹ ሽክርክር እያሉ......ተደራርበው......እንደተቃቀፉ ፍጡራን።

የአንደኛው መፅሐፍ አርዕስት 'አማኑኤል ደርሶ መልስ' ነበር.....የሁለተኛው መፅሐፍ አርዕስት 'ብር አምባር ሰበረልዎ' የሚል ነበር።

"ብር አምባር ታውቃለህ?" ጠየቀኝ ኤልያስ።

"የእጅ ጌጥ ነው አይደለም?"

"ሌላ አታውቅም......?"

"የሠርግ ዘፈን ይዘፈንበታል......ብር አምባር ሰበረልዎ ብር አምባር ሰበረልዎ

አሆሆ ሺጋው ልጅዎ......እየተባለ......»

"አላወቅኸውም" አለ እየሳቀ።

"እና ምንድን ነው? "



@BOOKALEM

"ያቺ ሴት ትዝ ትልሃለች እ......እሷ ብር አምባርህን ልትሰብር ነበር"

ምን የሚሰበር አለኝ? ግራ ገብቶኝ ሳየው፣

"መጀመር" ማለት መሰበር ማለት ነው" አለኝ::

ድዴን ገሸለጥኩ::

"አንብበህ መልሳቸው፣ እንዳትሸጠው ደሞ ጠጅ አማረኝ ብለህ"

"ምነው እባክህ"

"ስቀልድ ነው"

"ሽጠሃል አንተ?"

"በል እንውጣ"

ቀን ስንዞር ዋልን:: ሲደክመን ዛፍ ስር ተኮልተን ስናወራ እሱም ሲሰለቸን ሻይ ቤት ሙዚቃ ስንሰማ:: ኤልያስ ሥራ መያዝ እንደሚፈልግ ይናገራል:: ተሰላችቷል:: እንዳይበሳጭ ብለው ለማባበያ ከቤተሰቦቹ የሚሰጠውን ገንዘብ ተያይዘን እናጠፋለን:: ብዙ ጊዜ ብቻችንን ነበርን:: በጣም ሲጠፋ ገንዘብ እንደያዘ አውቃለሁ:: ወይም ወረቀት ላምጣ ብሎ ምክንያት ፈጥሮ ዋናው ከተማ ይሔድና ሁለት ሳምንቶች ቆይቶ ይመጣል:: "ብዙ ጊዜ አብረን መታየት የለብንም" ያለኝን ነገር እራሱ ደጋግሞ ያፈርሰዋል::

እኔ በብርሐኑ ፍቅር ልሞት ነበር:: "ብር አምባር ሰበረልዎ" የተሰኘው መፅሐፍ ደስ ብሎኝ ደግሜ ደግሜ አነባለሁ:: ሌሎች መጻሕፍትን ለማንበብ ኤልያስን ስፈልገው ስለማላገኘው እበሸቃለሁ:: ቤቱ ውስጥ ያለ ፈቃድ መግባት ሁሉ ፈለግሁ:: ፍቅር ምን እንደሆነም፣ ሴቶች ምን እንደሆኑም በትንሹ እየተረዳሁ ነበር:: ደስ የሚል ነገር መሆኑን መጠርጠር ችያለሁ፣ አንዳንዴ በትንሹ በፍርሓትም ቢሆን ከዚያች ቀይ ወፍራም ሴት መሸሺ ይቆጩኛል:: አንዳንዴ ተቀምጩ አስባታለሁ:: ብቻዬን መሔድም አስባለሁ:: ኤልያስንም እሷንም አፍራለሁ:: 'ቆጩህ እንዴ' የሚሉኝ እየመሰለኝ::

አንድ ማታ በሕልሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ራቁቷን የቆመች ሴት አየሁ:: ራቁቷን:: መጀመሪያ ወሰንን ትመስል ነበር ግን አተኩሬ ሳያት ዕሽም የተሰራች ትልቅ ሴት ናት:: ልትስመኝ አፏን አሞጥሙጣ ስትቀርበኝ እንጀራ እሁቴ ሆና አገኘሁዋት ባንኜ ተነሳሁ:: ከስመአብ እያልኩ::

የብርሐኑ ዘሪሁን ወሰን የሌለው ስጦታ:: ቢያደናብረኝም:: ጠዋት ከመንጋቱ ብርድ ልብሴን ተከናንቤ የጠዋት ፀሐይ መፅሐፌ ገፅ ላይ እያበራ አነባለሁ:: የምመኘው ኤልያስ ከዞደበት ተመልሶ እንዲመጣ ነበር::



@BOOKALEM

ብሬ አስማተኛ ናት። ፅጌሬዳ በሌላ ስምም ቢሆን መዓዛውን ውበቱን አይለውጥም ትላለች ብርሐኑ።

መዝገቡ መዝገቡ ነው እንደማለት ነበር።



@BOOKALEM

# ጨረቃ ስትወጣ፡ ስድብና ፌዝ

"የእኛ ምሁር!"

"አንተ ጉረኛ"

"ዱርዬ ከመቼ ወዲህ ነው ቁም ነገረኛ የሆነው"

"ወገኛ"

"ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ"*

"ሲያደርጉ ታይቶ"

"ማንበቢያ ቦታ ጠፋ?"

"ቁም ነገረኛ መኩኑ ነው?"

"መጀመሪያ ልብስህን እጠብ"*

"ተመራማሪው!"

"ትልቅ ሰው!"

"የኩሌጅ ተማሪ!"

"ኡኡቴ አናውቀውም እንዴ!"*

"ከተማውን ማን ይጠብቅልን"*

"እርፈህ ጠጅ አትጠጣም?"*

"ኩስታራው!"

"አይ ልብ"*

"አዋቂው"

"ሊቀ ሊቃውንት"

"አማረብኝ መስሎታል"

"ምሁር"

"ሥራ ጠፋ እንዴ?" *

"ወሰንስ?" *



@BOOKALEM

"የወንዙ ሰይጣን ብቻውን ነው"

"ፓስቴውን ማን ይብላው"

"አደግሽ እንዴ?"

ተረሳኝ እንጂ ያልተባልኩት ነገር አልነበረም። ይረሳል። ብዙ ነገር ይረሳል። በተለይ አቅም ከሌለን ብዙ ነገሮች እንረሳለን። ካልረሳን እናብዳለን። ካበድን 'ዕብድ' ተብለን ልንሰደብ ነው ደሞ። ጤንነት ያምራል። ጤንነት ይሻላል። ስድቦቹ ግን ብዙ ነገር አስተማሩኝ። ስድቡቹ በመሰለል ላይ እንዳለሁ ሁሉ ነገሩኝ። ከዘረዘርኳቸው ስድቦች (*) ይኼ ምልክት ያለባቸው ሆድ ሲያውቅ ደሮ ማታ፣ መጀመሪያ ልብስህን አጠብ፣ ኡኡቴ አናውቃትም እንዴ፣ አርፈህ ጢጅ አትጠጣም፣ አይ ልብ፣ ሥራ ጠፋ እንዴ፣ ወሰንስ?፣ የተሰኙ ስድቦች ያውቁኛል ብዬ ባልጠበኳቸው ሰዎች መደረጋቸው በመሰለል ላይ እንደሆንኩ ጠቆሙኝ። ልብሴ ቆም ነገር ሆኖ በሰዎች የሚታይ አይመስለኝም ነበር። ጠጅ መጠጣቴን ማን ነገራቸው? የሚያውቁት ጥቂት ሰዎች ነበሩ። እነሱ እርስ በእርስ እየተማሙ ቢጠላሉም ሌላ ለማማት ይገናኛሉ ማለት ነበር? እንዲህ እየተንገላታሁ መሸፈትና ጥሩ አድርጌ መሳደብ አለመቻሌ ፍርሃት እንዳለብኝ ያሳያል ማለት ነበር? አለነገር ልቤን አልተቹትም፣ ስለ ወሰን እንዴት እንዳወቁ ግን እጅግ ገርሞኛል። ወሰን አውርታ ይሆን? አጥላልታኝ አወራች ወይስ አዋዳ......አዋዳ አታወራኝም። ስለእሷ መነሳቱ ሠላም ነሳኝ። ከዚያ ሥራ ጠፋ እንዴ? ይሉኛል። ምን ይሠራል? ምን ልሥራ......የምወደውን ምን ነገር ልሥራ? ምን ይሠራል? ስጡኝ! አልኩ በልቤ። ስጡኝ......የሚሰራ ስጡኝ። ብርሐኑ ዘሪሁንን ማንበብ ሥራ አይደለም? ሌላ ጊዜ ደ'ሞ 'እከሌ ጎበዝ ተማሪ ነው! ጥሩ ያነባል!' ብለው ሲያደንቁ እሰማለሁ። እያደነቁም፣ ያደንቃሉ። ተዘባረቀብኝ። በሌላ በኩል ደ'ሞ ይንቁኛል፣ የማያስፈልግ ተራ ልጅ፣ የማይታይ፣ ዐይን የማይገባ ያደርጉኝና ዞር ብለው ደስ የሚለኝን ነገር እንዳላደርግ ያቆሙኛል። ይሰድቡኛል። ታዲያ ከሰደቡኝ......ይሰልሉኛል፣ ያዩኛል፣ ይከታተሉኛል ማለት ነው። ሁሉ ያቅሙን ጀሮ አጋሚ ነበር። እንጢቆ ዙፋን ትቶን የሄደው ለዚህ ይሆናል። የትኛው ነኝ እኔ? ሁለቱን መሆን እችላለሁ?

ከእኔ ምንድን ይፈልጋሉ?

ምንድነው ትፈልጉት የነበረው?

እየቆየማ የብርሐኑ ዘርይሁንን መፅሐፍቶች ፈራሁዋቸው። አንድ ቀን የብርሐኑን ፎቶ ግራፍ ሳይ ከተማው መሐል ቡና ቤት ያላቸውን ረዥሙን አቶ ሳላን መሰለኝ። አቶ ሳላ ብርሐኑን መሰሉኝ። ብርሐኑ ባለ ቡና ቤት መሰለኝ። መፅሐፉን የፃፈው ወደ ሌላ ከተማ ለመሻገር ሲመሽባቸው እሱ ሆቴል ያደሩ ፍቅረኛሞችን ታሪክ ትንሽ ለዋውጦ መሰለኝ። ብርሐኑን እንደቡና ቤቱ ባለቤት እንደ ሳላ ፈራሁት። ፎቶውን ሳይ ሳይ ሳይ ብርሐኑን



@BOOKALEM

ከመነፅሩ ፈራሁት:: እኔን ሳነብ ቢያዩኝ እንደ ቡና ቤቱ ባለቤት እንደ ሳላ "ኩሊጅ ገባህ እንዴ?" የሚል መሰለኝ:: እቤቴም የአባቴ ጥቁርና ነጭ ፎቶ ግራፍ ነበር ልክ እንደ ብርሐኑ የተነሳው ግን ያለ መነፅር:: መፅሐፉን ትራሴ ስር ደበቅሁት:: መፅሐፉን ፈራሁት:: አንዳንዴ ልቤ ተከፍሎ ለማንበብ ሳወጣው የመፅሐፉ ሰማያዊ የሽፋን ቀለም እንደ ውሓ ወደ መሬት የሚከነበል ይመስለኝ ነበር:: ገፆቹ ላይ የሰፈሩት ፊደላት ከወረቀቱ ላይ እየለቀቁ በእጆቼ ላይ እንደጉንዳን እየተጓዙ ገላዬን ወረው የሚነካክሱኝ......በተለይ 'ጨ' የምትባለዋ ፊደል 'ጨረቃ' የተፃፈችበት......ንክስ ንክስክስ ንክስክስክስ የምታደርገኝ መሰለኝ:: ለእኔ የማይገባ ያልተፈቀደልኝ ነገር እንደማደርግ ተሰማኝ:: ከዚያ አቆምኩ:: ማንበብ አቆምኩ:: የሚያዩኝ፣ ያዩኝ ግን በመርዘኛ ነገራቸው ነክሰው......አለቀቁኝም::

"ድሮውንስ?"

"ወግ ነው ብለን የለ?"

"ዱርዬ ቁም ነገር መች ይችላል"

"ሲያደርጉ ዐይቶ"

"ያላደገበትን"

"ወስላታ እኮ አይሆንለትም"

በወግት ገደሉኝ::

ሰው ከመቀበሩ በፊት እንዲህ ነፍሱ ትፈለፈል ይሆን እንዴ......በአሸሙር? አንዳንዴ ብርሃኑን እንደገና ማንበብ ይናፍቀኛል:: ወይም ሌላ ነገር ማንበብ:: እቤቴም፣ ቤቴ ውጭም ስለማላገኝ ግን ተውኩት:: ውስጤ ሞኝ አይደለምና ግን ብዙ ነገሮችን አወጣና አወርዳለሁ:: ለምሳሌ እናቴ በሕይወት ብትኖር ደስ እንደሚለኝ:: ደስ ይለኝ ነበር:: እናቴ ማርያም ጆርባ ከገደሉ ከፍ ብሎ ነው አሉ የተቀበረችው:: መቃብሯን አይቸው አላውቅም:: መቃብር ይታያል:: ማየት ግን እመኛለሁ:: በመቃብሩ ሥፍራ ሣልፍ ግን እርበተበታለሁ:: ገላዬን ይወብቀኛል፣ ያልበኛል:: ራሴ ያሳዝነኛል:: የሚገርመው የእሷ መቃብር ቦታ እየቆየ ይምታታብኝ ጀመር:: ሁሉ ጉብታ የእሷ ይመስለኛል:: ከቅርቦቹ ሙታን በስተቀር የከረሙት በአረንጓዴ ሣር፣ በእንቧይ፣ በአረግ ሬሳና በእጠ ፋርስ ተሸፍነዋል፤ ሳር ለብሰዋል:: ለዘለዓለም 'ም ተከደነች ይመስለኛል::

ከሞተችበት ተነስታ እኔና ወሰንን ግራና ቀኝ ይዛ ጉናን ቀደን እልፌን......ቀይ ባሕር ላላ ነበረ ጆርባ ላይ ሰንቁ ጎዝጉዛ የምትድረን ይመስለኝ ነበር:: ወሰን ሁለመናዋ በወርቅ ተሸፍኖ:: ከንፋስ መውጪያ እንቅፋቶች ያዩናል:: አቤት ቅናታቸው! አቤት ጠላትነታቸው! በጅቡቲ በኩል በየሉስ ጆርባ ላይ እኔና ወሰን እጅ ለእጅ ተያይዘን:: ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ውሐ



@BOOKALEM

ጠጥተን። አባይ ሐይቅ በሚያምር ጀልባ ተንሸራሽረን በጅማ ቡና እስከ በረካ ተቀምጠን፣ አዲስ አባን አስደንቀን። ንፋስ መውጪያ ያየናል። ንፋስ መውጪያ ይቀናል። ይቀናሉ። አቤት ሲቀኑ።

ከዚያን ሰሞን ጀምሬ ግን መፅሐፍ የሚባል ገልጬ ማየት አቆምኩ። እንደለመዱኝ ሆንኩላቸው። ግልብጥ ስድባቸውን ትንሽ ቀን ጠጣሁና ፈዛዛ ኑሮዬን መኖር፣ በሐሳቤ ከወሰን መዳርና መፋታቴን ቀጠልኩ። ሳይሻለኝ ይቀራል?



@BOOKALEM

# ስለ ሽሮ፣ ስለ ጓንትና ስለ እንጀራ

ብዙ ጊዜ የሚስማሙ ሰዎችና ጉዳዮች ሲገለፁ ወይም ሲብራሩ፡—"እጅና ጓንት ሆኑ" ይባላል። ይሔ አባባል ግን ይገርመኛል። የሚገርመኝ "ለምንድን?" ነው ተብሎ ቢጠየቅ 'ጓንት' የሚባል ነገር አይቼ ስለማላውቅ ነበር። 'ጓንት' ማለት ፈረንጅኛ እንደሆነ ይገባኛል። ጣሊያንኛ፣ እንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሩሲያኛ፣ አረብኛ ይሁን ግን አላውቅም። ጓንት ለብርድ መከላከያ ፈረንጆች እጆቻቸው ላይ የሚያጠልቁት ልብስ ነገር እንደሆነ ትምህርት ቤት ተነግሮኛል። ውርጭ የሰፈነበት ጉና ተራራ ላይ እንኳን ጓንት የሚያደርጉ ገበሬዎች እስከዚያን ጊዜ ድረስ አላየሁም። እጅና ጓንት ሲባል ታዲያ ዘይቤው ይገርመኛል......

ምን አልባት እኔ ብጠየቅ......ማለቴ በድርጊት የሚስማሙ ግን የተለያዩ ሁለት ነገሮችን "እንዴት በአባባል ትገልፃቸዋለህ?" ተብዬ እኔ ብጠየቅ፡ አትፍራ ተብሎ ተነግሮኝ ሳልፈራ፣ ሳልግደረደር 'እንጀራና ሽሮ' የተሰኙትን ቃላት እጠቀማለሁ። እንጀራውም ሽሮውም ኢትዮጵያ ውስጥ አለ። ለምሳሌ "የምርጥ መኩንኖች መንግስትና የባንዶች እጅና ጓንት መሆን" የሚለውን ሀረፍተ ነገር እንደ እኔ "የምርጥ መኩንኖች መንግስትና የባንዶች እንጀራና ሽሮ መሆን" በሚል እለውጠው ነበር። ለዚህ አባባል መስራትና ቶሎ ተቀባይነት ማግኘት መቻል ብዙ ማስረጃዎች ማቅረብ እችላለሁ።

በፀሎቱ እንኳን "የዕለት እንጀራችንን ስጠን" ሲባል ነው የምሰማው ("የዕለት ጓንቲያችንን" መችም አይባል)። እንጀራ በተለያየ መልኩ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ ጤፍ፣ ዘንጋዳ፣ ስንዴ ወዘተ። ጤፍ የማያገኝ ስንዴ፣ ስንዴ የማያገኝ ዘንጋዳ ብቻ እንጀራ የትም ናት። ታዲያ እንጀራ ብዙ ጊዜ ብቻዋን አትበላም። ማባያ ያስፈልጋታል። ታዲያ አገራችንን ወጦች ቢሞሏትም እንደ ሽሮ ወጥ ግን ሁሉ ቦታ የሚገኝ ያለ አይመስለኝም።

ሌሎች ዐይነት ወጦች (ዶሮ፣ ምንቸት አብሽ ፣ የጥብስ ወጥ ወዘተ) ቢኖሩም የሚገኙበት ቦታ ጥቂት ነው። በዋና ጠባያቸውም በዓል ጠብቀው የሚመጡ ናቸው። የእነዚህ ወጥ በላተኞች ሳይሆኑ አይቀሩም "ወጥና ወንድም ማስፈራሪያ ነው" ብለው የተረቱት_ውድ ወጣቸው እንዳያልቅ። በዚህ ምሳሌ አባባል የመበላት ዕድሉ በአብዛኛው ወደ እንጀራ ይሆንና የእንጀራን አምባገነንነት ሁለገብ ያደርገዋል። ተረቱ ግን ለሽሮ ወጥ አይሰራም። የማይረባ ሽሮ ማስፈራሪያ አይሆንም......ቢያንስ ብዙዎቻችን ለለመድናቸው የሽሮ ዐይነቶች።

እሲ ለእኔ ያስለመደችኝ የሽሮ ወጥ ዐይነቶች ሦስት ነበሩ።

1) ቀጭን መላጣ ሽሮ
2) ወፍራም መላጣ ሽሮ
3) ፍትፍት ሽሮ ናቸው።



@BOOKALEM

መላጣ ሽሮ ማለት ሽንኩርት፣ ቅመም ማራኪ ጠረን የሌለው ማለት ሲሆን ብዙ ጊዜ ይቀጥናል (ቀጭን መላጣ ሽሮ) አንዳንዴ ይወፍራል (ወፍራም መላጣ ሽሮ)። እእ እኔን ከሞናው ከእነሱ ማዕድ ለማራቅ ወይም ጊዜ ካልበቃት ዱቄት ሽሮ ታወጣና እሱን በውሐና በጨው በጥብጣ እንጀራውን ትፈተፍትበትና (ፍትፍት ሽሮ) የተቦካ ነገር ታቀርብልኛለች። ይሔ ሁሉ ተጠራቅሞ ታዲያ የምጠላው ነገር ሽሮ ነበር።

ሽሮ ብቻ ሳይሆን በግም እጠላለሁ።

በጣም የምጠላው ግን ሽሮ ነበር።

እእ እንጀራውን ግፋ ላይ እንደ አንሶላ ታነጥፈውና......በእንጀራው ዐይኖች ወጡ እንዲገባ ነው መሰለኝ ቀጭን መላጣ ሽሮ አፍሳበት ትመጣለች። አንዳንዴ ዘግይቼ ማታ እቤቴ ከገባሁ ይሄ ወጥ ከእንጀራው ላይ ደርቆ አንፎርጎ ወንዝ ዳር አንዳንዴ የማየውን ስስ የድቡሽት ቂጣ ይመስላል።

ይኼንን ሽሮ ስበላው ታዲያ ሌላ ሌላ ነገር እያሰብኩ ነበር። ስለመሞት እያሰብኩ ነበር። ተሰባብሮ ምንገድ ዳር ስለመውደቅ እያሰብኩ ነበር። ስለመደምሰስ እያሰብኩ ነበር። ሁልጊዜ ታዲያ ይሔ ሽሮ ከእንጀራ ጋር ነበር የሚመጣው።

በፖለቲካ ውስጥ ታዲያ "ኢምፔሪያሊዝምና ተገንጣዮች እንጀራና መላጣ ሽሮ ሆነው" ተብሎ ለምን እንደማይገለጥ አይገባኝም ነበር። ኤልያስን ልጠይቀው ሁሉ ሀሳብ ነበረኝ። ምን አልባት የምቀልድ ይመስለዋል። ኤልያስ ፖለቲካ ይወዳል ያውቅ ነበርም መሰለኝ። እኔ ደሞ ምን እንደምወድ አላውቅም። ምን አልባት ጊንት ኢትዮጵያ ውስጥ ባይደረግም ጥሩ ነገር ሳይሆን አይቀርም እል ነበር።

ፖለቲከኞች ደሞ አገራቸውን ስለሚያፈቅሩ በመላጣ ሽሮ ምሳሌ በመስጠት ዓላማቸውን ትንሽ አድርገው ማሳየት አይወዱ ይሆናል። ምናልባት ሶሻሊዝምና ሕዝቡ ሲያሸንፉ ለእያንዳንዳችን የሚሞቅ ጊንቲ ይታደለን ይሆናል። ምናልባት ወደፊት ፖለቲከኞች ለሕዝብ ሽሮ ሲያድሉ የሽሮው አቀማመም አፈር ስለሚበዛው ጣቶቻችን እንዳይቆሽሹ የምንዘላበት ጊንት ለእያንዳንዳችን ይታደለን ይሆናል። . ኢምፔሪያሊዝም፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና፣ ፊውዳሊዝምን እናወድማለን ከሚሉ ቀጭን መላጣ ሽሮን፣ ወፍራም መላጣ ሽሮንና ፍትፍት ሽሮን ከምድረ ገፅ እናጠፋለን ቢሉ የፈለጉትን አደርግላቸው ነበር።

እና ኢጋሮቻቸውን......



@BOOKALEM

# የወንዝ ጉዞ

ጉብታዬ ከፈረሰች በሁዋላ ስፈልግ ወናው ቤት፣ አለበለዚያ ወንዝ እወርዳለሁ:: ወደ ወንዝ የምወርደው የዋና ፍቅር ይዞኝ ሳይሆን ብዙ ራቁታቸውን የሚታጠቡ ሴቶች ስለማይ ነበር:: ገለል ያለ ኮካ መሬት መርጬ እቀመጥና አያለሁ:: በሕሊናዬ ብርሐኑ ዘርይሁን እንደዚህ ዐይነት ሴቶች ከአየ በሁዋላ ይሆን 'ጨረቃ ስትወጣ'ን የጻፈው? እላለሁ:: የብዙዎቹ ሴቶች ጡቶች ትላልቆች ናቸው:: መጽሃፏ ውስጥ *'ጨረቃንም ባልስጥሽ እስተዚህም ድረስ ኦሮአችን መጥፎ አይሆንም'* ብሎ በቀለ የሚናገርላቸው እነዚህ ጡተ ትላልቆች ለመታጠብ አያፍሩም፤ ጡቶቻቸውን ሳሙና ተቀብተው ግራና ቀኝ እያወናጨፉ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው በፀሐይ እየተንቃቁ (ጋኔንም አይፈሩ?):: ልጃገረዶቹም ይታጠባሉ:: ልጃገረዶቹ ሚስጢር ሚስጢር ቦታ ፈልገው ይታጠቡ ነበር:: መሬት ውስጥ መግባት እስኪቀራቸው:: እኔ እናደዳለሁ:: በጨረፍታ የልጃገረዶቹን ጠንቃቃነት አምልጦ የሚታይ የጡት ስር፣ የጡት ጫፍ፣ ሆድ፣ ሽንጥ፣ ጀርባ በሕሊናዬ እየገጣጠምኩ እራሴን አስገርም ነበር:: 'አለንጋ ሽንጥ' ተብሎ የሚሰየመው የየትኛዋ ልጅ እንደሆነ አላውቅም:: 'ጉልላት' ተብሎ የሚሰየመው ጡት የትኛው እንደሆነ አላውቅም......ጥናቴን አላቆምኩም:: አንዳንድ የማውቃቸው ሴቶች ሲታጠቡ በአልባሌ ጨርቅ የተሸፈነ ገላቸው ብቅ ብሎ ውበታቸውን ሳይ: "ሽሮና እሹቅ እንዲህ ያደርጋል?" ብዬ ራሴን እጠይቀዋለሁ:: ወጠጤው ወንድነቴ ሰውቀት ያስፈልገው ነበርና ማፍጠጤን አላቆምኩም::

አንዳንዴም በመንገድ በልብስ የተሸፈነ የሴት ደረት ዐይና እዚያ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የጡት ዓይነት፣ የቆዳ ልስላሴ የመሳሰሉ ብልቶችን ውበት በሐሳቤ ልገምት እሞክራለሁ:: አልችልም:: ባለጌ ነኝ? ባለጌ ነበርኩ እንዴ?



@BOOKALEM

## ፈላስፋ ሆንኩ

አንድ ዕለት እንጀራ እናቴ በጠዋት አቡኪታ ያስቀመጠችውን ሊጥ ውሻ ስለደፋባት እውጭ እየተንጎራደደች የኢትዮጵያን ውሾች ጠቅላ ስትራገም አገኘሁዋት።

"ምን ታየኛለህ አንተ ደሞ ከውሻ አትሻልም" አለችኝ።

"ሕይወት ወጣ ገባ ነው" አልኳት።

የሚረሳ አይደለም። ሕይወት ወጣ ገባ ነው። ጉጉ። ፈላስፋ ሆንኩ።

"ምን?" አለች ዞር ብሎባት።

ያዞርባትና የሚያዞር።



@BOOKALEM

# ዋና ከተማው ጠባሳ ይመስላል

ኢልያስ የኪስ ገንዘቡ እንደተሰጠው ዋናውን ከተማ መጎብኘት እኛ እንደሆነ ጠይቆኝ እሺ ብዬው ተያይዘን ሔድን። አውቶቡሱ ውስጥ እኔና ኢልያስ ትርፍ ተሳፋሪዎች ነበርን። ሰዎች እየተጠጋጉ መቀመጫ ቦታ ሰጡን። አውቶብሱ በሲጃራ ጢስ ተሞልቷል። አንዳንድ ተሳፋሪዎች ለአጭር ጊዜ 'ይኼ ግማት ገደለን' ሲሉ ቆዩ። ጭቅጭቅ ስለፈራሁ አላጤስኩም።

......ለአጫጭር ጊዜያት በየመሃሉ ፀጥታ ይሰፍንብን ነበር......

አልፎ አልፎ ጫት የሚቀባበሉ ነበሩ። እኛ አካባቢ ንፋስ መውጪያ ጫት ስለማይበቅል ብዙዎቹ ልማዱን በመብሸቅ ይተቻሉ። በምኖርበት ከተማና በክፍለሐገሩ ከተማ መሐል ያለው ቦታ የማያቋርጥ የገብስ እርሻ አምባ ነው። ሊታጨድ የደረሰ እርሻ ነበር። ገብሱ እንደ ሐር በንፋስ ይርገበገባል። እንደ ክር በሰነሰነ የወርቅ ማግና ድር የተሰራ ሠፌ......- በጣም ሠፊ ምንጣፍ ይመስላል። በየመሐሉ የእህል ማጨጃ ሞተሮችና ሰማያዊ ቱታ የለበሱ ገበሬዎች አያለሁ። ሜዳው የማያልቅ ይመስላል። ከመኪናችን በስተሁዋላ ወደ ሰማይ የሚነሳ አቧራ ያለፍነውን ምንገድ እንዳናየው ይጋርደናል። ፊት ለፊታችን አድማስ ውስጥ የሚጠፋ ቀይ ቀጭን ረዥም የኩርኩንች ምንገድ ነበር።

......ለአጫጭር ጊዜያት በየመሃሉ ፀጥታ ይወሰውሰን ነበር......

አውታንቲው በር ተደግፎ እንደሚያፋዋጭ ሰው አፉን አሞጥሙጧል፤ ግን የፉጨት ድምፅ አይሰማም። የአንገት ልብሱ ቆሻሻ ነበር። ሳያቋርጥ ይናፈጥበታል። የሰውዬው የላይኛዎቹ የፊቱ ሁለት ጥርሶች ወልቀዋል። ዙፋን ትዝ አለኝ። ስለምን የሚያምረው ሰሙ ፊት እንጢቆን ደነቀሩበት? አልኩ ለራሴ። ሰውዬው በማያቋርጥ የመኪናው ዝዝታ ነሁልሎ የታች መንገጭላው ወደ ታች ሲወድቅ በወላቃው መሃል የአውራጣት ሰበከት የመሰለ ምላስ እየተንፏቀቀ መጥቶ ይወተፋል። በዚህ ምክንያት ሳይሆን ይቀራል ጠንቅቴ ወደ ማላውቀው ዓለም የገባሁ የመሰለኝ? መኪናዋ አንድ ጉብታ ላይ ስትወጣ ዝቅ ብሎ በለምለም ተራሮችና ገና አረንጓዴ በሆነ እርሻ የተከበበ፣ ጠፍጣፋ ሜዳ ላይ የሰፈረ ትልቅ ከተማ አየሁ። ከተማው ጠባሳ ይመስል ነበር። መሬት እንደሰው ትታመምና፣ ለምሳሌ እንደመብረቅ እንደ እሳት ያለ ነገር ሃመልማሏ ላይ ወርዶ ወይ ገሞራ ከታች ፈንድቶባት እንዳቃጠላት ዐይነት......ቁስሏም ብዙም ሳይሽር እኔና መሰሎቼ እንደ መጣንበት።

......በየመሃሉ እንደ መልከም መብል ትዝ የሚል ፀጥታ እተቀመጥንበት ይወስውሰኝ ነበር......

ከተማ ስንደርስ ኤልያስ "ሰው እንጠብቅ" ብሎኝ ሻይ ቤት ተያይዘን ገባን:: ተጠባቂው ሰው የሚመጣው ከአንድ ሰዓት በሁዋላ ነበር:: ከዚያ ከተማ መሐል ፅጥታና ጩኸት እየተፈራረቀ ሻይ ቤቷ ውስጥ እንደደፈረሰ የወንዝ ውሐ ይገባል:: አለባበሳቸውና ሁኔታቸው ከእኛ ከተማ አራዶች ብዙም የማይለይ ልጆች ሻይ ቤት ውስጥ እየገቡ ይወጣሉ:: የፓስቲያቸው ጣዕም እስተዚህም ነበር......ውስጡ በደንብ አልበሰለም:: ሲኒዎቻቸው ትናንሾች ናቸው ሻያቸው ቅርንፉድ የለውም:: ከዳቦዎችና ፓስቲዎች ማኀርያ ከመዷና ጀርባ የቆመው ሰው መላጣና ወፍራም ነበር:: የሙስጠፋ አቻ:: ይጮሃል:: ምናልባት እንደ ሙስጠፋ እኩያነቱ፣ እንደ እህቴ ያለች ሴት ወዶ እንደ እኔ ያለ ልጅ ደብዳቤ አስይዞ ልኮ ብዙ ሳይቆይ የተመለሰለትን ደብዳቤ በእጁ ጨምድዶ ይዞ በክርኑ ጀርባ-ቆራጤ ዳቦ ተደግፎ ሲያለቅስ በሕሊናዬ አውጠነጠንኩ:: ሰውዬው ይጮሃል:: ከመሐል ያ ጩኸቱ እንዳረካው ወይም እንዳደከመው ሁሉ ባንኮኒ ተደግፎ መሬት መሬት እያየ ትልልቅ ዐይኖቹን ያጉረጠርጣል::

ለኤልያስ ስለ አነበብኩዋቸው መጻሕፍቶች አወራሁትና ሌላ የማነበው እንደምፈልግ ነገርኩት::

"ቀላል ነው:: ከሠራተኞችን ጋር አስተዋውቅህና በፈለከው ጊዜ እየሄድክ ትወስዳለህ" አለኝ::

"በጣም ድንቅ ነው" አልኩ በመቁነጥነጥ::

"ያ ልጅ የሚመጣ አልመሰለኝም:: እኔ የምሔድበት ስላለኝ ደርሼ እስክመለስ ዞር ዞር እያልክ ጠብቀኝ:: ከሁለት ሰዓቶች በሁዋላ እመጣለሁ:: የምናድርበት ቦታ ሁሉ አዘጋጅቼ እመጣለሁ:: አንተ ዞር ዞር እያልክ ጠብቀኝ.....ከተማው የሚደብት ይመስላል? መጠጣት የምትፈልግ ከሆነ ሦስት ብር ይበቃሃል እ? ከፈለግህ ሲጃራ እዚህ ሻይ ቤት አለልህ ከጠጣ ከዚህ ፊት ለፊት አንድ ኩሮኩንች ምንገድ አለ 'የደጋ ንብ ጠጅ ቤት' የሚባል ጥሩ ነው እዚያ.....ምናልባት እዚያ እመጣለሁ"

ስዞር ቆየሁ:: ከተማው ሰው ይበዛበታል.....የኢህአፓ መፈክር ይበዛዋል:: በየጎዳናው ዳር ያሉ የቆርቆሮ አጥር በሮች፣ የሲሚንቶ ግድግዳዎች በቀይ ቀለም ተንበግቡገዋል:: እዚያ ዓይነት አካባቢ ወዲያ ወዲህ እያልኩ ስራመድ ከተማው ውስጥ ካሉት ልክ እንደ እኔ ከማሉ ጉብሎች ጋር በማይታይ ሚስጢራዊ ሽርክና ውስጥ እንዳለሁ ሳውቅ ደስ አለኝ:: ከማይታይ ከማያየኝ ግን ከሚያፈቅረኝ ብዙ ሕዝብ ጋር ነኝ አልኩ:: ከተማው ፈረስ በቅሎ ይበዛዋል፣ መኪና ይበዛዋል፣ አቧራ፣ ድንጋይና ቆሻሻ ይበዛዋል:: ትልቅ ነፋስ መውጫ ነበረች:: ሻይ ቤቱ



@BOOKALEM

# ዋና ከተማው ጠባሳ ይመስላል

ኤልያስ የኪስ ገንዘቡ እንደተሰጠው ዋናውን ከተማ መጎብኘት እሻ እንደሆነ ጠይቆኝ እሺ ብዬው ተያይዘን ሔድን:: አውቶቡሱ ውስጥ እኔና ኤልያስ ትርፍ ተሳፋሪዎች ነበርን:: ሰዎች እየተጠጋጉ መቀመጫ ቦታ ሰጡን:: አውቶብሱ በሲጃራ ጢስ ተሞልቷል:: አንዳንድ ተሳፋሪዎች ለአጭር ጊዜ 'ይኼ ግማት ገደለን' ሲሉ ቆዩ:: ጭቅጭቅ ስለፈራሁ አላጤስኩም::

......ለአጫጭር ጊዜያት በየመሃሉ ፀጥታ ይሰፍንብን ነበር......

አልፎ አልፎ ጫት የሚቀባበሉ ነበሩ:: እኛ አካባቢ ንፋስ መውጪያ ጫት ስለማይበቅል ብዙዎቹ ልማዱን በመብሸቅ ይተቻሉ:: በምኖርበት ከተማና በክፍለሐገሩ ከተማ መሐል ያለው ቦታ የማያቋርጥ የገብስ እርሻ አምባ ነው:: ሊታጨድ የደረሰ እርሻ ነበር:: ገብሱ እንደ ሐር በንፋስ ይርገበገባል:: እንደ ክር በሰነሰነ የወርቅ ማግና ድር የተሰራ ሡፌ......- በጣም ሡፌ ምንጣፍ ይመስላል:: በየመሐሉ የእህል ማጨጃ ሞተሮችና ሰማያዊ ቱታ የለበሱ ገበሬዎች አያለሁ:: ሜዳው የማያልቅ ይመስላል:: ከመኪናችን በስተሁዋላ ወደ ሰማይ የሚነሳ አቧራ ያለፍነውን ምንገድ እንዳናየው ይጋርደናል:: ፊት ለፊታችን አድማስ ውስጥ የሚጠፋ ቀይ ቀጭን ረዥም የኩርኩንች ምንገድ ነበር::

......ለአጫጭር ጊዜያት በየመሃሉ ፀጥታ ይወሰውሰን ነበር......

አውታንቲው በር ተደግፎ እንደሚያፋዋጭ ሰው አፉን አሞጥሙጧል፣ ግን የፉጨት ድምፅ አይሰማም:: የአንገት ልብሱ ቆሻሻ ነበር:: ሳያቋርጥ ይናፈጥበታል:: የሰውዬው የላይኛዎቹ የፊቱ ሁለት ጥርሶች ወልቀዋል:: ዘፋን ትዝ አለኝ:: ስለምን የሚያምረው ሰሙ ፊት እንጢቆን ደነቀሩበት? አልኩ ለራሴ:: ሰውዬው በማያቋርጥ የመኪናው ዝዝታ ነሁልሎ የታች መንገጭላው ወደ ታች ሲወድቅ በወላቃው መሃል የአውራጣት ሰበከት የመሰለ ምላስ እየተንፏቀቀ መጥቶ ይወተፋል:: በዚህ ምክንያት ሳይሆን ይቀራል ጠንቅቄ ወደ ማላውቀው ዓለም የገባሁ የመሰለኝ? መኪናዋ አንድ ጉብታ ላይ ስትወጣ ዝቅ ብሎ በለምለም ተራሮችና ዥ አረንጓዴ በሆነ እርሻ የተከበበ፣ ጠፍጣፋ ሜዳ ላይ የሰፈረ ትልቅ ከተማ አየሁ:: ከተማው ጠባሳ ይመስል ነበር:: መሬት እንደሰው ትታመምና፣ ለምሳሌ እንደመብረቅ እንደ እሳት ያለ ነገር ሃመልማሏ ላይ ወርዶ ወይ ገሞራ ከታች ፈንድቶባት እንዳቃጠላት ዐይነት......ቁስሏም ብዙም ሳይሽር እኔና መሰሎቼ እንደ መጣንበት::

......በየመሃሉ እንደ መልካም መብል ትዝ የሚል ፀጥታ እተቀመጥንበት ይወሰውሰኝ ነበር......



@BOOKALEM

ከተማ ስንደርስ ኤልያስ "ሰው እንጠብቅ" ብሎኝ ሻይ ቤት ተያይዘን ገባን:: ተጠባቂው ሰው የሚመጣው ከአንድ ሰዓት በሁዋላ ነበር:: ከዚያ ከተማ መሐል ፀጥታና ጬኸት እየተፈራረቀ ሻይ ቤቷ ውስጥ እንደደፈረሰ የወንዝ ውሐ ይገባል:: አለባበሳቸውና ሁኔታቸው ከእኛ ከተማ አራዶች ብዙም የማይለይ ልጆች ሻይ ቤት ውስጥ እየገቡ ይወጣሉ:: የፓስቲያቸው ጣዕም እስተዚህም ነበር......ውስጡ በደንብ አልበሰለም:: ሲኒዎቻቸው ትናንሾች ናቸው ሻያቸው ቅርንፉድ የለውም:: ከዳቦዎችና ፓስቲዎች ማሳያ ከመደዳ ጀርባ የቆመው ሰው መላጣና ወፍራም ነበር:: የሙስጠፋ አቻ:: ይጮሃል:: ምናልባት እንደ ሙስጠፋ እኩያነቱ፣ እንደ እህቴ ያለች ሴት ወዶ እንደ እኔ ያለ ልጅ ደብዳቤ አስይዞ ልኮ ብዙ ሳይቆይ የተመለሰለትን ደብዳቤ በእጁ ጨምድዶ ይዞ በክርኑ ጀርባ-ቆራጤ ዳቦ ተደግፎ ሲያለቅስ በሕሊናዬ አውጠነጠንኩ:: ሰውዬው ይጮሃል:: ከመሐል ያ ጬኸቱ እንዳረካው ወይም እንዳደከመው ሁሉ ባንኮኒ ተደግፎ መሬት መሬት እያየ ትልልቅ ዐይኖቹን ያጉረጠርጣል::

ለኤልያስ ስለ አነበብኩዋቸው መጻሕፍቶች አወራሁትና ሌላ የማነበው እንደምፈልግ ነገርኩት::

"ቀላል ነው:: ከሠራተኞችን ጋር አስተዋውቅህና በፈለከው ጊዜ እየሄድክ ትወስዳለህ" አለኝ::

"በጣም ድንቅ ነው" አልኩ በመቁነጥነጥ::

"ያ ልጅ የሚመጣ አልመሰለኝም:: እኔ የምሔድበት ስላለኝ ደርሼ እስክመለስ ዞር ዞር እያልክ ጠብቀኝ:: ከሁለት ሰዓቶች በሁዋላ እመጣለሁ:: የምናድርበት ቦታ ሁሉ አዘጋጅቼ እመጣለሁ:: አንተ ዞር ዞር እያልክ ጠብቀኝ.....ከተማው የሚደብት ይመስላል? መጠጣት የምትፈልግ ከሆነ ሦስት ብር ይበቃሃል እ? ከፈለግህ ሲጃራ እዚህ ሻይ ቤት አለልህ ከጠግህ ከዚህ ፊት ለፊት አንድ ኩርኩንች ምንገድ አለ 'የደጋ ንብ ጠጅ ቤት' የሚባል ጥሩ ነው እዚያ.....ምናልባት እዚያ እመጣለሁ"

ስዞር ቆየሁ:: ከተማው ሰው ይበዛበታል.....የኢህአፓ መፈክር ይበዛዋል:: በየጎዳናው ዳር ያሉ የቆርቆሮ አጥር በሮች፣ የሲሚንቶ ግድግዳዎች በቀይ ቀለም ተንቦግቡገዋል:: እዚያ ዓይነት አካባቢ ወዲያ ወዲህ እያልኩ ስራመድ ከተማው ውስጥ ካሉት ልክ እንደ እኔ ከመሰሉ ጉብሎች ጋር በማይታይ ሚስጢራዊ ሽርክና ውስጥ እንዳለሁ ሳውቅ ደስ አለኝ:: ከማይታይ ከማያየኝ ግን ከሚያፈቅረኝ ብዙ ሕዝብ ጋር ነኝ አልኩ:: ከተማው ፈረስ በቅሎ ይበዛዋል፣ መኪና ይበዛዋል፣ አቧራ፣ ድንጋይና ቆሻሻ ይበዛዋል:: ትልቅ ነፋስ መውጫ ነበረች:: ሻይ ቤቱ



@BOOKALEM

ሲሰለቸኝ ጠጅ ቤት ገብሁና ሁለት ሰዓቶች ያህል ቆይቼ ሞቅ፣ ራብ ብሎኝ ወጣሁ። የኤልያስ ዳና ጠፍቷል።

*(ሀ) የጎርኪ «እናት»*

የኤልያስ ዱካ ጠፍቷል። አንድ መፅሐፍ የሚሸጥበት ሱቅ ልብወለዶች ለመመልከት ገባሁ። መፅሐፍት ቤቱ ባለ አንድ ትልቅ ክፍል ነበር። ወለሉ ሲሚንቶ ሲሆን አልፎ አልፎ ተሰነጣጥቆአል። ሦስቱን ግድግዳዎች መፃሕፍት መደርደሪያዎች ተደግፈውታል። የቀረው አንደኛው ግድግዳ በስፋት ተሸንቁሮ ነጭ ቀለም የተቀባ በር ተተክሎበታል። በሩ አጠገብ ተቀምጦ ቀና ብሎም ሰው የማያይ ሻጭ አለ። ሸበት ጣል ጣል ያደረገበት ጠይም ሰው ነበር። ሲያነብ ትላልቅ ከንፈሮቹ በዝምታ ይንቀሳቀሳሉ። ከእሱ ጀርባ አንድ ሰው ሊሸከማቸው የማይችል ወፋፍራም መፃሕፍት ተደርድረዋል። ወደ መፅሐፍት ቤቱ የሚገቡት ሰዎች፦

"ሠላም ንጉሤ!" ይሉታል።

ብዙዎቹ እዛ ያየሁዋቸው እንደ ጊዜው ፀባይ የፖለቲካ (ያውም በእንግሊዝኛ የተፃፉ) መፃሕፍት ነበሩ። የመፃሕፍቶቹ ሽፋን የመሳጣና የጢማም ፎቶ ይበዛቸዋል። ከመሃል ንጭንጭ ሰማሁ። ንጭንጩን የሰማሁት ንጉሤ የተባለው ሰው ከተቀመጠበት ቦታ ነበር። አንድ የሸሚዝ እጀታውን የጠቀለለ ረዥም ሰው ጀርባውን ወደ እኔ ሰጥቶ ያወራል።

"ምን ቸገረህ አንተ? ሰው ገዝቶ የማንበብ መብት አለው" ይላል።

"መረረኝ። ሌላ ነገር ጠፋ?"

"የአንተ ሥራ መሸጥ ነው። የቀጠርኩህ ለዚህ ነው። እዚህ ቆመህ ንግዴን እንድታበላሽ አይደለም። አሁን ከደበቅህበት አውጣና እዚህ ላይ ደርድር" ብሎ ባንኮኒውን በጥፊ ሁለቴ መታ።

"ባልፈልግስ" አለ ንጉሴ የሚሉት።

መፅሐፍት ቤቱ ውስጥ ገብተን የነበርን ሰዎች ጭቅጭቃቸውን በአትኩሮት መከታተል ይዘናል።

"የት ነው የደበቅኸው?"

"የማይሆን ነገር ከማንበብ መደንቆር ይሻላል"

"ማነው ያለው? ማክሲም ጎርኪ ነው እንዴ የማይሆን? በዓለም የታወቀ የጭቁኖችን ሕይወት አብጠርጥሮ የፃፈ ደራሲ ነው። ዝም ብለህ የማታውቀውን ትዘባርቃለህ"



@BOOKALEM

"ጎርኪ ስለራሱ እናት ይሆናል የጻፈው፣ ስለ እኔ እናት ስለ አሰገዱ አይደለም:: ለምን ራሽያ አትሄድም?"

"ምን ታውቃለህ? አሁን አንተ ምንህ አስተማሪ ነበር? በጣም አድሓሪ ነህ:: ከጊዜው ጋ ተራመድ:: እኔ የዚህ ቤት ባለቤት ነኝ:: እኔ ነኝ የምወስነው:: ገበያተኛ ነው የሚወስነው:: የት ነው የደበቅኸው? አሁን አምጣ::"

"ለምን ስለራሳቸው እናት አያውቁም ስለ ፓቬል እናት ከሚያነቡ:: አይመስልህም? ቀላል ይመስላል:: ለውጥ የሚወሰነው በዚህ ነው:: ተለወጡ የምንላቸው በየት በየት ተደርጎ ነው? የፓቬል እናትን ለከተን ቀሚሱን ለአሰገደች እንሰፋለን እንዴ:: ዲቃላ ሁላ" አለ ንጉሤ የተባለው ሰው::

"ይሄ የደብተራ ንግግርህን ወዲያልኝ:: ፖሊስ ሳልጠራ በፊት የደበቅኸውን መፅሐፍ አምጣና ውጣልኝ" አለ በቁጣ ወደ ንጉሤ እየተጠጋ::

ሊደባደቡ መስሎአቸው ቆመው ያዳምጡ የነበሩ ሰዎች ለመገላገል ወደ ባንኮኒው ጠጋ ጠጋ አሉ::

ንጉሤ ጎንበስ ብሎ ከከመዲናው ስር ጎራጎረና በእቅፉ ሦስት አራት መፃሕፍቶች ይዞ ቀና አለ:: አለቃው ሁሉ ሰው እንደ ተረጋጋ ወደ በሩ መድረፍ አለ:: አለቃው ከዞዋላው የሚንጀላጀለውን የንጉሤን ኮት ያዘው:: ንጉሤና አለቃው እየተጓተቱ ከመፅሐፍት ቤቱ ወጡ:: ሰዎች ሳቅን::

"ምኑ ያስቃል! ምኑ ያስቃል!" ይላል ንጉሤ::

ከመሃል መፅሐፍት ሲወድቁ ሰማሁ::

ከሱቁ ፊት ለፊት ገና ያልደረቀ የዝናብ ውሃ ያቁረ ደቂቅ ኩሬ ነበር፣ መፅሐፍት ቤቱ ስገባ ይሄን ውሓ ያቁረ ረባዳ ሆሬው ነበር:: ገና ከመፅሐፍት ቤቱ ሳልወጣ መፅሐፍቶቹ ውሃው ውስጥ ሲወድቁ ብዙ መንቦጫረቅ ሰማሁ:: ከውስጥ የነበርነው ሰዎች በሙሉ ውጭ የሚሆነውን ለማየት እየተንጋጋን ወደ በሩ ሔድን:: ባለቤቱ እውጭ ቆሞ እናቱን ያካል::

"ስንት ዕብድ አለ ጃን፣ ስንት ዕብድ አለ ጃን" ይላል ዝቅ ባለ ለራሱ እንደሚናገር ሁሉ::

ጭቃ ውስጥ ወድቀው የተበላሹትን መጻሕፍት በብስጭት በእግሩ እየነካ: "እንዲህ ዐይነት ሰው ባለበት ምኑ ለውጥ ይመጣል" ይላል:: ጎርኪ ስለ ተባለው ደራሲ ያውራ ስለ ንጉሤ ያውራ አይታወቅም:: ሰዉ ወደ ውስጥ መመለስ ሲጀምር እኔ በር አጠገብ ቀረሁ:: ባለቤቱ በሚያይደብት አቅጣጫ ስመለከት ንጉሤ የተባለው ሰው ዞር ብሎ እየሳቀ እያየ ወደ

ግራ ታጥፎ የሆነ መንደር ውስጥ ገባ። ከሶጭ ጥርሶቹ መሃል የፍንጭቱ ጥቁር ይታያል። ከድርጊቱ ሚተካከል ይሄ ሪባሽ ከሩቅ የሚታየው ገላማጭ ፍንጭቱ አስደነቀኝ።

ጭቃው መሃል ከወደቁት መፃሕፍት አንደኛው የፊት ለፊት ሽፋኑ ይታያል። ለመጀመሪያ ጊዜ ከብላክቦርድ ውጭ፣ ከደብተሬ ውጭ፣ ትምህርት ሚኒስቴር ከመደበልኝ የእንግሊዘኛ ፅሁፎች ውጭ የመፅሐፍ አርዕስት አነበብኩ። ኤም ኦ ቲ ኤች ኢ አር። ማዘር።

የመፅሐፍ ሽፋኑን ማንበቤን እንደ ጨረስኩ እንደ ራብኝ ታወቀኝና ቀድሞ አረፍኩበት ሻይ ቤት ያገኘሁትን ለመብላት ሞቅ ወዳለው የከተማው ማዕከል መንገዴን ቀጠልኩ።

*(ለ) ሳይሻል ይቀራል?*

ወደ ከተማው ማዕከል መንገዴን ቀጥዬ ከመሃል መብላቴንም ዘንግቼ ከአህያና ከብዙ እግረኛ ጋር እየተጋፋሁ ወዲያ ወዲህ ስንገላወድ ከየት እንደመጣ ልብ ሳልል ንጉሴ የሚባለው ሰውዬ ፊቴ ለፊቴ መጥቶ ድቅን አለ።

"እ? ምነው?" አልኩ በመደናገጥ።

"መፅሐፍት ቤቱ ውስጥ ነበርክ አይደለም?" አለኝ።

"አዎን"

"የሰራሁት ልክ ነው አይደል?" አለ።

"የሰው ንብረት ነው የወረወርከው" አልኩት አፌ እንዳመጣ።

ደንገጥ ብሎ አየኝ።

"የሰው ሐብት የሚከበር መስለኝ" አልኩት።

የተበረገደ ፍንጭቱን እያሳየኝ ሳቅ አለ።

ከዚያ፡ "ልጅ ነህ አንተ። እስኪገባህ ጊዜ ይወስድብሃል"

"ምነው?" አልኩ ለመከራከር።

ንጉሴ አለፍ ብሎ ገላመጠኝ።

'ከእኔ ምን ይፈልጋል?' አልኩ በልቤ።

"ያን ሀይነት መፅሐፍ ከማንብ እዛው የተወለድኩበት ከተማ ጉብታ መርጬ ወሬ ሳይ ብውል ይሻላል። ከምናየው የማናየው የሚያምረን ጅሎች ነን" አለ።



@BOOKALEM

መጀመሪያ በአባባሉ ሳቅ አልኩ። በአፍታ ግን ነገሩ ከንክኖኝ ዞር ስል እንዲያ ተከሳትሮ የተናገረው ሰው ያን አስደናቂ ፍንጭቱን እያሳየኝ ወደ ግራ ታጠፈና:

ማየትማ ያያል
ዐይን ያለው ፍጡር
ትንሽ እናንጣጥር
ትንሽ እንጠርጥር

ብሎ በጩኸት ሲናገር ሰማሁት። ተደናብሬ፣ ከመደነባበሬም ነቅቼ ንጉሤ በሄደበት ስሄድ በታጠፈበት ምንገድ ላይ ምንም ዓይነት የሰው ፍጡር አልነበረም። ከሩቅ ከግራ ወደ ቀኝ የተዘረጋ ሌላ ጎዳና አየሁ። እዚያ ጎዳና መገናኛ ድረስ ግራና ቀኝ ጥቂት ቤቶች ነበሩ። ምናልባት ስምንት የሚሆኑ። ልከተለው አልፈለግሁም። ብከተለውም የማገኘው አልመሰለኝም። ባገኘውስ ምን እለዋለሁ? ወደ ሻይ ቤቴ አቀናሁ።

*(ሐ) የፍርፍር ነገር መች ተላቀቀኝና*

መጀመሪያ ወደ ነበርኩበት ሻይ ቤቴ አቀናሁ። እዛም ስደርስ ባዶ ቦታ ፈልጌ ተቀመጥሁ። ያዘዝኩት ሻይ ከመድረሱ አንድ ሰማያዊ ጥቁር የራንግለር ጃኬት የለበሰ ልጅ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ። ጭንቅላቱ ላይ ፀጉር አልነበረውም።

"ሠላም" አለኝ

ለሠላምታ ጭንቅላቴን ዝቅ አደረኩ።

"ኤልያስ እንዳመጣህ ነግሮኝ ነው። እሱ ወዳለበት አብረን እንሔዳለን"

"የማን ኤልያስ?" አልኩ

"ኤልያስ......እዚህ አብራችሁ ተቀምጣችሁ የነበረው"

"ማነህ?"

"ጓደኛው ነኝ"

"እንዴት አውቃለሁ?"

"ወፍራም እህት አለህ"

"ብዙ ልጆች ወፍራም እህት አላቸው"

"የእንቁላል ፍርፍር ለመብላት ሥራ ለመቀጠር ንፋስ መውጫ ስትዞር አልነበረም?"



@BOOKALEM

መጀመሪያ በጣም ደነገጥኩ:: ቀጥሎ በሸቅሁ:: ስለዚህ ነገር የሚያውቀው ሙስጠፋ ብቻ ነበር:: ሙስጠፋ ስለ እኔ ማስጥራችንን ለምን ያወራል? እኔ ስለማልቀሱ አውርቼበታለሁ? ወይስ እኔ የማወራብት ወይም ያወራዛብት መስሎት መቅደሙ ወይ መበቀሉ ነው? ኤልያስ አይረባም:: ሙስጠፋ አይረባም:: ሁለቱም አይረቡም:: ውርደቴን ልጁ እንደ መጨረሻ ማንነቴን ለማረጋገጫ እንደተጠቀመበት ቢገባኝም፣ ብረዳም ወሬውን በማሰራጨታቸው ኤልያስና ሙስጠፋ አናደዱኝ::

"የትም አልሔድም"

"ለአንተ ነው.....ባንዶች ይከታተሉሃል"

"ምን ሰራሁ?"

"አንተ ታውቃለህ የሰራኸውን"

የምሰራው አልነበረኝም:: ሻዬን ቶሎ ቶሎ ጠጣሁና ወጣን:: በሻይ ቤቱ ጀርባ የሔድን ይመስለኛል፡ ቤቶች እርስ በርሳቸው የተያያዙበት የተነካከሱ የሚመስሉበት የጠባሳዎች ጠባሳ የመሰለ ቦታ ደረስን:: እስከ ዛሬ ድረስ የሔድንበትን ምንገድ ውስብስብነት በሐሳቤ በትክዞ ልቀይሰው አልችልም:: ልጁ ከሩቅ የምገባበትን ቤት አሳይቶኝ በግራ ይሁን በቀኝ በኩል ተሰወረ:: በመጠኑ ጨልሞ ነበር:: ያመለከተኝን ቤት ከፀይኖቼ እንደሚሰወር ዐይነት ፊት ለፊት አፍጥጬ ተጠጋሁትና በቀስታ በር አንኳኳሁ::

"ማነው?" አለ የሴት ድምፅ

"እኔ ነኝ"

"ማነው? ስም የለም?"

"መዝገቡ"

ሥሜ እንግዳ መሰለኝ:: ለማላውቀው ሰው ስሜን መንገሬ ይሁን ወይስ እንግዳ በሆነ መልክ መተዋወቂ ሥሜን በራሴ ልሳን ስጠራው እንግዳ ሆነብኝ:: እኔና የማላውቃት ሴት የጠራችው ስሜ ግኑኝነት የሌላቸው ነገሮች መሰሉኝ:: በር በቀስታ ተከፍቶ አንድ የሴት ፊት አየኝ:: የትልቅ ከተማ ጥሩነት መብራት መኖሩ ነው:: በሩን ገፍቼ ገባሁ::

"ቀስ ቀስ" አለች ሴትዮዋ:: ፊት ለፊቴ ማን ቆሞ ነበር?.......የበሰለ ወደ ጎን የሰፋች ወደ ወይዘሮ የተለወጠች ፀሐይ:: በሩን በብረት መቀርቀሪያና በመወርወሪያ መልሳ ዘጋችው:: ኤልያስ ዝቅ ባለ ድምፅ ከጓዳ እያፋዋጨ ወጣ::

"ምነው አስጠበቅኸኝ?" አልኩት

"ችግር.....ተዋወቁ ፀሐይ ትባላለች"



@BOOKALEM

"አውቃታለሁ" አልኩ። ንፋስ መውጫን ያራበሸች ፀሐይ። እጄን በለስላሳ እጆቿ ወስዳ አርገበገበችው። አረንጓዴ ጃፖኒ ሹራብ ለብሳለች። እና ክንዶቿ ስር ያሉት ጡንቻዎቿ እንደ ኩልኩልት ይነቃነቃሉ።

"ማነህ?" አለችኝ።

ሳልመልስላት በፊት አተኩራ አይታ፦ "እንዴ እንዴ እንትና.....መዝገቡ ነህ አይደለም?"

"አዎ" አልኩ ሳቅ ብዬ። የማላውቀው ቦታ ሄጄ የማውቀው ሰው ማግኘቴ ደስ ብሎኝ ነበር።

"በጣም አድገሃል። በስምአብ" አለች አፏን ይዛ።

"እዚህ እንደ መጣሽ ሰምቻለሁ ግን......"

"ዓለም ትንሽ ናት" አለች ተቀብላኝ።

አባባልዋ አልገባኝም። ፊቴ ላይ መገረሜን (ምናልባትም ዐይኖቼ ውስጥ "መች ለካሁዋት" የሚል ነገር አንብባ ይሆናል) አንብባ ነበር መሰለኝ–

"ተቀመጥ ተቀመጥ። አንድ የንፋስ መውጫ ልጅ ተገኘ። አበበን ታውቀዋለህ.....እሱ እዚህ አንዳንዴ እኅት አለው ሲመጣ አገኘዋለሁ"

ተቀመጥኩ። አፌ ጠጅ ጠጅ እንደሚሸት አውቃለሁ። 'በጣም አደግህ' ስትለኝ ጠጄን የምትተች መስሎኝ ነበር.....'ለመጠጣት ደረስክ?' ዐይነት።

"አበበ? አዎ አበበ" አልኩ በቸልታ።

"ራት አንበላም ፀሐይ?" አላት ኤልያስ። የተረጋጋ አይመስልም።

ሲጃራ ወረወረልኝ። ክብሪት ወረወረልኝ። ሁለቱንም መቅለብ ከባድ ሥራ ነበር። ለኩሼ እንደተቀመጥሁ ፀሐይ በትልቅ ትሪ ላይ ተጣጥፈው የተኙ ሁለት ጠይም እንጀራዎች አምጥታ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች።

"ድንቅ ምሥር ወጥ አለ" አለ እየሳቀ ኤልያስ።

"አድገህ ሲጃራ ለመጠጣት ደረስክ" አለች ፀሐይ የመጀመሪያ ጉርሻዬን እንኳን አፌ ሳልዶል።

"ተደው እጣክሽ ይዝናናበት። ያለን ነፃነት ይሄ ነው" አለ ኤልያስ።



@BOOKALEM

የተቀመጥኩበት ክፍል ንፁሕ ነበር:: ግድግዳው በሚገርም መልክ የተለሰነ ነበር:: ከምግሽ ወገቡ እስከ ጣሪያው ሰማያዊ ቀለም ወደ ታች እስከ ወለሉ ነጭ ቀለም ተቀብቷል:: በስተግራዬ ግድግዳ ላይ ከቀለሞቹ መለያያ መስመር ከፍ ብሎ የአንድ አንበሳና የአንዲት ቀይ ቀበሮ ስዕል ተራርቆ ተለጥፎአል:: ቀበሮዋ ቀያቱ አበባ ስር ቆማ እኛን የምታይ ትመስላለች:: ወደ ውስጥ ክፍሎች አሉ ግን በቅጡ አይታዩኝም:: ያለሁባት ክፍል ጠባብ ብትሆንም ቅልብጭ ያለች ነበረች:: መሃል ላይ ባለአበባ ጨርቅ የተሸፈነ የእንጨት ጠረጴዛ አለ:: ዙሪያውን አራት የደካከሙ የእንጨት ወንበሮች በዕድሳቸው ተማምነው ከበውታል:: መሃል ላይ ባለረጋ ነጭ ጣሳ አለ:: ውስጡ በከፊል የረገፉ በከፊል የደረቁ ነጫጭ አበቦች አለብት:: በስተግራ ቀና ስል ግድግዳ ላይ ትልቅ የቀበሮ ስዕል አለ:: ካየሁዋት ረዥም ጊዜ ስለሆነኝ ሳይሆን አይቀርም ፀሐይ ቂጧ በጣም ትልቅ ሆነብኝ:: በጣም ተጠግቼ ስላየሁዋት ይሆን? ፈገግታዋ ግን እንደ ድሮዋ ነበር:: ገላዋ ያኔም ለመንቀልቀል የተዘጋጀ ይመስላል:: ወዲያ ወዲህ ስትል ለምን እንደሆነ አላውቅም ለመጀመሪያ ጊዜ አቶ እንግዳ እሷን መድፈራቸው አጠራጠረኝ:: ዳሌዎችዋ ግራና ቀኝ ተዘርግተዋል:: ከፊትዋ ጎራዳነት ጋር የማይመጣጠን የሚያምር ሳሁጫ ጠጉሯ አናቷ ዘውድ ላይ በፈረሰ ጉንጉን ተያይዟል:: ኤልያስ በተመስጦ ያየኛል:: ልክ ያጠፋሁት ነገር እንዳለ ሁሉ:: እሷን በተመስጦ ስላየኹዋት ይሆን?

"እኔ አልመርጥም" አልኩት ስለምስር ወጡ::

ሲጃራዬን ስለጨረስኩ ጠረጴዛ ላይ ያገኙት ማልገኒያ ላይ ተርኩሼ ከሁለቱ ጋር ማዕድ ከበብኩ:: እየበላን ሁለቱ ስለማላውቀው ነገር ትኩስ ወሬ ያወራሉ:: ጋብ አድርገው ተጫወት ይሉኛል:: ከመሃል ከተማ ስላጋጠመኝ ነገር አወራሁዋቸው::

"ንጉሤ? ንጉሤን አውቀዋለሁ" አለች ፀሐይ::

"ነገረኛ ነው:: ግን ተንኮል የለውም" አለ ኤልያስ::

"የነ ገላጋይ አስተማሪ ነበር" አለች ፀሐይ::

"ኸረ" አለ ኤልያስ::

"የነገረኝ መሰለኝ:: የት ከተማ አስተማሪ ነበር አሉ:: አስራ ሁለት ዓመት አስተምሮአል አሉ"

"ታዲያ መፅሐፍ ቤት ተቀጥሮ ምን አሰራው?"

"ተባሮ ነው አሉ:: የአንድ አስተማሪ ልጅ አባልገሃል ተብሎ"



@BOOKALEM

"ያደርጋል:: ዕብድ ነው:: እንዴ.......እንዴ...... 'ዲያሌክቲካል ማቴሪያሊዝም' የምትባል መፅሐፍ ስገዛ 'ምን ያደርግልሃል?' ብሎ ሲነጨንጨኝ ነበር:: ጥሩ መፅሐፍ ነው ግዛው እንደ ማለት"

"ፍንጭቱ አይገርምም?" አልኩ አፌ እንዳመጣ:: ሁለቱም ትኩር ብለው አዩኝ እንደተሳሳትኩ ሁሉ::

"ያው ፍንጭት ነው:: የተለየ ነገር አለው እንዴ?"

የሚናገሩት ፍልስፍና ስላልገባኝ ተብሳጭቼ አርዕስት ለመለወጥ ጥረት ያደረግሁ መስሎት ይሆናል:: ወዲያው የማይገቡኝ ስሞች እየጠቀሱ የማይገባኝ ነገር መነጋገር ጀመሩ:: ግን ጥሩ በላሁ:: የቀኑ አውቶብስ፣ ዙረቱ፣ ጠጁ፣ ጭንቀቱ ተደማምሮ አደከመኝና መተኛት እንደምፈልግ ተናገርኩ::

"ሦስታችን አብረን አንድ አልጋ ላይ እንተኛም?" አለ ኤልያስ::

"አልጋው አይበቃም" አለች ፀሐይ::

"እኔ መሬት እተኛለሁ ግድ የለም" አልኩ::

የተከራከረኝ አልነበረም::

"ይኼ ክፍል ይበርዳል......እዚህ ስለሚበርድ መኝታ ቤቱ ውስጥ ቢተኛ ይሻላል" አለች ፀሐይ ለእሱ እያወራች::

መኝታ ቤት ውስጥ ካልጋው ብዙ ሳይርቅ ስሌንና አሮጌ ጨርቅ ተነጥፎ ተከታትለን ገባን:: ክፍሏ በእውነትም ትሞቅ ነበር:: መሂጃ ያጣ ወጥ የተሰራበት እሳት የለቀቀው ሙቀት የትም ሳይሄድ ስለደረስኩበት ይሆናል:: የእኔኑ መኝታ ቤት አስታወሰኝ:: ከእንጀራ እናቴ ሳይታይ ያመለጠ መጠነኛ ምቾት ቢኖር የአልጋዬ ሙቀት ነበር:: ሰባራም ቢሆን፣ ብርድ ልብሶቹ ያለቁም ቢሆን፣ ካሊሚ የቆሸሸ እንኳን ቢሆን ሁልጊዜ ሞቆኝ ያድር ነበር::

ፀሐይ ከአልብሴ ብተኛ የበለጠ እንደሚመቸኝ እየተናገረች ሳለች ድንገት ወደ ተኛችበት አልጋ ራስጌ ዐይኖቼ ሲቃኙ አንድ ፎቶግራፍ አየሁ:: ፎቶግራፉ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ማንነት ተገንዝቤ ከማወቄ በፊት የክፍሉ መብራት ጨለመ:: ፎቶግራፉ ውስጥ ሦስት ሰዎች ነበሩ:: አንደኛዋ ወጣት ሴት ናት (ፀሐይ ራሷ)፣ ሁለተኛው ሰው የእሷን ቀሚስ ይዞ በስተቀኝዋ የቆመ ምናልባት ሦስት ዓመት የሚሆነው ወይም የሚሆናት ጨቅላ፣ ሦስተኛው ግን የማውቀው የመሰለኝ ግን በትክክል በመተማመን ስም ልሰጠው ያልቻልኩት ሰው ነበር::



@BOOKALEM

ወንድዬው ፀሐይ አንገት ላይ እጄን አስቀምጦአል:: ፎቶግራፉን በአእምሮዬ በማውጣትና በማውረድ ማን እንደሆነ ለማወቅ ጣርኩ::

መብራት እንደጠፋ ፀሓይ ልብሷን ስታወልቅ አዳምጥ ነበር:: በጨለማው ውስጥ ቅርንፉድ ይሸተኛል:: የጭነት መኪና ሲያምጥ (ሲያላዝን!) እየሰማሁ:: ድቡልቡል ድምፅ ያለው ውሻ ራቅ ካለበታ ብስጭቱን ያንከባልልብናል.......ፀሐይም ወፍራምኛ እየተነፈሰች እሰማታለሁ.......

"መዝዝቡ ተመቸህ?" አለችኝ::

"በጣም" አልኳት::

"ደግ" አለች::

ቤቱ ፀጥ አለ:: ውሻውና የጭነት መኪናው ግን አላቆሙም:: ሁለቱም ነገሮች አንድ ግቢ ውስጥ ያሉ ይመስላል:: ከማል ኢልያስ ቀን የሰማውን የባለጌ ቀልድ ለፀሐይ ሊነግራት ይፈልጋል:: 'ተወኝ' ትለዋለች:: ይጒተታሉ መሰለኝ:: አልጋው ሲነቃነቅ እሰማለሁ ሽቦ አልጋ ነበር:: ሳቀች:: አልጋው ሲተረማመስ እሰማለሁ......ከተከናነብኩበት ተነስቼ ጨለማ ውስጥ አፈጠጥኩ.......የቅርንፉዱ ጠረን ጠፍቶ የፓራፊን ፀጉር ቅባት ጠረን በየቦታው ይበናል.......ይሄን ጠረን በእህቴ ሰበብ አውቀው ነበር:: እንደ ወንድሜ ምናምን የሚያደርገው ጠረን ነበር:: አልጋው ፀጥ አለ:: በሌላኛው ክፍል ጣሪያ ቀዳዳ የሚገባ የጨረቃ ብርሐን ይታየኛል.......አልጋው ስልት ባለው ምንገድ መነቃነቅ ጀመረ.......አፈርኩ....... ምን እንደሆን ጠረጠርኩ.......ጥርጣሬዬ አሳፍሮኝ ሳላመስማት ተከናነብኩ.......በተከናነብኩት ጨርቅ ላይ የተንጠለጠለው የቅባት ጠረን አልጣመኝም ነበርና እንደገና ተገለጥኩ::

ሥራ ከመፍታት ብዬ የአልጋውን ንቅናቄ መቁጠር ጀመርኩ.......



@BOOKALEM

# ደህና ሰንብት ኤልያስ

ፀሐይ ጠዋት ላይ ስታየኝ አፈረች:: እኔም አፈርኩ:: ኤልያስ በባዶ እግሩ የሚሰራው እንደጠፋው ሰው ወዲያ ወዲህ ይላል:: ተኮሳትሮአል:: እንዲህ ሲኮሳተር አይቸው አላውቅም:: እተኛሁበት ቦታ እንደተቀመጥሁ ሲጀራ ሰኩስኩ:: ቅር ብሎኛል......ልክ የረሳሁት ነገር እንዳለ ሁሉ::

"አንተ ከቁርስ በፊት አታጢስ" አለ ኤልያስ::

ያልሰማ መሰልኩ:: ፀሐይ ለቁርስ የሚሆን ዳቦ እንደሌለ ስትናገር እኔ መግዛት እንዳለብኝ ገባኝ:: ኤልያስ ስለፈራ አይወጣም:: አንደኛውኑ ኢሕአፓ አልሆንኩ:: አንድ ብር ከፀሐይ ተቀብዬ የቁርስ ዳቦ ልገዛ ወጣሁ:: ሲጀራው አቅለሸለሸኝ:: ከተማው መሃል ላይ የጠጣሁበት ቤት ሔጄ በምንገድ የምበላው አንድ ፓስቲና ለቤት የሚሆን ስድስት ዳቦ ገዝቼ ተመለስኩ::

ፀሐይ ቤት ልደርስ አንድ ምንገድ ስታጠፍ ጠመንጃ የያዘ ሰው ከፀሐይ ቤት ሲወጣ አየሁ:: ወደ ሁዋላ ሸሸት አልኩና ፊቴን ብቻ ብቅ አድርጌ ሳይ ጭር ካለው የፀሐይ ቤት ጩኸት ወጣ (ግራ በሚያጋባ መልዕክት ትቼው ስሄድ ድምፅ ያሌለው መስሎኝ ነበር):: "እረ!"...... ሦስት ሰዎች ከፀሐይ ቤት ወጡ:: ሁለቱ ከማሐላቸው ኤልያስን ይጐትታሉ:: ሌላኛው ከጀርባ ሆኖ ጠመንጃውን ኤልያስ ላይ ደግኖአል:: እተደበቅሁበት ቆየሁ:: ግራና ቀኝ አየሁ፣ ወደ ጀርባዬ አየሁ:: ወደ ጀርባዬ ራቅ ብሎ ሕፃናት ግራና ቀኝ ምንገድ ዳር ቲጥጥ ብለው ገበጣ ይጫወታሉ (በሌሊት ገበጣ):: ታግሼ ጠበቅሁ:: አንዳንድ ሰዎች ከግቢያቸው ወጥተው ያያሉ:: ቀጠሮ አበጅተው ፈጠጣ የሚሰሩ ይመስል ነበር:: እኔ እተሸሸግሁበት ሳይደርሱ አብዮት ጠባቂዎችና ኤልያስ በሌላ ምንገድ ካለፉ ብዙ ደቂቃዎች በሁዋላ እጄ ላይ የተላከከውን የፓስቴ ዘይት በሱሪዬ እየጠረግሁ በሩጫ ፀሐይ ቤት ገባሁ:: ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ በእርጋታ ተነሳች:: ዐይኖቿ ቀልተዋል:: ፊቷ ረጥቧል:: ዕንባዋ ይወርዳል::

"በል ጥፋ ከዚህ" አለችኝ እያቃተተች::

"የት ወሰዱት?" አልኩ

"ምን አውቃለሁ.....በል ጥፋ ሳትያዝ"

"እኔ ኢሕአፓ አይደለሁም" አልኳት::

"ጥፋ በል......"

"የት እሔዳለሁ?"



@BOOKALEM

"ወደ ምታውቀው ሒድ"

"እኔ ማንንም አላውቅም"

"ከየት መጣህ? ወደ መጣህበት አትሔድም?"

የመጣሁባትን ከተማ ለረዥም ጊዜ የተውኳት መስሎኝ ነበር:: በዚያች ምድር ላይ ያለች አልመሰለኝም ነበር:: ፀሐይ ስትጠቀስልኝ ግን በመጀመሪያ ጉብታዬ ትዝ አለችኝ ከዚያ ሙስጠፋ ከዚያ እህቴ ቀስ በቀስ ንፋስ መውጫ እየተገነባች እንደ ሰውነት ታየችኝ:: ወደዚያ መመለስ ግን እንደማልፈልግ ገባኝ:: የምሸሽበት (መችም ሽሽ ከተባልኩ ምን ላድርግ?) ሌላ ቦታ ግን አልነበረኝም:: ለድንገት ልቤ ሌላ ሌላ ነገር እያሰበ ወደ መኝታ ቤቷ ዐይኖቼን ጣል አደረግሁ:: ቀድሞ ተሰቅሎ ያየሁት ፎቶግራፍ ከቦታው አልነበረም::

"በል ሒድ የአውቶብስ ገንዘብ የለህም?"

"አለኝ" አልኩ ከውስጧ የፎቶው በድንገት መሰወር ገርሞኝ::

"ከሌለህ ልስጥህ"

ኪሴ ያለውን ሳንቲም ቆጥሬ እንዳለኝ ነገርኳት::

"ብትያዝ አታውቀኝም እሺ:: ብትያዝ ኤልያስ እኔን አያውቀኝም:: ውሸማዬ ነው እሺ"

"ገባኝ"

"በል ሒድ"

ዳቡውን ወደ ደረቷ ገፋሁና አሳቀፍኳት:: በሩጫ ወጣሁ:: ፀሐይ በሩ ድረስ እንኳን አልተከተለችኝም:: ዝባጣ ሲጫወቱ ባየሁዋቸው ሕፃናት መሐል ሮጥኩ:: አንድ ነገር አበሳሽሁባቸው መሰለኝ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተሳደቡ.......አውቶብሱ ጣቢያው በተሽከርካሪዎች ሙሉ ነበር.......ወደ እኔ ከተማ የሚሔደውን መለየት አልከበደኝም....... እውስጥ ገባሁ......ሎንቺናው ሲሞላ ነበር የሚሔደው......እውስጥ ከእሥር የሚበልጡ ሰዎች ነበሩ:: አውታንቲው ይጮሃል....... ወንበር መርጬ ጭንቅላቴን ዝቅ አድርጌ ተቀመጥሁ:: ከውጭ የሚያይ......ቢታየው ምንአልባት መላጣዬን ነበር:: ሎንቺናው ሊነሳ ሞተር ሲያሞቅ አንድ የታጠቀ (ሽጉጥ) ፖሊስ እየተንጉራደደ ገባ:: ሞቀመጫ ለመምረጥ ሲንቆራጠጥ ሰው የሚፈልግ መሰለኝ:: ከእኔ ፊት ለፊት መጥቶ ተቀመጠ:: ተረበሽኩ::

ነፋስ መውጫ እስከደርስ ድረስ የውጋት ጉዞ ነበር:: የማየው ነገር ቢኖር የፖሊሱን ማጅራት ብቻ ነበር:: የባርኔጣውን ጠርዝ ነበር:: የዩኒፎርሙን ካኪ የከውያ ተነዶስ መስመር



@BOOKALEM

ነበር:: ንፁህ ሆኖ የተላጨ የፊቱን ግማሾች በየተራ ነበር:: ድንገት አጏጉል ዞር ሲል እንዳለየ ዐይኖቼን እሰብራለሁ፣ በጉሪጥ የማጠናው ግን እሱን ነበር:: ንፋስ መውጫ ስደርስ በችኮላ አልወረድኩም:: ከፖሊሱ ጀርባ በቀስታ......እንዳልተሳደደ ሰው:: ምናልባት ይሔ ሰው ያስብ የነበረው ጫማው ስለመቆሸሹ ይሆናል:: ምናልባት ይሔ ፖሊስ የሚያስበው ሽማሙን ስላለማጠቡ ይሆናል:: ከሉንቺናው እንደወረድኩ በቀጥታ ሙስጠፋ ቤት ሔድኩ:: ሙስጠፋን ላንድ ቀን ሳይሆን ለረዥም ጊዜ የተለየሁት መስሎኝ ነበር:: ዘልዬ ላቅፈው ፈለግሁ:: ሙስጠፋ ግን አልገረመውም:: ለሰላምታ ጠቅሶኝ ሌላ ስራ ለመስራት ወዲያ ወዲህ ሲል ሳነጋግረው እንደምፈልግ ሌላ ሰው እንዳይሰማኝ ድምፄን ዝቅ አድርጌ ነገርኩትና መግፋትና መጎተት ቀላቅዬ ወደ ጓዳ ይዤው ገባሁ:: የሆነውን ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አወራሁት::

"ጥፋ. እንጂ. ምን ትጠብቃለህ?" አለኝ ኮስተር ብሎ ሳያወላውል::

"እኔ ምንም አላደረኩም እኮ" አልኩት::

አልሰማኝም::



@BOOKALEM

# ትልቢቱ እንደገና

ማደሪያ አልነበረኝም:: ፍርሃትን ከተገናኘሁት ስንት ጊዜዬ ነበር? ፍርሃትን እረስቼው ነበር:: ያን ቀን ግን ፍርሃት በዐይኖቼ ገብቷል:: ፍርሃት በአፌ ገብቷል:: ፍርሃት በቆዳዬ ገብቷል:: ፍርሃት በአጥንቴ ገብቷል:: ፍርሃት በደም ሥሬ ውስጥ ይሮጣል:: ፍርሃት የልቤ ምት ሆኗል:: ፍርሃት ሳንባዬ ውስጥ እንደ አየር ይንሳፈፋል:: ፍርሃት በኩላሊቴ ውስጥ እንዳልፀዳ ውሐ ይንቦጫቦጫል:: ፊኛዬ በፍርሃት ማይ ሞልቷል:: ፍርሃት በሕዋሳቶቼ ገብቶ ትናንሽ ጦሮቹን ይሰብቃል:: ፍርሃት አጫጭር ፀጉሮቼን አቁሟቸው ነበር::

ቤቴ መግባት አልፈለኩም:: ቤቴ ይታወቃል:: ከተማዬ ውስጥ ከሙስጠፋ ሌላ የማውቀው ሰው ኤሊያስ ያሳየኝ ቀይዋ ሴትዮ ብቻ ነበረች:: ከእነዚህ ሌላ የማውቀው ዱር ነው:: የመጀመሪያዬ ምርጫ ቤት ነው:: ቤት መሥራት የሚቻለው ሰው ነው:: የማውቀው ሰው ደሞ ከሙስጠፋ ሌላ ኤሊያስ ያሳየኝ ሴትዮ ናት:: እሷ ላይ የፈፀምኩት ያለፈው ድርጊቴ አሳፋሪ ሆኖ ቢታወሰኝም ከገባሁበት አደገኛ ሁኔታ የሚከፋ ግን አልነበረም:: አሳፋሪነቱ ከተዘፈዘፍኩበት ፍርሃት የገነነ አልነበረም::

ቀን ደን ዋልኩና ማታ ሁለት ወይም ሶስት ሰዓት ሲሆን ሴትዮዋ ቤት ሔድኩ:: አልነበረችም:: ከቤቷ ትንሽ ራቅ አልኩና (ሰውም እንዳያየኝ እሷም እንዳታመልጠኝ አድርጌ) ምናልባት ትመጣ እንደሆን ብዬ በድካም ስልምልምት ውስጥ የጅቦች ጩኸትና የእንቁራሪቶች ጫጫቴ እየሰማሁ ጠበቅሁዋት:: ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ ላይ ነጭ የለበሰ የሴት ምስል በሩን ቀርቦ ሲከፍት እንዳላስደነግጣት አድርጌ ሠላምታ ሰጠሁዋትና ከሁዋላዋ ተጠጋሁዋት::

"እ......ማነህ?"

"እኔ ነኝ"

"እ......የኤሊያስ ጓደኛ "

"አዎ"

"ምነው መጣህ ዛሬ?" አለች በሩን ለቀቅ አድርጋልኝ ስገባ:: ውስጡ ጨለማ ነበር:: እየተደናበረች ሄዳ ኩራዝ ለኮሰች:: ቤቱ ከውጪው የበለጠ አይሞቅም::

"ጠበቅኸኝ?"

"አሁን ነው የመጣሁት"



@BOOKALEM

መልሴ ግድ አልሰጣትም። ጋቢዋን አግዳሚ ወንበር ላይ ወርውራ ወደ ጓዳ ገባች።

"ተቀመጥ" አለችኝ።

ልብሷን ስትጥል ሳያት በፍርሃት ሮጬ መውጣትም ፈለግሁ። ገና ያልመጣው ጉዷን መደረግ ይኑርበት አይኑርበት አወጣ አወርድ ነበር።

"እራት በልተሃል?" አለች።

"በልቻለሁ"

"የደነዘምክ ትመስላለህ......ካልበላህ ተናገር። ሁለተኛ ጊዜ ሞሰብ አልከፍትም"

"በልቼአለሁ"

ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ግማሽ እንጀራ ላይ የማይጤስ ቀዝቃዛ ወጥ አፍስሳ ይዛ መጣች። ኩራዙ አጠገብ ተቀመጠች። አትናገርም። በዝምታ ትበላለች። የኩራዙ ደካማ ብርሃን ዙሪያዋን ይበራል። ግማሽ ፊቷ ላይ ያበራል። ባለአበባ ሻሿ ላይ ያበራል። ያለድምፅ የሚያላምጥ ቀይ ፊቷ ላይ ያበራል። ያሞጠሞጠ አፏ ላይ ያበራል። የተራቆተ ክንዷና አንገቷ ላይ ያበራል (አንገቷ ላይ ቀይ ክር አያለሁ። አንድ የብር ድንብል ጡቶቿ መሃል (ሠላጤው መጀመሪያ) እደረቷ ላይ ይነቃነቃል) ጣቶቿ ላይ ያበራል። ሰድፍ የሞላቸው እረዣዥም ጥፍሮቿ ላይ ያበራል። ቀኝ እጅዋ ላይ ያበራል። የተጣጠፈው ደረቅ እንጀራ ላይ ያበራል። በወጥ የረጠበ የተጣጠፈው እንጀራ ላይ ያበራል። ያልተቆረሰው እንጀራ ላይ ያበራል። በእንጀራው ዐይኖች ውስጥ ያበራል። የሳህኑ ጠርዝ ላይ ያበራል። የሣፋው የአበባ ስዕሎች ላይ ያበራል። ወጡ ላይ ያበራል። በጭንቀት ያበራል። የወጡ እርጥብ ክኮች ላይ ያበራል። ክኮቹ ቀይ ነበሩ። ክኮቹ ለስላሳ ነበሩ። ክኮቹን በጣቶቿ በተጫነቻቸው ቁጥር ወደ ሊጥ ይለወጣሉ። ወደ ክክ ሊጥ ይለወጣሉ። አትናገርም.......ቆይቶ.......ቆይቶ......መብላቷን ጨርሳ ሳህኗን ሲታጥብ.......

እኔ በዝምታና በድካም ተጠቅልዬ ተቀምጬ ነበር።

አግዳሚው ወንበር ይቀዘቅዛል......የሱሪዬ ቂጥ ለመቀደድ እንደሳሳ ይገባኛል። ጫማዬን አየሁት። አፍንጫው መሰንጠቅ ጀምሯል.....የግራ እግሬ ጫማ ማሰሪያው ተበጥሶ የተቀጠለ ነበር። የጃኬቴ እጅታ ከፊፍ ተበልቷል። ሸሚዜ ከታጠበ ብዙ ጊዜው ስለሆነ እንደለመደው መቆመል በመጀመሩ ብብቴን አልፎ አልፎ አካለሁ። ደስተኛ አልነበርኩም። በፍፁም ደስተኛ አልነበርኩም። እንደ እንስሳ ነበር የምኖረው። እንደ እንስሳ። ጨርቄ ውስጥ የተራቡት እንስሳት ነፃ ናቸው። ሙቅ ቦታ ፈልገው ይራባሉ። የሚመች ቦታ ፈልገው ደሜን ይጠባሉ.....የሚመች ጉድባና ዳገት ግለትና ጎፈሬ ፈልገው.....የጨርቅ እጥፋት መርጠው



@BOOKALEM

እንቁላሎቻቸውን ይጥላሉ:: ዕንቁላሎቻቸውን ጠዋት ጠዋት ይጉበኙዋቸዋል:: ማታ ማታም ያንቀላፉባቸዋል:: እኔም የማደርገው ግራ ገብቶኝ ከቦታ ቦታ እሸሻለሁ......

"ሾፌሩዋን፣ ጭልፋዋን፣ እጆቿን እየታጠበች:......"ኤልያስ አልመጣም?"

"አልመጣም"

"ደፈርከ እንዴ?"

ዝም አልኩ::

"ታድራለህ ወይስ ትሔዳለህ?" አረፍ አለችና: "ዋጋውን ታውቃለህ?"

"እስዎ ምን ይላሉ?"

"እርስዎ አትበለኝ......ከአንተ ባረጅም......'አንቱህን' ሌላ ቦታ" ቁጣ ቁጣ አላት::

ተጠጋችኝ::

"ታዲያስ ማሙሽ አወላልቃ......መጀመሪያ አምስት ብር ደንቡ ነው:: አሁን መክፈል አለብህ"

የምመልሰው ጠፋቶኝ በፀጥታ ተቀመጥሁ:: አልተንቃነቅሁም:: አሊጋዋ ዙሪያውን በመጋረጃ ተጋርዶአል:: ያንን አየሁ:: ምን የሚሉት ዘዴ እንደሆን አላውቅም:: ልብሷን ማውለቅ ጀመረች:: ፊቴን እሷን ወደ ማላይበት አዞርኩ:: ጭንቅላቴን በአንድ እጇ ይዛ ፊቴን ወደ እሷ አዞረችው:: ጡቶቿ ትልልቅ ናቸው:: ከምንትሲዋ ከፍ ብሎ የሰም ደጋን የመሰለ ቦርጭ ነበራት::

"እትዬ......እኔ ለማደር ብቻ ነው የመጣሁት......አምስት ብር ደ'ሞ የለኝም"

"እትዬ አትበለኝ:: ስሜ አልቤቲ ይባላል:: ታዲያ ስንት አለህ?"

"ሁለት ብር" ብዬ ያለኝን ገንዘብ ሁሉ አውጥቼ አሳየሁዋት::

ከእጄ ላይ ወስዳ አልጋዋ አጠገብ ያለች ትንሽ ባለመሳቢያ ጠረጴዛ ውስጥ አስቀመጠችው:: ጠረጴዛዋ ጭስ የጠጣ የማድ ቤት ዕቃ ትመስል ነበር-አንከርት እላዩ ላይ አቁማ ውጥ የሰራችበት ወይ ቡና ያፈላችበት......

"በል መሬትህ ተኛ ከፈለግህ......ወንድ አብሮኝ ተኝቶ ልቤ እሺ አይለኝም"

"ኸረ ግድ የለም"

"ወንድ ነህ ምንድነህ? ትልቅ እኩ ነህ"

ምንም አልተናገርኩም.......እንደ ውሻ በዐይናቼ የምተኛበት ወለል እመርጣለሁ::



@BOOKALEM

"ላንተ የሚሆን ሌላ ብርድ ልብስ የለም:: አልጋው ላይ ፊትህን አዙረህ ተኛ.....ራቅ በል ደ'ሞ::"

ቆየሁ:: እሷ የቦንዳ አልጋዋ ላይ ወጥታ በምቾት ስታቃስት ጨለማው ውስጥ እንደ አውሬ እያደባሁ ቆየሁ:: ያየሁት ትልቅ ሥጋዋ ለሥላሳነቱና የማያልቅ የመሰለ ቅላቱ አስፈርቶኝ ሁለመናዋ ቅላት ነበር:: ከገላዋ እስከ ድዷ::

ልብሴን አውልቄ የአልጋውን የውጭ ጠርዝ ዳብሼ ተጋደምኩ:: የፍራሹ ጉርባጣ ጐኔን ይሰማኝ ነበር:: ፍራሹ የተሞላበት ሣር እንደ ብዙ ነፍሳት ድምፅ ይንሺሻል:: ዕንቅልፍ ሳይወስደኝ ብዙ ቆየሁ:: የሴትዮዋ ትንፋሽ በመጀመሪያ የለመድኩት ስልቱ ሲረበሽ ሰማሁ ቀስ በቀስ እንደ ድመት ማንኩራኩር ጀመረች.....ብዙ ሳይቆይ ሰውነቷ ሁሉ እንኩርፍት የሆነ መሰለ ቤቱ በእንኩርፍት ሞላ.....የቤቱ ዕቃ.....ግሪያ.....ቤቱ የተሰራበት መሬት የሚያንኩራፋ መሰለ:: ከሞት ጋር እንደተኛሁ ሁሉ ነበረ:: ይሀቺ መሬት ከስሬ በቀስታ እንደምትናድ ሁሉ ነበር:: ወደ ድንጋያማ ጉድጓድ እንደምገባ ሁሉ:: አልቤቲ በጀርባዋ ስትገላበጥ.......ከአፏ የሞቀ አውሎ ንፋስ ይወጣል.......ጉሮሮዋ ውስጥ የሆነ ነገር ይንፈራፈራል......የምራቅ ኳስ......ምናልባት ተጠርጎ ያልወረደ የክክ ራቷ.......:: ከመሐል......ይቋረጣል:: ድምፁ ሁሉ አቋርጦ ከአልጋው ላይ እየተንፈቀቀች ተነሳች:: ክብደቷ ጭኔ ላይ እንደ አውቶብስ ነበር:: መጋረጃውን እንደያዘች ከአልጋው ስር ባሬታ ነገር አውጥታ.....በማያበሽቅ መልክ መፀዳዳት ጀመረች:: ዐይኖቿን ጨፍናለች:: የሽንቷ ድምፅ ወደ ነጠብጣብ መለወጥ ሲጀምር.......በሕልም እንደሚጓዝ ሁሉ እየተሳበች ሔዳ የኩራዙን ነበልባል በደከመ ትንፋሽ አጠፋች:: ወደ መተኛዋ እየረጋገጠችኝ ተመለሰች:: የኩራዙ የነበልባሉ ጉጥ ቀይ ነበር:: የጋዝ ሽታ እተኛሁበት ድረስ እየተሳበ መጣ ከሽንቱ ጠረን ጋር ሰርኔ ውስጥ ይታገላል::

ሊነጋ ሲል ነው መሰል የተኛሁ::

ስባንን ጠዋት የሞቀ ጠዋት ነበር:: የቤቱ በርና መስኮቶች አልተከፈቱም ነበር:: በግሪያውና በግድግዳው ቀዳዳ ጥጥ የመሰለ ብርሐን ይገባል:: ሁለታችንም ፊቶቻችንን ወደ ጣሪያው አቅጣጫ አድርገናል:: ልቤ ከተኛሁበት እንድነሳ ይፈልጋል:: በጐን አይታኝ ሳቅ አለች:: ትልቁ ከተማ ያደረኩት መሣላና የተሰማኝ ቁጭት አናደደኝ::

"ጥሩ ተኛህ?" አለችኝ

"አዎ"

እጄን እግሬ መሐል ላከች:: ፍርንትቴን ከአደጋ ለመጠበቅ እግሮቼን መስቀልኛ አነባበርኩ:: ፊቷን አዙራ......ደረቴን መዳበስ ጀመረች:: እጇ ሸካራ ነበር:: እጇ እንዳረጀ ካሊም:: አርጅቶ ሰንበር ብቻ እንደሆነ ካሊም:: እንደበቃው ካሊም:: እግሬ......የእግሮቼ



@BOOKALEM

ጣቶች፣ ቁርጭምጭሚቶቼ፣ ባቶቼ ብቻ ቤት ውስጥ ያደሩ መሰለኝ:: እጄ እየሰረቀ የሚያደርገውን በፈሩ ጆሮዎቼ አዳምጣለሁ::

"ኤልያስ የት ጠፋ?"

"ዘመድ ሊጠይቅ ሔዷል"

"ዘመድ ይጠይቃል እንዴ እሱ.....ቁምነገር ያውቃል?"

"ቁምነገረኛ ነው" አልኳት::

እየተኛችው፣ እያባለገችው ቁምነገር አያውቅም ትላለች:: ብዙ ላወራት አልፈለግሁም::

"እንዲህ.......ከምትዞሩ......." እጄ እግሮቼ መሐል አረፈ:: አባረርኩት::

"እውነቴን ነው ከምትዞሩ ወታደር ብትሆኑ ይሻላል.....ለሌላ ቁም ነገር አትሆኑም"

ዝም::

"ከእናንተ የተሻለው ጨዋ ነው ከትናንት ወዲያ ትምህርት ቤት ሲመዘገብ የዋለው"

ዞር ብዬ አየሁዋት......ምን እንደምፈልግ ባላውቅም ከገባሁበት ረግረግ ማምለጥ ፈለግሁ:: ወሬዋን እንድትቀጥል ጠበቅሁዋት:: የዐይኖቼን ማተኩር ተገንዝባ እሷን የፈለግሁዋት መስሎአት ነበር መሰለኝ እጇ እንደገና......አባረርኩት:: በዝምታ ተኛን......እያደባሁ፣ እየፈራሁ የምትፈልገውን ሳልሰጣት እኔ የምፈልገውን መጠየቄ የወንጀለኛነት ስሜት እየፈጠረብኝ ስስታም እንደሆንኩ ሁሉ የምሰጠው ነገር እያለኝ ለማላውቀው ምክንያት ደብቄው እጆቿ እየለመኑኝ......ሰውነቷ በፍላጎት እየተንዘፈዘፈ.......የሚፋጅ ወጣት ጉድ አስቀምጣ......እንደ ዕልበት በርዶባት......

"የት ነው ሲመዘገቡ የዋሉት?"

"ምነው?"

"ለማወቅ"

"ማዘጋጃ ቤቱ በር ላይ ነዋ.......አላየህም?"

"አላየሁም"

"ከተማ ውስጥ ያለ ነገር ያመልጥሃል? አንተ 'ዝቢ' የምትባለው ልጅ አይደለህም?"

"ምን?"

"ዝቢ"

"ምንድነው ጉቤ?"

"በል ቅፅል ሥምህንና ሥራህን አታውቅም? "

"ገባኝ"

"ታዲያ ምን እንደማያውቅ ትጠይቀኛለህ?"

"መርሳቴ ነው"

"ተረሳ እቴ......ለመመዝገብ አሰብክ እንዴ?"

"ምናልባት"

"ጥጋብ እኮ ነው:: አባትህ አንተን ማስተማር፣ ማልበስ፣ መቀለብ አቅቶት ነው? ጉድ እኮ ነው......ምናለ ልጅ ቢኖረኝ...... ኡህ!" ከንፈሯ በሐዘን መጠጠች::

"ልጅ አትወልጂም ታዲያ?"

"አባት እፈልጋለሁ፤ አባት አትሆንም አንተ?"

"ልጅ ነኝ"

"አንተ ወታደር ለመሆን፣ ለመሞት ልትሔድ ከሆነ ማስወለድ ያቅትሃል?"

"ምንም ነገር አልፈልግም"

ከአልጋው ዘልዬ ተነሳሁ:: ተኝቼ የነበረበት ቦታ ላይ ግራ እጇን ዘርግታ በሐዘን ፊት ታየኝ ነበር::

"በጣም የምታምር ልጅ ነህ አንተ.....አብረኸኝ ተኝተህ ምንም ሳታደርግ መሔድህ በጣም ያበሽቃል:: የኮርምት መክፈል ነበረብህ፣ ወንድ እንደ ወንድ ካልሆነ የሚቀጣበት ጊዜ ቀርቷል" አለች በመሳቅ::

*እንዳልነበርኩ ቁጠረው* - በልቤ::

ልብሴን ለብሼ የላስቲክ ባሊ ውስጥ ባገኘሁት ቀዝቃዛ ውሐ ፊቴን ደባብሼ ልወጣ ስል......ከመሳቢያዋ አንድ ብር አውጥታ ሰጠችኝ:: እየተግደረደርኩ ተቀበልኩ:: ጠረዼዛት ተሰማኝ::

"ጥሩ ሽርሙጣ ነኝ......አይደለም?" አለችኝ:: እየሳቀች::

አመስግኜአት ወጣሁ:: ከሁዋላዬ ኢልያስን ሠላም እንድለው ስትጠይቀኝ ሰማሁዋት:: የመጀመሪያው ዓላማዬ ስለምዝገባው ማወቅ ነበር:: ወደ ቤቴ መሔድ አልፈለኩም:: "ቤቴ"



@BOOKALEM

የማላውቀው ወይም ከዕለታት አንድ ቀን እግር ጥሎኝ ያየሁት ቦታ ዐይነት መስሎ ይታወሰኛል:: ባሪያውን ከሩቅ አየሁት:: በአባቴ ሱቅ ፊት ለፊት ሳለማለፍ ወደ ቀኝ ታጥፌ መሐል በሙስጠፋ ሱቅ ፊት ለፊት ከተማው መሃል ብቅ አልኩ:: ሙስጠፋ ሻይ ቤት ሁለት ጸቦና አንድ ሻይ አዝዤ ስበላ ሙስጠፋ ሥራው ጋብ ብሎለት እንደ ልማዱ ባንኮኒ ተደግፎ ሲያርፍ በመጀመሪያ የጠየቅሁት......

"ወታደር ይመለምላሉ አሉ"

"ወታደር? ወታደር አይደለም ፖሊስ ነው.......ምነው?"

"መቀጠር እፈልጋለሁ"

ሙስጠፋ ዝም ብሎ አየኝ:: ራሱን አከከ:: እንደገና አየኝ:: ዐይኖቹ ዕንባ አቅርረው ደረቴን በቀስታ በቡጢ ገፋኝ::

"ስማ መዝገቡ ሳስበው አንተ ለወታደርነት፣ ወይም ለፖሊስነት የምትሆን አይደለህም:: የሚሆንህን ግን አንተ ታውቃለህ"

"ምን እሰራለሁ እዚህ? አንድ ዝቤ እዚህ ምን ይሰራል? ቤት ውስጥ እኮ በግድ ነው የምኖረው፡ እና ምናልባት ብያዝስ? ኤልያስን ይዘውታል"

"ምን አድርገሃል? አትያዝም:: ኤልያስ የታወቀለት ኢህአፓ ነው"

ስላደረኳቸው አንዳንድ ነገሮች ልነግረው ፈለግሁ:: ባምነውም አላመንኩትም:: ብወደውም ፈራሁት::

"ለማንኛውም ከዚህ መሔድ እፈልጋለሁ:: ፖሊስ መሆን ደግሞ አደጋ የለውም"

"ምን ይታወቃል? ችግርህ ይገባኛል ግን በ ንክኪ(17) የሚገመት ብዙ ነገር አለ" የሚናገረውን ሳይጨርስ ወጣ::

ሰዐን ላይ በቀረ የጻቦ ፍርፋሪ እየተጫወትኩ ብዙ ቆየሁ:: ከየት እንደመጣሁ.....የት እንዳለሁ.....ወደ የት እንደምሔድ አላውቅም ነበር:: (ዐይኖቼ ያን ዕለት ለምን ዕንባ አቅርረው እንደነበረ እስከዛሬ አይገባኝም):: ከርቀት የሚመጣ የሚመስለውን የሙሉቀን መለሰን ዘፈን ("ቼ በለው!! ኧረ ቼ በለው") እየሰማሁ ከተቀመጥኩበት ሳልንቀሳቀስ ብዙ ቆየሁ::

ቀትር ላይ በሻይ ቤቱ ጀርባ ወጥቼ እያደባሁ ወደ መመዝገቢያው ቦታ ሔድኩ:: በመጀመሪያ ወና ቤት ከነበረው.....ቀበሌ ከገባበት ቤት ሆኜ የማዘጋጃ ቤቱን መግቢያ ሰለልኩ:: እውጭ ሁለት ፖሊሶችና ጥቂት ወጣቶች ቆመዋል:: ያወራሉ:: አንድ ጎረምሳ እየሮጠ ገባ:: አፍታ ጠብቄ ቀረብ አልኩ:: የአህል መሸጫውን ሱቅ አልፌ የጤና ጥበቃ



@BOOKALEM

ወኪል ያለበትን የፈረሰ ጀኅል ታክሲ ቆሜ ማየት ቀጠልኩ። የገባው ልጅ ወጣ። ከጉብታዬ ላይ ተቀምጬ ቢሆን ኖሮ የሰዎችን ፊትና ጠባይ ብቻ ሳይሆን የኪሳቸውን ጉድጓድ ማየት እችል ነበር። መሐል አናታቸውን......የጥርሶቻቸውን ገበር አይ ነበር። ያን ዕለት ፈራሁዋቸው። ተስተካክዬ መሬት ላይ በመቆሜ ነበር መሰለኝ ፈራሁዋቸው። የወሰን እናት ከክሊኒኩ መንጋጋቸውን በግራ እጃቸው አቅፈው ወጡ። በሌላ እጃቸው ትልቅ የጥጥ ኳስ ጨብጠው ይዘዋል። ሳያዩኝ በፊት ከበሩ ሸሸት ብዬ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ አጥር ጠጋ አልኩ......

ፊቴን አዞርኩ። ተመልሶ የመጣው ልጅ ከፖሊሶቹ ጋር ቆሞ ያወራል። እየተመዘገቡ እንደሚወጡ ይገባኛል። ማሰብ ነበረብኝ። መዝጋቢዎች ምን ይፈልጋሉ? ለመመዝገብ ከእኔ ምን ይፈልጋሉ? አደን ላይ እንዳለ አውሬ እየተሳብኩ ወደ ሰዎቹ ቀረብኩ። አንደኛው ፀጉረ ልውጥ ፖሊስ አየኝ.......

"ተመዝጋቢ ነህ?"

"አዎ......"

ከፍ ዝቅ አድርጉ አጠናኝ (በሁዋላ ያጋጠሙኝ የፖሊሶች ፀባይ ነው። እንደሚመረምሩ አተኩረው ያያሉ ግን ጉራቸውን ነው)።

"የትምህርት መረጃ ይዘሃል?"

"ስምንተኛ እመስልሃለሁ?"

"ስምንት ይደርሳል ይሔ?" አለ አንዱ ሌላውን።

ትከሻዎቼን ከፍ ዝቅ አደረግሁ።

"የትምህርት መረጃህን ማምጣት አለብህ። የተለጠፈውን አላነበብከም?"

"የት ነው የተለጠፈው?"

"እዚህ ጋ አለልህ"

ፖሊሱን ትቼው ወደ ተለጠፈው ወረቀት ሔድኩ።



@BOOKALEM

# ሕፅን ማስታወሻዎች/ወሽመጦች

## (1) መንገዶች፡

የነፋስ መውጫን ከተማ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ መሐል ለመሐል የሚያቋርጥ ትልቅ የጊኛ፣ የመኪናና የሰው ምንገድ አለ:: ከዚህ ጎዳና በስተቀር በየሰፈሩ ውስጥ ያሉት መንገዶች ትንንሾች ናቸው:: በበጋ በበጋ አመዳም፣ በክረምት በክረምት ደሞ አድካሚ አረንቋ የሚሆኑ:: ከጉና ገመገም ላይ ሆነው ከተማዋን ወደ ታች ሲያይዋት በተለያዩ አቅጣጫ በመንገዶች የተሸነሸነች ናት:: ረባም አልረባም በዚህም በዚያም ብሎ ታዲያ ከተማዋ መስቀለኛ ምንገድ ይበዛታል:: ሰዎች ሲናገሩ ስለማ መስቀለኛ ምንገድ ላይ ሰይጣን......«ያ ምናምንቴ» ደፍሮ አይቀመጥም ይላሉ:: ከተማዋ ውስጥ በጠቅላላ ሁለት የመኪና ባለቤቶች ስድስት የብስክሌት ባለቤቶች አሉ:: ጊኛ መዓት ነበር:: አደጋም ይበዛል:: አህያ ቂጡን አረግጦት እንዴት ቢረግጠው እንደሆነ እንጃ የሆድ መታወክ የደረሰበት ሰው አውቃለሁ:: ከተረገጠ ጊዜ ጀምሮ የሚበላው አይረጋለትም:: በወሬ በወሬ ለሰማ ምናልባት «አህያው ሰበብ ነው እንጂ ሰውዬውን ሡይጣን ለክፎት ነው» የሚሉ አሉ:: መስቀለኛ ምንገድ ላይ እንደቆመ ቢረገጥ ኖሮ ብዙ አይጉዳም ነበር አሉ:: ከተረገጠ በሁዋላ እንኩዋን ታምረኛው የመድሐኒያለም ደወል ጥላ ስር ለሶስት ቀን በያስቀምጡት ኖሮ ቀልጥ ብሎ ይፈወስ ነበር ይላሉ:: ታዲያ ዋናው የትራፊክ አደጋችን በአህያ የሚመጣ ነበር:: ስንጎዳም በደወል የሚፈውስ እንደ ሐኪም ቤት የሚያገለግል ቤተክርስቲያን ነበረን:: በጎዳና ላይ መወዝወዝ ስለማበዛ በአህያ ተረግጬ መታመሜ አይቀርም ብዬ በመፍራት በዚያ ቤተክርስቲያን አጠገብ ካለፍኩ ደወሉን ልጎበኝ ጎራ እል ነበር:: የመጀመሪያ ጥንቃቄዬ (ፈርስት ኤይድ) ትንሽ እንኩዋን ቢያንሸራትተኝ ቶሎ ብዬ ማማተብ ነበር::

ግራጫው ከፈወሰ መረገጥ ምን ክፉ የሚል አይጠፋም......

## (2) ግራጫው፡

ከቤተክርስቲያኑ ጎን ከግቢው ሳይወጣ በረዥመ የ«በ» ቅርፅ ካለው መስቀያ ላይ የተዘቀዘቀ ዋንጫ የመሰለ ከዕንብርቱ ውስጥ ከብደቱ ለዐይን የሚመዝን ቁላጥ ያለው ግራጫ ደወል ነበር:: በአጋጣሚ በቤተክርስቲያኑ አጠገብ ካለፍኩ የነገርዬው አሰራር አስገርሞኝ ወደ ቤተክርስቲያኑ ግቢ አዘልቅና አየዋለሁ:: ከሩቅ ለሚያየው ተራ ደወል ይመስል ነበር:: ሁልጊዜም ከደወሉ ስር እስከ አፍንጫው ድረስ አፈር የመሰለ ጋቢ የተከናነበ ዲያቆን ያጋጥመኝ ነበር:: ቀርበው ሲያዩት ግን ተራ የመሰለው ግራጫነቱ አስደናቂ ግርማ ያወጣል፣ አልባሌ ደወል መምሰሉ



@BOOKALEM

ይቀርና እጅግ ይረቃል፡፡ ታዲያ ቆሜ እየዋለሁ፡፡ በተመስጦ፡፡ ከስሩ (ዲያቆኑ ለሴሳ ጉዳይ ዞር ሲል) ሄጄ ለኩሸት ስቆም የግራጫው ጥላ በደም ስሬ ውስጥ በዕድ አካል መስሎ እንደ በረዶ አቃዊ ሲፈስ ይሰማኝ ነበር፡፡ ማንም ደፍር ነኝ ባይ ይሄ ልምድ ቢያጋጥመው ይፈራል፡፡ ለመድሐኒያለምና ለበዐል ቀናት ያን የጠራውን የንፋስ መውጫ ሰማይ ባማረ ድምጹ የሚሸነሽነው ይሄ ግራጫ የመድሐኒያለም ደወል ነበር፡፡ ከተቀመጥኩበት ጉብታ......ፊቴን ወደ አንጢቆ ዙፋን ቤት አቅጣጫ አድርጌ......ትንሽ ወደ ግራዬ ዞር ካልኩ...... የቤተክርስቲያኑ የቆርቆሮ ጉልላት በከበቡት ዛፎች በሰሩት ክፍተት ውስጥ ይታየኝ ነበር፡፡ ከብዙ መኖሪያ ቤቶች የበለጠ ፀዐዳ ቆርቆሮ ነበረው፡፡ በፀሃያማ ቀን ይሄ ቆርቆር ቀለበትማ ከከበቡት አረንጉዋዴ ፅዶች መሃል እንደ ብርማ ጨርቅ ሲፈልቅ አየው ነበር፡፡ ዓመት በዐል ሆኖ በተደወለ ቀጥር የሚያምር የዕጣንና የጠጅ ሳር ሽታ በንፋስ እየተሰራጨ ጉብታዬ ድረስ ይመጣል፣ አልፎኝም ሳይሄድ አይቀር፡፡ ታዲያ ሰዎች የደወሉ ጠረን ነው ይላሉ፡፡ እጅግ ረቂቅ፣ መኖሩን እንኳን ለመንገር የሚከብድ ቢያወሩት ውሸታም የሚያስብል የእንኮይና የአልባብ ጠረን ነበር፡፡ አንዳንዴም በምሽት በተለይ ጨረቃ ሰማዩን የምትቀድ ዕለት እና በጠገበ ሆዱ፣ በእርግብግብም አፍንጫዬ ካነፈነፍኩ ያሞቀሞቀ ቀጋ ይሸተኝ ነበር፡፡ ንፋሱም ይሆናል ከጉና የሚመጣው፡፡ ግን መድሐኒያለም ይመስለኝ ነበር፡፡ ቃጭሉን ተጠግቼ ስላየሁት ሳይሆን አይቀርም እል ነበር ስራሴ ይሄ ይሄ ተፅዕኖ የስሜት ሕዋሴ ላይ የመጣብኝ፡፡ እንደዚህ የሚያምር ለጆሮ ብቻ ሳይሆን ለአፍንጫ የሚደርስ የደወል ድምጽ የትም የለም ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ ወሬ የጋራ፣ እምነት የግል ነው እንዲ፡፡

ደወሉን ከታች ገደል ስር ቆፍረው ያስወጡት የከተማው ከንቲባ የአቶ እንግዳ አባት ናቸው ይባላል፡፡ ታዲያ በአባታቸው ገድል ምክንያት ዝነኛ ሆነው ለብዙ ዓመታት የነፋስ መውጫ አስተዳዳሪ ነበሩ፡፡ አቶ እንግዳ ሲያመሩ የሚምሉት በመድሓኒያለም ደወል ነበር፡፡ «እሱ ጆሮዬን ይዝጋው» «እሱ ይሰንጥቀኝ»፡፡

አቶ እንግዳ የመድሓኒያለምን ስም ካነሱ እውነታቸውን ነበር ማለት ነው፡፡

## (3) አቶ እንግዳ፡

የአባቴ ጥቁር እንግዳና አጠራጣሪ ዘመድ (ሙሉ ዘመድ መሆናቸውን አንዳንዴ እጠራጠር ነበር)፡፡ የከተማው አስተዳዳሪ ነበሩ፤እኔ ንፋስ መውጫ እሰከነበርኩ ጊዜ፡፡ አቤታችን አባቴን ሲጠይቀ ወይም እንደጠፉ ሲነግሩት ይመጡና ሁልጊዜ የሚያወሩት ግን ባለፈው ጊዜ አበሳሽቶ ስለቀረጣቸው ፀጉራቸው ነበር፡፡ ከፊት ለፊት አሰማማሩን እንዳደገመግሙት መላጣ ናቸው፡፡ ከጆርባቸው ያለውን እንዴት ይተቹታል? እንዴት አዩት? ይተቹታል፡፡ እንደሚያውቁ ሁሉ ይተቹታል፡፡ አባቴ ቤት መጥተው አባቴን ይቆጡታል፡፡ "አቶ እንግዳ" ተብለው ነበር የሚጠሩት፡፡



@BOOKALEM

ያለ "አቶ" ተጠርተው አያውቁም። አባቴ ዘመዴ እንኳን ቢሆኑም "አቶ" ካልጨመረ ስለእሳቸው አያወራም። የእኒህ ሰውዬ ሆድ ስፋት የሚገርም ነበር። አንድ በግ ይጨርሳሉ። አንድ ዶሮ ያጠናቅቃሉ። አባቴ ለምን ይጠቅሙናል ይል እንደነበር አላውቅም። ደሞም ዘመዴ ናቸው ይላል። ሰውዬው እኔን ምንገድ ላይ ሲያገኙኝ እንደ ትንኝ "እሽ!" ብለውኝ ያልፉ ነበር። ትናንት፣ ከትላንት ወዲያ ከዚያ ቀድሞ እኔ አይቸው ከማላውቅ ማዕድ እንዲበሉ ያን ድቡልቡል እጃቸውን እንዲታጠቡ ውሓ እንዳላንቀረቀርኩላቸው ሁሉ። የሚገርመኝ እኒህ ሰውዬ ከቤት በልተው፣ ጠጥተው ከሄዱ በሁዋላ አባቴ 'ይኼ ቦርጫም' ሲላቸው ነበር። ብዙ ሰው ግን "እንግዳ ጮሌው!" ነበር የሚላቸው።

*አያ እንግዳ እንግዳ*
*አሀሆ*
*አያ እንግዳ እንግዳ*
*ጠቀሰኝ በማለዳ*

የተባለውን ዘፈን ከሬድዮ ኮርጄ እዘፍነው ነበር። የዕውነቴን ነው ለምን እዘፍነው እንደነበር አላውቅም። ብቻ እሳቸውን ያየሁ ዕለት ከዚያ በሁዋላ ለጥቂት ቀናት ይሄን ዘፈን እዘፍነው ነበር። አባቴ «ይሄን ለነገር ነው የምታንጎራጉረው» ብሎ ወርፎኛል። ኩርኩምም ሰንዝሮ ለትኖኛል። የከተማው ፈጣሪና አፍራሽ ናቸው ይባላል። የሰው ድምፅ እየረበሸ የሚያስቸግራቸው አዲስ ቤት ቀላሾች መጀመሪያ የሚያምሙት አቶ እንግዳን ነበር፡......

«ካልጠፋ ቦታ ምንገድ ዳር ካልሰራችሁ አይፈቀድላችሁም ብሉ፣ በለካራም እንቅልፍ ሲያስረብሽን ያድራል። የከብቱስ ኮቴ? ጉድ ነው። እያቱ ደወል አገኘና በእንቅልፍ ማጣት እንበድ እንዴ? የሚነቀል ይንቀለው» ይላሉ።

አንዱ «ነፋሻ ቦታ ቤትህን ካልሰራህ ብሎ አስፈራራኝ» ይላል።

አንዱ «ገደል ላይ ወስዶ ካልሰፈረከ ብሎ እንደ ዝንጀሮ እኖራለሁ» ይላል

አንዱ «ወንዝ ዳር ቤቴን አስተክሎ ሚስቴን አዞ ሲጠልፍብኝ ነው» ይላል

እሳቸው ደሞ «የወፍ ጎጆ ይቀልሱና 'ቢላ' እንደ ሰራ ሁሉ ልቤን ያደርቃሉ» ብለው የመልስ ተረብ ይወረውራሉ።

አባቴ ይሄን ይሄን ሲሰማ ትልቅ ግራ ጆሮውን እያከከ በቤቱ አቀማመጥ እንደተደሰተ የአቶ እንግዳን ስም ጠርቶ በደስታ ይስቃል።



@BOOKALEM

(4) የቤቱ(?) አቀማመጥ፡

ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የከተማው ቤቶች የሣር ጣሪያ ያላቸው ነበሩ፡፡ የአባቴ ቀርቀሮ ቤት በሁለትና ሦስት ሣር ቤቶች የተከበበ ነበር፡፡ ዋና መግቢያው በፀሐይ መጥለቂያ በኩል ነው፡፡ የቦዘን ቀን ጠዋት ጠዋት ለስስስ ያለች ፀሐይ ውስጥ አባቴ የጉሬዛ አጎዛ የተነጠፈባት ኩርሲ ላይ እስከወገቡ ድረስ ራቁቱን ተቀምጦ የሚያሳክከውን ጀርባውን እስከ ቀትር ድረስ በእንጀራ እናቴ የማይሰለቹ ጣቶች ይጠቀማል፡፡ እንደ አስተኳሽ እየጮኸ...... «ወደላይ!......ወደታች!......ወደጐን!......ከፍ!ከፍ!ዝቅ!......አ!......አ!......አዎ! ......»፡፡ እከኩን ሲያፈርጥ ያረፍዳል፡፡ በመሃልም ይዳራታል፡፡ ቂጧ መተምተም ሲሰለቸው «ኸረ ምሳ አልሰራሁም» እያለች በመግደርደር ወደ ማድቤቷ ተመልሳ ትሄዳለች፡፡ እኔ ደ'ሞ ሰው ሆን ብሎ በየጓዳው በየጓሮው ተመቻችቶ ፀሐይ ሲሞቅ ይገርመኛል፡፡ ፀሐይ እኮ የትም ትገኛለች......

እቤታችን ፊት ለፊት እንጀራ እህቴ የተከለቻቸው አበቦች ነበሩ፡፡ ከአበቦቹ ጀርባ አጥሩን ታኮ ረዣዥም ፅዶች በሰልፍ ተተክለዋል፡፡ የሚገርመው ነገር እነዚህ ፅዶች ላይ ወፎች ጎጆ ሲሰሩ አላየሁም፡፡ ከቤቱ በር እስከ አጥሩ በር ድረስ ትላልቅ ድንጋዮች መሬት ውስጥ ቢያንስ ስንዝር ያህል ድረስ እየተቀረቀሩ ለክረምት ጊዜ መረማመጃ እንዲሆኑ ተነጥፈዋል፡፡ ለባዶ እግሬ ጭቃውና ሣሩ የበለጠ ስለሚመቸኝ እኔ ረግጬአቸው አላውቅም፡፡ ቁጥር ካስፈለገ የድንጋዮቹ ብዛት ሰባት ነበር፡፡ የመጀመሪያውን አለት ወደ ግቢው በር የሚጠጋውን፣ ከበር የመሰለውን በጣም ነበር የምጠላው፡፡ በተለይ ማታ መጥቼ በጨለማ የአጥሩን በር ስከፍት አፈር ለብሶ እንቅፋት እንደ ሆነብኝ ነበር፡፡

ከ«ቤታችን» ፊት ለፊት ለቆመ ሰው ደሞ ራቅ ብሎ የሚታየው የጎለልታ ተራራ ነው፡፡ በጀርባም እንዲሁ የጉና ተራራ ሰንሰለት ልጥልጥ ኑግ መስሎ ይታያል፡፡ ክረምት ክረምት ያኔ ጉናን እፈራዋለሁ፡፡

በስተቀኝ አቶ በቀለ፣ በስተግራ አቶ እንዳይላሉ፣ በስተጀርባ ጀርባውን ወደ እኛ ቤት የሰጠ ወ/ሮ አሰገደች የሚባሉ ባላቸው የሞተባቸው ሴት የሚኖሩበት ሰቀላ ከመሃል አነስተኛ የጋር አርሻ ነበረችን፡፡ ክረምት ግው ሲል በዚህ አርሻ በቆሎ፣ አተር፣ ነጭሽንኩርት የመሳሰለ ይተከልበታል፡፡ በጋ በጋ የገላ መታጠቢያ፣ ቆሻሻ መጣያ ነበር፡፡ ቆሻሻ መጣያው ዘንድ ቀትር ቀትር አትሂዱ እንባላለን፡፡ «ምናምንቴው እንዳያገኛችሁ» እየተባልን፡፡ ስለዚህ ምናምንቴ ሳስብ የሚገርመኝ ሹል አፍንጫ፣ ሹል አገጭ፣ ሹል ዐይኖች፣ ጠባብ ግንባር፣ ረዥም ነበጥ ያለ አፍንጫ፣ ጠማማ ቅንድቦች......እና ተራርቀው የተተከሉ በመሐሳቸው ምላስ የሚያሣይ መንታ የጥርስ ሰልፎች ያለው ሰው ይታየኝ ነበር፡፡ ቀንድ ሲኖረውም



@BOOKALEM

ይችላል:: እዚያ ንፋስ መውጫ ዘመዶቹን ሲጠይቅ(ጠሳ ሻጥዋ ዘመዳ ናት)ከዩንቨርሲቲ የመጣ አንድ ሰው ሲያወራ ነበር እሱ አባቱ ጋ ፀጉሩን ሲስተካከል መጥቶ «ፈረንጆች አገር የብዙ ቤቶች እርዝመት ከዚያ ይበልጣል» ብሎ ወደ ጎስልታ የተራራ ጉብታ እየጠቆመ አሳይቶአቸው በከተማው ሲያስወሩለት ነበር::

አባቴ ኮስተር ብሎ ታዲያ: «እንዲህ እንዲህ ከጎስልታ የረዘመ ቤት ከበዛማ የፈረንጅ ቆስና የሰውም ማለት ነው» ሲል ነበር::

(5) ጎስልታ:

በስተፀሐይ መጥለቂያ ካለው የኩረብታ ሰንሰለት ጀርባ የአንድ የሚያስገርም ተራራ ጫፍ ይታያል:: ይሔ ተራራ እንደሌሎች ብዙዎች ሠፊና የተንዛላዘለና ቦርጫም አልነበረም:: ጠባብ፣ በቂጡ እንዳረፈ ሽብልቅ የቆመና የሾለ ነበር:: እንደሚያወሩት ወደ ጫፉ ለመድረስ ያለው ምንገድ አንድ ብቻ ነበር......እዚያ ላይ ከወጡ ጠቅላላ «ጦቢያን ማየት ይቻላል» ይላሉ......:: ሰው ሲያወራ እንደሰማሁት እርቆ በሚያሳይ መነጥር እቶ ማን ናቸው ስማቸው ጠፋኝ የአዲስ አበባ ከተማ ወጋገንንና ቀይ ባሕር አሣ የሚያጠምዱ ጥቂት አፋሮችን ከነጀልባቸው አይቻለሁ ይላሉ:: ደቦና የሚባል የጣሊያን ጄኔራል በንፋስ መውጫ በኩል ሲያልፍ ሰዎች ስለዚህች ስለጉስልታ ጉብታ አጋነው ቢነግሩት ሀበሻን ከነጉጆው በያለበት አጠቃልዬ በመነጥሬ ልየው ብሎ ይወጣና እሱ መቀለዱ ይሁን መሳደቡ ጉስልታ ጫፍ ላይ ሱሪውን አውርዶ ይጠዳዳና ይመለሳል......ታዲያ ሲጠዳዳ መቀመጫውን ወደ ሮማ አዙሮ ነበር አሉ:: ከብዙ ጊዜ በሁዋላ ይኼ ወሬ ተሰዋውሮ ጣሊያን ተራራው ላይ ብርና ወርቅ ደብቆአል......ስከፉ ቀን ሲያደርገው ተብሎ ሁለት ሰዎች ወጥተው ቢያዩ ያገኙት ነገር ቢኖር የደረቀ የፓስታ ዐይነምድርና የጣሊያንኛ የጋዜጣ ቁራጭ ብቻ ነበር:: ብዙ ጊዜ ታዲያ እኔ በታሪኩ ሳይሆን በጎስልታ ቅርፅና ግዝፈት በአምፖሊ እንደማደርገው የማየት ጨዋታ እጫወት ነበር:: ፀሐይ ስትጠልቅ ጎስልታ ረዥም ቀጥን ጥላሞት እኛ ቤት አይድረስ እንጂ በምናርበት አቅጣጫ ይጥላል:: ክረምት ክረምት ጉስልታ ጫፍ ላይ ነጭ የደመና ባርኔጣ ብዙ ጊዜ አያለሁ:: እንዝርት ይመስለኛል:: ለእኔ ጉስልታ ለዓይኖቼ አስማት ነበር:: ማየት፣ ማየት፣ ማየት::

ወርቅና ብሩ አልገኝ ሲል ሰዎች በራሳቸው ቂልነት መሳቃቸው ነበር መሰል: «ደቦናን እኮ ብዙ ሰዎች እዚህ የሚያውቀት በነፍስ እሱ:: እሱ ምኑን ወርቅ ይተዋልና ቅልጥ ያለው ጮሌ አይደለም እንዴ!» ይሉ ጀመር:



@BOOKALEM

## (6) ጨሴዎች:

ከተማው ውስጥ በጣም ደጋግሞ የምሰማው ቃል «ጨሴ» ነበር:: ጨሲ ማለት እንግዲህ ብልፕ ማለት ነው:: ጨሴ ለማታለል ብቻ የሚያታልል ማለት ይመስለኛል:: ሰው ለመጉዳት ብቻ የሚያታልል ይመስለኛል:: እኔ ጨሲን 'ሳንሳ ግባ' ዞር የምለው:: አራዳ አይጉዳም:: ሙስጠፋ ያው አራዳ ነበር:: አራዳ መሆን ከባድ ነው:: ጨሴ መሆን ቀላል ነው:: ጦጣ ለምሳሌ ጨሴ ናት:: ታዲያ ለምን 'ጨሴ' የሚለው ቃል (መልካም ቃል ከሆነ) ለእግዚአብሔር፣ ለማርያም፣ ለመድሐኒያለም፣ ለመሐመድ ሰዎች ለምን አይጠቀሙበትም ነበር?

"ማርያም ወይም የከተማዋ አድባር ጨሴ ናት" ማለት የሚፈልጉ ቢኖሩ ባለጌ ያደርጋቸዋል::

## (7) የአድባር ዛፍ:

ከቤታችን በስተደቡብ ሁለቱ የተራራ ሰንሰለቶች መካፈቻ መሿለኪያው ላይ ትልቅ የሾላ ዛፍ ነበር:: ለብቻው ዠንጥላ መስሎ ካገር ወዲያ የሚታይ:: በማርጀቱ ፍሬ ማብቀሉን ያቆመ:: የድሮ የድሮ አገዎች አድባር ነበረች ይባላል:: እንደ ወሬው ዮዲት የምትባል ንግሥታቸው አክሱምን ለማጥፋት ስትሔድ አርፋበታለች ይላሉ:: ጣሊያን ሲመጣ ሕዝቡ ለእስዋ እተሳለ ስለሸፈተ በቂም ተጉና ተራራ ሆኖ በመድፍ ሲመታት እስቦ አልሆነለትም ይባላል:: ይተኩሳል መሳት፣ ይተኩሳል መሳት:: በሁዋላ እዚያው ወረደና ካምፕ አድርጉ ጥላዋ ስለጠቀመው ተዋት እንጂ ይላሉ:: ግንቦት ሲገባ ታዲያ ቂጣና ቆሎ፣ ጠላ በገንቦ ይዞ፣ ጥቁርና ነጭ በጉች እየነዱ ወደዚያ መሔድ የተለመደ ነበር::

ለማንም ግልፕ ባልሆነ ምክንያት (አንዳንድ አሹዋፌዎች «ፍቅር ያስያዛቸውን የልጃገረድ ከንፈር የሳሙት እዚህ ስር ስለሆነ ነው» ይላሉ:: አንዳንዶቹ ደሞ «ሐብታም የመሆን ሚስጥሩ የተነገራቸው እዚያ ስር በቀትር አርፈው ለነበረ ጊዜ ነው» ይላሉ) ከዛፏ ጋር ልዩ ፍቅር የነበራቸው የሙስጠፋ አባት ሐጂ አብዱራህማን ነበሩ::

## (8) ሐጂ:

ከሐጂ ሁለመና የሚማርከኝ ነገር ቢኖር ቆባቸው ነበረች:: የዚያች ዓይነት ቆብ እንዲኖረኝ ብዙ ጊዜ እመኝ ነበር:: ነጭ ሆና እንደ መስታወት ትፈልቃለች:: አንዳንድ ጊዜ ቆቧ የተሠራችበት ጨርቅ ሱሪ ቢሠራ እያልኩ አስብ ነበር (ስለ ጨርቅና ስለ ሱሪ ብዙ ባላውቅም):: ሐጂ እስላም ቢሆኑም በአባቱ መድሐኒያለም ዝክር በእናቱ የማሪያም ዝክር ቀርተው አያውቁም:: ጥርሶቻቸው በጣም ነጭ



@BOOKALEM

ነበሩ። ባርኔጣቸው ከጥርሶቻቸው ወይ ጥርሶቻቸው ከባርኔጣቸው የተሰሩ ነበር የሚመስሉት። ከአባቴ ጋር ድሮ ተቀያይመው ነበር ሲሉ እሰማለሁ። በወላጅ እናቴ። እንግዲህ ወላጅ እናቴ የደላንታ ሰው ናት። ሃጂም ከደላንታ ነኝ በሚል (ሽፋን ነው እሱ ለማማገጫ) እሰዋን ጥየቃ ሲያበዙ ጊዜ ዱቤ (አባቴ) ትቀናና ሐጂን ትገላምጣለች። እናቴ ከሞተች በሁዋላ ግን ነገሩ ተረስቶ ተሻርከው በዝክር ቀን እቤታችን ይመጡ ነበር።

ጥርሶቻቸው ነጫጭ ናቸው። ሙስጠፋ ለእህቴ ደብዳቤ መፃፉ አባቴን ያበሸቀው...... «ሐጂ ምነው በልጃችሁም አስቀቀኝም» ይሆናል፣ መችም ስገምት። ለማንኛውም ሐጂ ቤት መጥተው......ቆሎ ፈጭተው፣ ቂጣ ቆርጠው፣ ጠላ ነፍተው ይመለሳሉ። ታዲያ ብድር ለመመለስ ብለው ሥጋ ያልነካው የእሠላም ምግብ በጣም የሚጣፍጥ እቤት ይልካሉ። እንዳንዴ ነው ታዲያ። ካልሳኩ የሆነ የረመዳን ቀን የክርስቲያን ምግብ ቤታቸው ተሠርቶ መሰለኝ አባቴንና እኔን ይጠሩዋቸው ነበር።

የከተማው በጣም ሐብታም ሰው ነበሩ። መኪና ሁሉ የመግዛት ሐሳብ እሳቸው ይባል ነበር። ሌላ ሁለት ከተሞች ውስጥ ሱቆች ነበሯቸው። ከብት ይነግዳሉም ይባላል። ትልቅ ስሆን የእሳቸውን ዓይነት ቆብ አደርጋለሁ እያልኩ እመኝ ነበር። የዚያ ዓይነት ቆብ ቢኖረኝ መዓት ሴቶች ሳይማልሉልኝ አይቀሩም።

ሐጂ አብዱራህማን በወጣትነታቸው ስራቸው ንግድ መነገድና ሰላ ነበር እሱ። እሳቸው ያልዳበሰዋት ኮረዳ በንፋስ መውጫ አልነበረችም ይባላል።

## (9) ሰሳ:

ያችን ከተማ የሚበጠብጣት ትልቁ ነገር የጅብና የውሻ ሰሳ ነበር። ጅቦች ሌሊት ለድሪያ ሲመጡ ተቀምጠን እናድራለን። ከብት ያለው ከብቱን ሲጠብቅ፣ የቀረነው ግን እኔን የመሰሉት ዕንቅልፍ ተነስተን። የሚገርመኝ እንዴ የማትረባ ጅቢት ለየችና ስንት ሺህ ሕዝብ የሚኖርባት ከተማ ልብ ተሰቅሎ ማደሩ። ለእኔ ግን ጅብ ሲያሽካካ ለሰማ የሚመጣልኝ ነገር አለ። እልፎ እልፎ ከካካታቸው መሐል እንደምታሳግጥ ሴት ድምፅ......እየተሰበቀ የሚወጣ የተሳለ ጦር የመሰለ ድምፅ አለ። እእ ትመስለኝ ነበር። እንዲያውም አንዳንዴ በክረምት ድምፃች (በካፊያና በመብረቅ) ቤቱ ሲረበሽ እእ እነዚህ ጅብ የተባሉት ዘንድ የሔደች ይመስለኛል። ግን ደፍሬ እመኝታ ቤቷ መኖር አለምኖሯን ያረጋገጥኩበት ጊዜ አልነበረም። የጅቦቹ ሰላ ከከተማው ጀርባ ጀርባ ቢሆንም እልፎ እልፎ በዋና ዋና መንገዶች ላይ በድፍረት ይወጣሉ። ውሾች ግን የማይገቡበት አልነበረም። ከሰዎች መቀራረባቸውና መጠጋታቸው ትዕቢት ይሰጣቸዋል መሰለኝ እጥር እየሰበሩ፣ በጊር



@BOOKALEM

ላይ (በደረሰ ሽንብራ፣ በደረሰ አተር ወዘተ) ይረማመዳሉ፣ ይዳራሉ፣ ይጠቃቃሉ......አንዳንዴ ቅክክ ብለው በየሰው ቤት በረንዳ ላይ ሲወዛወዙ ያመሻሉ:: የሚገርመኝ በውሾች ሰላ ላይ ጨዋ የሚባሉ ቤት ተዘግቶባቸው የሚውሉ ውሾች ሁሉ ከጌቶቻቸው እንዴት እንደሚያመልጡ አላውቅም ምላሳቸውን ጉልጉለው ባይችሉበትም ጠንካራ አፕዊ ሲያድቡ አያቸዋለሁ:: ብዙ ጊዜ ልብ ሳልል ቀርቼ ይሆናል እንጂ የውሾች ሰላ ክረምት ላይ የሚበዛ ይመስለኛል:: ከእንቁራሪቶችና ከዝናቡ ጩኸት ሌላ የማይገለው ውሾች እየተናከሱ ሲጯጯሁ ነው::

ዝናብ ባልወድም አልፈራውም:: ከክረምት ድምፃች (ነጐድጓድ፣ መብረቅና ሌሎች) ግን የሚያስጠላኝና የሚያስፈራኝ ሰላው ነበር::

## (10) የክረምት ድምፃች:

ክረምት ክረምት የዝናብ ድምፅ ብቻ ሳይሆን በተለይ ከባድ ዝናብ ሲጥል ከሰኔ መጨረሻ ጀምሮ ከጉረቤታችን ከአቶ በቀለ ግቢ ለሽንት ቤት ብለው የቆፈሩት ጉድጓድ ውሐ ሞልቶት ዕንቁራሪቶች ይረቡበትና ከምሽት እስከ ንጋት ከላይ በዝናቡ ከታች በእንቁራሪት ደንቁረን እናድራለን:: እንደ አባቴ እምነት ግን እንቁራሪቶቹ አንዳንድ ጊዜ እንደ እንቅልፍ ማስተኛ ዘፈን ያገለግላሉ:: (ዝናብ እያካፋ የቤቱን ጣሪያ ሲገርፍ የእንቁራሪቶች ጩኸት ከሩቅ እንደሚመጣ የክራር ድምፅ ይሰለስልና የተሸፋፈንኩበትን ካቢም ፓሶ ገብቶ በጆሮዬ ሲንቆረቆር ......እእምሮዬ ውስጥ ሲፈስ ስትረበሽ የዋለችው የልጅ ነፍሴ ዕረፍት ይሰማትና ዕንቅልፍ ጠርጉ ይወስደኝ ነበር)

«የወሰን አባት ገ/መንፈስቅዱስ ሲያወሩና እነዚህ እንቁራሪቶች ሲጮሁ የሚረብሹ ይመስላሉ እንጂ ያስተኛሉ» ይል ነበር አባቴ::

## (11) ገ/መንፈስቅዱስ:

የወሰን አባት ናቸው:: እሳቸው ለሠርግ፣ ሰው ሲሞት፣ ሰው ሲታመም ስለማይመጡ ሰው አይቀርቡም እየተባለ ይታማሉ:: ሲራመዱ እጅግ ቀሰስተኛ ነበሩ:: መቸም መቸም ጭንቅላታቸው ላይ የሚያስቀምጡት ባርኔጣ አያጡም:: ሲናገሩ እንደ ህመምተኛ ነበር:: "ገመምተኛው" ይባላሉ በቅፅል ስማቸው:: እኔ ብዙ ጊዜ የማያቸው እሁድ እሁድ ቤተክርስቲያን ተሳልመው ሲመለሱ ነበር:: ሲሄዱ ሳይሆን ሁልጊዜ ሲመለሱ ነው:: ያውም ጉብታዬ ላይ ከተቀመጥሁ:: አልፎ አልፎ ከወሰን ጋር አያቸዋለሁ:: ዝም ነው:: "ገብሬ ተጫወት እንጂ......እየበሉ እየጠጡ ዝም፣ የጋን ወንድም ሆንክ እኮ" ይሏቸዋል:: ስለ ጋንና ተሸሉት ከአልጋው ስለተነሳ ገመምተኛ ሲወራ ትዝ የሚሉኝ ገ/መንፈስቅዱስ ናቸው::



@BOOKALEM

አንዳንዴ ደ'ሞ ያ የእግዚር ሰው! ይሏቸዋል:: የትኛውን መምረጥ እንዳለብኝ ግን አላውቅም:: ቅፅል ሥም ከሥም ሳይከብድ ይቀራል?

ብዙ ጊዜ የሚያዋሯቸውና ጆሮ የሚያውሱአቸው ንስሐ አባታቸው ናቸው:: ለነፍሴ ብለው ይሆናል::

## (12) የንስሐ አባት:

አባቴና የእኔ የጋራ የንስሐ አባት ነበራቸው:: ለመድሐኒያለምና ለማሪያም ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለፋሲካ፣ ለገና፣ ለእንቁጣጣሽ እቤታችን ይመጡ ነበር:: ጢማቸው ሁልጊዜ ይገርመኛል:: ጥንቅላታቸውም ይገርመኛል:: ጢሙ-ጉፈር፣ ጥንቅላተ-መላጣ ነበሩ:: ታዲያ በመጡ ቁጥር ጋቢያቸውን ገለብ ያደርጉና አቧራ የመሰለ ቁምጣቸው ያልጋረደውን ጉልበታቸውን እንድስም ይጠሩኛል::

ንሥሐ! ማለት ግን ያን ጊዜ ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር:: አባትና እኔን የማይመከሩአቸው ነገር አልነበረም:: ለምሳሌ......ልጅን ገርፎ ተቆጥቶ ማስተማር ነው:: ምን አገባቸው? ጢማቸው ግን እስከ ዕንብርታቸው መድረስ ብቻ ሳይሆን......የሚያምር የሸበት ሪጋ ነበረው:: እኔ እግዚያብሔርን ብሆን ኖሮ ጥንቅላታቸውም ላይ ሌላ ጎፈሬ አስቀምጥና እፍሮ አደርጋቸው ነበር:: ታዲያ ይሔን ጢም ብዙ ጊዜ ልነካው እፈልጋለሁ:: ሲነኩት ምን ምን እንደሚሰማ ማወቅ እፈልጋለሁ:: ታጥዶ ስጥሩ ሽማኔ ቢሰጥ ኖሮ......ለክረምት የሚሆን አንድ የሚሞቅ ቡልኮ ሳይወጣው አይቀርም::

ታዲያ ያንን ሰብሺ አዲስ አባ ደጋ ነው እሱ አዲስ አባ ስሄድ እለብሰዋለሁ፣ የአዲስ አባም ነገር ካልሆነ በማንም ያልተበገረውን ሳንሳ ገደልን ለመውጫ ገመድ እፈትለዋለሁ እያልኩ አስብ ነበር::

## (13) ሳንሳ ገደል:

ከጉና ተራራ ስር ከእኛ ቤት ጀርባ ሆኖ የሚታይ ትልቅ ደረቱ ፍው ብሎ ደሚታይ ገደል ነበር:: ሳንሳ ገደል ወይም አቦ ገደል ይሉታል:: ነጭ ነበር:: ከስሩ ቆመው ሲያዩት ገደሉ በሰው ላይ መጥቶ የሚገለበጥ ይመስላል:: በታሪክ እንደሚወራው አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ሰይጣንን ገደሉን መውጣት ተፎካክረውት አሸንፈውት ነበር አሉ:: ታዲያ እዚያ ገደል ላይ እንኳን ሰው ዕባብ እየተንፏቀቀ መውጣት አይችልም ሲሉ ሰምቻለሁ:: ግልብጥ ያለ ነገር ነው እኮ:: እኔ ነፍስ ሳውቅ ለማር ቆረጣ ገደሉ ላይ የወጡ ሁለት ሰዎች እንደሞቱ ሰምቻለሁ:: ሬሳቸው ከተማ የገባ ዕለት ጉብታዬ ላይ ነበርኩ::



@BOOKALEM

ታዲያ ሰዎች ሲራገሙ "ሳንሳ ግባ" ይላሉ:: እንደ "ጀሐነም ግባ" ማለት ሳይሆን አይቀርም:: ሐሜተኛ እንደሚለው መልካም እግር ያስፈልጋል ሳንሳን ለመውጣት፣ ግን የንፋስ መውጫ ሰው ብዙው በሞያሌ ስለተንሻፈፈ አይችልበትም::

አንዳንድ የነፋስ መውጫ ሰዎች «ሳንሳን ሰጥቶ ሞያሌን ሰጥቶ ገደል ውጡ ብሎ ነገር ምንድነው?» ይሉና በሳቅ ይፈርሳሉ::

(14) በሞያሌ:

ሞያሌ ስል ይኼ ኬንያ ወሰን ያለውን የቦረናዎች ከተማ ማለቴ አይደለም:: ሞያሌ ስል ይህቺ የምታሳክከዋን ቁንጫ ማለቴ ነው:: እዚያች የምኖርባት ከተማ ሞያሌ ያልያዘው ሰው ያልነበረ አይመስለኝም:: ጫማ ለበሰ አለበሰ:: እኛ ንፋስ መውጫዎች ስሌላ ዓለም የምናስተሳልፋቸው ቀምነገሮች ቢኖሩ ሞያሌና ገበስ ሳይሆኑ አይቀርም:: ሰዎች ቀን ቀን ይሰራሉ፣ ይማራሉ፣ ያወራሉ፣ ማታ ማታ ይተኛሉ መተኛታቸው የግድ ነው:: አለበለዚያ በሚቀጥለው ቀን ሲሰሩ፣ ሲማሩ፣ ሲያወሩ አይችሉም:: ሞያሌን ያነሳሁበት ምክንያት ብዙዎቹን እንቅልፍ ስለምትነሳ ነው:: ተዲያ ማታ ማታ ጠቅላሳችን እናካለን:: ቀን ብዙ አታስቸግርም:: እንቅልፌን እየሰጠፕኩ ግን በእሷ ቁጥቆጣ እንደመቀስቀስ የምጠላው ነገር አልነበረም:: ሰርቶ ወይም በዕድሉ ሐብታም ሆኖ ልብሱን ከቀየረ፣ ቤቱን ካሳመረ "እከሌ ሙጀሌውን አራገፈ" ይባላል:: ያደግንበት ዘይቤ ነበር:: ከሌሎች ከተሞች የሚመጡ፣ ከተማችን ዙሪያ ያሉ ገበሬዎች ሳይቀሩ እንዲህ ይሉናል:......

"የእናንተን ሰው ኪሱን ፈትሸን እናውቀዋለን"

"እንዴት?"

"እኪሱ ውስጥ ወስፌ አይጠፋም"

"ለምን?" እንላለን ቢገባንም::

"ለሙጃሌው"

ጉለልታን ለፈረንጆች ሲያስጉበኙ አብሬ ካልመጣሁ ብለው የወረዳው አስተዳዳሪ እግራቸው ተሰብሮ መጡ:: ግራ እግራቸው:: ምነ ሲባል ገደሉ መሃል ወገቡ ሲደርሱ ማከክ ጀመሩ......ታዲያ ልባቸውን ስተው ቢጥላቸው ሁለት የገደል አርከን ወረዱ:: ዕውነት ይሁን ውሸት አላውቅም......አሁን አሁን ሰልጥኖ ቀለል አለ እንጂ ድሮማ ድሮማ እጅግ ብዙ ሰው በእሷ ይያዝ ነበር አሉ::

በአፈ--ታሪክ ሙጃሌው ከሱዳን በረሐ ነበር መጣ የሚባለው:: ጥንት ጥንት:: ከ600ና 700 ዓመታት በፊት:: አንድ የሱዳን ገዢ ነጋዴ ተመስሎ ጉንደር ይገባል:: በፀጉረ ለውጥነቱ ሲጠረጠር ጊዜ አዳል የምጠይቀው ዘመድ አለኝ ብሎ



@BOOKALEM

ወሎን ከመሻገሩ በፊት በትንሽ ቀረጢት የያዛቸውን የሙጃሊ ቀንጫዎች ዛሬ የከተማዋ መሐል የሚገኝበት ቦታ አራግፎአቸው ሔደ ይባላል:: እንደ እሱ ግምትማ ደሳሉ በሰባና በመቶ ዓመታት ውስጥ ንፋስ መውጪያና ዙሪያዋ ያለው ወንድ እግሩና እጁ በሙጃሊ ተንቀርፎ ጦር ሲመጣ መመከት አይችልም ብሎ ነበር:: በዚህ ስለሚተረቡ ነው መሰለኝ ዘፈን ነበራቸው እንዲህ የሚል ግጥም የከተተ:

*እግር ለሰኝ ብለሽ አትበይ ደንበር ገተር*
*አያውቅም ማን አለ ንፋስ መውጫ ማፍቅር*

በከባድ የታመሙት ልጆች ብዙ ጊዜ ወደ ወንዝ እየተነዱ ሔደው እንዲወጣላቸው ይደረጋል:: «ውሐው ይወስድላቸዋል» ተብሎ::

ልጃገረድ ሴቶች በእምነት ታች ሁለት ፍቅረኛች ተከታትለው አሞቱበት «ሻግዬ» የተባለው አዙዋሪት ዳር ይነቀላሉ:: የወደፊት ትዳራቸውን ያሰምርላቸዋል ተብሎ ነው እሱ:: በዚያ ግዛት ለወንዝ አዟሪት ስም የተሰጠው ንፋስ መውጫ ብቻ መሰለኝ::

(15) ሻግዬ/ልብማ:

ቻች ያለው ወንዝ አንድ ታላቅ አዙሪት ነበረው:: «ሻግዬ» ይባላል:: ክረምት ክረምት ወንዙ ዳርቻ ቀሞ ሳዳመጠ አዙሪቱ እየተሽከረከረ ሲያጓራ እያጉዋራ ሲሽከረከር ባር ባር የሚያሰኝ ግርማ ያወጣል:: አግበስብሶ ያመጣውን ግንድና ከብት አንዳንዴም ሰው እያገላበጠ ወስዶ በዚያ በሚሽከረከር ቀዳዳ ሲዶለው ጉድ ጉድ ያሰኛል:: ያባባል:: በጣም ያባባል:: ሰዎች ስለዚህ አዙሪት የሚነግሩት ተረት አላቸው:: ተረቱ እንዲህ ነው:: አንዲት የመኪንንት ልጅ ከደበናንሳ የሚወስድ ጎረምሣ ገበያ መሐል ታይና ትወደዋለች (ያን ጊዜ ንፋስ መውጪያ አገር የመሰከረላት የሸክላ ሥራ ትሰራ ነበር እሱ) በገበያ በገበያ ዕለት ታዲያ እየደጋገመች እየመጣች እየተመላለሰች እንደምትወደው ታሳየዋለች:: ያን ጊዜ መችም መኳንንትና ደበናንሳ በምንም በምንም እንዲገናኝ ማንም አይፈቅድምና ቢወዳትም ምንም ሲፈፐር እንደማይችል ስለገባው ችላ ይላል:: እሷ ግን ሙጭጭ ብላ የፍቅር ነገር ነዋ:

*አንተ ሻግዬ አንተ ልብማ*
*ሸክላህን ትተህ ለቅሶዬን ስማ::*
*መኳንንትነት ይኸው ተረታ*
*በማሰሮ ሺያጭ በዚያ ዘንካታ::*
*ሸክላህን ትተህ ልቅሶዬን ስማ*
*አንተ ሻግዬ አንተ ልብማ::*



@BOOKALEM

እያሰች ብቻዋንም ሰው እየሰማትም ትዘፍን ነበር አሉ:: ይኼን ታዲያ አባቷ ይሰማና ቀጣ ቀጣ ብሎት ፈረሱን ጥና ከጉና (ጉና ነበር አሉ የሚኖሩት) ንፋስ መውጪያ ይወርዳል:: በገበያ ዕለት:: ማንን ያገኛል አጠያይቆ የልብማን አባት:: (እውነተኛው የጉረምሳው ሥም ስለማይታወቅ ወይም ስለተረሳ «ሸግዬ» ወይም «ልብማ» ነበር የሚባለው) ታዲያ የልጅቷ አባት ልጃቸው ከማበዷ በፊት ሲድሯት ሐሳብ ነበራቸውና ለፍተሻ ብለው የሸግዬን አባት ያስፈራሩታል:: ደፋር ወንድ ይወዳሉና:: የሸግዬ አባት መች ንቅንቅ......እንደውም ቆጣ ቆጣ ማለት:: የልጅቷ አባት «በል ልጅህ ዘንድ ውሰደኝ» ይሉና በልባቸው የተሰማቸውን ደስታ ደብቀው ተያይዘው ጉዞ ጀምረው ትንሽ ምዕራፍ እንደሔዱ የልጁ አባት ልፀዳዳ ብለው ሸሸት ይሉና ለአንድ ሁነኛ ገደኛቸው ልጃቸው ልብማ ዘንድ ሔዶ ለልብማ «የዚያች ቀንጆ አባት እሳት ለብሶ እሳት ጉርሶ መጣልህ የሚደረገውን አድርግ ብለህ ንገርልኝ» ይሉታል:: ገደኛቸውም ቀደም ብሎ እየገሰገሰ ሄዶ ለጎረምሳው «አባቷ መጡልህ» ይለዋል:: ይህን ሲሰው ይደነግጥና ለማምለጥ ጉዞውን ሲጀምር ከደጋ ዝናብ ጥሎ ኖሮ ወንዝ ይሞላል:: ታዲያ ወደ ሁዋላ ተመልሼ እንደምንም ዋድላ አባቴ ዘመዶች ዘንድ ልሒድ ብሎ ፊቱን መለስ ሲያደርግ፣ የወንዙ ውሐ ልክ እንደ ሰው የሚፈስበትን ምንገድ ትቶ ወደ ልጁ ይወርድና ዘግኖ ወስዶ አዙሪት ውስጥ ይከተዋል:: ከበስተላይ የልጁ አባትና የልጅቷ አባት ለካስ ሲደርሱበት ኖር እሳቻ ዳገት ላይ ቆመው ይሄን ተአምር ያዩ ኖሯል:: ጉድ ተብሎ ጉድ ተብሎ የልብማ ሬሳ ተፈልጎ ታዝኖና ተሰቅሶ ይቀበርና ጥቂት ቀኖች እንደቆዩ ገና አርባውም ሳይወጣ ልጅቷ ከምትኖርበት ዙሪያ አገር ገና ከመንጋቱ በቅሎዋን ጥና መጥታ ሸግዬ የገባበት አዙሪት ዘላ ትገባለች:: ምድረ አዳምና ሄዋን እያያት:: ያኔ ትዘፍነው አትዘፍነው አይታወቅም እንጂ እንዲህ ብላ ነበር አሉ:

*የዐይኖቹን ልጅነት በሰንባዬ ከምገፍ*
*ሸጌ ተከትዬህ ካንተ ጋር ልረፍ::*
*መውደድ የማያውቀ ወሬ ያበዛሉ*
*ወደደች፣ ወደደች፣ ወደደች እያሉ::*
*አንቺ ማርያም እይ ሰው ያደረገኝን*
*መድሐኒያለም እይ ሰው ያደረገኝን*
*አኔንም እንደሱ ውሐ ያስጠማኝን::*

የተረቱ ሞራል:......

(1)ፍቅር ያጳጅላል (ከልጅትዋ ድርጊት)

(2)ከአፈቀርክ አትፈርጥጥ (ከልጁ ድርጊት)



@BOOKALEM

ፍቅረኛ ከሆንክ እንደ በሳይ ዘሰቀ ያድርግህ ይሳሉ:: ለፍቅር መዋጋት ያስፈልጋል ይሳሉ:: እንደ ልብማ ያሰ ፈሪ በአሂሪት ይታወሳል እንደ በሳይ ያሰ ወንድ በማይፈርስ ድንጋይ ሐውልት ይቆምለታል ይሳሉ::

## (16) የበሳይ ድንጋይ:

የበሳይ ድንጋይ ወንድ አደወሰድብሽ ሜዳ ሳይ ከከተማው በስተምስራቅ፣ ከሚሸኖቹ ቤተክርስቲያን በስተቀኝ፣ ከዋናው ምንገድ በግምት ሁለት ኪሎሜትሮች ያህል ርቆ የሚገኝ ትክል ድንጋይ ነው:: በጎኑ በግምት ሃያ ሜትር ይሰፋል፣ ወደ ሳይ ከፍታው ሰባት ሜትር ይሆናል:: ግምቱ ነው:: በአፈ-ታሪክ ግራኝ ከጉና ተራራ የማርያምን ቤተክርስቲያን ለመምታት የወረወረው ነበር ይባላል:: ድንጋዩን ቆፍሮ አወጣው ወይስ ተቀምጦ አገኘው? እኔ ድንጋዩን ሳየው ትዝ ይለኝ የነበረው በመቶ የሚቆጠሩ ደማ የያዙ ቆፋሪዎች ነበር:: ለፖሊስ ስልጠና ከንፋስ መውጫ ለሰናበት ወንድ አደወሰድብሽ ሜዳ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ ሲለወጥ ነው ተብሎ በደንብ ይወራ ነበር:: ይህቺ ትንሽ አይሮፕላን የለችም? ሣርና የመሳሰለ ሳይ የምታርፈው? ለፓይለቶች ምልክት እንድትሆን ወንድ አደወሰድብሽ ድንጋይም ነጭ ቀለም ተቀባች:: አይገርምም? ንፋስ መውጫ በአብዮቱ ልትለወጥ ነው እየተባለ ሲወራ ነበር:: መሃል መሃሉን ሥራ የፈታ የከተማዋ አዝማሪ ለሰበሳይ ድንጋይ ይህቺን አለ አሉ:......

*አገር ዳኖ ሆነ አገር ቀሳ ቢሉት*
*እሱንም ነጭ ቀቡት ወተት አስመሰሉት*
*ንጠን ንጠን ብናይ ምነው አገዋት ሆነ*
*የበሳይ ጉብታ ከሳም መሰለ*

እግሩን አያነሳ ውሸኛ እየሸናባት እንዳልኖረ:: በሳይን ማደናነቅ የጀመረው ዘግይቶ ነበር:: ሲሸሽ እንዳልኖረ:: መተቃቀፍ ሽሽቶ በአዝማሪ አፍ መነካካት ሳይሻል አይቀርም ብሎ:: ከመሆን ይልቅ ለንክኪ የሚንሰፈሰፍ::

## (17) ንክኪ:

«የተነካካ» ሲባል እሰማለሁ:: የሆዷን ነገር እንደ ማንም ሆዷን ይመዘምዘኛልና:: በተናጋሪው ጠባይና ዐይን የሚወሰን ነው:: ለምሳሌ እንጀራ እናቴ የንፋግነት፣ የግብዝነት፣ የአድልኦነት፣ የጨካኝነት ምልክት ትሁን እንበል:: «ደሄ የነካካውን ብሳ» ትለኝና (እሷ የማትፈልገውን፣ እሷ የምታሸሸውን) ምን የመሰለ የተቆራረጠ፣ የመጀመሪያ የልደት በዓሉን እሷና አባቴ ጣቶች ስር ያሳለፈ ደረቅ እንጀራ ትሰጠኛለች:: ስም ተሰጠፈበት እንጂ የተነካካ አልነበረም:: ጉልበቷን



@BOOKALEM

ተጠቅማ ስም ትሰጥፍበታለች:: የተነካካ ማለት በእሷ አባባል የእንጀራው ሰበከት ሳይ ሁለት ቀዝቃዛ ምስርች ወይም ክኮች የተሰጠፉበት (እነሱም አንዳንዴ እንጀራውን ስመብሳት ስዘረጋውና ስጠቀልለው እየተፈናጠሩ የሰፌድ ረጋ መሃል ወይም ጉልበተኛ ከሆኑ ተፈናጥረው የቤታችን እቱና ሳይ ያርፉ ነበር) ከሆነ በእርግጥ የተነካካ ነበር:: ለእኔ የተነካካ ማለት ወጥ እንደ ልብ ሳይሆን ግን ለማላመጥ የማያዳግት ለመዋጥም የሚስብ ለሃሣ ማለት ነው:: ለለሒ መለሒ ይሁን ማለቱም አይደለም):: ግንባሬ ሳይ ንቃትና ቅሬታ ካነበበች፡ «እየው እኔ ስበላው» ትለኝና እንጀራ ቀንጥራ አፏ ታስገባለች:: ያኔውኑም ወደ ማድቤት ትሄዳለች:: (ወይ ባለብዙ ልጋግ ናት:: ወይ በሳዩ ወጥ እንደ ሻይ ፋት ትልበት ይሆናል)

ታዲያ ሙሰጠፋ ንክኪ ሲለኝ የቸገረኝ እንጀራው ማን እንደሆነ ወጡስ ማን እንደሆነ መለየት ነበር:: እኔ ነኝ ወይስ ኤልያስ እንጀራ? ሃሳብ እንደወጥ ሰው ሳይ ይነካካል? ኤልያስ ወረቀት በትን ሲለኝ አስገድዶኝ ወይም አታሉኝ አልነበረም:: ገና ሲጀመር በመንደር ሐሳብ እየተነዳ (በንክኪ) እንደ ወሰን የለሽ አሳገለለኝም:: ስለምወደው አድርጌለታለሁ:: ሆንኩ እንጂ አልተነካካሁም:: ይህቺ "ንክኪ" የምትባል ቃል ሰው ከሰው ጋር እንዳይኖር የተፈጠረች ሳትሆን አይቀርም:: የፈረዎች ቦተሊካ:: ከጉንፋን፣ ከቁምጥና፣ ከእከከ፣ ከተስቦ እንደምንሸሸው ከሰው ሐሳብ እንድንሸሽ::

በንክኪ በንክኪማ እኔ እንደ አባቴ ሐብታም እሆን ነበር::

በንክኪ በንክኪማ ሰበታዎች አዲስ አባ ይሆኑ ነው፡

በንክኪ በንክኪማ ቡሬዩዎች አዲስ አባ ሊሆኑ ነው::

በንክኪ በንክኪማ ሸናዎች አዲስ አባ ሊሆኑ ነው፡

በንክኪ በንክኪማ ሱሉልታዎች አዲስ አባ ሊሆኑ ነው::



@BOOKALEM

# ክፍል ሁለት



@BOOKALEM

# ፋሲካ

ከፖሊስ ማሰልጠኛ ተመርቄ ስወጣ ከሌሎች ሃያ ከሚደርሱ ፖሊሶች ጋር አዲስአባ ተመደብኩ:: በግሌ ቤት እስካገኝ አንድ ትልቅ የቀበሌ ቤት በጅጊ ተከራይቼ ገባሁ:: ቀን ከጥበቃ ሥራ ስመለስ.......ኰንትራት ምግብ የምትሰራልን ሴትዮ ቤት ሔጄ ራቴን እበላና ወደ ደቦ ቤቴ እገባለሁ:: አንዱ ቀን ከአንዱ ብዙ የማይለይ ተመሣሣይ ነበር::

ምግብ በኮንትራት የምታበላን ጫልቱ ትባላለች:: የሱሉልታ ቤት (1) ነበረች:: ለእኔ ሁልጊዜ የሱሉልታ ልጅ ትመስለኛለች:: እሷ ቤት ምግብ የምንበላው ፖሊሶች ስድስት ነበርን:: የማንለቅ የተጣበቅን ደንበኞቿ:: አንድ ጊዜ የፋሲካ በዓል ደርሶ ሌሎች ጓደኞቼ ወይም ደባሎቼ (ወይም በተደራረበ ትርጉሙ) ወደ ዘመዶቻቸው ሲሔዱ እኔ ብቻ ቀረሁ:: ማታ ጫልቱ ዘንድ ለራቴ ስደርስ ዶሮ ሰርታ ጠበቀችኝ:: ስለዚህ ዶሮ መሰራት ከእስዋ ጋር ቀደም ብሎ አልተነጋገርንም::

"አንተ ልጅ በዕውነት ዘመድ የለህም?"

"የለኝም"

"ከየት ተገኘህ?"

"ከአፈር"

"ሌላ አዲስ የመጣው ፍልስፍና ነው 'አፈር' የሚባለው እ?......ከዝንጀሮ ለምን አትልም?"

"እህህ......" ሳቅሁ::

"የት ነው የምታድረው?"

"ያው ቤቴ ነዋ!"

"ብቻህን አትሆንም?"

"ጃፓን አለ" (ጃፓን የፖሊስ ራዲዮ ኦፕሬተር ነበር)

"አላድርም አላለኝም?"

"ቢያድርም ባያድርም.......መሔዱ አይቀርም"

"የምትገርም ልጅ ነህ"

"እንዴት.......?"



@BOOKALEM

"እንደ ሌሎች ልጆች ጨዋታም አያሰኝህ.......ጎረምሳ አይደለህም እንዴ?"

"ምን ጨዋታ?"

አልመለሰችልኝም:: ወፍራም ጠላ ቀድታልኝ እግሮቿን ገጥማ የገጠመቻቸው እግሮቿ ላይ ትልቅ ያረጀ ፎጣ ጣል አድርጋ(ምኔን ያይብኛል ብላ ፈርታ ነበር?) ፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: ፋሲካ ያቁነጠንጣል መሰለኝ:: እኔን ምንም አቁነጥንጦኝ አያውቅም:: ፋሲካ ምኑ ያቁነጠንጣል:: ሣር ይጐዘጐዛል.......በግና ዶሮ ይታረዳል.......ሰንቁላል ይበላል (ካለህ ነው ደሞ):: ለሐይማኖት እንደሆነ ብዙ ዐይቻለሁ:: ለክርስቶስ ግድ የሚሰጠው ጥቂት ይመስለኛል:: ፋሲካ ደስታን የሚሰጥ አይመስለኝም:: ሚልቱ......የዋዜማው ዕለት ስለ ኑሮ መወደድ ስታወራ ነበር.......ስትጨነቅ ነበር.......ለሚቀጥለው ወር የምግብ ሒሳብ ብዙም ባይሆን ያው ያቅሚን ልጨምርላት ቃል ገብቻለሁ:: በሆድ ከመዳራት በእሱም ለመበላለጥ ከመሯሯጥ የተለየ አይደለም:: እኔ ፋሲካን ያላከበርኩ:: ፋሲካም ያላከበረኝ::

"ለአንተ ምን ጥሩ እንደሆነ ታውቃለህ?"

"ምን?"

"ጥሩ ልጅ ፈልገህ አግባና ልጅ ውለድ"

እንዳልሰማ ዝም አልኩ::

"ሰማኸኝ?"

"አዎ......."

"እውነቴን ነው.......እንደ እህትህ ልምከርህ......ቆንጆ ልጅ ነህ፣ ጨዋ ነህ.......በልብህ ምን እንደምታስብ ባይታወቅም......ትሰማለህ?.......ሴት ልጅ ስትኖርበት ደስ አይለኝም የምትለው በዓል እንኳን ያምራል"

"በዓመት ስንት ፋሲካ አለ?"

"ስንት ይኖራል:: ያው አንድ ነዋ"

"ለአንድ ፋሲካ ሚስት ላግባ?"

"ነገረኛ ነህ እባክህ.......ዝም የሚል ሰው እኮ.......እንዴ! ሁልጊዜ ፋሲካ ይሆንልሃላ"

መብላቴን ቀጠልኩ::

"ጥሩ ሚስት ልፈልግልህ?"



@BOOKALEM

የጠቀለልኩትን ጉርሻ ይዤ አየሁዋት:: በሐሳቤ የመጣብኝ ሸካራ እጅ ነው.......እንደ ካሊም የሚፍቅ እጅ ነበር::

"ሥራ ከጀመርክ ስንት ወር ይሆንሃል? ሳስተዋውቅህና.......እያት.......ከሆነ ከአንድ ዓመት በሁዋላ ትጋባላችሁ"

ጉርሻዬን በላሁ:: ወጡ በጣም ይጣፍጣል:: ፖሊስነቴ የሰጠኝ ነገር ቢኖር...... ከድሮ የተሻለ ጥሩ ጥሩ ምግብ ነበር:: የማዝበት ገንዘብ ነበር:: ሰው አለመለማመጥ ነበር:: ይሄን የሚሻማኝም ሰው አልፈልግም:: በራሱ ዕውቀት እስከ መዳፌ የሚሳበውን የወጥ ቅባት (ስብ ይሁን ቅቤ ግድ አይሰጠኝም) ከማንም ጋር ልካፈለው አልፈልግም:: ቢመጣስ? በሚስት ስም ሴላ የእንጀራ እናት:: ቢመጣስ? በልጅ ስም ሌላ አባት:: እንዲሁ በነጠላ ሞትን መጠበቅ ነበር የምፈልገው–በነጠላ......እንደ ሞጆ ባቡር ሳልጊተት::

"ጫልቱ.......ጥሩ ሴት ነሽ:: ጥሩ ምግብ ትሰሪያለሽ:: ዛሬ አስበሽ ሁሉ ዶሮ አበላሽኝ.......ግን ማግባት አልፈልግም:: ብቻዬን መሆን ነው የምፈልገው"

ጭንቅላቷን አከከች:: ዕሽም የተሰራው ፀጉሯ ውስጥ ርካሽ ቅባት ነበር:: ፀጉሯ ውስጥ ባለ አንድ ብር ግማሽ ሊትር የሚገዛ ፓራፊን አለ:: ያስበችልኝ ሚስት እንደዚህ ልትሆን ትችላለች (ተመሳሳይ ላባ ያላቸው ወፎች በተመሳሳይ ሰማይ ላይ ይቀዝፋሉ ይባል የለ):: ያቺ ያሰበቻት ሴት ይኼን ቅባት ተሸክማ አብራኝ ትተኛለች:: ጫልቱ ትዳር ያልያዘችው ለዚህ ይሆናል::......በዚህ ቅባቷ ደረቴን ትደገፋለች.......ዩኒፎርሜ ይቆሽሻል.......ታዲያልኝ ቀን በቸርችል ጐዳና......በሜክሲኮ አደባባይ የሚዞረው ተቆጣጣሪዬ መቶ አለቃ ሞላላ አፍንጫውን እየገፋ ይመጣል......."ዩኒፎርምህን የት ጥለኸው ነበር......ኢስፓአኮ ፅህፈት ቤት ድረስ ይሸታል" ሊለኝ ይችላል:: ሚስቴ ብትሆን ጫልቱ......አይደለችም ግን መሆኑ አይቀርም እንዲህ:: እንደ ወሰን ዐይነት ሴት ብትሆን ጥሩ.......ወሰንም ስታድግ እንዲህ ታደርግ ይሆናል:: ታደርጋለችም:: ወንድ ለመሳብ፣ አቧራ ያደረቀው ፀጉሯን ቅባት ውስጥ ዘፍዝፋ.......እንዲተኟት አፏን ቀዳ የምትቀርብ:: ወይ ካልሆነላት እንደዚያች እንደ ጫልቱ እንደ እኔ የተመረረ ጎረምሳ የምትመክር:: ቢያዳልጠው ሊወድቅላት.......ለእሷ ሊወድቅላት::

"አንድ ነገር ልጠይቅህ?"

"ምን?"

"አትቀልድም.......ቀልድ አይደለም"

"ምን?"

"ለመሆኑ ሴት ታውቃለህ?"



@BOOKALEM

"ታዲያስ.......ብዙ"

"አይመስለኝም"

"ያንቺን ግምትና፣ ጥርጣሬ እንድመልስልሽ ነው የምትፈልጊው?"

"ጊደኞችህ እንደዚያ አላሉም"

"ሴት ጊደኛዬን ይገዬ ነው የምተኛው?"

"አልወጣኝም.......ምን ይታወቃል.......እንዳልከው የምትምርህ ሴት አትኖርም"

ዐይኖቿ ሲቀልጡ አየሁ። እነኝያን የመሰሉ ዐይኖች ድሮ አይቼአለሁ። ፖሊስ ሆኜ ከመምጣቴ በፊት ንፋስ መውጪያ አልቬቲ ፊት ላይ።

"ቡና ላፍላ?"

ድምጿ ትንሽ አስፈራኝ። ጫልቱን የማውቃት.......ምግብ ሰርታ እንደምታበላኝ ሴት ነበር። ጫልቱ የራሷ ትንሽ ሆቴል ያላት.......እኔም የዚህ ሆቴል ደንበኛ ነኝ። ጫልቱ ቆንጆ አይደለችም። ጫልቱ ደግ ናት። ጫልቱ ወንዳወንድ ናት። ከሱልልታ በመምጣቷ በሱልልታ ሴቶች ስም ብትነግድም፣ ሴትነቷ ከፆታ መለያነት አልፎ አይታየኝም ነበር። በሴትነቷ ያለች አትመስልም። በቂጧ ትኩራለች። አንዳንዴ በጥፊ ትመታውና 'ይሔ ያሳድረኛል' ትላለች። አንዳንዴ ሊሆን ይችላል.......ግን ውሸቷን ነበር። ቀን ሳያሳልፍላት ተሸክማው እንደምትኖር ይገባኛል። ዐይኗ ውስጥ ሁልጊዜ ሹመት እንዳመለጠው የቢሮ ሰራተኛ ባዶ ቦታ፣ ጉድጊድ አያለሁ.......በተለይ በራሷ ላይ ያላትን ዕምነት ለማብራራት አንዳንድ ነገር ስትናገር፣ አንዳንድ ነገር ስታደርግ ማየት የማትፈልገውን አይባታለሁ። ለመደበቅ የምትፈልገውን አይባታለሁ። የመከናነብ ጥበቧን ለማሳየት ስትሞክር ጨርቁ እጅግ በመሳሳቡ ተገፋፋ.......የተሸነቆረ ዕምብርቷን አያለሁ.......የብቸኝነት ንፋስ በቀዘቀዘ ምላሱ የሚያረጥብባትን ዕምብርቷን አይባታለሁ.......አልናገርም። ጫልቱ የሚያምርባት ደግ ስትሆን ነው። የተወለደችው ደግ ለመሆን ነው.......ወይስ ደግነቷ ከድኖባት ይሆን?.......ሴትነቷን ደግነቷ ከድኖባት ደብቆባት ይሆን? ዝምተኛነቴ የመታዘብ ችሎታዬን እንደሚጋርደው። የወሰን ውበት ነገረኛነቷን እንደጋረደው። የኤልያስን ጊደኛ ሽርሙጣነቷ ደግነቷን እንደሸፈነው፣ አባቴን አባትነቱ የማይረባ መሆኑን እንደሸፈነለት፣ የሙስጠፋ ጢምና ትልቅ ደረት አልቃሻ መሆኑን እንደጋረደለት። የህዳስ ሻሽ መላጣቸውን እንደጋረደላቸው፣ የፋሲካ ዶሮ መብላቴ.......ደስተኛ እንዳልሆንኩ እንደጋረደልኝ።



@BOOKALEM

ሁሉ የሚታየኝ ስታወራልኝ ነው። ምንም አልመልስላትም። መጋቢያችን ብቻ ብትመስልም ከጃፓን ጋር እንደተኛች አውቃለሁ። ከጊደኛዬ ጋር ተኝታ እኔን ማግባት ትፈልጋለች? (በቴክኒክ በአግድም ማግባባት?) ጃፓን ነግሮኛል። ለጃፓን ሴት ሁሉ አንድ ነው። ለጃፓን ሴት ሁሉ ሥጋ ነው። እንደ ሥጋ አመዳደብ የራሱ ስልት አለው። የሽንጥ፣ የጐን፣ የሻኛ፣ እንደሚባል የሴት ነገድ አለው። ጫልቱ 'ቢችግር' ናት። ለጃፓን ሴት ታርፎባት የምትረሳ እንደ ተራ የሕይወት ክፍል ናት። ከዚያ ውጭ በትርፍ ጊዜው አሮጌ ሬድዮ ይገጣጥማል። በርካሽ የምኖረው ቤተሰቤን ለመርዳት ነው የሚለው ሲዋሽ ነው። ሽፋን ነው። ፋሲካው ነው። ፋሲካ ሽፋን አይደል። የአንድ ዓመት ውጋት በአንድ ቀን ነቀልን ለማለት። ያውም የዘመኑ......የሚያማርሩት ፋሲካ።

ስለዚህ ጫልቱ ስትናገር አልወድም። እንደ አዋቂ ያደርጋታል። ሳስተምር ልትል ትፈልጋለች። ዕድሜዬ ከእሷ ቢያንስም እንደመካሪ ስትናገር አልወድም። አፏንና ድርጊቷን አወዳድሬ ለማጤን ጉያዋን አስገድዳኝ ማየት አልፈልግም። ቅቤ የሌለበት ሽሮ በበሶብላ አጥና ሰርታ ቅቤ አለበት ትለኛና......ስለ ቅቤ መወደድ፣ ስለቅቤ ለሰውነት አስፈላጊነት፣ ስለቅቤ የሐብታም ምግብ መሆን ታወራለች። ነጠላ ጫማ ያልጋረዳቸው የተሰነጣጠቁ እግሮቿን፣ በማድቤት ስራ የቆረፈዱ የእጆቿን ሰበከት፣ በደጋግ ሽረሪቶች ድር እንዳይናድ የተያያዘ የቤቷን ጣሪያ ዐይና ዝም እላለሁ። አልናገርም። እንዳልገባው፣ እንዳልተረዳ፣ ነገሩን እንዳመነበት አንገቴን ደፍቼ ዝም እላለሁ። እንደማውቅባት አታውቅም። ፈዕሞ አታውቅም። 'እግባ' ትለኛለች። ለምን እሷ አታገባም? የእሷን ድክመት በእኔ ልትወጣ ነው? ሰላሌ ሜዳ በበቅሎ ተድራ ሰልችቷት የፈረጠጠችለትን ትዳር ለእኔ ስጦታ ታቀርበዋለች። ያስመረራትን ታጠባኛለች?

በክፉ ግን አላይባትም።

ቀኑን ሙሉ ስለሰራችው ነገር ስታወራኝ ውላ ጥሩ ሆኖ ሲመሽ ወጣሁ። ቃል አስገባችኝ። እንዳላስከፋት ቃል ገባሁ።

እንዲህ አለች፡ "በሚመጣው ፋሲካ ቤትህ መጥቼ ከሚስትህ ጋር፣ ከቆንጆ ሚስትህ ጋር......እርግዝ ሞላ ያለች ሚስትህ ጋር እፈስካለሁ"

እኔም፡ "ይሁን" አልኳት.......

አዲስአባ ድልህ የበዛበት ዶሮወጥ የፈሰሰባት ትመስላለች......በዩ፣ ጎድጊዳው፣ ንፋሱ......ማንም የማያመልጠው የበዓል ጠረን ነበር።



@BOOKALEM

# ናና ከረሜላ

አዲስአባ ስገባ እንደማንም የባላገር ሰው ብዙ ድንቅ ነገር ነበር የጠበቅሁት:: መጀመሪያ የገረመኝ የአዲስአባ ስፋቷ ነው:: ሁለተኛ የገረመኝ የመኪናው ብዛት ነው:: ሦስተኛ የገረመኝ የሰው ብዛት ነው:: ሌላው የገረመኝ አዲስአባ እንደ ንፋስ መውጫ በምስራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን በተራራ መከበቧ ነው.......በዚህ ተደናግጬአለሁ ......ቤታች በቦሌ ያየሁት ክፍት ቦታ ከታፈንክ ማምለጫ(2) ይመስላል:: ገጠር እያለሁ የምሰማው ብዙ የሚገርሙኝ ነገሮች አብዮቱን ጨምሮ ከአዲስአባ ነው የመጡት ሲባል ነበር:: እና አዲስ አበባ ልዩ ሐይል ያላት ይመስለኝ ነበር:: እንዲህ ሕዝብ በዝቶ ባለበት ቦታ የእያንዳንዱን ሰው ፍላጎት ማሟላት በጣም አስቸጋሪ ነገር መሰለኝ:: የመጀመሪያ የጥበቃ ዕለት ታዲያ ሱቅ ጠጋ ብዬ ለአፌ ሥራ ማስያዣ የጠየቅሁት ናና ከረሜላ ነበር::

"ናና ከረሜላ አለህ?" አልኩት ባለሱቁን::

"ሃ ሃ ሃ የለም" አለኝ እየሳቀ::

ምን ያስቃል? አብሬው እንደ ቂል ፈገግ አልኩና ትቼው ሔድኩ:: እንደገና ሌላ ሱቅ ጠየቅሁ:: ሦስት ሱቆች ጠየቅሁ:: ናና ከረሜላ የለም:: ዐይኖቼ መገረም አቁመው መተቸት የጀመሩት ያኔ ነበር::

ያፈረ፱ ቤንዚን ውጠው የሚሮጡትን መኪናዎች ላይ፣ ቦይ ተጠግተው የሚታጠቡ የጃፓን መኪናዎች ላይ፣ ተጊያጊጠው ቦርሳ አንግበው የሚሄዱ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶችን ላይ፣ መሐል ጣቱን እንዳቆመ ስድ ጉረምሳ የማዘጋጃ ቤት የዕብነበረድ ሕንፃ በኩራት ቆሞ ሳይ፣ የጠቅላይ ፖስታ ቤት ሕንፃ እንደባልጩት ሲፈልቅ ሳይ፣ የፖለቲካ ሰዎች በክላቺንኮቭ ታጅበው ሲያልፉ ሲያገድሙ ሳይ፣ በእንግሊዘኛ የተፃፉ ማስታወቂያዎችና መፈክሮች በየቦታው ተለጥፈውና ተንጠልጥለው ሳይ፣ የቀይና ነጭ ሽብር ትርፍራፊው .......ዝንጥፍጣፊው በየበዓሉ በግ አሥሮ ሲጎትት በምሽት.......በምንገድ የሚተመውን የሚነጠር ቅቤ ሽታ.......እንደ ጉም የሚቦነውን የጥብስ ጪስ ሳይ.......መፈክሩ፣ ጋዜጣው አዲስአቢትን ሲያመሰግን.......በላተኛው ሲተች....... ሲያስተምር.......ወዘተ ሳይ ፈራሁ::

ምን ያስፈራኛል?

ከልክ በላይ በየሱቁ መስኮቶች የተሰቀሉ ውድ ውድ ልብሶች ሳይ፣ በጉራማይሌ ቋንቋ የሚናገሩ ወጣቶች በአጠገቤ እየተሳሳቁ ሲያልፉ ሳዳምጥ፣ ከረሜላ፣ መስቲካና



@BOOKALEM

አቾሎኒ ሻጮች በየቦታው ውልብ ውልብ ሲሉ ሳይ፣ የሙዚቃ ሱቆች የፈረንጅና የአበሻ ዘፋኞች ፎቶግራፎች ሰቅለው ካሴት ሲቸረችሩ ሳይ.......

"ናና ከረሜላስ?" አልኩ።

የለም። ስለዚህ ፈራሁ።

ናና ድሮም ለእኔ የሚስጥር ምልክት ከረሜላ ናት። ሁሌ ትጠልቅብኛለች። አዲስአባ ይሔን ሁሉ አግኝታ ናና ከረሜላን ካጣች የሆነ ያልተረዳችው፣ ያመለጣት ሚስጢር አለ። ይህቺን ሚስጢር የናቀች ማን መሆኗ የተሳታት ከተማ

አስፈራችኝ.......

የምታወላውል ነፍሴ ናና ስመጥባት ትረጋጋ ነበር። ምላሴ ላይ ናናዋ ተቀምጣ የዱር ጣዕሟን ዕርጥብ ላንቃዬ ላይ ስትነሰንስልኝ ዘባሪቆ ነፍሴ በትኩረት ትገዛ ነበር፣ ዐይኖቼም አፎት አልፈው ደንባራ የብልጥ ስል ያዩ ነበር።

የታለች ናና?



@BOOKALEM

# ሰፈሩ ጣቢያ

ቤቴ ከተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን በስተምዕራብ ያለ የተተራመሰ ሰፈር ውስጥ ነው:: አንድ ሰፊ ክፍልና......ለመኝታ ቤት እንደገና አንድ በሦስት የሆነች ጓዳ......ለዕቃ ማስቀመጫና ለሻይ ማፍያ:: የምኖረው በኩረ፣ ጃፓን፣ አለማየሁ፣ ነጋሳ ከተባሉ ሰዎች ጋር ነበር:: አራታችንም ፖሊሶች ነን:: ነጋሳ ነርስ ነው......ፖሊስ ሆስፒታል የሚሰራ:: የጃፓንን ትክክለኛ ስም እንደ አስፈላጊ ነገር ጠርተን ተጠቅመንበት አናውቅም:: ቅፅል ስሙን ይወደዋል:: የጃፓን ቴፕ፣ የጃፓን ቴሌቭዥን፣ የጃፓን መኪና፣ የጃፓን ቴክኖሎጂ ስለሚደንቅ......እሱም በቅፅል ሥም መደነቁ ቢደርሰኝ ነው መሰል ይወደዋል:: ስለመኪና የተሳሳተ ነገር ቢናገር.......ስለፍሬቻ የተሳሳተ ነገር ቢናገር......መቀበል አለብን:: ቅፅል ስሙን መከራከሪያ ያቀርባል......"ጃፓን ነኝ":: ተሰጥቶት ይጠቀምበታል:: እኔ አልሰጠሁትም:: ሲሉት ሰማሁ:: ቅፅል ስሙን እንደሚወድ ሲናገርም ሰማሁ:: በጣም የሚኮራው ግን በአያቱ ነው (የአባቱ አባት):: እንደሚነግረን አያቱ የመጀመሪያው መኪና አዲስ አባ ሲገባ በሚኒሊክ ታዘው ከሚሾፍሯት ፈረንጆች ሁዋላ ተቀምጠው ለሰላሳ ደቂቃዎች ያህል አብረው ተጉዘዋል:: እንደሚለን ያችኑ መኪና ቀዳማዊ ሐይለሥላሴ ወይም በእሱ አባባል <<ማጂካ>> አልጋወራሽ ለነበሩ ጊዜ ይነዱዋት ነበር(3):: በተጨማሪም ይችኑ መኪና ልጅ እያለሁ አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ ኤግዚብሽን ቆማ አይቼአታለሁ ይላል:: እንደሚያወራው ከሆነ ለሁለተኛ ቀን ከአባቱ ጋር ወደ ኤግዚብሽኑ ተመልሰው ሔደው የተነሱት ፎቶግራፍ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ቤታቸው ግድግዳ ላይ ነበር:: ታዲያ አንጀባ እንዳበዛ ሲነገረው፣ ወይም ማንጀብ ሲያምረው «ቴክኖሎጂ በደሜ ውስጥ ይመላለሳል» ይለናል::

በኩረ አይገባኝም:: አንዳንድ ቀን እጅግ ወዳጅ ይሆንና.......ደግነቱ ጫልቱን ያሳማና ዘመዶቹ ጋ ደርሶ ሲመጣ ፊቱን ይከስክሳል.......ይነጫነጫል.......ሣጥኔን ይተርባል:: ሣጥኔን አይወደውም—ዘመዶቹን አይቶ ሲመጣ......

"በእናትህ ያን የብረት ሳጥንህን አልጋህ ስር በደንብ አስገባው በጣም ነው የሚደብረው:: የዛገ ብረት ሳታቁዋርጥ ካሾተትክ ጉብትህ ሊታመም ይችላል (ሳይንሱ ባይገባኝም)" ይለኛል::

ወደ ውስጥ እገፋለታለሁ:: አድርጌለትም አይለወጥም:: የፊቱ የሰንበር መስመር አይጠፋም፣ አይሰወርም:: ምን እንደማደርግ ግራ ይገባኛል:: ንጭንጩን ከእኔ ሳርቅ እፈልጋለሁ:: ወይ እኔ ከንጭንጩ ልሽሽ:: ከዚያ አጉንብሼ ሳጥኑን ስገፋ ሲወጣጠር ያየውን ሱሪዬን ይተቻል::



@BOOKALEM

በኩረ፡ "ምነው ሱሪህ ተወጣጠረ:: የሠራዊቱን ጨርቅ መጫወቻ አደረከው"

እንደቀልድ እወስድለታለሁ:: አንዳንዴም ሰውነት እየመሰለኝ ልቦናዬን ሰጥቼው የጠየቀኝን አደርግለታለሁ፡ እንደ ሱሪዬን ማስተካከል፣ እንደ ሳጥኔን ወደ ውስጥ መግፋት፣ እንደ መሐረቤን ማጠብ፣ እንደ ጠማሁበትን ብርጭቆ መሰብሰብ:: ቢያበሳጩኝም በዝምታ እሸሸዋለሁ:: ሐብት ኖሮኝ ብቻዬን ብኖር እመርጣለሁ:: አልታደልኩም ወይም አልለፋሁም::

ሌላው አለማየሁ ነበር:: ዘፈን ይወዳል:: አዲስአበ የሚወጣ ሀበሻ ያቀነቀነበት ክር አያመልጠውም:: ምንገድ ካገኘነው እንኳን 'አዲስ ክር ይገኤለሁ:: እሱን ለመስማት ስለምፈልግ እቤት ነኝ' ይላል:: የመጀመሪያ ወር ዕቁብ ሰብሳቢ ሆኖ የገዛው እቃ ቴፕ ነበር:: የመጀመሪያም የመጨረሻም ሐብቱ ናት:: ከሐኪሙ ከኒጋሳ ጠዋት ማታ የሚጠይቀው ነገር አልኮል ነው:: በየሳምንቱ ቴፑን ይጠርጋል:: በየሳምንቱ ቅዳሜ ከሰዓት ወይም እሁድ ጠዋት ቴፑን ይጠርጋል:: ቴፕ፣ ክር፣ ቴፕ፣ ክር:: የሚወደው ሌላው ስራው የድር ዘፈኖች መሰብሰብ ነው:: ሴቶች ሙዚቃውን ፍለጋ ይመጣሉ:: ወሬው ሙዚቃ ነው:: የሙዚቃ ትርዕይት ሲኖር ራስ ቲያትር፣ ብሔራዊ ቲያትር፣ አገር ፍቅር አያመልጠውም:: እሁድ እሱ እቤት ካለ.......የሰፈራ ጣቢያችን ፀጥታ የላትም:: በመጠኑ የማዋራው እሱን ነው:: ያዝንልኛል:: ለምን እንደሚያዝንልኝ አላውቅም:: ከሁለት ሴቶች ጋር ከመጣ.......እኔን ሲያደናንቀኝ ይቆይና.......አንዷን በሀይኑ እየጠቆመኝ......"አንተ ያቺ ዘናጭ አይደለችም? ለምን?.......በጣም የምትገርም ነህ:: ምን እንዳሉኝ ታውቃለህ? ያዩህ ሴቶች ሁሉ ይወዱሐል:: በመልኩ የሚጫወት እንዳንተ አላየሁም:: አንተን መግደል ሳይሻል አይቀርም::" .......አለማየሁ በትንሹ ኤልያስን ይመስላል:: አለማየሁ ግን አንዲትም ቀን ስለፖለቲካና ስለ አገር ወሬ አንስቶ አያውቅም.......ቢብስ ሴቶቹን አሞከሻሽቶ እኔንም ደልሎ ሻይ እንዳፈላላቸው በእነሱ ስም ይጠይቀኛል:: ብልጠት እንዳለበት ባውቅም የጠየቀኝን አደርግለታለሁ:: መጠለያ ጣቢያችን ውስጥ አለማየሁ ቴፕ፣ ካሴት፣ ሴት ነበር::

ሠፈራ ጣቢያችን በሽታ ገብቶ አያውቅም:: ቢገባ ነርስ ነጋሣ ዘበኛ ነበር:: ነጋሣን የሚያክል ተክለ-ቁመና ያለው ሰው አይቼ አላውቅም:: ከሙስጠፋ ይተልቃል:: ነርስ ሳይሆን ታንክ ነጂ ነው የሚመስለው:: ነጋሳ የአምቦ ልጅ ነው:: ቤተሰቡን ስለሚረዳ ገንዘብ ይቸግረዋል:: ብዙ ጊዜ ገንዘብ ይቸግረዋል:: ግን አማሮ አያውቅም:: አንዳንዴ ከላልቫጅ ተራ የገዛቸውን ልብሶች አልጋ ላይ ያሰጣጣና......."ለወንድሞቼና ለእህቶቼ የገዛሁላቸውን እይ" ይለኛል:: ሁለት ወንድሞች ሦስት እህቶች አሉት:: ፈገግ ብዬ አይለታለሁ:: አያስደስተኝም:: አያስከፋኝም:: በኩረ፡ "ሊቃቀምክ" ይለዋል:: አለማየሁ የውሸቱን ያደንቀዋል:: "የተቻለኝን አደርጋለሁ.......የተቻለኝን አደርጋለሁ" ይላል



@BOOKALEM

.......ነጋሳ በትናንሽ አባባል ስህተት እንደሆነ የተነገረውን ነገር፣ እያፈረ በትናንሽ አባባል ያመልጣል::

የታመመ ሰው ካለ ነጋሣ አይተኛም:: እንደ ሐኪም ሙያ የሚወደው የለም:: ከተማረው በላይ ነው የሚያውቀው ይባላል:: ስለ አስፕሪን አንድ ሰዓት ያወራል:: አለማየሁ ልጃገረዶችን ሲያመጣ....... በየመንገዶችና በየፋርማሲዎች የሚሸጡ ተራ ቅባቶችን ዝርዝር እየገለፀ ጉጂነታቸውን፣ ጠቃሚነታቸውን ሲያብራራ.......ሳይንቲስት የሆነ ይመስለኛል:: ስሰማው እወዳለሁ:: አንዳንዴ ደ'ሞ ያበዛዋል:: ሠፈራ ማቢያችንን ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የለወጣት ይመስለኛል::

መጠለያ ማቢያዋ ጉድጓድ ውስጥ ናት:: ረዥም፣ ጥልቅ፣ የሚሸት ቀላይ ውስጥ ናት:: ከተክለሃይማኖት ከቤተክርስቲያኑ በእግር ተነስቶ መኖርያችን ለመድረስ በረዥም ጉድጓድ ውስጥ እንደመወርወር ይመሰላል:: ይኼ በርባሮስ በጋ ከክረምት በደሐነት የጨለመ ነው:: ጠርዙ በአስፋልት ተከፎ.......መሐሉ ሲያል ነው:: ይኼ ሲያል እሳት አለው:: ይኼ ሲያል ይጨሳል:: በዚህ የጉድጓድ ቀልቀል ግድግዳው ላይ ከጭቃ የተሰሩ የቆርቆሮ ቤቶች በበሰበሱ ማዕዘኖቻቸው እንደምስጥ ተንጠልጥለዋል:: ከአስፋልቱ የሚወርደው ዝናብ በየቤቶቹ መሐል እንደ ቀለጠ ሬንጅ ይንጠባጠባል:: እኛ ደቃቆች.......በዜግነትና በሙታን መሐል ያለን አፋችንን ገጥመን እንደጉድፍ በእነዚህ ቀጫጭን ጥቁር ወንዞች ላይ እየተንሳፈፍን መከራችንን እንደ ከረሜላ እየመጠጥን እንገባለን:: አለማየሁ ሙዚቃውን እየሰማ፣ በኩረ ነጭናጫነቱን እየዘፈነ፣ እኔ ዝምታዬን ታጥኜ፣ ነጋሳ አገሩን የሚፈውስበትን ጥበብ እያሰላሰለ፣ ጂጋን አፉ ዙሪያ የድራፍት ወዝ::

ተኝተን ወደላይ አንጋጠን በቱቦው አፍ የሚገባውን መሰላችንን እናያለን.......አስፋልቱ ጠርዝ ቆሞ፣ አምቶ መንግስትን አምቶ ሌላ የሚመቸውን ወይም አፉ የገባለትን አምቶ የጌሾ ሕልም የተተከለበት ዐይኑን እያሸ በምሬት እየዘለለ የሚገባ አለ.......አንዳንዱ አንድያውን ጎጆውን ነቅሎ ይወጣል:: «አመለጠ» እንላለን:: የፀሐይ ቁጣ ይገባል.......ዝናብ ከነጭቃ ሽርኩ ያለመጠን ይገባል:: አልፎ አልፎ ቀን አስፋልቱ ዳር ጥለነው የመጣነው ጥላ ሲመሽ ጠብቆን ዕላሉቱን እላያችን ላይ ይወረውራል::

የተረሳ ቦታ ነው::

የተረሳ ሰው የሚጠለልበት የተረሳ ቦታ ነው::

ከአራዊት ከብር ያጣ እንደ ቅንቡርስ ያለ ፍጡር አፈር ለአፈር እንደሚበረበር.......እኛም:: እኛም ሌላ ያገኘ፣ የቀናውን እያየን ዓለም ላይ ባገኘው ሐብትና ዕድል እንዲኩራራ ማወዳደሪያ እግሩ ስር ወድቀን......

በድብቅ የምንሸሽ.......



@BOOKALEM

በስተደቡብ ልደታ፣ በስተሰሜን መርካቶ፣ በስተምዕራብ ባልቻ ሰፈር፣ በስተምስራቅ ተክለሃይማኖት፥ በቅዱሳን፣ በነጋዴ፣ በአርበኛ ተከልለን.......

ነጋሳ ኪኒኑን ይቆጥራል:: አለማየሁ ቴፑን ይጠርጋል:: በኩረ ይነጫነጫል:: ጃጋን ሸቦ ይቀጥላል::



@BOOKALEM

## ፋሲካ (የቀጠለ)

ከእኔ በስተቀር ደባሎቼ በሙሉ ወደ ዘመዶቻቸው ዘንድ ሔደው ነበር:: ነጋሳ አምቦ ሔዶአል:: በኩረ እዚያው አካባቢ ሰባተኛ አካባቢ ያለች አክስቱ ዘንድ ሔዶአል:: ጃጋን ሐብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ሔዶአል:: አለማየሁ በላይ ዘለቀ ምንገድ ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ያለች ዘመዱ ዘንድ ሔዶአል:: ከእነዚህ ሁሉ አብሬአቸው እንድሔድ የጠየቁኝ አለማየሁና ነጋሳ ብቻ ነበሩ:: ፈቃደኛ አልሆንኩም:: በኩረ አጠገቤ ተቀምጦ ስለፋሲካ አልተናገረም:: እኔን ለመጋበዝ ፈቃደኛ እንዳልሆነ አውቃለሁ:: ቢጠይቀኝም አልሔድም:: ጃጋን ግድ አይሰጠውም:: ራሱ መሔዱንም አይወድም......የተገደደ ይመስላል......"ካልሔድክ ሊገሉህ ይደርሳሉ::" በእኔም የቀና ይመስላል፣ ግን የውሽቱን ለማብገር መጠራቱን እንደ ዕድል እያነሳ ስሜቴን ይፈትሻል፣ እንድቀና ቀንቼም ለመሄድ እንድነሳሳ እንደሆነ አላውቅም:: አለማየሁ ፒያሳ ስለራቀኝ ለመሔድ የማልፈልግ መስሎት በኩረ እኔን እንዲወስድ ለመጠየቅ ሲሞክር ሰምቶ......ዐይኔን በጉን ጣል አድርጌ ሳይ እጁን ያወናጭፋል......'ዝንብል እባክህ' ሀይነት:: አልከፋኝም፣ ደስ አላለኝም::

ሲጠቃቀስ ያላየሁት ወይም ያልገባኝ መስዬው ትንሽ ቆይቶ በኩረ፡ "አንተ መዝገቡ ምናለበት ፋሲካን ከሰው ጋር ብታሳልፍ" ይለኛል::

የማን ቤት መሔድ እንዳለብኝ አይጠቅስም:: ዓለማየሁ እንዳልሰማ ካሴት ይለውጣል:: ጃጋን ይበሽቃል::

"ለምን አንተ አትወስደውም......እኔ እንዲሔድ አልፈልግም......ዶሮ ሳብላው ብዬ አልደብረውም"

እኔ 'እርሱት' እላለሁ::

አይረሳም:: በኩረ አይረሳም:: ራሱ የሰራትን ትንሽ ንፍገት አይረሳም:: ለምን እንደማይረሳት፣ በልቡ እንደሚጠብቃት አላውቅም:: ብረሳለትም አይረሳም:: እቤት ውስጥ አምስት አልጋዎች አሉ:: አንድ ጠረጴዛ አለ:: ብዙ ጊዜ ጠረጴዛውን የሚጠቀምበት ነጋሳ ነው:: ይሄ ጠረጴዛ አልጋዬ አጠገብ ስለሆነ ስተኛ ልብሴን አስቀምጥበታለሁ:: ከነጋሳ ጋር የሚያጣላን እሱ አምሽቶ ስለ ሕክምና ለማንበብ ልብሴን የማስቀምጥበትን ቦታ እንድለውጥ ሲነግረኝ ነው:: እኔ መሬት እከምረዋለሁ:: እየተብሳጨ አልጋዬ ግርጌ ያንጠለጥላቸዋል:: "ይኼን ሰው ምን ማድረግ ይቻላል.......ስንቴ በስነሥርዐት ማጉደል መቀጣት ትፈልጋለህ" ብሎ ይቀልዳል:: የነጋሳን አማርኛ በኩረ እንደተረበው ነው:: በየቀኑ:: በየቀኑ ይተርበዋል:: እኔ ትዝ ብሎኝ



@BOOKALEM

አያውቅም፡ የነጋሳ አማርኛ ትዝ ካለኝ:: አይለኝም እንጂ:: ነጋሳ ረዥምና ትልቅ አስገምጋሚ ድምፅ ያለው የዋህ ልጅ ነው:: በኩረ እንዲህ መናገሩ ታዲያ ነጋሳን አያበሳጨውም:: እና አንዳንድ ጊዜ እንደተናደደ ሰው ማንበቡን አቁሞ የያዘውን ነገር መሬት ላይ ይወረውርና፡......

"አንቺ......አዋቂ ነኝ ብለሽ ነው?" ይላል በኩረን:: በቃ::

የፋሲካ ዕለት ነጋሳ ለቤተሰቦቹ የገዛውን ዕቃ እያወጣ እዚያች አንዷ ጠረጴዛ ላይ ደርድሮ የገዛበትን ዋጋ፣ የት እንደገዛው፣ ለምን እሱ እንደወደደው፣ ለምን ዘመዶቹ የገዛላቸውን ዕቃ እንደሚወዱት እየተነተነ ቆየና ነገሩን ሁሉ ራሱ ጠይቆ (ምን ያደርግላቸዋል?)፣ ራሱ መልሶ (ኑሮ ተወደባቸዋል አቦ)፣ ራሱ ስቆ (አይለብሱትም እኮ፣ ጉልት ነው የሚሸጡት).......የሰበሰበውን ዕቃ መቋጠሪያው ውስጥ መለሰና፡......

"መዝገቡ የፋሲካን በዐል ከቤተሰቦችሽ ጋር አለማሳለፍሽ ቅር ብሎሻል አይደለም?" አለኝ::

ትከሻዬን 'ግድየለኝም' ዐይነት ነቀነቅሁ.......

"አዎ.......ለምን አምቦ አብረን አንሔድም......ትራንስፖርት ትችያለሽ"

"አመሰግናለሁ የትም መሔድ አልፈልግም" አልኩት::

"ገጠር አይደለም:: ከተማ ነው.......አምቦ እኮ ነው"

"የትም መሔድ አልፈልግም"

ከመሐል አልጋው ላይ በሆዱ ተንበልብሎ ጥፍሩን ይቆርጥ የነበረው በኩረ፡ "አልፈልግም ካለህ አትተወውም?" አለ::

"ሐሳቡን ከለወጠስ?" አለ ነጋሳ::

በኩረ አልጋ ላይ ነው:: ነጋሳ ቀረጢቱን ይዞ ጠረጴዛ ተደግፎ ቆሟል:: አለማየሁ ያጠበውን ንፁህ መሐረብ ያጥፋል.......

ነጋሳ በኩረን አተኩሮ እያየው፡ "አንተ መጥፎ ሰው ነህ" አለው::

"ማንን ነው የምትለው?" አለ በኩረ::

"አንተን ነዋ"

በኩረ እንደተበሳጨ፡ "ምን አይተህብኝ ነው በል?"

"ምናለበት ይሄን ሰውዬ ብንወስደው.......ብቻውን ምን ያደርጋል?"

"ካልፈለገስ?"



@BOOKALEM

"ለምን እሺ አንተ ውሰደው.......ከዚህ ከተማ መውጣት ካልፈለግ"

"በእኔ ምን አገባህ?"

"አንተ ካላደረከው.......እኔ ባደርግ ምን አለበት?"

"የራስህ ጉዳይ" አለ በኩረ::

በዚህች አጭር ንግግር መሐል በኩረ 'መጥፎ ሰው' መባሉን የረሳው መሰለ:: አልረሳውም:: በመጨረሻ የተናገራት ዐረፍተነገር ስድብ ሆና እንድትወጣ የፈለገ መስሎ የተለየ ድምፅ ሊሰጣት ሞከረ:: እንደማጉረምረም ነበረች:: ነጋሳ ያልገባው መሰለ:: ወይም አልገባውም::

የጉዳዩን ተፅዕኖ ሳልገመግም ቁልጭ ብላ በምትሰማ ዐረፍተነገር: "ፋሲካ አክብሬ አላውቅም" አልኳቸው::

መጀመሪያ በቸልታ ያለፉት መሰሉኝ ነበር......ነገሩን ሳያምኑ:: አለማየሁ ነው: "ምን? ምን?" ያለው::

ደግሜ ተናገርኩ:: ምንም ሳልለውጥ ቁልጭ ብላ በምትሰማ ዐረፍተ ነገር::

"ፋሲካ አክብሬ አላውቅም"

"ለውነትህን ነው?" አለማየሁ

"እም"

"እስላም ነህ? ስምህ የእስላም አይደለም"

"ብዙ ነው ታሪኩ" እየሳቅሁ::

በደንብ የሳቅሁ አይመስለኝም (ቀላል ሳል የመሰለ):: በጀርባዬ ተጋደምኩ:: ብርድልብሴን ተከናነብኩ:: አጥብቀው ሊጠይቁኝ አልሞከሩም:: ከነጋሳ በተቀር የቀሩት ደባሎቼ ተራ በተራ ከቤት እየወጡ ሔዱ:: የብርድልብሴ ጠረን ይጣፍጠኛል:: አዲስ የደብረብርሐን ብርድ ልብስ ነበረች:: አንዳንዴ ማታ ማታ ልብሴን ማውለቅ ሲደክመኝ.......በሆዴ ብርድልብሱ ላይ ተደፍቼ ስተኛ በዐይኔ እንኳን ዐይቼ የማላውቃትን የደብረብርሐንን ከተማ አመሰግናለሁ:: አልፎ አልፎ ደብረብርሃንን አመሰግናለሁ:: ያን ሰለትም ሳመሰግናት ነበር.......ከደብረብርሐን ተራሮች (ተራራማ ነችን?) ከወንዞች ውስጥ (ወንዞቿ እንደማስባቸው እየደነፉ ይወርዳሉን?) ወይም ከብዙ የውሐ ጉድጓዶች ውስጥ (እንዲህ በዐይነ-ሕሊናዬ አጎንብሼ ሳይ ምንድነው እዛ ጉድጓድ ውስጥ? ወተት? ወይስ የታህሣሥ ጨረቃ ወድቃበት? ወይስ የወይዘሮ ስንዱ ትኩስ ኩታ—ትናንት ያ ድንቅ ሸማኔ የወለደው?)......ልክ የመድረክ አስማተኛ ከባርኔጣው ውስጥ አበባና ጥንቸል እንደሚያወጣ ሰዎች የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ብርድልብሶች



@BOOKALEM

ጠዋት ማታ እየመዘዙ የሚያወጡ ይመስለኛል:: ትልቅ አዳራሽ ውስጥ አስገብተው እየቆራረጡ ይልኩልናል:: መቀሱ ያስፈራኛል:: እኚህ ብርድ ልብሶቹ የሚቆራረጡበት መቀስ፣ በሕሊናዬ የምፈጥረው መቀስ ያስፈራራኛል:: ተንፈራጦ የቆመ ትልቅ 'ለ' ይመስላል:: ስለቱ እንደ ብር ያበራል.......ያለዕረፍት ስለሚቆረጥበት ግሉ ስለቱ እንደ ወርቅ ይቀላል.......የሚጐተተው ብርድ ልብስ ከፊሉ የሚከረክመው አጥቶ.......የደብረብርሐንን ከተማ ሽፍኖ በሰንዳፋ በሸኖ ጐዳና፣ የሰው፣ የመኪና ዱካ ተከትሎ ወደ አዲስአባ ይመጣል:: ጫፉን አየዋለሁ:: ጫፉ በከተማዋ የአፍንጫ ቀዳዶች ተሰክቶ ከተማዋን መተንፈስ ነፍጐአት.......(እንደ እንቆቅልሽ እየጠየቀ፣ `ስንት በግ ነኝ? ስንት በግ ነኝ?´ እያለ).......

ጠዋት ስባንን ነጋሳ ግርጌዬ ተቀምጧል.......በተረጋጋ መልክ፣ ልመና አንተርሶ አብሬው አምቦ እንድሔድ ጠየቀኝ:

"ሁሉ አለ:: አይቸግርም:: እንቅልፍ አላስተኛሽኝም:: እንዴት ፋሲካን አትወደውም? ባትወደውም እንኳን እንሒድ"

አልሰማሁትም:: ትከሻውን እየመታሁ ትላንት የተናገርኩትን ነገር ሁሉ፣ እሱም የተናገረውን ነገር እንደረሳሁትና ሊረሳው እንደሚገባ አለዝቤ አወራሁትና በመጨረሻ ሲያደክመኝ 'ዓለም ፋሲካ እንደሚበዛበት' ነገርኩት::

እየተገረመ "በል ደስ እንዳለህ" ብሎኝ ሔደ::

እስከ ቀኑ አምስት ሰዓት ድረስ ሁሉም ልጆች ወደ የዘመዶቻቸው ሲሔዱ የቀረሁት እኔ ብቻ ነበርኩ:: ቤታችን በር ፊት ለፊት ተቀምጬ ወደ ውጭ የለመድኩትን አያለሁ:: ቤታችን እንግዲህ አጥር አልነበረውም:: የቤታችን ግድግዳ እንዳለቀ ከአንድ እርምጃ በሁዋላ ቦይ ነው:: እዚያ ቦይ ላይ የተቦዳደሰ የጣውላ እልጋ እንደ ድልድይ ተነጥፎል:: ከሥሩ ቀለሙ የሚለዋወጥ እንደ ቀለጠ ጥቁር መስቲካ.......እንደ ማር ገፋ.......የተጐለተ ቆሻሻ ነው:: ዝናብ ሲጥል ይሄ ነገር ነፍስ ይዘራና እንደ አባ ጨጊሬ ወደ ተረገመ አቅጣጫ ይነቃነቃል:: ያውም ቅር እያለው:: ፊት ለፊታችን የእኛኑ የመሰሉ ቤቶች ናቸው......ሱቅ፣ ሻይቤት፣ ጠላ ቤት፣ ጥቂት አሮጊቶች የሚኖሩባቸው የሰልፍ ቤቶችና......ሁለት እህትማማቾች የሚኖሩበት (ከፊል ተማሪ ከፊል ሸርሙጣ) መደዳ ቤቶች አሉ:: አንዷን አለማየሁ የድሪያ ሲያዋራት አይቻለሁ (አንገቷን በቀኝ ክንዱ ብብት አስሮ ተዳክማ ሲለቃት ፊንር ብላ በተነሳች «በቤት ቀሚሷ» ስር እጁን ሰዶ በአደባባይ ምናልባት ቂጧን ከሆነም ምንትሿን በጥፊ ተም እያደረጋት:: በሳቅ እየተንካካች......."ሰው ምን ይለኛል አትልም አንተ??"):: ቁልቁለቱን ኩረኩንች ነው:: በቅርብ የተሰራ ምጥን ሽሮ የመሰለ ኩሮኩንች:: ጫልቱና ምግብ ቤቷ ያሉት በኩሮኩንቹ ምንገድ በስተግራ ጥቂት ከሔዱ በሁዋላ ነው:: ብዙ



@BOOKALEM

ጊዜ የእሷን ቤት ከእኛ ቤት እያፎካከረች በእሷ ቤት ጥራት ትኩራራለች:: ደካማዋ እህቴ::

ቤታችን ፊት ለፊት ተቀምጬ ወደ ውጭ እያለሁ:: ብዙ የሚታይ ነገር አልነበረም:: አንድ ወጣት ሻይ ቤቱ በር ፊት ለፊት ግን ሸሸት ብሎ ለሁለት ታጥፎ ቆሟል:: እንደራበው ገብቶኛል:: ልጁ ቁመና ውስጥ እራሴን ማስገባት አልቻልኩም:: ጠበበኝ:: ጠባብ ነው:: ገላው እንደሽንኩርት ልጣጭ ስስ ነው:: የሽንኩርት ልጣጭ ነው:: ልጣጭ ነበር:: መንገዱን ተሻግሮ ወደ እኔ በኩል ተጠግቶ ወደ ታች አየ:: ሰው የሚጠብቅ ይመስላል:: ያለ መደገፊያ የሳሳ ገላው እየተወዛወዘ አፈርና ድንጋይ ከሆነው ምንገድ ላይ በእግሮቹ እንደ አልቂት ተጣብቆ.......:: አንዲት አሮጌ ሹራብ ደርቧል......ክርኑ ተቦድሶል.......በየስፌቱ ክሮቹ ለቀው ቀዳዳዎች ሞልተውታል:: ሱሪው የተቆረጠ ቦላሌ ነው:: ከታች ከኩሮኩንቹ ምንገድ ሰዎች ግራና ቀኝ ያልፋሉ:: አንዳንድ ሰዎች እኔና ልጁ ባለንበት አቅጣጫ ዞር ብለው ያዩና ይሔዳሉ:: አንዳንዱ የሚገረም ይመስለኛል "ሰው እንዴት ወደታች ወደ መሬት ውስጥ ጉድጓድ ሳይቆፍር ጉድጓድ ይሰራል?" አንዳንዱ ራሱን፡ "እንኳን ደስ ያለህ እዚህ ያልገባህ" ሳይለው ይቀራል?

ልጁ እግሮቹ አያርፉም::

ይቁነጠነጣል::

"ሰማህ ጓድ ምን ሆንክ?" አልኩት

አላመነኝም:: ትክ ብሎ አየኝና በደንብ በማይሰማ ድምፅ "ምንም" ብሎ ፈቀቅ አለ::

"ፋሲካ እንዴት ነው?" አልኩት ቃሉ እያስጠላኝ::

"ያው ነዋ"

"ምንድነው ያው ነዋ!"

"አቦ" አለ እጁን አመናጭቆ::

ጓደኛ አገኘሁ:: ግን ጓደኛዬ ቢሆንም እንለያያለን:: እኔ ኪስ ውስጥ መልከመልካም ገንዘቦች አሉ:: የዚህ ልጅ ኪሶች እንኳን ገንዘብ አየር መቋጠር አይችሉም:: የትኛውም የገላው ክፍል አየር የሚያሳልፍ ወንፊት ነው::

"ና እስኪ እናውራ"

"ምን?"



@BOOKALEM

ከፊል ጆሮው ወደ እኔ ነው:: ያኔውኑ ከቆመበት.......ሳልቶ ከነበረበት አቋቋሙ በርግጉ ወደ ላይ መሮጥ ጀመረ:: አንገቴን በበሩ ወጣ አድርጌ ወደ ታች አየሁ:: አንድ ፖሊስ በአንድ እጁ ቆመጡን በሌላ እጁ የሚንቃንቀውን የወገቡን ሽጉጥ ይዞ ወደ 'እኛ' ይሮጣል:: ልጁን አየሁት:: ድምፁ የማይሰማ እሩጫ ይሮጣል:: የፖሊሱ ቦት ጓንታ ደንቀሮ ያነቃል:: ፖሊሱ እየሮጠ መጥቶ ልጁ ቆሞ የነበረበት ቦታ ሲደርስ እያለከለከ ቆመ:: አላየኝም::

"ቆይ ጠብቅ" አለ ለራሱ በሚመስል የድምፅ ከፍታ::

"ምነው?" አልኩት:: ሌላ ሰው እዚያ አካባቢ መኖሩን ስላልጠረጠረ ትንሽ ደንግጦ አየኝ::

"ምን እባክህ እነዚህ ልጆች.......ሥራቸው መስረቅ ሆነ"

"ምን ሰረቀ? ልጁ ምንም ይዞ አላየሁትም"

"ገበያውን አልረበሸም እንዴ?"

"ምን ሰረቀ?"

"ዶሮ"

መሳቅ አልፈለኩም::

"ሰርቆስ.......የት እንዳስቀመጣት......." አለ::

"ሴት ነው ወንድ ዶሮ የሰረቀው?"

"ዶሮ ዶሮ ነው ጓድ.......አርፈህ ተቀመጥ:: የጠየቀህ የለም.......ጣጣ እኮ ነው"

"እኔ ፖሊስ ስለሆንኩ ነው የጠየቅሁህ"

"ቤቱ ውስጥ ተቀምጦ ሌባ ሲያመልጥ የሚያይ ፖሊስ አላውቅም"

"ቆይ እስኪ......."

ፖሊሱ ዱላውን ወደ አፎቱ መለሰና የምናገረውን ይጠብቀኛል::

"ለምን እዚህ ገባ ብለህ አንጫወትም" አልኩ::

"ግዴታዬ ላይ ነኝ"

"ሁሉ ሰው ዓለም ላይ የሚኖረው ሁሉ የሆነ ግዴታ አለበት"

"ስለሌላው አላውቅም"

"ያ ልጅ ግዴታ አለበት"



@BOOKALEM

"ምን ያውቅና ነው......."

"ስርቃ ማደር የማትችል እናት ብትኖረውስ?"

"ምን አገባኝ"

"ፋሲካ ትደግሳለህ?"

"ምን አገባህ?"

"እሱን አስረህ አንተ ፋሲካ ትበላለህ?"

"ወንጀለኛ ስለሆነ......."

"አሥሮ አዳሪ ነሃ"

"ሕግ ያስፈልጋል"

"ፋሲካ አላከበርኩም ብሎ ቢነግርህ......ትስቅበታለህ ወይም......ታዝንለታለህ:: ግን ታስረዋለህ"

"ሰርቄ አይደለም......." አለ ልጁ::

"ይኼ ልጅ ሰርቆ ያውቃል?"

"አዎ"

"ሠርቶ ማደር ካልቻለ ይስረቃ"

"ጊድ ፖሊስ ነህ ሌባ ነህ?"

"ሌባው እላይ ነው ያለው.......እላይ እላይ".......ፖለቲካ መናገሬ አስፈርቶኛል:: ያልፈራ ለመምሰል ሞከርኩ:: ጨዋታ ቢጤ ላደርገው::

ሰውዬው መልስም ሳይሰጥ ፊቱን መለስ አደረገ:: እየተገላመጠ ያየኛል:: ስለምን እንደሚያስብ መገመት አልከበደኝም::

ራቅ ብሎ የረሳው ነገር እንዳለ: "እዚህ ነው ለመሆኑ የምትኖረው?" አለኝ::

"አዎ ይኼ ምንገድ አልጋዬ ነው.......የአዲስአበባ ከተማ የምትወረውረው ንፍጥ ብርድ ልብሴ ነው:: እንደዚያ ዐይነት ሌባ ህፃናት ትራሶቼ ናቸው:: ሴት አላውቅም ድንግል ነኝ.......ከዚህ ቦታ ውጣ" አልኩት::

ያበድኩ መሰለው:: በመገረም እያየኝ ወደ ታች ወረደ:: እየደጋገመ እያየኝ:: ለእኔም ለራሴ ያበድኩ መሰለኝ:: ልጅ መሆኔን.......ልጅ ሆኜ መወለዴን፣ ፖሊስ መሆኔን፣ እንደገና እዚያች መቀመጤን በየተራ እንደምጠላ ማን ያውቃል?



@BOOKALEM

ወደ ላይ የወጣው ጉብል ፖሊሱ ሲሄድለት ተመልሶ መጣ:: እያደባ፣ ቀስ እያለ.......ቀድሞ ወደነበረበት ቦታ ተመለሰ–በጥንቃቄ:: በዐይኖቹ ጠየቀኝ:: ስለፖሊሱ በዐይኖቹ ጠየቀኝ::

"ቤተሰቦች አሉህ?" አልኩት

"አዎ.......ከአባቴ ጋር ነው የምኖረው"

እግሮቹን እያቀያየረ በዐይነ ዐፋርነት ያራግፋል::

"አባትህ ይሰራሉ?"

"ይሠራል........ግን ሰካራም ነው"

"አንድ ነገር ታደርግልኛለህ?" አልኩት

"ምን?" አለኝ በጉጉት

"ምሳዬን መብላት እፈልጋለሁ.......የጫልቱን ቤት ታውቀዋለህ?"

"ጫልቱ? አላውቅም"

"ሌላ ሆቴል ታውቃለህ?"

"እዚያ ላይ አለ.......ነጋሽ ሆቴል"

"በቃ ጥሩ ከነጋሽ ሆቴል.......ሁለት ዶሮ ወጥ ታመጣለህ"

"የታለ ገንዘቡ.......?"

"ቆይ......ንገረው:: አሳላፊውን ታውቀዋለህ? ቀዩን......."

"አዎ......."

"እሱን መዝገቡ ላከኝ ትለዋለህ.......ስህን የለኝም አየህ.......ብሩ ይኸውልህ"

ስድስት ብር ቆጥሬ ሰጠሁት:: ንፋሱ በተዘረጋጉት ብሮች መሐል እየሾለከ.......እርስ በርስ እያተረማመሳቸው እያውለበለባቸው ውብ ያደርጋቸዋል:: እንዳይቆሽሹ ሰግቶ ወይ የሌላ ሰው ገንዘብ በመሆናቸው ፈርቶ ይሁን አላውቅም ልጁ የያዛቸው ከጫፋቸው ነበር:: ከእኔ ሌላ መልዕክትም ሳይጠብቅ እየሮጠ ሄደ.......ዞር ብሎ አየና፡ "ከሌለስ?" አለ::

"ቀይ ወጥ አድርገው"

"ሁሉም?"

"አዎ"



@BOOKALEM

ልጁ ብዙ ሳይቆይ መጣ:: ትልቅ ትሪ ትከሻው ላይ አጋድሞ:: መሸከም የሚችል አይመስልም:: በር ላይ ያመጣውን ተቀበልኩ ት:: አልገባም:: በር ላይ ቆሞ ያያል:: የገንዘብ ጉርሻ ጠብቆ ይሆናል::

"ግባ" አልኩት:: ጠረጠረ::

"ግባ"::

በቀስታ እየተቅለሰለሰ አንገቱን ሰብሮ ቤት ውስጥ ገባ:: በእጁ የአፍንጫውን ቀዳዶች ያሻል:: በዚህ ዐይነት ፍራቻ ከገበያ መሐል ዶሮ መስረቅ የሚችል አልመሰለኝም:: እንጀራውና ወጡ ትሪ ላይ ሆኖ ትልቅ የብረት ድስት ክዳን በላዩ ላይ ተደርጓል:: ቤቷን የዶሮ ወጥ ጠረን ሞላት:: አፌ ውሐ ሆነ:: እርቦኝ ነበር:: ከዚያች ካለሁባት ቤት ጫልቱ ቤት ሔዶ ቁርስ መብላት ሰንፌ ነው:: ትሪውን ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥኩና የላስቲክ 'ጆግ' ይዤ እጁን እንዲታጠብ ጠራሁት:: ግራ ገባው:: ግራ እንደገባው ግን አያውቅም:: 'ጆጉን' ከእጄ ነጥቆ ካላስታጠብኩ ብሎ ተከራከረ:: ሁለታችንም እየተቀያየርን ተጣጥበን ሳህኑን ሰሚንና ደቡብ ሆነን ከበብነው:: ወንበር ስላልነበረ አልተቀመጠም::

የልጁን ዐይኖች እያየሁ ነበር:: ሌሎች እኔን ጥንት እንዳዩኝ:: ሌሎች ድሮ እኔን እንደታዘቡኝ:: ጥንት ጠግቤ ከበላሁ ደስተኛ የምሆን ይመስለኝ ነበር:: ይኼም ልጅ ያስባል:: በመጀመሪያ የፀይኖቹን ሽፋሽፍቶች እንደ ረግኸም፣ ጥቋቁር፣ ቀጫጭን እጆች ትረው አየር ላይ ዘረጋ:: እንደ አሰሳ:: ከዚያ አየኝ:: ብቻውን ብተወው የሚወድ ይመስለኛል:: በትልልቁ እንዲበላ አበረታታሁት:: ይበላል:: ዐይኖቹን ሳይሰብር ይበላል:: ዶሮ ወጥ ወይም ሞት.......እንጀራ ወይም ሞት:: እንዳይደክም ራሱን እደባብሰዋለሁ:: እንዲበረታታ እንዳያፍር::

"ፖሊሱ ያለህን ልንገርህ?" ብዬ ወሬ ጀመርኩ::

"ምን አለ?"

"ዶሮ ስርቆአል አለ"

"ውሸት ነው.......ፖሊሶች ውሸታቸውን ነው......ሰው ማሰር ስለሚፈልጉ ነው"

"የዕውነት አልሰረቅህም?"

ዝም አለኝ:: አየኝ:: ጠበቅሁና እንደገና.......

"የዕውነት አልሰረቅህም?"

"ሰርቄአለሁ"

"ምን?"



@BOOKALEM

"ዶሮ"

"ለምን?"

"አባቴ ሰካራም ነው.......ለፋሲካ ምንም አልገዛም:: ለጎደኞቼ ሁሉ ተገዝቷል.......በግ ሁሉ ገዝተዋል"

"እናትህ የሉም?"

"ተፋታ......ሔዳለች"

"ዶሮውን ማን ይሰራልሃል?"

ዝም አለ::

"ዶሮ መስራት ትችላለህ?"

"ልመልሰው ነበር"

"ምኑን?"

"ዶሮውን"

"ለምን.......?"

"በሁዋላ ሳስብ በቃ ወላ ዶሮውን የሚሰራ ሰው የለም"

"መለስከው?"

"ልመልስ ሳስብ ፖሊሶች ደረሱብኝ"

"አሁን ዶሮዋ የት ናት?"

"አሁን አልመልስም"

"ለምን?"

"አንድ ጊዜ ሌባ ተብያለሁ"

"ሌባ አይደለህም ታዲያ?"

"ገና ሌባ አልሆንኩም.......ዶሮዋን ብበላት ወይም ብሸጣት ኖሮ ሌባ እሆን ነበር"

"ከሌላ ሰው ከሰረቅሃት ሌባ ነህ"

"እኔ ሌባ አይደለሁም:: ሌባ ነህ ካሉኝ.......ሌባ እሆናለሁ"

"ምን ማለት ነው?"



@BOOKALEM

"ሌባ ነህ ካሉኝ ሌባ እሆናለሁ:: ጥሩ ልጅ ነህ ካሉኝ ጥሩ ልጅ እሆናለሁ:: መዓት የቀበሌ ባለስልጣን አለ አይደለም ሌባ? እሱ አይከሰስም?"

"አሁን ፖለቲካ እየተናገርክ ነው"

ዐይኑ የተገለጠ፤ አዕምሮው የበራ መሰለ::

"ፖሊስ ብሆንስ እኔ?" አልኩት

ቀና ብሎ በድንጋጤ አየኝ......ጉርሻውን በጉንጩ እንደሞላ:: ላረጋጋው ፈገግ አልኩ::

"ቀልጬ ነው"

"ምንም ቀልጬ አይደለም.......ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ዩኒፎርሜን እይ"

"ለምን ምሳዬን ዶሮ አበላኸኝ ታዲያ.......ምኔ ነህ?......ዘመዴ ነህ ምኔ ነህ?"

"ምናልባት እንዳትፈራኝ ሊሆን ይችላል" ለመሣቅ እየሞከርኩ::

"ዐይቼህ አላውቅም.......አታስፈራም አራዳ ነው የምትመስለው"

"የፖሊስ አራዳ የለውም?"

"ዕውነት ፖሊስ ነህ?" ዐየኝ አተኩሮ

"እርሳው"

የቤታችን በር ደፍ ላይ አንዲት ሴት መጥታ ቆመች:: ተያየን:: ቀይ ልጅ ናት......በእሷ ተክለ ቁመና ሳይቆረጥ እያሙዋለጨ ከገባው ፀሐይ ጋር የሚተካከል ቅላት የነበራት:: እጆቿን ግራና ቀኝ በቻልታ ዘርግታቸው የበሩን መቃፀኖች ይዛ ነበር:: ከበበ-ተሰብአቷ የሚያምር......የክንዶቿ ቅጥነትም እንደ ሐረግ ነበር:: ዐይኖቻችን በድንጋጤ ተሣሠሩ:: ያ ዱርዬ ሌባ ሕፃን የገባው መሰለኝ:: ፈገግ ሲል አየሁት::

"ምን ልርዳሽ እህት?" አልኳት ተረጋግቼ.......

"ከበኩረ ጋር አብረህ የምትኖር ነህ?"

"አዎ.......በኩረ እዚህ ነው የሚኖረው......"

ልጁ መብላቱን አቁሞ.......ያየናል......እየሳቀ

"ግቢ.......ግቢ ምሣ እንብላ"

እኔንና ልጁን እያቀያየረች አየችን::

"ተቀመጪ.......እንደውም የበኩረ አልጋ ይኼውልሽ......."



@BOOKALEM

የራሴን ድምፅ እሰማዋለሁ:: የራሴ ድምፅ እንዲህ ያለ ቅላፄ እንዲህ ያለ የልመና ቅላፄ አውጥቶ አያውቅም:: እየለመንኩ ነበር:: እራሴ አናደደኝ:: እራሴ እያናደደኝ ግን እንድትቀመጥ የበኩረን አልጋ አመቻችላታለሁ::

"የት ሔደ?" አለች

"ዘመድ ቤት ፋሲካን አሳልፋለሁ ብሎ ነው"

"እኮ ሳስታውሰው ነበር የመጣሁት"

"እሱ አስታውሷል.......ሌላ ቦታ ካልሆነ የሄደው"

"የት የሔደ ይመስልሃል?" እየተቀመጠች::

"እዚሁ ቅርብ አካባቢ ነው መሰለኝ:: በጣም እርግጠኛ አይደለሁም"

ዐይኖቿ የሆነ አስማት ነገር ነበራቸው:: በዐይኖቿ ሁሉን ይዛው የምትሔድ ይመስላል:: ወደ ግራ ስታይ ሁሉ ጉድ አይኖቿን ተከትሎ ወደ ግራ የሚሄድ (እኔም ወንድ ነኝ ባይ ወጥ የተነከረ ቀኝ እጄን ወደ ሰማይ አንቀርፌ ላለመውደቅ እየተንገዳገድኩ):: ወደ ቀኝ ስታይ ያው ሁሉ እኔ፣ ልጁ፣ አልጋው፣ መንገዱ፣ ቤቱ፣ ሰፈሩ፣ አዲስአባ.......ጠቅላላ ኢትዮጵያ፣ ሕንድ ውቅያኖስ.......በመጨረሻ እግዚብሔር ራሱ በመተፋፈር እየተያየን......ወደቀኝ:: የምትነካ ናት:: የሚለፈለፍላትም የምትነካ ነበረች::

"ለስላሳ ይምጣልሽ.......ወይ ሻይ ይፍላልሽ?" 'እኔ ላድርግልሽ' እንዳይመስል እየለፋሁ:: ባልሰለጠነ ደንባራ መግደርደር::

"እቸኩላለሁ.......ትነግርልኛለህ?"

"እዎ.......ማን ፈልጎህ ነበር ልበለው?"

"ገነት"

"ገነት.......እሺ.......እኔ መዝገቡ እባላለሁ"

እጄን ዘረጋሁላት:: ልጨብጣት:: ተጨባበጥን:: ወጥ የነካው እጄን ሸሽታ ግራዬን::

እጅ::

እግዜር የእሷን ዓይነት እጅ ሰርቶ.......የገነትን አትክልት ቦታ ከበለስ ዛፍ ጋር ለምን ፈጠራት?.......በእሷ እጅ አምሳያ ቢፈጥር ኖሮ ሰውን ያለ ሽሽግ ደካማነት ይሰራው ነበር.......ሁሉን እኩል ያደርገው ነበር.......አብዮት አያስፈልግም ነበር.......ፖሊስ



@BOOKALEM

አያስፈልግም ነበር.......መንከራተት አይኖርም ነበር:: ወታደር፣ ጭቆና፣ ድህነት፣ ሞት አይኖርም ነበር:: እግዜር የእሷን እጅ እያየ ጭቃ ቢያቦካ ኖሮ::

ጨብጣኝ ስትሔድ ባቷን ከሁዋላ......ማንም ሳያየኝ በሚስጢር ባቷን:: ባቷን በገብጋባ ዐይኖቼ:: እሷን የጨበጥኩበት ግራ እጄ እንደተንከረፈፈ.......ወጥ የሸፈነው ቀኝ እጄ እንደተንከረፈፈ.......ዕንቁላሏን እንደ ዘረፉባት ጭልሊ.......ሁለመናዬ ተንከርፎ::

ስትራመድ ሌላ ናት:: በከፊል ንፋስ እየገፋት::

ደ'ሞ ሁለቴ ወደ እኔ ዞር ብላ አየች......ለአፍታ አፌን ብቻ አውጥቼ በሐይ ውስጥ የተንቃቃሁት.......ምች ሳይመታኝም እንዴት ቀረ?

የመብላት ፍላጐቴ ተቀጨ::

"በላህ?" አልኩት ልጁን

"እየበላሁ ነው"

"ዕንቁላሎቹን ብላ"

ሁለት ዕንቁላሎችና ሁለት የዶሮ እግሮች ትሪ ጥግ እንደተዘነጉ ነገሮች በቸልታ ወድቀዋል:: ልቦናችን ግን አልረሳቸውም:: እስር ቤት ታስረው የመፈቻ ጊዜአቸውን እንደሚጠባበቁ ፀረ-መንግስት እስረኞች......ቀድሞ ተጠርቶ ከተገደለው ተርፈው የሚጠብቁ:: ልጁ አንዱን ዕንቁላል በጣቶቹ ሰብሮ.......ጥፍሩን ጠባ::

"የአንተና የእኔ ፋሲካ ዛሬ ነው" አልኩት

ሣቀ::

"ዕድሜህ ስንት ነው?"

"አስራ አንድ.......መሰለኝ......."

"ደስ ይልሃል?"

"ምኑ?"

"አሥራ አንድ መሆኑ?"

"እኔ እንጃ"

"ሥምህ ማን ነው?"

"ዘገዬ"



@BOOKALEM

"ዘገየ.......ሲርብህ ማታ ማታ ጫልቱ ቤት ና.......አንድ ጠላ ቤት አለ ታች ወረድ ብለህ.......ታውቀዋለህ?......ሠፈርህ የት ነው?"

"ሰፈሬ ልደታ ነው:: የጫልቱን ቤት አውቀዋለሁ"

"ለምን አላውቀውም አልከኝ ቅድም?"

"ፈርቼ ነው"

"አትፍራ:: ለማንኛውም ከራበህ ማታ ከአንድ እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ ካልመሸብህ ጫልቱ ቤት በር ላይ ጠብቀኝ......እሺ?"

አንዲ ዕንቁላል ወደ ሆዱ ጠፍታለች::

"አትፈር.......ንፋ......."

ማቀ:: ቀስ እያለ ይበላል

"ጏደኞቼ ግን ኒንጃ ነው የሚሉኝ"

"ኒንጃ? ካራቴ ትችላለህ?"

"ካራቴ.......ታዲያስ......."

ያጣጥማል::

"አጥንቱ ይጣፍጣል?"

"አዎ......."

"የሰረቅኸውን ዶሮ ትመልሳለህ?"

ሀየኝ::

"አልመልስም:: ይሄኔ ሸጠውት ይሆናል"

"ማን?

"አብረውኝ የሰረቁት.......ሌባ ከተባልኩ ሌባ መሆኔ ስለማይቀር.......ሌባ መሆን አለብኝ......."

"ከቻልክ መልሰው......."

"ዕውነት ፖሊስ ነህ?"

"አዎ ለምን እዋሽሃለሁ"

ትከሻውን ነቀነቀ:: እንደ ግድ የለኝም::



@BOOKALEM

"በልተህ ከጨረስክ በሁዋላ.......እዛጋ በባሊ ውሐ አለልህ.......ትሪዋን ታለቀልቃትና.......ትመልሳለህ"

ጉርሻውን እንደያዘ.......እራሱን በእሽታ ነቀነቀ......

ገነት:: ገነት:: ዐይኖቿ እንደ ሴቶች ነበሩ:: አሙቀው እንደሚስሙ ሴቶች ናቸው:: እውስጤ......ከሩቅ፣ በጣም ከሩቅ ደስታ ነገር ተሰማኝ......ትርጉሙ የረቀቀ::

"ከበላህ በሁዋላ አትተኛም?" አለኝ ልጁ

"ምነው?"

"ብዙ ሰዎች ይተኛሉ"

"መተኛት ፈለግህ?"

"እኔ ሳልሆን ትልልቅ ሰዎች"

"ሰነፎች ናቸው"

"ጥሩ ነው አሉ.......ያወፍራል"

"ውሸት ነው......."

መብላቱን ቀጠለ:: ሁኔታው አጥንት ይሰብራል.,.....

ገነት:: ገነት:: ከንፈሮቿ ንፋስ ከመታው ዛፍ ላይ እንደሚረግፍ በቅቷቸው እንደበሰሉ አበቦች ነበሩ......

ገነት......ገነት:: ድምጿ......ተረስቶ እንደኖረ እንደ ልጅነት ዘፈን......ካረጁ በሁዋላ እንደሚሰሙት ነው......የድምጿ ቀላልነት ዕንባ ያሳድማል......

ልጁ የሰባበረውን አጥንት ወደ ውጭ ወርውሮ ሳህኑን ማለቃለቅ ጀመረ:: ጣቶቹን ወደ አፍንጫው ወስዶ ያሸታል:: ዐይኖቹ የዕንባ ቅባት ውስጥ እያብለጨለጩ ተኝተዋል:: የእኔም ዐይኖች እንደ ፈሰኩ ነበር......የትዕይንት ጠማቸውን በገነት እንደ ቆረጡ......



@BOOKALEM

# ማነህ አንተ?

ወደ በቅሎ ቤት የሚወስደውን ምንገድ ሳቋርጥ ከወዲያ ከበስተቀኜ ከነዳጅ ማደያው ትንሽ ከፍ ብሎ ዝተት ከሁዋላው እንደ ነገሥታት ካባ እየጎተተ የሚመጣ ሰው አየሁ:: ለአፍታ በጥንቃቄ ለማየት ቆም አልኩ:: ሰውዬው በእኔ ትይዩ ቆሞ የሆነ ነገር ጮኸ:: በጥራት አልሰማሁትም ነበር:: እንደ ሰብድ ስለቆጠርኩት ቆሜ ጠብቄ የተናገረውን ለማጣራት ፍላጎቱም አልነበረኝም:: መንገዱን አቋርጬ እንደ ጨረስኩ ከበስተላይ ዝግንትሉን እየጎተተ (የቡቱቶው እርዝመት የመኪና መንገዱን ግማሽ ሞልቶታል) ሲያቋዋርጥ በቀኝ ዐይኔ ቂጥ አየሁት:: አረማመዱ ቅጥ ውስጥ የአፈጣጠሩን አጨራረስ የሚያውቅ ይመስላል:: በሃሳቤ በጣም ረኀርም ሰውዬ ነው እያልኩ ነበር:: ጮኸ......

"ጎድ:: ፖሊስ ነፍሴ:: ፖሊስ የነጻነት የሠላም ሰንሰለት"

ዞር አልኩ:: ቆሜ እየጠበቅሁት አለበት እንዲቆም በእጄ ምልክት ባሳየው እንዳልገባው እየጣጣሰ መጣ:: ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ቆም ብሎ ቀኝ እጁን ወደ ጉያው ሰደደና እንደ ሃኔ የተቆለመመች አንዲት ባለቡሽ ዊንስተን ሲጃራ አወጣ:: በልቤ እንደዚህ ዐይነት እብዶች ከእኛ ለፍተን ከምናድረው የበለጠ ሳይዝናኑ ይቀራሉን? እላለሁ:: ሲጃራዋን ከአብዮት አደባባይ ንፋስ ለመጋረድ ቡቱቶውን ወደ ፊቱ ሰበሰበና ለኮሰ:: ከቡቱቶው መሃል በየቀዳዳው ነጭ ጢስ እየተንፈለፈለ ወጣ:: በልቤም አስገራሚ አጫጫስ ነው እላለሁ:: የፊቱ ግራና ቀኝ በጢም የተሸፈነ፣ ቅንድቦቹ አባ ጨጓሬ የመሰሉ፣ ግንባሩ በወዝ የተጠመቀ፣ ከንፈሮቹ ወፍራምና በትንባሆ የጠቆሩ ነበሩ:: ለአፍታ የማውቀው ሰው ፊት መሰለኝ:: የለመድኩት ግን ልገልፀው በማልችል ምክንያት ሰሸሸው የኖርኩት ፊት::

"ሰማ ወንድም ፖሊስ፣ ስምህ ማነው? "

"ምን ያደርግልሃል? ምን እያደረግህ ነው እዚህ? "

"ሰው ሁሉ ስም አለው:: አገሬ ላይ ነኝ ደሞ:: አይደለም እንዴ?»

"ምን ፈለግህ? "

"ማነህ አንተ? "

"ማነህ የምትጠይቀኝ? "

"ይቅርታ:: ይቅርታ:: ስሜ ከጠፋ ከረመ:: 'ወሉዬው' ይሉኛል:: ከወሉ ግን አልመጣሁም:: አይገርምም? 'ውሉዬው' በለኝ"



@BOOKALEM

"ምን ፈለግህ? "

"'ጌታዬ' እንዳልልህ ጌታህ የሚበዛ ሰው ነህ:: ስምህ ለእኔ ዐይነት ሰው አይነገርም? ማነህ? "

ለመመለስ አልፈለግሁም::

በጥያቄው አለመደሰቴን አውቆ: "ብዙ ጊዜ አይሃለሁ:: በተለይ ቸርቸር ጎዳና ላይ:: ላናግርህ እፈልግና:: ለመሆኑ ማነው በዐይን ብቻ ማን እንደ ሆን የሚታወቀው? ቾኩሎ ነገር አይሰራምና ይሄ ፖሊስ ብሩህ ነው ብሎ የመደበ ማነው? ኢትዮጵያን ዞሪያለሁ:: አጠናቅቄአታለሁ ማለቴ አይደለም:: እንዳንተ የፈዘዘ.......የረጋ ማለቴ ሃ! ሃ! ሃ! ቁመና ያላቸው ጥቂት ናቸው:: በየመንገዱ ሳንተያይ ተላልፈናል:: እስኪ ይታይህ እኔ ለፖሊስ ዐይን ስጋረድ:: ቅርናቴ ራሱ የሞተ አይቀሰቀስምን? አንተ ግን አልፈኸኛል:: ለምን? ሰው መሆኔን አውቀሃል:: ቢያንስ አደጋ ያለው ሌላ ቦታ እንደ ሆነ እውቀሃል:: የጤነኛ ሕዝብ እጅ ዐይቶ የሚኖር እንዴት አደገኛ ይሆናል:: ቀላል ነው" አለ::

"ምን ትፈልጋለህ? "

"ሳወራህ ስምህን እያነሳሁ መሆን አለበት"

"ይቅርታ ስራ አለብኝ:: ወሬ ሰልችቶኛል"

"ገባኝ"

"ያን ሰው ታየዋለህ? አብረን ነው የምንሰራው:: ወሬውን ስለሚያበዛው ሸሽቼ ወደዚህ መጣሁ:: ስሸሽ ምን አጋጠመኝ ወሎዬው ሆይ? ሠላም የማትሰጠው አንተን"

"ስምማ ውሻም አለው:: `መቻል´ መልካም ስም አይደል? ስንት የሚያምር ስም አለ:: *ስምስ ነበራት ብርቱካን፤ ነገሯ ነው የፈጀን* ሲባል አልሰማህም? ውስጥህ ማነው? "

"ምንድን ነው የምታወራው? ማነህ አንተ?!!" አልኩት ቆጣ ብዬ::

"ነገርኩህ:: ስም ሽፋን ነው:: መልክ ሽፋን ነው"

"ይሄን ሁሉ የምትነግረኝ ለምንድነው? የፈለግኸውን ሁን:: ወደምትሄድበት ሂድ:: ዞር በልልኝ ወንድም"

"ወንድም? ተመስገን:: እስከዛሬ አልተባልኩም ነበር"

ፊቴን አዙሬ ለመሄድ ጉዞ ስጀምር.......

"እስከ አሁን ለመሆኑ ምን ስትተነፍስ ነበር?" አለ::



@BOOKALEM

"ምን አልክ?"

"ምን ስትተነፍስ ነበር?"

"አየር ነዋ" አልኩ መንገዴን እየቀጠልኩ::

"ምን ዐይነት?"

"ንገረኛ:: ጠቢቡ አንተ አይደለህም?"

"ምነው ወንድሜ ፖሊስነት ችግር ካለበት ጋር ካልተነጋገርክ ቁም ነገር የለውም:: ሽሙጥ የፈሪዎች ጥበብ ነው"

"ምን አገባህ?" ልለው ዞር ስል በጣም ማራኪ የሆነ ፍንጭታም የሕጻን ልጅ ፈገግታ አሳየኝ::

ዝም ብዬ አየሁት::

"የምትተነፍሰው እኔን ነበር ወንድም"

"ምን?"

"እኔን ነበር" አለ እንደሚያዝን አንገቱን ሰበር አድርጎ::

አናቱ መሃል የተነሰነሰ አቧራ የመሰለው ነገር ሽበት መሆኑን አየሁ::

"ምነው ወንድም ወሎዬ በስተርጅና እየዞርክ ባትረብሽ:: ደሞ አንተ አየር ነህ ምንድነህ የምተነፍስህ:: አዲስአባ የማታመጣው ጉድ የለ"

"የሁሉ ነገር መጀመሪያው ይሄ ነዋ:: መተንፈስ:: ትንፋሽ:: ለመሆኑ ስምህን የማላውቀው አንተ ሰው በአሁኑ ሰዓት ንፋስ ወደየት እየነፈሰ ነው?"

"ወደ ምስራቅ.......ግን ምን አገባኝ?"

"እዎ:: እኔና አንተ ተቀራርበን ስለቆምን ንፋሱ በእኔ ላይ ነው የሚያልፈው:: ምን ማለት ነው? ጠረኔን አንተ እያሸተትክ ነው ማለት ነው:: ውስጥህ ነኝ:: በደም ስርህ ነኝ:: ሠላም ይነሳሃል እንዴ? "

"ምንም አልሸተተኝም"

"ምን እንዲሸትህ ጠብቀህ ነበር? አንዳንዱ ነገር ቆይቶ ነው የሚሸተው"

"በል እሺ ልሂድበት"

ጎኤ ኩስ ኩስ እያለ ጎን ጎኔን ተከተለኝና፡ "ይሄ ሕዝብ አያሳዝንህም? እጁን ሰብስቦ ሲሄድ? ደሴቶች አይመስሉህም? አንተስ? "

"ተወኝ:: የራሱ ጉዳይ"



@BOOKALEM

"እጅህን ሰብሳቢ ነህ? ንክኪ ትፈራለህ?"

"ምን ታወራለህ?" አልኩት ዞር ብዬ።

ቆም አለና ሲጃራውን ወደ መሬት በችኮላ ጣለ።

ለማውራት አቃተተና በቡሉኮው የተሸፈነ ትልቅ የቆዳ ኮሮጆ ለመሸኮም አመቻቸ።

"ቢያንስ ጣትህን ታስገባለህ? ወይስ በፍርሃት እንደነዚህ ከብቶች ትሸሻለህ? ባለ ጉዳይ አይመስሉም? ብዙዎቹን ሆነ ብዬ ተከታትዬአቸዋለሁ። ጉዳይ የላቸውም ግን ይቸኩላሉ። ፊታቸው የተላጨ እናት አይመስልም? ዐይኖቻቸውና አፎቻቸው በቀለም የተሰፉ አይመስልም? ስዕሎች ይመስሉኛል። ፈሪ በአስፈሪ የተፈጠረ አሻንጉሊት ነው። አንተስ?"

"ፈሪ ነህ ልትለኝ ነው? "

"አልወጣኝም ጓድ። ወደ ሕይወት እሳት እጅህን ማስገባት ትፈራለህ። ብዙ ሰው እንደዛ ነው"

"ያንተ ጉዳይ ነው ይሄ? አንተን ማሰር አለብኝ ደፋር ለመባል?"

"ደካማን ማሰር ማንን አሪፍ ያሰኛል"

"የፈለገውን ልባል ተብዬ ባስርህስ"

"ነገርኩህ። ውስጥህ ነኝ። እኔን ስታሰር ራስህንም ነው የምታስረው። ለዚህም ነው ቀደም ብዬ ውስጥህ አለሁ የምልህ። ገላህ በሆነ መልክ ገላዬ ነው። የኔንም ገላ ብዙ ሰዎች ወርሰውታል። ከሆቴል ቤት ትርፍራፊ ይገፔ ነው የምመጣው። ብዙው ቀይ ወጥ ነው። ሰዎች ለምን ክትፎ አያስተርፉም? ለአዋይ እንኳን አያስቀሩም—ለጥያቄው ያህል። የሃምሳ ሰዎች ትራፊ የምበላ ከሆነ የእነሱ ወዝ ሆዴ ውስጥ አለ። ብደምረው ብደምረው የሕዝብ ሰው አልሆንም? መንካካቴን አላፍርበትም። አዳምና ሄዋን ባይነካኩ እዚህ እንደርስ ነበር? እኔን ማሰር ቀላል ነው። በመከራ ታስሬ አልቄአለሁ። አሪፍነት የለውም። ደካማ የሚያሳድዱ የወጣላቸው ፈሪዎች ናቸው። ልጠይቅህ?"

"ምን?"

"ደሄ አቧራ ከየት መጣ? ፍርሃትህን በቾልተኛነት ትሸፍናለህ መሰለኝ። ግድየለኝም ግድ የለኝም"

ሌላ ትንባሆ አወጣ።

"ፈርቼ አላውቅም"

"ስቀልድ ነው። አፌ ማረፍ ይከብደዋል"

"እያየሁ ነው እሱን"

"ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! ቀልደኛ ነህ። አንድ የረሳነው ነገር አለ"

"ምን?"

"ስምህን አልነገርከኝም"

"ምን ያደርግልሃል? "

"ለማወቅ"

የስራ ጓዴ ከወዲያ በኩል ደንና ዱር አራዊት ሕንጻ ስር ቆሞአል። እጁን ያወዛውዝልኛል። 'ምነው?' አልኩት ራሴን በመነቅነቅ።

"ይሄን ሰው አልወደውም። ተራ ብልጥ ነው" አለ ወሎዬው።

ዞር ብዬ ወሎዬውን ሳየው እኔን በፍጥነት አልፎኝ መገስገስ ጀምሮአል። ጓደኛዬ ምንገድ እየተሻገረ ነው።

"ምን ይልሃል? " አለ ጮክ ብሎ ገና እኔ ጋ ሳይደርስ።

"ምንም"

"ረባሽ ቢጤ ነው"

ወሎዬው ስሜን ሲጠራ ሰማሁት። ዞር አልኩ ወደ ሁዋላዬ።

ወሎዬው ብሉኮውን አናቱ ላይ ሰብስቦ ነጭ ፍንጭቱን እንደ ጭላዳ ገሽለጠና፡ "በጣም አመሰግናለሁ ስላዋራኸኝ መዝገቡ!! " አለ።

ሳቁ አየር ላይ የቀረ መሰለኝ። የፍንጭት ሰልፉ በእሱ አፍ ቁመት ልክ አየር ላይ እንደ ትንሽ የሚፈልቅ የፊት መስታወት እየተንሳፈፈ።

"ስሜን ማን ነገረው? " አልኩ።

የስራ ጓዴ ጎኔ ቆሞ እየሳቀ ከደረት ኪሱ ሲጃራ አወጣና እየለኮሰ፡ "አውቆ አበድ ነው። የሚናገረውን ጤነኛ አይናገረውም"

"ማን ነገረው ስሜን? "

"ይጠይቃላ!! ጠዋት ላይ ስታድዮም ዙሪያ ነበር"

ሁለታችንም ቆመን እያየነው አንዴ ብቻ ዞር ብሎ አይቶን ያን ተንጠልጥሎ የሚቀር ሳቁን ደግሞ አሳየኝና የዕድገት በህብረትን ምንገድ አቅጣጫ ይዞ የአብዮት



@BOOKALEM

አደባባዩን ሷሬ የአስፋልት ሜዳ በሩጫ መሻገር ጀመረ። በዚህ ፍጥነት የሚሮጥ፣ እንዲህም ዐይነት ቡቱቶ ያግተለተለ፣ እንዲህም የረዘመ ሰው እስከ ዛሬ አላየሁም።

"ቡቱቶው ራሱ የትራፊክ ምንገድ አይዘጋም? ለምን አናስረውም?"

"ለምን? "

"ሠላም ይነሳል"

"ወሬኛ ነው በቃ"

"ለደኅንነት አያሰጋም?"

"ሽወደኝ"

"በዚህ ጉልበቱ መሸከም ቢሰራ በወር ሚሊዬነር ይሆን ነበር" አለ

ዞር ብዬ ወሎዬውን አየሁት። በአፍንጫው ቀዳዶች የሲጃራ ጢስ እየተናደ ይወጣል። ያስፈራል።



@BOOKALEM

# ሜልቱ ያሳወቀችው ነገር

ሜልቱ ፋሲካዬን እንዳጠናቀቅሁ አልገባትም ነበር:: እኔ ፋሲካዬን እንደጨረስኩ የእሷ ፋሲካ እንደማያስደነግጠኝ አልገባትም ነበር:: ሜልቱ ጥሩ ሴት ናት:: ሜልቱ ችግሬን መረዳት ያልቻለች ጥሩ ሴት ነበረች:: እንደ ጣቃ በተዘረጋው ሰቆቃዬ ላይ ደስታዎቼ አፍታ ነበሩ:: ከድምፆቼ ሰምብርት የፍስሓዬን ትኩስ የተገፈፍኩ ነበርኩ::



@BOOKALEM

# ፊት

እንደ ፊት የሚያናድድ የገላ ክፍል የለም። አንድ ጠዋት ሳይ ቁርሴን እንኳን ሳልበላ ከሰፈሬ ወጥቼ የደፈረሰ ሐይቅ የሚያስቀና ትልቅ ምራቅ፣ ግዙፍ ትፋት እንደ ቤኘ ብርድ ልብስ መሐል ጉዳና ላይ ወድቆ ሳይ......ፊት ባልተፈጠረ ብዬ ተራገምኩ። ፊት ባይኖር አፍ የለም። ዶሮዎች ፊት ስለሌላቸው ምራቃቸውን አይተፉም። የፀጉሬን መስተካከል ለመፈተሽ መስታወት ሳይ መጀመሪያ ድቅን የሚለው ካልጠፋ ብልት ፊቴ ነው። ስለ ፀይን ተብሎ ነው እንጂ ፊት ባይኖር መልካም ነበር።



@BOOKALEM

# ስሰጣጥ

እኔ መቸም ከተወለድኩበት ከተማ ('የተወለድከው እዚህ ነው' ከተባልኩበት ከተማ) የመጣሁት ፍፁም ንፁሕ ሰዎች ፍለጋ አልነበረም......

እንጀራዬ ነድቶኝ ነው የመጣሁት:: እንግዲህ ጫልቱ መጋቢዬ ናት:: ከእሷ ጋር ከመጋቢነትና ከተመጋቢነት የወጣ የተለየ ግንኙነት አልነበረኝም:: እንዲኖረኝም አስቤ አላውቅም:: የምትሰራልን እንጀራ ብዙ ዐይነት እህል የተደባለቀበት መሆኑን በላተኞች ሁሉ ብናውቅም እሷን ላለማስከፋት በተለይ ጃጋን "ይኼ ስንዴና ጤፍሽ አወፈረን" ይላት ነበር (በጆሮዬ ጠጋ ብሎ ግን ('እንጀራውን እንዳለ አንስተህ ወደ ላይ ብታንጠለጥለው ደዮው ወደ መሬት አይወድቅም:: ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? ሽሮው ጥፍር አለው:: ሃሃሃሀ' ቢልም):: እና ምን አልባት ታዲያ ፍቅር፣ መውደድ ከሁሉ ይበልጣልና......ሳይበልጥ አይቀርምና.......አንዳንድ የወዳጅ ስህተቶች ብንጋርድበት ምናለበት:: ጫልቱ አስከፍታኝ ስለማታውቅ፣ እኔም አንድ ቀን እንደ ጃጋን በራሴ አማርኛ ለመግለጥ፣ የእሷን ሥራ ለመካብ......

"ዋናው አሰጣጥሽ ነው" አልኳት::

በዚህ አባባሌ ቤቱ ውስጥ የነበሩ ጥቂት ሰዎች በሙሉ በሳቅ አይፈነዱም! ጫልቱ ራሷ አፏን ወደ ሰማይ ሰቅላ ተንካካች:: እየሳቁ፣ እያረፉ ደ'ሞ የተናገርኩትን ቃል እየደጋገሙ፤

"አሰጣጥሽ አላት!"

"ሆሆይ......አሰጣጥ!እ?"

"አሃ......የት ትተዋወቃላችሁ?!"

በቃ የመሳሰለ የሚያበሽቅ ነገር መናገር ጀመሩ::

ምን ለማለት እንደፈለግሁ እንዳልገባቸው ሁሉ ዕንባ ባቀረሩ ዐይኖቻቸው:: (ለመሆኑ ዕንባ የሚያስቀርር ምን ነገር ተናግሬ ነበር?)

ከመሐል ጫልቱ ከሳቋ አረፍ ብላ፡ "ኧረ ተውት እቴ መዝገቡ ይኼን ዐይነት ነገር አያውቅም:: ጨዋ ነው:: እሱ እንደ ወንድሜ ነው" እያለች የሰዎችን አባባል ስትሽር ዐይኖቿ ውስጥ የሚቃጠል ነገር አየሁ:: አስጠልታኝ ትቻት ባልሮጥም በልቤ ተቀየምኳት::

መቸም ከተወለድኩበት ከተማ ፍፁም ሰዎች ፍለጋ አልመጣሁም::



@BOOKALEM

በመጀመሪያ ከዚህ በፊት እንደፈለገችኝ አንዳንድ ነገር ጠቁማኛለች:: ሁለተኛ ያኔውኑ እዚያው ሰዎችን በአፍዋ እየከዳች ዐይኖቿ ውስጥ ለእኔ 'ለመስጠት' ያላትን ምኞቷን አየሁ:: ሦስተኛ በተቃራኒ ከሴት ጋር በፍትወት አለመገናኘትን 'ጨዋነት' ብላ መሰየሟም ገረመኝ::

የትኛው ነው ዕውነት?

ምናልባት የምሰማው፣ ሰዎች የምገነዘበው ስህተት ከሆንስ? በሌላ በኩል ደ'ሞ የቋንቋው ጠማማነት:: ሴት ለወንድ የምታቀርበው የአካል ስጦታና በቆሎ፣ ዘንጋዳ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ወዘተ የመሳሰሉ እህሎች የተደባለቁበት እንጀራ—ድንች፣ ምስር፣ ክክ፣ ሽሮ ተደበላልቀው የተሰሩበት ወጥ በመለስተኛ ትሪ አጭር ጠረጴዛ ላይ በአንዲት ጉራዳ ሴት ለመበላት መቅረባቸው ምናቸው ይመሳሰልና ነው.......

ትክክለኛ ቃል አለመምረጥ ሆን ተብሎ የሚሰራ ነው መሰለኝ-ለማምታታት::

ቆሻሻ ወለል ላይ ቆመን፣ ቆሻሻ ወንበር ላይ ተቀምጠን፣ ቆሻሻ ትሪ ላይ ሲበርድ እንደ ቀርከሃ የሚሰበር ዘንጋዳ እንጀራ እየበላን ቅኔ ያስፈልገናል እንዴ?

እንደው የሚገርመው......እኔ ለ 'አሰጣጥ' የሰጠሁዋት ትርጉም እነሱ በሰጡት የ'አሰጣጥ' ትርጉም ተበላች:: ስትበላ.......ስትቦጫጨቅ፣ ስትደማ፣ ስትፈራርስ......ተሳቀ:: በጣም ተሳቀ::

ውርጭ እንዳያገኘኝ የምከለልበት ስጡኝና፣

ሀሁ መቁጠሪያ ስሌዳ ስሩልኝና፣

የምዋኝበት ወንዝ ስጡኝና፣

የምጊዝበት እግሬን አትሰሩትና፣

ያን ጊዜ ከፈለጋችሁ 'አሰጣጥ' ብላችሁ ከቁም ነገር ይልቅ ዝባዝንኬ ማውጣት በለመደ አፋችሁ ሃ! ሃ! ሃ! ሃ!......ሳቁ::

በዚያ አፋቸው ይሳቁ::

ብልሐታቸው ከድምፅ ባላለፈ::

ዘንጋዳ እየሰበሩ.......እሱም እንዳያንቅ ቅራሪ እየጠጡ......

'አሰጣጥ!' ብለው በዚያ ቁም ነገር መውለድ በሚከብደው፣ ማሕፀኑ በደረቀ አፋቸው ይሳቁ:: ከፊቶቻቸው ላይ ባሉ ቀዳዶች እንግዴ ነገር ይውለዱ::

ቀይ ድድ ያላቸው አፎች አልወድም::



@BOOKALEM

የሚነክሱ አፎች አልወድም::

የሚያደሙ አፎች አልወድም::

የሚያዳልጥ ምራቅ የሚያዝረበርቡ አፎች አልወድም::

'አሰጣጥ'

አንዱን ወስዶ አንዱን ትቶ፣ እንደገና የተውትን አንስቶ የአነሱትን ትቶ......ሲመች ቅኔ አልወድም:: እሺ ይሳቁ:: ስቀውም ያቁሙ:: አቁመውም ለራሳቸው ያሰላስሉ:: ግን እኔን በዚህ ስህተት ውስጥ መተርጐም ምን አመጣው????

ታዲያ ከጫልቱ ቤት እንወጣና፣ ብርድ ያሳነሳቸው ከንፈሮቻችንን እየላስን፣ በጫማዎቻችን ቀዳዳ ንፋስ ስፒሉን እየተከለ፣ የብብታችን ፀጉር እንደዋሻ ሀረግ ሽብቶ፣ ከሳዳችን ጠቁሮ፣ ገፃችን ገርጥቶ፣ ከወገባችን እስከ ጉልበታችን ተባይ እየተንቀሳቀሰ፡— 'አሰጣጥ'

ሁላችንን በእንዲህ ያለ ቅኔ ያሰለጠኑን ከብርድ እርግማን፣ ከተባይ እርግማን፣ ከጾዮ እርግማን ፣ ከድንቁርና እርግማን፣ መቻ ነው የሚያላቅቁን::

'አሰጣጥ'

ጫልቱ ሰጠች አልሰጠች አያገባኝም:: ቅኔው ለእሷ ደስታ ሰጥቷታል:: ትፍነከንካለች:: እንደ ሽሮ ትፈላለች:: አሰጣጧ ቢያምር የት ትደርሳለች? ምነው ስድቧን እየኩራች ተቀበለች? ምነው እየኩሩ ሰዎች ስድብ ተቀበሉ? ታዲያ ብትፍነከነክ ዘንጋዳ ከመጠፍጠፍ፣ ሊጥ ሊጥ፣ አብሲት አብሲት ከመሽተት እንዴት እንደምታመልጥ ነገረዋታል? አዲስ ስፍራ ተዘጋጅቶላታል?

ከዚህ ወጥተን ለየብቻችን በሚያቃስት አልጋችን ላይ ስንሆን ያኔ እውነቱ ይመጣል:: ያኔ አፋችንን የሚሰፋ መልአክ ከሰማይ ድንቅ ወስፌ ይዞ ቢወርድ እንወዳለን::

ለችልታችን የምንከፍለው ሒሳብ አለ::

ለ 'አሰጣጥ' የምንከፍለው ሒሳብ አለ::

በሁዋላ ስሰማ 'አቀራረብ' ነው የሚባል አሉኝ::

ብለውስ? እነሱ አሳምረው ብለውትስ የት ደረሱ::



@BOOKALEM

# ኪነትና......

በፀሐያማ የበጋ ዕለት ከጠዋቱ አምስት ሰዓት እስከ አሥር ሰዓት ከሰዓት በሁዋላ ድረስ ባለው ጊዜ አብዮት አደባባይ አካባቢ ላምስት ደቂቃዎች ያህል ወዲያ ወዲህ መመላለስ የሚችል ሰው ያለ አይመስለኝም:: እዚያ አካባቢ ያሉት ነገሮች ሁሉ የፀሐይ ጨረር መልሰው የሚያንፀባርቁ አስፋልቶች፣ መስታወቶችና ሲሚንቶዎች ነው ያሉበት:: ብረታ ብረትም ይበዛዋል:: መፈክር የሚለጠፍበት ከጀርባ ያለው ግንብ እንኳን የአቅሙን አመድ የመሰለ ብርሐን ይወረውራል:: ከተለያየ አቅጣጫ ተንፀባርቆ የሚመጣ ጨረር እንዳያሰቃየኝ መነፅር አድርጌ ወዲያና ወዲህ እያልኩ መዘባነን ሳይሆን፣ የእኔ አላማ ዐይኖቼን ሳልጋርድ ከመጥበርበር መሸሽ ነበር:: መነጽር አልወድም:: መነፅር የሚያደርጉትን ሰዎች እንኳን ሳይ ድምፄን ከፍ አድርጌ ባልናገረውም በብሽቀት ውስጤ እጮሃለሁ:: ከጨረር መሸሽ ግን አልችልም:: ሥራዬ ያስገድደኛል::

በተደጋጋሚ እዚያ አካባቢ፣ እዚያ አደባባይ ውስጥ ሕዝቡ ከሚያሳየው የድጋፍ ሰልፍ፣ መፈክርና ንግግር ይልቅ የሚገርመኝ ያን ከባድ ፀሐይና ነፀብራቅ፣ ፍልቃት ተሳታፊው እንዴት ሊቋቋመው እንደቻለ ነው:: የእኔ እንኳን የእኔ ነው:: ከድሮም ልምድ አለኝ–እዚያች ጉብታዬ ስቀመጥ:: ሌሎችስ? እነዚያ ሁሉ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የእኔን ዐይነት ልጅነት አሳልፈው ነበር ማለት ነው? ብልጥ መሆናቸው ነው ታዲያ የእኔን ዓይነት የስቃይ ልጅነት እንዳሳለፉ መደበቃቸው? የሚበልጡኝ የሚመስሉት?

አንዳንድ ቀን አደባባዩ ውስጥ ሕዝበ–አዲስአበ ተለሽልሾ ሳይ......አሁን እነዚህ ሁሉ እንደሻማ ቢቀልጡስ? ይኼ ሁሉ ሰው እንደሻማ ቢቀልጥስ? ብዬ ራሴን እጠይቀዋለሁ:: የምናቤ ጉም ይትጎለጎላል.......እያንዳንዱ ሰው እየቀለጠ ጉኑ ካለው ሌላው ጋር ተያይዞ ቡኒ የቀለም ቂጣ ይሆናል......ይኼም የበለጠ ሙቀትና ግለት ሲሰማው......በጭቃ እንደዳበረ ወፍራም ጉርፍ በስቲቀኝ በኩል ይፈሳል......በስተቀኝ በኩል በአስመራ ምንገድ ቀበና ይቀላቀላል......ከቀበናም አልፎ በአካባቢው ባሉት የከትፎ ቤቶችና ሰራ–ዶርስ ዙሪያ ይተማል......እዚያም ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ደህንነት ሕንፃ ውስጥ ሁሉ ይገባል......በስተምዕራብ የጅማን ምንገድ ይዞ ከፊሉ የስታዲየሙን ዙሪያ ይዘጋዋል......ከፊሉ በግዮን ሆቴል ገብቶ የመዋኛውን ኩሬ ይሞላዋል......በዚህ የቀለጠ የሰው ጉርፍ መሐል ጢም ብሎ የሚፈሰው ተለብሶ የነበረ የጨርቅ ክምር፣ ጋቢ፣ ነጠላ፣ ባርኔጣ፣ ዩኒፎርም፣ ጫማ፣ መሐረብ፣ የጠጉርና የጢም ሰፈፍ፣ ጥፍር፣ ጥርስ፣ የሰው አጥንት፣ መፈክር ተፅፎበት የነበረ የሚነድ ካርታስና ወረቀት፣ ክላቼንኮቮች፣

የሚፈነዱ ጥይቶች፣ የስልክ ደብተሮች፣ እስክሪብቶዎች፣ ቀበቶዎች......መነጽሮችም ተያይዘው ይፈሳሉ......

መነጽሮች አልወድም::

ኩረብታ ላይ በመቀመጥ እራሴን ማጋለጥ ለምጄ የለ? ሲያዩ አይታዩም ማን አለ? ወደ ታች ሳይ ወደ ላይ የሚያየኝ መች ይጠፋል? እንደ ኤልያስ አሮጊት ውሽማ እንደ አልቬቲ--ቅጽል ስሜን እንደነገረችኝ:: ታዲያ ሰው መነጽር አድርጐ ሲያነጋግረኝ እጠላለሁ:: ማናችን የሚደበቅ አለንና ነው በመነፅር የምንጋርደው?

ድሮ ገጠር እያለሁ የአዲስአባ ሕዝብ የተመቸው ነው......ለስላሳ ነው ሲባል እሰማ ነበር:: እዚህ መጥቼ በምንገድ ስመላለስ ግን መጣጣ የበዛው፣ ብጉር የነደለው ፊት፣ ጠማማ እግር ያላቸው ሴቶች፣ ትልልቅ ሆቴል የሚመላለሱ ለምቾት የሚሽቅሉ ሽርሙጦች፣ የልቡን መናገር የተከለከለ ምላስ፣ ሸካራ ጥርስ (ብዙ መሳቅ የከበደው)፣ የትም መድረስ ያልቻለ ብልጥ፣ ጠላ ሲጠጣ ብቻ መዝፈን የሚፈቀድለት፣ ሳንቲሞቹን ኪሱ ውስጥ ማግኜት ዙሪያ ያያዘ፣ ተጠራጣሪ ሆኖ ተጠራጣሪነቱን የሚደብቅ፣ ለመወደድ የሚያነፈንፍ ሆነብኝና......ይባስ ብሎ አንዳንዱ መነፅር አድርጐ ያነጋግረኛል......ወላ ግን ከማን ይደበቃል?

ከዚያ በሁዋላ በአብዮት ያመሃኛሉ:: ቢሆንም.......ምንም ቢሆን ሰዎች እዚህ አደባባይ መሰብሰባቸው አይቀርም:: ይመጣሉ:: አብዮት አደባባይ ሰዎች ለምን እንደሚመጡ አውቃለሁ:: የመንግስት ተቃዋሚዎች የሚያወሩት ሕዝቡ ስለተገደደ ነው እያሉ ነው:: መንግስት ደግሞ ስለወደዱኝ ነው ይላል:: ሌላ ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም? ጊዜውን ማሳለፊያ ሌላ ቦታ ያጣ ሰው ወሬ ለማየት ሊመጣ አይችልም? የት ያሳልፍ? ሚስቱ ሰልችታዋለች፣ ልጆቹ ይነጨንጩታል፣ ጐረቤቶቹ ነዝናዦች ናቸው:: መሰላቸት፣ መነጭነጭ በፖለቲከኞች ከመጠዝጠዝ ይሻላሉ የሚል የለም:: ስለዚህ ወደ አብዮት አደባባይ ይመጣል::

አብዮት የሚወዱም ይመጣሉ:: አብዮት የጠቀመውም ይመጣል:: ወይ የሰልፍ መሪ ሆኖ ወይ ባይሆንም እያዳነቀ......

ፀረ-አብዮተኛ የተባለውም ይመጣል:: የተጠረጠረ፣ ወይም ውስጥ ለውስጥ የሚሰራው ተንኰል ያለው ሰው ራሴንና ድርጅቱን ከማስበላ ብሎ ከአብዮተኞች የበለጠ እየጮኸ አብዮት አደባባይ ይመጣል::

ዝም ብሎ ፖለቲካ የሚፈራም ይመጣል:: የሚሆነው አይታወቅም በሚል በዝምታ አንገቱን ደፍቶ.......ከቀበሌው እስከ አብዮት አደባባይ ይመጣና እዚያ ውሎ በቀበሌ ታይቶ የሚመለስ አለ::



@BOOKALEM

አብዮቱ ውስጥ ለመሳተፍ የሚፈልግም ይመጣል:: ለአሰላፊና ለተሰላፊ ክበር እየመታ፣ መፈክር እያወጣ 'እኔም አለሁ.......አብዮቱ በድርጅቱ አደርሳኝ' ብሎ የሚቀርብ አለ:: ዝና ሰምቶ በአብዮተኞች ቤት ጮማ ይቆረጣል ሲባል::

ለስለላ የሚላክም አለ:: አብዮቱና ፀረ-አብዮቱ ሰላዮቻቸውን ይልካሉ:: ሁለቱም ቴርሞ ሜትራቸውን ይዘው የሕዝቡን ሙቀት ሊለኩ......ሲመች እንደፍላጐታቸው ሊያደንቁ ወይም ሊያንቋሽሹ::

ለተለየ ጉጉት የሚመጣም አለ:: ብዙ ሰው ሲሰበሰብ ምን እንደሚመስል ለማየት የሚመጣ አለ:: ይቃርም ይቃርምና......'ሰው ተሰብስቦ አንድ ቦታ ሲቀመጥ ለካ ይኼን ይመስላል!' ብሎ ተደንቆ ይሔዳል:: የሚያስቅም ነገር ሊያይ ይችላል:: ሰው ሲጣላ፣ ሲሰዳደብ፣ ሲተማማ፣ ሲጠባበስ፣ ሲዳራ፣ ሲያሽሙዋጥጥ፣ አባ ወራ መፈክር ለማለት አፉን ሲከፍት የሚታየውን የጥርሱን ብዛት፣ አባኮዳ የመሰለች የሴት ማሕበር ሊቀመንበር ክበሮ እያስመታች እዩኝ ስትል፣ ካድሬ ካድሬን ሲያመሰግን፣ የተሸነፈ ፖለቲከኛ ግንብ ተጠግቶ እንደበረደው ጉጉት ሲያቁለጨልጭ፣ ሻይ መጠጫ ያጣ ተሰላፊ ስታዲየም ዙሪያ የሚያውቀውን ሰው ገንዘብ ለመጠየቅ ሲባዝን፣ ዕቃ የጠፋበት ሰማይና መሬት ሲራገም:: ይሔ ሁሉ ይታያል:: ከዚያ ወደ ሰፈሩ ተመልሶ ያየውን ያወራና ይደነቃል:: 'ሆሆ......ተጫዋች እኮ ነው እሱ' ይባላል::

ኪስ አውላቂዎችም ይመጣሉ:: ጣቶቻቸውን አሹለው፣ ዐይኖቻቸውን ስለው.......መዳፋቸውን አለስልሰው:: ወይ ተሰላፊ ሆነው በቀበሌ ይመዘገባሉ ወይም ካደሩበት መጥተው በየጠባቡ ጉዳና እንደትራፊክ ይኩለኩላሉ::

አብዮት አደባባይን መቀናዘሪያ የሚያደርጉትም ይመጣሉ:: ቤተሰቦቿ በሌላ የቦዘን ቀን ከቤት አትውጪ የሚሏት ልጃገረድ ወይም ባሏን መሸወድ ያቃታት ሴት ለአብዮት ሰልፍ በመውጣት ያመካኙና......እንዲሰሙ አድርገው:......"ይኼ ቀበሌ መከራ አሳየኝ" ይሉና በልባቸው ግን እየሳቁ ቡታንታቸውን ለውጠው ይወጣሉ:: በቀበሌ ፊታቸውን ካስመቱ በሁዋላ ወይም አብዮት አደባባይ ደጃፍ ድረስ ብቻ ተሰልፈው ወደ አሰኛቸው ቦታ ይቆያዩና ሠልፉ ከመበተኑ በፊት ተመልሰው መጥተው ከተራብና ከተጠማ ሰልፈኛ ጋር ወደየቤታቸው ይመለሳሉ:: ታዲያ ማታ እነሱም አደባባይ እንደዋሉ ሁሉ ለባላቸውና ለቤተሰባቸው ስለ በዓሉ እያማረሩ ያወራሉ:: ዝርዝር ካልቻሉም "ምን እኮ እዚያ እኮ ሲደርቁ መዋል ነው" ይሉና ባላቸውን አቅፈው፣ ትራሳቸውን አቅፈው ቀን ስለጠጡት ምንትስ፣ ስለቆረጠሙት ናና ከረሜላ ያልማሉ::

አብዮቱን የሚጠሉም ይመጣሉ:: በየሰልፉ ታዲያ አብዮቱን ባይሆንም ለአብዮቱ የሚጮሁትን ለማሽሙዋጠጥ፣ ለመተረብ፣ ወደሚያምኑት ሰው ጆሮ ጠጋ ብለው የሆነ ካድሬ ላይ የሚያስቅ ነገር ሹክ የሚሉ:: ካድሬው ሲጠጋቸው የሚሽኰረመሙና ስለሰልፉ



@BOOKALEM

መልካምነት የጠዋት ጥርሳቸውን እያሳዩ «የሚፎግሩ»:: 'ያለፈው ዓመት እንዲህ አልነበረም' ብለው የማያወላውሉ ታጋይ ለመሆን ወደ ራሳቸው የሚጠቁሙ::

የዕውነት ተገዶ የሚመጣ አለ:: አብዮቱን በፍፁም የጠሉና በፍፁም የግል ነፃነት የሚያምኑ:: ከመጀመሪያውም አብዮት የሚባል ያልወደዱ:: ስለሐብታቸው መወረስ ሳይሆን ጭቅጭቁን፣ ንዝንዙን፣ ስድቡን፣ መጠሳሳቱን፣ መገዳደሉን፣ መቆሳሰሉን፣ ያልወደዱ......የትኛውም የፖለቲካ ቡድን ያልጣማቸው፣ የማይጥማቸው 'ፖለቲካችሁን፣ አገራችሁን እንደፈለጋችሁ አድርጉና እኔን ተውኝ የሚሉ ነገር ግን ማምለጥ ባለመቻላቸው በአንድ ቀን ሰልፍ ታይቼ የዓመት ሠላም ላገኝ ብለው የሚመጡ:: እነዚህ አብዮቱን እንደሚጠሉት ለማሳየት ፊታቸውን አያጠቁሩም:: አድርባይ ለመሆንም በደስታ ሊንፈቀፈቁ አይፈልጉም.......ፊታቸው ላይ ምንም የሚነበብ የለም:: ደስ ይበላቸው ወይ ይከፋቸው አይታወቅም::

ዋና ጉዳዬን እረስቼ ወደሌላ ወደሌላ ያዘመምኩ መሰለኝ:: የፖለቲካና የአብዮት መሐይም ስለሆንኩ ማውራት አይገባኝም ነበር:: ብቸኝነት መርገቡ የሚታወቀው.......የምላስ የእግር ብረት ሲላላ ነው ብለው በሚሉትም ነገር አላምንም::

አንድ ጠዋት ላይ በግምት አራት ሰዓት ተኩል አካባቢ እንደልማዴ ተረኛ ሆኜ ከባቡር ጣቢያ የትራፊክ መብራት እስከ አብዮት አደባባይ ያለውን ቦታ እጠብቅ ነበር:: ግራና ቀኝ መኪና ይራወጣል:: የመኪና ጩኸት አሰልችቶኛል:: አልፎ አልፎ ታዲያ የድምፁ ረባሽነትና ስራ ፈትነቴ ገፋፉኝና ገለል ለማለት አብዮት አደባባይ ገብቼ ሕዝቡ ከሚቀመጥባቸው ደረጃዎች መሐሉን መርጬ ተቀመጥሁ:: እዚያ ጥግ ሆነው ሲያዳምጡት የመኪናዎችና የተላላፊው ሰው ድምፅ ከሩቅ የሚመጣ ይመስላል:: መጠናቸው ሁሉ ያንሳል:: ፊት ለፊቴ የሕዝብ ደህንነት ቪዛ የሚሰጥበት ሕንፃ ነው:: በአንበሳ ሕንፃና በቱሪዝም ሕንፃ መሐል ተሰንቅሮ አሥራ ሦስት እራቶች ያመለጡት የተራበ ድንክ ይመስላል:: ፊት ለፊቱ መንግስቱ ሐይለማርያምና ሌሎች ባለስልጣኖች የሚቀመጡበት ሰገነት ነው::

ከጀርባዬ ሁለት ግዙፍ ስዕሎች ተሰቅለዋል:: በስተቀኝ ከሩቅ ትልቅ የማርክስ የሌኒንና የኤንግልስ ስዕሎች በአንድ ትልቅ ቀይ ሸራ ላይ ተዘርግተዋል:: ፊቶቻቸው (ጉንጭ ለጉንጭ ተነካክተው) ተጠጋግተው በመሳላቸው ነው መሰለኝ ደፋርና ትብብር የሚያደንቁ ይመስላሉ:: በስተግራዬ የኢትዮጵያ ባንዲራና የኮሚኒስቶች ባንዲራ ጉን ለጉን ግዙፍ ልሙጥ ቆርቆሮዎች ላይ ተስለዋል:: ራቅ ብሎ በስተግራ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር የሚወስደው ምንገድ አጠገብ ስዕል ያልተሰቀለበት የእንጨት ፍርግርግ ጎን አጥንቶቹን ከፍቷል:: የቀኝ ፊቴን ፀሐይ......የረፋድ ፀሐይ ትገርፈዋለች:: እወዲያ



@BOOKALEM

ቪዛው ቤት ወደ ውጭ ሀገር ለመሔድ ፕሮሰስ የሚያደርጉ ሰዎች እንደ ጉንዳን ተሰልፈዋል:: ከየት እንደሆነ ከማላውቀው አቅጣጫ ይላል ዶጁ ፋዋ ፋዋ ይላል ዶጁ(4) የተባለው የአንድ ሰሞን ተወዳጅ ዘፈን በብዙ ድምፆች መሃል እየሾለከ ይመጣል::

ደረጃ ላይ ተቀምጬ ሳስብ......ምን እንደማስብ አላውቅም.......ዋናውን ምንገድ ተሻግረው ሦስት ሕፃናት ሰፊው ባዶ አስፋልት ላይ ኳስ መጫወት ጀመሩ:: ልከለክላቸው አልፈለኩም:: በቅርብ ዕርቀት በዚያ አካባቢ ያለው ኳስ መጫወቻ ሁልጊዜም ስታዲዮም ብቻ ነው:: ጫወታ ሊጀምሩ ሲሉ እኔን ፈርተው እየተገላመጡ ያዩኝ ነበር:: ቸልተኛነቴ አደፋፈራቸው መሰል እየተጨዋጨዋሁ ፊኛቸውን መጠለዝ ቀጠሉ::

ከመሐል ይሔን ሁሉ የሰፈረብኝን የድምፅ ክምር ሰብሮ እንጨት የሚደበድብ መዶሻ ሰማሁ:: ዞር ብዬ ሳይ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር በሚወስደው ምንገድ አጠገብ የተሠራው የእንጨት ፍርግርግ ላይ ሶስት ሰዎች እየተረዳዱ የሸራ ስዕል ነገር ይሰቅላሉ:: የአንድ መዶሻ ድምፅ ያንን ሁሉ እርቀት አልፎ እዚያ ድረስ እንዴት እንደተሰማኝ ገረመኝ::

ወሬ የመቃረም ፍላጐቴ ተነሳስቶ ይሁን ወይ ብዙ በመቀመጤ ስለተሰላቸሁ (ከሁለቱ መምረጥ ከብዶኝ) ስዕል ወደሚሰቅሉት ሰዎች ሔድኩ:: የስዕሉ ሸራ ስፋት በግምት አሥራ አምስት ሜትር ይሆናል:: በቁራጭ በቁራጭ እያነሱ ፍርግርጉ ላይ ሰቅለው ከጨረሱ በሁዋላ (ወደ ላይ ሦስት ቁርጥራጭ ወደ ጐን አምስት ቁርጥራጭ) ከስሩ ተቀመጡ:: አንደኛው ሰውዬ የሽቦ አጥር ተደግፎ ተቀምጧል:: ሁለተኛው ስዕሉ የቆመበትን ምሰሶ ተደግፎ ተቀምጧል:: የቀረው ሜዳ ላይ እንደሚፀዳዳ ሁሉ ቁጢጥ ብሎአል:: ሽቦ ተደጋፊው እየጮኸ ወደ እኔ አቅጣጫ:-

"ወንድም ክብሪት ወይም ላይተር አለህ?" አለኝ::

"የለኝም" አልኩት ባርኔጣዬ ተፈናጥሮ እስኪወልቅ ጮኼ::

ተቁነጠነጠ:: ይህቺ ተራ የቃላቶች ቅብብል ስባኝ ወይም ይህቺ ተራ በድምፅ ንክኪ የበለጠ እንድቀርባቸው ፈቃድ እንዳገኘሁ ምልክት ሆናኝ ነበር መሰለኝ ተጠግቼአቸው ቆምኩ:: ዩኒፎርም ለብሼ አጠገባቸው መሆኔ የመናገር መብታቸውን ለመግፈፍ የማነፈንፍ ሰላይ ሊያስመስለኝ ስለሚችል ተጠራጥሬ ነበር:: በግራ በኩል ከላይ ያለው አንዱ የስዕል ቁራጭ ከተያያዘባቸው ጣውላና አጣናዎች ተላቆ እንደባንዲራ መውለብለብ ጀመረ::

"ይኼው ብዬህ የለም ትተነው ብንሔድ ኖሮ ጉድ ሆነን ነበር"

"በል በኔ አመሃኝ.......እኔ ተነፈስኩበት?"



@BOOKALEM

"የምልህ አምስት ደቂቃ ሳይሞላ ተሳቀቀ" አለ ባለሲጃራው:: የማጭድ ቅርፅ ያላት ኒያላ አፉ ውስጥ ተሰክታለች::

"እንቅልፍ አጥቼ አደርኩ.......እንደ ገና ንፋስ እየጠበቅሁ ጨርቁ በተሳቀቀ ቁጥር እዚህ ተቀምጬ ሳስተካክል ልውል ነው?"

"ሥራ ነው"

"የእኔ ሥራ መሳል ነው:: መስቀል አይደለም"

"እኔ ልጨቃጨቅ አልመጣሁም ጊድ:: ሥራዬ ይኼን ስዕል ሰቅሎ መሔድ ነው"

"ማን አድረህ ሥራ አለህ?"

"እዛገቢስ......የአዲስአባ ከተማ ርዕዮተ ዓለም ክፍል"

"ሥራ ወይ የስራ ቦታ ለውጣ"

"በል ተመኝ.......የት ትለውጣለህ?"

"ፈልግ:: አትሞኝ"

"ንገረኝ:: እነሱ የሌሉብት ቦታ የት ነው?"

"ተጣበሳ"

"ምን ማለት ነው?"

"ሽርክ ሁን"

"ያሉህን ከመስራት ሌላ እንዴት ሽርክ ትሆናለህ? ምን ማለት ነው?"

"ተቀላቀላ"

"ካልፈለክስ?"

"ሌሊት እያደርክ ሥራ እንግዲህ......እኔ ላይ አትጮህ፣ ደካማ"

"ደካማ አትበለኝ"

"ደካማነት ነው"

"ሰማህ.......አለማቃጠር እስስት አለመሆን ደካማነት ነው?"

"አስመስል ማለቴ ነው"

"እንዴት ነው የምታስመስለው? ታዲያ ይሄ አሰራር ሊባል ነው እሰጣጥ?"

"ላስተምርህ ትፈልጋለህ? በዚህ ምላስህ እንዴት......"



@BOOKALEM

"ምን ታስተምራለህ! አንተ የመንገድ መሐንዲስ ነህ አይደለም? እዚህ ምን ትሰራለህ:: የተበላሸውን የአዲስ አበባ መንገድ አትሰራም.......እዚህ መጥተህ ምን ስዕል አሰቀለህ"

"አንተን ተቆጣጣሪ ሆኜ ነዋ:: ቀሉችን የሚቆጣጠረው እንደ እኔ ዓይነት ብልሀ ነው:: የወለደች የምትኩራብት"

"የከንቲባውን ጫማ ስንቴ ጠረግህ?"

"እየጠረግሁ ወደ ላይ እወጣለሁ:: አንተ ካልሲህን ሳትለውጥ ቀን ሳያልፍልህ ታረጃለህ::"

"ወደ የት ይሆን የምትወጣው? ደሞ ከሚሸት ነፍስ የሚሸት ካልሲ ይሻላል"

"ሃሃ ወግ ወገኛ ነህ:: የት የምወጣ ይመስልሃል? ጳመና ነዋ"

"ከቴም ተወጣ.......ዛፍ የሚወጣ ዝንጀሮ ቀድሞ የሚታየው ምኑ እንደሆነ ታውቃለህ? መላጣ ቂጡ"

"ምን ያጣላችሁዋል.......እዚህ" አለ አንደኛው::

"ይኼ ምን ያውቃል.......ተወው:: የሚገርም ጉረኛ ነው"

"ዕድሜ ልክህን ስዕል ስትሰቅል ልትኖር ነው?"

እኔ እንደ ሰላይ ልጠረጠር እንደምችል ገምቼ ከዚያ አካባቢ ሸተት አልኩና ስዕሉን ብቻ ማየት ጀመርኩ:: ሰዎቹ አላጓጉኝም:: ንትርካቸው ቢገባኝም አላጓጉኝም:: ከስዕሉ በስተግራ በመጠኑ ተንጋዶ የተሳለ የበሬ ብልት የመሰለ የአክሱም ሐውልት ነው:: ከቡናማና ከቢጫ ቀለሞች የተሰራ:: ከግራ ጎኑ ትንሽ ባለጉጆ ቤተክርስቲያን አለች:: ከሐውልቱ ስር ጋቢ የተከናነበ ሰው ተቀምጦ መፅሐፍ ገልጧል:: የመፅሐፉ አርዕስት አይታወቅም፣ በአርዕስቱ ምትክ አንዲት ትንሽ ጭረት ትታያለች:: (አርዕስቱን ለመደበቅ አስበው ይሆናል:: ለምሳሌ እኔ ይሔን ፅሑፍ ስፅፍ አርዕስት ማውጣት ከብዶኝ ያልወጣሁት ዳገት ያልተንጠለጠልኩበት ገደል አልነበረም:: መጀመሪያ እንደውም ያለአርዕስት በልሙጡ ላወጣው አስቤ ነበር:: ምን አለበት? መጨረሻ አሽሙዋጣጩንና ሒሰኛውን ፈርቼ የለመዱትን ላለመንፈግ አርዕስት ሰጠሁት:: ይኼም ሰዓሊ አርዕስቱን ትቶ መፅሐፉን በልሙጥ ያወጣው ደፋር መሆኑንም ሊያሳየን ይሆናል) ከአክሱም ሐውልት ቀጥሎ የጐንደርና የላሊበላ ሕንፃዎች ናቸው:: ጐንደር ሕንፃ አጠገብ የአገር ባሕል ልብስ የለበሱ ባልቴት የስሌን ዣንጥላ ይዘው ቆመዋል:: ከእግራቸው ስር ድንክ ቡጢ የመሰለ ጥላሞት ተኝቶአል:: ላሊበላ ቤተክርስቲያን አጠገብ ደሞ አንድ ቡናማ ቀለም ያላት ቀንዶችዋ እንደ ተዘረጉ እጆች የቆሙ ላም ሣር ትግጣለች (ወይም ስለ ሳር የምታስብ......) አጠገብዋ የበረደው የመሰለ እረኛ ቆሟል......ሴት እረኛ ትሁን ወንድ እረኛ አይለይም:: የለበሰው/ችው ብርድ ልብስ ይሁን ቡሉኮ አይታወቅም:: ከዚህ ሁዋላ በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ተሰብስቦ ንግግር የሚያዳምጥበት ቦታ ነው:: ሜዳ ላይ



@BOOKALEM

ወይም አየር ውስጥ የተሰበሰቡ ይመስላል:: ሰብሳቢው የአገሪቷ መሪ ናቸው:: ኮረብታ ላይ ቆመው እጃቸውን አንስተዋል:: አፋቸውንም ከፍተዋል:: ታዲያ ከአፋቸው ንግግራቸውን ለመጥቀስ ነበር መሰለኝ "አብዮታዊ እናት አገር ወይም ሞት" የሚል ፅሑፍ ተፅፎአል:: (ከዚህ ዕርቀት ድምፃቸው እንዴት ይሰማል?) ሕዝቡ ዙሪያ የኢትዮጵያ ኰሚኒስቶች ባንዲራ እሩቅ ድረስ ተለሸልሾአል:: ከመንግስቱ ኃ/ማርያም ከፍ ብሎ እርሻ ተስሏል:: ትናንሽ ትራክተሮች ዐይን እስኪያደክም ድረስ ተሰልፈዋል:: ፊት ለፊት ወዳለው ቀርቤ ትራክተሩ የተሰራበትን አገር ለማየት ሞከርኩ:: የለም:: ከእነዚህ ትራክተሮች በስተግራ አንድ ገበሬ (ከንፈረ—ከባድ፣ ዐይነ--ትላልቅ፣ ጥርሰ—በረዶ) በከንዱ ቢጫ ኮፊያ ያለው የታጨደ እህል አቅፎ በሳቅ ፈንድቶአል:: ያሳቀው ነገር አልገባኝም:: ከገበሬው ቀኝ ጎን የአገር ልብስ የለበሰች ወይዘሮ እየሳቀች ቆማለች፣ የምትታየው ከወገቧ በላይ ነው:: ትከሻዋ ላይም በቡናማ ዘንግ መፈክር ይዛለች:: መፈክሩም "ሴቶች የሕብረተሰባችን ግማሽ አካል ናቸው" ይላል:: ከገበሬው ግራ ጎን አንድ ባለ ቁንጮ ልጅ ጆሮው ከፊቱ የሚሰፋ እሱም እየሳቀ ከወገቡ በላይ ይታያል:: (ለምን እንደሆነ አላውቅም የኤልያስ ጓደኛ ፀሐይ ቤት ያየሁት ፎቶ ትዝ አለኝ:: ፀሐይ፣ ልጇና ያ......ያ......ጎረምሳው) ከዚህ በስተግራ ደግሞ ሰማዩ ጥቂት ደመናዎች ያሰፈፈበት ሰማያዊ ነው:: እዚያ ሰማያዊ ላይ ጥቋቁርና ግራጫ ጀቶች ተሰለዋል:: ከጀቶች ጉያ ከሰማይ በፓራሹት በሚወርዱ ሰዎች፣ ከስር ከስር ደግሞ የሚሊሺያና የወታደር ልብስ የለበሱ ሰዎች ጠመንጃዎችን ይዘው ከፊሎቹ እየተኮሱ፣ ከፊሎቹ እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ሰቅለው (እየጮሁ?) ይሮጣሉ:: ታንኩችም ከአፈሙዛቸው እሳትና ጭስ ይወጣል:: ከእነዚህ በስተግራ ዝቅ ብሎ ብዙ ሰዎች የቆሙበት መሬት በእሳት መብረቅ እንደተመታ ሁሉ ፈንድቶ ቆመውበት የነበሩ ሰዎችም እጆቻቸውን እየሰቀሉ አየር ላይ ይንሳፈፋሉ:: ከእነዚህ ከሦስቱ በአንደኛው ሰው ጀርባ ላይ 'ሻቢያ' የሚል ተፅፎአል:: ሁለተኛው ሰው ጀርባ ላይ 'ኢሕአፓ' የሚል ተፅፎአል:: ሦስተኛው ሰው ጀርባ ላይ ደግሞ 'ኢድሕ' የሚል ተፅፎአል:: ከስዕሉ መጨረሻ በስተግራ ቂጣ የምታህል ፀሐይ ወጥታ እንደ አስኳል ታበራለች:: ብርሐንዋ እጅግ፣ እጅግ ቢጫ ነበር::

ሰዎቹ የተገነጠለውን አንዱን የስዕል ቁራጭ እነበረበት ለመመለስ መሰላሉቻቸውን ያዘጋጃሉ......የግንባዩ አንደኛው ጫፍ የአክሱም ሐውልት ቆብ የነበረበት ስለነበር ነው መሰለኝ አንዱ "ይኼን ድንጋይ ለመሳል አቦ እንዴት አስቸግሮኝ ነበር" ይላል:: ሦስቱም ስለተዳከሙ በመሰላል ወጥቶ የተበላሸውን ለማስተካከል ትንሽ ከተፎካከሩ በሁዋላ አንደኛው "እንደፈረደብኝ እኔው ላድርገው" ብሉ መሰላሉን መውጣት ይጀምራል:: ሰውዬው በቀስታ በብረቱ መሰላል እየተረማመደ ወጥቶ ማስተካከል ሲጀምር......መሰላሉን በደንብ አያቁሙት፣ ወይስ በዚያን ወቅት እኛን ሊሰማን በማይችል ሁኔታ የአዲስአባ መሬት ተነቃንቃ እንደሆነ. አላውቅም መሰላሉ እንደተነካ ሁሉ በአንድ እግሩ ተሽከርክሮ ወደቀ:: ተሳፍሮበት የነበረውም ሰው እየጮኸ



@BOOKALEM

መሬት ወርዶ እንደ ተሰጣ ጨርቅ ሆነ:: የወደቀበት መሬት በጥቋቁርና ነጫጭ ጠጠሮች የተሸፈነ ነበር::

የሰውዬው አንገት እንደ እንጨት ሲቀጭ ሰማሁት:: ምናልባት በዚያች ደቂቃ የአዲስአባ ከተማ ፀጥ ብትል......ይኼን ስብራት ሽሮ ሜዳ፣ ናዝሬት፣ አዋሳ፣ አሰብ፣ መቀሌ፣ ጉንደር፣ ብቸና፣ ሱሉልታ፣ ነቀምት እያንቀሳቀሱ መስማት ይቻላል:: ሰዎች ተሰባስበው የወደቀውን ሰው ተሸክመው በመኪና ጭነው ወሰዱት:: የተቀደደው ስዕል ሳይጠገን ቀረ::

ሱስ አይዘነጋምና......እንደ ሽርሙጣ ደረት በተከፈተው የአብዮት አደባባይ ሜዳ ላይ ንፋስ ስድ ጨዋታውን ጀመረ::



@BOOKALEM

# ቀሻሻ ካልሲዎች፣ ቀሻሻ ካናቴራዎችና ሴቶች ስለቀያሚ ሰቃዎች

ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ አንድ ሰው በዚህም በዚያም ብለው ሊያመልጣቸው የማይችላቸው ነገሮች አሉ:: ወንድ ወንድ ከመሆን አያመልጥም:: ሴት ሴት ከመሆን አታመልጥም:: እንዲህ ያሉትን ነገሮች አይደለም:: ዛፍ ዛፍ ከመሆን አያመልጥም:: እንዲህ ዐይነት ነገርንም አይደለም::

ስለቆሻሻ ካልሲዎች፣ ስለቆሻሻ ካናቴራዎችና ይኼን ስለመሳሰሉ አስቀያሚ ነገሮች ነው የምናገረው:: ታዲያ እነዚህ ነገሮች የተሻለ ኑሮ መኖር ብጀምርም አለቀቁኝም::

አንድ ቀን ሳጥኔን ስከፍት......ያ የብረት ሳጥኔ ውስጥ......የእኔ ያልሆኑ ካልሲዎች፣ ካናቴራዎችና የውስጥ ሱሪዎች አገኘሁ:: በመጀመሪያ የተሳሳተ ሳጥን የከፈትኩ መስሎኝ ነበር:: ይሔ ግምቴ ግን በሁለት ማረጋገጫዎች ፉርሽ ሆነ:: በመጀመሪያ የራሴ ዕቃዎች በሙሉ ውስጥ አሉ:: ሁለተኛ እቤት የነበሩትን ጃፓንንና አለማየሁን ስጠይቃቸው የእነሱ እንዳልሆነ ነገሩኝ:: ጃፓን እንደውም ጨመር አድርጐ እንደኛውን ቡታንታ በኩረ ለብሶት እንዳየው ነገረኝ::

ጨርቆቹ ያልቆሸሹ ቢሆን እንኳን ነገሩን በቸልታ አልፈው ነበር:: ጨርቆቹ በላብና በጉድፍ የበሰበሱ ነበሩ:: የራሴ ሳጥን ቢሆንም ያስቀመጠውን ሰው ላለማስቀየም ውጭ (ከሳጥኑ ውጭ) ልጥላቸው አልፈለኩም:: ስለዚህ ነጋሳና በኩረ እስኪመጡ መጠበቅ ነበረብኝ::

መጡ......መሸቶ::

የበኩረን ነጭናጫነት ስለምፈራ ነጋሳን በመጀመሪያ ካልሲዎቹ የእሱ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ ጠየቅሁት:: እንዳልሆኑ ነገረኝ:: ከዚያ በኩረን አየሁት ሳልናገር::

የሚያስብ መሰለና ተናገረ: "ላስቀምጥ ብዬ ጠይቄህ ነበር"

"መቼ?"

"ቆይቷል"

"አላልከም:: ቢሆንስ' ያልታጠበ ካልሲ ነው እንዴ ታዲያ? የአንተ ሳጥን የት ሄደ?"

"ምንድነው ይሔ ልጅ ያነጫንጨዋል?" አለ ኩስተር ብሎ::

ፊቱን ሳየው ስህተቱ በፍፁም የእኔ ይመስል ነበር::



@BOOKALEM

"ምን ነው ያለው ካልሲው?......አንድ ሰባራ ሳጥን አለው ይንሰፈሰፋል" ቀጠለ።

ሳጥኔንም ይሰድባል። እኔ መኖር አልቻልኩም። ሌሎች ምልልሳችንን የሚያዳምጡ አይመስሉም። ምናልባትም ያዳምጡ ይሆናል። በኩራ አልጋዬ ጉን ተንበርክኩ ከአልጋው ስር ሣጥኑን ሳበና ከውስጡ የራሱን ዕቃ በችኩላ አወጣ።

"ይኼውልህ......ውዱ ሳጥንህን አላበላሽብህም" አለና ወደ አልጋው ሔደ።

ከዚያ በሁዋላ ድር ሳያቋርጥ የሚያወራው ሰው ከማንም ሳይነጋገር ተኛ።

እኔ እንዳልተሳሳትኩ አውቃለሁ።

ለሳምንት የሚሆን ጊዜ ከሌሎች ጋር ሲነጋገር እኔን ሊያናግር ቀርቶ ፊቴን ለማየት የተጠየፈ መሰለ። አልፎ አልፎ ሳጥኔን የሚመለከት ሽሙጥ ማንም ባልጠበቀበት ወቅት ይወረውር ነበር። ሳጥኔ ደግሞ የቀድሞ ራሴን ጠረን እስኪያገኝ ብዙ ጊዜ ወሰደ።

ያላመለጥኩት ነገር ቢኖር ቆሻሻ ካልሲ፣ ቆሻሻ ካኔትራ ሌሎች ቆሻሻ ጨርቃጨርቆችን ነበር። ከእኔ ጉያ ባጠፋቸው እንኳን ምንገድ ፊልገው ይመጣሉ።

ማንን ለማብሸቅ እንደሆነ አላውቅም ከጥቂት ቀናት በሁዋላ በኩራ የኩክኩላ ጠርሙስ ከተክለሐይማኖት አደባባይ ጉልት በሃምሳ ሳንቲም ገዝቶ አምጥቶ (ከቤት ወጥቶ ጀርባ መፀዳዳት ሲገባው) ሌሊት ሌሊት አልጋው ላይ ተቀምጦ ለመክፈያ ይጠቀምበት ጀመር። እንትኑን የጠርሙሱ አፍ ላይ ይለጉምና ጭር ባለ ሌሊት ቁርርር ያደርጋል። ድምፁ ሊያሳብደኝ ይደርሳል። በሌሊት እንኳን እንደ ኩክኩላ ጠርሙስ ያለ ለፍላፊ አሰራር ያለው ዕቃ ይቅርና ቢምቢዎች ሲበሩ የትናንሽ ክንፎቻቸው መርገብገብ እንደ ጀት ጆሮዬ ላይ እየጮኸ ይቀሰቅሰኛል። የእሱ አልጋ ግርጌና የእኔ ትራስጌ ስለሚነፃፀሩ አልጋው ላይ ራቁቱን ተቀምጦ ለመሽናት ሲቀመጥ በመጠኑ ወደ ጭንቅላቴ ይቀርባል......ታዲያ የሽንቱ ጠረን በዚያች ጠባብ የጠርሙስ አፍ እንደ ሲጃራ ጢስ አምልጦ እኔ የምተኛበትን ሰፈር ሲበክል አሸተዋለሁ። ካልሲውን ሳባርር......በዚህ......ሊቀጣኝ ነበር መሰለኝ።

ሌሎች ደባሎቼ ግን ነፍሴንና ጤንነቴን ካሰለሰለችው ከዚህች ዓይነት ከአደጋው ስለራቁ መሰለኝ ግድ አልሰጣቸውም። ምንም በደል እንዳልተፈፀመብኝ ሁሉ፣ አዲስ ጉድ አልጋዎቻችን አካባቢ ሰርጎ እንዳልገባ ሁሉ በፀጥታ ይተኛሉ። ስህተቱ ከእኔ የተፀነሰ፣ ከእኔ የተወለደ፣ የእኔን የቻልተኛነት ጡት እየጠባ አድጎ እኔን መልሶ የሚነጅሰኝ። ሳም እሳት ወለደች......። ለማንኛውም ሜዳ አድር የነበረ ሰው አልነበርኩም እንዴ? ይሄ ቀላል ችግር አይደለም እንዴ? ብዬ ተውኩት። መርሳት ሳይሆን ችላ። እየተማረርኩ ችላ።



@BOOKALEM

የማይለቅ ነገር አለ።

እንደጠባሳ ተጣብቆ የሚከተል።

ከራስ ባይመጣ እንኳን በሰው እየተሠራ።



@BOOKALEM

# ባለቤቷን በመጥረቢያ የገደለች ሴት እጅዋን ሰጠች

ባለቤቷን በመጥረቢያ የገደለች ሴት ማንም ሳያስገድዳት መጥታ ለእኔ እጇን ሰጠች:: ከሁለት ወራት በሁዋላ የታተመው የአብዮታዊ ፖሊስ ጋዜጣ ግን ሪፖርቱ ውስጥ ስሜን ሳያነሳው ቀረ:: አብዮታዊ ፖሊስ ጋዜጣ ነገሩ በምርመራ እንደተደረሰበት አድርጐ በነሐሴ 15 ቀን ጉዳዩን በጠቅላላ የመጀመሪያውና ሰስተኛው ገፅ ላይ አውጥቶት ነበር:: ምርመራ? ምንም ምርመራ አልነበረም:: እንዲህ ነው የሆነው......

የደሞዝ ዕለት ነበር:: እና ከሞቢል ቤንዚን ማደያ ሻይ ቤት የገዛሁዋትን በመልካም ወረቀት የተጠቀለለች አንድ ቦምቦሊኖ በልቼ ባለመጥገቤ ጫልቱን በሆዴ እመርቃለሁ:: (ቦምቦሊኖ ባለ አጭር ታሪክ ናት(5): እያታለሁ፣ እወዳታለሁ፣ እገዛታለሁ፣ እበላታለሁ፣ ባለመጥገቤ ግን ይቆጨኛል::)

አፌንና ቀኝ እጄን በወረቀት ጠራርጌ ጥፍሮቼም መንፃታቸውን እያገላበጥኩ ስፈትሽ አንዲት ሴት ተጠጋችኝና እየተንቀጠቀጠች:

"ሰማህ ወንድም ፖሊስ ጣቢያ ውሰደኝ"አለችኝ

"ለምን?" አልኳት

"ባሌን ገድዬአለሁ:: የእሱን ቆሻሻነት አልሰበስብም:: የእሱን ብልግና የምሰበስብበት ማሕፀን የለኝም:: ውሰደኝ ብዬሃለሁ ውሰደኝ" (እንኳን ሰው የገደለች ዝንብ ከእርጐ ውስጥ አውጥታ የወረወረች አትመስልም)

"ሒጂያ ፖሊስ ጣቢያ"

"አንተ ውሰደኝ"

"ወላ አቦ ተደብሬአለሁ......ስራዬ ምንገድ መጠበቅ ነው......ጣጣ ውስጥ አልገባም......ሒጂ. አንቺ......በዚህ ምንገድ በቀጥታ ትወጪና......መስቀልያ ምንገድ አለ እሱን ታቋርጪና እንደገና መስቀልያ ምንገድ ያጋጥምሻል......እዚያ ዘንድ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አለ......ሒጂ."

"አንተ ውሰደኝ"

"ከእኔ ምን አለሽ?"

"አለበለዚያ ሌላ ሰው እገላለሁ" አለችና ከነጠላዋ ስር በደም የተለወሰ መጥረቢያ ቀስ አድርጋ ጉትታ አውጥታ አሳየችኝ::



@BOOKALEM

"ምነው?" አልኳት ከተቀመጥኩበት ሳልነሳ

"ወንድ መገደል ሲያንሰው ነው። ሌላ ሴት ከፈለገ ለምን ትቶኝ አይሔድም......ቀላል ነገር እኮ ነው። ምግቡን እሰራለሁ። ልብሱን ካልሲውን አጥባለሁ። ነጋ ጠባ ቡና አፈላለሁ። ግን ናቀኝ"

"መግደልሽ ጥሩ አይደለም" አልኳት።

"ምን አገባህ......ፖሊስ ጣቢያ ውሰደኝ። ፖሊስ አይደለህም?" አለች

"መጥረቢያውን ስጪኝ" አልኳት

ሰዎች መሰብሰብ ጀምረዋል......ራቅ ራቅ ብለው። እኔ ከተቀመጥኩበት አልተነሳሁም። በመጥረቢያ መሞት ምን ይመስላል? ሞት ይጣፍጣል?

መጥረቢያውን እግሬ ስር ጣለችውና እንዳነሳላት አየችኝ። ትቼው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ዳገቱን ተያይዘን ወጣን......በብሔራዊ ባንክ፣ በባሕል ሚኒስቴርና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዳገት። ፖሊስ ጣቢያ ደርሰን "የገደልሽበት መሳሪያ የታለ?" ስትባል ወደ እኔ እየጠቆመች "ለእሱ ሰጥቼው ነበር......ጣለው......ጣለው" አለች። ሌላ ፖሊስ ተልኮ እስኪያመጣው እኔ እንድቀመጥ ተደርጐ እየተሰደብኩ ቆየሁ። መጥረቢያውን ያመጣው ፖሊስ አዲስ አህጉር እንዳገኘ ሁሉ እየፈነደቀ "ይኼን የመሰለ ኤግዚቢት ጥለህ ትመጣለህ?" ይለኛል። ለምን ኤግዚቢቱ እንዳስፈለገ አልገባኝም። እኔ ካላነሳሁት እሷ የግዷን ታነሳዋለች ብዬ ነበር። ግን "ገደልኩ" ብላ ካመነች ምን ያስፈልጋል?

ዕሁፉ በአብዮታዊ ፖሊስ ታትሞ ሲወጣ:

**"......ገዳይዋ ነፍስ ያጠፉችበት መሳሪያ አሟቻ ቦታ ተደብቆ ሲገኝ መግደሏንም ከብዙ ማስቀለኛ ጥያቄዎች በሁዋላ አምናለች......"**

ይላል።



@BOOKALEM

# ስለ ስመቧካች ጣቶች

የጥበቃ አሰልቺ ሕይወትን ጥርሴን ነክሼ እኖራለሁ:: ዕረግማለሁ:: በጣም ዕራገማለሁ:: ዕራገማለሁ:: በግራጫው የሕይወት ጎኔ (ግራጫና ብሩህ ጎን አለው--ብሩሁ ቢያንስም) የምለፋው ለስደት እንጀራ ነው:: ባርኔጣዬን አደርጋለሁ......ብረታብረት የተለጠፈበት፣ ጨርቅ የተተበተበበት ውስጡ ለሙቀት ተብሎ መሰለኝ በገበር የተደራረተ......እሱን የፖሊስተርና የጥጥ ጭንቅ በተሳጨ ጭንቅላቴ ተሸክሜው እዞራለሁ:: በጋ በጋ በሚያቃጥል ፀሐይ እስከ ባቴ የሚደርስ--ንፋስ የሚከትር......በወፍራም ገመድ የሚተበተብ ቆዳ ጫማ አጠልቃለሁ:: የማጠልቀውን ጫማ ክብደት ያልጠገበ ቅጥነቴ ለረዥም ጊዜ ተሸክሞ መዞር ይከብደዋል:: እሱን እየጎተትኩ አዲስአባን እዞራለሁ......ከአንድ ምንገድ ወደ አንድ ምንገድ:: ባዲስአባ የኮረኮንችና የአስፋልት ሽጣሽጥ:: ከቦቴ ጫማ ከፍ ብሎ የሱሪዬን እግሮች በላስቲክ እሰበስባቸውና የበለጠ ግለት እሰበስባለሁ:: የንብ አውራ ለመምሰልም ወገቤን በሰፊ ጥቁር ቀበቶ እፈድናለሁ:: ሸሚዜን እስከ አንገቴ እቆልፍና ለመታነቅ ከራሱ የተቃጠረ እመስላለሁ......ደምስሮቼ ከአገጬ ስር እንደ ጅራፍ በቅለው:: ይሄ ሁሉ እንድራገም ይገፋፋኛል:: ዐይኖቼ ሁልጊዜ ይርገበገባሉ:: ወንጀለኛ የማግኘት ረሃብ አይደለም:: በዚህ ምድር ላይ ከሚነቃነቅ የሰው ፍጡር ወንጀል ያልሰራ፣ ወደ ወንጀል በልቡ ያላሰላሰለ ማን ይኖራል? አይደለም:: ወንጀለኛ የማግኘት ጉዳይ አልነበረም:: ለመኖር፣ ለመኖሪያ ፖሊስ የሆንኩ ነኝ:: የተነገረኝ ነኝ.......ዐይኖቼ ስህተት ፍለጋ እንዲማስኑ:: የተነገረኝ ነኝ:: የልጅነቴ የጉቤ ልምድ ተጨምሮ የሚያመልጠኝ ነገር ግን አልነበረም:: እንኳን ከፊት ለፊቴ የማየው ከጀርባዬ ተደብቆ የሚደረገው እንኳን አያመልጠኝም:: ጉቤ አይደለሁ:: ጉቤ:: ዐይኖቼን ይደከማቸዋል:: ድሮ ጉቤ ሆኜ ዐይኖቼ አይደክሙም ነበር:: ምክንያቱም ጉቤ እያለሁ ዐይኖቼን የማዘው እኔ ነበርኩ:: ጉቤ እያለሁ የዐይኖቼ ጌታ እኔ ነኝ:: ያን ጊዜ ፊት ለፊት ተፈጥሮ የሚጠፋ......ተሰርቶ የሚፈርስ ወይም ጠፍቶ የሚፈጠር......ፈርሶ የሚሰራ አያመልጠኝም ነበር:: ያኔ ባይኖቼ፣ በረጉ ዐይኖቼ እየዳበስኩ በገለልተኛነት አልፋቸዋለሁ::

አሁን ፖሊስ ስሆን ግን መመጠን አለብኝ.......የመረጃ ፍርስራሽ ለቃቃሚ፣ ይሄን ልቅምቃሚ መዝኜ......ወንጀል ይሁን ቢልት......ቀልድ ይሁን ኩስታራ ጉዳይ ገጣጥሜ መግለጥ አለብኝ:: መወሰን አለብኝ:: አውቶብስ ፌርማታ እጁን ኪሱ ከቶ የሚንጉራደድ ጉረምሳ......ምን ሊሰራ እንደሆነ መጠርጠር አለብኝ:: ጉቤኛ መመልከት አይደለም:: ዝም ብሎ ማየት የለም......'ወሳ ምን አገባኝ' የለም:: ምናልባት ይኼ እጁን ኪሱ ከቶ እያፋዋጨ ባለቀጠሮ የሚመስለው ጎረምሳ በጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ ከተመቸው ወደ ኪስ አውላቂነት ሊለወጥ ይችላል:: ወይም ከደረቱ ኪስ የፀረ-አብዮት ወረቀት አውጥቶ



@BOOKALEM

ሊበትን ይችላል:: በምንገድ የሚነጫነጩ ሁለት ሰዎች ምን እየሰሩ እንደሆነ መጠርጠር ግድ ነው:: ወደ ድብድብ ይለወጥ አይለወጥ እንደሆነ ጠጋ ብሎ ነገሩን ማጤን ያስፈልጋል::

ተሰላችቼ ተዳክሜ በተለይ ዐይኖቼ በትራኩማ እንደተነደፉ ሁሉ ልመው ግንብ ተደግፌ ሳስለመልም ባልተጠበቀ ሰዓት አለቃዬ ሊመጣ ይችላል:: አንዳንዴ በተለይ ቸርቸር ጐዳናን ስጠብቅ እስከ አጥንቴ እሰላችና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አጥር ግንብ ላይ ወይም ከሥሩ በአሳፊ አግዳሚ ተከልዬ እናውዛለሁ:: ሰው ይሔዳል፣ ይመጣል:: አውቶብስ፣ መኪናዎች ያልፋሉ፣ ይሔዳሉ......እና እንደ ብረት የከበዱኝን የዐይኖቼን ሽፋሽፍት ያለፈቃዴም ቢሆን ለዕረፍት እከድናለሁ:: ብዙ ጊዜ አልታይም:: የቁጥጥር ዕለት ከሆነ በዐይን የማውቀው የአገር አስተዳደር ፖሊስ ዘንድ ሔጄ ወሬ እጀምረውና ሰንተርያውን አውሶኝ ወይም እዛው እሱ አጠገብ ባርኔጣዬን ፊቴ ላይ ጣል አድርጌ ዛፍ ስር ተጋድሜ እውሳለሁ:: ነውዜ ካልመጣ ከአገር አስተዳደር ደረጃ ላይ የራሴን የሚስጢር ጉቤ ፈጥሬ እንደ ልጅነቴ አፈጣለሁ:: ወገኔ ሠላማዊ ነው:: አስለፍቶኝ አያውቅም::

ብዙ ጊዜ ግምቴ ላይቀናት ይችላል:: አንዳንድ ጊዜ ያለቦታዬ ስዞር፣ ሳርፍ፣ ሳንቀሳፋ አለቃዬ ሳያስጠነቅቅ ይመጣል:: አብሮኝ የሚጠብቀው እንኳን የሆነ ደባች፣ የሆነ ወሬኛ ሊሸፍንልኝ አይሞክርም:: ከእኔ ጋር ከመመደቡ በፊት ስታድዮም ዙሪያ ሲሰራ በጥርጣሬና በማንአለብኝነት ያላሳሰረው ሰው አልነበረም:: እርስ በርሳቸው ያላባላቸው ዱርዬዎች አልነበሩም:: ወንጀል ግን አልቀነሰም:: እኔን ታዲያ አጨካከን እንዲላምደኝ ነው መሰል አብሮኝ እንዲሰራ አምጥተውት የመስበኪያ ጊዜ ይቅርና ዐይኖቼን የሚያይበት ጊዜ አልሰጠሁትም::

"በመጀመሪያ የአዲስአባ ዱርዬ እንዲፈራህ ያስፈልጋል:: ፊት አትስጠው:: ፊት ከሰጠህ ተበላሽህ" ይለኛል::

ዐረፍተነገሩን ሳይጨርሰው እርቃለሁ:: እሽሹዋለሁ:: ሰማይ አያለሁ:: መሬት አያለሁ:: ደስ እንዳላለኝ እነግረዋለሁ:: አንዳንዴ ሳልወድ ነበር:: አልፎ አልፎ የማራቸው፣ ያስፈራራቸው ዱርዬዎች በፍርሃት ሠላም እያሉ ያልፉታል:: በዚህ ይኮራል:: አንዳንዴ እሱ ግንብ ተደግፎ ቆሞ እኔ ተደግፌ ተቀምጨ......በሙቀት የጋሉ እግሮቼን እየረገምኩ አላፊ አግዳሚ ማብጠልጠያ ወሬ ይጀምርና ገና ወገቡ ሳይደርስ ማናወዝ እጀምራለሁ::

ከሚያሰለቹኝ ወሬዎች አንዱ ደ'ሞ የእግር ኳስ ወሬ ነው:: የእስታዲዮም ወሬ ነው:: ይሄ ዐይነት ወሬ ደሞ አያጣም:: የማያውቀው ተጫዋች ያለ አይመስለኝም:: አንዳንዶቹን ከመወለዳቸው ጀምሮ የነበረ ታሪካቸውን ያወራኛል:: እበሽቃለሁ:: በሰው መወለድ ምን አገባው?

"የድሮ የፖሊስ ቡድን ስሙን ታውቃለህ?"

"አላውቅም"

"አንተ እግር ኳስ አትወድም?"

"አልወድም:: ሩጫ ነው የምወደው"

"ሩጫ:: ሃ ሃ ሃ"

ሲስቅ እንደ አዋቂ ነበር:: ስታዲየም በሳምንት ሦስት ቀን በእግር ኳስ ደጋፊ ጩኸት ይበጠበጣል ግን የዓለም ዋንጫ ወስደዋል? ጩኸት ብቻ ነው:: ቢችሉ አገር መክዳት ነው:: አፍ ሲበዛ ይከሥራል:: በተለይ ብዙ ዐይኖች እያዩት የሚያወሩለት ነገር ይሸታል:: ይበሰብሳል:: ገና ሳያድግ ይረግፋል:: ሩጫ ላይ ያለው ዐይን ግን የሯጩ ሁለት ዐይኖቹና እግዚአብሔር:: ሰዎች ስለ ሩጫ የማይገባቸው ለዚህ ነው:: ሩዋጮች መነሻቸው ላይ ትተውን ሔደው ሲመለሱ ብቻ ነው የምናውቀው......መሐል ላይ ምን እንደተፈፀመ አናውቅም:: ሚስጢር ነው:: የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት እንደ ነበረ ዐይነት ሚስጢር::

"ስለ ሩጫ ታዲያ አውርተህ አታውቅም"

"ስለምን ላውራህ?"

"በቅርብ የሙኒክ ማራቶን ማን አሸነፈ?"

"ዘረዘርኩለት"

"ታውቃለህ እባክህ"

"የምወደው ማራቶን ነው:: ከማራቶን ሌላ ስፖርት የለም:: ምናልባት አስር ሺህ ሜትር.......እሱም ከስታድዮም ውጭ ከሆነ"

የማራቶን ሯጭ ከማስደነቁ በላይ ያሳዝናል......ሀያ ኪሎ ሜትር እርቆን ሔዶ እንደገና ተዳክሞ፣ በአለበት እኛን ተመልካቾች በልቡ እየረገመ ወይ እየመረቀ ተመልሶ ወደ ጀመረበት ሲመጣ ያሳዝናል:: እሱን አናውቅለትም:: የምናውቀው ማሸነፉንና መሸነፉን ነው:: እኛ የምናውቅለት ዕርቀቱን ብቻ ነው:: ያውም በሰሁፍና በወሬ::

"ማራቶን እኮ በዓመት አንድ ሁለቴ የሚደረግ ነው"

"ቢሆንስ:: ይሄ የሚያሳይህ ከባድ መሆኑን ነው" አልኩት::

ከሌሎች ፖሊሶች ጋር ከእኔ የተሻለ ሽርክና ነበረው:: አብረን ስንሔድ እጅ ጨባጭና፣ ተጨባጭ እሱ ነው:: ለእኔ የሚደርሰኝ ችላ ያለ ቀዝቃዛ እጅ ቀዝቃዛ ፊት ቀዝቃዛ ዐይኖች ቀዝቃዛ ጥርስ ቀዝቃዛ የራስ ንቅናቄ ብቻ ነው:: አይከፋኝም::



@BOOKALEM

ያልሰማሁት ስም እያነሱ፣ እየተጠያየቁ ትክክኛ ሲመታቱ አንዳንዴ ሊተኛኙ የሚቀጣጠሩ ይመስለኛል::

የአዲስአባ ከተማ መንገዶች ላይ ፖሊስ መሆኔ ሠላም አልሰጠኝም:: ሰው የተሰበሰበበት ቦታ ስደርስ ምንገድ የሚለቅ አለ:: መኪና አጠገብ ብቻውን የቆመ ዱርዬ ካጋጠመኝ ይሸሸኛል:: ይሸሻል:: ምንም ሳላደርገው ይሸሻል:: የዐይኑን ነፃነት ልነፍገው አልፈልግም:: ዐይን ይከለከላል? አንድ መኪና አጠገብ ቆሞ እያደነቀ ቢያይት ይከለከላል? እያደነቀ ማየት ብቻ ሳይሆን በልቡስ መኪናዋን ለመስረቅ ቢያስብ ይከለከላል?......ማሰብ ቀርቶ 'መኪናዋን ሰባብሬ መሽጥ እፈልጋለሁ' ብሎ ቢጮህና ሳያደርገው ዝም ብሎ ቢያይ ይከለከላል? ከእኔ ሸሽተው ሲሮጡ አዝናለሁ:: ልጠራቸው እፈልጋለሁ:: ስነስርአት አስጠባቂ እንጂ አስፈራሪ አይደለሁም:: ከዚህም መብቴ ክብር አለመንኩምም::

አለማማጄ ከሔደ በሁዋላ ከእሱ የበለጠ *በልጫጫ* ተኩብኝ ('በልጫጫ' ማለት በጣም ብልጥ መሆኑን ለማረጋገጥ እናቱን ከመጥበስ የማይመለስ):: ሺህ ዓመት ፖሊስ ሆኖ የሰራ ይመስላል:: የቀድሞው አብሮኝ የነበረው ፖሊስ ነግሮታል መሰለኝ "ቹልተኛ ነህ አሉ" አለኝ:: ይሄን ያለኝ ጠዋት ጠዋት ገና የአዲስአባ ሕዝብ ቢሮውን ሰብሮ ገብቶ ጥምጠማውን ሳይጀምር:: ገና ገና ያ አሰሳቹ የእንግሊዘኛ ዘፈን አይ ላብ ዩ ሞር ዛን አይ ካን ሰይ(6) የሚሉት በየቦታው መንተክተክ ሳይጀምር:: ማን ይሔን እንደመከረው አልጠየቅሁትም:: ማን እንደሆነ አውቃለሁ:: ዝም ብዬ አየሁት:: በፖሊስነቱ ይኩራል:: ኩራቱ ቀላል አልነበረም:: ኩራቱ ከብዶት ከእሱ አልፎ እኔን እየሰደበኝ ነበር:: አብረን እያለን ያልለከፈው ሴት በደረቱ፣ (ምናለበት ደሃ ወገኔ ለፍቶ ቢያድርበት?) ያላስፈራራው ሊስትሮ፣ (ሊስትሮ ማስፈራራት ምኑ ነው አርበኛነቱ?) ያልተቆጣው መኪና ነጂ......ሠላምታ ያልሰጠው ሕዝብ አልነበረም:: ታዲያ 'ተግባቢ' ይባላል::

"ፖሊስ ነህ ስልክ እንጨት?" ይለኛል::

ልቤ እንደተከፋ:: ተሰብሮ ተሰብሮ ተሰብሮ የትም ወድቆ የቀረው ልቤ......ይኼ እንጀቱን፣ ጉብቱን፣ ጣፊያውን፣ ኩላሊቱን ብቻ ተሸክሞ የሚዞረው እኔ:: ዝም እለዋለሁ......አልፈራውም፣ አልደፍረውም:: የትኛው የቀረ ነገሬን ልከላከል? ሲቆጣ ጎበዝ ፖሊስ የሆነ ይመስለዋል:: ብዙ ጊዜ ብዙ ያላጠፉ ሰዎች ይቆጣል......እንዲታይ አድርጐ:: ከብሔራዊ ቲያትር ሌባና ከስታዲየም አወናባጆች ጋር ቆሞ ይጫወታል......ስለስታዲየም ረብሻ እየቀለደ ያወራል......ይነጋገራል......ወሳ ጠቅላላ ሸርክ ይሆናል::

አንድ ጊዜ ስታዲየም ጋብዞ አስገባኝና ፖሊስ፣ ወታደርና አዲስ ቢራ ተባብሉ ተከፋፍሎ ላይ ሳልጨርስ ጥዬው ወጣሁ::



@BOOKALEM

"እናትክን ሳንቲሜን አስከፍለሀ?" አለኝ::

ሽልንግ አውጥቼ ወረወርኩለት:: ይሔ ስፖርት አይደለም:: ሲቪልና ወታደር ብዬ ከመደብኩ ሰው ሳልሆን ቂጥ ነኝ:: እንዴ......የአገሬ ሩጫ ይኼ ነገር የለውም:: አበበ ቢቂላ በዓለም ዝነኛ የሆነው ስለሮጠ ነው:: ስታዲዮም ውስጥ ለአጭር እርቀት የሺህ ሕዝብ ዐይኖች እየተከተሉት ቢሮጥ ኖሮ ምናልባት ዝነኛ አይሆንም ነበር......ማራቶን ግን የሚሮጠው ከብዙ ሰዎች ዐይኖች ውጪ ነው::

በነጋታው ታዲያ የሠራዊቱ አባል ሆነህ ቡድንህን የማትደግፈው ለምንድን ነው ብሎ ሊሰብከኝ ፈለገ:: (ስራውን አስተካክሎ ያልሰራ ፍጡር ባርኔጣ በማድረጌ ከሌላው ሊያገለኝ ይፈልጋል) ዝም ብዬ አየሁት:: ፈራኝ:: ለምን እንደፈራኝ አላውቅም:: ትቶኝ ለመሔድ ፈልጐም ይሆናል:: ብዙ ጊዜ የሚጐበኘን አለቃ ሲመጣ ቀድሞ ወሬ የሚጀምረው እሱ ነበር:: እኔ ሠላምታዬን ሰጥቼ አፈገፍጋለሁ:: የፒያሳ ልጆች፣ የስታዲየም ዙሪያ፣ የመርካቶ አጥፊዎች ሲመጡ......ሲያስተዋውቀኝ ቸል እያልኩ ነበር:: ይሄ ስራዬ አስመርሮት ነበር:: ያስተዋወቀኝን ሰዎች ደግሜ ሠላም አልላቸውም:: እያየሁዋቸውም ሠላም አልላቸውም:: ዐይነ-ዐፋርነት አይደለም:: ('ተግባባ' ይለኛል)

አንዳንድ ሰዎች ሽርክና ሲፈጥሩ አስልተው ነው:: ገና ሲያዩኝ ፖሊስ ነኝ......ፖሊስ ምን እንደሚጠቅም ያስባሉ:: ከእኔ ምን ሊገኝ እንደሚችል ያስባሉ:: ለእኔ ምን መስጠት እንደሚችሉ ያስባሉ:: ሠላምታው እኔን፣ መልኬን አይተው ደስ ስላላቸው ሳይሆን እቅዱ ለነገ ነው:: ነገ ዘመድ ሲታሰርባቸው ምንገድ እንድጠርግላቸው፣ ትራፊክ ሲያስራቸው እንዳነጋግርላቸው:: እጠቅም እንደሆነ ተገምቼ ነው:: መርዳትም፣ መረዳትም አልፈልግም:: ስታድዮም ውስጥ በመለዮ ለባሽነቴ ወደ ሌላ መድበውኛል......የስራ ባልደረቦቼ ከእነሱ የማንኙነት መረብ ባለመግባቴ ያሰቡትን ባለማሰቤ ቸል 'ይሉኛል:: ዙሪያዬን ጣት ነበር:: ብዙ ጣቶች አሉ:: ወደ እኔ የሚጠቁሙ ጣቶች ናቸው:: ለሲቪሉ የሚያስር የሚሰልል፣ የሚደባደብ፣ ለፖሊሱ በቂ ጊደኛ መሆን የማይችል፣ ለአለቆቹ የፈዘዘ፣ የተበላሸ፣ አትኩሮት የጎደለው......የገዛ መስሪያ ቤቱን የእግር ኳስ ቡድን መደገፍ ያፈረ ሰው ነኝ::

እነኚያ ወደ ግንባሬ የሚጠቁሙ ጣቶች ታዲያ ታጥፈው አያውቁም:: እነኚያ ጣቶች ሺህ አጥቅ አላቸው:: እነኚያ ጣቶች ሺህ ጊዜ መተጣጠፍ ይችላሉ......እነዚያ ጣቶች ጥፍራቸው ረዥም፣ የሾለና ጉድፍ የጎረሰ ነው:: የእነዚያ ጣቶች ጥፍር ጫፉ እሳት የተለኰሰ ነው:: እነዚያ ጣቶች ወፍራምና ደንዳሳም ናቸው:: ደንዳሳምና ደፋር ናቸው:: እነዚያ ጣቶች በስብ የተደረቱ 'ማን አለብኝ' ባይ ናቸው:: እኔ ሊበራይ እንደ ደረሰ የጤፍ ክምር የእነዚያን ጣቶች ድፍረት ቆሜ እጠብቃለሁ......አንዳንዶቹ



@BOOKALEM

እንደጠጠር ይወረወሩብኝና አንጥሬ እሸሻቸዋለሁ......አንዳንዶቹ እንደዘንግ ይመጡና አንጥሬ እመልሳቸዋለሁ:: አንዳንዶቹ ተለኩሰው ይመጡና አቃጥለውኝ ይሔዳሉ::

እነዚያ ሁሉ አመልካች ጣቶች......የብዙዎቹ አመልካች ጣቶች......እንደ ጦር የተሠሩ ናቸው:: እነዚያ ሁሉ አመልካች ጣቶች እንደጦር የሾሉ እሳቶች ናቸው::



@BOOKALEM

# ትዝታ ፈቀቅ

ብቆይም፣ ከተወለድኩበት ቦታ እርቄ ብዙ ብቆይም ኤልያስን አልረሳውም:: ኤልያስና ሴት ጓደኞቹን አልረሳቸውም:: እሱን ብቻ ሳይሆን እንጀራ እናቴን፣ እህቴን፣ አባቴን አስታውሳቸዋለሁ:: እነዚህን ብቻ ሳይሆን የታጠብኩበትን ወንዝ፡ ወዲያ ወዲህ የረገጥኳቸውን የእበት ጉልላቶች......በሩቅ ከዛፍ እዛፍ ሲንሸራተት ያየሁትን እባብ፡ ከዕለታት አንድ ቀን ባልተሰየመ፣ ጥሩ ሥም እንኳን በሌለው ቀን መዳፌ መሃል በሳቤ እስክትረጥብ የያዝኳት ጠጠር፡ ፀጉሬን ተቆርጬ ስወጣ ኩሊታዬ ስር ወይም አንገቴ ላይ ሳይጠረጉ ሳይራገፉ እየኩሰኩሱ ሰረፍት የነፈጉኝና የማራግፋቸው የፀጉሬ ቁራጮች፣ በልጅነት ጥጋብ ጥላሞታቸውን እያሳደድኩ የተጫወትኩባቸው ጭልፊቶች፣ ከዝግባ ዝግባ ነጭና ጥቁር ውሃ መስለው የሚፈሱትን ጉሬዛዎች፣ ጭር ባለ የግንቦት ሌሊት ቀን በዋለው ግለት ተቀስቅሰው የሚያሳክኩኝ የግራ አውራ ጣት ሙጃሌዎቼን ራቁቴን ከአልጋ ወርጄ መኝታ ቤቴ ጨለማ ውስጥ ከወለል እያፋተግሁ በተመስጦ ያከኩት......እነዚህ ሁሉ ጊዜ እየተለዋወጠ ባልጠበኩት ጊዜ ሕሊናዬ ውስጥ ብቅ ብለው......ሕልሜ ተረት ውስጥ ከቸች ብለው......በቀዝቃዛ ትዝታ እንድደውኝ ይሄዳሉ:: ከየት እንደመጣሁም ይነግሩኛል::

አንዳንዴ በምንገድ ገሁ፣ አቋሙና አለባበሱ ጥንት የማውቀውን ሰው ያየሁ እየመሰለኝ እደነግጣለሁ:: ባልደነግጥም፣ ይገርመኛል:: ባልደነግጥም፣ ባይገርመኝም የድሮዎቹ ሰዎች ትዝ እንዲሉኝ ይቀሰቅሰኛል:: አንዳንዴ ልቤ ይሰበራል......ያመለጥኩ መስሎኝ አለማምለጤ ሲጋረጠኝ:: አለማምለጤ:: በትዝታ ተመስሎ፣ አለማምለጤ በቸልታ፣ በአጠገቤ በሚያልፍ ሰው ተመስሎ፣ ሕሊናዬ ውስጥ ሲጫር ልቤ ልትተረተር ትደርሳለች:: አንዳንዴ ስለ ሙስጠፋ፣ ስለ ኤልያስ በሕይወት መኖር አለመኖር ለማወቅ ንፋስ መውጫ ያ ተመልሼ ለመጠየቅ አስብና ፍርሃት ፍርሃት ይለኛል::

መሰን አትረሳኝም:: ከእኔ ጋር የጠበቀ የግል ጉዳይ ኖሯት ባያውቅም:: መልኳ ሁልጊዜ የበለጠ አምሮ፣ ተቀባብቶ እየታወሰኝ ለራሴ የግሌ የቁንጅና መለኪያ አድርጌአት ነበር:: ታዲያ እነ አለማየሁ 'ቆንጆ አየን' ሲሉና ሲያደንቁ ያበሽቁኛል:: ዓባይን ያላየ ቁርጡማን ያደንቃል::

የበኩረን ዘመድ ገነትን ካየሁዋት ጀምሮ ትዝ የምትለኝ መሰን ነበረች:: በንኪኪ:: ቆንጆ ቆንጆን ሲቀሰቅስ:: ገነት ከድብቅ ሕሊናዬ ደን እያበራች ወጣች:: ቅላቷ ከባትሪ እንደሚወጣ ብርሃን በዐይኖቼ ሰርጎ በአፍንጫዬም ቀዳዶች የወጣ እስኪመስለኝ......ለከፋኝ ነበር:: ያን ጊዜ ሳይገባኝ በልቦናዬ 'ደስ ትላለች' ብዬ አቅልዬ ሰይሜአት ያቺ ተራ ሐረግ እንደዋርካ ሰፋች:: ፈራሁ:: ገነትን ፈራሁ......የራሴንም

ጠማማ ትውስታ......ወገቡን በወሰን ትዝታ የታጠቀውን:: ወሰንንም ፈራሁ......የማላያት፣ የማልደርስባት የሕልም ዓለም ልጃገረድ......የማላያት ዐይቼ የማልነካት::

ገነትንም ፈራሁ......

ሳስባት......የዚያን ቀትር ቀን ማማሯን ሳስበው......ልቤን እየከበደኝ......ለአጭር ጊዜ መኖሬን ፈራሁ:: ስለ እሷ ማሰብ ስህተት እየመሰለኝ ከሕሊናዬ ልፍቃት እጥርና እንደተሳካለት ሁሉ በጆርባዬ ስንጋለል ምስሏ የቆርቆሮ ጣሪያችን ላይ እንደ ብርሐን መሐረብ ተንጠልጥሎ አየዋለሁ......

ራሴም አስፈራኝ......

ዐይኖቼ ማሰብ ጀመሩ:: ሴት በአጠገቤ ስታልፈኝ በመጀመሪያ ቁንጅናዋን መልኳን ዐይና በተደራረበ ስልት ማወዳደር ጀመርኩ......መጀመሪያ ከወሰን፣ ቀጥዬ ከገነት መልክ ጋር::

በኩረ ሲመጣ ገነት የምትባል ልጅ እንደፈለገችው ስነግረው በመጀመሪያ የጠየቀኝ: "እዚህ ቆየች?" ብሎ ነበር::

"አዎ" አልኩት

"ምን ያህል ቆየች?"

"አንድ ሁለት ደቂቃ"

"ሌላ ሰው ለማየት ሔጄ እኮ ነው"

አለማየሁ ፀባዬን ያውቅበታል መሰል እኔን እየሳቀ አየኝና: "በኩረ መዝገብ ይጠብስብኛል ብለህ ነው አይደል......ቆየች ምናምን የምትለው"

"ይኼን?......ይኼ እኮ ሴት ይሁን ወንድ አይታወቅም" አለ ወደ እኔ እያመለከተ::

ዝም አልኩት::

አለማየሁ እንደተደናገጠ ሰው ሁለታችንን አቀያይሮ አየና (የተሰጠኝ ስድብ የሚያስገርመኝ መስሎት) እኔን ለመከላከል ይሁን ወይ እሱም ሴት ተነፍጐ......

"እንደ እህትህ ናት አይደል ዘመድህ......ልትቆርጣት ነው ምንድነው?" አለው::

"ከእናንተ ዱርዬዎች ጋር ተገናኝታ እንድትበላሽ አልፈልግም"

"አንተ እቤቷ ሔደህ ታድር የለም?"

"ዘመድ ነኝ"

"እንደ ሙሴ ዘመን አታስብ......በልጅቷ ምን አገባህ? ዘመድህ ከሆነች ምን እንደ ባል ያደርግሃል"

"እንዴ? ዘመዴ እኮ ናት......እህቴ በላት"



@BOOKALEM

"እንዴ......እኔ ብታጋጥመኝ እንደ በፊቱ አይቼ አሳልፋትም ድባቅ ነው የምመታት......የምታምር ጭቅና" አለ አለማየሁ::

በኩረ በሽቋል:: ስለነጋሳ አለመናር......ቶሎ ከአምቦ አለመመለስ ፈረስ ወይም አህያ ሲጋልብ ወድቆ እንደሆነ በመገመት ተረብ አንስቶ ሊያስቀን ፈለገ:: አልሳቅንም ማለቴ......የሚያስቅ ነገር አልነበረም:: የሚያስቀው ሰው በዘመዱ ሴት ሲቀና ነው:: ነጋሳን እንወደዋለን:: ነጋሳ የሚለከፍ አይደለም:: ነጋሳ እንደ ጥሩ አባት ነበር::

ተኝቼ ግን ገነት ባዶ በነበረው ልቤ ቦታ ተመቻችታ እንደምትመጣ ይገባኝ ነበር:: እኔ ውስጥ እንደምትቀር ይገባኛል:: እንደለከፈችኝ ይገባኛል:: ወይስ እግዜር አንድ ሴላ እርግማን ሊልክብኝ የመጀመሪያ ስቅዱ ናት? መጀመሪያ ገነትን:: ቀጥሎ ፍሬውን:: ቀጥሎ እባቡን::

በተለይ አንድ ቀን ማታ የቤታችን አምፖል ተቃጥሎ በጨለማ ተቀምጠን......ጃፓን አምፖል ሊገዛ ሔዶ......እኔ ወደ በሩ ስወጣ የበሰለ ሾላ የመሰለች ጨረቃ......እንዲህ የምታክል ወሳ ትልቅ ዱባ የመሰለች ጨረቃ ከመሬት ብዙም ሳትርቅ ሰማይ ላይ እንደ ወይዘሮ ቀጭ ብላ አየሁ:: ገፅዋ ትንሽ የቆሸሸ ይመስላል:: በእጄ ጥጥ ጨብጬ ልጠርጋት ብዘረጋ......የምደርስባት የሚመስል:: 'ጨረቃ ስትወጣ' የተባለችው መፅሐፍ ትዝ አለችኝ::

ከመሃል አለማየሁን ጠየቅሁት: "ጨረቃ ስትወጣ የምትባል መፅሐፍ ታውቃለህ?"

ከጨለማው ውስጥ: "ሰምቸ አላውቅም"

"አላነበብከውማ"

"ማ ይደበራል......ሙዚቃ እየሰማን እንጥበስ......ወይስ ደባሪ የአብዮት ነገር እናንብብ"

"ስለአብዮት አይደለም"

በጨለማ ሲያዳምጡት የአለማየሁ ድምፅ የሌላ ሰው ይመስል ነበር::

"ለምን?"

"ሰው ጥሩ ናት ብሎኛል"

"ማን አለህ?"

"እ......ለእኔ ሳይሆን ሁለት የኩሌጅ ተማሪዎች ቆመው ሲያወሩ ጆሮዬ ወደቀ" ዋሸሁ::

"ፖሊስ ነሽ......"

አምፖሉ መጣ:: ጃፓን ባልበላ ሳያጠፋ እየሳቀ ቀጠለው:: መብራቱ በራ:: ያኔውኑ የአለማየሁ ቴፕ ጩኸቷን ጀመረች:: ቀልቃላዋ ሕይወት ወደነበረችበት ተመለሰች:: ሙዚቃው:: ጃፓን ሙዚቃውን ተከትሎ መደነስ ጀመረ:: እኔም በጀርባዬ ተንጋልዬ



@BOOKALEM

የቤቱን ከዳን ቆርቆር የአባጣ ጐርባጣ ሰንበሩን መቁጠር ጀመርኩ:: የቆርቆሮውን ሰንበር እቆጥራለሁ:: ቀን ቀን የቀትር ፀሐይ ከበላይ ስትወጣ ቀዳዳዎች እቆጥራለሁ:: የዕድል ሴራ እንደሆነ አላውቅም የዝናብ ጊዜ ውሐ በሚንጠባጠብበት በኩል ነው አልጋዬ የተዘረጋው:: ለማንኛውም ግን ዝናብ አልፈራም:: በኩረ ይመስለኛል ሴረኛው:: ሴረኛም አልፈራም:: ሴረኛና ዝናብ አልፈራም:: ዝናቡ ሲጠና ነው ታዲያ:: ቆርቆሮው በምስማር ከወራጅ እንጨት ጋ ከተያያዘበት በኩል እየቆየ ጠብታ ውሐ አልጋዬ ጠርዝ ላይ ይወድቃል:: እዚያ ላይ ግልገል አሸንዳ የተተከለ ይመስላል:: ሲፈናጠቅ ትራሴ ድረስ ይመጣል:: አንዳንዴ አልጋዬን ስቶ መሬት ይወድቃል......አንዳንዴ እግሬ የደረሰበት የአልጋው ግርጌ ላይ 'ተም! ተም!' ያደርጋል......

ሴራውንም ዝናቡንም አልጠላም:: ሴራውም ዝናቡም ሁሉም ቢኖሩም ያሉ አይመስለኝም ነበር::

በሥራና በዕረፍት ቀናት በየመንገዶች ዳር አስፋልትና ኩረኩንች ላይ የተሰጡ መፃሕፍት መሐል ጨረቃ ስትወጣን መፈለግ ጀመርኩ:: ብዙ ዐይነት መፃሕፍት አየሁ:: የምፈልጋትን 'ጨረቃ ስትወጣ' ግን አላገኘሁዋትም::

"ጋሼ ይሔን ግዙ ጥሩ ነው"

"ጨረቃ ስትወጣ የምትባል መፅሐፍ አለህ?"

"የማን ነው?"

"ብርሐኑ ዘርይሁን ይባላል"

"የለኝም......መርካቶ ለምን አትወጣም? "

አንድ ቀን መርካቶ ወጣሁ:: ብዙ የውራጅ ሱቆች አዳረስኩና ሊሰለቸኝ ሲል አንድ ሱቅ ውስጥ አገኘሁዋት:: ልቦናዬን ስቼ ጨምድጄ ያዝኳት:: ሻጩ ከባድ ገንዘብ ጠየቀኝ:: አስራ ሁለት ብር ዋጋው ሊሆን አይችልም:: እንዲቀንስ ብጠይቀው አልሰማኝም:: ከእጄ ሊወስዳት፣ ሊነጥቃት ይፈልጋል::

"እምጣ እንጂ. ዩኒፎርም ብትለብስ እኮ አልፈራህም" አለ::

'ፍራኝ' ብሎ የለመነው ነበር?

"ስለ ዩኒፎርም አላነሳንም......ጋሼ......"

"እምጣው የመጨረሻ አስራ አንድ ውሰደው......ይሄ የማይገኝ የድሮ መፅሐፍ ነው:: ይኼን መግዛት ካልቻልክ ሌላ አለልህ" ብሎ አንድ አዲስ መፅሐፍ ፈልጎ አውጥቶ ዐይኔ ስር ገተረው::

"የአብዮት ዋዜማ" የሚል አርዕስት አሳየኝ::

"አልፈልግም:: የምፈልገው ይኼንን ነው"



@BOOKALEM

ትቼ በሌላ አቅጣጫ አዘገምኩ......ስምንት ውሰደው '7' '6' '5' እያለ ሲቆጥር እንዳልሰማ ሰው ዘግቼው ሔድኩ::

በመጨረሻ ከሌላ ቦታ ሲነፃፀር ያልቆሸሸ አግኝቼ አምስት ብር ከፍዬ ወሰድኩ:: ሁለት የማይጣጣሙ ስሜቶች አደሩብኝ:: አንድ ቦታ አረፍ ብዬ ለማንበብ መፈለግና መጽሐፏን በሱሪ ኪሴ ከትቼ ወደ ሰፈሬ በእግሬ መመለስ:: መፅሃፏን ሁዋላ ኪሴ ከተትኩ:: መፅሐፏ ጭኔና ቂጤ ላይ ትሰማኛለች:: አባጣ እጥፋቷ: የእርጅናዋ የብል ጢስ፣ የእርጅና አመዷ ለአመል ጣቶቼ ላይ ቀርቷል:: ወረቀቶቹ ጠረናቸውን......ፊትና ሁዋላ ሳወዛውዛቸው (የሱሪዬ ቴትሮን እንደ ወንፊት ሆኖ)......በመርካቶ እየነሰነሱ፣ በሲኒማ ራስ ምንገድ ዳር እየነሰነሱ፣ በማርስ ሆቴል፣ በበላይ ዘለቀ አደባባይ፣ በተክለሐይማኖት:: ከምንገድኛው አፍንጫ ሳትደርስ......ጠረኗ ከመሬት ከፍታ ምናልባት አንድ ሜትር ተኩል እንደ ትኩስ ጥብስ ጢስ......ጥላ መጣል ያቃተው አመልማሎ ደመና ሆና::

መርካቶ እንደ ሰየች ኮረዳ አብዳ ነበር:: ያው በራሷ አቧራ::

ቤቴ ስደርስ መጽሓፏን ጠረጴዛዬ ላይ አመቻችቼ አስቀመጥኳት:: ከፊት ለፊት ልባሷ ላይ ያለችው የጨረቃ ስዕል ደብዛዛ ሰማያዊ ሆናለች:: ልባሷ ላይ ያሉት እርጅና የሰራቸው ሸንተረሮች በውስጣቸው የጠቆረ አቧራ ነክሰው ይዘዋል:: የስዕሉ ዛፍ በከፊል ተልጦ ቆሻሻ የጣት ማህተሞች ይታዩበታል:: መፅሐፏን የውሐ ፈረሰኛ ከወሰዳት በሁዋላ አንድ አሣ አጥማጅ በመረብ ጠልፎ ያወጣት ትመስላለች:: የውስጥ ወረቀቶቿ የቆሸሸ ቢጫ ቀለም ነበራቸው:: አልፎ አልፎ መፅሐፏ ውስጥ ሕዳጉቹ ላይ የደም ነጠብጣቦችና አንዳንድ የማይገቡኝ ቃላቶች በሰማያዊ ብዕር ተፅፈዋል:: የመጀመሪያዋ ገፅ ካርታ ነገር ተስሎባታል::

የጀርባ ሽፋኗን ከተሸመለለበት ስዘረጋው ቀድሞ ወደ ነበረበት ይመለሳል:: ቢቸግረኝ ለማስተካከል ብዬ እላዩ ላይ ትልቅ የፊት መስታወት ከግድግዳ ላይ አውርጄ ደረብኩበት:: በጀርባዬ ስጋደም እስከዛሬ ተሰምቶኝ የማያውቅ ትርጉሙን ያልተረዳሁት ስሜት ደረቴን ያዘኝ:: ደስ አለኝ:: ሰንባ የሚጠራ ደስታ ነበር:: ትርጉሙን ግን አላውቀውም:: ለምን እንደዚህ እንደተሰማኝ ትርጉሙ አልገባኝም ነበር::



@BOOKALEM

# ሞጂያን (1)

አዲስ አበባ የሚገርም አገር ነው:: ለዚህ በአሥር ጣቶቼ እፈርማለሁ:: በአውራጣቶቼ፣ በአመልካች ጣቶቼ፣ በመሃል ጣቶቼ፣ በቀለበት ጣቶቼ፣ በግልገል ጣቶቼ:: ትርፍርፍ ፊርማ ካስፈለገም በጠቅላላ የእግር ጣቶቼ::

መቸ ዕለት ነው ከአገር አስተዳደር ጀርባ ምሳዬን (ዳቦና ወተት) ልበላ አንድ ደንበኛዬ ሻይ ቤት ስሄድ ዳገቱ ላይ በስተቀኝ በኩል ወደ ውስጥ የምታስገባ ቀጭን የአስፋልት ምንገድ አየሁ:: ይህቺ የአስፋልት ምንገድ ከዋናው ምንገድ ጠርዝ ትገነጠልና በግምት መቶና ሁለት መቶ ሜትሮች ዕርቀት ላይ ሔዳ ሔዳ......ሰተት ብላ ሔዳ.......እንዲት ቀጭን የቆርቆሮ በር ስር ስትደርስ ትቆማለች:: የዚህች ምንገድ ጠርዝ ግማሽ እርቀት ያህል በሰዎች ሰልፍ ተሞልቶአል:: እንደዝምዝማት፣ እንደጥለት:: በሙሉ የተሰለፉት ታዳጊ ወጣቶች ነበሩ:: ነገሩን ችላ ብዬ መንገዱንና ሠልፉን አልፌ ትንሽ ዕርቀት እንደሔድኩ ከነከነኝና ወደ ሁዋላ ተመለስኩ:: ግንባይዋ ምንገድ ገባሁና ትንሽ እንደ ሄድኩ የሰልፉ መጨረሻ ላይ ደረስኩ:: ከሠልፉ በስተመጨረሻ የቆመችውን አንዲት ልጅ ከጀርባዋ ነካካሁና:

"ሰማሽ እህት የምን ሰልፍ ነው?" አልኳት::

"ፈለግህ አንተም?" አለችኝ::

"የምን ሰልፍ ነው? ምንድነው የምፈልገው?" አልኳት::

በዚህ በኩል ቀበሌ እንዳሌለም አውቃለሁ::

"እግሮቻችንን እያሰራን ነው"

"ምንድነው የምታሰሩት?"

"እግሮቻችንን......ለምን ተሰልፈህ አታየውም:: ትደርሳለህ" አለችኝ

ሚስጢር ሰላበዛችብኝ ከፊት ለፊቷ የነበረችውን ሌላ ልጃገረድ ቀድሞ የጠየቅሁትን ተመሳሳይ ጥያቄ ጠየቅሁዋት:: እሷም እንዲሁ ተመሳጥራ መለሰችልኝ:: ነገሩ አበሸቀኝና ከሁዋላ መሰለፌን ትቼ በቀጥታ የሰልፉ ቆብ ወዳለበት ወደ ቆርቆሮዋ በር ሔድኩ:: ሠልፉ መጀመሪያ ላይ ያለውን አንድ ግንባሩን የሚያክ ቡግራም ጐረምሳ ይሔ የማየው ሰልፍ ምን እንደሆነ ጠየቅሁት:: እንደ ልጃገረዶቹ ተመሳሳይ መልስ ሰጠኝ:: ከተለመደው ውጪ አንድ ነገር እዚያ አካባቢ እየተሠራ መሆኑ ገባኝ::

የተገረበበችውን ሸንቃጣ የቆርቆሮ በር አንኳኳሁና ገባሁ:: ፊት ለፊቴ የጫማ መሥሪያ የመሰለች ትንሽ ባለ አንድ ክፍል ቤት አጋጠመኝ:: ሁለት መሐከለኛ ዕድሜ



@BOOKALEM

ያላቸው ሰዎች ግራና ቀኝ እንደ አጋፋሪ ቆመዋል:: የፀዳ ኩትና ሱሪ ቢለብሱም ለምን እንደሆነ ጫማዎች አላደረጉም ነበር:: እግሮቻቸው የቆሰሉ ወይም የተጉዱ ይመስላሉ:: አንደኛው ሰው ምን እንደምፈልግ እንደ መልካም አጋፋሪ እጆቹን ወደ ሁዋላ አጣምሮ በትህትና ጠየቀኝ::

"ይኼ ሰልፍ ለምን እንደሆነ ለማወቅ ነው......ይኼ ቀበሌ ነው ወይስ ትምህርት ቤት ነው?" አልኩት::

"ሱቅ ነው" አለኝ ፊቱ በሳቅ ተፈነካክቶ::

"የምን ሱቅ?" አልኩት

"እግር የሚሰራበት" አለኝ

"ምን ማለት ነው? ማየት እችላለሁ?" አልኩት

"በተራ ነው ጋሼ......ብዙ ሰው ከጠዋት ጀምሮ እየጠበቀ ነው" አለኝ::

በፖሊስነቴ መብት ተጠቅሜ ሰውዬውን ወደ ጐን ገፋሁትና ወደ ውስጥ ገባሁ:: ሊያቆመኝ አልሞከረም:: ውስጥ ድንግዝግዝ ያለ ነው፣ ምን አልባት ዐይኖቼ የውጭውን ጠራራ ፀሐይ ስለለመዱ ይሆናል:: ዐይኖቼን ከክፍሉ ጥቁረት ጋር እስካላምድ ቆሜ ስጠብቅ ወፍራም ሾከክ ያለ ትሁት ድምፅ ሰማሁ::

"ጋሼ ተቀመጥ......ምን እንድንረዳህ ትፈልጋለህ?"

"እዚህ ምን እንደሚሰራ ለማወቅ ነው" አልኩ:: በትሁት ድምፅ የተናገረው ሰው መልክ ግን አይታየኝም::

"ተቀመጥ......ይኼን ለመከታተል እንኳን ሕግ አይፈቅድልህም......ቢሆንም አረፍ በልና ታያለህ" አለኝ::

እውጭ ቆመው እንደነበሩት ባለ ባዶ እግር ሰዎች አንደኛው ብቅ ብሎ አንዲት ኩርሲ አመጣና ሰጠኝ:: ትህትናው ወደ መሽኮርመም ይጠጋል:: ተቀመጥሁ:: ዐይኖቼ ጨለማውን ተላምደው ሲጨርሱ እነበርኩበት ክፍል ውስጥ ስድስት ሰዎች እንዳሉ ተረዳሁ፣ እኔን ሳይጨምር:: ከነዚህ ከስድስቱ አምስቱ ወንዶች አንዷ ሴት ነበሩ:: አንደኛው ወንድ ሴቷ ፊት ለፊት ተቀምጧል:: ሁለቱ ሴቷ ግራና ቀኝ ቆመዋል:: ወንበር ያመጣልኝ ሰው እጆቹን ወደ ሁዋላ አጣምሮ ልትገሠሥ እንደተዘጋጀች ድንግል ሙሽራ በትኩረት ያየኛል:: ራቅ ብሎ ግድግዳ ጥግ የቆሰሉ እግሮቹን ዘርግቶ አንድ ሰው ተቀምጧል:: ከመሐል ከብዙዎቹ ገለል ብሎ አንድ ሰው የተነጠፈ ፍራሽ ላይ እንደ ድሮ አዜዎች ተቀምጦአል:: ባለሪዝ ነበር:: እንድቀመጥ የጋበዘኝ ነው::

"እንደልጅቷ እንዲሆንልህ ትፈልጋለህ?" አለ ፈገግ ብሎ እያየኝ



@BOOKALEM

"ምን? "

"እግርህ?"

"ምንድነው የሚሆነው?"

"እንደገና ይሠራል"

"እግሬ ምንም አልሆነም"

"የተበላሽ ነው......"

የእሱን እግሮች አየሁዋቸው......በሚያምሩ ካልሲዎች ተጋርደዋል::

"ለማንኛውም ሴቷ ስታደርግ እይ" አለኝ በፍጥነት::

ስሜቴን ከዐይኖቼ ለማንበብ የሚጥር ይመስላል:: ግራና ቀኝ የቆሙት ሰዎች የልጅቷን እጆች እንደምትሰቀል ዐይነት ወዲያና ወዲህ ወጥረው ይዘዋታል:: ፊት ለፊቷ ተቀምጦ የነበረው ሰው እግሮቿን ግራና ቀኝ በደንብ እንድትከፍት ነገራትና የቆመውን ሰው ጠራው:: እጆቹን አጣምሮ የቆመው ሰው በችኮላና በሥነሥርዐት መጥቶ አንድ እግሯን ያዘ:: ቀሚሷ ተገልቦ ቡታንታዋ ይታየኛል:: በማፈር ፊቴን አዞርኩ::......ፊት ለፊቷ ቆሞ የነበረው ሰው ቂጡን ወደ ልጅቷ ፊቱን ደሞ ወደ እኔ አዞረና አንድ እግሯን በእግሮቹ መሐል አሾልኮ እንደኩርቻ ተቀመጠበት:: አሁን በጉጉት ማየት ጀመርኩ:: ከለበሰው ጥቁር ካኪ ኩት ኪስ ጥቁር ብልቃጥ አወጣና ልጅቷ እግር ስር አስቀመጠ:: ቀጥሎ ወደ ሌላ ኪሱ እጁን ሰዶ ወስፌ የመሰለ ነገር አወጣ:: በወሬኛ ጉጉት እመለከታለሁ::

"በሉ በደንብ ያዙልኝ" አለ አጋሮቹን::

ሰዎቹ ልጅቷን ግራና ቀኝ ልትበጠስ እስክትደርስ ድረስ ወጥረው ያዟዋት:: ሰውዬው በመጀመሪያ እየጋለበ ያለውን የግራ እግርዋን ጣቶች ለየብቻ እየያዘ ጥፍሮቻቸው ስር ያለውን ሥጋ ተራ በተራ በወስፌው ወጋ:: ከሁሉም ጣቶች ደም ይወጣ ጀመር:: ልጅቷ በሕመም ትሰቃያለች፣ ትፈራገጣለች:: ቀጥሎ ብልቃጧን ከፍቶ በቀስታ እየዘቀዘቀ ከውስጧ በቁጠባ የሚወጣ ጥቁር ነገር በአመልካች ጣቱ ተቀበለና ደም የሚወርዳቸው ልጅቷ ጣቶች ላይ ጠረገ:: በተመሳሳይ መልክ ሁለተኛ እግሯን አደረገንትና ግራና ቀኝ ደጋግፈው አቆሟት:: እያቃሰተች ተነሳች:: ሲያልቅ አልጮኸችም፣ አላለቀሰችም:: እግሮቿን ጫማዎቿ ውስጥ እንድታስገባ ከረዷት በሁዋላ በቀስታ እየገፉ ከቤቱ/ከሱቁ አስወጧት (የሚከፈል ገንዘብ ነገር ግን አላየሁም):: መራመድ ስለከበዳት ነው መሰለኝ ጉልበቶቿ በመጠኑ ጎብጠው ነበር::

የተቀመጠውንና መጀመሪያ ወደ አናገረኝ ሰው ፊቴን ለጥያቄ ዞር አደረኩ::



@BOOKALEM

"ሕገ ወጥ ነው ብለህ እያሰብክ ነው አይደል?" አለ በብልጠቱ እንደኩራ ሁሉ የፍየል የመሰለ ጢሙን እየጐተተ......እንደ መልካም አዛውንት::

"አይደለም:: ምንድነው የምታደርጉት ትርጉሙ አልገባኝም"

"እግር እየሰራን ነው"

"ምን እያደረጋችሁ ነው?–ምንድነው የምትሰሩት?"

"ያቺን ጥቁር ብልቃጥ አይተሐል?"

"አዎ"

"በዚያች ብልቃጥ ውስጥ የሙጃሌ ቀንጫዎች ተሞልተውባታል"

"እና"

"እናማ ሙጃሌ እየተከልን ነው"

"ምን?"

"ሞያሌ አታውቅም?"

"ይሔ እግር የሚያሳክከው?"

"አዎ"

"እሺ ይላሱ ልጆቹ?"

"ይህቺ ልጅ ያስገደዳትን አይተሃል? ተበለቃቅጣ እግርዋን ስትሰጥ"

"ግን ሕገ-ወጥ ነው"

"ምን ልታደርግ ነው?"

"ለሚመለከተው ባለስልጣን ማስታወቅ አለብኝ"

"የአንተ ሥራ አይደለም"

"ሥራዬን እኔ አውቃለሁ"

እሰልፉ መጀመሪያ ላይ ግንባሩን እያከከ ቆሞ ያየሁት ብጉራም ልጅ ተራው ደርሶ መሆን አለበት ገባ::

"ሠላም!" አለ የተቀመጠው ሰው ፊቱን በፈገግታ ሞልቶ ሪዙን በቀስታ እየሳበ::

"ሠላም!" አለ ልጁ:: አካሔዱ ለየት ያለ ነበር::



@BOOKALEM

"ይኼ ልጅ ደንበኛችን ነው" አለ ሰውዬው ወደ እኔ እያየ:: ሳቅ እያለ:: ኩራት የሚሰማው ይመስላል::

"የምን ደንበኛ?"

"አንዳንዴ የሰራነው ይበላሻል......ወይም እንደተፈለገው አይሆንም......እና ወጣቶች እየደጋገሙ ይመጣሉ:: አንዱ ደንበኛችን ይኼ የምታየው ዘንካታ ነው"

"ምንድነው የሚበላሸው?"

"አስሩም የእግር ጣቶች ላይ ሙጃሌ ከዘራንባቸው በሁዋላ፣ ለትንሽ ጊዜ ለምልመው ይደርቃሉ፣ ከፊሎቹ ከነአካቴው አይበቅሉም......"

"ሙጃሌዎቹ?"

"አዎ"

ብጉራሙ ልጅ ቀድሞ ልጅቷ የተቀመጠችበት ወንበር ላይ ሔዶ እግሮቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ ተቀመጠ:: ሰዎቹ ልጅቷን ይዘዋት እንደነበር አድርገው ያዙት:: ጫማዎቹን በቀስታ አወለቀለት:: ሁለቱም ካልሲዎቹ ጫፎቻቸው በደም የቀለመ ነበር::

"እንዴት ነው?" አለው ጫማ አውላቂው

"ከግራ እግሬ ሦስተ ጣቶቼ......ከቀኝ እግሬ አንዱ ጣት ተደግመው መሠራት አለባቸው:: እንደምፈልገው አያረኩኝም"

"ቀላል ነዋ......" አለ ጢማሙ ወደ እኔ እያየ:: እንደገና ወደ እግሮቼ እያየ::

"ሰማህ ወንድም ስለእኔ እግር አታስብ" አልኩት::

አፉን ወደ ላይ ከፍቶ ተንከተከተ:: በፀጥታ ተቀምጬ ማየት አልፈለኩም::

"ልጁን ሲራመድ አይተኸዋል?" አልኩት ሰውዬውን::

"ከማድረግ ይልቅ የማውራት ድፍረት ነው ያለህ" አለኝ::

"ቂል አይደለሁም" አልኩት

እንደገና አፉን ከፍቶ ሳቀ:: ገበሎ ይመስል ነበር:: ከጀርባው ግድግዳ ላይ በሠልፍ አስር የሚደርሱ ከጉሬዛ ፀጉር የተሰሩ ጭራዎች ተሰቅለዋል::

"ይኼ ልጅ ቂል ይመስልሃል? ከአንተ የበለጠ ምላጭ ነው:: አካሔዱ የተለየ ያልከው አዎ የተለየ ነው:: ታዲያ ምን መጥፎ ነገር አለው:: ደስታውና አላማው አካሔድን ለማጣመምና (እኔ ማጣመም አልለውም) በእከኩ ለመሰቃየት እኩ ነው:: ስቃይን መምረጥ ነው:: ደስታ ይሰጣል:: እከክ ሲታክ የሆነ ዕርካታ አይሰማህም?



@BOOKALEM

ስቃይን በትንተና ፈልጐ ማግኘት የቻለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው:: የምርጥ ስቃይ ዕድለኛ ነው:: ይኼ እኔ እንደምገምተው ታላቅ ችሎታ ነው:: እንዲህ የተሳካለት ጥቂት የዓለም ክፍል ብቻ ነው:: የተሠለፈውን ሕዝብ አይተሃል? እንዲህ የሚፈልገውን ነገር እኔ በነፃ ባድለው ምን አለበት:: ደግ ሰው ነው የሚያሰኘኝ:: አፍ አልሰማም እየሀ ድርጊት ነው የማየው:: ሰው የሚያወራውን ሳይሆን የሚያደርገውን ነው:: የማደርገው በላተኛና አቅርቦትን የማገናኘት ነው:: እንደውም ያስመሰግነኛል:: የቤቴን በር ከፍቼ ብቀበለው ምን አለበት?:: አንተ ምን ትሰራለታለህ?"

"ታዲያ ለምን ገንዘብ ትቀበላለህ?"

"እየሀ ገንዘብ ስቀበል? የፈለግሁ ቀን አገልግሎት ይሰጡኛል:: ማን ሲከፍል እየሀ?"

"ሴቶቹስ? ሴቶቹ እግራቸው ሲበላሽ ምን ያገኛሉ?"

"ስለ እኩልነት አልሰማህም? እሱ እንኳን አይጨንቀኝም:: ሴቶቹ እዚህ ሲመጡ ተስፋ ቆርጠው ነው:: አስቀያሚ ሆኑ አልሆኑ ግድ አይሰጣቸው......"

"ስንት ሰው እንዲህ አድርገሃል?"

"አሥር፣ ሃያ ሺህ እዚህ ከተማ ብቻ"

"አገሩ ተንሻፎ አልቆአል ማለት ነዋ"

"ሌላም ሌላም ቦታ ነበርን ምን ይሠራልሃል ባወራህ......በነገራችን ላይ እንዲህ እግራቸው ተሠርቶ የምታያቸው ሰዎች ሞጆያን ይባላሉ:: በነጠላ ሞጂያ......ወንዱም ሴቱም:: በእኔ ዘንድ የፆታ እኩልነት የተከበረ ነው" አለ እየሣቀ::

"ይኼን ለሚመለከተው ክፍል መንገር አለብኝ"

"ይቅርብህ"

"ምነው?"

"የትም አትደርስም"

"እናያለና"

አፉን ወደ ሰማይ ከፍቶ የገበሎ ሳቁን ተንከተከተ:: እግሮቹ የተሰሩለት ልጅ ከሱቋ እየተንሻፈፈና እየሳቀ ወጣ:: ከሁዋላው ተከተልኩት:: ቀጭኗን የአስፋልት ምንገድ በዝምታ ጉን ጉኑ ስሔድ ቆየሁና እየተገረምኩ ያጋጠመኝን ማመን ከብዶኝ ወደ ዋና ምንገድ ገብቼ ወደ ቀኝ ታጠፍኩና ነገሩን ለማመልከት ወደ ፖሊስ ጣቢያ በሩጫ ሔድኩ......እንደዚያን ቀን የሰው ነገር አሳስቦኝ አያውቅም::



@BOOKALEM

ፖሊስ ጣቢያ ስደርስ ተረኛው ፖሊስ ከጠቆረ አሮጌ ጠረጴዛ ጀርባ [illegible] መቶኪያ ጥርሱን ሲልግ አገኘሁት። ስላጋጠመኝ ነገር በአጭሩ አወራሁት።

"እንዲህ ያለ ነገር የለም። እንደለመድከው ምንገድ ዳር ሲታንቀላፉ ያለምከው ነው" አለኝ።

"አብረን እንሒድ ወይ ሰው ስጠኝና ላሳይ" አልኩ።

"ይኼ ያንተ ጉዳይ አይደለም። ጤና ጥበቃ ከፈለገ ይቆጣጠር። አንተ ምንገድህን ብቻ ጠብቅ"

"ጊድ እኔ ለበላይ መንገሬ አይቀርም"

"ማን ያምንሃል? ያንተን ቅዠት ማን ያምናል? እንዲህ እንዲህ ዐይነት ማቃጠር እንኳን አለመደብህም። አንተም እንደሌሎቹ ተበላሸህ እንዴ?"

"ማቃጠር አይደለም ጊድ"

"በል አትነዝንዘኝ። ይሔ የአንተ ጉዳይ አይደለም። ጤና ጥበቃ ከፈለገ ይቆጣጠር። አንተ የታዘዝከው ምንገድ እንድትጠብቅ ብቻ ነው"

"ለጋዜጠኛ ባሳይስ?"

"ጋዜጠኛ ምን ብሎ ይሰማሃል? የዚህ አገር ጋዜጠኛ የተባለውን ነው የሚሰራው"

"ፖለቲካ ስላልሆነ መቸም መውጣቱ አይቀርም"

"ፖለቲካ አይደለም?"

"ምኑ ነው ፖለቲካ?"

"ለማንኛውም አይገባህም። ወደ ምንገድ ጥበቃህ ተመለስ......ተመለስ"

"ፖሊስ መምሪያ ሔጄ ለሚመለከተው እነግራለሁ"

"ቆይ ሳስደስትህ......ከአምሳ አለቃ ጋር ሂዱና እዩ"

"አምሳ አለቃ ባለጉዳይ አለው"

"ሁሉ ነገር አንተ እንደፈለከው አይሆንም......ይልቁን አምሳ አለቃን ልጥራልህ"

አምሳ አለቃ በስልክ ተጠርቶ ሲገባ ሠላምታ ሰጠና ቆመ......ከተረኛው ጋር በዐይኖቻቸው ሊገባኝ ያልቻለ የሆነ ነገር ተነጋገሩና:

"አብረኸው ትሔዳለህ?" አለው

"አዎ ግን ባለጉዳይ ተቀምጦአል"



@BOOKALEM

"በል ተወው አብሬው እሔዳለሁ......መዝገቡ 'ዕብድ ነው' ነው የሚባለው ያለ ነገር አይደለም......ጃን"

መፋቂያውን የጠረጴዛ መሳቢያ ውስጥ ከተተና ከተቀመጠበት እየተጉተተ ተነሳ:: በተገኘች እንዲት እሮጌ ቮልስዋገን ወደ አገር አስተዳደር ጀርባ በቀስታ እየነዳ ሔድን:: ከመድረሳችን በፊት ከሩቅ በጣቴ ቀጭኗ ምንገድ የምትጀምርበትን ቦታ ለተረኛው ጠቆምኩትና ብዙ ሳንቀርብ ወረድን:: እኔ ፊት ለፊት እሱ በቀስታ ሁዋላ ሁዋላ ተከታትለን ምንገዷ ያለችበት ቦታ ስንደርስ......ምንገዷ የለችም::

በመጀመሪያ ተሳስቼ እንደሆን በማለት ከላይ እስከታች ስቃኝ በፍፁም እዚያ አካባቢ እንኳን ከአስፋልት የተሰራ ምንገድ ይቅርና የጉንዳን መጉዳኛ አይታይም:: አብሮኝ የመጣውን ሰው ተረብሼ አየሁት:: ቤቷ የነበረችበት አካባቢ በሙሉ አጫጭር የደረቁ ሳሮች የበቀሉበት ቦታ ሆኖአል::

"ምነው?" አለኝ ሰውዬው ፊቴን አጢኖ::

"እንዴት ነው እባክህ? እዚህ ዘንድ ምንገድ ነበር" አልኩ

"ታዲያስ? ጠፋ? መንገድ እግር ማብቀል ጀመረ?" አለኝ

"ይኼ ዛፍ ትዝ ይለኛል......ያ ታችኛው ቤት......ልክ እዚህ ዘንድ ነበር ምንገዱ::"

"ሌላ የሚመስል ቦታ እንደሆነ" አለ አፉን ጠመም አድርጐ ሊስቅ እየከጀለው::

"እኔ አላበድኩም ጓድ"

"ማን ያምነኛል ነው? በመጀመሪያ ሙጀሌ የሚታደልበት ቦታ አየሁ አልክ:: እንዳታፍር አመንኩህ:: መጠራጠር ሲገባኝ:: እንደገና ያሌለ ካርታ ላይ ያልሰፈረ ቦታ አለ ብለህ አመጣኸኝ......ዕብድ መሆንህ የተረጋገጠ አይሆንም?"

"ዕብድ አይደለሁም ጓድ"

መንገዱና ያቺ የእግር መስሪያ ሱቅ የነበረችበት ቦታ በሙሉ ታጥሮ ቤት ቀርቶ ሙጃ እንኳን ያልበቀለበት ወና ቦታ ሆኖአል:: ራሴን እያከኩ ወገቤን ይዤ ቆምኩ::

"ትመለሳለህ?" አለኝ ሰውዬው

"የት?"

"የት ይላል?......ዕህፈት ቤት"

እያሰላሰልኩ ነበር::

"አልሔድም"

"ምን ልትሠራ ነው?"



@BOOKALEM

"ያው ሥራዬን ነዋ!"

"ይሔን ጉዳይ ሪፖርት አደርጋለሁ"

"አድርገው"

"አትለማመጥም?" አለ እየሳቀ::

"አድርገው"

ተረኛው እኔን ትቶኝ መኪናዋ ወደ ቆመችበት ሲመለስ ዞር ብዬ አየሁት:: ድንጋጤ ከላይ እስከታች እንደ ነፋሻ ውርጭ መታኝ:: ሰውዬው ሲራመድ መንሻፈፍ ብቻ ሳይሆን አካሔዱ ያን እግሩን ሲሰራ ያየሁትን ጉረምሳ ልጅ ይመስል ነበር:: መኪናው ውስጥ እስኪገባ ድረስ አተኩሬ በዐይኖቼ ተከተልኩት:: መኪና ለመግባት ቀኝ እግሩን ሲያነሳ......የታመመና፣ የቆሰለ እግር የሚያነሳ ይመስል ነበር......ግራ እግሩ አግልቶ መሬት አይረግጥም:: በመጠኑ በተረከዙ እንደቆመ ዐይነት:: መኪና ውስጥ ገብቶ እስኪቀመጥ በድንጋጤና በመገረም አየሁት:: መኪና ውስጥ ገብቶ ከተረጋጋ በሁዋላ አፉን ወደ ላይ ሰቅሎ ከት ብሎ ሳቀ......የቮልስዋገንዋ ጋቢና ውስጥ የተንጠለጠለችውን የጉሬዛ ጭራ ያየሁዋት መኪናዋ ተነስታ መንቃነቅ ስትጀምር ነበር......

ከዚያ በሁዋላ ለረዥም ጊዜ እጅግ፣ እጅግ ፈርቼ ነበር::



@BOOKALEM

# የአዲስ አበባ አፎች

የአዲስአበባን አፎች ከሌሎች ከማውቃቸው ጥቂት ከተሞች አፎች የሚለያቸው......አንዳንድ ቀለም የተቀቡ ስላሉባቸው ነው:: በተጨማሪም ጠረናቸውን ለማሻሻል በየመንደሩ ኩልጌት የጥርስ ሳሙና ይሸጣል......ሱቅ በደረቴው የሐረር መፋቂያ ይደረድራል......እነዚህ ኩልጌቶች ከብዙ ዐይነት ዕቃዎች ጋር ሱቆች ውስጥ ይደረደሩና እስከንፈልጋቸው ይጠብቁናል:: አንዱ ጡጦ አንድ ብር ከሃምሳ:: እንደገና የጥርስ ሳሙና ያለቡርሽ ስለማይሰራ አንድ ቡርሽ በአንድ ብር......

የእንጨት የጥርስ መፋቂያዎችም ምንገድ ዳር እግርና ጫማ ስር አቧራ እየቦነነባቸው ትልልቆቹ በአሥር ሣንቲም የተበላሸ ወይም ይበላሻል ተብሎ የተጠረጠረ አፍ ማረሚያ ይሸጣሉ......ያው ነው::

ከሌላ ከተማ የሚለያቸው የአዲስአበባ አፎች ቀለም መቀባታቸው ነው:: በሳሙና መታጠባቸው ነው:: ጥርሶቼን ፍቄ አላውቅም:: ጥርሶቼ ግን ነጫጭ ነበሩ:: እስከዛሬ የአፍ ነገር አስደንቆኝ አያውቅም:: ምናልባት ቀን ይመጣ ይሆናል እኔም እንደ ሌሎች ለአፍ አፍ አፍ አፍ አፍ አፍ አፍ አፍ አፍ አፍ አፍ ለአፍ አፍ አፍ ለአፍ አፍ የምልበት::



@BOOKALEM

# ሰዓት ስባሬ

እንደምሽት ጥበቃ የምጠላው አልነበረኝም:: ዛሬም:: እንደ ምሽት ጥበቃ የምወደው አልነበረኝም:: ዛሬም:: አብሮኝ የሚያድረውን የስራ ጓደኛዬን እንዲህ ስለው 'ትዘባርቃለህ' አለኝ:: ከእኔ ሮንድ ጥበቃ የበለጠ የሚገርመኝ ሌሊት ለመዝረፍ ከአልጋው ተነስቶ የሚመጣው ነው:: አንድ ሰለት ሁለት ሰካራሞች አጋጠሙን:: ሰው አልጠላም፣ አልወድም:: ሰካራምም አልጠላም አልወድም:: ባልደረባዬ ለቀበሌ አሳልፈን ሰጥተን እስር ቤት እናሳድራቸው አለኝ:: ሃሳቡ ደስ አላለኝም ነበር:: ሰዎቹን ብንጠይቃቸው የትም ቢወሰዱ ግድ እንደማይሰጣቸው ተናገሩ::

"ገንዘብ አላችሁ የሚከፈል?" አልኳቸው

"ታስረን እናረጃለን......በእሱም ነፃነት ከተገኘ ምናለበት" አለ አንዱ አሹዋፊ::

"ሊነጋ ስለቀረበ አብራችሁን ቆይታችሁ ቤታችሁ ግቡ" አልኳቸውና አብረን ድልድይ ላይ በሰልፍ ተቀመጥን:: እነሱም ፖሊሶች ይመስላሉ ግን ያለ ዩኒፎርም::

"ሰው ቢያየንስ ከፖሊስ ጋር?" አለ አንዱ::

"ምናለበት?" አልኩት::

"በሰላይነት እንታማለን"

"ታዲያ ታስረህ ብታድር ይሻልሃል?" አለው ባልደረባዬ::

"የት ነው ያመሻችሁት?" አልኩት አንዱን::

"ተረት ሰፈር"

"የት ነው የምትሔዱት?"

"ጣሊያን ሰፈር"

"ወደ ላይ እንሸኛችሁ?» አልኩት

"አንተ አላበዛኸውም......ንጉሥ አደረካቸው?" አለ ባልደረባዬ::

"ኀረምሶች ናቸው"

"ሥድ ሁሉ" አለ ባልደረባዬ::

"ተማሪዎች ናችሁ?" አልኩ

"ምን አገባህ–አርፈህ አትሸኛቸውም?" አለ ጓደኛዬ



@BOOKALEM

"እስኪ እናውራበት" አልኩት መልሼ::

"የጥበቃ ሥራ የጥበቃ ሥራ ነው......የቀል ሥራ ትሰራለህ......በግ ሆንክ" አለኝ::

ሁለቱ ሠካራሞች ያዩናል:: ዝም አልኩ:: ነገር መመለስ አልፈለኩም::

"ከማን ጋር አደራችሁ?" አልኩ ፈገግ ብዬ (ፈገግታዬ በጨለማ እንደሚታይ ተማምኜ)

"ዕውነትም ፖሊስ ነህ ጥያቄ አበዛህ" አለ አንደኛው......

"ሴት:: ሴት ጋ ነው ያደርነው......የእሱ ውሽማ ዘመድ ሞቶባት ሌሊት ሲያረዷት ተቀሰቀስን:: ብቻውን ከሚወጣ ብዬ የእኔን የሚሞቅ አልጋ ትቼ ተከተልኩት......ምን ያስደብቃል?" አለ ሌላኛው::

"ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ያረዷሉ?" አለ ጓደኛዬ......

"ምቀኝነት ነዋ" አለ እየሳቀ ከዚያም......"ያለወንድ ያደሩት ተመቅኝተዋት:: ቆንጆ ሆኖ መወለድ መከራ የሆነበት አገር አለ"

"ጥሩ ፖሊሶች ትመስላላችሁ" አለ አንደኛው ሰካራም::

ጓደኛዬ ሳቅ አለ......ምስጋናውን ለመሻማት::

"ነገ የስራ ቀን ነው......ምን ትሰራላችሁ?" አለ ጓደኛዬ::

"የምን ሥራ......ከኰሌጅ ተመርቀን ሥራውን እየጠበቅን ነው" አለ አንዱ ሲጃራውን እየለኰሰ::

ክብሪቷ የሚያምር ቢጫ ብርሐን አወጣች:: ተቃጥላ እስክታልቅ ጠበቀና ወደ ድልድይዋ ስር ጣቶቹ እንደተቃጠሉበት ሁሉ ተቻኩሎ ወረወራት::

"ሰማህ" አልኩት አንዱን

"ምነው?" አለ በትንሹ እየተኰላተፈ

"መቸም የኰሌጅ ተማሪ ነህ...ልብ ወለድ አንብበሃል?" አልኩት

"የምን ልብ ወለድ?"

"ምን ዐይነት ጥያቄ ነው?" አለ ጓደኛዬ

" 'ጨረቃ ስትወጣ' የምትባል ልብ ወለድ"

"አላውቅም.......ማነው የፃፈው?"

"ብርሐኑ ዘሪሁን የሚባል"



@BOOKALEM

"እርሳው እባክህ ሌላ ችግር አለብኝ"

"እንደ እሱ ትፅፋለህ?" አልኩት

"በብዕር ወረቀት ማረስ ቁም ነገር አደረከው?" አለኝ።

ልናገረው ፈለግሁ። ልሰድበው ፈለግሁ። እሱ እየተሳደበ ነበር። 'ጨረቃ ስትወጣ' እህቴ ናት። ከሰው ይልቅ የሞቀች......ሲነጋ ሲነጋ ከትራሴ ተስባ ጉንጮቼን በሆሄዎቿ የምትስም፣ ፊቴን በወተት ወረቀቷ የምታጥብ ናት።

"ካላነበብከው እንዴት ትሰድበዋለህ?" አልኩት

"የው ይታወቃል.......የረባ አይፃፍም። ፕላስ ሳላነበው ልነግርህ አልችልም"

"አንተ ምንድነህ? ምንድነው የተማርከው?"

"እርሻ"

"ምን ሰርተሃል?"

"ምን ይጨቀጭቀኛል?......ሰዓት አላፊ እንዳልታሰር አዳንከኝ ማለት እኮ የመጨቅጨቅ መብት አለህ ማለት አይደለም"

"ገርሞኝ ነው"

"ምን ይገርማል?"

"ያጋጠመኝን ሰው ሁሉ ብጠይቅ......የሚያውቅ የለም። የት ብጠይቅ ይሻላል?"

"እርሳው" አለ ባልደረባዬ

ጎረምሶቹ ሲጃራ ተቀባበሉ።

"የማያስጨንቅ ያስጨንቅሃል" አለ አንዱ ሰካራም።

ብርዱ ጠንክሮአል። ጓደኛዬ ወደቆመ የፖሊስ መኪና ተጠግቶ ያወራል። ወደ እኛ እየተገላመጠ ያያል። ከላንድሮቨሩ ወፍራም የሚቆጣ ድምፅ ወጣ። ትንሽ ያስፈራል። በተለይ ፀጥ ባለ ጨለማ ሲሰሙት። ኤሊ ስትፈሳ በምትሰማበት ጫታ።

"ጓድ መዝገቡ......እነዛን ሰዎች ተዋቸው......የፈለገው ቢደርስባቸው ምን አገባህ......ቢቻል ለቀበሌ ማሳለፍ ነበረብህ። ብዙ ችሎታ ታሳያለህ አንተ ሰው። ለምን መጠቀሚያ ትሆናለህ። ይኼ የአዲስአበባ የሚሊዮን ሕዝብ ከተማ ነው። የሁለት ጋጠ-ወጦች አይደለም። አሁን ልቀቃቸውና በዕድላቸው ይንጋባቸው።"

ልጆቹን አየሁዋቸው። ተደናግጠው ነበር። እንዳልፎከሩ ሁሉ።

"እሺ ጓድ" ብዬ ሠላምታ ሰጠሁ



@BOOKALEM

ጊደኛዬ ተመልሶ መጣና: "የመቶ አለቃው ተቆጣ" አለኝ:: እንዳልሰማሁት ሁሉ::

"መቶ አለቆች ሁል ጊዜ እንደተቆጡ ነው" አልኩት

"እኔን ነው የምታስጠጣኝ......አንተስ ቢሆን? ስንት ነገር ፋይልህ ውስጥ እንደገባ ታውቃለህ? ምን ለመሆን ነው?" አለኝ

"እርሳው"

"በጣም ሞኝ ነህ"

"እነዚህ ልጆች ታሰሩ አልታሰሩ አብዮት አይጎዳም ......ገንዘባቸው የሚያልቅ የእነሱ:: ለእኔ ሰዓት እላፊ ከመያዛቸው ይልቅ ያናደዱኝ 'ጨረቃ ስትወጣ'ን አለማንበባቸው ነው"

"ቁም ነገር አግኝተህ ሞተሃል:: ፖሊስ እንጂ ደራሲ አይደለህም"

ችግር የሚያመጡብን ከሆነ ሊሄዱ እንደሚችሉ ከጎረምሶቹ አንዱ ይናገር ነበር:: እኔ ሊነጋ ስለተቃረበ ቆይታችሁ ሂዱ እላቸዋለሁ:: ሌላው ጐረምሳ ስላዳንናቸው ገንዘብ እንፈልግ እንደሆነ በአግቦ አድርጐ ይናገራል:: የሚያበሳጭ ነበር::

ጨረቃ ስትወጣን ያነበበ ማሽሙዋጠጥ የሚችል አይመስለኝም::

በዝምታ በዚህችው የአመለካከት ልዩነታችን ተኮራርፈን ብዙ ቆየን:: ተዘዋዋሪ ፖሊሶች ሲመጡብን ዛፍ ስር፣ ግንብ ስር እየደበቅናቸው ሊነጋጋ አካባቢ ለቀቅናቸው:: ወደ ላይ ወደ ማዘጋጃ ቤት ዳገቱን ሲወጡ ጨረቃ ስትወጣን እንዲያነቡ ለመንኳቸው::

አንዱ 'እርሳው' ዐይነት አንድ እጁን ወደታች አራገበ::



@BOOKALEM

# ቀለበት ተከትዬ

አዲስአበባ እንደገባሁ የሚቀርበኝ ሰው ሁሉ የሚያወራው ስለ ሐብት፣ ስለ ዲ ኤክስ፣ ስለ ቪላ ሆኖና ነው መሰለኝ እንድ ሰሞን ሐብታም ለመሆን ፈለግሁ:: ሀብታም ለመሆን ደ'ሞ ወይ ለረዥም ጊዜ መስራት ወይ ለአጭር ጊዜ መዝረፍ ያስፈልጋል:: ሁለቱንም አልችልም:: ስለዚህ ሐብታም በመሆን ምኞት ብቻ አበድኩ:: ያን ሰሞን በሀል ሆኖ ጥበቃውን አጠንክሩ ተብሎ የሆነ የማይደክም ፖሊስ ጉኔ አቁመው ስንከራተት እውላለሁ:: ያን ቀን ደ'ሞ የደመና ግላጭ ለሚባል ሀሐይ ተጋልጬ ራስ ምታት ይዞ ያንገላታኛል:: ለባልደረባዬ እንዳመመኝ ነግሬው ጥላ ፈልጌ እንደተጠለልኩ አንዲት ቀጭን ሴት ካ.ስ የሚያክል ቀለበት በግራ እጇ መሐል ጣት(7) ያጠለቀች ቀይ ዣንጥላ ስቅላ በአጠገቤ እየተመመች አለፈች:: ቀለበቱ የወርቅ ነበር:: ቀለበቱ ላይ ያለው ፈርጥ ተንቦግቧጊ፣ ትልቅነቱ ለአይነ ስውር ይታያል:: ያ ቀለበት ገበያ ቢወጣ አንድ የጭነት መኪና ሳይገዛ አይቀርም:: የሚገርመው የቀለበቱ ፈርጥ ከመክበዱ የተነሳ መሰለኝ እንደ አንድ ትልቅ የውሐ ጠብታ ያደርገውና ለመውደቅ ያንዣበበ ይመስላል:: ከተጠለልኩበት ወጥቼ ሴትዮዋን ሁዋላ ሁዋላዋ ተከተልኳት::

ወርቅ ያለበት እጇ ብዙ አይወዛወዝም:: ምናልባት ትንሽ ወደፊት ወደሁዋላ በፍጥነት ቢንቃነቅ ኖሮ በጣቷ ስክታው የነበረው ቀለበት በራሱ ክብደት ወልቆ እንደ ዝናብ ወደ መሬት እንደሚወርድ አልጠራጠርም:: ተከተልኳት:: የማጤነው የእጇን እንቅስቃሴ ነበር:: እጇ ደሞ ከላይ ከትከሻዋ ጀምሮ በቀርቀሃ እንደታሰረ ሁሉ ቀጥ......ላቤን ከግንባሬ እየጠረግሁ ዐይኖቼን ከቀለበቷ ላይ ሳላነሳ ሁዋላ ሁዋላዋን......- ፀጥታ እንደሚጠብቅ:: ቢወድቅና እጄ ቢገባ በቀለበቱ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላውቅም፥ ምን እንደማደርግበት አላውቅም ነበር:: አንድ ሕንፃ ስር ደረሰችና ቆም አለች:: ባለቀለበት እጇ ለአፍታ ተወዛውዞ ወደ ፊቷ ሄደ:: አፏን ጠረገና እነበረበት ተመለሰ:: እጇን ስታነሳው ወርቁ ቦታው እንዳለ ለማረጋገጥ፣ ለመፈተሽ መስሎኝ ነበር::

በሴት የሕንፃው ዘበኛ ተፈተሸችና ገባች:: እውጭ ቀረሁ:: ወዲያ ወዲህ እየተመላለስኩ ለግማሽ ሰዓት ያህል እንደጠበቅሁ ሴትዮዋ ከሕንፃው ወጣች:: ገና ብቅ ከማለቷ ጥቁር ዣንጥላዋን ፏ አድርጋ ዘርግታ በመጣችበት ምንገድ መመለስ ጀመረች (ዣንጥላውን የት ለወጠችው?):: ራቅ ብዬ እከተላታለሁ:: ጥቂት ደቂቃዎች ተጉዛ ምንገድ ለመሻገር ስትጀምር ዐይኖቼ ወደ ጣቶቿ ተመለከቱ:: ቀለበቱ አልነበረም:: ደነገጥሁ (በዣንጥላ ለወጠችው?):: ጠርቼ ልነግራት ትንሽ ነበር የቀረኝ::



@BOOKALEM

ቀኑ ኪዳነ ምህረት ሳይሆን አይቀርም ከውይይት ታክሲ የሚወርዱ ማስሮና የደብር ዣንጥላ የያዙ ሴቶች ቦታውን ወረሩትና ጠፉችብኝ:: ወደ ሁዋላ ተመለስኩ:: ሲትዮዋ ያለፈችበትን ምንገድ በጥንቃቄ እያየሁ:: መንገዱ ደሞ ንጹህ አስፋልት ነው:: እንኳን ወርቅ የጥፍር ቁራጭ አይደብቅም:: ሁለት ጊዜ በዐይን ዳሰሳ መንገዱን ወጣሁና ወረድኩ፣ ወረድኩና ወጣሁ:: ሕጋዊ ጥበቃዬን ረስቼዋለሁ:: ይኼ ኪስ የመሰለ ወርቅ......በፀሐይ ግሎ ድንገት ለሲትዮዋ ጣት ቢሰፋና (እንዲህ መሆን ይችላል?) ቢሾልክ ተረጋግቶ አስፋልት ላይ ይወድቃል? ሊሆን አይችልም:: ጠፍጣፋ ቢሆን እዎ......ክብ ሆኖ ግን መንከባለል አለበት:: ወድቆ ቢንከባለል የሚገባው አስፋልቱ ምንገድ ጠርዝ እተሰራው በፍርግርግ ብረት እተዘጋው የጎርፍ ውሃ ማስገቢያ ጉድጓድ ውስጥ ነበር:: አጉንብሼ ያጋጠሙኝ ጉድጓዶች ውስጥ ማየት ጀመርኩ:: ጉድጓዶቹ ውስጣቸው ጨለማ ነው......ወረቀትና ድንጋይ ሞልቷቸዋል:: እውስጣቸው መግባት ወይም ከውጭ በረዥም እንጨት ወይም ብረት ነገር እየጉረጉርኩ ወረቀቶቹንና ድንጋዮቹን እያገላበጥኩ መፈለግ ነበረብኝ::

ያኔውኑ የስራ ጓደኛዬ ከነበረበት ወደ እኔ አቅጣጫ እየሮጠ መጣና:

"የት ጠፋህ አንተ? ተቆጣጣሪ መጥቶ አጣህ......ምን ትሰራለህ እዚህ......?"

ግንባሬን እየጠረግሁ አየሁት::

"ስማ እንጂ?"

ዝም አልኩት:: በሽቄአለሁ::

ከዚያ ቀን በሁዋላ በዚያች ጉዳና ሳልፍ በጉሪጥ በየተራ ጉድጓዶቹ ውስጥ አይ ነበር......::

ቀለበቷን መከተልና መፈለግ የወሰደብኝ ጊዜ ሁለት ሰዐቶች ያህል ሳይሆን ይቀራል?

የበግ ላት ይወድቃል ብሎ እንደተከተለ ውሻ (ቀበሮ?)::

ራሴን የማይረባ ተረት ውስጥ የዶልኩ መሰለኝ::



@BOOKALEM

# ወሉዩው ከነተረቶቹ

ሳልፍ ሳገድም አንዳንድ ጊዜ አየው ጀመር:: የአቀማመጡ ቾልተኝነትና (ባይሆንም) የዐይኖቹ ዝግተኛነት (እኚህም ባይሆኑም) ይገርመኝ ነበር:: የሚያይ አይመስልም፣ የሚያጤን አይመስልም፣ ግራ ጉንጩ ተላምጦ በማያልቅ ጫት ሁልጊዜ እንዳበጠ አየዋለሁ:: ባጋጠመኝ ቁጥር ሰዎች ሲጠሩት 'ወሉዩው' እያሉ ነው:: ብዙ ጊዜ ስለምንተያይ ተላምደን ከተገጣጠምን እጁን ለሠላምታ ያነሳልኛል:: አብዮት አደባባይ አሳዶ የለከፈኝን የረሳው ይመስላል:: የእጅ አነሳሱ ዝግተኛነት እንደ ተገደደ ሁሉ ነበር:: ሠላምታው ሳይሆን አደራረጉ ቅር ስለሚያሰኘኝ ምን አልባት ፖሊስ በመሆኔ ፈርቶ ወይም ባለፈው ጊዜ «ወማድልኝ» ስላልኩት ቂም ይዞ እንደሆነ በማለት ላላቅቀው ስለማልፈልግ ድምፅ ሳላሰማ ሳልፈው እሞክር ነበር:: ይኼ ድርጊቴ ይገባዋል መሰል ይጠራኛል:: አፉን የሞላው ጫት ታዲያ ብዙ አያናግረውም::

"ታዲያስ......" ይለኛል ድምፁን ከፍ አድርጐ::

ከዕለታት አንድ ቀን እግር ጥሎኝ በአጠገቡ ሳልፍ ስሜን ጮክ አርጎ ጠርቶ አጠገቡ መጥቼ እንድቀመጥ ጐኑ ያለውን የፈራረሰ ደረጃ በእጁ ደበደበ:: ትዕዛዝ ይመስል ነበር......ወዳጅ ወዳጅን ሲያዘው:: ስሜን ማን እንደነገረው እስከዚያን ጊዜ ግን አላውቅም:: ስሜ በእሱ አፍ ሲጠራ እንግዳ ዐይነት ቅላፄ ነበረው:: ያለቀ፣ የተፈፀመ:: ስሜን ከዚያ በላይ ማንም አጠናቆ ሊጠራው የሚችል አይመስልም::

"ምነው?" አልኩት

በእጁ ጐኑ ያለውን ሲሚንቶ እንደገና ደበደበ::

"ለምንድን ነው የምትፈልገኝ?"

አሁንም ደበደበ::

አጠገቡ ሳልቀመጥ ፊት ለፊቱ አንድ እግሬን ከፍ ያለ ደረጃ ላይ፣ ሌላ እግሬን ዝቅ ያለ ደረጃ ላይ አቁሜ ፊቱን አየሁት:: እጅግ ቀርበው ሲመለከቱት የተለየ ሰው ይመስላል:: ቆዳው ለስላሳና በወፍራም ወዝ የተሸፈነ ነበር:: አፍንጫው ትልቅ ነው:: የአንድ ዐይኑን (ግራውን?) የታችኛ ሽፋሽፍት ማርያም በትልቁ ስማዋለች::

"ጫት?" አለኝ ከጉያው በትናንሽ ሽቦ የታሰሩ የቀያይ ጫት ቾቦዎች እያሳየኝ::

"አልፈልግም......ግን ምነው ጠራኸኝ?" አልኩት::

"ስምተሃል?" አለኝ

"ምን?" አልኩት



@BOOKALEM

"ስለ እስስቶቹ?" አለኝ

"የምን እስስቶች?"

"አዲስአባ የሚወራው እሱ እኮ ነው"

"የምን እስስት? አልሰማሁም"

"ፖሊስ ነህ ምንድነህ አንተ?" አለ እየሳቀ

"ፖሊስ ሁሉን መስማት አለበት እንዴ?"

"ለማለት ሳይሆን ብዙ የተወራ ጉዳይ ካይሆን አይቀርም ብዬ ነው። አንተ የለመድኩት የፖሊስ ዐይነት አይደለህም.......የተለየህ ነህ......"

"አልሰማሁም። ምንድነው ስለ እስስቶቹ የሚወራው?"

"ተቀመጥ"

ቆሞ አልኩ።

"አዲስአባ መሬት ውስጥ ከዋናው ፖስታ ቤት ስር ሌሊት ሌሊት እስስቶች እየወጡ ይዞሩ እንደ ነበረ አልሰማህም?" አለ።

ተረት ሊያወራልኝ የጀመረ መሰለኝ።

"ምንድነው የምታወራው?"

"ተደብቋል ማለት ነው"

"አይተሃል? እስስት ደ'ሞ መሬት ውስጥ ይኖራል?"

"የተለዩ ናቸው እነዚህ"

"ምን ማለትህ ነው። አይተሃቸዋል?"

ዙሪያውን ገልመጥ ብሎ ተመለከተ። በአጠገባችን ሁለት ወጣት ሴቶች እየተሳሳቁ ያልፋሉ። አንደኛዋ ያነገተችው ቦርሳ ትንሽና የምታንፀባርቅ ነበረች (የሚያምር ቦርሳ)። ታኮአቸው እንደ ኩርኩም ይጮሃል። አራቱም እግሮቻቸው ገዳዳዎች ናቸው። ሳቃቸው እንደ ንጥኝ ይፈናጠራል።

"አይቼአቸዋለሁ"

"የት አየሃቸው?"

"ከሐራምቤ ሆቴል ጀርባ ካለው ድልድይ በሰልፍ ተያይዘው ሲወጡ"

"መቼ?" እንደ አመነ ሰው



@BOOKAlEM

"ከአንድ ወር በፊት"

"ቀን?......ሰው ነበር?"

"ማታ......እዚያ ወንዝ ዳር ካለ ሱቅ ጀርባ ሜት እቅም ነበር። ባቡር ጣቢያ ነው የማድረው አየህ። ሰዓት እኳፌ ሳይደርስ ቤቴ ለመግባት ስወጣ ድልድዩን በሰልፍ ሲያቋርጡ አየሁዋቸው"

"ዕውነትህን ነው?......እንዴት አምንሃለሁ?"

"ሀይናቸው ያበራል አቦ......በግድ እመነኝ አልልህም......እኔ ያየሁትን ነው የምነግርህ"

"መርቅነህ ያየኸውን ነው?"

"የሚገርምህ ነው.......ያኔ ካሽ አልነበረም......የሚበቃም አልቃምኩ......የሚፈለጥ ሰው ብነፋ"

"እይተህ ታዲያ ምን አደረክ?"

"ልነግርህ እኮ ነው......በመንገዱ ማለፍ ስላለብኝ ወደ እስስቶቹ ቀረብኩ:: መጀመሪያ እስስት መሆናቸውን አላወቅሁም:: ትናንሽ አዞዎች ነበር የመሰሉኝ። ፈርቼ ብጠብቅ ሰልፉ አያቋርጥም:: በሩጫ ዘልዬ ላቋርጣቸው ፈለግሁ:: ተመልሼም ጫት የሚቅሙትን ሰዎች መጥራት ፈለግሁ:: ለሰዎቹ ከነገርኩ መርቅኜ የፈጠርኩት ስለሚያደርጉት የመሰለኝን ነገር ወሰንኩ:: ከመሐል ድፍረት ተሰማኝና ወደ እነዚህ ተንቀሳቃሾች ጠጋ ብዬ ሳይ ሀይኖቻቸው እንደ ባትሪዎች ናቸው:: ትናንሽ እነዚህ በኪስ የሚያዙ የጭቃ ቀለም ባትሪዎች ታውቃለህ?......እና ልክ በሰልፍ......በተለካ ርቀት የሚሄዱ ነገሮች ናቸው:: ጠጋ አልኩና አንዱን በእግሬ መታ አደረኩት:: እየፈራሁ ነበር አየህ:: ቶሎ ነካ አድርጌ እግሬን መለስ አደረኩ። ገላቸው እንደ ብርጭቆ ወረቀት ነበር......የገፋሁዋት እንስሳ......የሆነች ትልቅ እንሽላሊት ምንም ሳታደርገኝ ቀርፋፋ ምንገዷን ቀጠለች:: ከሁዋላዋ ያለችዋን አንዷን እንደገና ካልቾዬን ጠንከር አድርጌ መታሁዋት:: ከሠልፉ ወጥታ በጀርባዋ ወደቀች። በሆዷ መመለስ አልቻለችም:: አሁን አደገኛ አለመሆናቸውን ሳውቅ የበለጠ ስለነዚህ እንስሳት ለመረዳት ፈለግሁ። ሠልፉ ከአንዱ የድልድይ ዳር ወደ ሌላው የድልድይ ዳር ከሄደ እነዚህ እንስሳት ወንዝ ውስጥ ዘለው ይገባሉ ብዬ ጠረጠርኩ:: አንድ ነገር ከድልድይ ከፍታ ወንዝ ውስጥ ወይም ውሐ ውስጥ ሲዘል ድምፅ አይሰማም? ግን ድምፅ አልነበረም። ወደ ቤቴ መሄዴን ትቼ ፍልስፍናዬን ቀጠልኩልህ። የዚህ የእንሽላሊት ሰልፍ የት እንደሚገባ ለማየት ፊት ለፊታቸው ስሔድ ይሔ ሰልፍ ወንዝ ውስጥ ከመግባት ይልቅ ድልድዩ ጠርዝ ሲደርስ



@BOOKALEM

በድልድዩ ስር በጀርባው ይታጠፋል:: ታጥፎስ?......አትለኝም? ተመልሶ በሌላ በኩል ይመጣል:: ክብ ነበር የሚሰሩት:: አይገርምም? የሚሔዱ ይመስላሉ ግን አይሔዱም:: በመጀመሪያ አንዱ ከአንዱ አይለይም:: እንደገና እነሱው ራሳቸው የማያቋርጥ ክብ ይሰራሉ......

"ከዚያ በሁዋላስ?" አልኩት::

"ከዚያ ነቃሁባቸው:: ስልህ እንደቀድሞው አልፈራሁዋቸውም:: ከዚያ ከመሐል አንዱን በደንብ በእግሬ መታሁትና ከሰልፉ አስወጣሁት:: የዚህ እስስት መጠን የአንድ እጅ መዳፍ ቢያክል ነበር:: ሠልፉ ቀጠለ:: እኔ አውሬውን በእግሬ እየመታሁና እያንከባለልኩ አምባሳደር ቲያትር ፊትለፊት ድረስ ወሰድኩት:: አንድ የቲያትር ቤቱ ዘበኛ ቆሞ ያየኝ ነበር:: ታውቀው ይሆናል:: በእግሬ ምን እንደምገፋ ጠየቀኝ:: ከነበረበት መጥቶ በእግሬ የምገፋውን እንስሳ አየና 'ይኼ እስስት ነው:: የት አገኘኸው?' አለኝ.......ነገር ለማሳጠር ብዬ 'እዚህ ድልድዩ ጋ' አልኩት:: ዞር ብለን ስናይ የሚገርምህ ድልድዩን የሚዞረው የእስስት ሰልፈኛ ጠፍቷል:: የት እንደሄደ አላውቅም......ዐይኖቼን ስላላመንኩ ወደ ድልድዩ ተመልሼ ተጠግቼ አየሁ:: የሉም:: አይገርምም? ከምኔው ሔዱ? ወደ የት ሄዱ? እስስቷን እግረኛ ምንገድ ላይ አውጥቼ ባስቀምጣት ደህና ነበር:: ዘበኛው እስስት መሆኗን አውቆ መጠበቂያው በረንዳ ላይ እንደተመለሰ አንድ ቀልቃላ መኪና በእስስቷ ላይ ይሔዳል:: ይገርምሃል:: በጣም የሚገርም ነበር አቦ......እንደ ጉማ ፈነዳች:: መኪናው የጆሮአችን ታንቡር እስኪበጠስ ድረስ ፍሬን ያዘ......የራሱ ጉማ የፈነዳበት መሰሉት:: ሾፌሩ ከወረደ በሁዋላ ጉማውን እየዞረ አይቶ ጨኸት ወደ ሰማበት ወደ ሁዋላው ተመለሰ:: በጣም የሚገርመው ነገር አሁን ነው የሚመጣው:: መኪናው በእስስቷ ላይ ሲሄድ ምን ይሆናል መሰለህ......ኩክ ታውቃለህ? ውስጡ ጠጣር የሆነ አሁን የበሰለ ኩክ ውሰድና ጨፍልቀው ፍሬው አይጨፈለቅም አየህ እናልክ እንደዚያ ልክ እስስቷን መኪናው ሲሄድባት ከውስጧ ሌላ ነፍስ ያላት እስስት ወጣች:: ከሌላዋ ሆድ የወጣችው ነገር ከመኪናው ምንገድ ተፈናጥራ ወጥታ ሽፍኖአት የነበረውን በደም የተለወሰ ቆዳና ሥጋ በጅራቷ ተሸክማ መንቀራፈፍ ጀመረች:: ይሔ አደጋ በመድረሱ ችላ ብሎ የነበረው ዘበኛ ከበረንዳው ተመልሶ በመገረም ያይ ጀመር:: ከአንድ እስስት ውስጥ ሌላ እስስት ሊወጣ አይችልም:: በፍፁም:: እስስቶች ይወልዳሉ ብትል እንኳን በደንብ ያደገ ትልቅ እስስት አይወልዱም:: ዘበኛው መራገም ጀመረ:: 'ይኼ ሰይጣን ነው......ይኼ በእስስት የተመሰለ ሰይጣን ነው......' እያለ ቆየና ለእኛም ሳይነግር ያቺን የምትላወስ ነገር ጥይት ሳለመተኩስ ብሎ በሰደፍ ከቆሙ መታት:: የሚገርም ነው......ጀርባዋ ላይ ነው የመታት......ቆዳዋ ቆም በቆም ለሁለት ተሰነጠቀ ......እንደሞተ አድርጎአት ቆመች:: ከዚያ በቀስታ መፈራገጥ



@BOOKALEM

ጀመረች......እኔ እራሴ ፈርቼ......ሁላችንም ፈርተን ልበልህ ራቅ ራቅ አልን:: ከዚያ......ጆርባዋ ተሰነጠቀ አላልኩም እና ከዚህ ከተሰነጠቀ ጆርባ......ምን የመሰለች በደምና በልፋጭ የተጨማለቀች እርጥብ እስስት ጭንቅላቷን ብቅ አታደርግ መሰለህ? አታምንም መችም አታምንም:: ማንም አያምንም:: ያወሩታል እንጂ አያምኑትም:: ልክ እንደ እንትን ገና እንደተወለደች ቡችላ ዐይኖቿን ጨፍና እየተንፋቀቀች ወጣችና ቆመች:: ከዚያ ዐይንዋ ተከፈተ:: የሚያስደነግጥ ነገር ነበራት፣ የሚያቅለሸልሽ ነገር አላት......የማያስፈራ ነገር አላት::......የእኔና የዘበኛውና የባለመኪናው አፎች በድንጋጤ ተዘግተዋል:: ከዚያ ይኼ ቀልቃላ ዘበኛ እንደገና ጨዋታ አድርጐ 'እርጉም' ብሎ በጠመንጃው ሰደፍ አይመታት መሰለህ ታዲያ ወደ ወንዙ አቅጣጫ ተፈናጠረች::......ከቲያትር ቤቱ ትንሽ ዞር ካልክ እንግዲህ ጨለማ ነበር:: ማየት አትችልም በደንብ......ተበሳጭቼ ነገሩ ሳያልቅ አልሔድም እያልኩ ከዚያ ባለመኪና ጋር ወደ ወንዝ ተጠግተን ብናይ በፍፁም ልናገኛት አልቻልንም:: በሽቅሁ በቃ:: ስመለስ ዘበኛው ሰደፉን ይጠርጋል......ቆመን ስላየነው ነገር ብዙ ብዙ አወጋንና ተለያየን:: የዚያን ቀን ይኼንን ነገር ያየነው ሦስት ነን:: ግን አሁን አዲስአባ የሰማው ይመስለኛል......አላመንከኝም?"

"ይኼ የማይታመን ነው......መርቅነሃል"

"ስለዚህ ነገር ለማረጋገጥ አራት ኪሎ ወጥቼ አንድ የዩንቨርሲቲ ተማሪ ጠየቅሁ"

"ምን አለህ? "

"አላመነኝም"

"የሚታመን አይደለም"

"እያየሁት?"

"መርቅነህ ነበር......"

ይኼ ሰውዬ የሚገርም ወሬ ቢያወራኝም ሊያሳምነኝ ስላልቻለ ተለያየን:: ግን የነገረኝ ጉድ ከሃሳቤ ሊጠፋ አልቻለም ነበር:: ለሌላ ሰው ለማውቀው እንዳላወራ 'ቁጭ በሉ' የሸወደው እንዳልባል በማለት በፍርሃት ቆየሁ:: ጥቂት ሳምንታት ያህል ከከረምኩ በሁዋላ በዚያ ሰው ወሬ የተቀሰቀሰው ህሊናዬ ተመሳሳይ ጨዋታ ርቦት ነው መሰለኝ ወሎዬው ይቀመጥበት ወደነበረበት ቦታ ሔድኩ:: እዚያ ስደርስ ግን ባጋጠመኝ ነገር ደነገጥሁ:: ወሎዬው እዚያ አካባቢ የሚቀመጥበት የሲሚንቶ ደረጃና ዙሪያ ግባው በቡልዶዘር ፈርሶ አዲስ የኢንሹራንስ ህንፃ ሊሰራበት በቆርቆሮ ታጥሮአል:: ይኼ ሁሉ ገጠመኝ ተረባርቦ አእምሮዬን በሚስጢር ሞላው:: ለመሆኑ የሰውነት ከሰውዬው ጋር



@BOOKALEM

ተነጋግሬአለሁ? ወይስ ሕልም ቅዠት ነበር?፡፡ ወሉዬውን በሰውን እዚህ ቦታ አይቼዋለሁ ወይስ ተክለሐይማኖት አልጋዬ ላይ ራዕይ ገልጠውልኝ ነበር?

ያን ቀን ነፍሴ አሳርፍ ስላለችኝ በእግሬ ወደ አምባሳደር ቲያትር ሔድኩ፡፡ ቀትር ይመስለኛል......ሲኒማ ለማየት ትኬት ለማስቆረጥ የተደረደረው ሰልፈኛ ዕርዝመቱ ሐራምቤ ሆቴል ቤንዚን ማደያ ያርሶአል፡፡ ሕዝቡ ሊያየው የሚሻማበት የፊልም አርዕስት "The other side of the mountain" የሚል ነበር፡፡ (ለመሆኑ ከተራራው ወዲያ ምን አለ? የፈረደበት ፍቅር? ወይስ እነ አልማዝን የሚቆረጥም አጋቦስ? ከተራራው ወዲያ ሌላ ተራራ አለ፡፡ ከተራራው ሌላ ጎን ያው ሌላ ተራራ ነው፡፡ በተራራዎቹም መሃል ሸጥ ነው--ጠንካራ ኤሊዎች የፈረሱበት፡፡ ከዚህም ተራራ ጀርባ ያለው ያው ሌላ ተራራ ነው፡፡ ከተራራ ወደ ተራራ፡፡ ከሸጥ ወደ ሸጥ፡፡ መንገዱ የአፋፍ፡፡ እንደ አውቶቡስ ፌርማታ፡፡ እየወረዱ ቢያዩ ያው እየወረዱ ቢያዩ ያው፡፡ ለመሆኑ ከተራራው ወዲያ ምን አለ?) ቲያትር ቤቱ አጠገብ ያለው ድልድይ ሔድኩ......ድልድዩ ድልድይ፣ ወንዙ ወንዝ......ቆሻሻው ቆሻሻ ነው፡፡ እንዲያውም ከበስተታች መናፈሻ ሊሰራ ነው መሰለኝ ቦታው እየተጠረገ ነበር፡፡ ከበስተላይ ከአሮጌ ቤቶች ጀርባ ገደሉ ደረት ላይ ቂጡን ወደ ጉዳናው አዙሮ በግራ እጁ እንደጥጥ የሚያበራ ወረቀት ይዞ ጭንቅላቱን ቀብሮ የሚፀዳዳ ሰው አድፍጦ.......

ከዚያ በሁዋላ ምናልባት አምስት ስድስቴ ይሆናል ሆን ብዬ ወሉዬውን የፈለግሁት......ጠፋ፡፡ የነገረኝ ዕውነት ቢሆን ኖሮ ሳገኘው ስለ ሞጂያን ሳወራው ነበር፡፡ ባገኘው ያለትዝብት አብሬው ስቄ ሳልፈው፣ ይቅር ለቅዝርትህ ልለው፡፡ እንዲለኝም፡፡

ጠፋ፡፡



@BOOKALEM

# ሞጀያን (2)

አንድ ግንቦት ወር ፒያሳ ከሥራ ውጭ ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ካለው አቢራማ ሜዳ በስተምሰራብ በኩል ባለው ተዳፋት በኩል ቆሜ በጠራራ ፀሐይ የተጠቀለለ ወሬ ሳይ፣ ከላይ ከአራዳው ጊዮርጊስ አንድ ወጣት ወንድና፣ አንዲት ወጣት ሴት ተቃቅፈው ወደ ታች ሲወርዱ አየሁዋቸው:: ልጁ ዚፕ የበዛው ትልቅ ቀይ ፕላስቲክ ጃኬትና ጥቁር ራንግለር ሱሪ ለብሶአል:: ልጅቷ ነጭ ሱሪና ሰማያዊ ሸሚዝ አድርጋለች:: የወንዱ ቀኝ እጅ በልጅቷ ወገብ፣ የልጅቷ ግራ እጅ በልጁ ወገብ ላይ አርፈዋል:: ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ ያወራታል:: ታላቅ ሚስጢር በማንሾካሾክ ላይ ያሉ ይመስላሉ:: በግራ እጁ ከጃኬቱ ኪስ መስቲካ አወጣና ሰጣት:: ልጁን ለቃው የመስቲካውን ሽፋን ገፋ ከጣለች በሁዋላ (ወደ ቀኝ የሚነፍሰው ንፋስ የልባሱን ወረቀት መሬት ከመንካቱ በፊት ተሸክሞ ከእኔ አስር ሜትሮች ያህል አርቆ እንደ ሞተ ቢራቢሮ ጣለው) እንደገና ተቃቀፉ:: የልጁ አካሔድ የሞጅያ ነበር::

ልጅቱ ሞጅያ መሆኑን የማታውቅ፣ ያላየች ትመስላለች:: እሱ እየተንሻፈፈ እሷ እየተንሳፈፈች እንዳለፉኝ ጃኬቱ ጀርባ ላይ በትልቁ ምላሱን ያወጣ የእስስት ስዕል አየሁ:: እስስቱ ቀይ ጃኬቱ ላይ ቦግ ብሎ የሚታይ ቢጫ ተንቀሳቃሽ:: ለማንም የሚታይ:: የእስስቱም ምላስ ወደ ወጣቱ መጋፊያ በቅልጥፍና የተዘረጋ ነበር:: የሴትዋ ጣቶች ዕቅፋቸውን ሲያጠብቁ መሰለኝ ከዚህ ሆኜ ሲነቃነቁ አያቸዋለሁ (ወይስ 'ጀርባዬን እሱ ጋ እከኪልኝ' ብሏት ነበር?)::

እግሮቹ ተንሻፈዋል:: በተረከዙ ጫፍም የቆመ ይመስላል:: ልጅቷን እንዳቀፈ፣ እሷም እንዳቀፈችው በቀስታ እየተንኳተቱ ቸርቸር ጉዳና ገቡ:: ልጅቷን ከዚያ ከቆምኩበት ሳያት ቂጠ--መልካም ትመስል ነበር (የቂጧ ክብነት ለጨዋታ እንደተነፋ ጉንጭ)::



@BOOKALEM

# ገነትና ምናብ(1)

*(ኸረ ምነው ቤቴ በጠዋት ይንኳዋኳዋል*
*የገነትዬ ፍቅር እዚህ ከደጅ ቆምአል)*

ገነትን ከዚያች የፋሲካ ዋዜማ በሁዋላ በዐይነ-ስጋ አይቻት አላውቅም:: ተመልሳ እንድትመጣ ሌላ የፋሲካ በዐል መድረስ፣ ደርሶም እሷ በኩረን ለመጋበዝ መምጣት አለባት:: አዲስ ፋሲካ ብቻ ሳይሆን በኩረ የዚያን ዕለት ከእሷ ጋር የሚኖረውን ቀጠሮ መርሳት ወይም ከቀጠሮው መዘግየት አለበት:: በኩረ የዘመዱ ቤት የት ጋ እንደሆን አስተካክሎ ስለማይናገር......ሆን ብሎ እንደሆን ይገባኛል......ሔጄ ራቅ ብዬ ከቤቷ ስትወጣና ስትገባ ላያት እንኳን አልችልም:: አጋጣሚ ሆኖ በኩረ ቢታመም፣ ቢቆስል......ስራው ላይ ዱርዬዎች ደብድበውት ሆስፒታል ገብቶ ልትጠይቀው መጥታ ወይም የዓመቱ ተከለሐይማኖት ሆኖ ወይም የሆነ የቅዱስ በዓል የዚህ ቤት ነዋሪዎች ከበኩረ ጋር አብረን ካልተጠራን፣ በፍፁም በዐይነ-ሥጋ ላያት እንደማልችል ይገባኛል::

በዐይነ-ሕሊናዬ አያታለሁ......በዐይነ-ሕሊናዬ ግን ደግሜ ደጋግሜ ብዙ ሰዎች ማሳፈር እንድችል አድርጌ አስባታለሁ (ተኩሶ ከሳተኝ የአልቤቲ ገላ፣ ከሐይለኛውና ከርብቃ ሐጢያተኛ ድርጊት፣ ከነአለማየሁ ዝርዝር የፍትወተ ሥጋ ወሬ እንዳንዴም ጫልቱ ከአንዳንድ ደምበኞችዋ ጋር ከምታደርገው የቃላት ሰላና የተቀናጣ ድሪያ የሰማሁትን ያየሁትን ልቅምቅም ስዕላዊ ወሬና ምስል ወደ ራሴ የሃሳብ ልምድ በመለወጥ ራሴንም የልምዱ ቀንደኛ ተዋናይ በማድረግ......የወደደ በተጨማሪም ለአቅመ አዳም የደረሰ እፍረተ ቢስ ነውና) እንደ መጀመሪያው ሰሞን የውስጤ እፍረት አዞኝ አልቆጥባትም:: እንደ መጀመሪያው ሰሞን በዛገ የወሰን ትውስታ አልተካትም:: ወይም የወሰን ውበት አእምሮዬ ውስጥ ትቶት ከሄደው የትዝታዋ ደለል አላወዳድራትም:: እንደማስባትና እንደምሻት ማንም አለማወቁ፣ ሚስጢርነቱ ደስታ የሚሰጥ ነበር:: በኩረ አጠገቤ ተቀምጦ ቀን ያጋጠመውን እየሳቀ ሲያወራ (እያወራ ጥርሶቹን በሐረር መፋቂያ ማጽዳት ይወዳል--ወዳጋጠመው አቅጣጫ እርጥብ ሲጋቱራ ቱፍ! እያለ) ዐይኖቼን በዐይኖቹ እያየ፣ አጠገቡ በትኩሳቴ እንደ ሸቶ የሚሰራጨውን የጉርምስና ጠረኔን እየማገ፣ ከዘመዱ ከገነት ጋር እሱ በማይፈልጋቸው ቦታዎች እዞራለሁ:: ያለመድኩት ብልግና በአንጎሌ መሰላል ላይ እየወጣ ይወርዳል:: ወሬ የማዳመጥ ችልተኛነቴን ከማግርታምነቴ ጋር ስለሚያገናኙት የማሰብ ነፃነቴ ሰፊና ምቹ ነበር......

እንደ ፋሲካው ዋዜማ ተመልሳ ስትመጣ አስባታለሁ......እቤት ማንም አይኖርም:: መንገዱም ጭር ያለ ነው:: በሩ ይንኳኳል፣ በቀስታም ይከፈትና አልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ አያታለሁ:: ግራና ቀኝ በሩን ይዛ ቆማለች.......ከበበ-ሰብአትዋ ከጀርባው



@BOOKALEM

ለስላሳ እንጆሪ የመሰለች የንጋት ፀሐይ ጋርዶ። ከንዶቿ እንደ ብርሐን ዘንጎች። አወይ ይች ንጋት። አወይ ይች ክረዳ። ሳቅ ትልና በኩረን ሳይሆን መዝገቡን እንደምትፈልግ ትነግረኛለች፣ እኔ መዝገቡ እንደሆንኩ ስነግራት......

"ለምን ጠፋህ የእኔ ፍቅር" ትለኛለች......

ባለፍስሐ እኔ።

እኔም ብቻ ሳልሆን አሊጋዬ ሊበር የአቡጀዲ አንሶላዎቼን እንደ ክንፍ ያራግፋል......

ሀይኖቼን እከድናቸዋለሁ......

የልቤ ምት......

የልቤ ምት የጉን አጥንቶቼን ይገጫል......

ጉን አጥንቶቼ ብርድ ልብሱን ይመታሉ......

ብርድልብሱ አየር ይገፋል

አየሩ የቤቱን ጣሪያ ያነሳል......

እጆቿ ደረቴ ላይ ሲያርፉ......

ልቤ ከዕብደቷ በርዳ በቀስታ እንደ ድመት ታንከራፋለች......ፊቷም......ያቺ የፀሐይ እህት።

ከንፈሮቿ የተከፈሉ ትርንጉዎች ናቸው......

ከአፏም ውስጥ የቀለጠ ዘቢብ ወደ አፌ ይወርዳል......

በሆዴ ውስጥ ትልቅ የወይን እርሻ እንዳረዘች አንሾካሻካ ትነግረኛለች......

የላይና የታች ጥርሶቿን ያያያዙትን የምራቅ ዘሀዎች በምላሴ መቀስ እቆርጣለሁ......



@BOOKALEM

# ኒንጃና ጫልቱ

የሆነ ዕለት ማታ ራቴን በልቼ ቤቴ ልገባ ስል ከበሩ ራቅ ብሎ መጀመሪያ ቀን ያየሁበት ቦታ ኒንጃ ቆሞ አየሁት:: ጣቶቹን እያሻሸ ወደ እኔ ተጠጋ:: እሱ መሆኑን ሳላውቅ በፊት መንታፊ መስሎኝ ነበር::

"ጋሼ መዝገቡ?"

"ኒንጃ ነህ?"

"አዎ......"

"ጋሼ የምትለኝ ከመቼ ወዲህ ነው......ምን ትሰራለህ በጨለማ?"

"ጫልቱ ቤት ስመጣ......ጫልቱ ቤት መግባት አልቻልኩም:: ሙሉ ቀን አልበላሁም"

"ና አላልኩህም?"

ትከሻው ላይ አቅፌው በቀስታ መሔድ ጀመርን:: ከወዲያ በኩል የሚመጣ ደካማ የጎዳና ብርሐን ፊታችን ላይ ይበራል......ዐይኖቹ ዕንባ እንዳቀረሩ አየሁ::

"ጫልቱ አታስገባኝም"

"ምን አገባት:: ጫልቱ ጥሩ ሴት ናት:: በል አሁን እንሂድና እራትህን ትበላለህ"

የእጆቹን ጣቶች ያጠላልፋቸዋል፣ ይፈታቸዋል.......እፉ አሞድሙዶአል......ጭንቅላቱን ከንዴ ላይ አስደገፈ:: እንደ ደከመው ገብቶኛል::

"ሲርብህ ዝም ትላለህ?"

"እስከ አሁን ፖሊሶች እየፈለጉኝ ነው"

"የቶቹ ፖሊሶች......ቆይ እኔ አስቦካልሃለሁ"

ደስ ያለው መሰለኝ::

በዚያ በሚበርድ ምሽት ውስጥ ገላው ይሞቃል::

ተያይዘን ወደ ጫልቱ ቤት ሄድን:: ኒንጃ ላለመግባት ፈርቶ ቆመ:: ግራ ገባኝ::

"የሆነ ነገር አድርገሃታል?"

"ምንም" አለኝ



@BOOKALEM

እኔ ስገባ እውጭ ቀረ:: ሜልቱ ተመልሼ ስመጣ ስላየችኝ ገሪማትና ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ውጭ አየች::

"ይኼ ነው እንዴ?" አለች:: የታመመ እና ድሮ ታሞ አይታው እንደነበር ውሻ......በሚዘቅጥ ድምፅ ስትጠቅሰው ይሰማኛል::

ልጁ ጨለማ ውስጥ ሲጠቁር አየዋለሁ:: እግሮቹ አያርፉም:: ሊሮጥ የሚዘጋጅ መሰለ:: ሮጠ:: በጣም ይሮጣል:: አይታይም:: ተናደድኩ::

"ምን አደረገሽ?" አልኳት ሜልቱን

"አንተ እኩያህ ነው? ምንህ ነው? ሰው ሠላም ከነሳ ዱርዬ ጋር"

"እሱ የእኔ ጉዳይ ነው......ርቦታል ልጁ:: ራት እንዲበላ ነው ያመጣሁት:: አንቺን ምን አድርጉሻል"

"እኔን? እኔን ምን ያደርገኛል......ቢያደርገኝ እለቀዋለሁ:: ለሁለት ነበር በአለት የምከፍለው"

"ልጅ እኮ ነው"

"ልጅ? ከቴም ልጅ......የት ታውቀዋለህ?"

"ለምን አትነግሪኝም......ያደረገሽን?"

"ምን ያደርግልሃል?"

"ይብላበታ ልጁ:: ደክሞት ወድቆ አውሬ ቢበላውስ?"

"የራሱ ጉዳይ"

"እንዴት እንዲህ ትያለሽ? ጥሩ ልጅ አይደለሽም"

"ተወኝ አትሸንግለኝ"

"መሸንገሌ አይደለም......"

"አባቱ አያበላውም?"

"አባቱን ታውቂዋለሽ?"

"አባቱን የማያውቅ አረቄና ጠላ ሻጭ ፈልገህ አግኝ"

"ጉዳይሽ ከአባቱ ነው ከእሱ ነው?"

"ምን አገባህ አንተ......እሱ እዚህች ቤት አይደርሳትም"

"ማን?"



@BOOKALEM

"ሁሉም:: አባቱም እሱም"

"የሰውነቱን ለምን አትነግሪኝም?"

"ሁሉም ሌቦች ናቸው"

"ማን ምን ሰረቀሽ?"

"አባቱ ዱቤ ጠጥቶ ሳይከፍል......ይኼም የዶሮ ሌባ ነው......አንተ ደ'ሞ ሌቦች ትደግፋለህ?"

"ስለሰውዬው አላውቅም፣ የማውቀው ስለ ልጁ ነው"

"ያው ነው"

"ተይ እባክሽ......አንቺን አንቺን አትመስይም:: እሺ እራት እሰሪልኝ"

"ራትህን አልበላህም?"

"ርቦኛል......አይበቃኝም ሌሊት ሌሊት ይርበኛል"

"ለልጁ ነው አይደለም?"

"ብቻ እሰሪልኝ"

"መጀመሪያ የተረፈ ሳህን እንዳለኝ ልይ:: ሰዎች ሰሃኑን ሁሉ ወስደው ጨርሰውታል"

"ቢጨርሱም ባይጨርሱም ራቴን ይዤ መሔድ አለብኝ"

ወደ ጓዳዋ ገባች::

"ተቀመጥ......ምነው ዛሬ አፍ ለቀቀብህ" አለች::

ብዙ እንደተናገርኩ ትዝ አለኝ:: በከፊል አፈርኩ:: ግን ብዙ ፋራዎች በአፍ ሊብለጠለጡብን ይችላሉ:: የፈለገው ቢሆን ግን የአሥር ዓመት ልጅ ጠሙን አያድርም:: ሰይጣን እንኳን የሚበላው ቢያጣ ጅራቱን ቆርጦ ጠብሶ አብልቶ የሚያሳድረው ነው::

በጉድጓዳ ሳህን እንጀራውን ይዛ መጣች:: ተቀበልኳትና 'ደህና እደሪ' ብዬአት ወጣሁ:: ወደ ቤቴ መታጠፊያ ምንገድ ላይ ኒንጃ ቆሟል:: ሳንቲሞች ከኪሴ አውጥቼ ሲጃራ ገዝቶልኝ እንዲመጣ ሰጠሁት::

"ምን ዐይነት ላምጣ?"

"ኒያላ"



@BOOKALEM

ሳህኑን ይዤ ቤት ስገባ አለማየሁና ጃፓን አልጋ ላይ ተጋድመው ያወራሉ:: ሳህኑን ሲያይ ጃፓን በርግጎ ተነሳ::

"አንተ ሊርበኝ ጀምሮ ነበር......እስቲ ሚልቱዬን እንይላት"

"አይቻልም" አልኩት::

የቃሌ አራቂነት ይሁን የድምፄ ጉላት እንበረበት መለሰው:: አለማየሁና ጃፓን ሲተያዩ በዐይኔ ቂጥ አያለሁ::

"ከመቸ ወዲህ ስስት ጀመርክ?" አለ አለማየሁ

"ስስት አይደለም......" ብዬ ጠረጴዛ ላይ ሰሃኑን እያስቀመጥሁ: "የራበው ልጅ አለ እዚህ.....እባክህ......"

"አ......ተስፋ ድርጅት ሆንሽ እንዴ?"

"አትቀልድ እባክህ......"

እጄ ሳያርፍ ሳህኑን ከፈትኩት:: እንጀራውን ገልጩ ወደ ውስጥ አየሁ:: ወጧ በጣም ትንሽ ናት:: ቀይ ትልቅ የበግ በጠጥ ትመስላለች:: ወጧ ጉን የሻገተ ጥርስ የምትመስል የተቀቀለች የአልጫ ጉመን ተጉልታለች:: ጫልቱ ባለጌ ናት:: ሰዎች ከዚህ ዓይነት ክፋት ምን እንደሚተርፋቸው አላውቅም:: ደስ የሚል የቀን ሕልም ስናስብ እንውልና ላም አለች በሰማይ ወተት ያጋተች......ስታዝረበርበው እኔ ዘንድ ሳይደርስ በደመናዎች እየተመጠጠ......በቁመታቸው በሚበልጡን ሰዎች እየተጠጣ ቢቀር እንኳዋን ወይ መዝለል ተስኖኝ የእሱን ጣዕም እያለምኩ እዚህ ስደርስ......ሳህኑን በንዴት ከድኜ አልጋዬ ላይ ተጋደምኩ:: ዕንቅልፍ እንዲወስደኝ ፈለግሁ::

ልጁ ሲጃራውን ይዞ ገባ::

"ጋሼ መዝገቡ ሲጋራው ይኼውና"

"የማን ሲጋራ ነው?" አለ ጃፓን

ከልጁ ተቀበልኩና ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠ ላይተር ወስጄ ለኩስኩ:: ጭሱ ጉሮሮዬን እየሰነጠቀ ወረደ:: ሳልኩ::

"ሲጋራ ማጤስ ጀመርክ?" አለ አለማየሁ በመገረም

"ድሮም አጨሳለሁ፣ ትንሽ ጊዜ ትቼ ነው" አልኩት::

"መቼ ድሮ? ጡት ስትጠባ?"

"ቁጭ በል እዚህ ጣውላው ላይ እና ብላ......" አልኩት ኒንጃን::



@BOOKALEM

እየተቅለሰለሰ ሳህኑን ይዞ መሬት ተቀመጠ:: ሳየው አልፈለኩም::

ልጁ በፀጥታ መብላት ጀመረ:: የአለማየሁ አልጋ ጥላ በከፊል ገፁን ሸፍኖታል:: ሲያላምጥ ድምፅ ይሰማል:: እግሩን ግራና ቀኝ አንፈራጧል:: ነጩ ሳህን ከእግሮቹ መሃል ነበር:: ቀና ብሎ ለሰኮንዶች ደስታ በከፈታቸው ዓይኖቹ ሲያየኝ የልጅነት ፊቴን የተመለከትኩት መሰለኝ:: ጠይም ፊቱ ጉድፍ በሰረሰሩ ነጫጭ የሰንባ ሰንበሮች የተሞላ ነበር:: ሊጠርጋቸው ደክሞ? ሳያፍርባቸው? ከተጋደምኩበት የሲጃራ ጢስ እንደሚቀረና ጉም ይነሣል:: ጉቤ ትዝ አለኝ:: ሌላ መዝገቡ አልጋዬ ጉን በደረቀ ዕፍታ ነፍሱን ሲያድን.......

በኩረ በር ከፍቶ ገባ:: እያጨበጨበ:: ምን እንዳስጨበጨበው አላወቅሁም::

"ታዲያስ ሠራዊቱ......እንደምን አለ......?" አለ

አለማየሁ ሠላምታ አጉረመረመ::

"መዝገቡ ጫልቱን ምን አደረካት?" አለ በኩረ::

ቀና ብዬ አየሁት::

"ምን አደረጋት?" አለ ጃጋን::

"ትበሽቃለች:: 'ፖሊስ ሆኖ ከሌባ ጋር አሜረብኝ' ትላለች"

"የምን ሌባ?" አለ ጃጋን

"ዝም ብላ ነው" አልኩት::

"ይኼ ጎረምሳ ማነው?" አለ በኩረ እየተቀመጠ:: ጎረምሳ?

ምን መናገር እንደፈለገ ይገባኛል::

"ይኼ እንግዳ ጎረምሳ በሠላም መኖር የሚፈልግ ነው" አልኩት::

"ሲጋራ ከመቼ ወዲህ ነው ማጤስ የጀመርከው?" አለ በኩረ::

"ምን አገባህ?" አልኩት::

"አ አ" አለ በኩረ በማሽሙዋጠጥ::

ልጁ እንጀራውን ጨርሶ ተቀምጦአል:: የአለማየሁን አልጋ ተደግፎ ያንቀላፋል:: ያሳዝናል:: ግራና ቀኝ ከራራይሶ እንደሚሰሩ አሮጊት እጆቹን ዘርግቷል:: ከተጋደምኩበት ተነስቼ አልጋዬ ጉን ጨርቅ ጉዘጉዝኩና ቀሰቀስኩት:: የዞረበት ይመስላል:: ሳህኑን አንስቼ እጁን (በልቶበት ያልታጠበ) እየጎተትኩ ወሰድኩና ወደ



@BOOKALEM

መሬት መራሁት:: ድምጹን ሳያሰማ ተጠቅሎ ተኛ:: እኔ ከምጠቀምባቸው ሁለት ብርድልብሶች ከአልጋዬ ላይ አንዱን ገፍፌ ደረብኩለት::

"ይኼን ልጅ በደንብ ታውቀዋለህ?" አለኝ በኩረ::

"ወንድሜ ነው" አልኩት

"ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ" አለ በኩረ በማሾፍ

በኩረ ልብሱን ማውለቅ ጀመረ::

አለማየሁ ቆሞ እየተንጠራራ ያዛጋል::

እኔ ሲጃራውን ጠረጴዛው ጠርዝ ላይ ተረኮስኩ::

በኩረ እየበሸቀ፣ እየጮኸ ቡሿን አንስቶ ወደ ውጭ ወረወራት

"ምንድነው? በዚህ ጠባብ ቤት ተጤሰበት፣ አመድ ተተርኩሶበት፣ ሌባ አድሮበት.......እንዴት እንችላለን......ጫልቱ ደ'ሞ ሳህኔን ቶሎ መልስልኝ ብልሃለች"

አሁን ቆምኩ:: ካጐነበስኩበት ቆምኩ::

ትክ ብዬ አየሁት:: አለማየሁ ሁለታችንን እየለዋወጠ ሀየን:: ተነቃነቅሁ:: ሐሳቤ በኩረን ለመምታት ነበር::

አለማየሁ ተናገረ:

"መዝገቡ ተኛ......መሸቷል......በጣም"

ከበኩረ ፊት ላይ በፍርሃት የተበረዘች ፌዝ እንደ አቧራ ስትነሳ አየሁ.......ለጥቂት--ለሰከንዶች::



@BOOKALEM

# ሞጆያን (3)

አንድ እሁድ ጠዋት ብሔራዊ ቲያትር አጠገብ ያለው አንበሳ ሐውልት ስር ቆሜ ፀሐይ እሞቃለሁ:: እየሞቅሁ እያለሁ የብስክሌት ውድድር ይደረጋል ተብሎ ተፎካካሪዎች በተከለለላቸው አስፋልቶች ዙሪያ ሰውነታቸውን ለማሟሟቅ ብስኪሌቶቻቸውን በቀስታ ያሽከረክራሉ:: በአጠገቤ ብሔራዊ ቲያትር የጠዋት የሕፃናት ሲኒማ ለማየት የሚገቡ ወላጆች በረንዳው ላይ መአት ውሪ ያንጫጫሉ:: ከአንበሳ ቡና ቤት ይመስለኛል የዕንቁላል ጥብስ፣ የትኩስ ዳቦ ሽታ እቆምኩበት ድረስ እየተሳበ ይመጣል::

የአዲስአባ ንጋት ዘለለት እንደዚህ ናት......በጉራ፣ በታላቅነት፣ በማን አለብኝነት፣ ትጀምርና የነፋችው ደረቷ እየቀለለ፣ እያነሰ፣ እየጠበበ ሲመሽ አጥንቷ ይቀራል:: የአዲስአባ አጀማመሯ ሁልጊዜ ገናናነት ሰብካ ነው......ትልቅ ሐውልት ነኝ ብላ ነው:: ሲመሽ፣ ድንግዝግዝ ሲል ግን ትፈራርስና ጭሪ የማትገል፣ ጨረባ የማትነድፍ ጅል የወረወራት ትንሽ ጠጠር ትሆናለች:: የአዲስአባ ጠዋት ስትጀምር በትልቅ ጡት ነው፣ ወተቷን እንደ አራስ እያዝረበረበች ነው፣ እንደማር የሚላስ ፀሐይ አሳይታ ነው፣ ሲመሽ ግን ጀንዲ፣ ሲጨልም ግን መንጉል ትሆናለች:: ድንቅነቷ ፈርሳ አትፈርስምና ተመልሶ ሲነጋ ያው ጉራዋ ዞሮ ይመጣል:: ያ የለመድኩት ክብ:: ታዲያ ሁሌ ሆሞቴ እንደፈሰሰ ነው:: ቢሆንም ቆሜአለሁ:: የሕፃናት ጫጫታ እያየሁ፣ የወላጆች ፍቅር እያየሁ፣ ያቺን ጠዋት እያየሁ፣ የእንቁላል ጥብስ እያሸተትኩ::

ከላይ በኩል፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ወደ እኔ አቅጣጫ ቀድሞ ከስንት ወራት በፊት አይቸው የነበረ አንድ ሞጆያ ሲመጣ አየሁት:: ልጁ አሁንም ዚፕ የበዛበት ትልቅ ጃኬት ለብሷል (በኩንትሮባንድ የሚመጡ ጃኬቶች መሆናቸውን ስምቻለሁ በሁዋላ) ጥቁር ጅንስ ሱሪ ለብሶአል:: ልጅቷም ሰማያዊ ሸሚዝና ነጭ ሱሪ ለብሳለች:: አሁን የቆምኩት ብሔራዊ ትያትር ዘንድ መሆኔ እንጂ ቀድሞ ፒያሳ እንዳየሁዋቸው ነበሩ:: ቀን ያላለፈ ዓይነት:: ወይም የመጀመሪያው ቀን ይሆንና እኔ በፍጥነት ከፒያሳ እዚህ ወርጄ የምጠብቃቸው ይመስላል::

ልጁ ከኪሱ አንድ ነገር አወጣና ሰጣት:: ተቀብላ በአፏ አስገባች:: እየተሳሳቁ ተቃቀፉ:: ዐይኖቼን ወደ ታች ወርወር አደረኩ:: ልጁ አሁንም እንደተንሻፈፈ ነው:: በዚህ ዐይነት አካሄድና እግሮች እንዴት ብዙ እርቀት እንደሚጓዝ አይገባኝም:: ልጅቷን



@BOOKALEM

እየሁዋት፡፡ እሷም እንደ ወዳጇ እግሯን ተሰርታ ሽፋፋ ሆናለች፡፡ ደንግጬ ፊቴን ወደ እንበሳው አዞርኩ.......

እንግዲህ የአዲስአባ ጡት ከአሁኑ መንጠፍ ጀመረ አልኩ ለራሴ፡፡

ያውም ገና ሳይቀትር፡፡



@BOOKALEM

# ገነትና ምናብ(2)

*(ሀይን ያወጣ ፍቅር በአንጀቴ ሰንቄ
ምን ታደርጊዋለሽ አልኖር ተደብቄ)*

"ጎኔ ሆይ! ለምን ወጥተን ጨረቃ ስትወጣ አናይም?" እላታለሁ:: እሷ ጎኔ መጥታ ትጋደማለች......ባለ አበባ ቀሚሷ ከአልጋው ተርፎ......ወለል ላይ......ከወለል ተርፎ......ቤቱን ሞልቶ......ከቤቱ ተርፎ ወጥቶ ምንገድ ላይ......ከምንገድ ተርፎ አዲስአባን በሚሞቅ ጠረኑ......በሰንደል ጠረኑ ይከደንባታል.......በደከሙ እጆቼ እሰበስብላታለሁ......በአደይ የተንቆጠቆጠ ቀሚሷንም ወደ ሰማይ እየዘረጋሁ እራግፈዋለሁ......ሰዎችም ይላሉ:

"እነዚህ የሚረግፉብን አበቦች ከየት መጡ? ያቺስ ልጅ ሸንቧ የተራቆተው፣ ደረቷ ላይ ፀጉሯ የሚፈሰው ማንናት?......ያ ጠይም ልጅስ ከብርቱካን ጡቶቿ ጫፍ ላይ ያለውን ቋጠሮ ስለምን ለራሱ ብቻ ይበላዋል?......እንዴትስ ሆኖ ነው ከተከፈተው አፏ ለጋ ሾላ የሚሸተን?......."



@BOOKALEM

# የምሽት ሰላምታ እስኪ ነጋ አይደረሳም

ከአራት መልስ አንድ ሰዓት አካባቢ አልጋዎቻችን ላይ ተቀምጠን እኔ፣ ጃፓን፣ ነጋሳ በተለይ የነጋሳ የቀን ውሎው የሚያስቅ ሆኖ ስናወካ አለማየሁና በኩረ ተያይዘው ገቡ:: በኩረ ሲያየኝ የተናደደ ይመስል ነበር:: በ'ኒንጃ' ምክንያት አኩርፎ ቆይቶ መስሎኝ ነበር:: ኩርፊያ የሚቆይበት ሰው አለ:: ቁጣው ረግቶ ቂም የሚሞቅበት አለ:: አልተከፋሁም:: ቂም ያልያዘ፣ የማይይዝ፣ ያልረጋበት፣ ያልተጋገረበት፣ ፊቱ ላይ እንደ ላብ የማይወጣበት ማን አለ?

"ታዲያስ መዝገቡ......ዝም እያልሽ ለካ......" አለ አለማየሁ

"ተውት እባክህ ይቀባጥራል" አለ በኩረ ፊቴን ሳያይ

"ምን?" አለ ነጋሳ

"ሰው ሠላም ብሎሃል" አለ አለማየሁ ወደ እኔ እያየ እየሳቀ::

"የምን ሰው?"

"ገነት......ገነት የበኩረ ዘመድ ሠላም ብላሃለች......ምን አድርገህላት ነው እ?" አለ አለማየሁ::

"አላለችውም" አለ በኩረ::

"እንዴ ተው እንጂ......ሠላም ብቻ አይደለም ምን አለች መሰለህ......" እየተሽኮረመመ......ልክ ራሱን እንደ ሴት አድርጎ: "......ያ ማነው ቆንጆዬ ልጅ......መዝገቡን ሠላም በሉልኝ" አለ አለማየሁ::

"ሆሆ......ቆንጆ ተባለ" አለ ነጋሳ::

ልቤ ስትቆም እሰማታለሁ:: ቆም አለች:: ከዚያ በፍጥነት እንደ ሰረገላ......ድምጿ በደም ስሬ ችክ......ችክ......ችክ......ችክ......ተመልሳ መጣች:: እነ አለማየሁ ሲገቡ ከፍተው የተዉት በር የሰፋ መሰለኝ:: ከዚያም ቀዳዳ አዲስ ወርደ–ሰፊ ብርሃን የተወለደ.......አንጎሌ ፌሽታ ላይ ነበረ:: ፊቴን ብርድ ልብሴ ውስጥ ቀብሬ በሳቅ መታመም መጣብኝ.......የበኩረ እንቅፋታም ፊት ነፍሴ በመጣላት የውጋጋን መደብ ላይ ጥላሸት የተነከረ ማሰሮ.......ሀሊናዬ ወደ ተረበሸ ትርጉሙ ወደ ማይገባኝ ለዐይኖቼ የሚጣፍጥ መስከ ላይ ተሰደደ:: የደጋ መስክ:: ቀላል ዝናብ አልፎበት የሄደ.......እንደ ሰላሌ በሳር ሐመልማል የነደደ:: በዚያች ግልገል አሀጉር እኔና ገነት ነበርን:: እሷ



@BOOKALEM

ቄጤማ መሃል እንደ ቄጤማ:: የሚፈልቅ ወንዝ ሜዳው ላይ እንደ ብር ድግ እርፎአል.......ሰማይ በማትታየኝ ፀሐይ የፈካ ነበር.......

ፈቴን ብርድ ልብሴ ላይ ደፍቼ በደስታ መቁሰል መጣብኝ::

ገነት እንደ ተጋደምኩ ተመልሳ መጣች.......

ዕንቅልፍ በዐይኖቼ ሳይዞር ሳስባት አደርኩ......

ጠዋት ከአልጋዬ ዐይኖቼ አብጠው ሲነሱ ስሟ ግን ጆሮዬ ውስጥ እንደ ሙጫ::



@BOOKALEM

# ምንገዶች፡ ትንንሾችም ትልልቆችም

በቸርቸር ጀግና ምንገድ ጠዋት ቀዝቃዛ ንፋስ፣ ቀትር የሞቀ ንፋስ ሲመሽ ተመልሶ ቀዝቃዛ ንፋስ ቁልቁለቱን ይወርዳል:: እኛም ፖሊሶች እንደ ቅጠልና አቧራ የዚህን ጉርፍ አቅጣጫ ተከትለን እንወጣለን፣ እንወርዳለን:: ከዚህ ቦታ እንደምቀየር ሀሳብ እንዳለ ቢወራም የነካኝ ግን አልነበረም:: ነጋ መሸ እንዲህ ስንሸራሸር በዐይኖቼ ከሚሰለሉት ነገሮች አንደኛው ሴቶች ሆነዋል:: በፊት እንደተለየ ፍጡር የማይታዩኝ ከመንገደኛ ጉርፍ መሐል፣ ከሰልፉ ከትርምሱ መሐል በብሌኖቼ አውጥቼ እገመግማቸው ጀመርኩ:: በፊት የባልና የሚስት ልዩነት የማይታየኝ ያን ሰሞን ጐን ለጐን የሚሔዱ ወንድና ሴት ሲያጋጥሙኝ ዐይኖቼ ለሴቷ ያደሉና ከወንዱ ጐን ይወስዱዋታል:: አካሔዷን ያያሉ፣ የፀጉሯን ነገር ያያሉ፣ የፊቷን ቅርጥና አቀማመጥ፣ የዐይኖቿን አገላለጥ ያያሉ:: የከንፈሮቿን አሰራር የጆሮዎቿን ነገር ያጤናሉ:: ዐይኖቼ በርቀት ሲሸነፉ ወይም አብጠልጥለው ጨርሰው ሴቷን በጥቂት ቃላት መጥነው ሲያበቁ ወደ ሌላ ይዞራሉ:: ይጥሏትና፣ ከባሏ ጐን ይመልሷትና ለሌላ ስለላ ይዞራሉ::

ዐይኖቼ ተራቡ፣

ዐይኖቼ በጣም ተራቡ::

አብጠልጥለው ጨርሰው ሴቷን በጥቂት ቃላት......ቆንጆ ፊት፣ ሸፋፋ፣ በርጫም፣ ቂጣም በመሳሰሉ ቃላት መጥኜ በህሊናዬ ሳሎን እንደ ህልም ቅሬታ የምትንሳፈፈውን የገነት ምስል (ቀድሞ በረንዳ ላይ ነበር የተቀመጠችው፣ ዣንጥላ ቅድ ቀሚሷን ለብሳ የምመኘላትን ድንግልና ግንባሯ ላይ እንደ ንቅሳት አስፍራ) አውጥቼ ለውድድር አቆማታለሁ:: በሙሉ ሴቶች ይወድቁ ነበር:: በሙሉ::

ዘፍ::

ዐይኖቼ መራባቸውን ቀጠሉ:: ግን ያስገቡትን እየተፉ:: የአዲስአባ ጐዳናዎች ሁልጊዜም የሴት ድግስ ናቸው:: ግን ሁሉ ወጥ አያምርም:: ሁሉ ክትፎ አያምርም:: ዳቦዎች ሁሉ አንድ አይደሉም:: (ሌላም ቀውስ ነበረብኝ:: እኔ በዐይኖቼ ያልወደድኳትን ሌላ ከእኔ ያማረ፣ የተሻለ የመሰለ እንዴት ወደዳት? በዐይኖቼ እያየሁ መሸበር የሰውን ገላ እንዳጠና ገፋፋኝ:: አልፎ አልፎም ወደ አለፈው በትውስት ተመልሼ በሃሳቤ በመከለስ (8) (እዚችው በዚችው)) ቆማ ወይም ልደርስባት በምችል ፍጥነት የምትራመድ ከጀርባዋ የማያት ሴት ደስ ካለችኝ ወደ ፊቷ የሚጐትተኝ ነገር ይፈጠርና እጠጋታለሁ:: ቆቤን ወደ ፊት ደፋ አድርጌ 'ሳሳስበላ' ገጿን አጠናዋለሁ:: ቻል ያለች



@BOOKALEM

ሴት በየዋሕነት ፊቷን ለግምገማዬ ትከፍታለች (ፊት አይደበቅ መቸም)። ማተኩሬ፣ ማፍጠጤ ሠላም የነሳት ደሞ ፊቷን ታዞራለች። አንዳንዷ ሴት ለራስዋ ታጉረመርማለች። አንዳንዷ የተፈለገች የመሰላት የመጠበሻ መግቢያ ልትከፍትልኝ ለማስመሰል ትሽኮረመማለች......ዐይኖቿን ወደ ጎን ጣል አድርጋ ቁመቴን በሻፈዱ ዐይኖቿ እየለካች። የቸርቸር ጀግና ምንገድ የንፋስ መውጫ ጉብታ ሆነ።

አልሸሹም ዞር አሉ።



@BOOKALEM

# በተሰቀሰው

የቤታችን ግድግዳዎች ላይ ብዙ ለጌጥ የተሰቀሉ ነገሮች አልነበሩም። ከሩዋሪዎቹ ብዛት እንጻር (*በአርታኢው ምክር የገባ ቃል። ደራሲው የሚሸሸው) በእያንዳንዱ አልጋ ራስጌና ጐን ባሉት ግድግዳዎች ላይ ሁለትና ሦስት ሚስማሮች ተተክለው፣ ምስማሮቹ ላይ ልብሶች ይሰቀላሉ። በሩ አጠገብ በስተቀኝ አለማየሁ የገዛው የፊት መመልከቻ መስታወት ነበር። በአለማየሁ በኩል ያለው ግድግዳ ከፊሉ በዘፋኞች ፎቶ ተሸፍኖአል......ቦብ ማርሌ፣ ኤልቪስ፣ ሬይ ቻርለስ፣ ጀምስ ብራውን፣ ማይክል ጃክሰን፣ ሙሐመድ አህመድ፣ ፀሐዬ ዮሐንስ፣ ሒሩት......ብዙ ብዙ። ነጋሳ ግድግዳ ላይ እሱ ራሱ ከካሌንደር ቀዶ ያወጣው የአምበን ራስ ሆቴል የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ የኢትዮጵያ ተራሮች ላይ የምትወጣ የጠዋት ፀሐይ የምትታይበት ከኢትዮጵያ የቱሪዝም ድርጅት የተገኘ (የተገዛ) ፖስተርና በትንሽ ሚስማር ላይ የተሰቀለ የእናቱ ፎቶ ግራፍ ያለበት መስታወት ነበሩ። እናቱ ኩስተር ያሉ ሴት ይመስላሉ። የሻሻቸው አስተሳሰር ይሁን ወይ ፀጉረ-ረዥም ሆነው አላውቅም.......የሾጣጣ ጭንቅላታቸው ሩብ በካሜራው አልተገኘም። ጃፓን ግድግዳ ላይ ቅል፣ በቆሉ እሸትና የሆነ ሐረግ የመሰለ ጠመዝማዛ-ብርማ ሽቦ ተሰቅሎአል። ይኼ ሽቦ ከሩቅ ሲያዩት ገመድ ስለሚመስል ነው መሰለኝ በር በተከፈተ ቁጥር እንደ ክር የሚወዛወዝ እየመሰለኝ አፈጥበት ነበር። ከጃፓን ገፅ ጋር የሚመሳሰልብኝ ግን ቅሉ ነበር። ቅል ሳይ ትዝ የሚለኝ ጃፓን ነበር።

ዛሬም......

በኩረ ግድግዳ ላይ ግን ምንም አልነበረም። ለብዙ ጊዜ ምንም አልነበረም። ከዕለታት አንድ ቀን ትልቅ ፖስተር ይዞ መጣና እዚያች ግድግዳ ላይ እንዴት መስቀል፣ መለጠፍ፣ ማንጠልጠል፣ መቸከል እንዳለበት አወራ። ስዕሉ የሚያሳየው የሆነች ትንሽ ጉብታ ላይ የተሰቀለውን ክርስቶስን ነው። ስዕሉ የሚያስፈራ ቢመስልም የሚያምር ነገር ነበረው። ብዙ ጥቁር፣ ቡናማ፣ ቀይ ይበዛዋል......የተሰቀለው ክርስቶስ ዙሪያ መጠነኛ ብርሐን አለ። በግራውና በቀኙ አብረውት የተሰቀሉትን ማጅራት መቺዎች በጥንቃቄ ካልተመለከቱ የሚታዩ አይደሉም። በኩረ ግን ቢያንስ የአንደኛው ወንበዴ ጭንቅላት ይታየኛል ይላል። ስዕሉ ስር......"መንገድና ሕይወት እኔ ነኝ" የሚል መፈክር በትልቁ ተፅፎአል። በኩረ እንዳወራው ከሆነ ቃለ ሕይወት የተባለ ድርጅት ያሳተመው ነው።

ለእኔ የሚገርመኝ የጌጥ አመራረጣቸው ነበር። ጃፓን ቅል ሲመርጥ በቆሉ እሸት ሲመርጥ በኩረ ደ'ሞ ክርስቶስን። ያኔ ቀጭ ብዬ የተንጠለጠሉትን ነገሮች በየተራ ሳይ



@BOOKALEM

ይገርመኛል:: አንዳንዴ ጃጋን ቅሷን በጣቶቹ እየመታ ግራ ቀኝ ሲያወዛውዛት (በገመድ ነው የተንጠለጠለችው) ነፍስ ያለው ነገር ትመስላለች:: ለምሳሌ የበሬ ቆለጥ::

በእኔ በኩል ያለው ግድግዳ ላይ ግን ባዶ:: ያቺ የአበበ ቢቂላ ፎቶ ከንፋስ መውጪያ ጀምሮ ይገፉአት ብዞርም ከሳጥኔ አትወጣም:: አልፎ አልፎ ልብስ ሳስገባ ሳወጣ .የተወሸቀችበትን ስለማውቅ ወደ ጀርባዬ ሰው ሰልዬ በፈጠነ ፍቅር እያታለሁ:: ግድግዳ ላይ አደባባይ ያላወጣሁዋት የምሸሚጠጥ መሰሉኝ ነበር:: አዲስአባ አበበ ቢቂላን ከልብ የምትወደው ስለማይመስለኝ:: ለምሳሌ «ቸርችር ጐዳና» የሚባል አለ:: «አበበ ቢቂላ ጐዳና» የሚባል የለም:: «ሰድገት በሕብረት ጎዳና» የሚባል አለ «አበበ ቢቂላ ጐዳና» የሚባል የለም:: ስለዚህ አበበ አይወደድም አልኩ ለራሴ:: አለማየሁ የዘፋኝ ፎቶ አምጥቶ ሲሰቅል ይደነቃል:: ይጠየቃል፣ ይገመገማል......ብዙ የተያያዘ ወሬ ይነሳል:: ስለቅሷ ሲነሳ ጃጋን ረዥም ታሪክ ያወራል::

በኩረ ግን የዚያን የክርስቶስ ስዕል ከሰቀለ በሁዋላ የሁላችንን ፍላጐት ተጠራጠርኩ:: ዕውነት አለማየሁ ሙዚቃ ይወዳል? ዕውነት ጃጋን መካኒክነት ይወዳል? ዕውነት ነጋሳ ቤተሰቦቹን፣ እናቱን ይወዳል? እኔስ አቤን በዕርግጥ እወደዋለሁ? ስለ ኀንት የማለልኩት ከአንጀቴ ነውን? የመሳሰሉ ጥያቄዎች::

ማን ያውቃል?

ማን ያውቃል ድንጋይ እንደሚያብብ......አበባም ድንጋይ እንደሚሆን?

ማን ያውቃል?

ያሳየኝ አልኩ እሱ ሁሉ የሚሆንለት......ድንጋይ ሲያብብ......አበባም ድንጋይ ሲሆን:: የማይሆነው ሲሆን፣ የሚሆነው ሳይሆን::



@BOOKALEM

# ስንደኛ ክፍል

ታዲያ ዐይኖቼ ታመሙ:: የተለያየ ቀለም ያላቸው ቀሚሶች፣ ሱሪዎች፣ ሹራቦች የለበሱ ሴቶች እያፈጠጥኩ ሳይ ዐይኖቼ ጉልበታቸው እየደከመ ሲመጣ ታወቀኝ:: አልፎ አልፎ እራሴን ያመኛል:: ሴት የማይበት ግራና ቀኝ የማዞረው አንገቴ ማታ ገብቼ ስተኛ እንደ ስፖርተኛ 'ስትራፖ' ይይዘዋል:: አልፎ አልፎ ገነትን የሚያስንቁ ሴቶች ዐይና ለእይ መጨነቴን በቀሰስተኛ ሚስጥር መውደዴን እረግመዋለሁ:: አለባበሳቸው አዲስ የሆነ እየተሳቡ የሚበሉ የሚመስሉ ሴቶች ዐይና የገነት ትልቅ ቀሚስ፣ የገነት ተራ ባለገመድ ሹራብ፣ የገነት ባለ አራት ራጋ ጉንጉን ውብ መሆኑ ይበላሽብኛል:: ዐይኖቼን ደግሜ ደጋግሜ እረግማለሁ:: የራሴ ዐይኖች የሠሩብኝን የመስታወት ግድግዳ መስበር ይከብደኛል::

አንድ ቀን ብሔራዊ ቲያትር ስር ያለች አንዲት ካፊቴርያ ፊት ለፊት እንደቆምኩ አለማየሁ የማይክል ጃክሰን ቀይ የላስቲክ ጃኬቱን፣ ስኒከሩን፣ ትራቮልታውን......ሁሉን ሆኖ መጣ:: 'አሌክስ' ሽርሽር ሲወጣ ቄንጥ ጨምሮ ነበር:: ሠላምታ ገና ሳይሰጠኝ እጁን እንደጉራ አፍንጫዬ ስር አምጥቶ አቆመው::

"ሽቶ ነው:: እንዳንተ ዐይነቱ በረንዳ ላይ ሲንቃቃ አራዳው አሌክስ እም......ከሽቶ ጋር......እ!እ!"

"እሺ አሁን ምንድነው የምትፈልገው?"

"ወዳጄን ሳድነው ነው......"

"ማን አደጋ ላይ አለ?"

"አንድ መዝገቡ የሚባል......ትልቅ ትልልቅ አደጋ ላይ አለ"

"ምን ሆንኩ?......መለከት አበዛህ"

"በይ ነይ......ኩስታራ ጉዳይ አለ"

ጉትቶ ወደ ቲያትር ቤቱ ግድግዳ አስጠጋኝ:: ግራና ቀኝ ዐይቶ ድምፁን ዝቅ አደረገና: "ገነትን አገኘሁዋት" አለኝ::

"እናስ"

"ተይ እባክሽ አትፎግሪኝ......ደስ ትላለች አይደል?"

"እንጃ"



@BOOKALEM

"እኔን ትደብቀኛለህ! እናትክን......ስማ ዛሬ ማታ ገነት ትመጣለች"

ዝም አልኩ።

"ምነው ደስ ያላለህ ትመስላለህ?" አለ ቀጠለና

ሐሳቤ ገና የበስተላይ ንግግሩ ላይ እንዳተኮረ ነበር። ማታ መምጣቷ ነው። ልቤ ትደበድባለች።

ስሟን ስትሰማ እንደ ድቡልቡል ሻማ ትቃጠላለች።

"ማታ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ትመጣለች......ሔደህ ጠብቅ......"

ሣቅ ብዬ አየሁት።

"ንቃ በይ......ሌላ መረጃ ትፈልጊ እንደሆን ፖሊስነቴ ለምንድነው......አንድ ውጤት መስማት እፈልጋለሁ"

"ለምን እመጣለሁ አለችህ?"

"በኩረ ይጠብቅሻል ብዬአታለሁ" እየሣቀ።

"በኩረ ቢኖርስ?"

"ከበኩረ ጋር ብሌን ሰባተኛ አብረን ነው የምናመሸው። እኔ ቡና እጋብዘዋለሁ"

ሳቅሁ። ከት ብዬ ሳቅሁ።

አለማየሁ ትከሻዬን መትቶ ወደፊት ገፋኝ። ዞሬ በመገረም አየሁት። ለአፍታ ኢልያስን መሰለኝ።

"ግን ምን እንደምታደርግ ታውቃለህ? እየሔድን እናውራ"

ተያይዘን በቀስታ ወደ ራስ ሆቴል አቅጣጫ መሔድ ጀመርን።

"ስኳር አልቋል። ስኳር ገዝተህ ሂድ። ፍራፍሬ ግዛ......ኬክ ግዛ......ካሹን አትቀርቅረው......ያልጠበቅሃት ምስል......እሱን በየተራ ስትጋብዛት ጊዜ ይረዝማል። ለመነካካት ምክንያት ፈልግ። ከዚህ በላይ የሚነገር አይደለም። አትቸኩል። የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ይባላል። ይሔ የጠበሳ አንደኛ ክፍል ትምህርት ነው። ከዚያ በሁዋላ ብዙው ራሱ ይመጣል። ብዙ ሳይመሽ አክብረህ ቤቷ። አትርሳ ቤቷ ሸኛት......ተግባባን?"

ስቄ አየሁት።

"በል ስራህን አልረብሽህ" አለኝና ባርኔጣዬን ከአናቴ ላይ መቶት ሔደ።



@BOOKALEM

ያቺ አሥራ ሁለት ሰዓት ታዲያ እንደ አውስትራሊያ ራቀች::

ስኪሬን ከሱቅ፣ ብርቱካን፣ ሙዝ እና መንደሪኖች ከግሮሰሪ ገዝቼ በቅርብ በተፈጠረ ውይይት በሚባል ታክሲ (በደንቡ የአውቶቡስ ተጠቃሚ ብሆንም) ሰፈሬ ገባሁ:: ስራመድ፣ የመኪና ምንገድ ስሻገር በቅጡ ትዝ አይለኝም:: የቤቴን በር ገና ከፍቼ እንደገባሁ የሁላችንንም አልጋ በስነስርዓት አለባበስኩና ቴፕ ከፍቼ ተቀመጥሁ:: ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ማውጣት ማውረድ ከበደኝ:: እኔን ስታይ በኩረን ብቻ ጠይቃ መልዕክቷን በቸልታ ወርውራ ብትጠፋስ?

ይመስለኛል::

'ተቀመጪ' ስላት 'እቸኩላለሁ' ብላ ብትሔድስ? 'በኩረ የለም እንዴ?' ብላ ለራሷ ተናግራ ዐይን-ዐፋርነት ገፋፍቷት ውልቅ ብትልስ? እኔን ገና ስታየኝ ተደናግጣ እንደው 'ጉዴ ፈላ' ብላ ብትመለስ?

ይኼ ይኼ ዐይነት ሀሳብ አድክሞኝ ነውዝ ቢጤ ሲጀምረኝ በር ተንኳኳ:: በሩ ዝግ ነበር:: ቤታችን ምንገድ ዳር ስለሆነ ሁልጊዜ እንዘጋዋለን:: አንዳንዴ የተወረወረ ድንጋይ፣ በእግር የተጠለዘ አፈር የተሸከመ የልጆች ኳስ እየበረረ ስለሚገባ:: ቶሎ ተነሳሁ:: ልብሴን አመቻችቼ በር ከፈትኩ:: ገነት ነጠላዋን ተከናንባ ቆማለች:: መሬት ላይ እንደ ተተከለ ፍሎረሰንት እያበራች:: ቀኝ ጉንጯ ላይ ልትጠልቅ የምትዳዳ ፀሐይ ውጋጋን ማር ቀብታታለች:: መናገር አልቻልኩም:: ፈዝዤ ቆምኩ:: አንደኛ ክፍልነቴ ጀመረኝ::

"......እንደምን ዋልክ? ......በኩረ የለም......?"

"ግቢ......ግቢ......" ከንፈሮቼ ይካበዳሉ:: ምላሴ ላንቃዬ ላይ እንደ ጭቃ ይለጠፋል:: እየተደናበርኩ ከበሩ ገለል አልኩላት:: እየተንሳፈፈች ገባች:: እስከ አናትዋ ድረስ የደረበችው ነጠላ ጦስኝ ጦስኝ ይሸታል......እንዲህ ያለ ዓላማ ዳብሶኝ ሲያልፍ::

"ተቀመጪ"

ተቀመጠች:: ባለአበባ ቀሚሷ የበኩረን አልጋ ሰባ አምስት ከመቶ ሸፈነው:: ብትቀመጥብኝ ተመኘሁ:: እያሰብኩ ነበር:: እንድትቀመጥብኝ:: ከዚያ በሁዋላ የማደርገው ጠፋኝ:: በቀሳሉ በባዶ ሜዳ መውደዴ አበሸቀኝ:: ነጠላዋን ገለጠች ......አንገቷ ሿ ብሎ ወጣ::

"መብራቱን ላብራው?" (አንገቷ እያበራ?)

"ግድ የለም......"



@BOOKALEM

"ጨለመ......ትንሽ......"

መብራቱን አበራሁ፣ በሩን ዘጋሁ።

*ብራቮ*

"የት ሔደ በኩረ?"

"እ......እንጃ......አላወቅሁም"

*ብራቮ*

"ሻይ ላፍላልሽ?"

"ጥሩ......ግን እቸኩላለሁ"

"ምን ያስቸኩላል......ጠብቂው......ይመጣል"

ወደ ጓዳ ገብቼ የኤሌክትሪክ ምድጃዋን ለኩሰኩ......ውሐ ከባሊ ቀዳሁና......ብርጭቆ ማጣጠብ ጀመርኩ። ፀጥ ብላ ተቀመጠች......ሳትንቃነቅ። እንደ ሐውልት። ጉድ!......እንደ ሐውልት። ማጠቤን እያቆምኩ አያታለሁ። በጎን እየሰረቅሁ። ለራሴ ሳወራ የምትሰማኝ ይመስለኛል። ውሐው መንቦጫረቅ ሲያቆም......በሐሳቧ...... 'ፈዞ ሲያየኝ ነው' ትል ይሆናል።

"ብርቱካን ትበያለሽ?"

*(ዝንጀሮ እንኳን ያቅሙን ያውቃታል ወዳጁን*
*የፈለፈለውን ይሰጣታል የእጁን......ሙሉቀን መለሰ)*

"ራት በላሁ አሁን......"

"እንዴ ብርቱካን ምን ይጎዳል?"

ሁለት ብርጭቆዎች ደርድሬ......

"ቆይማ ኬክ አለ......ኬክ አትበይም?"

ሳቅ ብላ፡ "እንዲህ ዐይነት ነገር እዚህ ታስቀምጣላችሁ?"

"ምናለበት" አልኳት "ምናለበት ቆንጆ እንግዳ ሲመጣ"

ተሽኰረመመች።

*ብራቮ ብራቮ መዝገቡ......*

ሁለት ባለክሬም ለስላሳ ኬኮች (እኔ በሕይወቴ የበላሁዋቸው ወይ አንዴ ወይ ሁለቴ) ጠፍጣፋ የላስቲክ ሳህን ላይ አደረኩና በእጇ ሰጠሁዋት።



@BOOKALEM

"እኔ አንዱ ይበቃኛል......አንተስ?"

"እለ ግድየለም......"

መብላት ጀመረች:: ራቅ ብዬ የጓዳ ጨለማ ውስጥ ጀበናዬ ጉን ቆሚ እያታለሁ:: ሻይ፣ ብርቱካን፣ መንደሪን፣ ሙዝ አብረው መሔድ የሚችሉ ግብዣዎች መሆናቸውን አላውቅም:: ለማረጋገጥ ልጠይቃት ፈለግሁ......

"ገነት......ራት ካልበላሽ......ራት ላምጣ......"

"ኸረ በልቼአለሁ......ይሔ ራሱ ራት አይሆንም?" በጣቶቿ ኬኩቹን እያሳየችኝ::

ጣቶቿ:: አለንጋ ውሸት ነው:: 'አለንጋ ጣት' የሚባለው ውሸት ነው:: ጣቶቿ ተጋራፊ አይመስሉም......እንጊ እንዳላቸው የጠዋት ጨረሮች ነበሩ:: ጨለማ ለማፍካት መስመራቸውን ሰባብረው ጉያ እንደሚፈልጉ የጠዋት እግረ-ፀሐዮች::......ለዐይን የሚያምሩ፣ ቆዳ ሲነኩ ደስ የሚሉ:: ጥያቄዬን ዘንግቼ የምናገረውን እያሰብኩ ጀበናውን አመቻቻለሁ:: ማንኪያዎቹን አመቻቻለሁ::

"ሙዚቃ ማንን ትወጃለሽ?"

"ሙሉቀን አለህ?"

"እንዴ አይጠፋም......"

በዚያ ቴፐና ካሴት ተጠቅሜ አላውቅም:: አሰራሩን የምችልበትም አልመሰለኝም:: የሙሉቀንን ካሴት መፈለግ ጀመርኩ:: አለማየሁ በመልክ ያውቃቸዋል:: እኔ እያንዳንዱን እያነሳሁ፣ እያየሁ ስም ማንበብ ነበረብኝ:: አንዳንዱ በእርሳስ ተፅፎ ደሞ በደንብ አይነበብም:: አንዳንዱ በችኩላ ተፅፎ ግልጥ አይደለም:: ሻይው መፍላቱን ተናገረችና ከተቀመጠችበት ተነስታ ጀበናውን ለማውጣት ሔደች::

"ሙሉቀን እዚህ ነበር ላገኘው አልቻልኩም"

"ግድ የለም ካላገኘኸው:: ሌላ አድርግ......"

ድምፇ ጥልቅ:: ካሴት አስገባሁ:: የሙሉቀን ነው:: ደስታ አነቀኝ:: ሣቅ ብላ አየችኝ::

"አገኘኸው?"

ሻይው ይንቆረቆራል:: እንደገና ተቋርጦ ይንቆረቆራል:: ሻይውን ታማስላለች:: እንደገና አቋርጣ ታማስላለች::

እሷ የበኩረ አልጋ ትራስ ላይ እኔ አልጋዬ ትራስ ላይ......መሐሉ ......ጠረጴዛ......ተቀምጠን መጠጣት ጀመርን:: አንዷ ኬክ አልቃለች:: ኬኩን ወዳው ይሆናል:: እኔን ወዳኝ ይሆናል:: ኬኩንና እኔንም ወዳ ይሆናል:: ሀ ሀ ሀ—ውስጤ::

"ሩቅ ነው የምትኖሪው?"

"ቅርብ ነው ከአብነት ሆቴል ከፍ ብሎ"

"ቅርብ ነዋ"

"ቅርብ ነው? ሩቅ ይመስለኛል"

"ይኼ የሙሉቀን ዘፈን ደስ ይለኛል......ደስ አይልም?"

"ይላል"

*እንደ እየሩሳሌም እንደ አክሱም ፅዮን*
*ተሳልሚው ልምጣ ዐይንና ጥርሷን*

"ሲዘፍን ዐይተኸው ታውቃለህ?"

"ፈፅሞ"

"እንዴ አይቼዋለሁ:: በኩረ ብሔራዊ ቲያትር ይሆን ገብቶ:: በጣም ደስ ሲል"

"አይቸው አላውቅም"

"ፖሊስ ከሆንክ ስንት ጊዜህ ነው?"

"ኸረ ብዙ ዓመቴ ይሆነኛል"

"እስከ አሁን አልተሾምክም?"

"አሥር አለቃ ሆኜአለሁ:: መሆኔ ትዝ አይለኝም"

"ኰሎኔል ምናምን የሚኰነው መቼ ነው?"

"እኔ እንጃ"

"እንዴ? እንዴት አታውቅም?"

"እኔ ለመኖር ነው የምሰራው"

"በአጭር ጊዜ ሻለቃ የሆኑ አሉ"

"እንጃ እንግዲህ"

"ሻይ ልጨምርልህ......ሴት ስትቀዳው ይጣፍጣል"

"ትማሪያለሽ?"

"ታዲያስ?"

"የት?"

"ጥቁር አንበሳ"



@BOOKALEM

"ስንተኛ ክፍል ነሽ?"

"10"

"እኔም ማታ ማታ እማራለሁ:: ይደክማል ግን:: ቀን ስቦር እውላለሁ"

"የት ትማራለህ? "

"አዲስ ከተማ"......

*ምነው ቤቴ በሩ በሌሊት ይንኳኳል*
*ሰረፍት የሚነሳ ናፍቆት ከደጅ ቆሞአል*
*ትዝታሽ ረቂቅ ካለጊዜው ገዳይ*
*ቅስሜን ሰባበረው......*

ዝምታ::

"ለምን ፖሊስ ሆንክ?"

"ለምን እንደሆነ አላውቅም" ደበቅሁዋት::

ሻይ የተሞሉ ብርጭቆዎች መጡ::

"ለምን ሙዝ አትበይም:: ከፈለግሽ ብርቱካን:: መንደሪን አለ"

"መንደሪን እወዳለሁ"

"የወረቀቱን ቀረጢት ከፍቼ እንድታወጣ አሳየሁዋት:: እነዚያ የሚያማምሩ እጆቿን ከታ መንደሪን አወጣች:: እጆቿ መንደሪኖች ናቸው:: መናገር አለብኝ:: 'እጆችሽ መንደሪኖች ይመስላሉ' ልበላት?

"እጅሽ ያምራል" አልኩ::

"እንዴ?" አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ::

ደነገጥሁ::

ተርበድብጄ ሳላቆም፡ "ብዙ ሰው ይላል" አለችኝ::

"ማን ይላል?" መጠየቅ ያልነበረብኝ::

"ቤት፣ ዘመድ፣ ትምህርት ቤት--አስተማሪዬ ስፅፍ አይቶ......

"እፍሽስ......ከንፈሮችሽም ያምራሉ"



@BOOKALEM

ዐይኖቿ በድንጋጤ ክፍት አሉ:: የማታውቀውን ነገር የነገርኳት መሰለኝ:: የሚታይ ነው፣ ግን አፏ የሚታይ ነው:: ትልቅና የፋፋ ነው:: ግራና ቀኙ ጠርዝ በመጠኑ ወደ አገጯ ዘቅዘቅ ይላል፣ እዚያም ያሉት ጫፎቹና ሰርጓዳዎቹ ትንንሽ ከብ ጥላዎች ናቸው:: ከዚያ ተሽኰረመመች:: የጨበጣ አድራጐቴ ግብ ያገኘ መሰለኝ::

መንደሪኑን በዝምታ ላጠች:: እንደጨረሰች ግማሹን ሰጠችኝ::

"ሌላ አለ" አልኩ::

"ቢሆንስ......" አለች

መንደሪኑን ተቀበልኩ:: (እናሳዝንም?)

"ስምሽ ለምን ገነት ተባለ?"

"እንዴ አንተስ ለምን መዝገቡ ተባለ?"

"ቀላል ነው:: እኔ የተወለድኩ ዕለት ቤታችን ግቢ የዕድር ስብሰባ ነበር:: አባቴ የዕድር ፀሐፊ ነበር:: እናቴ ምጥ ላይ ነበረች:: አንድ ሰው 'የዕድሩ መዝገብ የታለ:: መዝገቡን አምጡ እንጂ ብሎ ተናገረ:: ሰውዬው እየተናገረ እያለ ተወለድኩ"

ሣቀች......

ሣቀችና: "በስማም እቴ ያሌለ ታወራለህ"

"በቃ እውነት ነው"

"ኸረ እባክህ ተው......"

"አንቺስ ስምሽ ለምን ገነት ተባለ?"

"እኔ የት አውቃለሁ?"

"ልገምት?"

"በል ተወኝ የቅድሙን ዐይነት ነገር ልታመጣ ነው"

"እሺ ተይው"

"በላ ልስማው"

"ተወው አላልሽኝም?"

"ስቀልድ ነው"

"አንቺ ገነት የተባልሽበት ምክንያት በጣም፣ እጅግ በጣም ቆንጆ ስለሆንሽ ነው"

"ሒድ......ደረቅ......አሁንስ......"



@BOOKALEM

ደስ ብሎአት ነበር። ልጅቷ ደስ ብሏት ነበር።

"ቀልዴን አይደለም"

"በል ሌላ ሻይ ትፈልጋለህ?......ብርቱካን ልላጥልህ?"

የሚርበተበቱ እጆቿን የወረቀት ቀረጢት ውስጥ አስገባች። ሙዝ። መለሰችው። እንደገና ሌላ ቀረጢት ውስጥ። ብርቱካን። ብርቱካኑን እያሻሸችው እኔን ገልመጥ እያለች አየች። ተሳሳትኩ። እጇን ልነካ እጄን ሰደድኩ። ማንስ እንዲህ ከመሞከር ይመለስ ነበር? ገነት እግዚያብሔር ወደ መሬት የላካት በፍቅር የመውደቅ ፈተና ናት። እንጀራ እናቴ የክፋት ፈተና። ኤልያስ የወዳጅነት ፈተና። በኩረ የነጭናጫነት ፈተና። አለማየሁ የማዝናናት ፈተና። 'ኒንጃ' የሰብአዊነት ፈተና። እኔስ?

እጇን ሰበሰበች። ፊቷ ተደናግጦአል። ከተቀመጠችበት ተነሳች።

"መዝገቡ ልሒድ መሽ"

የጅብ ችኩል አየር ይነክሳል ዐይነት ሊሆን። ቀንድ እንኳን ላይደርሰኝ።

"እንዴ ቆይ......አትጠብቂውም በኩረን?"

"ቀጥሮኝ ይጠፋል......ቆይ ይጠብቅ"

"እነግረዋለሁ......ቢሆንም ትንሽ ጠብቂው"

"ልሒድ ሌላ ቀን እመጣለሁ"

"ልሸኝሽ"

"ግድ የለም ቅርብ ነው"

"አይ ጥሩ አይደለም። ዩኒፎርሜን ልለውጥ ጠብቂኝ......ራቁቴን ስለምሆን ፊትሽን መለስ ብታደርጊው ጥሩ ነው"

"ኧረ ይኼ ልጅ"

ጠምዘዝ ብላ ወደ አለማየሁ 'ክፍል' አለፍ አለች። ብርቱካኑን ልጣ ጨርሳ ሥጋውን ስትመጠው እሰማታለሁ። ብዙ ጊዜ አልወሰደብኝም። ጫማዬን ሳስር ተመልሳ መጥታ የብርቱካኑን ልጣጭና ፍሬዎች ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች።

እግሮቿ ነጠላ ጫማ ላይ ናቸው። ጣቶቿ እንደ አለንጋ ተኝተውበታል። ብርቱካን እንድበላ ዘረጋች።

"ሶሚ ገነት መንደሪን እወዳለሁ ብለሽ የለም?"



@BOOKALEM

"እዎ"

"ይኼን ውሰጂው" አልኩና ገና ወደ አልነካነው የካኪ ወረቀት ቀረጢት አሳየሁዋት::

"እንዴ ምን ሆንክ......ልጆቹስ?"

"ግድ የለም ሌላው ይበቃናል:: ጎረምሳ አጥንት ከጋጠ ይበቃዋል"

"ጥሩ አይደለም"

"ለምን? "

"ለአንተ ነዋ የገዛኸው......"

"አንቺ ትበልጫለሽ ከእኔ"

"አንተ እንዴት ነው የምትናገረው......በኩረ አትናገርም የሚልህ አያውቅህም ማለት ነው"

"ከሚመስለኝ ጋር ነው የማወራው"

እንደ መደነስ እያለች ቆመች:: ቴፑ ሞቶአል:: ቴፑ በርዶአል:: ቴፑ ጠፍቶአል:: ቴፑ ተኝቶአል:: ቴፑ ዝም ብሉአል:: የሙሉቀን ዕንጥል ጥብጣብ ውስጥ ያናውዛል:: ገንት በነጠላ ጫማ እንደ መደነስ እያለች ቆማለች:: ዳሌዋ ከቀሚሷ ስር የሚቅበጠበጡ ቅንፎች ይሰራል:: ፍራፍሬው ያለበትን የወረቀት ቀረጢት በእቅፌ ይዤው ከቤት ወጣን:: የምናወራው ብዙ ነገር አልነበረም:: ሰማይ ጨለማ ነበር:: ሰማይ መሃል እዚያ ጥቁረቱ ዕምብርት አመልማሎ ደመና እንደ ለምዕ ተኝቶአል::......መታጠፊያው ስንደርስ መንገዱ ግራ እንዳጋባት ሁሉ ስታንገራግር ቀኝ እጇን በግራ እጄ ያዝኳት:: አለቀቅሁዋትም:: ጣቶቿ ሊያመልጡኝ ይታገላሉ:: እኔ ሰማይ ሰማይ እያየሁ ብሞት አልለቀውም ብዬ ያዝኩ:: አፏን በነጠላዋ እየጋረደች እየተሽኰረመመች ትስቃለች:: አልበኛል:: ወይም አልበናል:: እጆቻችን መሃል ያለው ላብ የማን እንደነበር እግዜር ይወቅ:: የሚያየን ያለ አይመስለኝም:: በሕይወቴ የሴት እጅ ይዤ በጎዳና ስሔድ የመጀመሪያዬ ነበር:: የሆነ ችሎታ ይጠይቃል:: እጅ ለእጅ ተያይዞ መሄድ የሆነ ችሎታ ይጠይቃል:: አንዳንዴ አቻኩላታለሁ ልክ ሰሉልታ ይዤአት እንደምገባ:: ነቃ እልና እንዳቻኮልኳት ሲገባኝ እንደ ኤሊ እንቀራፈፋለሁ:: ፍጥነቴን በየደቂቃው በመለዋወጤ መድሓኒያለም ሆይ ልጅቷን ባር ባር ሳይላት ይቀራል? ሽቅብ ሽቅብ ሳይላት ይቀራል? በሰባተኛ ወጥተን ቁልቁል ወደ አብነት ይዤአት ወረድኩ:: የጎዳናው ላይ ጩኸት ጆሮ ይበጥሳል:: ማቋረጫ አለ ብላኝ ደንገዝገዝ ባለ ምንገድ ገባን:: ጥቂት መብራቶች ናቸው ያሉት:: ሁለቱም እጆቻችን በላብ ያዳልጣሉ::



@BOOKALEM

ለቀቅሁዋት። እጇን ሰበሰበች።

ቀኝ ትከሻዋን አቀፍኩት። ልቤ ይረግጣል። ልቤ ቡም ቡም ቡም። እጄን ገፋችኝ።

"ቻኩልክ" አለች።

የጭንቅላቴ ዐገር እንደ ቆብ የወለቀ......ወልቆ መሬት የወደቀ ወድቆ የሚንከባለል......ሲንከባለል ንፋስ ሊያነሳው......አንስቶም እግሮቻችን ስር ሲጥለው.......እና እኔም......እሷም.......እየረገጥነው.......ጨለማ ውስጥ ከሁዋላችን የቀረብኝ......። አንጀቴም በድንጋጤ ሲላላ ይሰማኛል። ቆም አልኩ። ዝም ብላ ምንገዷን ቀጠለች። አፍረቴን፣ መደናገሬንና ስዱብነቴን ውጬ ተከተልኳት። ቤቷ ደረስን። ትልቅ በእሮጌ ቆርቆሮ የታጠረ ግቢ ውስጥ ነበር። ግቢው መግቢያ ላይ ጋቢ የተከናነቡ ሦስት ሰዎች ጨለማው ውስጥ ተሰብስበው ያወራሉ። መንደሪኑን አስያዝኳት።

"ግባ" አለችኝ።

የሚያወሩት ሰዎች ዝም አሉ። ሁለቱ ማን እንደሆንኩ ለመለየት ዐይኖቻቸውን ከጨለማው ያታግላሉ። አንዱ የገባው ነገር እንዳለ ሁሉ ወደ መሬት ያያል።

"ልሒድ......መሽቷልም"

"በኩረን......ቆይ ጠብቅ በለው" አለችኝ።

ገብቶኛል። ያንቺ ነገር እንጃ. ሌላውስ ገብቶኛል።

"ቻው"

"ደህና እደሪ"

ቤቷ እንዳይጠፋኝ የመጣንበትን ምንገድ እያጠናሁ ተመለስኩ። ምንገድ ከማጥናት ሌላ የማስበው አልነበረም። የማየው አልነበረም። ሁለመናዬ ሲለሰልስ ይሰማኛል። እንደ ዳቦ ልብ። የዳቦ ልብ የሆንኩ። እንግዳ ስሜት ነበር። ለራሴ ሳላየው ለብቻዬ ፈገግ ሳልል እቀራለሁ? በዐይነ-ሕሊናዬ ገነትን እከተላታለሁ......እያፈረች ግቢውን አቋርጣ ቤቷ ትገባለች......እናቷ ወይም ቤተሰቧ መንደሪኑን ያያሉ.......በኩረ እንደገዛው ጠርጥረው ይነግሯታል......በኩረ እንደገዛው ሳይሆን በአሻሚ አማርኛ 'ከበኩረ ቤት አመጣሁት' ትላቸዋለች......ገነት መንደሪኖቹን ጠረጴዛ ላይ ታስቀምጣቸዋለች......ትንሽ እህቷ እየሮጠች ገብታ ገነትን በትዝብት ታያትና ምላሳም ስለሆነች......

"አንቺ ገኒ ማነው ያ ልጅ?"

"ምን አገባሽ!?"......



@BOOKALEM

"እማማ......ካንድ እንግዳ ልጅ ጋር መጣች"

"ማነው እሱ?" ይላሉ እናቷ......

"ከበኩረ ጋር የሚኖር ልጅ......'ያ ዝምተኛ ልጅ' እያለ የሚያወራልን" ትላለች አፈር እያለች......

"ምንም አላወራችሁም ስትመጡ?" ይላሉ እናቷ በጉን እያዩ በሽሙጥ......

"ሸንኛ በቃ......አንቺ ደ'ሞ ሌላ ሌላ ታስቢያለሽ"

እንደተበሳጨ ሁሉ ወደ መኝታዋ ትሔዳለች......በዐይን-ሕሊናዋ እኔን እያሰበች......ልብሷን ጨለማ ውስጥ ታወልቃለች......ዙሪያዋን በሕሊናዋ የፈጠረቻቸው የእኔ ዐይኖች ናቸው......ሺህ ናቸው......አትፈራቸውም......በየቦታው የእኔ ዐይኖች ናቸው......ልብስ መስቀያዋ ላይ እንደ ውስጥ ልብስ ተንጠልጥለዋል......ግድግዳ ላይ እንደፎቶ......እንደ ልብስ መስቀያ የምስማር ቆብ......ዐየር ውስጥ እንደ ወፋፍራም አመዶች......ጆሮዎቿ ላይ እንደ ሎቲዎች......ትራሷ ውስጥ እንደ ጥጥ......ባቶቿ ላይ እንደ ጥፍር ጭረት ቢሆንም አትፈራቸውም......ገላዋ ለእኔ እንደተፈጠረ ስለምታውቅ አትፈራቸውም......እንደውም ራቁቷን ትቆምና ትንጠራራለች......በልቧ እኔን ትጠራለች......በልቧ እኔ ስለራቅሁ ትራገማለች......በልቧ እኔን እኔን ትላለች......እኔ ደ'ሞ ሌላ ጋ ነኝ......እኔ ደ'ሞ ያለእሷ ባዶዬን በምኞት እየሞትኩ......በረሐቧ እየሞትኩ......

እነ በኩረ ሰክረው መጥተው ሲጮሁ አልሰማቸውም:: እዚያው ያሉ አይመስለኝም:: ድምፃቸው ከሩቅ......ሕንድ ውቅያኖስ መሐል እንደሚንቦጫረቁ ጀልባዎች ድምፅ ነበር:: ጣና ሐይቅ የደቅ ደሴት ጠርዝ ከሰው ዐይን ተሸሽገው እንደሚዋኙ የገዳም አናኮዎች ነበር::



@BOOKALEM

# ስጦታ

አንድ ዕለት ከስራ ውጭ በምንገድ ስመላለስ በምንም ዐይነት ከንፈሮች ያልተነካ የሊፒስቲክ ዘንግ ጎዳና ዳር አገኘሁና የምሰጠው ሰው ብፈልግ አጣሁ:: ያኔውኑ የሊፒስቲኩ አወዳደቅ ያስታወሰኝ ነገር ቢኖር የሆነ ምሽት ዘግይታ ቤቷ ለመድረስ ትንሽ ርቀት የቀራት ሴት በግድ ተደፍራ ምንገድ ዳር ወድቃ እቃዋም ወዲያና ወዲህ ተበታትኖ ነበር:: የሊፒስቲኪ ሰቃ የሆነች ጉድጓዳ ቦታ አቧራ ለብሳ ነው ያገኘሁዋት:: አጠገቧ ያላለቀ አንድ መሄጃ የቀረው የአውቶብስ ትኬት ወድቋል:: ዐይነምድር የተጠረገበት ድንጋይም ይህቺን ትኬት ተጭኗታል:: በሁዋላ ቆይቶ የከፋ ግምቴ ስላላማረኝ ከሴትዮዋ ቦርሳ አምልጦ የጠፋ መሆን አለበት ብዬ በሌላ በማይሰቀጥጥ ጥርጣሬ ተካሁት::

ቦታው: ወመዘክር ጀርባ::

ዕለቱ: ሃሙስ::

ሰዓተ : ከቀኑ ከ10 ሰዓት እስከ 10 ሰዓት ከሃያ::

የቀለሙ ብልቃጥ የወደቀው ከመንገዱ ራቅ ብሎ የተበላሸ ነጭ ድንጋይ ስር ቢሆንም......ከምመላለስበት ዕርቀት የወርቅ ቅብ ስለነበረው እንደ አንበሳ አውቶብስ ደምቆ ይታይ ነበር::

ታዲያ ይኼን ብልቃጥ ለአንዷ አይቼአት ለማላውቃት ልጅ ልሰጣት ከምንገድ አቋሜአት ስዘረጋላት ገላምጣኝ አለፈች:: ሁለተኛ ጊዜ ሌላ ኮረዳ ሞከርኩ:: እሷም ገላምጣኝ አለፈች:: ሦስተኛ ሞከርኩ:: አሁንም ይህቺኛዋ ጥሩ አድርጋ ገላመጠችኝ::

አስፋልት ላይ ጣልኩትና በጫማዬ ቆምኩበት......አልተሰበረም:: ትቼው ሔድኩ:: ከአምስት ደቂቃ በሁዋላ በዚያ ቦታ ሳልፍ አልነበረም:: ሃ ሃ ሃ::



@BOOKALEM

# ጉድጊዱና ውሃው

አንዳንዴ እያካፋ......አዲስአበ ቀላል ደመና ተከናንባ......እንደ ነጠላ......ሲያካፋ፣ ፀሐይም......ፀሐይ ከራ ወበቅና የቀዝቃዛ አየር እጥረት እግሮቼን አሳስሮአቸው ያጋጠመኝ ቦታ ተቀምጬ አገጬን እጆቼ ላይ አስደግፌ ሳስብ፣ ሕሊናዬ በእጅና በእግሩ እየዳኸ፣ እየወደቀ፣ እየተነሳ ወደ ንፋስ መውጪያ ይነዳኛል። ብጠላውም፣ ተዘርቼ የበቀልኩበትን ብጠላውም የማላውቀው፣ የማልረዳው ነገር ይስበኝና ሕሊናዬ ወደ ንፋስ መውጫ ይወስዳል......

ግብተ-ሕሊናዬ ሲጐትት......እኔ ስስብ ከመሐል የሆነ ቀዳዳ ይፈጠርና......እንደ መንፈስ ቀዳዳ ዐይነት ነገር......የፍርሃት ቀዝቃዛ ሩሕ ያውም እንደ መርፌ የቀጠነች በውስጤ እያፋሸከች ታልፋለች......እየቆየ ፍርሃቴ እያስፈራኝ ለግብተ-ሕሊናዬ ግፊት እጄን ስሰጥ ከኤልያስ ጋር እንዋኝበት የነበረው ኩሬ በቅዝቃዜውና በኩልነቱ እየተንቦጫረቀ......እየሰረበ መጥቶ ጉድጊዳውን ይሞላዋል......አያለሁ......

ዐይኖቼን ከድኜ አያለሁ......

የደረቁ ቅጠሎች እንደ ጀልባ ተቀንፈው...... በጠራው ውሐ ላይ እየተንከበከቡ ሲያልፉ...... አያለሁ በባፎቹ መሐል ሰማይ የታጠበ ጉሎ መስሎ......አያለሁ ኤልያስ በሙታንታ ብቻ ራቁቱን ሆኖ የኢሕአፓ ወረቀቱን ሲያነብ፣ ፀጉሩ በውሐ ተሳስሮ ፊቱ ጡጦ ጠብቶ እንደጠገበ ሕፃን ሠላም ሰፍኖበት......

አያለሁ ውሐ በእጆቼ ዘግኜ ስወረውር በነጠብጣቦቹ ውስጥ የሚያልፈው ብርሐን ዕንቁ የረጨሁ ሲያስመስለኝ......አያለሁ ዕርግቦች ዛፍ ላይ ለፍቅር ሲወጡ......ጨቅላዋንም ያዘለች ዝንጀሮ ገደል አቅፋ ስታናውዝ......ባሏ የቀላ ደረቱን ከፍቶ አብራኩን ሲያክ......አያለሁ እነዚያ አረንጓዴ ቅጠሎች እነዚያ እልፍ አእላፍ ሓመልማሎች ትርጉሙን የማላውቀውን ዝማሬ ከጥንት ከተፈጠሩበት ዘመን ጀምረው የተማሩትን ሲያርከፈክፉት......እስክስታቸውን አያለሁ......ወንዙም፣ የወንዙም ድንጋይ......ዳገቱና ረባዳው፣ ግራጫው ሽጥ እንደትልቅ ጆሮ ተከፍተው ውሐ ውስጥ የሚወድቀው ገላዬን ሲያዳምጡ ያውቁኝ ነበር? ቁልቁለቱን ተንደርድሬ ሚስጢራቸውን በአብራኬ ስቀድ ያውቁኝ ነበር? ያውቁኝ ነበርን?......ቀዝቃዛው ውሐ......ከልጅነት ቀዳዬ ላይ እንደ ተከለሐይማኖት ዕንባ እርኩስ መናፍስትን እንደቅርፊት ይጥላቸዋል......ይጥላቸው ነበርን? ወንዙ ውስጥ ያሉ ሰይጣኖች እንደ ጥንቸል ይርበደበዳሉ......ይርበደበዱ ነበርን? ኤልያስን እየዋለሁ በማይገባኝ ጉዳይ ቆሞ ሲስቅ......



@BOOKALEM

ውሐ እረጨዋለሁ......

እየሸሸ ይስቃል......

ውሐ እረጨዋለሁ......

በአየር ላይ እንደዘንዶ ተወርውሮ ገብቶ ባሕሩ ውስጥ ይደፍቀኛል::

ዘተፈጥሮ የነበረ......ዘማማርም::

ውሐው ጠግቦ እንደተኛ ፍቅር ለስላሳ ነበር......

አየር አጥሮኝ ባቃስትም የውሐውን ለስላሳነት አደንቃለሁ::

አ! ይኼ ውሐ እንዴት ለስላሳ ነው! እላለሁ

እላለሁ......ሁሉ ለምን እንዲህ ለስላሳ አይሆንም እላለሁ:: የልጅነት ኩሸታችን የሰራችው ለመምቴዎች ወዲያ ጥግ እስከ ቁርጭምጭምቷ የተነከረችው ወይዘሮ ባቷ ድረስ ቢመጡባት ስርቆት እንደተሳመች ሁሉ አልተንከተከተችም? ውሓ ቀጂ ብላቴናስ ራቁት ደረቱ ላይ ተሳቦ እያጫወተ የተዘናፈለው ቁንጮው እየተርገፈገፈ አልሳቀም? ውሐ የሚቀዱ ሴቶች ሽተት ብለው ያልፉናል:: እረቅ ገላችንን አፍረው:: ኢልያስ ሁለት ጣቶቹን አፉ ውስጥ ከቶ ያፏጭላቸዋል......ሲያፏጭ ስቀናበት:: ያን ጊዜ በዓለም ላይ ሴቶች የሚፈልጉት አንድ ነገር ቆንጆ ፉጨት ይመስለኝ ነበር......እስከ ወገቤ ውሐው ውስጥ ቆሜ አራት ጣቶች በአፌ አስገብቼ እኔም እሞክራለሁ:: ትልልቅ ትንፋሽ ይወጣኛል......ከውሐ ጋር የተደባለቀ......ለሐጭ በአገጬ ላይ ይወርዳል::

አቤት ሲያፏጭ ስቀናበት::

ከላይ ካዙዋሪቱ ዐረግሬሳ መሬት ለቆ ባንዣበበበት......በእዚያም ጥላ ስር ችልተኛ ቆቆች አንዱ አንዲ ላይ ቆሞ ኩታቷንም በትኩረት ነክሶ በረከቱን ትፍ ሲያደርግ ሹፈት ተማርንሳ......እንደገናም እዚያ ገደሉን ተንደርድረው ከመሃል እርከን የቆሙ የእንጆሪ ፍሬዎች ቅላታቸውን ንቀናልና እንዲታወሱን ራሳቸውን ከሾህ ጉያ ነቅለው በለጋ ሳሮች፣ በሚፈልቁ ርጥብ መርግዶች ላይ በምንጭ ውሃ ፈፋ ኮለሊታ ወርደው ለውሃ እናት ጌጥ ቢሆኑ......እንደ ሕይወት አድነን አልቃምናቸውም?......ደሞም እወዲያ ጋ ትንሽ ልጃገረድ የእናቷን ነጠላ ስታሰጣ እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ ሳትመልሰው ጭኖቿ ከድተዋት የተጎሰጎሰ ቀሚሷ ለቆ ያልደረሰ ሴትነቷን ዐይቼ አፌን ለሳቅ አልያዝኩም? እና የደረቷ የብር መስቀል የፀሐይ ብርሓን አርፎበት ጨረቃስ ወረደች ብንል......ደሞስ በደረቀ የበጋ ዕለት ካፊያ ከመሬት የሚያነሳው የአፈር ጢስ ሳንባችንን እንደ እስረኛ ይዞት ስናቃትት ዝበሬአችን «እሽት ማታ» እላለንም? ሾላዎች

ደርሰው ቀልተውና ተከፍተው የውስጣቸውን ቁጫጭ በትንፋሻችን አጥበን አልተጎራረስንም.......ይሄ ሁሉ ስጦታ ለምንስ ይዘነጋል? በአውሊያ ያበጡ አበቦች በለዘዘ ዕለተ-ቀትር ፊታችን ላይ በውበት ሲፈነዱ.......እነሱን ወለላዎች የመጠጡ ቢራቢሮዎች ጀርባችን ላይ እንደንቅሳት ቢወቀሩ ምኞት አላለምንም?.......ይሄ ሁሉ ቀለም አግረ አላማረ ለምንስ በመርሳት ይታጠባል? ደስታ አላቂ ነው:: ሐዘንም አላቂ ነው:: ውሸት አልኩ? ውሸት አልኩ እንዴ? አስባታለሁ.......ያቺን ትንሽ ጊዜ፣ ያቺን ትንሽ ዘመን......የቆሰለ ባህር ላይ እንደምታንፀባርቅ ንዑስ ጨረቃ::

ሐዘኔ ታሪክ መች ነበረው??

መሰንየለሽ ሐሙስ አስቀይማኝ ዓርብ ነግቶ በጉጉት አላየሁዋትም?

በጀርባዬ ተንጋልዬ የደመና መልካምድር በዓይኖቼ አልቀረጥኩም? ባደከመኝ ቀትር ስርስ ጥላቸው አልጋረደኝም? በሚያዝያ ነጭ ቀናት ጨረር በቅንድቤ ቀልቤ በሽውራራ ዓይኖቼ እንደሚያውቅበት ሁሉ የትምህርት ቤቴን በሬዱዎች (ነጋሳ እንደሚለው) አግድሜ አላየሁም? አግላይ ትኩረታቸውን ንቄ ያኮረኮረ ደረታቸውን ሳነብ «እንዴ?» ብለው አላለፉኝም? የኩሽቴንም ሳቅ የሚጋራኝ ባይኖር እንኳን አብራኬ እንደ በሰለ አልመዘንኩም? ከሰል የመሰለው ሰማይ ላይ እግዜር የሚያሳየኝን ከዋክብቶች ስቆጥር «በቃህ» ያለኝ ማን ነበር? ስቆቃ የቀደደው ቁስሌንስ በጨረቃ ብርማ ጨረር አልሰፋሁም?

በምኞት ቅዠት እየተራመድኩ የገበያችንን ባቢሎን ሳቋርጥ ትርንጎዎች መዓዛቸውን ቆምጣጤዎችም ቀለማቸውን የት ነፈጉኝ?

የጠራ ውሃ ባቋረበት እንቅልፋም ላሞች በሚግጡበት ሳር ሜዳ ላይ ለስላሳ ካፊያ ውስጥ ባዶ እግሮቼን ቆሜ የሳቅሁትስ? እጄ ላይ ከያዝኩት የቡሄ ጥቢኛ ላይ በአፌ የተረተርኩት የነጣ ቅጠል አንቆኝ ስስል ጋጋሪዋን መች ተቀየምኩ? በረመዳን ምሽት የገዳፊ እስላሞችን የቤት ግድግዳ ታክኬ ሳልፍ መረቅ ቢሸተኝ መዓዛውን በሳንባዬ ሳምኩ እንጂ መች ቀናሁ? ደሞስ በሩፋኤል ሜዳ አደዮች ባሞጠሞጡበት በቢጫና አረንጓዴ የካፊያ ቀን በዚያች በተመረቀች ጳጉሜ አሪቄን በዘመዶቼ ዐይን ስር ስሮጥ በሙርጡ መፍዘዝ መች አፈርኩ? ጭር ባለ ቀተር የተበሳጨች ወይዘሮ ያሰጣችውን ስጥ የዶሮ ሰልፈኛ ቢተከትክባት «ያንሳችሁ እቴ!! ምጥማጥ ይላክባችሁና.......የተረገሙ.......አንገታቸውን እየጠመዘዙ መጣል ነበር!!» ስትል ዕውነቷን ነበር? ውደ ጓዳዋ ገብታስ የተንጀለጀለ እርጥብ ጡቷን መዛ ነጭ ጤዛ ልጇ አፍ ውስጥ አላለበችም?



@BOOKALEM

ትንሽ የከፋትና የደግነት ወሰን ተደበላልቆብኝ ልጅነቴም ማንጠር ከብዶት.......

ትንሽ ልቤ ቢከፋት

ዓይኖቼም ሰንባ ቢያቀና

ትንሿ ነፍሴ ብትንሜነጭም

ጨልሞብኝ ከተኛሁብት አልጋ ላይ

ያገሬ ጠዋት ኅትታ አላነሳችኝም?

.......ብቸኛ ቆዳዬ ላይ እኔ ችላ ያልኩ ዕለት ንፋሿ እንደ ወላንሳ ክትባት ረጋብኝ አይደለ:: የተደፈሩትን ዐይኖቼንስ የትዝታ ማይዋ በለሆሳስ አጠባቸው አይደለ?

ከዚያ ኩሬዋ መፍሰስ ትጀምራለች......ኩሬዋ መናድ ትጀምራለች:: ጠራራ ያደከመው የቀን ሕልሜ ተቆራርሶ ያልቅና አዲስአባ መሐል እኔና ጉድጓዴ እንቀራለን......ማንም የማያይት ጉድጓዴ እንቀራለን:: ጮሌዎችና፣ ፖለቲከኞች፣ ሌቦች፣ የመብት ነጣቂዎች፣ የሀበሻ ድፍርስ ፈላስፎች፣ የንዑስ ከበርቴ ሸርሙጦች፣ የሚፈልጉትን የማያውቁ ተናጋሪዎች፣ ተቺዎች የማያይዋት ጉድጓድ እንቀራለን::

ከእነዚህ ሁሉ

አንዳንዶቹ ሾልከው ያልፉሉ.......

አንዳንዶቹ ጉድጓዱ አፍ ዙሪያ እንደ ሲሚንቶ ይመረጉና አፈር በመሰለ ጥርሳቸው እየሳቁ ያዩኛል.......

አንዳንዶቹ.......ታከው.......በጨዋታቸው መቀመቂን እንደ ጥጥ ሊከድኑልኝ ይለፋሉ.......

እንደ ወሉዬው::



@BOOKALEM

# የኩብ መፀት

ብሔራዊ ቲያትር ጀርባ ለቀኔ ሒሳብ ከመደብኳቸው ሲጋራዎች ሁለተኛዋን ለማጨስ አውቶቡስ መጠበቂያ ተደግፌ ተረጋግቼ ቆሜአለሁ:: ጊዜው ከቀትር ያልፋል:: ምናልባት ሰባት ሰዐት ተኩል:: ኒያላዬን አንጣጣለሁ:: ረዥም ጊዜ ስላጤስኩ ራሴን ትንሽ ዞር አድርጎኝ ዐይኖቼን ጨፈንኩ:: በልቤም እላለሁ፡—

መጥፎ ልማድ .......

መጥፎ ልማድ .......

መጥፎ ልማድ .......

መጥፎ ልማድ .......

ሲጋ ረሐብ ሆዴ ውስጥ ሽር ይላል የጨጓራ ፎጣ እየጧጠጠ:: ዐይኖቼን ስገልጥ ከፊት ለፊቴ ወሉዬው እየሳቀ እያፈጠጠብኝ ቆሟል:: ከፊቱ ስፋት ግማሹ ካሬ ሜትር አንድ ሽንቁር ባለው የጥርስ ሰልፍ ተሸፍኗል:: ትልቅ የቆሸሸ የካኪ ሳርያን ኮት ለብሶአል......የግራ ኪሱ ተዘንትሮ የተንጠለጠለ:: ያልመጠነው የሱፍ ሱሪ አጥልቋል.......ከጉልበቱ የተበጣጠሰ:: አግዳሚ ወንበር የሚያክል አገርህን እወቅ ጫማ አድርጓል:: እዚያ ጫማ ውስጥ የመረሬ መሬት ድቅድቅ የመሰሉ እግሮች.......አውራ ጣቶቻቸው ቆስለው በቆሸሸ ፋሻ የታሰሩ:: ጀርባው ላይ ታላቅ ጭነት በማዳበሪያ ቀረጢት ተሸክሟል......እውስጡ በጠቀጠቀው ቁሳቁስ ምክንያት ልክ እንደ ግንድ በጉጠት ፈንጣጣ የተሸፈነ::

የመገረም ሳቅ ለመሳቅ ሞከርኩ:: ሲጋራው ነው መሰል ደሞ ሆዴን ያቅለሸልሸኝ ነበር:: ሳቄ ተበላሽቶ ሲጋራውም ትን ብሎኝ በቀላሉና በደንብሬ .......ከት.......ከት......:: አፉና አፉ ዙሪያ የዘረጋውን ድምፅ የሌለው ሳቁን ሳይገል እጁን ለልመና ዘረጋ:: ወይስ ሊያሾፍ ነበር?

ፊቴን በንቀግንት አዞርኩ::

እንደገና ዐይኖቼን ወደ ዘረጋው እጁ ስመልስ መዳፉ መሓል አሮጌ አሥር ሳንቲም አየሁ::

"ምን ፈለግህ ሙሌው? " አልኩት::

እንገቱን ሰበር አድርጎ:



@BOOKALEM

"ወንድሜ ወንድሜ ሙሌ አይደለሁም:: ሙሌ እንዲህ ዐይነት ጭነት ተሸክሞ ይዞራል? በነገራችን ላይ...... "

"ምን ነገር ጀምረናል:: ተረት ልትጀምረኝ ነው?"

"ተረት የሚያስጀምርህ ሕይወት ነው:: አስጀማሪም አስጨራሽም አይደለሁ:: አስጀማሪም አስጨራሽም ሕይወት ነው"

"ፍልስፍና የመረረኝ ነገር ነው:: ዳቦ አይሆንም:: ምን ፈለግህ ታዲያ?"

"እራሱን መጠየቅና መተቸትን ለሚፈራ ሕዝብ እግዚአብሔር ስጦታ አዘጋጅቶአል:: በተለያየ መንገድና ምክንያት በመፍጠር ለሚሸሽ ሕዝብ......."

"ምን? "

"እከክ"

"በል ዞር በል....... "

"ይህቺን ሳንቲም ታያታለህ? በደንብ እያት....... "

"አየሁዋት"

"ምን ታያለህ? "

"አስር ሳንቲም" አልኩ በመሰላቸት::

"ጫፍዋ የተላላጠ የተጣመመ አስር ሳንቲም"

"እና ምን ይጠበስ? "

"የሚገርመው በትክክል ላስበው:: ቆይ እም......እም...... እም......ከስድስት ወር በፊት እኔ እጅ ነበረች"

"ጉድ አመጣህ"

"አዎ:: ማመን ይከብዳል"

"ተረትህን ጀመርክ? እስስቶቹ ወስደዋት ነበር?"

"ጠጋ ልበልህና ላሳይህ? ሳስብ የተጠየፍከኝ መሰለኝ"

"አልወጣኝም"

"ግምት ነው:: በእርግጥ ግምት ሁሉ ትክክል ነው ማለት አይደለም"

"ተሳስተሃል"

"ጎሽ የእኔ ጌታ"



@BOOKALEM

ተጠጋኝና እጁ ላይ የተኛችው ሳንቲም አተኛኘቷን ሳይለውጥ ወደ ፊቴ አስጠጋ:: ከሲጋራዬ ሳብኩና ጢስ ወደ ጎን ወርውሬ (እሱን እንዳይነካው) ሳንቲሟን አየሁዋት::

"እሺ እናስ? "

"እነዚህን ጭረቶችና የተጣመመ ጎኗን ለመለየት እንዲመቸኝ አድርጌ ለጨዋታ፣ ለኩሸት እኔ ነኝ ሳንቲምዋ ላይ ያደረግሁባት"

"ውሸት እንደሆነስ? "

"ምኑ? ማድረጌ? ለዚህ አታምነኝም? "

"ባለፈው ጊዜ ስለ እስስቶቹ ነግረኸኝ አምኜህ ለሰው ባወራው መሳቂያ ነው ያደረግኸኝ"

"እሺ የኛ ሰው የማይስቅበት ነገር የለም:: ክርስቶስ ተመልሶ ቢመጣ ይስቀበታል:: የሚያደርጉትን አያውቁምና......ሳታምን ስማኝ:: ለመስማት ማመን የለብህም:: አይደለም እንዴ?"

"ሌላ ሰው እንደዚህ ታስቸግራለህ? ወይስ እኔን መርጠህ ሠላም እየነሳኸኝ ነው?"

"ዞር ዞር ብለህ እይ:: ጆሮ ጠፍቶአል:: የዛሬ ጆሮ ጎመን ሆኗል ነው:: ብትበላው እንኳን አይሰማህም"

"የማውቀው ነገር የለም:: የጀመርከውን ጨርስ"

"ስለምትሰማኝ ነው:: ለምን እንደሆነ አላውቅም:: እንዲህ ነው:: ይህቺን ሳንቲም ከመርካቶ አግኝቼአት በአዲስነትዋ ስጫወትባት ቆይቼ እዚያው ቆሎ ገዛሁባት:: ሸንብራ ዱቤ እወዳለሁ:: ዱቤ ጥሩ ናት:: ሆድ ያዝ ታደርጋለች:: አንድ እፍኝ ታውልሃለች:: ልብ አድርግ ጭሬአት አጣምሜያት ነው:: ከስድስት ወር በሁዋላ ተመልሳ እጄ ገባች:: ትንግርት አይመስልም? ግን አይደለም:: በምሳሌ ልምጣ:: በየቀኑ የሚሰክር ሰው አንድ ሌሊት በመኪና ቢገጭ ይገርምሃል? እኔ አይገርመኝም:: ለምን? አየህ «ተው ይቅርብህ እረፍ አንድ ነገር እንዳትሆን ሲባል ኖሮአል"

"ምን አገናኘው?" የሲጋራዬን ቁራጭ ወደ አስፋልቱ ዳር ወረወርኩ::

"ስለመያያዝ ላወራህ ነው"

ቀረጢቱን መሬት ጣለና ከሳርያን ኮቱ ኪስ ጠመኔ አወጣ:: ጠመኔውን ወደ ላይ አንስቶ አሳየኝ:: ጠመኔ እንደማላውቅ ሁሉ:: ፍንጭቱ መሓል ትንሽ የሥጋ እንጥል ትታያለች:: ገፁ ከድሮው በልዞአል:: ጠቁሯል:: ሽበቱም በርትቶበታል:: ችግር የከበበው


ላይሆን እስከ አጥንቱ እንደሰረገበት ያስታውቃል:: ይሄን ችላ ያለ ነው የሚመስለው:: ቾክ ተሸክሞ ምን አዞረው? ቾክ ለእሱ ምንድን ነው?

ቁጢጥ አለና መሬት ላይ የ 'ተ' ምልክት በትልቁ ሣፈ:: ቀና ብሎ አየኝና:

"ይሄ እኔ ነኝ"

"እና"

"ሳንቲሟ ከእኔ ተነስታ እኔ ጋ መጣች" ብሎ ከ'ተ'ዋ መስመር መሳል ጀምሮ አንድ ክብ ከተረና መልሶ ወደ 'ተ' ዋ አመጣው::



"እና"

"ዞር እንባለን እንጂ አንሸሽም:: ለሰራሁት ነገር ሁሉ አላፊነት አለብኝ"

"እና"

ትዕግስቱ እንዳለቀ ሁሉ 'እናዎቼን' ተናግሬ እንደጨረስኩ ኮስተር ብሎ አየኝ::

"ምንገድ እያበላሸሁ አይደለም:: ከመሰቀያው የሸሸ መሰቀያውን አያመልጥም:: ሂሳቡ ሲወራረድ ይተላለፋል እንጂ አልቦ አይሆንም:: ሾርባህንም ታገኛለህ:: ዙር ነው:: የእኔ ቀንበር ዛሬ ያስቅሃል ነገ በተራህ ትሸከመዋለህ:: አንዱ ሲላጭ ሌላህ ታጠብ ያሉት:: ብጠይቅህስ:: እኔ 'ይህቺ ሳንቲም መንግስቱ ሐ/ማርያም ኪስ ነበረች' ብልህ 'አልነበረችም' ማለት ትችላለህ? ማረጋገጫ የለህም:: እኔም የለኝም፣ ግን የእኔ ይሻላል:: ከዓሣ ነባሪ አየህ 'ታዲያ ሳንቲሟ ለስድስት ወር የት ነበረች?' ብዬ መጠየቅ እችላለሁ:: ከዓሣ ነባሪ ያመለጠ ለምን በጉንፋን ይሞታል? ለእኔ ሚስጢር የለውም ሒሳብ ሲወራረድ ነው:: የጣድከውን ትቀበላለህ:: የጠላሃትን ትወዳለህ:: ክቡ ምን ያህል ዓመትና ወር ወሰደ ነው አየህ:: ይህቺ ሳንቲም ከእኔ እጅ ስትወጣ ያገኛት ሰው ወዜን ነክቶአል:: ፊት ለፊት ቢያዩኝ ይንቁኛል:: ግን በመኖር ኪነጥበብ ተነካክተናል:: አያመልጥም:: ከለማኝ ወደ ቻሪው ይሄዳል:: ገንዘባቸውን ቤት ውስጥ የሚደብቁ ሰዎች አልወድም:: ያሳፍራል:: ለምን አትለኝም? ከንክኪ ስላራቁት"

"አውቃለሁ"



@BOOKALEM

"ደግ:: ግን ይሄ የሚያሳየኝ ደሞ ሌሎች ብዙ ሰዎች እንደተጠቀሙባት ነው:: ሐብታም ደሓ መሆኑ አይደለም ጉዳዩ:: ወገኔ መሆኑ ይበቃኛል:: አየህ ሳንቲሟ ተመልሳ እስክትመጣ ብዙ ሰው እኔ የነካሁትን ነክቷል:: አየህ ቃል ኪዳን ነበር ይሄ:: እኔ መራቤ ከሰው አያገለኝም:: አየህ..... " አለና ያሰመረው መስመር ላይ ጭረቶች ሰራ:: ቁጥራቸውን እርግጠኛ አይደለሁም::

"ጭረቶቹ ሰዎች መሆናቸው ነው:: ምሳሌ ናቸው"

"እነሱ ጭረቶችህ የሰው ምሳሌ......?"

"አልኩህ:: ሺህ ሚሊዮን ሊሆኑ ይችላሉ:: የምናገረው በምሳሌ ነው:: ምሳሌ አይሞትም"

"ድብን ይል"

"ይዘነጋል እንጂ አይሞትም"

"ያው ነው"

"ያው አይደለም:: አባትህን ዘነጋኸው ማለት ሞቷል ማለት ነው? የሞተስ እናስታውስ የለ? ሞቷል ማለት ነው? "

ዐይኖቼን አተኩሮ አያቸው:: ልክ ስለእኔና ስለ አባቴ የሚያውቅ ይመስል ነበር:: ወይም ከቤተሰቤ የመለያየት ችግር ያለብኝ ወጣት::

"ከሺህ ዓመት በፊት የተፈጠረ ተረትና ምሳሌ እስከዛሬ አለ:: ለምን? ብዙ ያልጠፋ ነገር ስላለ:: ለውጥ ለውጥ ብንል ተረትና ምሳሌው ካልተለወጠ ለውጥ የለም ማለት ነው:: ለውጥ ነፍስ ውስጥ ነው:: ነፍስ ደሞ ቋንቋ ነው:: ልባስ ብንለውጥ ምን ይሰራል? 'የአባት ዕዳ ለልጅ' ብዬ ብተርት ዛሬም ይሰራል:: ለምን? ድሮም ዛሬም አባትና ልጆች አሉ:: ዛሬ ያሳበጀነው ነገር ቢተላለፍ ችግሩ ነገ ብቅ ይላል:: ዛሬም አለ:: የተረትም ክብ አለው:: ምክንያቱም ሰው ክብ ነው:: ሮጦ ሮጦ ወደ ጀመረበት:: የሚለወጠው ዕውቀትህ ነው:: ይሄ ዕውቀት የትም አይደርስም:: ለምን? ማስተማር ትፈልጋለህ ግን የሚማር የለም:: ትክክለኛው ይሄ ነው ብትል የሚሰማህ የለም:: እያንዳንዱ ሰው በስህተት መኖርን ይሸታል:: ሕይወት ክብ ስለሆነ:: ሰዎች በእንጀራ ይጣላሉ፣ ሰዎች በሹመት ይጣላሉ፣ ሰዎች በሴት ይጣላሉ፣ ሰዎች ይወለዳሉ ይሞታሉ፣ ሰዎች ከተቃራኒ ፆታ ጋር በአልጋ ይተኛሉ፣ ይዋለዳሉም:: አልተለወጠም:: ድሮ ያኛፉ እንደሆነ ዛሬ ይተኮሳሉ:: ቢለወጥ እንኳን ካልተለወጠው አይበልጥም:: አየህ ስተርት ነገር እንዳያልፈብኝ ስለምፈልግ ነው:: ብሩህ ሰው ግን አይደለሁም:: ተረቴ ስር ይያዝ



@BOOKALEM

አይያዝ አላውቅም::......ጊዜህን ወሰድኩብህ:: እንዳንተው አገሬን እጠብቃለሁ:: እኔ ግን ተረቷን ነው የምጠብቀው:: ተረት ይከስማል:: ችላ ካሉት ይሰደዳል:: ይጠፋል"

"በምንህ ነው የምትጠብቀው? "

"እንዲህ እየዞርኩ በወሬ"

"በወሬ? "

"ምነው? በወሬ የፈለግሁትን መፍጠር እችላለሁ:: በወሬ የትንሽ ልጅ እናት መግደል እችላለሁ:: በወሬ ሰይጣን የእንጀራ እናትን ቅዱስ ማድረግ እችላለሁ:: በወሬ ውሃ ማቃጠል እችላለሁ:: በወሬ በሬ ማስወለድ እችላለሁ:: ከድሮ ባሕልህ የቀረህ ምንድነው? ፍልስፍና? አይደለም:: ልዩ ሕንፃ ስራ? አይደለም:: ለሁላችንም የቀረን የወሬ ቴክኖሎጂ:: ይሄ ቴክኖሎጂ የሚቀመረው በቋንቋ ነው:: ተረት የማበዛው ስለዚህ ነው:: ግን ሁላችን እኩል ዕውቀት የለንም:: እኩል ዘበኞች አንሆንም:: ይሄ ዕውቀታችን ከአፍ ወደ መፅሐፍ አልገባም:: እስኪገባ እለፋለሁ:: በሆሄ ወይም በወሬ:: ሰማህ? በሆሄ ወይም በወሬ"

"ማነህ አንተ? እስስት በዚህ ገባ......እስስት በዚህ ወጣ ማን ያምንሃል? ማን ግድ አለው? ዝም ብለህ በሠላም ቅፈፍ:: እዚህ ምድር ላይ መፈጠርህንም የሚያውቅ የለም"

"ማን ለመናቸው እንዲያምኑ:: መብቴ ነው ግን የሚመስለኝን መናገር:: ወይስ መብቴን መለመን አለብኝ? ዳቦ ለምነን፣ መብት ለምነን፣ ሴት ለምነን፣ የሚጠጣ ለምነን:: ዓለምን ስንዴ የምንለምነው ይሄ ለምዶብን ይሆናል:: ምንም አትለምን:: በሥነሥርዐት መብትህን ውሰድ:: የአንተ ወንዝ ያንተ ነው"

"ለምን ይጠፋል ተረት?" አልኩት ሳቅ ብዬ ለመቀለድ::

"ሲጋራ ልስጥህ? አሰኝቶሃል?"

"ግድ የለም"

"በቀን በጀትህ ከሦስት በላይ እንደማታጤስ አውቃለሁ"

ደነገጥኩ:: አተኩሬ አየሁት:: ዐይኖቼም ውስጥ ብሽቀት ይነበባል::

"አይዞህ አልሰለልኩህም:: ምንገድ ላይ ከጓደኛህ ጋር ስታወሩ ነው የሰማሁህ:: ቆይቷል:: ይቅርታ እንደ ብልግና አልወሰድኩትም:: ግድ የለም አንድ ውሰድ:: ሰውን አትፍራ:: የሕዝብ ሠላም ረባሽም ሰው አይደለሁም:: ታውቃለህ".

ሲጋራውን በመገረም ተቀበልኩ:: የለዘዘ ሲጋራ ነበር:: ስታሊን እርጋን አወጣና ለኮሰልኝ:: የንፋስ መውጫ ማጤስ ትዝ አለኝ::



@BOOKALEM

የትይዩው አውቶቡስ ማቆሚያ ላይ ወደ ጦር ሐይሎች ሆስፒታል በሚወስደው አቅጣጫ እንዲት ልጃገረድ ቆማለች። ጢስ ቡፍ እያደረኩ አያታለሁ። ቀሚሷን እልፍ እልፍ ነፋስ እንደ ቅጠል ያነሳዋል። እስከ ጭኖቿ ግማሽ አያታለሁ። ቸል ብላ እጆቿን ከጭኖቿ ላይ ስታነሳ ተንኮለኛው ነፋስ ጠብቆ ይገልባታል። እኔና ወሎዬውን በመገረም የምታይ ትመስላለች። ሳቅ አለች ልበል? ረኸም ገነት ትመስላለች። ለምሳ የወጣው ሰራተኛ ሁሉ ወደ የመስሪያ ቤቱ እየተመለሰ ነው።

ወሎዬው ያወራል: "ምሳሌ የሚዘነጋውማ አየህ እንደ ሰው የላይና የታች ስላለው ነው። የቁንጅና ደረጃ እንዳለው ሁሉ። አየህ እነዚህ የማላውቃቸው አንዳንዶቹ ምናልባት ባጠገባቸው ሳልፍ በቀሻሻነቴ የሚጠየፉኝ ይሆናሉ"

"ይሄን ሁሉ ምን አሳሰበህ?"

"እንዲህ ያለ ነገር ሲያጋጥምህ አይገርምህም? ሌላ ሌላ ነገር አያሳስብህም?"

"ሰው ያለ ሰውማ አይሆንም"

"ቢወድም ቢጠላም። አንተ ስለምትረዳልኝ ነው ላዋራህ የምወደው። ልዩነት ግን አለን"

"በምን? "

"እኔ አደርጋለሁ። ስህተት አላልፍም። ሰው አያስፈራም። ማየት ምን ይጠቅማል? ለመውደድ ለመጥላት ካልወጣህ? ትንሽ ካልረበሽክ፣ ትንሽ የአንተን ቦታ ካላሳየህ። መፈጠርህን ማስመስከር አለብህ። እዚች ምድር ላይ እንደ ነበርክ ማሳየት አለብህ። ያወቅኸውን ማሳወቅ። ያሳቀህን ያሳከከህን ያሳዘነህን ካልገለጥክ ሰው መሆን ምን ረባ? ካላስተማርከኝ......እንደ አገር አንድ ተራ ሰውም ታሪክ አለው......ሰው እንደ ሰማይና እንደ ምድር ታሪክ አለው......ታሪክህ ያፅናናል ያስቃል የማይተያዩትን ወዳጅ ያደርጋል። ሰው የሚፅፈው ለዚህ ነው......ሀ ሁ የምትችል ከሆነ በፅሁፍ የማትችል ከሆነ በወሬ ታሪክህን ንገር......ዘመናት ያቆራኛል.......አየህ ሁሉ ነገር ይደጋገማል......ነገር በወሬ ከጠፋ ነገር በወሬ ለምን ዐይነሳም?......በሆሄ ወይም በወሬ ያልኩህ ለዚህ ነው"

ልጅቷ ትስቃለች። ፀጉሯ ለመሆኑ ምንድን ነው? ከጀርባዋ አየር ቀልብሶት ትከሻዋ ላይ እየተርመሰመሰ ይወድቃል። ቀይ ዳማ ጭኖቿ በአስደንጋጭ ውበታቸው ጉሮሮዬን ይዘው መተንፈስ ከልክለውኛል። እና ለምንድን ነበር ቀሚሷን ትንሽ ከፍ አድርጋ ጭኖቿ መሃል የምታከው? እና ሳቀች? ለምን ሳቀች?

"ሰማህ?......ሰማህ?.. "



@BOOKALEM

"ም.......ም.......ምን አድርግ ነው የምትለኝ? እስኪ ይብቃን" አልኩ ከእንቅልፌ እንደነቃሁ ሁሉ::

ወደ ሁዋላዬ እየና ወሎዬው ሳቅ አለ:: ልጅቷ ጭኗን እያከከች ሳቅ አለች::

"አድርግ አልኩ" አለ:: የልጅቷ አሳሳቅ ድንቅ ነበር:: ጥርሶቿ ከመቅለጥ ያመለጠ የበረዶ ግድግዳ::

"ምንገድ ዘጋህ:: ሰው እየገፋህ ሲያልፍ ታያለህ? ብሰማህም ስርዓት አበላሽ ያለህ የለም::"

"አየህ ፍርሃትህን በስልጣንህ እየጋረድክ ነው:: አዲስ ሓሳብ ማምጣት እንዳልቻለ ዶክተር:: ሁሉ በየቦታው አንካሳነቱን መደበቂያ ቴክኒክ አለው......"

አቋረጥኩት::

"ምንድነው የምታወራው? በል ዞር በል" ቶሎ እንዲሄድልኝ፣ ወደ ልጅቷም ለመሻገር ፈለግሁ::

"አንተን አልወጣኝም"

"ልትሰድበኝ ነው የመጣኸው?"

"ይቅርታ እንደዚያ ከተረጎምከው"

"ይቅርታው አያስፈልግም"

ሌላ ሲጋራ አሰኘኝ:: ወሎዬው የተናገረው ውስጥ የሆነ የሰውነትን ኩረት ነበረ:: ይሄን ዐይነት ሐሳብ አንድ ቦታ ሰምቸው ነበር ግን የሚያምር ዝርዝሩ ትዝ አይለኝም:: አልፎ አልፎም የምሰላቸውና የምደበተው ድርጊት የፈለጉ አካሌንና ነፍሴን በግዴታ እንቄ ስለምይዛቸው ይመስለኛል:: በራሴ የብቸኝነት ጎዳናዬ ላይ ያጋጠሙኝን ሰዎች በግዴታ ከማወቅ ሌላ ሰውን ልወዳጀው፣ ተጋጭቼ ላርመው የፈለግሁበት ጊዜ አልነበረም:: ጓደኛ የመሆን ፍላጎቴ እንኳን ቢኖረኝ በቸልተኛነት አስቀረዋለሁ:: ተጣልቼ አላውቅም:: አፍቅሬ አላውቅም:: በአካባቢዬ የተሳሳተ ነገር ባይ ለማስተካከል ከሰው ጋር መሆን እንዳለብኝ እዘነጋለሁ፣ ወሎዬው ሲያወራ በደንብ አልሰማሁትም:: የሳበችኝን ልጅ እንኳን ረስቼ ወሎዬው ወደ የቀሰቀሰብኝ የሓሳብ አረፋ ውስጥ እንፈራፈር ነበር:: ወሎዬው ትንሽ አስፈራኝ......የማላውቀው፣ ላውቀውም የማልፈልግ ሰው እንደ ዕብድ ተጠግቶ ችላ ብዬው የነበረውን ድክመቴን አንስቶ ሲያብጠለጥል.......

"አሰላቸሁህ መሰለኝ ወንድሜ" አለ ልጅቷ ላይ ሳፈጥ እጅ ከፍንጅ ያዘኝና::



@BOOKALEM

"ደክሞኛል:: ምሳም አልበላሁም" አልኩ እንደ ባንዲራ የሚሰራውን የልጅቷን ቀሚስ እያየሁ:: ትንግርት ነበር::

"በል ልሂድበት:: አሳሰላችሁ" ብሎ እጁን ዘረጋ::

"ወደ የት ልትጠፋ ነው? "

"ሡርግ አለብኝ...... "

"ሡርግ? "

"የልጅ ልጄን እድራለሁ"

"ትቀልዳለህ? "

"ለምን? ምነው? ይልቁን የአንተንም የእኔንም ጊዜ አበለሻሸሁ::"

ሐሳቤ መንገዱን ለመሻገር ነበር:: ልጅቷ ከቆመችበት ተነስታ ወደ ግራ መራመድ ጀመረች:: ወሉዬው እጄን ሊበጠስ እስኪደርስ ለሰላምታ ወዝውዞኝ አለፍ አለኝና ምንገዱን ማቋረጥ ጀመረ:: እኔም ፈራ ተባ እያልኩ ማቋረጥ ስጀምር ወሉዬው በክላክስ ለሚያደናቁሩት መኪናዎች በክንዱ ስድ ነገር እያሳየ ከእኔ ቀድሞኝ አውቶቡስ መጠበቂያው ደረሰ:: ልጅቷ ፈጠን ፈጠን እያለች ከእኔ ስትርቅ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ:: ባገኘትስ ለመሆኑ ምን ላደርጋት ነበር? ምንገዴን አቋርጬ ቀና ስል እንደዚያ የምታምር ልጅ ግራ እጇን ዘርግታ ወሉዬው ጀርባ ላይ እጇን ስታሳርፍ አየሁዋት:: በመገረምና በመደነቅ እጄን አፌ ላይ ሳሳርፍ ወሉዬው ዞር ብሎ አየኝ......እሷን እያቀፈ ሳቅ ብሎ አየኝ:: ምኑ ናት? ልጁ? የልጅ ልጁ? ምኑ ናት? ውሉዬውንና ልጅቷን ከዐይኖቼ እስኪሰወሩ አየሁዋቸው::



@BOOKALEM

# ገነትና ምናብ(3)

*(እናቷ ምቀኛ፣ እህቷ ምቀኛ*
*እኔም ያልታደልኩት ልበ-በሽተኛ)*

አንዳንዴ አለሁብት ትመጣና የቤታችን ሰው እንደተሰበሰበ "መዝገቡ እፈልግሀለሁ" ትላለች:: በኩረ ይበሽቃል......በኩረ ስለሚበሽቅ ብዙ ብዙ ደስ የማይል ነገር ይናገራል......

......ጨረቃን እንደ ብዬአት *(የላሊበላን ዱካ ተከትለን)* ከተራሮች ሁሉ ትልቅ ወደ ሆነው ወደ ዳሽን እንሔዳለን......አንበላም፣ አንጠጣም:: አይርበንም፣ አይጠማንም:: የትም ታይታ የማታውቅ ትልቅ አደይ የመሰለች ጨረቃ ላስታ አምባ ላይ ስትወጣ እናያለን......'ላሊበላ የተወለደው በዚህ ቀን ነው' እላታለሁ:: አንገት ላንገት ተቆላልፈን ስንላሳም......ሲያልፍ የነካን ንፋስ ሁሉ እየገረመው......በስተምዕራብ ዝናብ ሆኖ ይወድቃል:: (የዚህ ንፋስ ጠረን ምን ተለወጠሳ? ምነው አሪቲ አሪቲ አለሳ? ምን ነክቶ መጣሳ? ይላሉ እነ አልሰሜ:: እነ አላዋቂ) ቀያቴ ዕጌዎች እንጥፈን ሰማይና ምድርን ሲመሹ እናያቸዋለን:: ኩሽ ጥቁር ወላንሳ ስትሆን እናያለን......ጐኔ ብርሐን አለች:: ጐኔ እፀ አለች:: ክንዴ ምቹ ነው:: ወዛችን እንደ ምንጭ ከተራራው ይወርዳል:: ወፎች አምላክን እያመሰገኑ ይጠጡታል:: ከጡቶቿ ጠዋት ጠዋት የሚሞቅ ጣዝማ......ቀትር ቀትር የአምበር ጠረን ይወጣል::

ደብተራ ተጠግቶን እንዲህም ይላል:

"ሽብሽባ ላሳያችሁ......ያሬድ አባታችን እንደዘለለው......ለፍቅረኛው እንዳሳመረላት......ቄስ ተፈራርቶ የደበቀውን ማኅሌተ-ገንቦ......" እንዲህ ተናግሮ በቀጭን እግሮቹ እንደ ደገኛ እየዘለለ ወተት ባጠቡ ጥርሶቹ እየሳቀ ሽብሸባና እስክስታውን ይጎነጉንልናል......የባዶ እግሮቹ ዱካ ሮሓ ጤዛ ላይ......ሙሉ በጋ ሳይጠፉ......



@BOOKALEM

# ያስቀጠር የሚናገር አለ?

ሁሉ ሰው ለነገ ያስባል:: የመጨረሻው ግድ የለሽ ነኝ ባይ ነገን እያሰበ ይጨነቃል:: እንቅልፍ ይነሳዋል:: ዛሬ ማንም ሰው ሲተኛ ነገ እንደሚነቃ ጠብቆ ነው:: እራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች እንኳን ነገን አስበው ነው—ነገ እንደማይቀናቸው አስበው ነው--የነገው መልከ ቀና ቀጠሮ እንደማይሰምር ተሰምቷቸው ነው:: ለነፍሴ አደርኩ የሚሉ ቅዱስ እንኳን ነገ፣ ከነገ ወዲያ መምጫው የማይታወቅ እግዚያብሔር በመንግስቱ እንዳይረሳቸው ይመኛሉ......ዛሬ ደግ ይሠራሉ፣ ዛሬ ይራባሉ፣ ዛሬ ይጠማሉ፣ ዛሬ ይቀድሳሉ፣ ይዘምራሉ፣ ዛሬ ይመፀውታሉ፣ ዛሬ ዛሬ ደግ ይናገራሉ:: ጉንዳንና ነፍሳት ዛሬ በዚህ በጋ ለፍተው ማስነው ለክረምት መኖአቸውን ይደብቃሉ:: መንቆረሪቶችና ጉርጦች በጋ ሲመጣ አፈር ለብሰው ክርመው በጋ አልቆ ጠል መውረድ ሲጀምር ከተኙበት ይነሳሉ:: ነገ የሚዘነጋ አይደለም:: ነገ ለዓለም ሕዝብ ሕመም ነው:: ከፕሬዝዳንት እስከ ለፕሬዝዳንት እስከሚያጨበጭበው:: ከሰው እስከ እንስሳት የነገ ነገር የማያብሰለስለው የለም:: ቢለያይ «የነገዎች» እርዝመት ነው:: ቢለያዩ ሊሰየም በሚከብድ ደረጃቸው ነው እንጂ የነገ ነገር የማያስደነግጠው የነገ መምጣት የማያባባው የለም::

እኔ ግን የቂል ሥራ መስራቴ......ገነትን ያገኘሁዋትና ቤቴ የጋበዝኳት ዕለት ሳልቀጥራት ቀረሁ:: ይህ አድራጎቴ ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ ነበር:: ስለ ነገ አለማሰቤ ብቻ ሳይሆን.......ነገን ዛሬ ሆኜ አላዘዝኳትም፣ አልተቆጣጠርኳትም:: ዛሬ ሆነው ነገን፣ ከነገወዲያን የሚመጣውን ዓመት የያዙ ናቸው ብልሆች:: አስቤው ነበር ግን አላደረኩትም:: ማሰብ ምን ይሰራል? የጭንቅላት ውስጥ ጉም ምን ይሰራል? ጠዋት ላይ ቆጨኝ:: ሁለተኛው ቀን ላይ ቆጨኝ:: ሦስተኛው ቀን ላይ ቆጨኝ:: በሁዋላ እየፈራሁ......የቂልነቴ ክብደትና ስፋት እየጉላ ቢጫነኝም የአለማየሁን አብሻቂ ግፊት እንኳን ችላ ብዬ ሣምንት ያህል ሳልጠይቃት ቆየሁ::

ሥነኛ ድርጊት አልነበረም::

አንድ ቀን ቅዳሜ ከሰዓት በሁዋላ እያመነታሁ (ትንሽም እያፈርኩ) እሷን ፍለጋ ቤቷ ሔድኩ:: ቅዳሜ ከሰዓት በሁዋላ ያውም አርፍዶ:: ቅዳሜ ጥሩ ቀን አይደለም:: ቅዳሜ ከሥራዬ ዙረት እንዳየሁት ቂጧ የሚያርፍ የአዲስአባ ሴት ያለች አይመስለኝም:: የአዲስአባ ኩል የሚያልቀው ያኔ ነው:: ቤቷ ያለበት ግቢ ስደርስ ፊት ለፊቱ ሕፃናት ሲጫወቱ አገኘሁ:: ከተሰበሰቡት ሕፃናት አንዷ መሯሯጧን አቁማ ፊቴን አተኩራ አየችኝና እየሮጠች ወደ ግቢው ውስጥ ገባች:: ስትጣራ እሰማታለሁ:

"ግኒ! ገኒ! ገኒ! ሰው ይፈልግሻል"



@BOOKALEM

ምን መሆኗ ነው? ዝም ብዬ ባልፍስ ኖሮ? ለስፖርት እንደመጣሁስ? ለአበበ ቢቂላ ስፖርት ቀን የፍጥነት እርምጃ እየተለማመድኩ እንደነበርስ?

የልብሴን ሁኔታ ተቆጣጠርኩ:: ጂንስ ጃኬቴ ንፁህ ነበረች:: ቡናማ ሸሚዜ ከአንገትጌው ዝቅ ብሎ ያለችው ሁለተኛዋ ቁልፍ ወድቃ ተከትላት ያልጠፋችው ቆንጥጣ ይዛት የነበረችው ትንሽ ክር እንደ ደረቅ ንፍጥ ተቀምጣለች:: እሷን ለማውጣት እየጐተትኩ ገንት እስክትመጣ ጠበቅሁ::

የገንት ድምፅ ከሩቅ: "ማነው?"

ወደ ግቢው በር ቀረብ አልኩና ፊቴን ብቻ በበሩ ጮለቅ አደረግሁ (ለምን ፊቴን ብቻ?):: ተያየን::

"መዝገቡ ነህ? ግባ!"

እንድትወጣ በእጄ ጠራሁዋት::

"ወጥ እየሰራሁ ነው.......ምች ቢመታኝስ በዚህ ፀሐይ"

ገባሁ:: የሸሚዜን የክር ጉንድሽ ብስባት አልወልቅ አለች:: ብዙ ጊዜ ልቦናችን የአንድ ጠቃሚ ያልነው የሆነ ጉዳይ ዕምብርት ላይ ሲያተኩር ዳር ዳር ያለ ጠቃሚ ነገር ይስታል::

ለሠላምታ ጥርሶቿን ብቻ አሳየችኝ:: አ ጥርስ::

አንገቷና እስከ ጡቶቿ የላይ ጠርዝ ድረስ ራቁቷን ነበረች::

ላብ ችፍ ብሉባታል:: ሁለቱም እጆቿ ሊጥ ተነክረዋል::

"እንጀራም እየጋገርኩ ነበር" አለች::

ስገባ ቤቱ እንደ ምድጃ ግሎአል:: አጭር ያረጀች ግን በግማሽ ያልሸፈነቻት ቀሚስ ለብሳለች:: ማር የመሰሉ ባቶቿ ሊጥ ተንጠባጥቦባቸዋል:: ባጥብላት እወዳለሁ:: እያንዳንዷን ፍንጣሪ እየለቀምኩ.......ወተት ወንዝ ዳር አስቀምጬ ባጥባት እወድ ነበር::

"ትኩስ እንጀራ ልስጥህ"

"የምትሰሪ ከሆነ አልረብሽሽም"

"ምን አለበት አትረብሽኝም:: ብትረብሽኝስ?"

የቤታቸው ግድግዳ ጭቃ:: ወለሉ የተበታተነ ሰሌን:: ጣሪያው ያለ ኩርኒስ በጭስና በዕድሜ የጠቆረ ቆርቆሮ ነው:: ፊት ለፊቴ የአንዲት ልጅ እግር ሴት ፎቶ ተሰቅሏል:: ፎቶው ዙሪያ ጥቁር ጨርቅ ተጥሏል:: ከጐኑ ይህቺው ሴትዮ ከአንድ ጠቆር



@BOOKALEM

.ያሉ ሰውዬ ጋር ጉን ለጉን ሆና ፎቶ ግራፍ ተነስታለች፡፡ ጉን ለጉን ሆነው ለፎቶው የሚሻሙ ይመስላል፡፡ የሁለቱም ዐይኖቻቸው ቀጥ ድርቅ ብለው ወደ ፊት ያያሉ፡፡ ሰውነታቸው በፍፁም ተመልሶ እንደማይላላ ነበር፡፡ ሴትዮዋ እናቷ፣ ሰውዬው አባቷ መሆናቸውን መገመት አላቃተኝም፡፡ ወደ ጊዳ ገብታ ስትመለስ......እየተናፈጠች......

"ሻይ ላፍላልህ እሺ."

"እሔዳለሁ......"

"ለምን መጣህ ታዲያ?"

ምን ልበላት?

"ላይሽ"

"ወይ አንተ ልጅ" ሳቅ ሞከረች፡፡ በከንፈሮቿ ብቻ፡፡

"ለምን ነገ አንገናኝም?" (የቸኮልኩ ይመስለኛል......ግን ሌላ ምን ማድረግ እችል ነበር?)

"ነገ? ነገ? ነገ አይመቸኝም"

"ለምን?"

"የምሰራው አንዳንድ ነገር አለ"

"ምን?"

"ምን አውቃለሁ፡፡ አባቴ የሚለው ነገር ምን ይታወቃል"

ዝም አልኩ፡፡ ተመልሳ ማድ ቤት ገባች፡፡

"እኚህ አባትሽ ናቸው?" ቢገባኝም ለወሬ፡፡

"አዎ......ሴትዮዋ እናቴ ናት፡፡ ዕድሜዬ ስድስት ሲሆን ነው የሞተችው"

እናቷ ከመስታወቱ ውስጥ ኩስተር ብለው እኔን የሚያዩ መሰለኝ፡፡ ዐይኖቻቸው አልለቀቁኝም፡፡

ፊቴን አዞርኩ፡፡

"መቼ ይመችሻል?"

"እኔ እንጃ!"

"ነገ ከሰዓት በሁዋላ ብንገናኝስ......ልምጣና አብረን ንፋስ እንቀበላለን" (ስራዬ ንፋስ መቀበል እንዳልሆነ-ጉድ እቴ)



@BOOKALEM

"ሞክር እሺ.......የምሰራው ከሌለኝ......."

"አሁን ልሒድ እንግዲህ......."

"ትኩስ እንጀራም እንቢ አልክ.......ሻይም እንቢ አልክ......"

እጇን አጭር ቀሚሷ ላይ እየጠረገች ልትጨብጠኝ መጣች::

የሆነ ነገር ሳበኝ:: የሆነ ነገር ጐተተኝ:: እጇን ከመያዜ በፊት ፊቷን በሁለት እጆቼ ይዤ ጉንጯን ሳምኳት.......

"ሒድ ወዲያ!" ኩስተር ብላ እንደሚናደድ እየተፋናጠረች::

የሆነ ስሜት ከአፌ ከአፍንጫዬ ከጆሮዬ ከፊቴ የጀመረ በመላ ገላዬ እንደ አንዳች ተራራ ሸርሸሮ እንደሚጥል ጐርፍ ተሰራጨ:: ነገ ዐይኖቼ ስር እንደ አሳዛር ከጉድጓዷ ወጥታ ስትቆም እየሁዋት.......



@BOOKALEM

# ከሁለት በላይ መዋስ ለትችለም

ወመዘክር ሔጄ አራት መፃሕፍት አቅፌ እንደቆምኩ አንድ ስስ ከናፍርትና ሞጣጣ ፊት ያለው ነገረኛ የሚመስል ሰው ከተቀመጠበት ሳይነሳ (ወገቡ ሕመምተኛ ሳይሆን አይቀርም፣ ወይም እግሩ ቁርጥማት ነበረበት)

"ከሁለት መፃሕፍት በላይ መዋስ አትችልም" አለኝ። (በዐይን......እስኪመረር ያውቀኝ ነበር እኮ)

እኔ የመሰለኝና የፈለኩት በሙሉ የብርሐኑ ዘርይሁንን መፃሕፍት በአንድ ጊዜ አውጥቼ ደግሜ እስኪበቃኝ ለመከስከስ ነበር። ሰውዬው ይኼን ሲነግረኝ በሽቄ ልሞት። ጥዬው ወጣሁ። አንገቴን ደፍቼ ጥዬው ወጣሁ። ያልገባኝ ነገር ግን ሽጉጤ ስድስት ጥይቶች አሉት። መዋስ የተፈቀደልኝ መፃሕፍት ሁለት ብቻ ናቸው።

ቁርጥማታሙ/ወገበ ሰባራው: "ከሁለት መፃሕፍት በላይ መዋስ አትችልም" ብሎ ሲናገር ፕሬዝዳንት ይመስል ነበር።

ፊቴን እንኳን ማየት የተጠየፈ ይመስል ነበር......ያልበሰለ ሕጉን በቃሉ ሲያነብ።



@BOOKALEM

# ሦስት ዘቢብ ኬኮች

ከገነት ጋር (የመጀመሪያ ቀጠሮአችንን) መርካቶ ሸገር ለሁለት ሰዓት ያህል አብረን ቆየን:: ብዙ የማወራው አልነበረኝም:: እሷ ግን ትሽኰረመማለች:: ስትሽኰረመም ታምራለች.......ዐይኗን ስትዘቀዝቅ የሽፋሽፍቷ ጫፎች ጉንጯ ላይ ጥላ ይወረውራሉ ልበል? እግሮቿን ግራና ቀኝ ከፊት አድርጋ ተቀምጣ ቀሚሷ ሲወጠር ጭኖቿ እንዳይጋለጡ እጆቿን ከመሐላቸው ጣል አድርጋ ቅርፃቸውን ሳይ.......ማየት ብቻ ደስታዬ ሆኖ......የለበሰችው ጥቁር ቀሚስ ነበር:: ከላይ የደረበችው ቀይ ሹራብ:: የቀሚሷ ጥቁረት ከእግሮቿ ወጥኔ ቀለም ጋር......ቀይ ሹራቡ ከከንፈሮቿ ብስለት ጋር-- ታዲያ እኔ ሦስት ዘቢብ ኬኮች በላሁ::

......የምሰራው ቢጠፋኝ::

ወደ ቤቷ ስንመለስ እጅ ለእጅ ተያይዘን ነበር::

አልፎ አልፎ በሰራ ገላዬ ክንፍ ክንፍ የሚያሰኝ ደስ የሚል ንዝረት ይሰማኛል:: ዐይኖቼን ወደ ሰመመን በተጠጋ ስሜት እከድናለሁ:: በዐይኖቿ ታቀላምጠኛለች፣ ታሽበለብለኛለች:: ሳላቋርጥ እጎመዣለሁ:: እንዲያ የመሰለች ልጅ ትታኝ እንዳትሔድ ገና ከመጀመሪ እፈራለሁ::



@BOOKALEM

# ቡት ጫማ

ከዮት እንደመጣ ለረዳው ያልቻልኩት የማማር የመዋብ ፍላጐት ከጠዋት እስከ ማታ ይጠናወተኝ ጀመር። እንደ ሕመም ነበር። እንደው ሕመም እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። ጠዋት ብርኤባዬን ከማድረጌ በፊት ሱሪዬን ከማጥለቄ በፊት ሸሚዜን ከመደረቤ ቀድሞ ፊቴን በሳሙና እታጠብና (አድርጌው የማላጠቀው ነገር) ፀጉሬን ሙልጭ አድርጌ እበጥራለሁ.....ከባድ ዐይነት ሙልጭ። እንደዚያ ቶሎን እያውቅም። ቀድሞ በጥሞና አይቸው የማላውቀው ፊቴን በጥንቃቄ ማጥናትና መረዳት ቻልኩ። ትላልትና ጥቋቁር ዐይኖች አሉኝ። አፍንጫዬ ቀጥ ያለ ነው። ከሜቴ ትንሽ ዘንበል ያሉ። አፍንጫዬ ስር ስስ ብን ያለች ሽንጉበት አለች። ስገለፍጥ የማየው ነጫጭ ቀጥ ያሉ በቆሎ እሸት የመሰሉ ጥርሶች ነው። የድዶቼ ጠርዝ ይቀላል። ጉንጮቼ ብዙ ፂም የላቸውም። ከሁኔታው ፂም የሚበቅልባቸውም አይመስልም ነበር።

አንድ ቀን ጠዋት ፊቴን አይቼ ሳበቃ የጠባዬ መለወጥ ገርሞኝ ሳቅ አልኩ። ጉንጮቼ ስርጓዳ እንዳላቸው ተገነዘብኩ። ከዚያ በኋላ ጠዋት ጠዋት ጉንጮቼንና ጥርሶቼን በመስታወት እያየሁ እስቃለሁ። ስርጓዳዎቼንም እየቸዋለሁ። አንዳንዴ ጥሩ አድርጌ ከገሸለጥኩ አንድ አንድ ሳንቲሞች ያክላሉ። አንገቴ ከብ......ዙሪያውን ስንበሮች ያሉበት ነው። የእናቴ ፀጉር ግንባሬ ድረስ ይመጣል።

መስታወቱ ከዚህ የበለጠ አያሳየኝም።

ቀን ቀን ስዞር ቁመናዬን በሕንፃዎች መስታወት ገልመጥ እያልኩ ማየትም ጀመርኩ.....አንዳንዴ ሥራ እንዳለበት ጠባቂ ጥሩ የሚያሳይ መስኮት ፊት ለፊት እየተንጐራደድኩ እቆማለሁ። ከሕንፃው ውጭም ዐይኖች ሊኖሩ ይችላሉ። ጉርደድ እያልኩ፣ ገልመጥ እያልኩ ቁመናዬን አያለሁ። ድሮም አየዋለሁ ዩኒፎርሜን ሳስተካክል። ያን ጊዜ የማየው ግን የጨርቁን አቀማመጥ፡ በገላዬ ላይ ያለውን አወራረድ ነበር። የቅርፊቱን ጠባይ ነበረ። ጠባዬ ተለውጦ ግን የማየው ከጨርቁ ስር የነበረውን፣ የለበስኩትን ጨርቅ ደግፎ አቁሞ የያዘው ገላ ምን ዐይነት እንደሆነ መገመት ነበር። ብዙ ጊዜ አልረካሁም። ታዲያ የአዲስአባ ሰው ለአንድ ደቂቃ ያህል በየመንገዱ እንቀላፍቶ ወይም ታውሮ ልብሴን አወላልቄ እርዝመቴንና አቋቋሜን በነዚያ ታላላቅ መስታዎቶች ውስጥ ማየት እፈልግ ነበር።

አንድ ቀን ጠዋት ስነሳ በድንገት የለበስኩት ልብስ አስጠላኝ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከገንት ጋር ቀጠሮ ነበረኝ። ሱሪዬ ባለሰንበር ቴትሮን፡ ጃኬቴ የሆነ የታይዋን የውሸት ቆዳ ጃኬት (ካምሱር ይበዛዋል) ነበሩ። ሸሚዜ ነጭ ሆኖ ክሳዱ መበለዝ የጀመረ፣ ጫማዬ ርካሽ የጎማ ስኒከር......በጋ በጋ የሚሞቅ፣ ክረምት ክረምት ተጨማደ



@BOOKALEM

እንደ ጊንቲ የሚጠብ ነበር(ከሁሉ ልብሶቼ የበለጠ ያስጠላኝ):: ብዙ ጊዜ ልለውጠው አስባለሁ፡ «ከለወጥኩት ደግሞ ተረከዘ-ረዥም በሆነ ጫማ ከሆነ ነው» እል ነበር ለራሴ:: 'ሒል' የሚባል ተረከዘ-ረዥም ጫማ እወድ ነበር:: 'ሒል' ብቻ ሳይሆን ጫፉ ሾል ያለ፣ በዚህ ላይ ጥቁር......ቀለም ሲቀባ እንደ አሳበው የኩንኙ ሰው ማብለጭለጭም ነበረበት:: ማብለጭለጭም ብቻ ሳይሆን ሲታይ ደስ እንዲል ያስፈልግ ነበር:: ሲታይ ደስ እንዲል ብቻ ሳይሆን ምርጫዬ መደነቅ ነበረበት፣ ምርጫዬ መደነቅ ብቻ ሳይሆን ዋጋውን በሰዎች መጠየቅ ነበረብኝ:: ዋጋውን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን 'እግዛህበት ቦታ ውሰደን' መባል አለብኝ፣ 'እቦታው ውሰደን' መባል ብቻ ሳይሆን 'በእናትህ' ብለው መለማመጥም ነበረባቸው::

የሆነ ሰኞ ጠዋት ታዲያ በቀጥታ መርካቶ ወጣሁ:: በሐሳቤ የሳልኩትን ጫማ ለመፈለግ ብዙ፣ ብዙ ባዘንኩ:: በመጨረሻ በሰባ ብር የተመኘሁትን የሚጠጋ አመዴ ዝበያ አግኝቼ (ኬኩን ከበላን ጫማውን ለምን አናደርገውም? እንደ ማለት) ገዝቼ ቤቴ ተመለስኩ:: እቤቴ ውስጥ ለሙከራ ስዘዋወር በመጀመሪያ የታዘብኩት ነገር የጫማው ተረከዞች ጣውላውን ሲመቱት የሚወጣውን ድምፅ ነበር:: ቁመቴ ዘለግ አለ:: ምናልባት ገነት 'ሒል' በገነባው ቁመቴ ከትከሻዬ ወረድ ትል ይሆናል::

ማታ ሰፈሯ ሔጄ ለጥቂት ጊዜ ቤቷ ደረጃ ላይ ከተጫዋወትን በሁዋላ ስለናበታት ገነት ጫማዬን እንደወደደችው ነገረችኝ:: ምናልባት ጫማዬን ላሳያት የሔድኩ እንዳይመስልብኝ ፈርቼ ነበር:: ፈራሁ:: ገነት እንደዚያ የምታስብ አይደለችም:: እንደ ወደድኳት የምታውቅ ይመስለኛል:: ገነት ሐብት አልነበራትም:: ገነት ግን ሲሚንቶ ከመሰሉ ከጉደፉ ጨርቆቿ ውስጥ ከብዙ ደመናዎች መሐል ብቅ እንደምትል ፀሐይ ነበረች::

ማታ ቤቴ ስገባ በመጀመሪያ ማንም የሰማው ጫማዬ ወለል ሲመታ የሚወጣውን ድምፅ ነበር:: በተለይ በኩሬ መንሻ 'አገኘና 'የብረት ጫማ ስለማድረግ' ያወራል::

"ለምን ለሠራዊቱ የብረት ተረከዝ ያለው ጫማ አይሠሩልንም፡ ይቆጥብላቸዋል"

ሽሙጡን::

እንዳልገባው ልብሴን አውልቄ ተኛሁ:: በኩረን በጣም የሚያበሽቀው ከምሰራው ድርጊት ይልቅ ዝምታዬ ነበር መሰለኝ:: ምን እንደማስብ ባለማወቁ እየተበሳጨ ይሆናል:: ሌሊት ትዝ ያለኝ ለራሴ ጫማ ስገዛ ለገነት አንድ ነገር መግዛት እንዳለብኝ ነበር:: ታዲያ አልነጋ አለኝ.......

እንደዚያ እንደ እኛ ሰፈር ጭምልቅ ያለ ድምፅ በሌሊት የሚወጣው ቦታ አዲስ አባ ውስጥ ያለ አይመስለኝም:: ውሻውና ኡኡታው:: አንድ ኡኡታ ይጀመራል ከዚያ ውሾች ከላይ እስከ ታች ምን ይጠበስ ብለው እንደሆን አላውቅም ጩኸታቸውን



@BOOKALEM

እየተቀባበሉ ሰው ሊያሳብዱ ይደርሳሉ:: የበለጠ የሚያበሽቀኝ......ጩኸቱ የጀመረው ዳርማር ጫማ ፋብሪካ አጠገብ እንደሆነ ከስፈሬ ጩኸቱን ዘግይቶ የተቀበለው ነጭናጫ ውሻ እስኪነጋ ማላዘኑ ነው:: የሰው ኡኡታው አንድ ጊዜ ነው:: ያለተቀባይ:: ያው እኛ መችም የሰማነውን ኡኡታ ሁሉ ፖሊስኛ እንተቻለን («ይህቺ ባሏ ደብድቧት ነው»— ከአንድ አቅጣጫ የሚመጣ እተነሳበት የሚንከለከል የሴት ድምፅ ከሆነ:: «ይሄ ሌባ የምታባርር ተዘራፊ ሴተ-ላጤ»......ቀጭን አቅጣጫውን የሚለዋውጥ ድምፅ ከሆነ:: «ስለምንድነው በእናታችሁ የእኛ አገር ወንጀለኛ—ወንዶች፤ ኡኡ የሚሉት ደሞ ሴቶች የሆኑት?» ሴቶቹም ያውቃሉ......ወንጀለኛ ወንድ ሲሮጥ ሌላውም ወንድ በዝምታ ወንጀለኛውን ተከትሎ ሲሮጥ እሷም ሴቴ ከሁዋላ ሁዋላ እየተከተለች ድምጿን እንደ ዘፋኝ እየሰነጠቀች):: ከአንሶላችን ጋር እንደቀለጠ ዕጣን ተያይዘን የአምስታችንም ወንጄ ጠረን ቤቱ ውስጥ እንደማይታይ ጉም እየተንሳፈፈ:: አንዳንዴ ጠዋት ስነሳ ታዲያ ትንሽ ቡችላ አብራኝ እንዳደረች ሁሉ ቡፍ፣ ቡፍ የሚል ድምፅ ጭንቅላቴ ውስጥ ይነሳብኛል::

ጆሊው አለማየሁ እንኳን ጫማዬን አመስግኖ ተቸው:: ስለ እኔና ስለ ገነት ግኑኝነት አላወራሁትም:: ለማውራት በትንሹ አፍሬአለሁ:: በሌላ በኩል ደሞ ገነትን መጥበሴ የእሱ ጥረት ብቻ ተደርጐ እንዲተረጎምብኝ አልፈለግሁም:: እሱም ይሔን ፈልጐ ይሆናል ብዙ የማይነዘንዘኝ::

"ያ እንዴት ነው?" ሲለኝ

"ምንም አይል" ከማለት በስተቀር የዳበረ መልስ አልሰጠውም ነበር:: አንዳንዴም ስለሚያስፈራኝ ነው:: 'ምንድነው እሱ አላበዛውም?' ብላ ገነት የነሲብ ምክንያት ፈጥራ ብትዘጋኝ ብቻዬን እቆጭ እንደሆን እንጂ ሁኔታውን ተጠቅመው የሚያበሽቁኝ ወይም 'ልዘንልህ' የሚሉ ሰዎች አይፈጠሩም::

እንግዲህ ሜዳው ላይ እኔና ገነት ነበርን:: ሜዳ ላይ እንደ ጥጥ የለሰለሰ ቆዳዋን ለብሳ፣ ለምለም ሳሯን እየነጨች፣ ደጉስ ያለች ላቷን ግራና ቀኝ እያወዛወዘች አልፎ አልፎ 'ባእ' 'ባእ' የምትል......ገነት:: እኔም ጠመዝማዛ ቀንዶቼን አሹዬ ቀይና ነጭ ጠጉሬን ለብሼ ላቴን እያወዛወዝሁ ራሴን እየነቀነቅሁ እንደ ሙክት እግሯ ስር የሚወድቀውን ውሐ አሸታለሁ......ፊቴንም ወደ ፀሐይ መጥለቂያ አንስቼ የሚያማምሩ ጥርሶቼን እገለፍጣለሁ:: ከሩቅ ዘንጉን ይዞ የቆመ እረኛ ነኝ ባይ በኩረ እንደሰፈራችን ውሾች ይጮሃል:

እኝእኝእኝእኝ::



@BOOKALEM

# ለድባርና.......

በዚህ በኩል የእኛ ቤት አለ አይደል--እንዲህ ከተሰለፉቱ አንዱ:: በዚያ በኩል ደ'ሞ ሌሎች ቤቶች ነበሩ--በነገረ-ሥራቸው ከእኛው የማይለዩ:: ግራና ቀኛችን ለመቶ ሜትሮች ያህል ቤቶች:: ቤቶቹ በሙሉ ትናንሾች ሲሆኑ የሚኖረው የሕዝብ ብዛት ግን የጉድ ነበር(ዛሬም እንዲያ ነው):: በዐይን ብቻ የማውቃቸው ኑዋሪዎች ብዙ ነበሩ:: ሠላም የምላቸው ጥቂት:: ቆሜ የማወራቸው የበለጠ ጥቂት ነበሩ:: በጅምላ ሕይወታቸውን መረዳት አይቻልም:: ይከብዳል:: በአንድ ጊዜ ሁሉንም የማያቸው ለሰፈርዋ ቆሌ ሲደግሱ ነው:: እዚያ አድባር ላይ የነበረው የተሰብሳቢው መጠን እንዴት እንደተወሰነ ግን አላውቅም:: እኔ ስገምት ቆሌዋን ለማክበር ይመጡ የነበሩት በመንገዱ የመቶ ሜትሮች ዕርዝመትና ስፋት ላይ የሚኖሩ ይመስለኛል:: ግንቦት ልደታ ቀን ማታ ከአስራሁለት ሰዓት ጀምሮ በየዓመቱ መንገዱን መሐል ላይ በሶስት ጉልቻ፣ በገላዎቻቸው፣ በብረት ምጣዳቸውና በቡና ማፍያቸው ይዘጉታል:: ሁልጊዜም እንገቴን ሰብሬ ሳልፍ ስል ይጠሩኛል.......

ጠሩኝ::

ከዚያ አካባቢ ውጭ እዚያ መጥቶ ንፍሮ የሚቅም ሰው ያለ አይመስለኝም:: የድንበር አፈጣጠሩ ይገርመኛል፣ ያሳፍረኛል:: በዚህ ምንገድ ከሚኖሩ ሰዎች ልጁ ያልሞተበት አልነበረም:: እንደሰማሁት:: የሚጋሩት ሐዘን አለ:: ወፍራም ሰው የለባቸውም......ብዙዎቹ ፊቶቻቸው የተመጠጡና የበለዙ ወንዶችና ሴቶች ናቸው:: ዝም የሚሉ ዐይኖቻቸውን እሳት ላይ የሚተክሉ የተሸነፉ አባወራዎች ያሉበት ነበር::

የአድባሩ ንፍሮ የሚበላው በቡድን ነው:: አልፎ አልፎ ከቀና ላይ ስሻማ ነጩ ሰንዴ ከምር መሐል የሚገቡት፣ ገብተው የሚፍጨረጨሩትና የሚዘግኑት ብዙዎቹ ጣቶች ጥፍራቸው ያልተቆረጠ......ቆሻሻ የሰበሰቡ.......አንዳንድ ጊዜም የእሳት ጠባሳ የማይጠፋቸው ነበሩ::

ዙሪያችንን ሕፃናት ይጫወታሉ:: መንገዱ ቢመሽም ሙቀቱ አልጠፋም:: የእኛ ቤት በር ተከፍቶ ነበር:: በዚያ ክፍት ወፍራም የ40 ቁጥር ሻማ አምፖል ብርሐን ጨለማው ምንገድ መሐል ነጭ ቁመተ--ረዥም አራት ማዕዘን ቀዳዳ መስሎ ወድቆአል:: ከዋናዎቹ ሁለት ጐዳናዎች ከላይም ከታችም ብዙ ድምፅ አይመጣም:: የንፋስ መውጪያ የግራር አድባር ትዝ አለችኝ:: ጀርባዬን ይበርደኛል:: ምናልባት ንፋስ በጐዳናው ውስጥ እንደ ወንዝ ይፈስ ይሆናል:: ፊት ለፊቴ የተቀመጠ አሰፋ የሚባል የጐረቤታችን ሰው በስተግራ ካለው ቤት የሚኖር እፍኝ እፍኝ ንፍሮ እየዘገነ በአፉ ቀዳዳ ያስገባል.......ጉንጩ እንደ ቡጢ ያብጣል.......ዐይኖቹ ብርሐን ገብቶባቸው እንደማያውቁ



@BOOKALEM

መንታ ጉድጓዶች የሚመስሉ.......የእሳት ብርሐን አልፎ አልፎ እየወደቀባቸው እነዚህ ጉድጓዶች ውስጥ የተጨማደዱ ተጋልጠው ሊወጡ የፈሩ የብርሐን ብልጭታዎች.......ግንባሩ ላይ ግራና ቀኝ ላይና ታች መስመሮችና ረባዳዎች.......ፊቱ ብድር ይመስል ነበር:: ብድሩን ያልከፈለ ሰው ፊት ይመስል ነበር:: ምናልባት እንደ ሁላችን ፊት:: አድባር ለመድረስ ካልተመቻት ሴትዮ ደሳሳ ቤት ሩካቤውን አጠናቆ የወጣ ወንዳታ ፊቱን በታላቅ ጥረት አንገቱ ውስጥ በዕፍረት የደበቀ.......እሱንም እንደ ማጋለጥ የሚከተል በጨለማ ውስጥ እንደ ቁራ የሚበር ልቅላቂ ውሐ.......ወርቅ ወንድነቱ አልማዝ ሴትነትዋ ጎዳና መሃል ሊሰበር.......በታችኛው ምንገድ ቀዝቃዛ ፖለቲከኞች በቀዝቃዛ ቶዮታ ክሩይዘር ያልፋሉ:: ትኩስ የጠገበ ሻኛቸው እንደ ፍሬቻ ያበራል:: የጉፈሬአቸው ጫፍ እንደ ክብሪት የተለኮሰ ነው:: ኸረው ብለው ሲያልፉ ባሕላቸው ሳይሆን አይቀርምና የብርድ አዙዋሪት ይሰራሉ::

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ነበር:: ከማታ ትምህርት ቤት የምወጣው በዚህ ሰዓት ነው:: ደብተሬን ሳስቀምጥ ብዬ ምክንያት በመፍጠር ቤቴ ገብቼ ለመተኛት ወይም ራቴን ልብላ ብዬ ጫልቱ ዘንድ በመሔድ ከዚያ የአድባር ስብስባ መሸሸ ፈለግሁ:: የአሰፋ ፊት ግን እንደ ታላቅ ቅዱስ መፅሐፍ ተከፍቶ.......

"ውጋት ነው:: የሕይወት ታሪክ ውጋት ነው:: የሕይወት ታሪክ የጀርባ ውጋት ነው:: እዚያ እሳት ዙሪያ እንደ ዶሮ ተሰብስቤ ንፍሮ የምበላው ውጋቴን ለማሸት ነው:: አታየውም እንጂ የገላዬ ቆዳ በየቦታው ተቀዳዶአል:: በቆሌ በዓል፣ በትንሽ ቀልድ፣ በፌዝ ክር ነው የምሰፋው:: የደረት አጥንቶቼ በስጋ የተያያዙ የበረዶ ዘንጉች ናቸው:: ልቤ በዕዳ ሙሉ ነው:: ንፍሮ ያልያዝኩበት እጄ በደመወዝ የሞዴል ፎርሞች፣ በሠፈር የአራጣ አበዳሪ የሥምምነት ወረቀቶች ታስሮአል.......ሲመሽ የቀረ ጉልበቴን ሚስቴ ላይ አፈሳለሁ:: ልዩነታችን ምንድን ነው? ተጉዘን ተጉዘን የምናርፍበትን እኔም አንተም አናውቅም:: እነሆ የልጅነት ተስፋዬን ለአገሬ ሰጠሁ፣ ጠጋ በል ወንድሜ ጠጋ በል......ለቃቅመን እሳት የለኮስናቸው እንጨቶች ይሙቁህ:: አትፍራ:: እኔና አንተ የምንፈራው የለም:: ጫማ ለብሰን፣ ጨርቅ ደርበን የምንዞር ሬሳዎች ነን".......የሚለኝ መሰለኝ::

መሔድ አፈርኩ:: ለመሳቅ እየሞከርኩ ምንገድ ዳር ድንጋይ ላይ ቁጭ ብዬ ንፍሮ መሻማት ጀመርኩ:: ጥቂት ሕፃናት ሊዘፍኑ ይሞክራሉ:: ብስማቸውም ግድግዳ እውስጤ እንዳለ ይታወቀኛል......ከትንንሽ ድንጋዮች የተሰራ እድሞ......የእነዚህ ሕፃናት ድምፅ እንደ ውሐ ሊሸረሽረኝ ሲሞክር እሰማዋለሁ......የድምፃቸው ክንድ እስከ እንጦጦ እንደ ላስቲክ እየተሳበ ሲወጣ......ወፍራም የዋሕነት ነው:: ወፍራም እንደ እንጉቻ የሚጎመድ የዋሕነት ነው:: የሰፈሬ አርማ ተስፋ መቁረጥ ነው:: አንድ ልጅ ወደ ተቀመጥኩበት መጥቶ ግራ እግሬን አቀፈኝ:: ምን እንደሚፈልግ አላውቅም:: ደብተሮቼን የያዝኩበት



@BOOKALEM

እጄን አልበኛል:: ነጠላና ኩታ የደረቡ ልጃገረዶች መጥፋት የጀመረው እሳት ዙሪያ ለመዘፈን ጭብጨባ ጀምረው እየተፋፈሩ ከመሐል ይቆማል:: 'አንቺ በይ' 'አንቺ በይ' ይባባሉና ከመሐል በወሬ የተሳሰረ ፀጥታ ይመጣል:: በስተግራዬ አንዲት ወይዘሮ ዝናሽ(9) የሚባሉ ሴት ፊታቸውን አንድ እጃቸው ላይ አስደግፈው የእሳቱን ፍም አግድም ያዩታል:: ውስጣቸው እንደበረደ ያስታውቃል:: አንጀታቸው ውስጥ ቀዝቃዛ ርጥብ የጨርቅ ኳስ እንደተቀመጠ ሁሉ ነበር......ስለዚያም ጨርቅ እንደሚያስቡ:: ጥቁር በጥቁር ለብሰዋል:: አጠገባቸው መጥቼ ከተቀመጥኩ ጀምሮ አልተናገሩም:: ሰዎች ከሚቀባበሉት ንፍሮ አልፎ አልፎ ይቆነጥራሉ:: ቡናቸው ላይ ኩስታራ ናቸው:: ቅንድቦቻቸው የጉግ ደጋን ናቸው:: የከሳ ገፃቸው ላይ ሳያቋርጡ የሚያናውዙ አስገራሚ ትላልቅ ዐይኖች አሉ:: አፍንጫቸው ላይ በደብዛዛው ጨለማ ውስጥ አፍጦ የሚታይ በዕርጋታ የሚያንቀሳፋ የማድያት ጥቁር ሊጋግ አለ:: አልፎ አልፎ እንደ ሲጃራ አጢያሽ ይስላሉ:: የሚጫወቱትን ወጣቶች በገለልተኛ ዐይኖች ያጤናሉ:: ከዚያ እሳቱን ያያሉ:: ከዚያ ጥሬ እንዲዘግኑ የተዘረጋላቸውን ቆና በትዕዝብት በጎሪጥ ዐይተው በቸልታ ይዘግናሉ:: ሲያላምጡ የመንጋጋቸው አጥንት ሪጋ ፊታቸው ላይ ቦግ ድርግም ይላል:: ለቅፅበት እዚያ የተሰበሰብነው ሁሉ አደጋ ላይ እንዳለን ገባኝ:: ዙሪያችንን የከበበው ብርድ ጠንክሮአል:: ጥቂት ሰዎች ወደ የቤታቸው እየገቡ ነበር:: ሽሽት?

ቀዝቃዛው ንፋስ በከተማዋ እንደ እንድስትጢ ሲወራጭ አስባለሁ......አንድ ግራጫ እንድስቅጤ ከተማችን ሳንባ ላይ እንደተለጠፈ እስማለሁ:: በእንጦጦ በሽሮ ሜዳ እንድስቅጤ ከተማችን ሳንባ ላይ እንደተለጠፈ እስማለሁ:: በእንጦጦ በሽሮ ሜዳ ሲወርድ......    ስድስት ኪሎ ቤንዚን ሞልቶ የየካቲት 12 አደባባይን ሐውልት ሰብሮ......አራት ኪሎ ቤንዚን ሞልቶ በፒያሳ......ከፒያሳ......መርካቶ......ከመርካቶ በተክለ ሐይማኖት......ማይጨው    አደባባይ......ከማይጨው    አደባባይ......አብዮት አደባባይ......ከዚያ ቦሌ......ከቦሌ......አስመራ ምንገድ......በራሱ ላይ ተረማምዶ......በወሎ ሠፈር......ፖፖላሬና    ቄራ......በቄራ......በኩቶኒ......    ልደታ......ከልደታ    እኛ    ሰፈር መግቢያ አስፋልቱ ዳር አፉን ከፍቶ......ጅራቱ ግን ከእንጦጦ ሳይነሳ::

አድባር ለማመስገን የተሰበሰበው ሰው እንደ ጭኮ ኩረብታ እየተናደ ነው:: ጥቂት ሰዎች ብቻ ቀርተናል:: እኔ በሕልሜ የምኖር ይመስለኛል::

ፊት ለፊቴ አንዲት ጠይም ልጅ: "ከበኩረ ጋር የምትኖረው ልጅ ነህ አይደል?" አለችኝ

"አዎ "አልኳት

"በኩረ አለ እቤት?"

"እኔ እንጃ......"



@BOOKALEM

"አንቺ ምነው በኩረ በኩረ ማለት አበዛሽ......" አለቻት አንዷ ቤ. መንታ(10) ይመስላሉ::

"ምነው አንቺ?" አለች በመሽኩርመም

ብዙ ለመናገር አልፈለኩም::

"ለምን ንፍሮ አትበላም? ስትበላ አላየሁህም" አለችኝ::

"ብዙ በላሁ"

"አድባር ደስ አይልም?" አለችኝ

"አዎ" የምመልሰው አልነበረኝም::

"ደስ አላለህም እ?" አለች ሌላዋ::

"ጫማው ደስ አይልም?" አለች አንዷ

ሁለቱም በሕብረት እግሮቼን ዝቅ ብለው አዩ:: እግሮቼን እንደ ጅራት አልጠቀልላቸው:: ብዙ እንደ ሬድዮ አንቴና የማይጠቀለሉ ነገሮች አሉ:: ሁለቱ፡ ብዙ የሚያወራ ምላስና አዲስ ጫማ ያጠለቁ እግሮች::

ቀዝቃዛ ንፋስ ጀርባዬ ላይ ይሰማኛል:: ይህቺም ቆንጆ ነበረች:: በትዝብቴ ግን ፀጥታ የላትም ብዬ መዘንኩ:: ከአፍዋ የሚወጣው ድምፅ የተፈጥሮ ውበቷን እያጠፋው ነው:: የሚያምሩ ጥርሶች አላት......እንደው እንዲህ በጨለማው ውስጥ እንደማሾ የሚያበሩ:: ዐይኖቿ ይጫወታሉ:: ቀዝቃዛ ንፋስ ከጀርባዬ የመታኝ ይመስለኛል:: አውሬ እንደፈራሁ ሁሉ ወደ ሁዋላ አያለሁ::

"መሸ ልሂድ......ከማታ ትምህርት ቤት እንደመጣሁ ደብተሬንም አላስቀመጥሁ" አልኩ::

"አድባራችንን ወደሃታል ማለት ነው?"

"አዎ......ደህና እደሩ"

አንዷ ልጅ አጠገቤ ያለችው የጠይሟ ጊደኛ እጇን ዘረጋች:: ተንደፋድፌ እጄን ሰጠሁዋት:: ደረቅ ናት:: ቆንጆ ነበረች ግን እሳት ያጥራታል:: እሳት አልነበራትም:: አፍ ነበራት......ወላፈን የላትም......ታስታውቃለች:: ብልጥ ናት:: አንገቷን እንደ መበቅ አደረገች:: ደረቷ እንደ ሳንቃ ሰፋ ይልና ጡቶቿ በእራፊ ጨርቅ የተጠቀለለ በትንሹ ከወይን የተደበቀ (ቡዳ ተፈርቶ?) የሕፃን ልጅ ቂጥ ይመስላሉ:: የቀሚሷ ደርዝ ገደድ ያለ ነበር......ከፊት ለፊት ዘቅዘቅ ከሁዋላ ወደ ላይ የተሳበ:: ተራ ሳቅ ሳቅሁ፣ ትርጉም የሌለው:: ወደ ሁዋላ አየሁ......



@BOOKALEM

እኛ ገብሶች ነን:: እኛ የገብስ ቆሎዎች ነን:: እኛ ከገብስ ቆሎ የተሰራን ዱቄቶች ነን፣ እኛ ቅቤ የተነከርን (ከራሳችን ጭንቀት የታለበ) የገብስ ዱቄቶች ነን:: እኛ የጭኮ ኩረብታዎች ነን.......ከደኖቻችን ከኩረብቶቻችን እንድስቅጤ የበቀለ:: ከፍ ብሎ ከአየር ላይ/ከሰማይ መሐል ታላቅ ጎሚት አፉ ተከፍቶ አየሁ.......እነዚህ ቆነጃጅት እንደሚሰበሩ አውቃለሁ:: ታች፣ በጣም ታች......ታች ወድቀው ተሸራርፈው ያልቃሉ.......እኔም እየተበላ በሚጠፋው ግማሽ ጉኔ እንደ እንሽላሊት ሞቼ የምለብሰውን አፈር እሰባለሁ.......

ብርዱ አንጀት ውስጥ ከበሮ ሰማሁ:: ድቤ አዳምጣለሁ:: እሳት ዙሪያ ተሰፍቸው የተቃጠለ እጆች የቅማንት ዜማ በጭብጨባቸው ይወልዳሉ:: ከዛሬ እስከ ነገ.......ከነገም እስከ ነገ የጨለማ ችቦ ነው በግራጫ ነበልባል የበለፀገ:: አድባሯ ያቺ አሮጊት ልጃገረድ በቀሯት ማውለቢያዋ ትስቅ ይሆናል አልኩ:: መፍነክነኳ በቅሬታ የተተበተበ......

ቤት ስገባ ማንም አልነበረም:: ጓደኞቼ በሩን ከፍተው ምናልባት ጉረቤት ጠላ ሊጠጡ ሔደው ይሆናል አልኩ::

ታላቅ ዲን አድባሯና እንድስቅጤው ሲባሉ ነፍሴ መስከ ላይ ሰማሁ:: መታዘቢያ እንጂ መሮከሪያ ድምፅ አልነበረኝም::

የዚች አድባር ጡቶቿ እንዴት ደርቀው ነበር?

ባቶቿ እንዴት ከስተው ነበር?

ሮጬ ወጥቼ ከሴቶቹ ጋር ልቀላቀል ፈለግሁ:: ወገባቸውን ይዤ አብሬአቸው ልዘፍን ፈለግሁ:: ግን ከልቤ ማዕከል ዘፈን አልፈልቅ አለኝ::

ከዕለታት አንድ ቀን......

ምናልባት ከዕለታት አንድ ቀን......

ልጃገረዶቹም ፈጥነዋል......

በየቤታቸው ገብተዋል......

መሰኩት ከፍቼ ለምን እንደሆነ አላውቅም......ወደ ውጭ ሳፈጥ ብዙ ቆየሁ::

ጫማዬ? ዝነኛው ጫማዬ አስከፍቶኝ ቤቴ እንደገባሁ ነበር ያወለቅሁት::

*(ይሄ ምዕራፍ በ1985 ዓም የተጨመረ ነው)*



@BOOKALEM

# ጠፍጣፋ ትዝታ

ለጥበቃ ሥራ አውቶብስ ማቆሚያ ስንገዋለል አንድ መፅሐፍ ሻጭ ብዙ መፅሐፍት በኩሽኔታ ጋሪ ጭኖ መጣና ግንብ ስር ጨርቅ አንጥፎ ከጋሪው እያወረደ ዘረጋቸው:: በሙሉ ያረጁ መፃሕፍት ነበሩ:: ምናልባት ጥቂት አዳዲሶች ቢኖሩ ነው:: ጤነኛ ገላ የነበራቸው በባዕድ ቋንቋ የተፃፉት ነበሩ.......በእንግሊዘኛ በፈረንሳይኛና በሩሲያኛ::

የተዘረጉት መፃሕፍት ዙሪያ ወዲያና ወዲህ ስል ቆየሁ:: ነጋዴው በፍርሃት ያየኛል:: የማባርረው መሰለው:: እንዳይፈራ ሠላምታ ሰጠሁት:: እየሳቀ፣ እያረገደ ሠላምታ ሰጠኝ:: በዚያ አካባቢ ብዙ ሰው ቢመላለስም ዝቅ ብሎ የተነጠፉትን አሮጌ መፃሕፍት የሚመለከት ጥቂት ነበር::

`ብዕለ ግራሕት´ የሚባል መፃሕፍ አየሁ......ምን ማለት ነው?

`ሥራና ሕይወት´ የሚባል መፅሐፍ አየሁ......ያስፈራል:: በመጨረሻ ቀጫጫና ኮስማና የሆነች ልባስዋ የወለቀ፣ የደራሲው ፎቶግራፍና ከፎቶግራፉ ስር የደራሲው ፀሎት ይሁን ፍልስፍናዊ ጥቅስ ያለባት መፅሐፍ አይቼ አነሳሁት::

ደራሲው ኩስተር ያለ ፊት አለው:: ደራሲዎች ሁሉ ኩስታራ ቁም ነገረኞች ናቸው ማለት ነው? ከፎቶው ስር እንዲህ ይላል:–

*"እንቅፋቴን ሁሉ አስተካክሉ ምቀኞቼን ጠርጎ ለዚህ ያበቃኝ አምላክ ምስጋና ይግባውና ዳዊት በመዝሙሩ እንዳለው....."*

እነበረበት ቦታ መለስኩት:: ሌላ መጽሐፍ አነሳሁ:: `ጠፍጣፋ ትዝታ´ የሚል አርዕስት ነበረው:: የመጀመሪያውን ምዕራፍ ማንበብ እንደጀመርኩ ብዙ ሳልቆይ እንዲህ የሚል አገኘሁ......

*"ጥሬው ከደረሳቸው ይልቅ የጥሬው ፍንጣሪ የነካቸው ልቅሶ ያበዛሉ" አለና በሳቅ ተንፈራፈረ:: አጠገቡ የነበሩትም ሰዎች አብረው ሳቁ"*

የመፅሐፉን ገፆች በብዛት ገለጥኩና ካጋጠመኝ ቦታ ጀመርኩ:: እንዲህ የሚል አነበብኩ......

*"አንተ ጨምላቃ የያዝከውን መፅሐፍ አትጥልም?' አሉት በቁጣ–ሰውዬው የሚያወሩትን አልሰማ ብሎ ቢያስቸግራቸው......"*

መፅሐፏን ከቁሜ ጣልኳት::

ከሌሎች አስፋልት ላይ ከተዘረጉ እንሶላ ተንተርሰው ከሚያናውዙ መፃሕፍት ጋር ተላተመችና የሚያስደንቅ ብዛት ያለው አቧራ በተነች:: ነጋዴውን የበደልኩት አልመሰለኝም ነበር::

ቀና ብሎ ቅር ያለው ሳቅ አሳየኝ::



@BOOKALEM

# ቅመመንና ጭቅና (11)

አ! ቅዠት ልሞት......ለጥ ባለ ሜዳ ላይ ሐመልማል እንደ ምንጣፍ በተዘረጋበት እሱንም እንደ አቃቢት መቀነት ለሁለት ከፍሎት በሚያልፍ የጭቃ እግር ምንገድ ላይ በከባድ ፍጥነት እየተንሸራተትኩ አልፋለሁ:: እንዲህም ስል ነበር ለራሴ: «እንዴት ልቆም ነው? ጫማዎቼንስ የት ጣልኳቸው?» እግሮቼን ዘቅዘቅ ብዬ ሳያቸው ቆመዋል:: ቀና ብዬ ወደ ፊቴ ሳይ ግን በሸርተቴ እየተጣደፍኩ ነው:: ንፋስ ፊቴን ይመታኛል:: መተንፈስም ይከብደኛል:: ዐይኖቼንም መግለጥ ይሳነኛል:: የምንሸራተትበት አረንጓዴ ሜዳ ሊያልቅ ትንሽ ሲቀረው ነጭ የለበሰች ሴት ከበስተቀኜ ስሜን ስትጠራኝ ሰማሁ:: ይሄን ድምፅ አውቀዋለሁ ብዬ ለራሴ በለሆሳስ ስናገር መንሸራተቴን አቆምኩ:: ከበስተቀኜ ትንሽ ወደ ሁዋላ አንዲት ወጣት ሴት ዋርካ ተደግፋ እየሳቀች ተቀምጣለች:: የለበሰችው አገር ልብስ ዙሪያዋን እንደ ነጭ ባሕር ከቦአታል:: የጥለቱ ቀለም ደማቅ አረንጓዴ ከሆን ቄጤማ የተሸመነ ነው:: ሴትዮዋን ስቀርብ በስተቀኟ ገንቦ አየሁ:: ገንቦውና ዛፉ ንፋስ መውጫ ያለችውን አድባር አስታወሱኝ:: ዐይኖቼን ከገንቦው ላፍታ ዞር አድርጌ ስመልስ ሴትዮዋ ታረጀለች:: እየተገረምኩ ጎኗ እተኛለሁ:: እጆቿ ቀልጠፍ ብለው ሱሪዬን ሊገፉኝ ይታገላሉ:: ልትስመኝ ስትጠጋ ወይዘሮ ዝናሽ መሆናቸውን አየሁ:: ተደናግጬ ሽሽት ለማለት ስጥር እላዬ ላይ ተቀመጡ:: በእንቢታ መፈራገጥ ጀመርኩ:: መፈራገጥ ቀጠልኩ......

ሰባንን......ጃፓንን ሲስቅ ሰማሁት:: ሕልሙን እንዳየሁ ያወቀ መሰሉኝ አፍሬ ነበር::

መልኩን እየለዋወጠ የሚመጣው ቅዠቴ ዝናሽን ይጎትታል:: በሕልመ-ዝሙትም ዝናሽ ደጋግመው ደፈሩኝ:: ከባንንኩ በሁዋላ ብቻ ሳይሆን ስራ ላይ ቀኑን ሙሉ ካልጠፋ ሰው በዝናሽ ያለፍላጎቴ መሳደዴና መደፈሬ አስጨነቀኝ፣ ሠላም ነፈገኝ:: ይሄ ሠላም መነፈግ ነበር መሰለኝ ምግብ በፍፁም አልበላልህ አለኝ:: ገላዬ በረሃብ ይደክማል ግን አፌ የምከተው ምግብ ሁሉ አፈር አፈር ይለኛል:: ምራቄ ይደርቃል:: ጫልቱ በአላት አቅም ብትለዋወጥልኝ ሁሉ ዐይነት ምግብ ውስጤ አልቀመጥ አለ:: ትንሽ ሳስገባ ተመልሶ ይመጣል:: ይህ ሠላም ማጣቴ ግን ኣንዳንዴ ደፍሬ ልቀበለው በማልፈልገው ዐይነት ደስታ ይገሰሳል:: ከዝናሽ ጋር መተኛቴ እያስደሰተኝ መጣ!! አንዳንድ ጊዜ ከስራ ጉደኞቼ ጋር ምንገድ ዳር ቆሜ ወይም ለዕረፍት ሻይ ስንጠጣ ፍቅር እንደያዘው ሰው ዝናሽ ሌሊት ያደረጉኝ ነገር ትዝ እያለኝ እንሆልላለሁ:: ዕድሜዋ ጠና ያለች ሴት በምንገድ ስታልፍ ሳይ በወሲብ የቁም ቅዠት እተካታለሁ:: በተለይ ጠና ያሉ የቢሮ ሠራተኞች ሹራባቸውን ሳይለብሱ እንዲህ ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ፊያት 600



@BOOKALEM

ወይ 127 መኪናቸው ውስጥ ለመግባት እግሮቻቸውን ሲያነሱ የሚሰበሰቡት ጉርድ ቀሚሶቻቸው በባልና በውሽማ የተኮመኮሙ ጠይም፣ ቀይ ዳማና ቀይ ጭኖቻቸው የወጣትነት ቅንዝሬን አነሳስተው በማፈርና ራሴን በመጥላት ትግል መሃል ሙት ዝናሽ ሌሊት ያደረጉኝን እስታውሳለሁ:: በዚህ ሳወራው በማልችል ብቸኝነት በሚከት አሳፋሪ ሕልም ውስጥ የዝናሽ ገላ ልጅ እየሆነ፣ ፀጉራቸው በትንፋሼ አየር ብቻ የሚነቃነቅ ለስላሳ እየሆነ፣ የወደቁት ጡቶቻቸው ልጅነት እየተሞሉ፣ ሽበት የተርከፈከፈበት እፍረታቸው እንደተወቀጠ ኑግ የሚፈልቅ ጥቁረት እየለበሰ፣ ሕፃን እንደሚያጫውት ፊቴን ይዳብስ የነበረ እፋቸው እንደ መስኮት እየተከፈተ፣ ገላቸው ውስጥ በፍርሃት ተነከሬ......

......ሳቃትትና ስፈራገጥ የሚሰሙት የቤት ልጆች «ዱካክ አሸሁ» ይሉኝ ነበር:: ያጋጠመኝን ለሰው ማውራት አልፈለኩም:: ምናልባት ሳላውቀው ሜክሲኮ አደባባይ በመኪና ተገጭተው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ዕለት *(ሕፅን ማሲታወሻ ይመልከቱ- ......አርታኢው)* ያየሁት የዝናሽ ሕቡዕ ውበት ለራሴም ልቀበለው ያሳፈረኝ የሚስጥር ከጀላዬ ሆኖ የማያሳድደኝ መሰለኝ::

አንድ ዕለት ምናልባት ከወር ከአስራምስት ቀን በሁዋላ ከቅዠቴ ባንኜ በከፊል የመንፈስ ቅሬታ በከፊል በሥጋ እርካታ ውስጥ እንደ ተጋደምኩ የቤተክርስቲያን ደወል ሰማሁ:: ከርቀት:: ከልደታ ይምጣ ከተክለ ሐይማኖት ይምጣ እርግጠኛ አልነበርኩም:: በሌሊቱ ዳታ ውስጥ ከነዚያ ጎረምሶች እንኩርፍት እየተጋፋ ወይም ከኩር-ኩራቸው ጋር እየተጎነጎነ የቅላፄው ማማር እስኪያደናዝር (አያምርም ወይ?)፣ ከምታገለው ሰመመን መልሶ ወደ ቅዠቴ ሊነዳኝ ከሚያባብለኝ ዕርግማኔ ልላቀቅ እየለፋሁ፣ የማን እንደሆነ ልለየው ያልቻልኩትን የቃጭል ኪሊታ ሰማሁ:: የንፋስ መውጫ መድሐኒያለም ግራጫ ትዝ ሲለኝ (ስለምንስ እሱ ብቻ ትዝ አለኝ? ትዝ)፣ ቅዱሳን አገር አቁዋራጭ ተያይዘው ምሱን ሳይከፍል ዕትብቱ ከተቀበረበት ተሰዶ የወጣውን እኔን ሊያዳክሙኝ የሚያሴሩብኝ መሰለኝ፡ «ሲጀመርም ችላ ብሎናል» ዐይነት በቀል:: በአደባባይ ላይ አልብሼአቸው— ጭኖቻቸውን ለመቀላወጥ ሁኔታው ሳይፈውድልኝ ቀርቶ.......«እንዴት መልካም ሰው ነው!» የተባለ አድናቆት ግን አልብሶኝ (ወይስ ቀልምጫውን በምላሱ የይምሰለን ሰርዞ ነው?)፣ ለሕልሜ ግን ቀጥሬአቸው......

በፍጥነት ከአልጋዬ ተነሳሁና የፊቴን ላብ ጠረግሁ:: ፊቴ ያዳልጣል:: ላቤ መራራ ጠረን ነበረው:: ሳላመነታ ለባብሼ ወደ ውጭ ወጣሁ:: እሁድ ጠዋት ይመስለኛል:: ታዲያ መንደሬ ስለምን ጭር ብላ ነበር? ከፊት ለፊቴ የዝናሽ ቤት ነበር:: አዲስ ሰዎች ከቀበሌው ዕሀፈት ቤት ተከራይተውታል:: ቆሜ በሩን በዐይኖቼ ሙሉ ማየት አልደፈርኩም:: እኔም የእቅሜን ከንፈር መጣጭ ነበርኩ:: በበራቸው ቀዳዳ ባዶ ነገር እያየሁ የጠቅላላ እናቶችን ውጋት ልለካባቸው ሞከሬአለሁ......እግሮቼ በእንግዳ መልክ



@BOOKALEM

ይቀሉኛል:: በጆሮዎቼ የቃጭል አድራሻ እያደንኩ፣ እየተበሳጨሁና እያዘንኩ ተክለሐይማኖት ቤተክርስቲያን ሄድኩ:: ቤተክርስቲያኑ ግቢ ስደርስ ደወሉ ቆመ:: ስለምን? ወይስ በእኔና በጆሮዬ መሃል አቅም አለኝ የሚል ተንኮለኛ መንፈስ የድምፅ ሞገዱን ውሃ እንደሚዘግን ሁሉ በመዳፎቹ መሃል ከትሮአቸው ይሆን? ቤተክርስቲያኑ ጭር እንዳለ አየሁ:: ለማስቀደስ ይሰበሰባል ብዬ ያልገመትኩት ዐይነት ጥቂት ሰው ስላጋጠመኝ እየተገረምኩ ወደ ውስጥ ዘለቅሁ:: ውርጩ ከባድ ቢሆንም የድሮውም የፖሊስነቱም ልምዴ አሳልፎ አልሰጠኝም:: ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላወቅሁም:: መፀለይ ነበረብኝ? እንዴት ነው የሚፀለየው? የአሁኑ ችግሬን ፀሎት ውስጥ ማንሳት አለብኝ? ምንስ እንዴትስ ብዬ ነው የማነሳው? ከዕለታት አንድ ቀን ሲቸግረኝ በመምጣቴ ተክለ ሐይማኖት ንፉግ አይሆኑብኝም? ልቤንስ አያነብም እግዜር......ቅዠቴ ጥቂት እንደጣፈጠኝ? እንደዞረብኝ:: በሌሊት ብርድ በፊልድ ጃኬቴ ተገንዤ በንጋት መከፈት የጀመረውን ሰማይ እያየሁ አጠገቤ ደወል ተጠለዘ:: ጥፍር ያለው ድምፅ ነበር:: እንደ ጨጓራ አሲድ:: ጆሮዬን ብቻ ሳይሆን የውስጥ ገላዬን ሲቧጥጠኝ ይሰማኛል:: ጆሮዎቼን–ሁለቱንም በእጆቼ ጋረድኩ:: የደወሉ ድምፅ ትዕግስቱ ሳይጎል እየተደራረበ ይገርፈኛል:: የምበታተን ሁሉ መሰለኝ:: ቀድሞም የሰማሁት ይህ ነበርን? ድምፁ ወደሚመጣበት ቀና ብዬ አየሁ:: ከደርዘን ዛፎች መሃል እንደ ጎል እንጨት የቆመ መዋቅር ላይ ከመሃሉ አንድ ትልቅ ግራጫ ደወል ተንጠልጥሏል:: ከሥሩ ደብዛዛው ጎሕ በከፊል ጀርባው ላይ አርፎበት ከቃጭሉ ሆድቃ የወጣ ትልቅ ገመድ ይዞ እየቆመና እየተንጠራራ ደወሉን የሚደበድብ ሰው አለ:: «አቁመው!» ለማለት ቃጣኝ:: መላ ሥጋና አጥንቴን ይነዝረኛል:: ከበፊቱ የበለጠ በረደኝ:: ቆዳዬ እየተሰጠጠ በስንጥቆቹ ውርጭ የሚያስገባ መሰለኝ:: ፊልድ ጃኬቴም ወንፊት መሰለኝ:: ጆሮዎቼን ሳልለቃቸው እያጉረመረምኩ ከቤተክርስቲያኑ ወጣሁ:: አደባባዩ አጠገብ አንድ የድንጋይ አግዳሚ ወንበር ላይ ካረፍኩ በሁዋላ ከሞቀ አልጋዬ መነሳቴ ቆጨኝ:: ወደ ቤቴ ከመመለስ ይልቅ ቁርሴን ለመቁረስ ወደ ክፍለሐገር አውቶቡስ ጣቢያ እያዘገምኩ ወጣሁ::

እህል ሳይ ቋቅ አለኝ::

የዚያኑ ዕለት ከማታ ትምህርት ቤት እንደ ተመለስኩ ራቴን ለመብላት ስወጣ ጃፓንን አገኘሁትና ጫልቱ ጋ ተያይዘን ሄድን:: እንደ ፈራሁት ሆዴ አልከፈት አለ:: ጃፓን እንድበላ ተለማምጦ የሚሰማው ቢያጣ የኔኑ ደርቦ በላና ውሃ ብቻ ጠጥቼ ወጣን:: መሃል ምንገድ ስለ ቅዠቴ አጫወትኩት::

"ዕድሜህ እኮ ነው:: ለምን ሴት ጋ አትሄድም?" አለኝ::

ወይዘሮ ዝናሽን ምን አመጣቸው አልኩ በልቤ:: ከእሳቸው ሌላ ሴት የለም? ለእሱ ላለመንገር ብጥርም አልቀረልኝም::



@BOOKALEM

"በሕልምህ የምታየው ምኞትህን ነው" አለች::

"እንዲህ ሀይነት ነገር አላስብም......ብዙ ጭንቀት አለብኝ ለራሴ" አልኩት::

"ጥሩ ምግብ ለመብላት ሞክር:: አንዳንዴ የበላኸው ምግብ ቅዠት ያመጣብሃል::"

"ምን እበላለሁ?" አልኩ::

"ቅዳሜ አንድ ቦታ እወስድሻለሁ:: ሳንቲም ያገኘ:: ሐሙስ ወይ ዓርብ ደመወዝ እንወስዳለን:: ልዩ ቦታ ነው:: የምታውቀው ሰው አታጣም እዚያ:: ብዙ ፖሊሶች ይሰበሰባሉ:: ስታድዮም አካባቢ ነው"

"ሰምቻለሁ"

"ባለቤቱ ጡረታ የወጣ ፖሊስ ነው"

"ምን ሊታበላኝ ነው?"

"እንደርሳለን:: አትቸኩል"

ለእኔና እኔን ለመሰሉት የበሽበሽ ዕለት መቼ እንደሆነች እናውቃታለን:: ያውም የተመጠነች ጥንቃቄ የገራት በሽበሽ:: ወደ ማታ አካባቢ ከጃፓን ጋር ስታድዮም ዙሪያ ተገናኘን:: ከስታዲየሙ ዋና መግቢያ በስተግራ ያለ አንድ ሆቴል ገባን:: የሆቴሉ ውስጥ የሚያፍን ሙቀት ነበር:: የስጋ ጥብስ እየተነፈስን ወደ ውስጥ ዘለቅን:: የምሽቷ ፀሐይ በመጋረጃ ብትገለልም ደካማ ትኩሳቷ ገብቶ የቤቱን አየር ንፍሮ መጥበስ በሚችል ሐሩርነት ሞልታዋለች:: በላተኛ ታጭቋል:: በግራና በቀኝ ጠቅላላ የሚበላው ጎድን ነው:: ቀና ያለ ሰው አይታይም:: ቶሎ የጨረሰ ፉክክር ያለ ይመስል ነበር:: ጃፓን እንደምንም ቦታ አግኝቶ ከሌሎች ሰዎች ጋር አግዳሚ ወንበር ላይ ተገፋፍተን ተቀመጥን:: ለመብላት እንዲህ መተረማመሴ ትንሽ አሳፈረኝ::

ያኔውኑ የሚታዘዝ ጉብል መጣ:: ገፁ በላብ የተጠመቀ......ፊቱን ዘቅዘቅ ቢያደርግ ጠረጴዛ ላይ ሊንጠባጠብ የሚችል::

"ሁለት አፐሬቲፍና ሁለት ጭቅና አምጣልን" አለ ጃፓን::

የሰማው ሰው በፍጥነት ተመለሰ::

"እልኮል ነው ያዘዝከው?"

"አፒታይትህን ይከፍታል"

ዙሪያ ገባዬን አየሁ:: በስተቀኜ ቶሎ በልታችሁ እንድትጨርሱ ዓለም ነገ ታልፋለች እንደተባለ ሁሉ......ሰው ያተኮረ ፍስፈሳ ይዞአል:: በመጋረጃዎች መጋጠሚያ



@BOOKALEM

ሾልካ ያለፈች የብርሃን ዘንግ አንድ ሰፊ ጠረጴዛ መሃል ለመሃል እንደ ሰይፍ ወድቃ ነበር:: በላተኛው በስልት ሽሽቷታል::

ከመሃል ሰሜን ሰማሁ:: ቀና አልኩ በመደናገጥ:: ትምህርት ቤት የማውቀው አስተማሪዬ የነበረ አንድ መቶ አለቃ ነበር:: ቀድሞ ካየሁት ወፍሯል:: ጉንጮቹ ከአፍንጫው ረዝመዋል:: ከስር የሲቪል ለብሶ ፊልድ ጃኬቱን ከላይ ደርቧል:: እየገባ ነበር:: ወደ ተቀመጥኩበት መጣ:: ከተቀመጥኩበት ተነስቼ የወታደር ሠላምታ ሰጥቼው እጁን ለመጨበጥ ዘረጋሁ::

ያዘኝና ተጠግቶ አቀፈኝ:: ወይም እጁን ትከሻዬ ላይ አስቀመጠ:: እንደ ሹክሹክታ ወደ ጆሮዬ ቀርቦ፡

"ኬማ(12ሀ) ሁሉ እዚህ ምን ይሰራል?" አለ::

አንዳንድ ሰው ዘይቤው ቢያረጅበትም ሙጭጭ የሚል አለ:: እንዴ ሲያምርለት ለዘለዓለም የሚመስለው::

"ከማን ጋር ነህ?" አለ:: ልመልስለት ፋታ ሳይሰጠኝ:: ወደ ጎኔ ጃጋንን አሳየሁትና መቶ አለቃው ከእኔ ቀድሞ ጃጋንን ጨበጠው:: ጃጋን የወታደር ሠላምታ መስጠት አይወድም:: እንደ ተቀመጠ በፈገግታ ጨበጠው::

"እዚህ ትመጣለህ?"

"ዛሬ ብቅ ማለቴ ነው:: እሱ ወንድሜ እያስተዋወቀኝ ነው"

"አሁን ነው መብላት:: ካረጁ በሁዋላ ጥፍር ነው የሚሆነው::"

"እይሰማም:: በሽሮ ሊያልቅ ነው" አለ ጃጋን::

"ለምን እንኖራለን ካልበላንና ካልጠጣን:: ለመሆኑ ሥራህ ተስማምቶሃል? መኮንንነት መግባት አለበት:: ሥነሥርዓት አለው" አለ ጃጋንን እያየ::

"ካልበላ ምን ያደርጋል" አለ ጃጋን በመቀለድ::

እየሳቅሁ ተቀመጥሁ::

"ዋናው ጤንነት ነው:: ይሄ ጥሩ ቤት ነው:: ቅዳሜ ቅዳሜ ብዙ ጊዜ እዚህ ነኝ" አለ መቶ አለቃ::

እጁን ከትከሻዬ ላይ አንስቶ ወደ መጣበት መመለስ ጀመረና፡ "ኬማ ሁሉ አትጥፉ" አለ ሁለታችንን እንደሚናገር ሁሉ::

ጃጋን ግራ ገብቶት ያየኛል:: መኮንኑ እንደ ሄደ መጀመሪያ አፕሬቲቶ ፊታችን መጥቶ የእንጨት ጠረጴዛ ላይ በኃላቅ ድምፅ ተቀመጠ:: አሳላፊው ጠረጴዛውን ሆን ብሎ ለመምታት የመጣ ይመስላል:: ጎምዛዛነት የሚበዛውን አፕሬቲፍ ግማሽ



@BOOKALEM

እንዳደረግን ጥብሱ በትንሽ ትሪ ላይ ጢሱን እያትጎለጎለ መጣ:: ያምራል ጠረኑ:: ሆዴ እዬዬ ሲል ሰማሁት:: በከፊል ያረረ፣ በከፊል ለብ ለብ የሆነ ጥብስ–ከጎኑ ደሞ ወደ ጥቁረት የሚወስደው ድልህ በሙጫ እንዳያያዙት ሁሉ ትንሽ ሸክላ ሳህን ላይ ተጣብቆ:: ላፋው ላይ ሁለት ቢላዎች በመሳል ብዛት ቀጥነው የተዘጋ ዚፕ የመሰሉ፣ እንጨት እጀታቸው በስብ የጠቆረ፣ በደብዛዛው ብርሃን ውስጥ እንደ ሲጃራ ወረቀት እየፈለቀ ተጋድመዋል:: ቀና ብዬ አየሁ::

ይበላሉ:: ሰዎች በእርግጥ ይበላሉ::

አንዳንዱ ወደ ላይ እንጋጦ ከታች ወደ ላይ ቢላውን እየሰነዘረ ሙዳ ስጋ ከጎድን አጥንት ላይ ሊያላቅቅ ይገዘግዛል:: እንዲህ ነው እንዴ የድሮ መኳንንት ይበላሉ ይባል የነበረው? የድሮ ነገር አምልጧቸው በቁጭት በግነው የተሰበሰቡ ሰዎች ያሉ ይመስላል:: ጣቱ ተቆርጦና በፋሻ ተጠቅሎ ከሥጋ የሚታገል ሰው አያለሁ:: (ለአፍታ እዚያው ፌዴሬሽን የቦክስ ልምምድ ሲያደርግ የቆሰለ ሰው መሰለኝ)(ወይስ እየተቆረጥን እንበላለን–እየበላን እንቆረጣለን ዓይነት ነገር ነው?) ጃጋን እንድበላ ጎሰመኝ:: በደስታ ጀመርኩ:: በየመሃሉ አፕሬቲፌን እየተጎነጨሁ.......

......በልተን ጨርሰን ስንወጣ ደከመኝ::

"ሌላ ጭቅና ሌላ ቦታ አትበላም?"

"ምን መሆንህ ነው ጠገብኩ"

"እንሂድ ግድ የለም"

ግራ እንደገባኝ ቸርቸር ጎዳናን አቋርጠን ብዙ ሴቶች ያሉበት ቡና ቤት ገባን:: አንዳንድ አፕሬቲፍ አዘን እንደተቀመጥን ጃጋን የተንኮል ፈገግታ ሰጠኝ::

"ምነ?" አልኩት::

ቤቱ የደራ ነው:: የጊዜው ዘፈን ከትልቅ የሚብለጨለጭ ቴፕ መጠጦች ከሰፈሩበት መደርደሪያ ላይ ይፎክራል:: ምኑም አልጥም ያለኝ ሊገባኝም የከበደኝ የፈረንጅ ዘፈን የብዙ ሰው ቀልብ የያዘ ይመስላል:: ገና አልሰለጠንኩማ:: የሚያማምሩ ሴትኛ አዳሪዎች ወዲያ ወዲህ ይላሉ:: በማማራቸው ሥጋቸውን በገንዘብ የሚቸረችሩ አይመስልም:: ብዙዎቹ በእውነት ከሆነ ከገነት ያምራሉ:: ፊታቸው ላይ ቆሻሻ አይታይም:: እንዴት ቢታጠቡት ነው? ወይስ ተወልደው እግቢ ወንድ ተኩሶ የሳታቸው፣ ወይስ ተኩስ ሰምተው የሸሹ?



@BOOKALEM

ቄንጠኛ ወንድ ወጣቶች ለግላጋነታቸው የሚያሳዝን ባንኮኒ ተደግፈው እየተሳሳቁ ድራፍት ይጠጣሉ፣ ትንባሆውንም ያትጎለጉሉታል። እነዚሁ ቄንጠኛ ወጣቶች ከሸርሙጦቹ ጋር ይዳራሉ። ያቅፉዋቸዋልም፣ በአሳፋሪ መልክ ይዳብሱዋቸዋልም። ሴቶቹ በልፊያና በድሪያ ተቃጥሎ የሚጤስ ቂጣቸውን ይዘው ወዲያ ወዲህ እየዞሩ የሚተን ሽቶአቸውን ይነሰንሱብናል። ጃፓን ጥያቄዬን ሳይመልስ እየሳቀ ያየኛል።

"ጭቅና አትፈልግም?" አለኝ።

"ለዛሬ የሚበቃኝን አግኝቼአለሁ"

"በሬ ማለቴ አይደለም"

ምን ለማለት እንደፈለገ ገባኝ።

"አልፈልግም"

"አንተ በሽተኛ ነህ? እንዳታብድ በሁዋላ። በሕልምህ የሞተች አሮጊት ከማየት ከነዚህ ምን የመሰሉ አንዷን እኔ እጠራልሃለሁ......ጣ ጣ ታደርጋለህ" አለ......ወደ እኔ ጎንበስ ብሎ በሴረኛ ድምፅ።

"አልፈልግም"

"ታዲያ ለምን እዚህ መጣን?"

"አፕሬቲፍ ልንጠጣ ነው"

"የተግባባን መሰሎኝ ነበር"

"አዎ ተግባብተናል። ልበላ ነው የመጣሁት። አሁን አቢታይት አለኝ። ሳላውቀው ለካ ደዮ አስልችቶኝ ነበር"

"ወደ ቁም ነገሩ"

"ነገርኩህ ጃፓን። እነዚህን ሴቶች አላውቃቸውም እኮ"

"ታዲያ እሱኮ ነው ጥሩ"

"ሳላውቃት? እንዴ? ደሞ ለእንትን ገንዘብ እንኪ ማለት። አይሆንም"

"ከቅዠትህ ትድናለህ። ወይስ በየቀኑ ስትባንን ልትኖር ነው? ባለትዳሩ ሁሉ ነው የሚያደርገው"

ከፊት ለፊታችን አንዲት ጥርሰ–መልካም በግራ እጅዋ የሳንቲም ቦርሳ ጨብጣ ግራና ቀኝ እንደ ክንፍ የበቀለ ዳሌዋን እየነቀነቀችና እየሳቀች ፈረንጅኛ ትደንሳለች።



@BOOKALEM

ፀጉሯ ውስጥ ያልገባ ዐይነት የሚብለጨለጭ ነገር የለም:: ትልቅ ጭኖች አሏት:: ለአፍታ በእነዚህ መሃል ተሰንቅሬ ራሴን አሰብኩት::

"እሷን ልጥራልህ? "

"እ......አበድክ እንዴ? "

"የባላገር ባላገር ነህ" ከሚያንሾካሹክበት ቀና አለ::

ከአፕሬቲፌ ጎንጨት አደረግሁና በዐይኖቼ ስለላዬን ቀጠልኩ:: ጃፓን ትወዛወዝ የነበረችውን ድንቡሼ ጠርቶ ድራፍት አዘዛት::

*ድንቡሼ ገላ ያብሽ ገለባ*
*ሜዳ ነው ብዬ ገደል ልገባ......*

በልቤ ይሄን እላለሁ:: ባላገር?

"ሕልሜ በተሻለ ሕልም እስኪተካ እጠብቃለሁ"

"ይለቁሽ መስሎሻል ዝናሽ:: ምናቸው ሞኝ ነው? ድንግል የሚለቅ አለ?" የቀረ ጭላጭ አፕሬቲፉን በወፍራም እጆቹ አንቆ በራሱ ቀልድ(?) ጎብጦ በሳቅ ፈረሰ......

ሞቅ ብሎን ቤት ገባን:: «ጭቅና» የተባለውን ነገር ግን ሳልነካ:: እቤት ድረስ ጃፓን እየተማረረ መጣ:: የማይማረርበት ነገር የለም:: የሚያኮርፈኝ፣ ለንቦጩን የሚጥልብኝ መስሎኝ ነበር:: ምናልባት ከሴተኛ አዳሪ ጋር ለመተኛት ብቁ የምሆነው በብዙ ነገር ስማረር ይሆናል:: ስጠጣ ያልበኛል ብሎም የግንባሩን ላብ በመሐረብ እየጠረገ ነበር:: ከሩቅ ለሚያያቸው ምንገድ ዳር ለቆሙ ሴቶች ምላሱ እስኪቃጠል ያፋዋጫል:: ይጣራል:: እንዲህ ማድረጉ ለምን እንደሚጠቅመው አላውቅም:: ቤት ሁሉም ልጆች ተኝተው ደረስን:: በየመንገዱ ሲጮህ የነበረው ጃፓን አንዲት ቃል ሳይተነፍስ ልብሱን አወላልቆ ተኛ:: እኔ ከነ ልብሴ በጀርባዬ ጋደም አልኩ:: ቤቱ በሦስት አቅጣጫ በእንኩርፍት ታጥሯል:: የጃፓን ግንብ መሆን አለበት:: እንኩርፍቱ እንደ ድንጋይ ይከብዳል:: የአለማየሁ ቁጥቋጦ......ንፋስ በውስጡ የሚያልፍበት:: የነጋሳ ጨፈቃ......በውስጡ እሾልኬ የአምቦ ጨረቃን ለማየት እንድችል:: የበኩረ አጋም......-በወዳጅነቴ ቻልታ ውስጥ የማያፍር ቡዋጠጣ:: የእኔ ግድግዳ ድካም ነበር......መሃሉ ላይ ተሳፍሬ ዕውንና ቅዠት እየተቀባበሉኝ:: ምላሴ ላይ የአፕሬቲፉ ምሬትና ስኩዋር እየተለዋወጠ ይሰማኛል:: አፌን አጣጥማለሁ:: ሎሚ፣ ስኳር፣ ሎሚ፣ ስኳር:: ዐይኖቼን በቀስታ ጨፍኜ ዙሪያ ገባዬን አዳምጣለሁ:: የልቤ ምት ረግቷል:: ነጋሳ ይገላበጣል:: ከቤቱ ውስጥ ስም መስጠት የሚከብዱ ድምፆች እየተነሱ ይጠፋሉ:: ምንገድ ላይ ከባድ ኩቴ እሰማለሁ:: እየራቀ ሲሄድ የሚያሳዝን ነገር አለው:: ምናልባት ባለጋሪው (13)



@BOOKALEM

ይሆናል:: በሕሊናዬ ረዥም ቤዥ ቀለም ያለው ጋቢ የተከናነበ ጎልማሳ አቀርቅሮ ሲንዝ ይታየኛል:: የባለጋቢው ኮቴው አይከብድም:: ሚዛኑም ጥላውም የቀለለ ነው:: መነሻና መድረሻ አልነበረውም:: እነዚህ ትንንሽ ድምፆች የማን ናቸው? ከየቅራቅንበው ጀርባ ሌሎቹ እነማን ናቸው? ከብብቴ የሚወርደውን ላብ የካናቴራዬ ጥጥ ይጠጣዋል:: ጠረኑ እንደ ደረቀ ቅጠል ነው፣ ማነው እንዲህ የሚለው? እንዲህ......«መዢ! መዢ!»

የሰማዩ ቀለም እንደተቀነሩ ጠፍ ጨረቃ ነው......ሜዳው ላይ የደረቁ ቅጠሎች እንደ ተሰበሩ ሺህ የደንገል ጀልባዎች በመስኩ ላይ ለመጥፋት ይዋዥቃሉ......መዢ! መዢ! ትለኛለች......ዐይኖቼን ማየት ያፈረች......ካናቴ ስንዝር ዕርቆ ከመቀነት የረዘመ ጥቁር ሻሽ ንፋስ ውስጥ እየተንገላወደ ያልፋል......እንደ ቆሰለ፣ ሞትንም እንደሚሸሽ እባብ......(«ይሄ ሻሽ የዝናሽ ነው» እላለሁ) የሚጣፍጥ ድምፅ ከማይታየኝ ረባዳ እየዳኸ ወደ እኔ ይመጣል......ሲሸት እንደ ሕብስት ያደርገዋል......የተራቡ ጆሮዎቼ እንደ ክንፍ ይራገባሉ......መዢ! መዢ!......መሮጥ ጀመርኩ......ድምፁን ለመያዝ ፈለግሁ...... ቁልቁለቱን መውረድ ስጀምር ነጠላ ጫማ ያደረገች የሚያምር ባት ያላት ወጣት ሴት ፊትዋን ከእኔ አዙራ ቆማለች......ማን እንደሆነች ማወቅ ከበደኝ......እኔን አልነበረም እንዴ የጠራችው? እያልኩ ሳስብ ዝናብ መዝነብ ጀመረ......የሚሮሖህ ዝናብ ነው......ወፋፍራም የውሃ ጠብታዎች ጀርባዬ ላይ ይወድቃሉ......ልጅ እንደነበርኩ ዐይነት......አንደኛ ደረጃ ስማር በዚህ ዐይነት ክረምት ውስጥ ልቤ እስኪፈርስ አልሳቅሁም ነበርን? አሳንብሼ ጆሮዬን ያዝኩ......ምን ነካኝሳ? አ! አ! ጆሮዬን......

ዐይኖቼን ስገልጥ ፊቴ ላይ እንደ ነጠረ ቅቤ አርፎ ያገኘሁት የእሁድ ጠዋትን ቢጫ ፀሐይ ነበር::



@BOOKALEM

# ጫልቱና ሰንቦጭ

እንግዲህ የጫልቱ ቤት እስተዚህም ትልቅ አልነበረችም:: ገና አንድ ሰው ሲገባ እውስጥ ቀድመውት በደረሱ ሰዎች ያኔውኑ ይታያል፣ እሱም እውስጥ ያሉትን ሰዎች በሙሉ በአንድ አፍታ ማየት ይችላል:: መቸ ሰለት ለእራት ዘግይቼ ደረስኩ:: የክፍሉ ወንበር ተይዞ በልቶ የጨረሰ እስኪወጣ እውጭ ቆሚ ተራዬን እጠብቃለሁ:: ከውጭ መንገዱ በጩኸት እንደደራ ነበር:: ለማፏጨት እሞክራለሁ:: ድሮም ልጅ ሆኜ አፏጭ አልነበርኩም:: ቢሆንም የማውቀውን ማንኛውንም ዘፈን ከርቀት እንዲሰማ አድርጌ ማፏጨት እሞክር ነበር:: አሁን እቆጥበዋለሁ፣ ለምን እንደምቆጥበው አላውቅም:: ፉጨት ይቆጠባል እንዴ?

በልተው የጨረሱ ሁለት ሰዎች ወደ እኔ ተገላምጠው ሳቅ እያሉ አፉኛና እጃቸውን ለመታጠብ ጫልቱ ቤት ግድግዳ ላይ ከሥሩ ቧንቧ የተሰራለት ውሐ የተሞላ ባሊ ስር እጃቸውን ለመታጠብ ግራና ቀኝ ተሰለፉ::

ፉጨቴን ሳልሰብር ገባሁ:: ረስቼ:: ፉጨቴን ማቆም ረስቼ:: ግራና ቀኝ ባዶ ወንበሮች አገኘሁና ጫልቱን እንደገና ሠላም ብዬ አንዱ ጋ ተቀመጥሁ:: ለሠላምታዬ መልስ አልሰጠችኝም:: መጀመሪያ ወንበር አጥቼ ስመለስ ሠላምታዬን ያልመለሰችው ሥራ በዝቶባት ሳትሰማ ቀርታ ይሆናል ብዬ ነበር:: አሁንም አልሠማች እንደሆን ብዬ ሠላምታ አቀረብኩ:: ፊቷን አዙራ ወደ ጓዳ ገባች:: አጠገቤ የነበሩ አንድ ሰው:

"ጫልቱ መዝገቡ ሠላም ይልሻል እኮ" አሏት::

"ሠላም!" የሚል ድምፅ በቀስታ......ከጓዳ ወጣ:: ምላሷ የታመመ ይመስል::

ሰውዬው ወደ እኔ ዞር ብሎ፡ "ለአቶ በቀለ ልጅ ያደረከውን ሰማሁ......ጥሩ አንጀት አለህ ወንድሜ......ልጁ እኮ የተበተነ ነው:: ዋሉ የቀረ:: ጋሻው ሰማህ! ሰማህ ጋሼ!" ብሎ ጮኸ-ፊት ለፊታችን ለተቀመጠ አንድ ሰው:: "ያ አንድ ቀን ያወራንልህ ፖሊስ ይኸው......እንዲህ ያለ ኢትዮጵያዊ አያስኮራም! እ! ሰው ባይመርቅህ ተክልዬ ይመርቁሃል......ሰውነት......"

እኔ አፍሬአለሁ::

ሮጬ መውጣት ሁሉ ፈለግሁ:: ጫልቱ የተለመደ እራቴን በትንሽ ትሪ ይዛ መጣች:: ማዕዱን ጠረጴዛ ላይ ስታስቀምጥ ቀና ብዬ አየሁዋት:: የታችኛው ከንፈሯ ከቀድሞው ተለቀብኝ::



@BOOKALEM

አንዳንድ ጊዜ የዐይኖች የአስተያየት ስልት የገላ አቅጣጫ፣ የብርሐን አስተራረፍ ያንድን ነገር ነባር ባህርይ ለቅፅበት እንኳን ቢሆን የተለየ አድርገው ያሳዩታል:: የለምቦጯን ነገር እረሳሁና መብላቴን ጀመርኩ:: ስለራበኝ በትልልቁ እጉርሳለሁ:: በትልልቁ መጉረስ ብቻ ሳይሆን ቶሎ ቶሎ ነበር የምበላው:: ረሃቤ ጋብ ካለልኝ በሁዋላ ለድንገት፣ በችኩላ ቀና ስል ጫልቱ እኔን እያየች ስትኮሳተር አየሁዋት:: ዐይኖቻችን እንደተገጣጠሙ ፊቷን ዞር አድርጋ ወጥ ላለቀበት ሰው ወጥ ልትጨምር ወደ አንዱ ጠጋ አለች::

ቀደም ሲል ያየሁት ለንቦጯ ትዝ አለኝ:: ከእኔ ጋር ያጣላት ጉዳይ እንዳለ ዓይነት ነገር ተሰማኝ:: የሚጉዳ ነገር አልሰራሁዋትም:: ያስቀየምኳት ጊዜ ትዝ አይለኝም:: በቀስታ እየበላሁ የበላተኛው ብዛት እስኪቀል ጠበቅሁ:: አሰላስላለሁ:: ባሰላስል፣ ባሰላስል እሷን ያስቀየምኳት ጊዜ ትዝ አልል አለኝ:: ፋጨቴ እንደሆነስ? እሱ አይሆንም......ቢብስ ተረብ እንጂ ኩርፊያ የሚጋብዝ ድፍረት አልነበረም:: የኒንጃ ጉዳይ ተጠናቆ የረሳችው መስሎኛል:: ኒንጃ ደ'ሞ ተመልሶ መጥቶ እሷን የረበሻት አልመሰለኝም:: ቢሆን ኖሮ መስማቴ አይቀርም ነበር:: መጠበቁ ሰለቸኝና ልወጣ ስል ከሰው አርቄ ላዋራት ወደ ውጭ እንድትከተለኝ ጠራሁዋት:: ያልሰማች መሰለች:: በልቤ ምን አስጨነቀኝ እያልኩ ትቼአት ሄድኩ:: በሌላ በኩል ደ'ሞ የነገሩን ስር ማግኘት ጓጓሁ:: ከለመድኳት መጋቢ ተለይቼ ሌላ ቦታ እንደገና ለመልመድ መጣር አልፈለኩም:: ጫልቱ ንፁሕ ውድ ያልሆነ ምግብ ትሠራለች::

እቤቴ ቆየሁና ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ወደ ጫልቱ ቤት ተመለስኩ:: በሩ ገርበብ ብሎ ነበር:: አንኳኳሁና ገባሁ:: ማንም ሰው አልነበረም:: ልታየኝ እንዳልፈለገች ሁሉ ፊቷን ከእኔ ዞር አድርጋ ግድግዳ ግድግዳ ማየት ጀመረች::

ሳልቀመጥ ጠየቅሁዋት: "ጫልቱ ምን ሆንሽ?"

ዝም::

"ስሚ አንቺን ነው......ተቀይመሽኛል?"

ፊቷን አዞረችና ለንቦጯ እየተንቀጠቀጠ ዕንባዋን ጠረገች:: በመጀመሪያ የወጡት ዕንባዎቿ በጣም ፈጣን ነበሩ:: ፍጥነታቸውን አደነቅሁት::

ቀና ብላም ሳታየኝ: "እኔ እንደ ወንድሜ ነበረ የማይህ:: ዘመዶቼ ሲመጡ......ስምሀን አንስቼ መዝገቡ ወንድሜ ነው እኮ የምለው......ስትበላ ዕውነቴን ነው በእንተ......ተቀረብኩህ በሁዋላ ነግጂ አላውቅም......አንተ ብቻ ሳትሆን እዚያ ቤት የምትኖሩ......ሳትጠግብ እንድትሔድ አልፈልግም......ቀጥነህ ሳይህ እኔ የጉዳሁህ



@BOOKALEM

እየመሰለኝ......ይኸው ይህቺ ማርያም እዚህ ቅርብ ናት ማህፀኔን ትዝጋው አንጀቴ ይረብሽብኛል......"

ለቅሶ ከመሃል እያቋረጣት፣ ሰንባዋን እንደ ልብ እየለቀቀችው:: እኔ የምሰራው ጠፍቶኝ ይገፉ ላባብላት እፈልጋለሁ:: ፍርሃት ያዘኝ፡ ፈራሁ:: ማባበል ከባድ ነው::

"ግን ሰው ሆዱ አይታወቅም:: ዘመዶቼ ይሉኛል:: አንቺ ሰው ታምኛለሽ......አንቺ ጥሩ የተናገረ ሁሉ ጥሩ ሰው ይመስልሻል ይሉኛል......እኔ ግን አልሰማሁዋቸውም:: ታዲያ ስሜን እየዞረ ማን ያጠፋል? እ......እንደ ወንድሜ የማይህ አንተ?"

"ምንድነው የምትይው እባክሽ?"

"ተወኝ እባክህ......አሁንማ ለየ......ለየ እኮ......እኔ ይህቺ የሴት ልቤ......መንታ ወልጄ......የሞቱብኝ ነኝ:: የባሌ እንጉጥጫ ሊገለኝ ሲል ነው የመጣሁት:: እናት መሆኔን ልደርስበት ስል እግዛቤር የነፈገኝ ነኝ:: ታድዬ መሰለህ......የእኔ ምግብ ከሌላ ከማንኛዋ ሴት ይከፋል? በዐል ሲሆን ዘመድ የለህም ብዬ ቅር እንዳይልህ ብዬ......'መዝገቡዬ' ብዬ አቆላምጬ ካለችኝ ከዚህችም ከዚያች ሰጠሁና እንጀራዋ በቆሎ ነው......ሽሮዋ ሽንብራ ነው......ሥጋዋ ዝባዝንኬ ነው......አይታመንም......እያልክ የምታስወራው:: እግዛቤር ይወደዋል......?" አቆመች::

መናገር አልቻልኩም:: ድሮ ሰው ማስለቀስ አስለቃሹን ያስደስት ይመስለኝ ነበር:: ማስለቀስ ቀርቶ ጫልቱ እኔን አስለቃሺ፣ ጉጂዋ አድርጋ ስታቀርበኝ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ:: የምሰራው ጠፋኝ:: የማደርገው ግራ ገባኝ:: ተቀምጬ በጭንቅላቴ እጆቼን ያዝኩ......ማለቴ......በእጆቼ ጭንቅላቴን ያዝኩ......

"ለውነትሽን ነው?" አልኳት::

"ታዲያ እንዲህ የምሆነው ለጫወታ ነው?"

"ማን ነገረሽ?"

"ሹክ ብለህ ስታወራ ነገሩብህ እንዴ?"

"ምንድነው የማወራው? እንዲህ ዐይነት ነገር አላወራሁም"

"ተው እባክህ ከታመነ ሰው ነው ጆሮዬ የሰማው"

"ጫልቱ እንዴት እንዲህ አወራብሻለሁ? እኔ......ስንት ዓመት ነው አንቺ ጋ የበላሁ......እ"

"ምን ይታወቃል የሰው ነገር"

"ምን ይታወቃል የሰው ነገር ለምን ትያለሽ? አንድ ነገር አድርጊአ......የነገረሽን ሰው......ሲያወራ ሰማሁ ያለሽን......አምጪው......"



@BOOKALEM

"ምን ያደርጋል እንደሱ.......ጠላቴን ከጉያዬ ጠቁሞ የነገረኝን ሰው አላጋልጥም"

"ማጋለጥ አይደለም እኮ......."

"ማጋለጥ ነው ሌላ አይደለም......."

"ታዲያ ሰውነተኛነቴን እንዴት ላረጋግጥልሽ.......?"

"ይኼ ወር ካለቀ በሁዋላ ሌላ ኩንትራት ፈልግ.......ክርክር አያስፈልግም.......ጉድ እኮ ነው.......ስሜን እያጠፋህ መጥተህ ትበላለህ?.......የሰው ሆድ የሰው ልብ"

"ለምን የምበላበትን ቦታ አልለውጥም ነበር መጥፎ መሆኑን ካወቅሁ?"

"ክፋት.......ክፋት ነዋ.......የሚገርመው እሱ እኮ ነው"

"እምልሽ.......ስለ ምግብሽ መጥፎ አውርተን እናውቃለን?.......ሁሌ እንዳመሰገንኩሽ አይደለም? እኔ እኮ አከብርሻለሁ ሜልቴ (እንዲህ መናገር እንኳን አልፈለኩም ነበር):: ትሠሪያለሽ፣ ለፍተሽ ነው የምታድሪው:: አንቺን እንደ እናቴ ነው የማይሽ.......አየሽ እናቴ ሦስት አመቴ እያለች ነው የሞተችብኝ (ይኼን መናገር አልፈለኩም ነበር) ያለ እናት ነው ያደኩሁት.......በሴት እጅ እንደምፈልገው ሆኜ ብዙ ጊዜ የተመገብኩት ባንቺ ነው:: ለእኔ ሰውነቴን ነው የምልሽ እንደብርቅ ነው የማይሽ.......እ......." ቀጥዬ ምን እንደምናገር አላውቅም ነበር:: እየተሰባበርኩ መሰለኝ:: እየተከፋፈትኩ መሰለኝ:: ይኼን ሁሉ ምን ያስወራኛል? እያልኩም ለራሴ እገረማለሁ (ግርመጥ–የመገረም ጥያቄ)

"ሰውነት እናትህ ሞታብሃለች?"

"አዎ"

"የነገረኝ ሰው ግን የሚታመን ነው ወንድሜ ('ወንድሜ' ስትል ስድብ የመሰለ ዜማ ነበረው):: ከልጅነቱ ጀምሮ የተበሳጨ ሰው ጨካኝ ነው......."

"ምን ማለትሽ ነው.......?"

"ኸረ ለመሆኑ እኔ ቤት ሰው ጋብዘህ ጠርተህ ታውቃለህ? ደንበኛ አምጥተህ?"

"ሰው አላውቅም......."

"አታውቅም? .......ፖሊስ ሆነህ ሰው አታውቅም.......ከተማው ጉብር እየዋልክ ሰው አታውቅም:: ነገር ቢኖር እንጂ»

"ኸረ እባክሽ ሜልቴ"

"እኔ ሰው አምናለሁ.......ስህተቴ ነው:: ዋጋዬ ነው:: የዚህ ዘመን ሰው ምኑ ይታመናል:: እየበላ የሚሳደብ.......እየጠጣ የሚራገም:: እኔ ባጉልብህ እንኳን ለእኔ



@BOOKALEM

ትነግራለህ እንጂ ስሜን እየዞርክ ማጥፋት የለብህም:: ከሌሎች አላሳንስኩህ ......እንደውም አዳላሁልህ እንጂ.......ግን ጥሩ ነው መዝገቡ:: ጥሩ ነው:: እንዲህ ከተሆነ እኩ መኖርም የሚወደድ አይደለም:: እኔ የምኖረው ለሰው ነበር:: የሠራሁትን ሲበሉልኝ በደንብ ጥርግ አርገው ሲበሉልኝ ደስ ይለኛል:: ሰው እወዳለሁ::"

"ስማሽ ጫልቱ የመጨረሻ ልንገርሽ.......እኔ አንቺን አላማሁም:: አምቷል ያለሽን ሰው ንገሪኝና ከሰውዬው ወይም ከሴትዬዋ ጋር እንነጋገር"

"መነጋገር አያስፈልገውም እኩ አልቋል"

"በይ እሺ እንግዲህ እንድመጣ አትፈልጊም"

"ተው አትምጣ......ለአንተም ጥሩ አይደለም:: የምትበላው ካመመህ መረዘችኝ ብለህ እንዳትል"

"ኸረ ጉድ ነው" አልኩና ተነሳሁ::

የማደርገውን አላውቅም:: ወደ ጊዳዋ ሸሸት አለች:: የምመታት መሰላት መሰለኝ:: አሰባለሁ:: ጭንቅላቴ ይፈጥናል እንደባቡር......የተናገረችውን ያገላብጣል......ያጐናል ይጥላል......እያንዳንዱን ከአፏ የወጣውን ቃል የተደጋገመውን ቃል ሚዛን ላይ ወንፊት ላይ እየደረደርኩ ለማበጠር እሞክራለሁ.......ጭንቅላቴ ጉም መሰል ነገር ሞልቶት ነበር......

"ደህና እደሪ!" ብዬአት ወጣሁ::

ከተናገረችው ሁሉ የሳበኝ ቃል 'የታመነ ሰው' የሚለው ነበር:: ምን ማለት ነው የታመነ? አንድ ሰው ለመታመን ምን መሆን አለበት? የቅርብ ሰው መሆን አለበት:: ለእኔ? ለእሷ? ለሁለታችንም? ለመታመን ቢያንስ ለእኔ የተጠጋ መሆን አለበት:: ጓደኛዬ መሆን አለበት:: እሷ የምታውቀው፣ እኔ የማውቀው ማን ነው? በመጀመሪያ አብረውኝ ቤቴ ያሉትን ነው.......ሌላ የምታውቀውስ የለም? .......ኒንጃስ? ምን አልባት ኒንጃ:: ስለገዛሁለት ዶሮ ወጥ አውርቷት በጥርጣሬ የእሷን ምግብ ንቆ ያደረኩ መስሎአት እንደሆነ?.......ሊሆን አይችልም.......ምክንያቱም ኒንጃ ታማኝ ሊሆን አይችልም.......ደስ ካላት ጥርጣሬ አስከፊ መደምደሚያ ልትፈጥር ትችላለች፣ ቢሆንም የታመነ ሊያደርገው አይችልም......«የታመነ» ሊመስል ይችል ይሆናል......ስለዚህ አብረውኝ ከሚኖሩት ልጆች መሆን አለበት......ግን ማነው ምን ላገኝ ብሎ እንዲህ ያለ ተራ ነገር ይሠራል? ያደረገ ቢኖር ተገናኝቼው ባነጋግረው እወዳለሁ......ቤቴ መግባት አልፈለኩም ነበር:: ጣሪያ ስር ማደር፣ መተኛት አልፈለኩም::

ቤቴን አልፌ ለመሔድ ዳገቱን ዝቅ ስል በር ተከፍቶ ብኩረን ቆሞ አየሁት:: ደማቅ አራት ማዕዘን መብራት ወጥቶ ቆሻሻው ምንገድ ላይ እንደ ንጹሕ ቢጫ



@BOOKALEM

የምንጣፍ ቁራጭ ወድቋል:: ያኔውኑ ከመቅፀበት የበኩረን ቁመና ሳይ፣ አሳሳቁን ሳይ የቦይ ድልድይ አዘባለሉን ሳይ እንደ ባለ ድል እንደሚያደርገው ገባኝ......ግን ምን ድል......ድሉ ምንድን ነው?......ምን ሠርቶ?......የኤሌክትሪክ ባቡር ሰርቶ?......ናና ከረሜላ ሰርቶ?......ይሄ ቀዳዳ መርፌ ሰርቶ?......ድሉ ምንድን ነበር ይኼ የእኛ ሰው?......ይኼ ለራሱ እያጨበጨበ የሚሮጥ ያ ብልጥ ድሉ ምንድን ነው?......ልቤ እንደ ቆመ ዓይነት ነበር:: መንቀሳቀስ አልቻልኩም:: በኩረ በእኔ አቅጣጫ ሳይመጣ እንዳላየኝ ሁሉ ፊት ለፊቴ ዳገቱን እየወጣ ጨለማ ውስጥ ጠፋ:: መሮጥ ፈለግሁ:: መሮጥ፣ በጣም መሮጥ ፈለግሁ:: በኩረ በጆሮዎቹ ከበሮ እንዲሰማኝ:: ማንባረቅ ፈለግሁ:: «እናንተ ታላቅ ሕዝቦች አቤት ስወዳችሁ» ልል ፈለግሁ:: እሪ ማለት ፈለግሁ:: «እናንተ ይህቺን አገር በኢንዱስትሪና በኪነጥበብ ያጥለቀለቃችሁ» ብዬ ልጮህ ፈለግሁ:: ጆሮዎቻችንን እንደ ቁራሽ እንጀራ ለቁርስ በልተናቸዋል:: ጨለማ ውስጥ እጄን ጨበጥኩ፣ ራሴን በቡጢ መታሁ:: ወደ ጫልቱ ቤት በሩጫ ተመለስኩ:: የጫልቱ ቤት በር ተዘግቷል:: ምናልባት የእኔ ነገር አበሳጭቷት ቶሎ መተኛት ፈልጋ ይሆናል:: ከውስጥ ይበራል:: አንኳኳሁ::

"ማነው? አለች

"መዝገቡ ነኝ"

"ምን ቀረህ ደ'ሞ?"

"ክፈቺ"

"ንገረኝ ምንድን ነው?"

"ስለቅድሙ ነው"

"አሆይ እቴ ያለቀ ነገር.......ምን አድርጊ ልትለኝ ነው.......የሌባ ዐይኑ-ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ......."

በር ከፈተች:: ገፍቼአት ገባሁ:: ፊቴን ስታይ ደነገጠች::

"ተጣላችሁ እንዴ መዝገቡ.......?"

"ምን?"

"ምንድነው የምትፈልገው?"

"ምንድነው ያልሽው? ተጣላችሁ? ከማን ነው የምጣላው?"

"ኸረ ዝም ብሎ አፌ ላይ መጥቶ ነው"

"አወቅሁ:: በኩረ ነው የነገረሽ አይደለም?"



@BOOKALEM

ከእኔ ራቅ ብላ ተቀመጠች:: በውስጥ ልብስ ናት:: ብልህ ትመስለኝ ነበር:: ሽንኩርት፣ ቃሪያ ገዝቶ ወጥ ሰርቶ መሽቀል ትልቅ ችሎታ አይደለም:: ኮሌጅ ተምሮ መውጣትም ትልቅ ችሎታ ላይሆን ይችላል:: እተቀመጠችበት አያታለሁ:: ደሐ ናት፣ አስቀያሚ ናት፣ ጅል ናት:: ሁሉን ጠቅልላ ያጣች ናት:: ነገሩ ግልጥ መውጣቱ አንገቷን ሰብሯታል:: አፍራለች:: አዝናለች:: ምን እንደሚያሳፍራት፣ ምን እንደሚያሳዝናት ግን አልገባኝም ነበር::

"እንዴት አወቅህ?"

"እውስጤ የነገረኝ ነገር አለ"

"እውስጤ የነገረኝ ነገር ብሎ ነገር ምንድን ነው?"

ተጠጋሁዋት::

"እሱ ነው አይደለም?"

"ተውኝ እባክህ"

ያዝኳት:: እጇን ጉትቼ ከተቀመጠችበት አነሳሁዋት:: ምን እያደረግሁ ነው? የአንገቷ ቆዳ በጣም እጅግ በጣም ለስላሳ ነበር:: የግድግዳውን የአምፖል ብርሐን የሚቀበል ጠይምነት ነው:: የወርቅ መስቀሏ ደረቷ ላይ ተንቀጠቀጠ:: ጆንያ ጡቶቿ ግራና ቀኝ ዋለሉ:: ልትነጥቀኝ ሞከረች:: ለቀቅሁዋት::

"ለማንኛውም ማን እንዳወራ አውቃለሁ:: እሱ ሰውዬ ለምን እንደሆነ አላውቅም ጠምዶኛል"

ታየኛለች::

"እኔ እንድሰቃይ ትፈልጊያለሽ እንዴ?"

እጇን ደረቷ ላይ አጣምራ ታየኛለች:: አንጀቴ ሊቆረጥ ይጉተታል::

"እኔ እኮ አንቺን አልጠላሽም"

"ለምን እንደዚያ ዐይነት ነገር ትናገርብኛለህ?" እንደ መሽኮርመም::

"ሰማሽ ሚልቱ የሰው እንጀራ አፍራሽ እንዳልሆንኩ ታውቂያለሽ"

ዝም አለች::

"ተግባባን?"

ዝም አለች::

"በይ እሺ ደክሞኛል.......ነገሩን እንርሳው.......እ"



@BOOKALEM

"ለምን ይረሳል?"

"ተናገሪ ሲሉሽ አትናገሪም። ትደብቂያለሽ። ማን እንደነገረሽ አውቄአለሁ። እኔ እንዳላውቅ ሚስጢር ማድረጋችሁ ከሆነ አውቄዋለሁ። በእናንተ ቤት እኔ ደንቆሮ ነኝ። እኔ ንቄሽ አላውቅም፡ ግን አንቺ ከዚያ መስሪ ጋር ሆነሽ ናቅሺኝ። ዝም እንበል በቃ። እኔ ንቄሽ አላውቅም፥ ግን አንቺ ከዚያ መሰሪ ጋር ሆነሽ ናቅሺኝ። ዝም እንበል በቃ። አንቺም ከባልጠትሽ ጋር፣ እኔም አለብህ ከተባለብኝ ድንቁርና ጋር። ከዚህ በሁዋላ ምን ልታደርጉ ነው? በመንኩራኩር ጨረቃ ላይ ልትወጡ? እ.......ወይ ለምን አትጋቡም.......?"

"ተው እንደዛ አትበል"

"ሰው ላይ እንዲህ ከምታሴሩ ያው ተጋብታችሁ ብትኖሩ ጥሩ ነው"

ጫልቱ አንገቷን ሰብራ ማልቀስ ጀመረች።

"ይኼም ኑሮ ሆኖ ንጭንጭ በዛበት እኮ"

ወለል ላይ ትናፈጣለች። ንፍጧ ከጣቶቿ አልበጠስ ብሎ እንደ ሸረሪት ድር ይወዛወዛል። ጣቶቿ ላይ ይተበተባል። ቅር አለኝ። ያንን ሁሉ ዕድሜ ኖሬ፣ ያንን ሁሉ ብቸኝነት አልፌ.......ከሰው መቀላቀል ስጀምር ማድረግ የቻልኩት ትልቅ ነገር አንዲት ምስኪን ሴት ማስለቀስ ነው እንዴ? የሕይወት ጉርፍ ከተለያየ ቦታ ነቃቅሎ እዚያች ጠርዝ ጥሎን መተሳሰብ ሲገባን፣ መታለሷን መረዳት ሲገባኝ.......ስሜን ያበላሸውን ሰው ገና ለገና ማን እንደሆን በላሁትና ምን ይጠበስ?። ቁስሎች በቁስል ይጠፋሉ እንዴ? ቂም በቂም ይጠፋል እንዴ? ያነሰን ፍቅር ነው። እኔም ያነሰኝ ፍቅር ነበር። እእን ያነሳት ገንዘብ አልነበረም፥ ፍቅር ነበር፡ ጥቂት ሰው መሆን ነው። ያነሰን ወንዝ አይደለም.......ለተከፋ የምናረግፈው አንድ የዕንባ ጠብታ ነው። እሱም ውድ አይደለም። ሁሉ በየሐይማኖቱ ይመረቃል። ብዙ የተማርኩ ባልሆንም አይቼአለሁ። ቁጭ ብዬ ቂጤ እስኪያብጥ ሰው ሲያሴር፣ ሲተበትብ፣ ሲያፈቅር አይቼአለሁ ሰምቻለሁ። በብዛት ካሉ ጥሩ ጎዳናዎች ለምን እግሮቻችን ሞለጭላጫውን እንደሚመርጡ አላውቅም። የአእምሮ ብስለት ነው እንዳልል ናና ከረሜላ ለልጆቻችን እንኳን አልሰራንም.......አንዳንድ ጊዜ ራሴ መንጋ ውስጥ የጠፋ ጉዳ ከብት ይመስለኛል......የጠጣ እረኞች ጅራፍ የሚያጮሁበት.......

እኔ ተቀምጬ እሷ ስታለቅስ አየሁዋት። ብዙ አየሁዋት። ጉኗ ጠጋ አልኩና አቀፍኳት። ለምንድን ነው ያልተሰጠኝን የምሰጠው? ማናባቱ ነው ቀድሞ እጁን ትከሻዬ ላይ ጭኖ ያፅናናኝ??!!



@BOOKALEM

# «እዩማ! ሁለት የሰበታ ቲማቲሞች»

አንድ ሰለት ከሲኒማ ራስ ወጥተን በአቋራጭ ምንገድ ወደ ቤቷ እንሒድ ተባብለን እጅ ለእጅ ተያይዘን ነበር:: በዚያች ደቂቃ ውስጥ በዚህች ምድር ላይ እንደ እኔ የተደሰተ ያለ የነበረ የሚኖር እንጃ አልኩ:: ቢኖሩም እንደ ገነት ያሉትን ያቀፉ መሆን አለባቸው:: አልታደሉምና ገነት አንድ ብቻ ነበረች:: ያቺም አንዷ ከራስ ቲያትር ዝቅ ብላ ተክለ ሃይማኖት አደባባይ መዝገቡ ከሚባል ሎጋ ልጅ ጋር ተቃቅፋ እየሄደች ነበር(እስኪ በሳቅ ልንደቅደቅ):: የማየው ነገር ቢኖር እሷን ብቻ ነበር:: እና የመኪና ምንገድ:: ወሳ እሱም የነፍስ ጉዳይ ሆኖብኝ:: ታክሲ መውሰድ እንችላለን:: አልፈለገችም:: የገዛሁላትን አዲስ ጫማና አዲስ ቀሚስ ለብሳለች:: አባቷ እኔ እንደገዛሁላት ያወቁ መስሉኛል::

አባቴ 'ግድ የለውም' ትለኛለች::

ሰፈሯ ስንደርስ ጨልሟል:: ቅዳሜ ቅዳሜ ማታ ደ'ሞ ያ ሠፈር ጨርቁን ጥሎ እንዳበደ ይሰራዋል:: ቤቷ እንድገባ ጠየቀችኝና ሳላንገራግር ተከተልኳት:: ገና እንደተቀመጥን የሚበላ ላምጣ ስትል ልከራከራት ፈልጌ እጇን ስይዛት ከመሐላችን ቆሞ የነበረ የሆነ የተጋረደ ነገር ወደቀ......(ወደ ገፅ 388) በሚጣፍጥ ሐይል እንደመዘንተር ነበር:: ክሱት ገላ በሌለው ሞገድ:: እየተንቀጠቀጥኩ ፊቷን በሁለት እጆቼ ያዝኩ......እሚልጮኝ እንደሚወድቅ ሁሉ፡ እንደሚፈስ ሁሉ:: የማደርገውን አላውቅም......ፊቴ ፊቷ ላይ ወደቀ.......

በሩ ክፍት ነበር?

እንዴታ:: በሩ ክፍት ነበር.......

ሁለቱም መስኮቶቹ የግቢውን አጥር ከፍተን ስንገባ ጀምሮ እንዲህ ግትር ብለው የሚያዩን......እነሱ......ክፍት ነበሩ::

የሳሎናቸው አንዷ ስድሳ ሻማ አምፖል ትበራለች::

ምን እንደማደርግ አላውቅም......

እጆቼ የማይነኩት የገላዋ ክፍል አልነበረም:: ሁለመናዋ ነበረ:: እጆቼ ንክ ሆኑ:: አለች:: ሁልጊዜ አለች:: ሁሉ ቦታ አለች:: ትንፋሼ እንደ ቆላ ነበር:: ደንከልን ውጨአት እንደ ነበር ሁሉ:: የእሷም ትንፋሿ እንደ አዳማ አምበር:: ፊቶቻችን ከርታላቸው እንደ ፈነዳ የሰበታ ቲማቲሞች ረጥበው......



@BOOKALEM

በፀጥታ ተቃቅፈን ተቀምጠን፡፡ ሕፃናት ደጃፍ ሲጫወቱ እንሰማለን......ስለ እህቷ ድምፅ ትኩስነት ትነግረኛለች......እንደ ላስቲክ በሚጎተት ቀስስተኛ ድምፅ......ጥቂት አዛውንት ዕዳሪ በምሽቱ ሙቀት ውስጥ ወሬ ያደሩ ነበር......መርካቶ የምሽት ቀኪዋን ታጮኻለች......የሽሮ ራቷ ላይ ወድቃ......የአዲስአባ ጉዳናዎች ኩሶ እንደጠጣ እንጀት መራቆት ጀምረዋል......የራስ ቲያትር የጫት ጠረን በልብሳችን ላይ ተንጠልጥሏል......የመርካቶ ዳሌ በምሽት ሰካራም እጆች ይዳበሳል......ጡቷንም ጥላ ለገበያ ወጥታለች......ይህቺ ከተማ ቢጃማዋን እያወለቀች......እኔና ገነትም በሕልምና በዕውነት መሐል እንደታዳጊ መላዕክት እየተንሳፈፍን......በፀጥታ ቃል እንዳይወጣን አድርገን ተቃቅፈን ለብዙ ጊዜ ቆየን......ባይመችም፡፡ ወገብ ቢያምም፡፡

ማታ ስሰናበታት ፀጉሬን ነጨሁ......ተሽከሜአት ልሔድ ፈለግሁ፡፡ ተሽከሜአት በሕንፃዎች ላይ፣ ከኤሌክትሪክ ሽቦዎች በላይ፣ ከዛፎች በላይ ነጭ ቀሚሷ እንደ ክንፍ እየተውለበለበ......ሰዎች አንጋጠው እንዲህ ሊሉ፡

"እዩማ......እዩማ ሁለት ተወርዋሪ ኮከቦች!"



@BOOKALEM

# «ጨረቃ ስትወጣ»

'ጨረቃ ስትወጣ' የተባለችዋን ፍቅረኛ መፅሐፌን አንድ ቀን ማታ አንስቼ ሳነባት ጀመርኩና ድግግሙን ስላበዛሁት ሳይሆን አይቀርም መሰለኝ (አስላችታኝ) በእንክብካቤ ወደ ነበረችበት መለስኳት:: ቢሆንም አስብ ነበር አንድ ቀን ጨረቃ ስትወጣ ጠብቄ ገነትን ይዤአት እንጦጦ ተራራን ለመውጣት:: ቢሆንማ የእኛን ነገር አይቶ መንግስት 1,000 እስረኞች ከከርቸሌ በነፃ ይለቅ ነበር:: መንግስታት ግን ብልጦች ናቸው:: ቀድሞ 'ብልጠት ከፍቅር ይበልጣል' ተብሎ በበልጫጮች ተነግሮአላ......ብርሐኑ እንኳን ባይመስለውም:–

*መከሩን ብልጦቹ ጅሎቹን ሲያፅናኑ*  
*እንደ ቅዠት እርሱት በፍቅር አትመኑ*  
*ፍቅር ጅልነት ነው፣ ይሁን! ከተባለ*  
*የሸነፈው ብልጠት አሳዩን የት አለ*

ብሎ የለ::

አንድ ጊዜ ይህቺን የምወዳትን መፅሐፍ ገነት ተውሳ ወሰደቻት:: እንድትመልስልኝ አልጠየቅሁዋትም:: የሰውነት ፍቅር ይበልጣል ወይስ የፍቅር መፅሐፍ???

ወዘተ......



@BOOKALEM

# ጠባሳ ሲተነትኑ

ድሮ ትከሻና መጋፈያዬ ላይ የፈላ ውሐ ፈሶ የሰራልኝን ጠባሳ በራሴ ሀይኖች አይቸው አላውቅም ነበር። ታምሜ የታከምኩት ዕለት እንኳን ነርሱ ይስሐቅ ከጀርባዬ ሆኖ ቁስሉን ሲጠርግና ፋሻ አስሮ ፕላስተር ለጥፎ ሲልከኝ እንጂ......የቁስሉን መጠን፣ መልኩን......እና እንዴት ቀስ በቀስ እንደ ዳነ እንኳን በዐይኖቼ አላየሁም ነበር። አልፎ አልፎ ስራ ባጣ እጄ ስዳብሰው ልስላሴው ያስፈራኝና፣ ያስደነግጠኝና ልረሳው እፈልጋለሁ። እረሳዋለሁ። ብቻዬን ስለማድር፣ ስለምተኛ፣ ብቻዬን ገላዬን ስለምታጠብ ምናልባት ከኤልያስ በስተቀር ልብ ብሎ ያየው ሰው ያለ አይመስለኝም። ኤልያስ እንኳን አይቶ ምን ሆኜ እዚያ ቦታ ላይ እንደተመለጥኩ አልጠየቀኝም። ምናልባት ስዳብሰው የቆዳው ልስላሴ ከሌላው የገላዬ ክፍል የተለየ በመሆኑ ባይታወቀኝ ኖሮ 'ጠባሳ አለብህ' ብለው ቢነግሩኝ የማምነው ሰው ያለ አይመስለኝም።

የዚህን ጠባሳ ስፋት አላውቀውም ነበር።

የዚህን ጠባሳ እርዝመት አላውቀውም ነበር።

ይሔ ጠባሳ ከትከሻዬ አጥንት ከመጋፈያዬ ምን ያህል እንደሚርቅ አላውቅም ነበር።

ይሔ ጠባሳ ጀርባዬን ወይም ግማሹን ጎኔን ብቻ ይሸፍነው አይሸፍነው አላውቅም ነበር።

ይሔ ጠባሳ ምን ዐይነት ቀለም እንዳለው አላውቅም ነበር።

የዚህ ጠባሳ መሐከሉ ቀይ። ጠርዝ ጠርዙ ጥቁር ይሁን ወይ አይሁን አልረዳም ነበር።

አልፎ አልፎ (ኸረ ብዙ ጊዜ) ስለ እኔ ጠባሳ ለመረዳት የምሞክረው የሌላ ሰው ጠባሳ በማየት ነበር። ቅንድብ ላይ ከሚሰሩት ጭረቶች ጀምሮ ምንገድ ላይ እስከተኙት ቆማጦች ድረስ የጠባሳ ዐይነት አጠናለሁ። ሁሉ ነገር ግን ይጨልምብኛል። ሺህ ዐይነት መጠን፣ ቀለም፣ ቅርፅ በተለያየ የአካል ክፍል ላይ ማየቱ ብቻ ሳይሆን ምክንያቱም መታወቅ ያለበት እየመሰለኝ የዐይኖቼ ጥናት ዋጋ ያጣብኛል። ተመሳሳይ ጠባሳዎች በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ። እኔ ከማያቸው ጠባሳዎች ሁሉ የትኛው ወይም የትኛዎቹ በፈላ ውሐ እንደተፈጠረ ወይም እንደተፈጠሩ መገመት አልችልም። ሁሉ ነገር ይጨላልምብኝና ልረሳው እፈልጋለሁ። እረሳዋለሁ።



@BOOKALEM

እቤት ውስጥ ቀን ቀን የለበስኩትን ካናቴራ ሳለውጠው ማታ እንደለበስኩት ስለምተኛ አብረውኝ የሚያድሩ ጊደኞቼ ጠባሳዬን የማየት በቂ ዕድል አሳገኙም ነበር:: መችም መሳሳት አይቀርም:: መሳሳት አይደለም:: መርሳት:: ቢታይ እንኳን ግድ ባይሰጠኝም ተሳሳትኩ:: ረሳሁ ልበል:: የበኩረ ዐይኖች ጥሩ አጋጣሚ አግኝተው ጠባሳዬን አይቶ፡—

"ምን ሆንክ አንተ ይኼን ጠባሳ?"

ዝም አልኩት

"ተቆማምጠህ የለም?"

ዝም አልኩት::

"ታያላችሁ......ጀርባውን......ባቡር ሔደብህ እንዴ?"

ዝም አልኩት::

"ካናቴራሽን ሳታወልቂ የምትተኚው.......እንዳይታይብሽ ነው ሃ......ሃ...... ሃ......"

ዝም::

ተኛሁ:: ልቤ፣ አእምሮዬ ግን አልተኛም ነበር::

የሚቀጥለው ቀን ወይም ሌላ ቀን በኩረ አልለቀቀኝም::

"ዛሬ እዚህ ተክለ ሃይማኖት አንድ አህያ ወድቃ ነበር.......እግሯ ተሰባብሮአል መሰለኝ መነሳት አትችልም.......መኪናው ሁሉ እየዞረ ያልፋታል.......መዘጋጃ ቤት እስኪያነሳት ድረስ.......ሁለት ሰዓት ያህል ቆይተን ስንመለስ.......አሁንም ተኝታለች .......የተሰቃየች አህያ መሆን አለባት.......ገጣባዋ ከማጅራቷ እስከ ጅራቷ ይደርሳል......."

ወዘተ.......

ዝም::

ተኛሁ:: ልቤ፣ አእምሮዬ ግን አልተኛም ነበር::

ምናልባት ይኼ ሰው እንቅልፍ ማጣቴን ይፈልግ ይሆናል:: እኔ እንቅልፍ ባጣ እሱ እንቅልፍ ይጨመርለት ነበር እንዴ?

አንዱ በፈላ ውሐ ሲያቃጥለኝ ወዳጁ ሌላ ቦታ ጠብቆ ያንገጥጠኛል:: ቁጣ በደም ስሬ እንደ ቶሎሳ ቆቱ ይሮጣል:: ይሮጣልም ይዘላልም......ፊቱ ግን የበኩረን የመሰለ:: እንዲህ እንደ እሱ ዓይነት አፍንጫ ያለው ሰው አላየሁም.......እሰው ጉዳይ እየገባ



@BOOKALEM

የሚያሸት:: ወይም ለእሱ የሚገባውን ጠባሳ ወስጄበት ይሆናል:: ጠባሳዬ ጌጥ መስሎት ቀንቶ ይሆናል:: ከአንዳንድ ችግሮች የምሸሸው በፍርሃት አይደለም.......አብሬው ላለመውረድ ነበር::

ነውን?

ትንታኔ ነውን?

አፌ ብረት ብረት ይለኝ ጀመር::

ወንድ ባይሆን ኖሮ በኩሬ እንጀራ እናቴን ራቧን::

ጥርሱንም ባይፍቅ:: (እእ ስትፍቅ አይቼአት አላውቅም:: ወይስ ረሳሁት?)



@BOOKALEM

# ሀኬተኛው እንዲህ ይላል፡ «ወሉዬው የት አለ?»

ኸረ የት አለ ያ ወሎዬ?

ኸረ የት አለ ያ ድምፅ?

ኸረ ያ ከዝተቶች ሁሉ ውብ የሆነው ዝተት የት አለ?

ኸረ ያ ከፍንጭቶች ሁሉ የፈነጨ ወሎዬው የት አለ?

ኸረ ያ ከፍንጭቶች ሁሉ የፈነጨ ወሎዬው የት አለ? እንዲያ እል ነበር፡፡ (sic)

አንዳንድ ቀን እሱና የእሱ ነገር ትዝ ይሉኛና ለብቻዬ እንዲያ እል ነበር፡፡ በአምባሳደር ቲያትር በኩል ሳልፍ በሕሊናዬ እሱ በመገረምና በፍርሃት እጠመዳለሁ፡፡ በአምባሳደር ቲያትር በኩል ሳልፍ በሕሊናዬ እሱ የተናገረውን እያሰላሰልኩ ዞር ይልብኛል፡፡ ደክሞኝ ጥቂት ዱርዬ አሩዋሩጬ ይገር፣ ወይ የፀሐይ ቃጠሎ በእናቴ ሳበርድ እውልና፣ ወይ ፕሬዝዳንት መንግስቱ የሚያልፉበት ምንገድ ሆኖ ሰውን ተመለስ፣ ምንገድ አትሻገር እያልኩ ጉሮሮዬን አድርቼ ስጨርስ፡ ጥላ ስር ተቀምጬ በባርኔጣዬ ስሜወት የሚጠራኝ ሰው፣ በራሴ ሳንቲም ጋብዤም ቢሆን ኒያላዬን እያጤስኩ የማጫውተው ሰው እፈልጋለሁ፡፡ ስሜን ምንገድ ላይ ጠርተው ካጫወቱኝ ሁሉ ወደ ልቦናዬ የሚቀርበው ወሎዬው ነበር፡፡ ቢኖርና ቢረብሸኝ እላለሁ፡ እንዲህ ስፈልገው ታዲያ የነገረኝ ታሪኮቹ ሁሉ እውነት ይመስሉኛል፡፡ ስሜን ሰልሉ ማግኘቱ ገርሞኝ ነበር፡፡ የማላውቃቸው ብዙ ዱርዬዎች ስሜን ያውቃሉ፡፡ ግን እሱ ም ሊጠቀመው? ይሄን እንኳን እንዲያብራራልኝ ሳልጠይቀው ነው የጠፋው፡፡ ጊዜ በራሪ፡፡

አወይ ጊዜ በራሪ.......

እኔም እንደተሰራሁት በአለባበሱና በጤናው ጠርጥሬ ችላ ስላልኩት አንዳንድ ገ ቁጭት የምሽት እልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ ሲቀጠቁጠኝ......ይህቺም የፖሊስነት ት ፍሉስ ተራ የማልመኘውን ኩራት ከትባኝ......ይህቺ የለበስኳት በከሰል የተተኮሰች ካኪ ከተገኘው ወገኔ የሚያገናኘኝን ድልድይ ሰብራ......በዚህም የዕርጉማን ዕርጉም ነኝ፡

የት ሄደ ግን?

ውሎዬው የት ሄደ ግን?

እያሰለስኩ እያሰለስኩ እንዲህ እል ነበር፡፡

ከጠዋት እስከ ማታ እለፋለሁ፡፡ የምለፋውም በቸልታ፡፡ ነገሥታቶቼ ምቹ ይተኛሉ፡፡ የሚንቀጠቀጥ ማለፊያ እንጀራ ሰሐኖቻቸው ላይ ዘርግተው የእኔ የደን ነገር ገርሞአቸው በሳቅ ይፈርሳሉ፡፡ በንቀት የመጣ አለመግባባት እንጂ ሌላ ም ነው? ይሄ ቸል ያደረገኝ ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉ በቆዳ ቦት የታሰሩትን እግሮቼን ማ



@BOOKALEM

አወላልቄ ሳያቸው ያበጡና የቀረኑ ናቸው:: ይሄም ቸል ያደርገኛል:: ስለእኔ ስለደሃው እያወሩ በቅቅል ባሕር ላይ፣ በበሬ ጎድን ጀልባ ውስጥ የክትፎ ዓሣ ያጠምዳሉ:: እኔ እህቴ ሜልቱ ቤት ነጭ ሽንኩርቱ ያልሞተ ሽሮ በቅራሪ አምጌ አድራለሁ (ምን? ብል ስንት ሺህ ሕዝብ በድርቅ ተጎድቶ ይሉኛል:: ደሐ ብትሞት ደሐ ትቀበል እንደማለት) ይሄም ቸል ያደርገኛል:: እኔ መማሪያ መፅሐፍ ሳይኖረኝ እነሱ ልጆቻቸውን አውግዙት እያሉ ወደሚያባሉን ምዕራብ አገር ይልካሉ:: ይሄም ቸል ያደርገኛል:: ከጉበኛ ትራፊኮች እላከፋለሁ፣ ሳይገባኝ ሁሉም ጉቦ እንደሚወድ:: ይሄም በልግም ይመታኛል:: ግድ የለሽ ያደርገኛል:: እያንዳንዱን ዜጋ እንደ መሪዬ ልጠብቀው እፈልጋለሁ:: እሱ ግን ይንቀኛል:: ሐሳቤን ሲሰማ 'የጠገበ ወታደር' ይለኛል.......ይሄም ቸል ያደርገኛል:: ያጠፋ ሳስቀጣ ያጠፋው ይጠላኛል:: 'ወንድሜ ከስህተትህ ተማር' ስለው ይገላምጠኛል:: ይሄም ቸል ያደርገኛል:: 'እህቴ ሆይ በእሱ በኩል አትሂጂ መኪና ሲታጠፍ ትገጪያለሽ' ስላት:: 'የማነው ዝተት' ትለኛለች:: መኪናው ይላተማታል:: እያነከሰች ተነስታ 'ያ ነጃሳ ፖሊስ ነጅሶኝ ነው' ትላለች:: ይሄም ያስከፋኛል:: ቸልም እላለሁ:: ሁሉም እላለሁ የከንቱ ከንቱ ነው:: 'አውቶቡሱ ውስጥ ቀስ ብላችሁ ግቡ' እላለሁ፣ 'ወሮበላ አለ' እላቸዋለሁ:: 'ከየት የመጣ ነው፣ ምጥ ለእናቷ አስተማረች' ይሉኛል:: ከዚያ ይዘረፋሉ:: ይሄም ያሳዝነኛል:: ይሄም ቸል ያደርገኛል:: ወሮበሎችም ይጠምዱኛል:: እነሱም ያማሩ ወሮበሎች በየመንገዱ ቆመው ወደ እኔ እየጠቆሙ 'እሱ ሕዝብ ደሕንነት ነው' ይሉኛል:: ይሄ ያስከፋኛል:: የወረበሎቹ ጠላት ነኝ የሚለውም ሠላማዊው ሰውም ያምናቸዋል:: ይሄ ቸል ያደርገኛል:: ይሄም ንዝህላል ያደርገኛል:: ለሕዝብ ስልክ አስር ሳንቲም ያወጡና ሳጥኑ ሲውጥባቸው ውዱን ማሺን ይደበድቡታል:: 'ኸረ ተዉ' ስላቸው 'የማን ነዝናዛ ነው' ይሉኛል:: ይሰበራል:: ሌላው ዜጋ መጥቶ ይሞክርና አልሰራ ሲለው 'የማይረባ ስልክ አስቀምጠው በዘበዙን' ይላል:: 'ከአንተ ቀድማ እህትህ እዚህ ነበረች' ስለው ያልገባቸው ዐይኖቹን በቁጣ ያገላብጣል:: በዚህም አዝናለሁ:: ሃኪትም በደም ስሬ ይሰርግብኛል::......

......በየሰፈሩ እየዞርኩ ጠላ እንድጠጣ ይፈልጋሉ:: እምቢ እላለሁ:: ከሱሶች እርቃለሁ:: በዚህ ያኮርፉኛል:: በዚህ ይስቁብኛል:: በሚያማምሩ ጥርሶቻቸው ይስቁብኛል:: ቸልታ ይነፍስብኛል:: እትትተት፣ እትትትት እላለሁ:: 'አትጃጃል' ይሉኛል:: 'ምኔ ተጃጃለ?' ስላቸው 'ለምን እንደ ሰው አትሆንም' ይሉኛል:: 'ድራፍት ሰው ያደርጋል' ይሉኛል:: የድራፍት አረፋ እያደነቁ ያወራሉ:: 'ካገኘኸው ሰው ተጋበዝ የሚጋብዝ ተገኝቶ ነው' ይላሉ:: 'አይሆንም ኸረ አይሆንም' እላለሁ:: 'ቀሽም ነህ' ይሉኛል:: ቢራ፣ ክትፎ የሰው ምግብ ነው ይሉና ከወንጀለኛ ይዳራሉ:: የምን ሰው? እላለሁ:: በዚህም ይስቃሉ:: በዚህም ቅር ይለኛል:: በዚህም ቸልታ ይጠናወተኛል:: ወደ እኔ እየጠቆሙ እየሳቁ 'ምነው ከስራው ቸለለ?' ይሉኛል:: 'እዩት ያን ሀኬተኛ' ይሉና



@BOOKALEM

በኮሚኒስቶቹ ሊመሰገኑ ይለምናሉ:: ማርያምን እኔም ለመከላከያ አስቀድሜ ከጠዋት እስከማታ እለግማለሁ:: ሁሉም ታዲያ ሁሉን ይተቻል:: ሌላውን ይተቻል:: 'ዐይኖቻችን ውስጥ ስንት ስልክ እንጨቶች አሉ? የሰው ሰናፍጭ ስናሳድድ' ስላቸው አንጀታቸውን ይዘው በሳቅ......ለሁለት ታጥፈው በሳቅ ይፈርሳሉ::

ይሄ ሁሉ ይጠረቃቀምና ከንፋስ መውጫ የተሳፈርኩበት አውቶቡስ (14) ምነው ቢገለበጥ ኖሮ እላለሁ:: ምናለበት የአውቶቡሱ ሹፌር ዐይኖቹን ጋርዶት የሆነ ዓባይ የሆነ ዴዴሳ ይዞኝ ቢወርድ:: ያቺ ልቤ ውስጥ የቀረችው በሰው ልጅ ላይ ያለችኝ ትንሽ ዕምነት እንደ በረድ ኩይሳ ስትቀልጥ እሰማታለሁ:: ብቻዬን ሆኜ ዕምነት የሌለው ለመሆን ትንሽ እንደ ቀረኝ ሲገባኝ ሰውነቴ በፍርሐት ይንቀጠቀጣል::

ከዚያም እነሱው መልሰው ይላሉ.......'እንዴት ነው ትንኙ ሁሉ ብልጥ በሆነባት በዚህች መሬት አንዲት ጠብታ ጣዝማ መሥራት የከበደን.......'

ቢቸግረኝ የሚሰማኝ ወዳጅ ባጣ ወሉዬው የት ሔደ?......አልኩ::

የማይሞቱ እስስቶች ሜዳችንን ሸፍነው እንደ ትራክተር ይንገላወዳሉ:: መሬቷ በቆሻሻ ወፍራለች:: ጠባሳችን ሁለመናችንን ሸፍኖታል:: ማሩ የደረቀ ቀፎ ውስጥ ተቀምጠን ክንፋችንን ተበላልተን በጉንድሻችን የምናቃስት.......በዝገት የኩራን.......ታሪክ እንደንብ፣ የየቀኑ ሕይወት ግን ዝንብ ያደረገን......ታሪክ ታላቅ......ዛሬ ዛሬ ግን ቆለጣችን (በግራ እጄ አቅፌዋለሁ:: እንዳይጠፋ ወይ እንዳልጥለው) ላይ የተመታን.......

ቢቸግረኝ የሚሰማኝ ሌላ ወዳጅ ባጣ ወሉዬው የት ሔደ?......አልኩ::

ክንፎቼን ማን ወሰዳቸው አንተ ወሉዬ.......? እንተ ስሜን በመውደድ የጠራህ፣ ሽበትህም ከየረር ዳመናዎች ይብልጥ የተቁጠረጠረ::

ቢቸግረኝ የሚሰማኝ ሌላ ወዳጅ ባጣ ወሉዬው የት ሄደ? እል ነበር......



@BOOKALEM

# ወይም የዕርጎ ዝንብ

ዕርጐ መጠጣት የጀመርኩት ፖሊስ ከሆንኩ በሁዋላ አልነበረም:: ሙስጠፋ ቤት በትልልቅ ብርጭቆ፣ «ክብር ዘበኛ» በተባለ ብርጭቆ እስከ አፍ ጢሙ ተሞልቶ በ25 ሣ እየገዛሁ አንዳንድ ጊዜ ጠጥቻለሁ:: እንደ ዳቦ የሚቆራረጥ የሐገር ቤት ዕርጐ:: እኔ አላጋጠመኝም እንጂ ዕርጐ ውስጥ ዝንቦች ይገባሉ ይባላል:: አይገርምም? አጋጥሞኝ አያውቅም:: ውሐ፣ ሻይ፣ ኮካኮላ ውስጥ ዝንቦች ገብተው ሲዋኙ፣ ሲንፈራፈሩ......ወይ ዋኝተው ሲድኑ......ወይ ተንፈራፍረው ሲሰምጡ ወይ ሞተው ሲዘረሩ አይቼአለሁ:: እንዲህ ያጋጠማቸው ሰዎች እንደ ፀባያቸው ዐይነት ወይ ይበሽቃሉ ወይ በዝንቧ ይቀልዳሉ:: ለዕርጐ የተሰጠው ክብር ይሁን ወይም የዕርጐ ንጣትና የዝንብ ጥቁረት አይጣጣሙም በሚል ሀሳብ ዕርጐ ውስጥ በሮ፣ ዘሎ የገባ ዝንብ አይወደድም......'የዕርጐ ዝንብ' የተባለ ዘይቤ ያኔ የመጣ ይመስለኛል:: ሌላ መጠጥ ለምሳሌ ጠላ፣ ጠጅ ውስጥ የገቡ ዝንቦች 'ሲሳይ' ይባላሉ::

በእንጀራ እጥፋቶች ተጠቅልሎ፣ በወጥ እረጥቦ ክንፉን አጣጥፎ 'ሰመመን' የገባ ዝንብ አጋጥሞኛል:: እኔም በሕይወቴ ተምሳሌታዊ በሆነ መልክ እርጐ ገቢ ዝንብ አጋጥሞኛል:: እንደገዛው፣ እንደለፋበት፣ ወይም ዕርጐው እንደጠራው......በጠረን፣ በጥቅሻ፣ በደብዳቤ፣ በሥም::

ወይም:

ዕርጐ - ገነት

ዝንብ - በኩረ::

ታዲያ አንድ ቀን ማታ በኩረ እየተንጐራደደ ገባና እኔ መኖሬን ጠየቀ:: መጠየቅ አያስፈልግም:: እዚያው አጠገቡ አለሁ:: ያየኛል:: ምናልባት እሱ ተናዶ ሕሊናውን ስቶ እኔም ቀጭን በመሆኔ አልጋ ላይ ስጋደም ጠፍጣፋና የማይታይ በመምሰሌ እንደሆን አላውቅም:: ዐይኖቹ ትግ ትግ ትግ ይላሉ::

"ምነው?" አልኩት

"ያቺን ልጅ ታባልጋለህ?" አለኝ

"ማንን?" አልኩት

"ማንን ይለኛል? እዩትማ" ጮሆ:: የተ/ሃይማኖት ወረዳ ሕዝብ ቢሰማ ብሎ ሳይሆን አይቀርም:: እቤት ውስጥ ጃፓንና እኔ ብቻ ነበርን::

"ማንን ነው?"



@BOOKALEM

"ገነትን ነዋ"

"ምን አደረጂት?"

"ምን አደረጂት ይላል?......ዱርዬ ታደርጋታለህ?"

ዝም አልኩና ዐይኖቼን ከደንኩ:: ማውራቱን ቀጠለ:: ጃፓን ይሰማዋል:: እኔም እሰማዋለሁ::

"ከቤት ወጥታ የማታውቅ ልጅ እኮ ናት"

ይንጉራደዳል::

"እሷ ምን አደረገችህ? እንዷት ጨዋ ስትኖር ዱርዬው ሁሉ ዕረፍት ያጣል"

ይንጉራደዳል:: መላጣ አናቱን ያካል? ብዙ ጊዜ ስለሚላጭ::

"አብረን እንኖራለን በሚል ሰበብ እኔ ችላ አልልህም"

ወላ በሩን እንኳን መለስ አላደረገውም:: አንድ የጉረቤታችን ሴት ሲጮሁ እሰማለሁ::

"ባለጌነቱን ስለሚያውቅ ሚስጢር አድርጉታል:: ጨዋ ከሆንክ ለምን አትናገረውም? ምን አስፈራህ?" አልጋው ላይ ተቀመጠ:: በሩን በእግሩ መትቶ ዘጋው::

"ልጅ ነህ:: ሙት ልጅ ነህ:: የበሰለ ሰው እንዲህ አይሰራም"

ጃፓን ሳል ሳለ:: አሮጊቷ እየጮሁ ያወራሉ:: ሁልጊዜ ጥቁር ሻሽ የሚያስሩ የወይዘሮ ዝናሽን ቤት የተከራዩ ሴት ናቸው:: በጉላት ማውራት ይወዳሉ:: ጉሮሮአቸው ሾስት ይመስለኛል:: የትርቡት ሴቶች ካድሬ መሆን ይችላሉ::

"ልጅ መሆንህ ዱርዬ መሆንህ የተመሰከረልህ:: አገር የሚያውቅህ ነህ" ንፍጡ ሊወድቅበት እንደከጀለ ሁሉ በአፍንጫው ረዥም ወፍራም በዐይን ለመታየት ትንሽ የቀረው አየር ሳበ::

"ምን እንዳደረገ ታውቃለህ? ሠርቶ የሚሮጥ ህፃን ልጅ ጠልሎ ያሳድር ነበር:: የእሱ ቢጤ:: እዚህ ይተኛ የነበረ ልጅ ትዝ ይልሃል?"

ጃፓን ከተቀመጠበት ተነቃነቀ:: ወሬው የተመቸው መሰለ:: ሬድዮ አፐሬተርና ●ሬ::

"ያንን ልጅ ፖሊስ ሊይዘው ሲመጣ የሠራዊት አባልነቱን ተጠቅሞ ልጁን ጋዮት ከረሙ:: አሁን ልጁ ሲያዝ አወራበት......ልጁ አወራበት"

እኔንም ወሬው አሳሰበኛል:: ከተኛሁበት ባልነሳም እነበርኩት ጆሮዬን አቆምኩ::



@BOOKALEM

ጃፓን ተናገረ።

"መቼ ሰማህ ስለልጁ?"

"ቆይቶ የለም ወሬ ሆኖ.......የማያወራ የለም.......ሜልቱን አትጠይቃትም"

"እዚያ ሔደህ ወሬ ነው የምትበላው ወይስ እንጀራ?" አለ ጃፓን።

"ምን አግባህ......እኔ ጉዳዬ ከዚህ ዱርዬ ነው......."

"ልጁን ምን አድርጉ አሠሩት?" ጃፓን

"መጀመሪያ ሲሰርቅ ይኼ የማይረባ ሰው ጠለለው። ቂልነቱ ደ'ሞ 'ፖሊስ ነኝ ብሎ ራሱን ያስተዋውቃል። ተረኛው ፖሊስ ሪፖርት ያደርግና ታዝበው ሲጠብቁ ልጁ ተገኝቶ ይያዛል.......ከርቸሌ ገብቷል አሁን.......የተከለ ሃይማኖት ወረዳ ፖሊስ......."

"ለምን አለማየሁን አንጠይቀውም? አለማየሁ እዚያ አካባቢ ይሰራል አይደለ?"

"እኔ እዋሽሃለሁ? የምነግርህን አታምንም አንተ?"

"መጀመሪያ ይኼን ጉዳይ ያየውን ፖሊስ ለምን አንጠይቀውም? ልጁ ሳይጠየቅ እስር ቤት ደ'ሞ አይገባም.......ምናልባት ጠባይ ማረሚያ ቢወስዱት ነው......."

"አንተ ምን አገባህ?"

"ትንሽ ነገር ታበዛለህ"

ከአልጋዬ ተነሳሁና እያዛጋሁ ወጣሁ።

"ስማ መዝገቡ እኔ ስከራከርልህ አንተ ትወጣለህ?" አለ ጃፓን።

ዞሬ ስመለስ እያንቀላፋ የሚነጫነጭ ነጋሳ በሩን ከፈተልኝ።

"ከመቼ ጀምሮ እስከ እኩለ ሌሊት መዞር ጀመርክ?"

ከእኔ ቤት እስከ ገነት ቤት ከገነት ቤት እስከ እኔ ቤት ሁለት ጊዜ ተመላለስኩ። በምሽት የገነት ግቢ ዐጥታ ዕንቁላሏን እንደምታሞቅ ወፍ ጎጆ ነበር።



@BOOKALEM

# .......ኪነትና ኪነት

ከብዙ ወራት በፊት ይኼንን ስዕል አብዮት አደባባይ ላይ ሲሰቀል አንድ ሰው አንገቱን ተሰብሮ ነበር:: መቸ ዕለት ቀና ብዬ ላይ ሁሉ ነገር ትዝ አለኝ:: ያ ሰው መቸም እንዲያ ወድቆ እንዲያ ያ ሁሉ የገላው ክብደት አንገቱ ላይ አርፎበት የሚድን አይመስለኝም:: ማን ይድናል?

ታዲያ የተሰቀለውን ስዕል ሳየው የተበላሸው ቦታ እንዳልታረመ ተረዳሁ:: እንደውም ንፋስ የሚጨበጥ ነገር ማግኘቱ ነው መሰለኝ ቀሉት ስዕሉን እስኪታች ድረስ ተርትሮታል:: ቀድሞ ያየሁዋቸው የጎንደሯ ሴት ያለ ሃንጥላ ቆመዋል.......እርጎ ይመስል የነበረ ነጠላቸው በነፋስ በዝናብና በፀሓይ ሙቀት ተበድሎ ግራጫ ሆኖአል......



@BOOKALEM

# ኪዮስክ

ገነትን ላያት ቤቷ ስሔድ ከአባቷ ጋር የግቢአቸውን አጥር አፍርሰው የትንሽ ጉልት ኪዮስክ ለመሥራት እየታገሉ መሆኑን ስትነግረኝ ለመርዳት መቆፈሪያ ገሶ፣ ዶማ፣ መጋዝ ይዤ ቀረብኩ። አባቷ ገፁ-ከስታራ ቢሆኑም ትንሽ አብረዋቸው ተቀምጠው ካወሯቸው ቀልደኛ ነበሩ። የዚያን ቀን ብዙ ማውራት አላሰኘኝም ነበር። ምን አልባት ዝም ማለቴ ሳያበሳጫቸው አልቀረም። አልፎ አልፎ ለእሷ ሹክ ሲሏት "ከእኔ ጋር ብቻ ነው የሚያወራው" ትላቸዋለች።

ጠዋት አራት ሰዓት የጀመርን እስከ ሰባት ሰዓት። እንደገና ከስምንት የጀመርን እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ሥርተን ጨረስን። አባቷ መረቁኝ። እኔ የሰራሁት ለአባቷ አልነበረም። እኔ የሰራሁት ለገንዬ ነው። በሥራው መሐል የምትናገረው ነገር ደስ ይለኛል:

"ካልቻልክ ተወው"

"ከደከመህ እረፍ"

"ኧረ አንተ ቀስ በል"

"በል ዞር በል እቴ......አባቴ እንደለመደ ይሥራው፤ አንተ ዞር በል"

ራት ለመብላት ስንቀመጥም ብዙ አላወራሁም።

አባቷ ግን: "እዚህች ምንገድ ላይ ብዙ ሰው ይመላለሳል። ያሉት ሱቆች የተራራቁ ናቸው እና እስኪ እንሞክር ብለን ትንሽ ሱቅ ልንከፍት ነበር። ቢቀናን። ዕቃው ሲበዛ መደርደሪያውም በሁዋላ ይጨምራል። ዛሬ አንቀልቅሎ አምጥቶህ ቤትህ አርፈህ የምትውለውን......."

የእኔ መልስ: "ግድ የለም ሌላም ጊዜ ቢሆን ስራ ከሌለኝ እረዳለሁ"

ወደ ቤቴ ስመለስ: "ቆይ ትንሽ" ብለውኝ ነበር አባቷ። አምልጧቸው መሰለኝ።

ሱቋ ግን ለወር ያህል ሽንኩርት እንኳን አልተደረደረባትም ነበር። በነገሩ እንዴ ገብቼበታለሁ ብዬ ነው መሰለኝ ገነትን ለምን እንዳልጀመሩ ስጠይቃት ለመንገር ፈቃደኛ አልነበረችም። በሁዋላ ዘግይታ ዘግይታ:

"ያልነገርኩህ ትንሽ ደስ ስለማይል ነው" አለችኝ

"ለምን?" አልኳት



@BOOKALEM

"አባባ ከሌላ ሰው ጋር በሽርክና ሊጀምረው ነበር። አባቴ ቤቱን ይሰራል......ለቤቱ ለሱቁ መስሪያ ዕቃ ይገዛል......እሱ አናጢ ይሆናል ወይም ይቀጥራል። ይኼ አባቴ የሚያደርገው ነበር። ሽርኩ ደ'ሞ ለንግድ መጀመሪያ የሚሆነውን ዕቃ ይሞላል......ተመጣጣኝ ዋጋ ተገምቶ.......እና......."

በጣም አዝና ነበር።

"ሰውዬው እምቢ አለ? "

"አዎ"

"ደስ አይልም" አልኩ

"አባቴን ሞኝ ያደርገዋል?"

"አይመስለኝም......ሰውዬውን ነው ባለጌ የሚያደርገው.......ግን በፅሑፍ አትዋዋሉም ነበር?"

"የአንድ አገር ሰው ናቸው። አባትና እናቶቻቸው እነኡ ይተዋወቃሉ። በመተማመን ነበር። አባባ ተበሳጭቷል"

"ለምን እንዲህ አደረገ ሰውዬው?"

"በቃ ተንኰል ቢሆን ነዋ"

"ምንም ማድረግ አይቻልም?"

"ምን ማድረግ ይቻላል.......ያለው ገንዘብ የምትረባ አይደለችም"

"አፅናኚያቸው......ጤንነት ይበልጣል"

እንደ ሽማግሌ ምክር ጀመርኩ። ሙቀት እንደምትፈልግ ድመት ወደ ጉያዬ ተጠጋች። ያሌለው አያገኝም ነው ያሉት? ተረቱን ረሳሁ።



@BOOKALEM

## .......የሆነ የተጋረደ ነገር ወደቀ....(ወደ «ስዩማ! የሰበታ ቲማቲሞች» ከገፅ 373)

......እየተስለመለምኩ ፊቷን በሁለት እጆቼ ያዝኩ:: አሚልጮኝ እንደሚወድቅ ሁሉ:: እንደሚፈስ ሁሉ:: ፊቴ ገነት ፊት ላይ ወደቀ......አፌ ውስጥ ከንፈሮቿን እንደ ቢራቢሮ ክንፎች (እንዲህ የሚቀስሙት አበባ ላይ አርፈው ምናልባትም በወለላ ሰክረው ልባቸውን ነስቶአቸው እያሉ ክንፎቻቸውንም እንደ መፅሐፍ ገፆች ገጥመው......በቀስታ ከበስተሁዋላቸው ተጠግቼ በአውራ ጣቴና በአመልካች ጣቴ አጣብቄ እንደማጠምዳቸው) ይዤአቸዋለሁ:: በገላዬ ውስጥ አየር እንደሚያልፍ ሁሉ ነበር:: እንኩይ እንኩይ ከሚል.......ውሐ እናቶች ከሚከናበሉበት የአምቦ ምንጭ ውስጥ እንደተኛሁ ነበር:: ዐይኖቿ ወተት መሃል እንደ ወደቁ አጋሞች ነበሩ:: ልቤ እንዳይፈነዳ እፀልያለሁ፣ ልቤ እንዳይፈርስ እንቀጠቀጣለሁም:: ጣቶቼ በጀርባ ቆዳዋ ላይ ተማስለው እንደተኙ ነበሩ:: ደማችን ተደባልቆ ሲፈስ......ፈረሰኛው ከተራሮች በላይ ነበር:: መዝፈን አማረኝ:: እንደ ንጋቷ ከልካይ መዝፈን አማረኝ:: እንደ ጥላሁን መጮህ አማረኝ:: እንደ አስቴር መተከዝ አማረኝ:: እንደ ሙሉቀን መጨፈር አማረኝ:: ከእግሮቻችን ስር የዚህች ከተማ የልብ ምት ከተቀበረበት ይሰማኛል:: የዚህች አገር የልብ ምት ከተቀበረበት ይሰማኛል:: የዚህች ምድር የልብ ምት ከተቀበረበት ተሰማኝ መሰል:: በከንፈሮቼ ተሰማኝ መሰል:: በአጥንቴ ተሰማኝ መሰል:: በጉበቴ፣ በጣፊያዬ ተሰማኝ መሰል፣ በብልቶቼ ሁሉ ተሰማኝ መሰል::

ገነት ከሩቅ እንደሚሸት

ትኩስ

ሕብስት

ነበረች::

ይቺ ልጅ ተጣጥፋ አፌ ውስጥ እንደ ናና ከረሜላ ነበረች::

*ናናዬን አገኘሁ*
*በፍቅር ልምጠጣት፣*
*መይሳው ዕድል ነው*
*ወደ እኔ ያመጣት::*

ከዚህች አስደሳች የሚገድበኝ ማን(ምን)ነበር?



@BOOKALEM

ከዚህች ከገነት የሚያቆመኝ ማን(ምን)ነበር?

እግዚአብሔር ተመልሶ እስኪመጣ እስከ ፍካሬ ኢየሱስ አቅፌአት ልጠብቀው ተመኘሁ:: ልቦቻችን እጆች ቢኖራቸው ደረቶቻችንን ሰብረው ወጥተው ያጨበጭባሉ::......እንዴት ይቀላል ፍቅር! ደ'ሞ እንዴትስ ይከብዳል! እንዴትስ ትንሽ......ደ'ሞስ እንዴትስ ትልቅ ነው:: አንጀቴ እሷን ምን ሳድርግሽ? አላት.......አንጀቴ በእርዝመቱ ተንሰፈሰፈ.......ምናለበት ትንሽ በሆንሽ?.......ምናለ እጆቼ መሐል ሓባ ዘቢብ ብትሆን ኖሮ.......

ውጬአት ብተነፍስ ተመኘሁ.......

ቢሉኝ......

*ውጠሐት እንደሆን ትፋት እንያት*
*ምድር ላይ ያለችው እሷው አንዲት ሴት*

ቆዳዬ ስር በደም ሥሬ ግድግዳዎች ላይ እንደ ረቂቅ ነገር ተሽከሚአት እንደምዞር ገባኝ.......ቆዳዬ ስር ደም ሥሬ ግድግዳ ላይ ከውስጥ ተለጥፋ......አይፍቁኝ፣ እሷን አይበጡኝ ነገር::

.......እየተስለመለምኩ ፊቷን በሁለት እጆቼ ያዝኩ:: ሾልካ እንደምታመልጠኝ ሁሉ፣ ከላል ብላ እንደምታመልጠኝ ሁሉ.......

ፊቴ ፊቷ ላይ አረፈ.......

.......ገነት ቤቴ መጥታ በር ዘግተን ስንቀመጥ ቀናተኛ የሰፈር ሴቶች ፊት ለፊት መጥተው እንድንሰማቸው አድርገው ስድ ነገር ያወራሉ:: ከመሃል ጠንቅቀው እንደሚያውቁኝ ሁሉ ስሜን ይጠራሉ:: ስለፍቅር እየዘፈኑ ግን ፍቅራችንን ሊያፈርሱ ይለፋሉ:: ከጀርባቸው ባለቅኔ በሚያምር ድምፅ ከአሮጌ ቴፕ ፍቅርን ሲያቀነቅን ሁላችን እንሰማለን:: ልጣላቸው አልፈለግሁም:: ከእምነቱ ከዘፈኑና ከተረቱ ተጣልቶ ተዋክቦ የኖረበት ሰው ቢመክሩት የት ይገባዋል? የገነት ለስላሳ ቅርጿ፣ እንዲህ አበጥ ያለው ዳሌዋ፣ በጎን ስትጋደም ፀሐይ እንደሚጋርድ አድማስ የተከተረ.......ከጎረቤቴ ቀናተኛ ሽሙጥ ርቀን እንሄድ ነበር.......አንዳንዴም የአልጋ አከራዬ የሚጎተት ኮቴ ከነጥላው በበራችን ያልፋል......አመልካች ጣቴ ትንግርት እንዳመለከተ ሁሉ ጉንጉኗ ፈትል ይገባና ነውዝ ይጥለኛል......ከጉንጮቼ ስርጉድ ላይ ገኒን እሰማት ነበር፣ ምራቋን በከንፈሮቿ መልሳ ስትመጥ......ግራ እጄ በፍርሐት መልካም ቂጧ ላይ ያርፋል.......ልብ ምቷንም ከዚያ ዕርቀት ያጠናል......ሁለመናዋን ወደ እኔ ስቤ በፍርሐት እርበደበዳለሁ......የውሸት መሽኮርመም ዐይኖቿ ላይ ጥላ ወደ ደረቴ ትሳሰማለች......



@BOOKALEM

አልጋ አከራዩም ይል ነበር በነቃ ድምፅ:

"ሰዓት አልቆአል!"

ፊቷን በቀስታ ወደ ግድግዳ ታዞራለች:: ትርጉሙ ይገባኛል:: ትንሽነቷን ሰብስቤ እንደ አምሳ እግር ሁለመናዋ ዙርያ እጠቀለላለሁ (እንደ ይቅርታ):: አፍንጫዬ ጡቶቿ አካፋይ ያርፋል......ከዚያም ሰርቀት ፈሪ ልቤ እንደተከለከለ ሁሉ የአገሬን ልጅ ማሕፀን ይመኛል:: ከውስጥ የሚበላኝ ሰደድ እሳት በትንሹ በትንሹ ፍቅርን ይረግማል::



@BOOKALEM

# ፶ ቀይና ነጭ ነገር ምንድነው?

ዝናብ ሊመጣ ነው መሰለኝ ወይም ዝናቡን ለማባረር ስለአየር ፀባይ ብዙ አላውቅም እንጂ. ንፋስ እንደ ሰብድ ይሰራዋል:: የማይመጣበት አቅጣጫ አልነበረም:: ከጐን፣ ከጀርባ፣ ከፊት.......አንዳንዴም ከሰማይ የሚወርድ ይመስላል.......

ታዲያ በዚያ ነፋሻ ቀን ባርኔጣዬ ተነስቶ እንዳይበር በእጄ ይዤው ምንገድ ዳር ቆሜአለሁ:: የንፋሱ ግፊት እንዳይራመድ የገተረው አንዱ ቀጫጫ መንገደኛ ፊቱ በሐፍረት ተቃጥሎ ይስቃል:: ያልቀለፈው ጥቁር ኰቱ እንደ ቁራ ክንፍ ወደ ሁዋላው እሰማይ ላይ ተሰቅሎ:: አንዳንዱ የቅንድቦቹ ፀጉሮች ወይም ሽንጉበቱ በንፋስ ተልጠው እንዳይጠፋበት ነው መሰለኝ ፊቱን በሁለት እጆቹ ጋርዶ በችኰላ ይራመዳል.......

አንዲት መሐከለኛ እድሜ ያላት ሴት ደጋግማ በንፋሱ መገላለብዋ አስፈርቷት ቀሚሷን እግሮቿ መሐል ሰብስባ......"ውውይ እቴ ከየት መጣ ይሔ ንፋስ?" እያለች ትሮኾለች.......ቀለም የተቀቡ ከንፈሮቿ የአውራ ዶሮ ኩታት ይመስላሉ.......

በአስፋልቱ ጉዳና መሐል የታጠበ ጨርቅ መሸፈኛ የላውንደሪ ላስቲክ እንደቆሰለ አሞራ እየተገላበጠ፣ እየተንፈራፈረ ያልፋል.......በንፋሱ ይሸመለልና እንደገና በንፋሱ ይዘረጋል.......መኪና ሲያልፍበት ይጠፈጠፍና.......እንደገና በንፋሱ ተቀስቅሶ ደካማ ክንፎቹን ለሌላ ሩጫ ይዘረጋል.......

አብለጭላጭ የሲጃራ ወረቀቶች በአቢራ ተሸፍነው.......እየነጠሱ ያልፋሉ.......

የፀጉሯ ቄንጥ እንዳይበላሽባት አንዲት ልጃገረድ ግንብ ተደግፋ ቆማ ነበር......ንፋሱን እንደ ዝናብ ለማምለጥ.......

አንድ ጉንጨ—ወፍራም ጢማም ሾፌር ፊታቸውን ከመኪናው ውስጥ ብቅ አድርገው አስፋልቱ መሐል ላንጋኖ የሚያክል ምራቅ ተፍተው አለፉ:: ክሱት እሜባ ይመስል ነበር::

ሕንፃዎች ላይ የተሰቀሉ መፈክሮችና ባንዲራዎች ያለብልሐት እንደተተከለ ወፍ ዘራሽ ሽምበቆ ኢጋድለዋል::

የጋዜጣ ቅዳጆች.......ንፍጥ የተጠረገባቸው ለስላሳ ወረቀቶች ተያይዘው ንፋሱ ወደ ነዳቸው ይሔዳሉ.......

እኔ ባርኔጣዬን ይዤ በንፋስ የሚውለበለብ ሱሪዬን እያየሁ ጀርባዬ ላይ የሚሰማኝን ቅዝቃዜ እያዳመጥኩ ቆሜአለሁ::



@BOOKALEM

የአንዲት ሴትዮ ዣንጥላ ወደ ሰማይ ተበልቅጦ እንደ እንጀራ ተቆርጦ ሔደ:: ጊደኛዬ ፖሊስ ጫማው እንዳለቀበት ሯጭ የበሸቀ ገፅ እያሳየኝ አንዲት ካፍቴሪያ ተጠልሎ ቆሞአል.......

ሳሊበሳ ሬስቶራንት በራፍ ላይ ባለገንዘብ፣ ምሁር፣ ዘናጮች ገብተው ለመጠለል ይሻማሉ.......

የማይሮጥ የለም.......

ሩጫው ስምረት አልነበረውም:: የሕዝቡ እግር የፈረሰ ይመስላል.......ጣቶቹ የወላለቁ፣ የጉልበቱ ሎሚ ፈንድቶ ዘይቱ እንደ ሰንባ የሚፈስ፣ የባቱ ስጋ ተቀዶ ከቂራ ያመለጠ በሬ የመሰለ፣ ፀጉራቸው ረግፎ በየመንገዱ እንደ ቃርሚያ የወደቀ.......ታዲያ ንፋሱ እየጐተተ፣ እያገላበጠ የጉነጉነው.......

ሩጫው......የፈረሰ ሩጫ ነበር.......

እኔ ባርኔጣዬን ንፋስ እንዳይገለብጠው በእጄ ይዤ ይሔን ትርዕይት አያለሁ.......

ከፍቼው ስለቆምኩ ነው መሰለኝ አፌ ደርቆአል.......

አፌ

እነዚያ ሁሉ አፎች የት ሔዱ?

እንደ ሕንድ ውቂያኖስ የሰፋ አፍ ቢኖረኝ ምን ነበረበት? ይሔን ሁሉ ንፋስ እንድውጥ:: ታውቃላችሁ? ሆዴ መቀመቅ እንደሆነ? ንፋሱ ከማን ማሕፀን ግን ፈለቀ? ንፋሱ ከምን ተቀምሞ ተሠራ?

ንፋሱ የብዙውን ልብ ፈቶታል.......

እኔ ባርኔጣዬን ንፋስ እንዳይገለብጠው በእጄ ይዤ ይሔን ትርዕይት አይ ነበር.......

አንድ ነጭ ነገር ከወዲያ በኩል ወደ ትልቁ ምንገድ ተጠምዞ ሲገባ አየሁ.......ምናልባት ከቸርቻር ጉዳና በንፋስ እየተገፋ የመጣ ወይም ንፋሱን የሚሸሽ ምንገድ ላይ የተኛ ሰው ይሆናል .......እየተንከባለለ፣ እየቀረበኝ ሲመጣ ትልቅ የጨርቅ ቁራጭ መሆኑን ተመለከትኩ:: ከፊሉን ጊዜ መንገዱ መሐል ይንከባለላል፣ ከፊሉን ጊዜ መንገዱ ዳር የሚያልፉ መኪናዎች በሚገርም አኳሃን ሳይድጡት ያልፉታል:: የንፋሱ ጉልበት ጋብ ሲል ጨርቁ እንደ ሞተ ፍጡር ጦር ሜዳ መሃል ነፍሱን እንዳጣ ሴርጃ ማጀር ይተኛል:: አውሎው ሲጀምር እንደገና ተነሣ:: እንደገና እየተገለባበጠ በመንገዱ ዳር፣ በመንገዱ መሐል.......እኔ ባለሁበት አቅጣጫ መጣ:: ዓለምን የሚያስተዳድረው የዕብድ ሕግ በማይታይ ብልጠቱ አንድ ነገር ሊያሳየኝ ያሴረ መሰለ.......



@BOOKALEM

ጨርቁ እየተንከባለለ መጥቶ እግሬ ስር ቆመ:: ትልቅ ጨርቅ አልነበረም፣ የክንድ ግማሽ ቢያክል ነው:: ከጉዞው የመጨረሻው ንቅናቄ እንደሆነ በይነት በቀስታ ተገለበጠና ደማቅ ቀይ ነገር መሐሉ ላይ ተመለከትኩ:: ሰው ሳያየኝ ግራና ቀኝ ተገላምጬ የጨርቁን አንድ ጉን ረግጬው ቆምኩ:: በጥጥ የተሞላ በጣም ትንሽ ስስ ፍራሽ ይመስላል.......

ባርኔጣዬን በእጄ እንደያዝኩ ነበር.......

ንፋሱ በጀመረበት ሐይሉ እንደገና መናድ ቀጠለ:: ጨርቁ እግሬ ስር ይፈራገጣል:: መሐሉ ደማቅ ቀይ ነው:: መሐሉ ደም ነው:: ይሔ የጨርቅ ቁራጭ ምን እንደሆነ ስረዳ የረገጥኩበት እግሬን አነሳሁ:: ንፋሱ ተቀብሎ እያንከባለለ ይዞት ሔደ.......

ክሽፈት::



@BOOKALEM

# ፋይል

በኩረ ስለ ፋይል ማውራት ይወድ ነበር:: ቤት ውስጥ ከገባ ጀምሮ ማውራት የማያቆመው በኩረ ነው:: በፍፁም የሚደክመው አይመስልም:: ይተረትራል፣ ይጎነጉናል:: በየቀኑ አዳዲስ ወሬ ያመጣል:: ወሬውን ከየት እንደሚያገኘው ይገርመኛል:: እሱ መስሪያ ቤት ባልሰራም ያን ጊዜ አብረውት የሚሰሩትን ባልደረቦቹን በስም የማውቃቸው ይመስለኛል:: ምናልባት ሾፌርነቱ ከብዙ ሰው ጋር ስለሚያገናኘው ይሆናል:: ያበዛው ነበር ግን:: ስለ አለቃው አለቃ ሲያወራ እንደ ጓደኛው አድርጎት ነው:: ስለ አለቃው ባላንጣ ሲያወራ እንደ ጉዋደኛው አድርጎት ነው:: ስለቤት ጠራጊዋ ሲያወራ እንደጓደኛው አድርጓት ነው:: የማያውቃቸው ሴቶች አልነበሩም:: እንደ እሱ አባባል መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ለወዳጅነት የማይፈልጉት ሴቶች አልነበሩም:: በኩረ ታዲያ በወንድነቱ መፈለጉን ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ፋይላቸውን ያውቃል::

"ዛሬ ያቺ ሒሳብ የምትሰራ አንድ እንትና የምትባል ጉኔን አልጉሸመችኝ መሰለህ?"

"ምን አልካት?" አለማየሁ::

"ከእሷ ጋር ልዳራ እንዴ ደ'ሞ ሰው ጠፋ"

"ምነው?" አለማየሁ

"ሽርሙጣ አይደለችም እንዴ?"

"ኧረ እባክህ?" አለማየሁ

"ፒያሳ ብትወጣ የማያውቃት የለም"

"አትለኝም" አለ አለማየሁ:: ግን እያሾፈ::

በኩረን ከእኛ ጋር አብሮ እንዲኖር ያመጣው አለማየሁ ነበር:: የመስሪያ ቤታቸው ፀሐፊ 'ዘመዴ ቤት ይፈልጋል' ብላው:: ለሴትዮዋ ምን ያህል ቅርበት ያለው ዝምድና እንዳላቸው እንኳን አያውቅም::

"አታምነኝም?.......አግኝተነዋል ፋይሉን" ይላል እየሣቀ::

በኩረ የሚያውቀው ፋይሉ ያልተገኘበት ሰው አልነበረም:: እሱ ያላወቀው ሰው ካለ ይበሽቃል:: መብሸቅ ብቻ ሳይሆን መረጃዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚገባው እኛ እየሰማነው ሲሬ ያወጣል::



@BOOKALEM

"ያ!.......የት ነው የሚሰራው? እንዴ? እዚያ የማውቀው ሰው አለ.......ስለ እንትና አልነገርኳችሁም? ስለዘውዴ.......ዘውዴ እዚያ አይደለም እንዴ የሚሰራው? አምስት ዓመቱ ነው እዚያ ሲሰራ.......ዘውዴ ማለት እኮ ምንም የማያመልጠው አራዳ ማለት ነው:: የሥራ አስኪያጁ ሾፌር ነው:: የማይፈራው የለም:: ታዲያ .......እሱን አልጠይቀውም እንዴ"

እንደ አገዳ ትል የሰው ሕይወት ይቦረቡራል::

"አንተ አርፈህ አትቀመጥም?" ይላል ጃፓን::

የእኔ ዝምታ በኩረን ያበሳጨዋል:: ስለእኔ የሚያውቀው የአባቴን ስም ብቻ ነበር:: ይሄ ወሬኛ ልቡን ያሳከከው ነበር መሰል:: አንድ ቀን ከየት እንዳገኘው አላውቅም ማታ እቤት መጥቶ እየሣቀ አልጋው ጠርዝ ተቀምጦ:

"ፋይልሽ ተገኘ እኮ" አለኝ::

በዝምታ አየሁት:: አልመለስኩለትም::

ጃፓን ይነጫነጫል:: አለማየሁ እየሳቀ ያየዋል:: ነጋሳ ካልመሸ አይመጣም:: ቀድሞ እንኳን ቢመጣ ተዳክሞ ይተኛል ወይም በመሰልቸት እያዛጋ ወሬ ያዳምጣል::

"ምን አገኘህ?" አለ ጃፓን:: ብሉን መፍቻ ብረት ቢጤ በእጁ ይዞ እየቀለበ ይወረውራል::

"ብዙ ነው.......ምን አስወራኝ.......የት እንደተወለደ ታውቃለህ?" አለ በኩረ::

"ምን አገባኝ?" አለ ጃፓን:: ሲወረውር ያመለጠችውን ብረት ከወለል ላይ እያለቀመ::

"ትደብራለህ.......ሙት ትደብራለህ:: አብሮህ የሚኖር ሰው የት እንደተወለደ ማወቅ ማንን ይጎዳል?"

"ደሞዝ ያስጨምርልኛል?" ጃፓን

"መቀለድህ ነው?" በኩረ

"የትኛው ቀልድ ሲያስቅሽ ነው:: ወሬ እንጂ ቀልድ ያስቅሻል እንዴ:: የሰው መዋረድ ነው የሚያንፈቀፍቅህ"

ያን ዕለት ማታ አልተስማሙም:: በንጭንጭ መሐል ታለፈ:: በኩረ ግን አልተወኝም:: አልፎ አልፎ በአግድም ብዙ ነገር ይናገረኛል:: አንድ ቀን ማታ ለምሳሌ ፀጉሩን ተከርክሞ መጥቶ–ያውም ብዙም ሳይቆረጥለት ፀጉር አስተካካይ ሲያማርር



@BOOKALEM

አመሸ:: እቤት የገባው አንድ ሰዓት ላይ፣ ሳያቋም ሲያወራ አራት ሰዓት:: ተሰላችተን ብናዛጋ እንኳን በተከፈተው አፋችን አድካሚ ድምፁን ያንገረሽራል::

"እኔ ዕውር ሆኜ ባስተካክል እንዲህ አልሠራም:: እኔን ብቻ መሰላችሁ እንዴ?.......አንዱ ለሥራ ጉዳይ ከክፍለሐገር ነው የመጣሁት ንፋስ መውጫ ከሚባል ቦታ ሥራ እዚህ ግብርና ሚኒስቴር አግኝቼ ብሎ ሊስተካከል ይመጣል......ምድምድ አድርጉ አይለቀው መሰላችሁ:: ተራግሞ ተራግሞ ሔደ:: ክፋት እኮ ነው:: ግን ለእሱም ማዘን ያስፈልጋል.......አይመስልህም መዝገቡ......እ......ማዘን አያስፈ ልግም? እኛ በአጋጣሚ ሹፌርና ፖሊስ ሆን እንጂ........እንደው በዕድል ፀጉር አስተካካይ ብንሆን እኮ እንደ እሱ መሰደባችን አይቀርም......."

"ምን ብሎ ሰደበው?" አለማየሁ

"ምን ይሰድበዋል.......የአስተካካዩ ዐይን ፀጉር እየገባበት ሊጠፋ ነው.......የሚያሳዝን ነው ራሱ"

"ታዲያ ምን ልታወራልን ነበር?" ጃፓን አልገባውም

"ምን ይገባሃል......? ዘፈን ስማ አንተ ብቻ......መዝገብ ገብቶታል......መዝገብን ጠይቀው"

"መዝገብ ገብቶሃል?" ጃፓን በየዋህነት

ራሴን አነቃንቃለሁ:: በአሉታ::

"ፀጉር አስተካካዮች እኮ በሙሉ እንደዚያ አይደሉም:: ነገሩን ያነሣሁት እንኳን ለማወዳደር ነው:: ባለፈው ጊዜ ያስተካከለኝ ሰንጋ ተራ ያለው ሰው ለምሣሌ እንክን አይወጣለትም:: እንደነገርኩው ነው የሚያደርግልህ:: ብሩህ ነው:: እኔ እነዚህ ቀሽሞችን ነው የምልህ:: ዛሬ ያስተካከለኝ ታዲያ እጁ ይንቀጠቀጣል:: ምን ይባላል? ፀጉር አስተካካይ ሆኖ እጁ ይንቀጠቀጣል::"

"የት ነው የሔድከው?"

"እዚህ ተ/ሃይማኖት"

"ሰንጋ ተራ አትስተካከልም ነበር" ጃፓን

"ረሳሁት:: ሠፈር ልደርስ ስል ትዝ አለኝ"

"ምን ሆኖ ነው ሰውዬው የሚንቀጠቀጠው?"

"ሚስቱ ታማበት ነው አሉ......."



@BOOKALEM

"ሚስቱ በታመመች የእሱ እጅ ይንቀጠቀጣል.......?"

"ከወር በፊት እናቱ እንደሞቱበት ሲናገር ነበር"

"እናቱ? ኡይ.......ጣጠኛ ነው እባክህ"

"እንዴ? ታዲያስ የእናት መሞት ቀላል አይደለም......እኔ እንኳን አልደረሰብኝም"

"ለእናቴ ደብዳቤ ከፃፍኩላት ሦስት ወር ይሆነኛል" አለማየሁ ከመሐል

"እኔም......አንተስ መዝገቡ ፅፈሃል?"

እኔ ዝም:: ዝምታዬን ይጠላል:: መበሳጨቴን፣ መደሰቴን ማወቅ ይፈልጋል::

ሌላ ቀንም ብቅ ይልና አልጋ ላይ ተጋድሞ ስላገኘው ፋይልና.......ስለተረዳቸው አስገራሚ የሰው ሕይወት ሚስጢር ያነበንባል:: ጆሮ መቸም አይቆረጥ:: እሰማዋለሁ::

አንድ ቀን ሠራዊቱ ስለሚያደርገው ጦርነት ስለሞቱ የሚያውቃቸው ልጆች ስናወራ (እኔ የማውቀው ሰው የለኝም) በኩረ እንደተናደደ ሁሉ እራሱን ሲነቀንቅ ቆይቶ:

"ሠራዊታችን የሚሸነፈው እኰ መዋጋት አቅቶት አይደለም፣ በውስጡ የተሰገሰጉ ፀረ-አብዮተኞች ናቸው.......መረጃ በማቀበል፣ ሞራሉን በመስበር፣ እርስ በእርሱ በማጣላት የሚጫወቱበት......." አለና ወደ እኔ አየ::

ዝም አልኩት::

"ዕውነቴን ነው" አለ

አለማየሁ ምድር ጦር ባለመግባቱ እራሱን ሲያመሰግን እሰማዋለሁ::

"ያ ኢሕአፓ የሆነው ሁሉ ወጣት የት ገባ ይመስልሃል? ተመልሶ ለደርግ የሚዋጋ ይመስልሃል?" እኔን እንደገና ያያል.......ቆይቶ ቆይቶ ወር ወይ ሁለት ወር ሲሆነው ነው የቀድሞ አግድም አባባሉን ስላልተረዳሁለት፣ ተረድቼለትም ስላልፈራሁት ነገሩን ግልጥ ለማድረግ......."ስሚ መዝገቡ......ኢሕአፓ አልነበርሽም?......ምንም ፖለቲካ ውስጥ አልነበርክም?" አለኝ::

"ምንም" አልኩት.......ለኢህአፓ ወረቀት.......ለኢህአፓ ሳይሆን ለኤልያስ ለጓደኞቼ ወረቀት መበተኔን እንኳን እረስቼዋለሁ::

"የመጣህበት አካባቢ ኢሕአፓ የሞላው አይደለም እንዴ? እንዴት አመለጥክ?"

ጃጋን: "መቼ ሔደህ አየኸው የተወለደበትን ቦታ?" ይለዋል በኩረን

"ብዙ ከዚያ የመጣ ሰው አውቃለሁ"



@BOOKALEM

"ይኼን ሰውዬ ተወው:: አሁን ኢህአፓ ሆንክ አልሆንክ ማን ግድ አለው:: ዝም ብለሽ የተረሳ ነገር......ያን ሻለቃ ታውቀዋለህ......ክፍል ሃላፊው......እዚህ አምስተኛ ያለው እሱ ቀንደኛ ኢሕአፓ ነበር:: ደሞ መዝገቡ ልጅ ነው:: ምን ያውቃል ፖለቲካ ሊገባ ይቅርና......አሁን ይመስልሃል ስታየው? ነገር ትወዳለህ:: ይሄን ሰው ተወው" ይላል አለማየሁ::

"አንዳንዴ የታመመ ይመስለኛል:: ለምን አያወራም.......ለምን አታወራም አንተ?" በኩረ እኔን እየጠየቀኝ::

እኔ ፀጥ:: አንዳንዴ እጁን እያወናጨፈ ሲያወራ፣ አፉን ከፍቶ ሲስቅ(15)......ተመስጠውና፣ ጉልበቱ ያስደንቀኛል......ያስጠላኛልም::

ቢሆንም ፀጥ::

ሌሊት ነው ያን ዕለት ማታ ተኝቼ ቅልብጭ ያለና የተረጋገጠ ባይሆንም በሽሙጥና በአግቦ ቢደረደርም በኩረ እንደሚለው የፋይሌን ከፊል ማግኘቱን የተረዳሁት.......



@BOOKALEM

# ቅምቡርስ ማር ስይሰፈም

(ቢሰራማ ሁሉ ታድሎ......ቅምቡርሱም፣ ሰውም):: ተንኮል የሚያስብና የሚሰራ፣ ሰዎችን በተንኮሉ ሠላም የሚነሳ ሰው በመጨረሻ ይጋለጣል የሚባለው ውሸት ነው:: ያኔውኑ ከተናገሩት ያኔውኑ ይጠፋ ይሆናል:: ይሆናል ነው:: ብዙ ጊዜ ግን ያኔውኑ አንናገርም:: መረቡን ሲዘረጋ አየር እንደጠማው አሳ አፋችንን ከፍተን ከማዳመጥ በስተቀር አንንቃንቅም:: እኔም እንደዚያው ነኝ......አፌን እየበለቀጥሁ ማዳመጥ::

ማታ እቤት ስገባ በኩረና አንድ በባርኔጣው የሚጫወት ጠይም ቀጫጫ ፖሊስ አልጋ ላይ ተቀምጠው አገኘሁዋቸው:: አለማየሁ ቴፕ በስክሪፕቶ እየጠቀለለ ይበሳጫል:: ይኼን ፖሊስ በፊት በፊት ኒንጃን ሲያባርር ያጋጠመኝ ነበር:: የቆየ የቆየ ሰው:: የተረሳ:: ለሠላምታ አንድ እጄን ብቻ ለሁሉም አንስቼ ገባሁ:: ገና አልጋዬ ላይ ቂጤ እንዳረፈ በኩረ መናገር ጀመረ......

"ስማ አሥር አለቃ ያ ያልኩህ ፀጥታ ጠባቂ ይኸው" (አሥር አለቃ የሚባለውን ቃል ምን አመጣው?)

ሰውዬውንም በዝምታ አየሁት:: ወደ እኔ ዞር ብሎ እንዲህ አለኝ፡ "አለቆችህ መስማታቸውን ካላመንክ ይኼውልህ ጠይቀው"

ትከሻዬን በቸልታ ነቀነቅሁ:: አለማየሁ ክሩን አስገብቶ ቴፑን ከመክፈት ተቆጥቦ በኩረን ያዳምጣል::

"ምንድነው የምትፈልገው?" አልኩት

"በግል ሊያነጋግርህ ይፈልጋል"

"ይኼው እዚህ ነኝ:: በግል ማነጋገር ስርዐት አይደለም:: ነገሩ አልቋል አይደለ እንዴ? በየሚዳው መነጋገር ከስርዓት ውጪ ነው" አልኩት

"ለምን አንወጣም?"

"ለምን እወጣለሁ:: አለማየሁ ጓደኛዬ ነው ይስማ:: ያውም እኔ ከሰማሁህ ነው ደሞ"

"ይኼ ከሌላ ሰው ጋር አይሆንም" አለ ልዩ ሚስጢር እንደሚነግረኝ ሁሉ::

"ካላወራህ ተወው......ልተኛበት ጊዜ......ለምንድነው የምትጨቀጭቀኝ? ለምን አትተወኝም? ምን ችግር አለብህ እኔን በመልከፍ የሚቃለል? ዛሬ የመጀመሪያህ አይደለም:: ታማኜሀለሁ:: ብዙ:: የገባህ አትመስልም:: የቆየ ነገር ማንሳት አልወድም::



@BOOKALEM

እኔ ላንተ አፍሬ ዝም ብዬህ ነበር:: ባለፈው ጊዜ ከእህቴ ከጫልቱ ሊታጣላኝ ወሬ ስትፈጥርና ስታመላልስ ነበር:: አትረሳውም:: ዛሬ ደሞ በሕግ ተጋርደህ ልትጨቀጭቀኝ ፀባይህን ያልተረዳ ሰው ጎትተህ ታመጣለህ:: የምፈራው ቅን ሰው ነው:: ያውም ልፍራ ካልኩ:: ሌላ ዐይነት ሰው አላከብርም:: አለቆቼ የምሰራውን ያውቃሉ:: አንተ አትመክራቸውም:: ስህተት ብሰራ ለተንኮል እንዳልሆነ ያውቃሉ:: እኔ የጠበቅሁብት አካባቢ ወንጀል የማይሰራው ለምንድነው? ይሄን ያውቃሉ አለቆቼ:: እሺ? አስበህ አውቀሃል? ወይስ ተንኮል ስትመዘምዝ ጊዜ የለህም? ከአሁን በሁዋላ እንኳን አንድ ተራ ፖሊስ......ይቅርታ ወንድም የፈለግኸውን ይዘህ ና:: የሚመጣልህ ካገኘህ:: አሁን ስራ ውዬ ደክሞኝ ነው የመጣሁት ማረፍ እፈልጋለሁ:: ገባህ?"

"በሁዋላ ይቆጭሃል!" አለ በኩረ

"ምን አስቆየህ አሁን አታስቆጨኝም"

ሰውዬው ተነሳ:: በኩረም ተከተለ::

"ለመነጋገር ከፈለግህ ጥቂት ቀን አለህ"

"ሲነግሩት አይገባውም:: ቀጥታ ነው የተናገርኩት:: የሚለውን እንደሚጠራጠር ሰው በሽሙጥ አላወራሁህም:: ማነህ አንተ ቀን የምትቆርጥ:: ደካማ ሸረኛ"

ተገላምጦ አየኝ:: ልክ ልዩ ነገር እንደሚያደርገኝ ሁሉ::

"ሠላማዊ ሰው በዚህ ነገር አትዱል" ልብሴን እያወለቅሁ:: ቀና ብዬ አየሁት:: ጠላሁት:: ሲለምነኝ ምን ላድርግ? ያፈጀ ነገር አንስቶ ጥላኝ ሲል ምን ማድረግ ይገባኝ ነበር?

ያን ዕለት ማታ ራት እንድበላ ጠርታኝ ገነት ቤት ሔድኩ:: አባቷ የሌሊት ሥራ ስለሚሰሩ አላደሩም:: ራት በልተን ሻይ ስንጠጣ በወሬ በወሬ ስለ በኩረ አንሳንና ያልጠበቅሁትን ነገር አወራችኝ:: በኩረ ዘመዷ ነው:: እስከዚያን ጊዜ ድረስ ያልነገረችኝ የመጀመሪያው እውነት:: ዝምድናቸው ግን እሱ "እህቴ" ብሎ እንደሚያስጠጋት ዐይነት ቅርብ አልነበረም:: ይርቃል:: ይወዳትና ሌላ ሌላ "ቤቴነቷን" ሊጠጋ አስቦ ዳር ዳር ቢልም "ዘመድ" የሚለውን ቃል ስለፈራ እየተሸማቀቀ ይሸሻል (እሱ ራሱ ግኑኝነታቸውን ሊያሰማምር በፈጠረው ቃል እጁና እግሩ ተሳስሮ፤ ወይም "እሺ" እንደማትለው ከመጀመሪያው ገብቶት ባልተኛትም ልዛመዳት ብሎ ይሆናል):: በሁዋላ ነገሩ አልሆን ሲለው ወዳጄ ብሎ ከሚያምነው ሀብተጊዮርጊስ ድልድይ ከሚኖር ተዘራ ከሚባል ሰው ጋር ያስተዋውቃታል:: ይኽ ዓይነት ነገር በመጀመሪያውኑ ከበኩረ ባለመጠበቁ ገነት ትውውቁን ችላ አለችው:: ተዘራ የተባለው ሰውዬው በዕድሜው ብዙ ይበልጣታል:: በዕድሜ መብለጥ ብቻ ሳይሆን ምንም አልጣማትም::



@BOOKALEM

"በገንዘብ ሰው የሚገዛ ይመስለዋል:: ደሃ ነኝ:: ግን ዕቃ አይደለሁም:: እስቀያሚ ቅንቡርስ የመሰለ ነገር እኮ ነው:: ገንዘብ ለስንቱ ትዕቢት ይሰጠዋል እቴ" አለችኝ::

የትልቅ ዳቦ ቤት ባለቤት ነው:: ከበኩረ ጋር በተለያዩ ጊዜያት እሷ ቤት እየመጡ በቃልም በገንዘብም ያባብሉዋታል:: ዓመት ሁለት ዓመት ይሆናል:: ከመሐል ኑሮ ሲወደድና አባቷ ፋብሪካ እያደከማቸው ሲመጡ ትንሽ ባጠራቀሙዋት ገንዘብ ሱቅ ለመክፈት ያስባሉ:: ይኼ አላማቸውን ሲናገሩ በኩረ ይሰማና:-

"ወሬኛ ነው እቤት ሲያወጣጣ" አለችኝ

ለተዘራ ይነግረዋል:: ተዘራ ይኼን የሰማ ዕለት ማታውኑ ቤታቸው ይመጣና 'የቢዝነስ' ሐሳቡን ይነግራቸዋል:: አባቷ በእምነትና በጥርጣሬ መሐል ይቆዩና.......

"ከአንተ ጋር የተዋወቅን ሰሞን ነው" አለችኝ

በመጨረሻ "እሺ" ይላሉ:: ከመሃል ሥራም ምኑም ዕረፍት አልሰጥ ብሎአቸው ለረዥም ጊዜ ቆይተው ከተዘራ ጋር ተነጋግረውና ተስማምተው የሱቁን ሥራ ይጀምራሉ::

"ይህቺ ሱቅ ለመጠሪያ ነበረች......ግቢ ውስጥ ያሉ ሰዎች ይቀኑና ለተዘራ ዳቦ ቤቱ ድረስ ሔደው ስለ አንተ ይነግሩታል" አለችኝ::

ተዘራ ይሔን ሲሰማ በኩረን ያገኝና ለትዳር ያሰባት ጎንት አብሮት በሚያድር ጓደኛው እንደተወሰደችበት ይነግረዋል:: በኩረ እነ ጎንት ቤት ይሔድና ስለ ነገሩ ሲጠይቅ:

"ምን አገባህ" ትለዋለች

"ቆይማ ሳያገባኝ ታያለሽ" ብሎ በሔደ በበነጋታው ተመልሶ መጥቶ ተዘራ በገንዘብ እንደማይረዳቸውና የሱቁን ነገር ራሳቸው እንደሚቀጥሉበት ይነግራቸዋል:: ያን ሌሊት አባትና ጎንት ዕንቅልፍ አጥተው ያድራሉ::

"አያናድድም?" አለችኝ

"በጣም" አልኳት

በኩረ እኔ ላይ ሊያደርግ የፈለገውን ነገር አልነገርኳትም:: ልነግራት ፍላጎቱ አልነበረኝም:: ለምን ይጠቅማታል ብዬ:: ነገሩን ከማክበድና በኩረን ከተራነቱ አውጥቶ ክብር መስጠት ስለሚሆን ዝም አልኩ:: ወደ ቤቴ መመለስ አልፈለኩም:: አብሬአት ባወራ ባድር እመርጥ ነበር:: ጉና አብሬያት ተጋድሜ ቆዳዋን በቆዳዬ እየነካሁ ባድር



@BOOKALEM

ደስ ይለኝ ነበር። ከአንገቷ በታችም ልስማት። እግሮቿን አጥቤ ጥፍሮቿን ልስማቸው። ለስላሳ ቆዳዋ ላይ እንደ ውሐ እንክብል ሸርር ማለት። እርጥበት ልሆን.......

እህቷን አስተኝታ ቤቱ ፀጥታ ሰፍኖበት ተቃቅፈን እንደተቀመጥን.......

"ለመሆኑ ንግዱን ለመጀመር ምን ያህል ገንዘብ ያስፈልጋል?" አልኳት።

"ምነው? አንድ ሺህ......ሁለት ሺህ ይበቃል"

"እኔ እሰጥሻለሁ"

"ከየት አመጣኸው አንተ? ምኑ በቅቶህ ነው ከደመዎዝህ እ......."

"ድሮ!......ሁለት ሦስቴ ዕቁብ በልቻለሁ"

"ቢሆንስ"

"ድሮ ገንዘብ ቢኖረኝ እል ነበር። ያልበላሁትን ለመብላት። ያልጠጣሁትን ለመጠጣት። ያ አሁን ደስታ አይሰጠኝም። ሳልበላ በሕይወት መኖር ብችል እወዳለሁ። ብጥር የምችልም ይመስለኛል። አንቺን የሚያስደስትሽ ነገር ካደረግሁ ለእኔ ትልቅ ደስታ ነው።"

"ወስጄብህ 'አላውቅም' ብልህስ?"

"ማን ግድ አለው"

"ብትታመም መታከሚያህ ይሆናል"

"በሽታዬ ሰው ነበር ታውቂያለሽ። ጀርም-አልፈራም። በሽታ ይዞኝ አያውቅም። ድሮ ድሮ በእንቅልፍ ልቤ የመንዝ በሽታ ነበረብኝ። ረሳሁት"

"አሁንስ?"

"ከተወለድኩበት አካባቢ ስለቅ ተወኝ"

"ሊያምህ ይችላል እንደገና"

"ግድ የለም። ፖሊስ ሆስፒታል ቆሞ ይሂድ። በእኔ ይሁንብሽ ውሰጂው"

"ተወው ጥሩ አይመስለኝም። አባባ እሺ የሚል ሰው አይደለም"

"ገንዘቡን ካገኙ ለምን 'እሺ' አይሉም?"

"ሰው የሚያምን አይመስለኝም"

"ገንዘቡን ያለ ፊርማ እሰጣቸዋለሁ"



@BOOKALEM

"አይሆንም ተወው"

"ምን ቸገረሽ የእኔ ገንዘብ ነው"

"ወደ ሌላ ቢተረጉመውስ?"

"ምን?"

"እኔን ለመጥለፍ ምናምን አለ አይደለ" እየተሽኰረመመች:: የሚያሽኰረምም አልነበረም::

"ዕውነት ነዋ" አልኳት

"ምኑ?"

"አንቺን ነው የምጠልፈው"

"እንዴ?"

"አዎ.......አንቺን ብቻ ነው የምፈልገው"

ተጠጋጋን:: የበለጠ ተጠጋጋን:: ዝም አለች:: እኔም ዝም አልኩ:: ሁለታችንም የምናስበው ይገባናል:: ላገባት:: ከዚያ በሁዋላ ሁለት ሚሊዮን ሕፃናት ወልደን አዲስአባን እናስጨንቃታለን:: አግብቼአት:: ልጆቻችን ወደ ሰሜን ወደ ደቡብ ወደ ምዕራብ ወደ ሰሜን እየሄዱ አገሪቷን ይሞሏታል:: በጣም ውብ የሆኑ ሁለት ሚሊዮን ሕፃናት:: መናገር ነበረብኝ:: የመጨረሻውን ዕውነት መናገር ነበረብኝ::

"ገንዬ"

"እ"

"ለምን አንጋባም?" (ገንዘቡን እሰጥሻለሁ ብዬ ያኔውኑ ሚስቴ እንድትሆን ስጠይቃት የአቀራረብ ደካማነት እንደሆነ እንኳን አልገባኝም:: አቀራራብ ገሌመሌ ፍቅር የት ታውቅና:: የስሜቴ ትርምሱ አላሳፈረኝም ነበር::)

"እ?"

"ለምን አንጋባም?"

"ዕውነትህን ነው?"

"ለምን እዋሻለሁ:: ለአንቺ አልዋሽም:: ብዙ የማውቀው ነገር ስለሌለ አልዋሽም"

"ቤት ያስፈልጋል:: ብዙ መዘጋጀት ያስፈልጋል እኮ"

"መተሳሰብ ካለ:: ከእኔ የበለጠ የምትወጂው ሌላ ሰው ከሌለ"



@BOOKALEM

"ምነው እንዲህ አወራህ?"

"ከአንቺ በላይ የምወደው የለም:: ለምን እንደሆነ ምክንያቱ አይገባኝም:: በጣና ነው የምወድሽ:: ሁልጊዜ የማስበው አብሬሽ ለመኖር ነው"

"መቸኮል አይሆንም?"

"ለእኔ አይደለም:: ከፈለግሽ መጀመሪያ ቀለበት እናድርግ"

"ጥሩ ነው እንደዚያ"

"ለአባትሽ ብንነግራቸውስ?"

"እኔ?......እኔ?"

"እኔ እነግራቸዋለሁ"

"አትፈራም? የምትፈራ ይመስለኛል"

"አልፈራም"

"ግን ደንቡ ሽማግሌ መላክ ነው"

"ደስ ያለሽን"

"ደንቡ ነው ማለቴ ነው:: ለእኔ አይደለም"

"እሺ"

"ሽማግሌ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ?"

"አላውቅም"

"ጓደኞችህ ሊሆኑ ይችላሉ"

"እንደዛ ጥሩ ነው"

ተያየን:: ከጓዳ ትንሽ እህትዋ ሳል ሳለች::

"ታድራለህ እዚህ?"

"ባድር እወዳለሁ:: ግን ብሔድ ይሻላል"

"እለ ቦታ"

"ጥሩ አይደለም:: ሌላ ነገር ያሳስበናል" በማሾፍና በመፍራት::

በእጆቼ ፊቷን እየነካሁ:: በከንፈሮቼ ከንፈሮቿን እየነካሁ:: አብሬአት መተኛት ግን ፈራሁ:: ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላውቅም ነበር:: ዕርግጠኛ አይደለሁም::



@BOOKALEM

ስንሳሳም እንኳን የተላመድነው ቆይቶ ነበር:: እየተማርኩ ነበር:: ይኼን ልነግራት ፈለግሁ:: ከሴት ጋር ተኝቶ እንደማያውቅ መንገር የሚችል ወንድ ግን ማነው? ይከብዳል:: ግን መንገር አለብኝ:: ከእሷ በላይ የምወደው፣ የማምነው አልነበረኝም:: ማታ አምስት ሰዓት ላይ ስትሸኘኝ ተረብሻ ነበር:: የራሴ ልምድ ማጣት አበሳጨኝ......

ነጋሳ ከዕንቅልፉ ተነስቶ በር ከፈተ:: አማረረ::

"ደሐ ያለው ሀብት ዕንቅልፍ ነው:: እሱንም ከለከልከን::"

በር አጠገብ ስለሚተኛ ብዙ ጊዜ እንደተረበሸ ነበር:: ባመሸሁ ቁጥር እንደተረበሸ ነው::

"ሌላ ቤት መፈለግ አለብኝ" ይላል ብርድ ልብሱን እየተከናነበ::

የአለማየሁ ካሴት መዝፈኑን ቢያቆምም ቀያይና አረንጓዴ መብራቶቹ አልጠፉም:: በአለማየሁ የሴት መተኛት ችሎታው ቀናሁበት:: በኩረ እንደ አረጀ ትንቡርስ በቡላ ብርድ ልብሱ ተጀቡዶ አልጋ ላይ እያንኮራፋ ወድቋል:: በሕልሙ ማር ሳይሆን ሬት እየሰራ:: እኔም እያዘገምኩ በራስጌ በኩል በአንሶላዎቹ መሐል በረዣዥም እግሮቼ ፈልፍዬ ገባሁ:: ነጋሳ ይስላል:: ጀርባን ውሽማው ዘንድ አድሯል መሰል አልመጣም:: እነ አለማየሁ ከአንድ ሴት ሌላ እንዴት ማሰብ እንደሚችሉ እየገረመኝ ተኛሁ:: ከእንግዲህ በሌላ እንስት መለማመድ እንደማልችል ገባኝ:: ከሴት ጋር ስለመተኛት በአፍ መረዳትና ማስረዳት ይቻላል? እያንዳንዷ ሴት አንድ ናት? እነ አለማየሁ አንዳንዴ ሲያወሩ እንደምሰማቸው ዐይነት ከገነት ጋር ማድረግ እችላለሁ?

ያን ሌሊት ስጨነቅ አደርኩ::

ወንድነቴ እርግጠኛ መሆኑ እያስፈራኝ::

የአፏን ጠረን ከአፌ ላይ እያሸተትኩ::



@BOOKALEM

# ታባቁ ፀሐፊ

«ጨረቃ ስትወጣ»ን ካነበብኩ በሁዋላ ሰዎች እንዴት እንዲህ ያለ ነገር መፃፍ ይችላሉ እያልኩ መቸም እገረም ነበር:: ግን ለሰው አልነግረውም:: አልጠይቅም:: ሰዎች ስለመፅሐፍ አንዳንዴ ሲያወሩ ከመሐል አቋርጬ ገብቼ እኔም 'አንድ ጨረቃ ስትወጣ የተባለች መፅሐፍ አንብቤአለሁ:: ከሁሉ የምወዳት እሷን ነው' ማለት ይቃጣኝና አፍሬ ዝም እላለሁ:: ልናገር፣ በወሬ ልሳተፍ ብል ኖሮ ደ'ሞ ደጋግሜ፣ ደጋግሜ አንድ መፅሐፍ ብቻ አንብቤአለሁ ማለቱ እንደ ጅል የሚያስቆጥረኝም መሰለኝ:: እኔ ደግሞ በፀባዬ አንዳንድ ምዕራፎችን በቃሌ ከማወቅ ሌላ፣ አንዳንድ የሚማርኩኝ ፀረፍተ ነገሮች ከመፅሐፉ ገፅ በስተግራ ወይም በስተቀኝ በኩል፣ ከገፆቹ እግርጌ ወይም በስተላይ ይሰፈሩ ከማወቅ ሌላ የጠቅላላ ድርሰቱ ትርጉም እንኳን አይገባኝም ነበር::

አንድ ቀን ታዲያ ገነት በድንገትና በጥልቀት ትዝ አለችኝና የሆነ የሚያብሰለስል ትዝታ ድንገት ሩቅ ሩቅ አገር፣ ሩቅ ቦታ ብትኖርስ አጠገቤ ባትሆን ኖሮስ የሚል ስሜት ተሰማኝ:: ሲመሽ ቤቷ መሔድ፣ ሲመሽ አመዴ ገበያ ኬክ ቤት መገናኘት፣ ሲመሽ ሜክሲኮ አደባባይ መዞር፣ ቅዳሜ ቅዳሜ ተክለሃይማኖት መናፈሻ በመኪናዎችና በሰው ጩኸት መሐል በግል ፀጥታችን ተጠቅለን መነካካት ይቀርና ደብዳቤ እንፃፃፋለን:: እኔ ደ'ሞ በሕይወቴ ደብዳቤ ፅፌ አላውቅም:: ደብዳቤ ለመፃፍ ሲመስለኝ በመጀመሪያ የሚያውቁት ሰው ያስፈልጋል:: የሚያውቁት ሰው ብቻ ሳይሆን የሚቀርብ፣ የሚወዱት ሰው መሆን አለበት:: ታዲያ ይሔን ጭንቅላቴ ውስጥ ያጉነቆለ ሐሳብ በድርጊት ልተርጉም አልኩና ደብዳቤ ለመፃፍ ጠረጴዛችን ጉን ያለችዋን ወንበር ስቤ ተቀመጥሁ:: ከግራ የሸሚዜ ደረት ኪስ ቢክ ጭቃ ቀለም አወጣሁ:: የስክሪፕቶው ክዳን ተነክሶ ተጣሟል (ጥበቃ ላይ ከምሰራቸው ነገሮች አንደኛው ቢክ ስክሪፕቶ በጥሞና መንከስና ማጣመም ነው):: ከጠረጴዛው መሳቢያ ተጣጥፋ የተቀመጠች ደብተር አገኘሁና ከመሐሏ ሁለት ቅጠሎች ነቅዬ አውጥቼ እነበረችበት መለስኳት:: ከወረቀቶቹና ከጠረጴዛው መሳቢያ ጉድጓድ በለሰስታ የሚተን የተቀቀለ የእንጨት ጠረን ሸተተኝ:: በመስኮት የንፋስ ጎርፍ በመግባቱ ሳይሆን አይቀርም አፍንጫዬ ውስጥ የተጠለለው ጠረን በአጭር ጊዜ ጠፋልኝ:: በምትኩ የሚጠበስ በቆሎ አሸት::

እንግዲህ ፊት ለፊቴ ጠረጴዛ ላይ ወረቀቶች ተዘርግተዋል:: በግራ እጄ ቢኬን ይዤአለሁ (ግራኝ ነኝና):: ቤቱ አይሞቅም አይበርድም:: ሕሊናዬ ውስጥ ገነት እንደ ደም እንደ ፕላዝማ ትፈሳለች፣ ሁለመናዋ ይታየኛል:: ቀጥዬ ምን እንደምፅፍ ባላውቅም በስተግራ በኩል አለው የወረቀት ገፅ ላይ ከመሐሉ "ውድ ገነት" ብዬ ፃፍኩ:: ብዕሬን



@BOOKALEM

እያንቃንቅሁ ሐሳብ እንዲመጣልኝ ጠበቅሁ:: ደቂቃዎች አለፉ:: ከመሐል የፃፍኩት ነገር እንደተሳሳተ ብልጭ አለልኝና "ውድ ገነትዬ" ብዬ አረምኩ:: በዕውን ስሟን ስጠራ "ገነትዬ" ብዬ ጠርቼአት አላውቅም:: አፍር ነበር:: ስዕፍም አፈርኩ:: በስሜት እንደ ሁለት የከሰል ፍሞች ተቀጣጥለን አፍ ለአፍ ስንያያዝ እንኳን ስሟን ስጠራ "ዬ" የተባለችውን ፊደል ሳልጨምር ነው:: 'ዬ' የተባለ ፊደል ጨምሬ የጠራሁት ሰው በሕይወቴ ውስጥ ስላላጋጠመኝ ይሆናል:: ምናልባት የልምምድ እጥረት ነበር:: ታዲያ ጉን ለጉን ተጋድመን አንድ ክንዴ አንገቷ ስር ሆኖ የሚሞቁ ቅንድቦቿን ስስማት፣ የእጇን መሐል ስስማት፣ እጄ ሰንበሌጥ ወገቧ ዙሪያ እንደ ሐረግ ሲዞር እንደ ቀለጠ ዘቢብ የሚሸት ትንፋሿ አንገቴ ዙሪያ ያሬድኛ ሲነፍስ፣ ምን ማን ብዬ እጠራታለሁ?

'የእኔ እናት':: 'የእኔ እናት' ብዬ እጠራት ነበር:: ይሔ አሰያየም ለብዙ ያራዳ ልጆች የሚያስገርም ይሆናል:: እንበል......ሲመሽ በእግሯ ከሰባተኛ ብሌን ሆቴል እቤቴ ድረስ መጥታ......'ራት ሰርቼልሃለሁ ና' የምትል ደፋር ሴት፣ አባቷ ቡና ለመጠጣት ወደ ጉረቤት ሲሄዱ ልትስመኝ የምትቸኩል፣ ልትይዘኝ የምትቸኩል፣ ለእግሮቼ የማይመች የቤታቸው ወለል ላይ ተቀምጣ ጭኔ ላይ ፊቷን አስደግፋ የምታናውዝ ልጅ......ምን ብዬ እንደምሰይማት አላውቅሁም......ታዲያ ለእሷ ደብዳቤ መፃፍ ከበደኝ::

"ውድ ገነትዬ" ብዬ ከፃፍኩ በሁዋላ እግሮቼን ዘርግቼ ተቀመጥሁ:: ቢኩን በግራ በኩል ጠረጴዛ ላይ ጣልኩት:: ሐሳብ የለም:: ገነት ከእኔ ተለይታ የምትሔድ አልመሰለኝም:: ብትሔድስ? ማለት ገነትን ነገ ቤቷ ስሔድ ጅማ፣ ጎሙጎፋ፣ ሐረር፣ አሰብ ሔዳለች ቢሉኝስ?

በመጀመሪያ ራሴን ይገፂ እጮሃለሁ:: ሰው የተሰበሰበበት? አዎ እጮሃለሁ......እጅግ በጣም ስለምጮህ የባሕር ዛፎች ቅጠሎች ይረግፋሉ፣ አዝራሮች ከልብሶች ላይ ይረግፋሉ:: ታዲያ የምወዳትን ሴት እንደምወዳት የምገልፀው እንዴት ነው?......መፃፍ አልቻልኩም:: "ውድ ገነትዬ" ካልኩ በሁዋላ መቀጠል አልቻልኩም:: ከላይ የጠቀስኩት ስሜቴን እንዴት ደስ ወደሚል የቃላት ዝርዝር እንደምለውጠው ትንኝ የምታክል ግንዛቤ እንኳን አልነበረኝም::

ታዲያ አልሆን ሲለኝ በብርሐኑ ዘርይሁን ቀናሁ:: ሐብታሞች ከደሐ ዘርፈው ነው ሐብታም የሚሆኑት እንደሚባል ብርሐኑ ለእኔ የሚገባኝን የዘረፈኝ መሰለኝ:: ታዲያ ስለራሴ ልጻፍ ስል እምቢ የሚለኝ ማን ቢነጥቀኝ ነበር?

ብዙ ጊዜ አለፈ......ሰዓት ያህል:: ምንም አልፃፍኩም:: የማስበውም ነገር የተዘበረቀ ነበር:: ገነት ናት:: በየቦታው ግን ገነት ነበረች:: ሐሳቤ ሜዳዎች ላይ ገነት ናት:: እንደ መፀው ንፋስ ሐሳቤ ጉዳናዎች ላይ ገነት ናት:: እንደ ጥቅምት እምራ::



@BOOKALEM

ሐሳቤ ሻላ ውስጥ ገነት ናት.......እንደ ወርቅማ ዓሣ.......እንደ እንደ ዝይ.......ስክሪፕቶዬን አነሳሁና "ውድ ገነትዬ" በሚለው ስር በሦስት ሰልፎች እነዚህን ፃፍኩ፡

ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት
ገነት ገነት ገነት

በር ተንኳኳ.......



@BOOKALEM

# ገነት ዲቃላ ናት

አባቷ በውሸት ማረሻ መሬት ይቀዳሉ፣ በየጉዳናው በፒያሳና በመርካቶ እየዞሩ ኪስ ያወልቃሉ ቢሉኝ፣ ፍራሽ አዳሽነት ለመሥራት እግራቸው እስኪያልቅ ድረስ ከእንጦጦ እስከ ቄራ ድረስ ይኳዛሉ ቢሉኝ፣ ቀይ ሽብር አፋፋሚ ሆነው ስድስት መቶ ወጣት አጥፍተዋል ቢሉኝ፣ በዘር የመጣ ውርዴ ይዞአቸው የህይወታቸውን 50% ጠበል ያሳለፉ ናቸው ቢሉኝ፣ በቤተ ክርስቲያን መቅደስ ላይ ምራቃቸውን ተፍተው ለቅጣት በመቋሚያ ተወግረዋል ቢሉኝ፣ አንድ ዐይን፣ አንድ ጥርስ፣ አንድ ጆሮና አንድ እግር ብቻ እንዳላቸው በስማቸው የሚጠራ አንድ ጣት ብቻ ነው የቀራቸው ቢሉኝ፣ እናም ምላሳቸውም እንደ እባብ ስንጥቅ ነው ቢሉኝ፣ ምንገድ ዳር ግሮሰሪ ከፍተው በፓስታና በማኮረኒ ምትክ የፀጉር ሽበትና ትላትል፣ በቅቤ ምትክ ቫዝሊን፣ በዘይት ምትክ ሽንት ይሸጣሉ ቢሉኝ እኔ እኔ መዝገቡ ግድ የለኝም። እናቷ እሁድ ፀሐይ ስታዘቀዝቅ ጀምሮ አራዳው ጊዮርጊስ ዝግባ ጥላ ሥር አንጥፈው ከሰበታ ኩተቤ ከእንጦጦ ንፋስ ስልክ ለአሳፊ አግዳሚው እራሳቸውን ለሰሳ ጨዋታ ይጋብዛሉ ቢሉኝ፣ በልጅነታቸው......ማለት ሞሳ እያሉ ቋንቋቸው የውሻ፣ ዐይኖቻቸው የጃርት ነበሩ ቢሉኝ፣ ገነትንም ከመውለዳቸው በፊት መንታ ድመቶች፣ መንታ ቁራዎች፣ መንታ ቀበሮዎች ወልደው ነበር ቢሉኝ፣ እሁድ በአፋቸው ሞጥማጣነት ወላ ጠመንጃ ያዥ ሰፈርን፣ ወላ መርካቶን፣ ወላ መሳለሚያን አፋጅተው ወደ ቦረና አሰደዱ ቢሉኝም፣ እኔ መይሳው ዝምተኛው ገላጩ ቡቃያ ግድ አይሰጠኝም።

ለእኔ ገነት እንዲያ አልነበረችም።

ገነት የርብቃ የጭን ቀለም፣ የወሰን ቁመና እና አንድ ሌላ የማላውቃት ሰባ ሴት ዲቃላ ነበረች።



@BOOKALEM

# ጠባሳው

ሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ አንድ ሆቴል ቤት አርፌን ነበር። በስተቀኜ በኩል ራስጌ ላይ ነጠላ ጫማዋን አውልቃ ትራስ ተደግፋ በከፊል ተቀምጣለች፣ በከፊል ተጋድማለች። ኩታዋን በቀስታ ከላይዋ ገፋ ከራስጌ ወንበር መደገፊያ ላይ በጥንቃቄ ጥላዋለች። ፍርሃት ፍርሃት ይለኛል። በሆነ ደስ በሚል ሙቀት የተከበበ ፍርሃት። አንገቴን ሰበር አድርጌ በዘፈቀደ የወደቁ አቧራ የለበሱ ነጠላ ጫማዎችዋን አያለሁ። በሀሳቤም ትራስ ተደግፋ ድልህ የመሰሉ ከንፈሮቿ ልቤን ሊያሳምሙት እንዠ ተዘጋጅተዋል እላለሁ። ጫማዬን አወለቅሁና በእረፍት ተንፈስኩ። በጎን አየሁዋት። ባለአበባ ቀሚሷ እስከ ጡቶቿ መገናኛ ክፍት ነበረች። ከነዚያም ስር ትንንሽ ጉልላቶች እንደሚሞቅ የማር ጉርሻ በአፌ ሊገቡ እየተንቀጠቀጡ ተቀምጠዋል። ሸሚዜን አወለቅሁ። ስትንቃንቅ ሰማሁዋት።

ገነት ጠባሳዬን በጉጉት ስትነካው እሰማታለሁ፤ ደነገጠችና: "ምንድነው ይኼ?" አለች።

"ጠባሳ" አልኩ ዞርም ብዬ ሳላያት።

አዞረችና ፊቴን አየችኝ።

"እሳት ነው ያቃጠለህ?"

ቀርባለች።

"የፈላ ውሐ" አልኳት

"አንተ ምሮሀል.......የአንገትህን ጅማት ቢያገኝህ ኖሮስ?"

ትከሻዬን ከፍ ዝቅ አደረግሁ።

"ምን ስትሰራ ነው?"

"አደጋ"

"ቆይቶአል?"

"ትንሽ ሆኜ.......አይቸው አላውቅም"

"ለምን?"

"አይታየኝማ"

ግን ጠየቅሁዋት: "ትልቅ ነው?"



@BOOKALEM

"እስከዚህ አይደለም"

"ምን ያክላል?"

እንደገና አዞረችኝና ጠባሳውን ካጠናች በሁዋላ መዳፏ ላይ በጣቷ የማይታይ ክብ በመሳል፡ "ይኼን ያህል" አለችኝ::

ጠባሳዬን ለጥቂት ጊዜ በዝምታ እየዳበሰችኝ ተቀመጥን:: ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላወቅም ነበር::

ዞሬ ፊት ለፊት ሳላያት ቀድማ ፊቷን ቀኝ ትከሻዬ ላይ አስቀመጠች:: በጉንጮቿ ስትዳስሰኝ ቆየች:: በግራ እጄ ያወለቅሁትን ሸሚዜን ይገፍ ዐይኖቼን ጨፍኜ አስማቷን አዳምጣለሁ:: አፏ በቀስታ ተከፍቶ በሞቀ ከንፈሮቿ ጠባሳዬን ሳመችው:: እንዲህ አጎንብሼ ወለል እያየሁ ግን ወለል ሳላይ......በቀኝ ጭኔ ላይ ተረማምዶ የመጣውን ስስ አቧራ የሸፈነው እግሯን ባላባቸው ጣቶቼ እየዳበስኩ ደሞም እየረሳሁት......እንዳትጀምረኝ አፍራ፣ እንዳልጀምራት ፈርቼ.......:: ተረከዙ ትንሽ ጠመም ያለ ቆዳ ጫማዬ አንዱ የእሷ አንደኛው ነጠላ ጫማ ላይ ተጋድሞ ነበር- ......ሁለቱም ጉዞ አድክሟቸው እንደ ነበረ:: ጠባሳዬን እንደገና ሳመችው.......የአፏ ፈሳሽ እንደ ጠበል ከቁስሌ ላይ አፍረት ሲገፍ:: ሌላ ለምን ነበር? ውጥኔ ጭና እንደ ጣዝማ ማር ነበር......እንዲህ በፍርሃት በጎን ሳየው::

እንደገና ሳመችው::

ጠባሳዬ ተደፈነላትስ?

የምላሷ ጫፍ ትኩሳት የአጥንቴ ቁስል ድረስ ከትባቱን ይዞ ይሰርጋል......

የሞቀኝ የምራቋ ቅባት ሳይደርቅ.......

እንደ ገና ሌላ::

የማደርገውን አላወቅሁም:: ወደ መሬት ወርጄ ዞር አልኩና ዓይኖቿን በዓይኖቼ እንዳላይ አድርጌ በቀስታ ፊቴን ከጉልበቶቿ ከፍ ብዬ ጭኖቿ መሃል በቀስታ አስቀመጥኩ:: እጆቿ ማጅራቴንና ፀጉሬን ይዳብሳሉ:: ቀሚስዋ ጠረኑ የቅርንፉድ ነበር:: በበሶብላ የተሰራም ወጥ ነበር.......የጭኖቿን የውስጥ ውስጥ .......እንዲህ ቀለም የበዛውን.......ወዝ ሽፍ ያለበትን.......ንፋስ እንኳን ያላገኘውን በቀስታ ሳምኩት:: ሌላ ምን ላድርግ? እንደሚጎርስም አፌን ከፈትኩ.......ምን ልፍጠር?

እጅግ የሚያምር ድምፅ አወጣችና (እንደሚያዝን ይሄም ሐዘን ውጋት እንደሆነባት ሁሉ) እስከ መጨረሻ አጎንብሳ ጠባሳዬን ደግማ ሳመችኝ::



@BOOKALEM

እንዴት እንደቻለችበት? አንቺ ያገሬ ልጅ ሽንጥሽ እንዴት ተሳበልሽ? ፊቴን ጭኖቿ መሃል እንደቀበርኩ (እንዴት ይሞቃሉ!) ወገቧን በሁለት እጆቼ አቀፍኩ......

እንዲህ ሆነን የሰዓት ኩርማን ያህል ፈጀን:: እመቤቴ ማርያም ከሰማይ ክንፏን እያርገበገበች የምትወርድ አፍቃሪ ብትልክልኝ ከዚህ የተለየ ትሰራለች?

ጆሮ ያለውም ይስማ......



@BOOKALEM

## ቤት ኪራዩ መክፈል የከበደው ጎረምሳ ሸማግሌ መሆን ለይችልም ያለው ማነው?

ማታ እቤት ንትርክ ቀልጦ ደረስኩ:: ነጋሳ አዲስ ቤት አገኘሁ ብሎ ከወጣ ሳምንት ሆኖታል:: አለማየሁና ጃፓን ይነታረካሉ::

ጃፓን: "ስማ መዝገቡ.......አዲስ ሰው ይግባ እንዴ በነጋሳ ምትክ?" ብሎ ጠየቀኝ::

የምመልሰው አልነበረኝም:: ትከሻዬን ነቀነቅሁ እንደ 'ግድየለኝም'

"ተናገር እንጂ. መደባደብ ነው የቀረን:: ይኼ አለማየሁ ገንዘቡን ለጭቅናና ለካሴት እየበተነ ተጨናንቀን እንድንኖር ይፈልጋል......እኔ እዚህ ቤት ከእንግዲህ ማንም አይገባም ብዬአለሁ:: አራት ሰው ይበዛበታል......ወንበር እንኳን የለንም ሰው ቢመጣ የምናስቀምጥበት"

አለማየሁ እጁን ያመናጭቃል::

"ለምን ስለዚህ ነገር ሌላ ጊዜ አንነጋገርም:: አንድ ጉዳይ አለኝ እኔ ሁለታችሁንም ማማከር የምፈልገው" አልኩ::

"አይሆንም መጀመሪያ ይሄ ይወሰን"

"ምነው የፀረ-አብዮት ርዝራዦች ያሉበት ስብሰባ ሆነ" አለ ጃፓን::

"ዝንበል እባክህ.......በወር ሰላሳ ብር አልከፍልም.......ምን ልበላ ነው?"

"ጫልቱስ?......ጫልቱ አንተን በርካሽ አይደለም ሆድህን ሞልታ የምታኖርህ? ይኼ ሁልጊዜ የተቀደደ ሆድ"

"ምን አባቱ ይላል......."

"አንተ አፍህን ያዝ......ለጠየቀህ ልጅ አዝነህ ነው ወይስ ገንዘብ ስለሌለሽ ነው.......ካልቻልክ ቴፕህን ሽጥ"

"ራስህን አትሸጥም?"

"እኔን ማን ይገዛኛል:: ሞክሬ አልቻልኩም:: ቢቸግረኝ ፖሊስ ሆንኩኝ"

"ሌላ ምን ትችላለህ? ሌላ ሰው አይገባም:: አይገባም"

በዝምታ ጫማዬን አውልቄ አልጋዬ ላይ ወጥቼ ግድግዳ ተደግፌ ተቀመጥሁ:: ብዙ ተነታረኩ:: በመጨረሻ አለማየሁ ያው በአራዳነቱ፣ ያው በችግረኛነቱ አዲስ ሃሳብ አመጣና ነገሩ ለሌላ ቀን ተሸጋገረ::



@BOOKALEM

"ሐሳብ አለኝ" አለ አለማየሁ::

"ተናገረዋ" ጃፓን

"ሰውዬው አይመጣም ግን እኔ የምከፍለውን ተጨማሪ ገንዘብ አንተ ትከፍላለህ"

"ለምን?"

"ተጨማሪ አልከፍልማ.......እኔ የቤቱን ኪራይ በአምስት ሰው ማካፈል ነው የለመድኩት:: እንደገና በአራት ማካፈል የምችል አይመስለኝም"

"ምን መሆንህ ነው? የማካፈል ሂሳብ አትችይም ወይስ አራዳ እየሆንሽ ነው?"

"ከባድ ነገር የለውም:: ነጋሳ ከሄደ የምንከፍለው ሰማኒያ ብር ነው አይደለም ኪራዩ? እኔ ከአስራ አምስት በላይ አልከፍልም:: አልችልም"

"በጣም ተጨቃጨቅክ:: ለማንኛውም ነገ ወይ ሌላ ቀን እንነጋገርበታለን.......መዝገቡ እፈልጋቸዋለሁ ብሎናል"

"እሱስ እራሱ ሐሳብ አይሰጥም?"

"ተወው.......ሌላ የባሰ ችግር ይኖርበታል"

"ምን ችግር አለበት ደሞ እሱ? ማደሪያውን ቢያዘጋጅ አይሻለውም? አንተ!.......ለምንአባክ ነው የምትፈልገን" አለማየሁ::

እየሳቅሁ አየሁዋቸው::

"ላገባ ነው"

"ምን .......?" ተያዩ

"ቀለበት ላደርግ ነው"

"ከማን? ከገነት ጋር እንዳትለኝ" አለማየሁ እያጨበጨበ ከተጋደመበት ተነሳ.......ገና ጭንቅላቴን በአወንታ ስነቀንቅ አይቶ::

"ሽማግሌ እፈልግ ነበር" አልኩ

"የምን ሽማግሌ?.......ወስደህ አታገባትም እሺ ካለች:: ይሄን ያህል ደረሳችሁ?"

ለመጨረሻው ጥያቄ መልስ ልሰጠው አልፈለኩም::

"ሽማግሌ እንድትሆኑኝ ነው የምፈልገው"

"ጃፓን ታደልክ:: ቁምነገር ሠርተህ አታውቅም" አለ አለማየሁ በማሾፍ::



@BOOKALEM

"ምናባቱን ዝም በል.......ጨዋታ አይደለም ይኼ" በመገረም ያየኛል::

"ለምን አንሆንም.......እንሆንልሃለን" አለማየሁ::

"መቼ ነው የምንሔደው?.......በጣም እፈልጋለሁ ሽማግሌ መሆን" አለ ጃፓን::

"ከሁለት ሳምንት በሁዋላ:: እሁድ ዕለት"

"ክራቫት ያስፈልጋል?" አለማየሁ::

"እንጃ--ደስ እንዳላችሁ"



@BOOKALEM

## ጭቃና ሰንቁ

እንደ ጨቅላ አፈን ከፍቼ በሐሳብ ሰምጬ እጓዛለሁ:: በግራ እጄ ባርኔጣዬን ይገፍአለሁ:: በስተግራዬ እስታዲዮም ነው:: በስተቀኝ ገነት ሆቴል:: ከሆቴሉ የሚወጡ መኪናዎች ጡሩንባቸውን እያንቦጫረቁ እንደውሐ እየፈሰሱ ይወጣሉ:: የሚገቡቱ አደናጋሪ ልማድ ኮሽታም አይሰሩ:: ፈጥኖ የሚመሽ ቀን ይመስል ነበር:: እንደጨቅላ አስባለሁ:: ስለገነት ወተቴ ነገር:: በፍቅር የበራ ልቤ ውጋጋኑ ዩኒፎርሜን አልፎ ለዕውራን እንኳን ሳይታያቸው ይቀራል? በሰራ አካላቴ የተሰራጨው ሙቀት እንዲህ ለተላላፊ ምንገድኞች እስኪታያቸው ጭስ ሳያንቦለቡል ይቀራል? ቀኝ እጄንም ዘቅዝቄ ብይዘው፣ እንዲህ ሳላራግፍ ከላዩ እርጥብ የማር እንጀራ (በወዝ የተመሰለ......ቀልዴንም አይደል) ይቀረፉል......የገነትን ራቁት ደረት፣ ራቁት ጀርባ......ራቁት ጭኗ የዳበስኩበት:: ጥርሶቼም ተወልውለው ነበር ከነጭ የነጣ ነጭ ሆነው ገነት የእኔ አበባ በዕብድ ምላሷ አጥባኝ:: የአዲቬንቲስቶችን ቤተክርስቲያን አለፍ እንዳልኩ የማውቀው ሰው ድምፅ ሲጠራኝ ሰማሁ:: ለረዥም ጊዜ የተለየነው ሰው ፊቱ ትንሽ የጥንቱን፣ ብዙ ግን እርጅናውንና መጥፋቱን ይዞ እንደሚያደናግረኝ:: ዞር አልኩ:: በስተቀኝ አጥር ስር ዐጉሩ ጨፍሮ፣ ገፁ ጠቁሮ፣ ጭስ የጠጣ የመሰለ ሰው ተቀምጦ ነበር:: ዙሪያውን ጉልበት የሚደርስ ለምለም ሳር ነው::

"ምነው ወንድም እዚህ መፀዳዳት ክልክል ነው" አልኩት::

ሳይመልስልኝ ከተቀመጠበት ተነስቶ ሱሪውን ማጥለቅ ጀመረ::

"አንተን እኮ ነው......" አልኩት::

"አይ መዝገቡ ሰው ትረሳለህ" አለ ሰውዬው በመሳቅ::

አተኩሬ አየሁትና ማን እንደሆነ ተረዳሁ:: ከወዲያ መንገዱን ተሻግሮ ሰዎች ሲስቁ እሰማለሁ:: አንድ ወንድና ሴት እጅ ለእጅ ተያይዘው ሊያልፉኝ ሲሉ ሰውዬውን ሳስረው ለማየት ፈልገው ነው መሰለኝ ቆሙ::

"መንገዳችሁን ቀጥሉ አያገባችሁም" አልኳቸው::

ገላምጠውኝ መንገዳቸውን ቀጠሉ:: ሰውዬው በሣሩ መሐል እየተራመደ በትከሻው ላይ በቁሳቁስ የተወጠረ ቀረጢት ይዞ ሊያቅፈኝ እጁን ዘረጋ:: እኔም ባርኔጣ ያልያዘው እጄን ዘረጋሁ::

"እነዚህ ፖሊሶች አልጠገቡም?" ስትል መንገድኛዋን ሴት ሰማሁዋት::

ወሉዬው ዐይነምድርና መሰየም የሚከብድ የእህል ዐይነት ይሸት ነበር::



@BOOKALEM

"ወዳጄ መዝገቡ......ወዳጄ መዝገቡ......አቦሌሳ መዝገቡ:: ተጠፋፋን ተጠፋፋን!!" አለ በጩኸት::

"የት ጠፋህ? የት እጠፋለሁ እዚሁ ነኝ"

"የተስማማህ ትመስላለህ:: ሁለታችንም ተመሳሳይ የምንገድ ላይ ሰዎች እንመስልም"

"የት ጠፋህ?"

ቀረጢቱን አስቀመጠ::

"ብዙ ነው:: ብዙ ነው:: እኔ የወጣሁትን የመከራ ተራራ:: ዋኘቼ ያለፍኩትን የስደት ጉርፍ ኖህ አይችለውም:: ያውም ያለ ጀልባ በዚህ እግር" አለና ወደ እግሩ አሳየኝ:: በጣም አዲስ ቆዳ ጫማ አድርጓል::

"የት አገኘህ ይኼን ጫማ?"

"ሰረቅሁ:: የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ ሲባል አልሰማህም' ሃሃሃሃሃ"

"ጥሩ ቀልድ አይደለም"

"ፊትህ ላይ ይታያል......አዎ......ፊትህ የፍቅር ምቾት አለበት:: ቀጭን ሆነህ ተወልውለሃል:: የሆዳም፣ የሀብታም ምቾት አይደለም:: የፍቅር:: ሚስት አገባህ?"

"አዎ:: አመት አለፈኝ"

"ትወዳታለህ? እ?" አለ በሚያሾፉ ዐይኖች::

"በጣም"

"አንድ ምክር ልጠይቅህ?" አለ ቀኝ እጁን ትከሻዬ ላይ አድርጐ በትንንሽ ጥቁርና ነጭ ጉንዳኖች የተወረረ የመሰለ ፀጉራምና ላባም ጠይም ፊቱን ወደፊቴ አስጠግቶ::

"ምን? ምን ፈለግህ? እኔ መካሪ አይደለሁም"

"ግድየለም:: አንድ ጉዳይ እነግርሀለሁ:: ስሜትህን ንገረኝ:: ስሜትህን ብቻ"

"ስሜት? ስሜት ብቻ?"

"ስሜት አይሳሳትም"

"ማን አለ?"

"ነገሩን ተርኬልህ ሳበቃ:: ያኔውኑ የተሰማህን ትነግረኛለህ"

"እ......እሺ......"



@BOOKALEM

"ጠረንህ ሁሉ ተለውጧል"

"እንሳ እጅህን ከላዬ"

"ባለቤትህ የምትወድህ መሆን አለባት"

"ሊታወራ የፈለከውን አውራኝ"

"በሚስቶቻቸው የሚወደዱ ጥቂቶች ናቸው:: 'ኑሮ ሲስማማህ ጠረንህ ይለወጣል' ትለኝ ነበር እናቴ:: እኔ አላልኩም እናቴ ናት:: ኑሮ ሲስማማህ እንደ ሉፍ ዘር ትሸታለህ:: ምን ልበልህ......እም......ወይም እንደ ናና ከረሜላ......"

ዞር ብዬ አየሁት:: እጁን ከትከሻዬ ላይ አነሳ::

"ልንገርህ እሺ:: በመጀመሪያ ልጠይቅህ ናና ከረሜላ ትወዳለህ?"

ጉንበስ ብሎ መሬት ላይ የጣለውን ቀረጢት ሸምቀቆ ከፍቶ ከውስጥ በጋዜጣ ቁራጭ የተጠቀለለ ነገር አወጣ:: ጥቅሉን በቀስታ ፈታታና......ትልልቅ አስፕሪን የመሰሉ የናና ከረሜላዎች አሳየኝ::

"አንድ ይበቃሃል? ሁለት?"

"አንድ ስጠኝ"

አንድ ለራሱ በላና ሁለተኛውን በአውራጣቱና በሌባ ጣቱ ይዞ ቁጢጥ ካለበት እጁን ዘርግቶ ሰጠኝ:: ተቀበልኩ:: ናና ከረሜላዋ ላይ ጋዜጣው ረጥቦ የተዋቸውን ጥቂት ፊደላት አያለሁ:: ፊደላቱ እንደ መስታወታዊ ምስል ናቸው:: እንደገናም ስስ ጥቁር ቅሬተ-ቀለም የከረሜላዎቹን ጠርዞች ሸፍኗቸዋል:: ከረሜላዋን ሳገላብጥ አይቶ......

"ቆሻሻ ሆነብህ? ትንቢት አልሰማህም? 'ከበረሐ አንበጣና ናና ከረሜላ እየበላ የሚመጣ፣ አዲስ ቆዳ ጫማ ያጠለቀ፣ ቡቱቱ የለበሰ፣ ጥፍሩ የረዘመ፣ የጠቆረ፣ የከሳ፣ ገልጃጃ......የተንገላጀጀ፣ ሌባ፣ ቀማኛ፣ እዚህ ግባ የማይባል ቀርፋዳ ምስኪን ስጦታ መልካም ስጦታ ይዞላችሁ ይመጣልና"......"

"ማሾፍህን ተውና አወራሃለሁ ያልከኝን ንገረኝ......"

"ተዘጋጅተሃል?"

"ተአበኛ ነህ" ከረሜላዬን አፌ አስገባሁ::

ወደ ቀረጢቱ ጉንበስ አለና: "የማሳይህ ዕቃ አለ:: እዚህ ሰው ይገናዘበናል:: ለምን ደበቅ ያለ ቦታ አንሔድም?"

"ምንድነው የያዝከው......"



@BOOKALEM

"ከተማው ያንተ ነው:: ደበቅ ያለ ቦታ ታጣለህ?"

ቦታ ስንመርጥ ትንሽ ደቂቃዎች አጠፋን:: በመጨረሻም ከኢትዮጵያ ሆቴል ጀርባ ዛፎች በበዙበት አንዲት ጠባብ አስፋልት ምንገድ ላይ ቆምን:: ጥቂት መኪናዎች ከጆማ ምንገድና ከቀኛችን ይመጣሉ:: በፍጥነት ያልፋሉ:: እኔ አጥር ተደግፌ ቆምኩ:: ባርኔጣዬን አጠለቅሁ:: ወሉዬው ጀርባውን ለምንገድ ሰጥቶ ቀረጢቱን እኔና እሱ መሐል ምንገድ ላይ አስቀመጠው:: ተጠጋኝ:: የአፉ ትኩሳት ፊቴ ላይ ይሰማኛል:: ላቡ ይሸታል:: ከቆሸሸ ፊቱ መሐል ብቅ የሚሉት ጥርሶቹ አስገራሚ ንጣትና ለቀቅ ያለ ፍንጭት ነበራቸው::

"ወታደር ነበርኩ" በድንገት ሳቀና (ሃሃሃ) በድንገት ዝም አለ:: ቀጠለ::

"የእስር ቤት ዘበኛ ነበርኩ:: ከዚያም በተጨማሪ ሙት ይብቃ የተፈረደባቸውን እሰቅል ነበር" ትክ ብሎ አየኝ:: ቀጠለ......

"አትፈራም? ፊትህ የተገረመ ይመስላል:: ወይስ ያንተ ፊት አይደለም:: ሰባት ሰዎች ሰቅያለሁ:: ሰባተኛው የሰቀልኩት ሰው በላይ ዘለቀ ይባላል:: ስሙን ሰምተሃል?"

በአወንታ እራሴን ነቀነቀሁ......

"ሰውዬው እስር ቤት እያለ ይበሳጭ ነበር:: እንደምሰቅለው እያወቅሁ አከብረው ነበር:: በአገሩ ሰው ይበሳጫል:: ተፈሪ ፊርጣጬ በሚባለው ንጉሥ ሳይሆን በሕዝቡ ይበሳጫል:: አንድ ቀን ምሳውን ሳመጣለት ምን አለኝ መሰለህ...... 'አንድ ቦታ ትወስደኝና የአንጀቴን እናገራለሁ':: ልወስደው አልፈለኩም:: ሰው ይወደዋል ስለሚባል ብቻ የሥራ ስነ ሥርአቴን ረግጬ የት እወስደዋለሁ መሰለህ ንፋስ መውጫ ያ:: ውሽታም ነው:: እዚያች ውሰደኝ አለ......እሺ ብዬው ወሰድኩት......አይ ገፉ አድርገህ እዚያች ውሰደኝ አለ:: እሺ አልኩት::......ቀጠልን......ስንል ስንል ቅልጥ ያለው የባላገር አገር ወስዶኝ ቁጭ:: ማን ቤት እንዳደርኩ ታውቃለህ? አልቤቲ የምትባል ወጣት ክልስ ቤት፣ እናቷን ባሊያን ሲገባ ሽርሙጣ አድርጎት የሔደ......ምንገድ ሠሪ ታስተናግድ ነበር አሉ ያኔ:: ከከተማው ወጣ ያለ ቤት......እሷ ስትሞት ልጇ ዛሬ መለኮ ሆናለች......" ትክ ብሎ አየኝ::

"ይኼን ሁሉ እንዴት አወቅህ?"

"ነበርኩ......ለሁለተኛ ጊዜ:: ድሮም ነበርኩ" ሳቅ አለ::

"እኔ ከዚያ እንደመጣሁ እንዴት አወቅህ?"

"አጋጣሚ የሚሠራው በእግዜር ነው......አታምንም?"

"ዱባለ የሚባል ሰው እውቀሃል?"



@BOOKALEM

"ፀጉሬን የቆረጠኝ እሱ ነው"

"እሺ ዋናውን ታሪክ ንገረኝ"

"ዋናው? የቱ ነው ዋናው ዞረብኝ" አለ በማሾፍ::

"ገባህ የምለው......"

"ታዲያ ይኼ አርበኛ ነኝ ባይ ትልቅ ድንጋይ ላይ ወጣና ሾስቴ አይሮጥህ መሰለህ?"

"ወንድ አይወለድብሽ" አልኩት::

"ታሪክ አዋቂ ይግደለኝ" አለ በማሾፍ::

"ቀጥል እሺ......"

"እርግማኑን ጨርሶ አንከብክቤ አመጣሁት:: እስር ቤት አስገባሁት:: ያወቀ አልነበረም:: ጉርሻ ለሚያስፈልገው ጉርሻ ሰጠሁ:: ኑዛዜአቸውን ሰማሁ:: ያው ሰቃይ ነበርኩ:: ሰቀልኩት:: ፎቶዬ በዚያን ጊዜ የወጣው ጋዜጣ ላይ ነበር:: ስሰቅል አይደለም የተነሳሁት:: እንደተመልካች ራቅ ብዬ ሳይ:: የእኛ አገር ሰው ስቅላት ማየት ይወዳል:: ስትፈራገጥ፣ ሽንትህ፣ ፈስህ ሲያመልጥህ......ፈሳሽ ሲወጣህ የሚደሰት ይመስላል:: ንጉሡ ራሱ በሐሳቡ በስቅላት ድርጊት ሳይዝናና አልቀረም:: ይገርማል በእግራችን ስንጓዝ......"

"የጭቃው ጫማ......" አልኩት::

"ታውቀዋለህ......?"

"ንፋስ መውጪያ ይወራል......"

ወደ ጆሮዬ ጠጋ አለ::

"የዕንቁ ጫማ ሊሆን አይችልም? ለማን ነው የምታደላው? ለዕንቁው ነው ለጭቃ?"

"ለዕንቁ"

"ለሐብት:: ዕንቁ ከጭቃ ነው የሚወጣው:: ዕንቁ ጭቃ ነበር አሉ:: እና እኩል ናቸው:: አይመስልህም?"

"ምን አገባኝ አቦ:: ወሬህን ጨረስክ?"

"ወሬ አልከው:: ዓለም ጭቃና ዕንቁ ያለባት ናት:: ጫማ ናት:: ኑሮ ምንገድ ነው የየራሳችንን ጫማ አጥልቀን የምንጓዝበት:: በላይን ንፋስ መውጪያ ስወስደው ዕንቁ



@BOOKALEM

ሆንኩ:: ስሰቅለው ጭቃ ሆንኩ:: የሰቀልኩብትን ገንዘብ ሚስቴና ልጄ ጋ ስወስድ ዕንቁ ሆንኩ:: ግን አንድ ሰው ነኝ:: ሁለት አልሆንኩም? አየህ ጭቃና ዕንቁ አልሆንኩም?"

"ከአርበኛ ጋር ምን አገናኘው......"

"የአንተ አርበኛ አበበ ቢቂላ ነው......"

"እንዴት አወቅህ?......" ደነገጥኩ::

"ቤትህ ነበርኩ:: አባትህ ወስዶ አሳየኝ:: ፀጉሬን ሲቆርጠኝ ስለአንተ አወራሁት:: እንደማውቅህ ሁሉ ካወራኸኝ እየነካካሁ:: አታላይ ነኝ?......የጀመርኩትን ልጨርስ......በነገራችን ላይ......"

ቀረጢቱ ውስጥ እጁን እስከትከሻው ከቶ እየዳበሰ ቆየና በእጁ ትልቅ በአሮጌ ካኪ ጨርቅ የተጠቀለለ ነገር አወጣ::

"ጫማው ነው እንዳትለኝ" አልኩት::

"በቀስታ:: ሰው ይሰማናል......"

የበለጠ ተጠጋኝና ጨርቁን በቀስታ እየፈታ ጥቂት ጊዜ ቆየ:: ግራና ቀኝ አየ:: ዞር ብሎም የማያይ ሾፌር አንድ ቀይ ሬኖልት አሥራ አራት እየነዳ አለፈ:: ወሎዬው ጥቅሉን መፍታት ሲጨርስ ከአሮጌው ጨርቅ መሐል የውስጥ እግር ቅርፅ ያለው በጭቃ፣ በዕንቁና በከበረ ድንጋይ የተገነባ የጫማ ሶል የመሰለ ነገር ወጣ:: የሚያስፈራራ ውበት ነበረው:: ጨርቁን እንደ ፎጣ አንገቱ ላይ አስቀመጠና ይኼን ጫማ የመሰለ ነገር ሲገለብጠው......ከሥሩም ተመሳሳይ በሆኑ ዕንቁዎችና የከበሩ ድንጋዮች ተሸፍኗል:

"ቀኝ እግሩ ደህና ነው......ግራውን እይ"

ግራውን ጫማ ሲገለብጠው ከስሩ የነበሩት (የት አይቸው አውቃለሁና ነው) የከበሩ ድንጋዮችና ዕንቁዎች ከፊሎቹ ወልቀው ተወትፈው የነበሩባቸው ቦታዎች ሠፋፊ ጉድጓዳዎች ይታያሉ::

"ከፊሉ ጠፋ:: ከፊሉን በላሁት:: በምን ልኑር? ጭቃና ዕንቁ:: እያስቀመጥኩ ልጨርሰው?"

የጭቃ ጫማ......ወይም የጭቃ ነጠላ ጫማውን በጣቶቼ ዳበስኩት......

"ጭቃው ውስጥ ሣር አለ......" አልኩ በአድናቆት::

"ሁሉ ነገር አለ......:: አንድ ሰሞን ዝናብ መትቶ ሳር እንዳይበቅልበት ብዙ ለፍቼአለሁ"

"ምንገድ አልነበረም የምታድረው?"



@BOOKALEM

"ዕንቁ ይገኜ ምንገድ ላይ አድራለሁ?......ዕንቁውን ለማዳን ጭቃ መሆን አለብኝ:: አስር ዕንቁ ለማዳን አንዱን ትሸጣለህ......ዘጠኝ ይሆንብሃል፡ የቀረውን ለማዳን አንዱን ትሸጣለህ—ስምንት ይሆንብሃል፣ እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: የመጨረሻውን ለፍፁም ሆድህ ትሸጠዋለህ:: ዕንቁ መሆንህ እንዲታይ በጭቃ በኩል ማለፍ አለብህ......"

"ለምን ትነግረኛለህ ይኼን ሁሉ......"

"ተረት ሁሉ ዕውነት አለው......ዕውነቱም ሁሉ ተረት አለው......"

"ምን ታደርገዋለህ ይዘህ......ይሄንን:: የምለው ብትዘረፍስ......?"

"ከእኔ ምን ይዘረፋል:: ራስህን ሌባና ዱርዬ ለማኝ ካደረግህ ሰው ይሸሽሃል......የምፈልገው እሱን ነው:: ሲሸሹኝ ነፃነቴ ይበዛል:: የእኛ ሰው ሀብታም ከሆንክ 'በጣም ሀብታም ሆነ' ብሎ ይሸሽሃል:: ስትደኸይ 'ዕድለ ቢስ' ብሎ ይሸሽሃል"

ከእጁ ላይ ጫማውን ተቀበለ::

"አልመለስክልኝም:: ይኼ ሁሉ ለምንድነው?"

"ቀረጢቴን ታስቀምጥልኛለህ?"

"ለምን አመንከኝ......?"

"መልካም ሰው ነህ:: ምንገድ ላይ አይቼሃለሁ:: አውቄ ሁሉ ልፈትሽህ ሥነሥርዐት አበላሽቼ ነበር:: አስጠንቅቀህ አልፈኸኛል......ትዝ ይልሃል?......አታውቀኝም እንጂ ምናልባት ንፋስ መውጫም አውቅህ ይሆናል......"

"ንፋስ መውጫ? እሱ እንኳን አይመስለኝም:: እዛ የማላውቀው ሰው አልነበረም:: ሳልወለድ ኖረህ ይሆናል:: ማስጠንቀቅ ምናምን ያልከውንም እንኳ አላስታውስም:: ትረብሸኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል......"

"እሃሃ......ሃ......ወንድሜ:: ታስቀምጥልኛለህ?"

ግራ ተጋባሁ::

መጠራጠሬን ዓይቶ: "ተወው:: አትችልም:: ለምን እንደሆነ ታውቃለህ?"

"ምነው ዘባረቅህ? መጀመሪያ 'እንካ' ቀጥለህ 'ተወው'......"

"ጭቃ አይተሃል:: ዕንቁ ማየት መጀመርህ ነው:: ሰንቁው ወደ ጭቃ ሲለወጥ ፈልገኝ:: ቢያንስ አንድ ዙር ጭቃና ዕንቁ ማለፍ አለብህ:: ገባህ? የአገራችን ፈላስፎች ምን ይሉታል? 'መብሰል?'......ይቅርታ ለመሳደብ አይደለም"

"ልክ ነህ:: ብዙ የማላውቀው ነገር አለ......"



@BOOKALEM

"በጣም አመሰግንሃለሁ:: አያድርገውና ከሚስትህ ብትለያዩ ከሁሉ ቀድሜ ደጃፍህ የምቆመው እኔ ነኝ"

አጉንብሶ ጠቅልሎ የጨ ( ውን ጫማ ቀረጢቱ ውስጥ ከተተ:: ቀና ብሎ አየኝና......

"ለሲጃራ በጥስ እስኪ......

"ዱርዬ ብትሆንም አርጅተሃል......የዚህ ዐይነት አማርኛ ምን ለመፍጠር ነው?"

"ሳንቲም እሺ"

ከሱሪዬ የጭን ኪስ ያገኘ ሁትን በሙሉ አወጣሁና ሰጠሁት:: ሳይቆጥር በእፍኙ ያዘና ኪሴን አየ::

"ያለህን በሙሉ?"

"እንዴት አወቅህ?"

"ሳንቲም ኪስ ውስጥ ሲከተት ጨርቅ ላይ ቅርፅ ይተዋል:: ቅርፆቹ የሉም"

"በዕውነት ፖሊስ ነበርክ"

"አመሰግናለሁ......ልሂድ" ሳንቲም ያልያዘበት እጁን ሊጨብጠኝ ዘረጋ::

"ለምን በላይ ተመረጠ ለዚህ ዐይነት ጫማ?"

"አጋጣሚ:: አንተን ፖሊስ እኔን ሰቃይ ያደረገኝ አጋጣሚ:: አጋጣሚውን አሳክተህ ሥራ"

"ፖሊስ የሆንኩት ፈልጌ ነው"

"ስንተዋወቅ......"

ሳቀ:: 'ጥርሱ እንዴት እንዲህ ነጣ?' እያልኩ ሳስብ አቋረጠኝ::

"ሰው ሳትበድል ጭቃውንም ዕንቁውንም ኑር:: አጋጣሚም ይሁን መርጠህም......እ?"

ባርኔጣዬን አጣጥፌ ቀበቶዬና ሱሪዬ መሐል ከተትኩት::

"ለባለቤትህ ሠላም በልልኝ"

"የንፋስ መውጫ ያ ዘመዶቼ ደህና ናቸው?"

"አንድ ቀን ብቅ ይሉልሃል......በሙሉ ደህና ናቸው:: ኤልያስ ሱዳን ተሰዶ ሞቷል ይባላል:: ዕርግጠኛው አይታወቅም:: ያቺ ልጁ አድጋ ትልቅ ሆናለች......"



@BOOKALEM

"ምን? የምን ልጅ?"

"አላውቅም እንዳትለኝ!"

"የምን ልጅ? "

"ፀሐይ የምትባል ልጅ ታውቃለህ? እ"

ብልጭ አለልኝ።

"የአቶ እንግዳ ዲቃላ ናት የተባለችው......"

ወሎዬው ከት ብሎ ሳቀ። ራሱን በቀስታ ነቅንቀና የሆነ ነገር ተናገረ። አልሰማሁትም።

"በል ደህና እንተያይ......ከሆነ ከሆነ ከዕንቁህ በሁዋላ......በዘመነ ጭቃ......ከክረምን መቼ ይቀራል። አይቀርም"

ዞር ብሎ መሔድ ጀመረ። ከማጅራቱ ሽብቷል። በረኸኛም ቁመናው እየተመዘዘ ወደ ቸርችል ጎዳና አቀና። በዝምታ ሳየው ቆየሁ። በጥንካሬ የሚረግጡ ባቶች ነበሩት። የሚያረጅ አይመስልም። ለአፍታ እንኳን ዞር ብሎ አላየኝም። እንዲያየኝና ለመጨረሻ እንድሰናበተው ፈልጌ ነበር። ከኢትዮጵያ ሆቴል ጀርባ የሚወጣ መኪና ጋረደው። አስገራሚ ድምፅ ሰማሁ። የማውቀው የቆየ ድምፅ። እንደው እንደው እንጀት የምትበላ ድምፅ። አንጀት የምትበላ ፉጨት። መጀመሪያ ከየት አቅጣጫ እንደ መጣች ለማየት እንደ ቆቅ ነቃሁ። እንደዚህ ቆቅቼ አላውቅም። ዙሪያዬን ሰው አልነበረም። ከጀርባዬ ያለው ግቢ ውስጥ ቀድሞ ያየሁዋቸው ግን ያላስተዋልኳቸው ሰው የሚኖርባቸው የማይመስሉ ቤቶች ነበሩ። የከበቧቸው ዛፎች የሚጥሉት ቅዝቃዜ ፊኛ ድረስ ይሰማል። ወደ ላይ ወሎዬው ወደሄደበት ቀና ብዬ አየሁ። ከኢትዮጵያ ሆቴል የሚወጣው መለስተኛ የጭነት መኪና ጅናው ከሆቴሉ የጀርባ በር ወጥቶ እንዳለቀ በተገለጠው እግረኛ ምንገድ ላይ ወሎዬውን አየሁት። ደነገጥኩ። ወሎዬው ወደ ሁዋላዬ ዞር ብሎ አየኝ። ያፏጫል። ከባድ ከንፈሮቹ ከቆምኩበት ከዚያ ዕርቀት እንደክንፍ አሞጥሙጠው። ሳቅ አለ። አፌን ያዝኩ......

"ዙፉን!!" ብዬ ጮኽኩ።

ዙፉን መሳቁን አላቆመም። በሚያስገርም ፍጥነት በአጠገቡ ያልፍ የነበረው የጭነት መኪና ላይ ከሁዋላ ዘሎ ወጣ። ግራና ቀኝ ምንገድ አይቼ በሱ አቅጣጫ ልደርስበት ሩጫ ጀመርኩ። መኪናው ወደ ቀኝ ወደ ኢትዮጵያ ሆቴል መግቢያ ተጠመዘዘ።



@BOOKALEM

እየሮጥኩ እያለሁ ቂልነቴ ገባኝ:: ለምን እንደምሮጥ ራሴን ጠየቅሁ:: ወሉዬው ራሱ ቢፈልግ እንጢቆ መሆኑን ይነግረኝ አልነበር:: ወሉዬው ቢፈልግ ራሱ ንጉሜ መሆኑን ይነግረኝ አልነበር:: በፈለገ ጊዜ የሚመጣ:: በፈለገ ጊዜ የሚሄድ:: ሩጫዬን አቁሜ በቀስታ እየተራመድኩ ወደ ብሔራዊ ቲያትር ስሻገር ወደ ቀኝ አየሁ:: የጭነት መኪናው ዙፋንን እንዳዘለ የለም:: እጅግ ቅር አለኝ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ረዥም ጎበጥ ያለ ጥቁር ጠይም ሰው ሳይ፣ አናቱን ሸበት የመታው፡ አንጀቴ ለሰኮንዶች በታውን ይለቃል:: አልጋዬ ላይ በጀርባዬ ተኝቼ የገኒን የእንቅልፍ ትንፋሽ ሳዳምጥ ፍርሃት ፍርሃት ይለኝና የተጠጋኝ ወይ ያቀፈኝ እጇን ፈልጌ እይዛለሁ:: በፍርሃት......ለማንም በማልናገረው ፍርሃት ወሉዬው ዐይኖቹን ሳያራግብ የተነበየልኝን የጭቃ ዘመን እጠብቃለሁ::

*(ይሄ ምዕራፍ በ1984 ዓም የተጨመረ ነው)*



@BOOKALEM

# የፍቅር ቋንቋ ስሰማድ ስያውቅም

ገነት የምትጠራኝ በእነዚህ ነጋሪት ባልተጎሰመባቸው ስሞች ነበር::

መዝገቡዬ

መዝሚሽ

መዝገብዬ

መዚ

መዙ

እነዚህ አምስቱ በአደባባይና በከፊል አደባባይ (ወዳጆቼ ባሉበት፣ አባቷ ባሉበት፣ የእናቷ ፎቶግራፍ ከተሰቀለበት ሊስቱ በዳዱ ዐይኖቻቸው እያዩን) የምጠራባቸው ናቸው:: ሊላው ፈተና የሆነብኝ ስም "መገር" ነው:: "መገር" ትለኛለች:: ከቁልምጫ የሚሰፋ ነገር ነው:: እስከዛሬ ልፈታው ያልቻልኩት ቅኔ ነው:: ወይም ይመስለኛል:: "መገር" ስትለኝ የምሰማት በግላችን ሜዳ ላይ በፍቅር ጉግስ አልቦን:: ላቦታችን ከአዲስአባ በስተምዕራብ ረፒ ኮረብታ ላይ ዳመና ሰርቶ:: አንሶላ ዙሪያችንን ተተብትቦ የረጠበ ደስታ ከረሜላ ስንመስል::

መገር::

አንዳንዴ መዝገር ልትል ይመስለኛል::

ተጣብቄ አልለቅ ስላት? ቆዳዬ ከቆዳዋ ሲላቀቅ እንደ ብላስቴር ሲጮህ?

ወይስ ምንድን ነበር?



@BOOKALEM

# ቀስበት ባሰርን በዉሬ

አንዳንድ ሰው አለመርሳትን ዕውቀት ሳይሆን ብልሐት ያደርገዋል:: አንዳንድ ሰው ጥፋቱን በሌላ ሰው ለክኮ ሊሰወር ይፈልጋል:: አንዳንዱም ጥፋተኛ ነኝ ብሎ አምኖ ባልተጠበቀ ወቅት መልሶ ይሰራውና በብልጦች መዝገብ ሊገባ ይፈልጋል:: የበኩሬ ጓደኛ ገነትን ያጣው እኔ በመሐል መግባቴ ሳይሆን ከመጀመሪያውኑ ስላልወደደችው ነበር:: ስለ ሴቶች ብዙ ባላውቅም ካጋጠሙኝ፣ ካወራሁዋቸው ጥቂት ሴቶች ከፉና ሴረኛ መስለው የታዩኝ አልነበሩም:: ምናልባት እነዚህ ጥቂት ሴቶች ግምቴን ማቆሚያ በቂ መሰረት ሳይሆኑ ይችላሉ::

ጓደኞቼን ለሽምግልና ይገፍአቸው በምሄድበት ወቅት እዛው መዋላችንን በተረዱ በተዘራ/በኩረ በተቀጠሩ ሰላይ ጎረቤቶች ተነግሮት ማታ ሌሊት የቤቴን በር አንኳኩቼ ስገባ ሳይተኛ ጠብቆ በኩረ ሽሙጡን ጀመረኝ::

ማንም ሰው 'ትዕግስት' የሚባል ነገር በውስጡ አለ:: ግን ደረጃው ይለያያል:: አንዳንዱ ትንሽ አለችው:: አንዳንዱ ብዙ አለው:: አንዳንዱ ትዕግስት ቢኖረውም ባይኖረውም ቸልተኛ ነው:: የሚሆነውን ነገር ሁሉ ይቀበላል:: ቢሰማም ባይሰማም ይቀበላል:: የአንዳንድ ሰዎች ሕይወትና የአኗኗር ጓዳና ብዙ ትዕግስትና ቸልተኝነት ያላቸውን ሰዎች የመጠቀምና በእነሱ እንዳሻቸው መጫወት ነው:: ቸልተኞችም ይሁኑ ትዕግስተኞች የአእምሮ ጉድለት የለባቸውም:: ስህተቱ የባሕርይ ነው:: የማሰብ አይደለም:: ባሕርይ ደ'ሞ ከአስተዳደግ፣ ሰዎች ካሳለፉት የሕይወት ዐይነት የሚመጣ ነው:: ቀድሞ ነፍስ ካወቅሁ ጀምሮ የመኖርና ያለመኖር ትርጉም አይገባኝም ነበር:: ትርጉሙ ቢገባኝም ልዩነቱ አይታየኝም ነበር:: አንድ አጋጣሚ ግን......አንድ በጣም ያልተጠበቀ ዕለት ግን ገነት ከምትባል ልጅ ጋር ተገናኝቼ ድንቅ ድንቅ የሚል የሕይወት ኩሬ ውስጥ ከእሷ ጋር አብሬ እየዋኘሁ ነበር:: ፍቅር:: ይሄ በመኖርና በሞት መሃል ልዩነት እንዳለ አሳይቶኛል:: ስህተት ልሆን እችላለሁ:: እኔና ገነት ተፈቃቅደን ለመጋባት ማቀዳችን ግን አንዳንድ አላፊ አግዳሚዎችን እንዳበሳጨም ገብቶኛል:: ለእነሱ ሴት ሴት ነው:: ለእኔ ገነት ሰንሰለቴን የፈታች ነበረች:: እሷን ካወቅሁዋት ጀምሮ መነጋገር ጀምሬአለሁ:: ቸልተኛነቴ እየፈራረሰ ከሕይወቴ ትርጉም እያገኘሁ ሔጃለሁ:: እንዲህ እንደ ገነት ያለች ሴት በእንደ እኔ ዐይነት ሰው ላይ ማሳደር የምትችለው ተፅዕኖና፣ የምትፈጥረውን ለውጥ የተገነዘቡ ብዙ አልነበሩም:: በዚህም እያንዳንዱ ሰው ከወርቅ የተሰራ መስሎኛል:: ሁሉንም በጅምላ ቅያሜ ደርቤ አልርቃቸውም:: ስራመድ በውስጤ አየር የሚያልፍ ይመስለኛል......ፍርግርግ እንደሆንኩ ሁሉ:: ሳንባዬ በደስታ ንፋስ ተወጥሮ ትልቅ በጣም ትልቅ የሆነ ይመስለኛል......ታዲያ አንዳንዱ ይሔን



@BOOKALEM

ፍርግርግ ሊያፈርስ ይሔን ሳንባ ሊሸነቁር ይፈልጋል:: ቤት ስገባ በኩረ ምን እያወራ እንደነበረ አላውቅም ከእነ አለማየሁ ጋር እየተጨቃጨቀ ደረስኩ::

"ሠላም" ብዬ ገባሁ::

በኩረ ግራ መሐል ጣቴን በጉሪጥ ዐየና: "ስማ አለማየሁ ያ ቂል ዘካርያስ......መምሪያ ያለው፣ ሚስት ካላገባሁ እያለ ሲንደላቀቅ......ትታው ሔደች"

"የቱ ዘካርያስ?......"

"በል ተወው......የሆነ ወርቅ ነው ብሎ የሆነ ቦንዳ ቀለበት ሰክቶ ይዞር የነበረ"

"ታዲያ አገባ አደል"

"እሱ! ሳጣ ጠብቂኗን ይሆናል ያገባው"

በፀጥታ ኩቴን አውልቄ አዲስ የተገዛ ወንበር ላይ አስቀመጥኩ:: ወንበሩን ማን እንደገዛው አላውቅም......ግን ኩቴን አስቀመጥኩ:: በኩረ ጮኸ::

"ጊድ......ወንበሩን ልቀመጥበት ስለሆነ ኩትህን ብታነሳ" አለኝ

"በመጀመሪያ ጓድ አይደለሁም:: ሁለተኛ ብትቀመጥበት ምናለበት:: ተቀመጥ ግድ የለም ኩቱ ቢበላሽ" አልኩ

"ለምን ኩትህ ይበላሻል? ገነት የተጨማደደ ኩት አትወድም" አለኝ

"እሷን ምን አመጣት እዚህ?" አልኩት::

"ዘመዴ እኮ ናት" አለ::

"ኸረ" አልኩ ውሸቴን እንደተገረመ::

"ምነው ክፉ ክፉ እናገረህ?" አለኝ

"አፍህን ዝጋው" አልኩትና ኩቴን አነሳሁ::

"ስማ......ጊድ ማንም የሚጮህብኝ ሰው አይደለሁም" አለ

ዞር ብዬ እሱንም ሳላይ ወንበሩ ላይ በአንድ እግሬ ቆምኩና መደገፊያውን ገጠልኩት::

"ምን መሆንህ......ምናባቱን" አለና በኩረ ከሚንጉራደድበት ወደ እኔ መጣ::

ጃፓንና አለማየሁ ከተቀመጡበት ተነሱ:: ወንበሩን አንስቼ ወደ ውጭ ለመወርወር ሳነሳው በኩረ ከሁዋላዬ መጣ:: ወንበሩን እንዳለ ወደ ሁዋላ አዞርኩት:: የወንበሩ እግር ጆሮ ግንዱን መታው:: ወንበሩን ወደ እነአለማየሁ ወርውሬ ጆሮውን ይዞ



@BOOKALEM

የሚያቃስተውን በኩሪ በእርግጫ እግሮቹ መሐል መታኩት። ወደቀ። አለማየሁና ጃንጋ ተተረማምሰው ከወደቁበት ተነስተው እየጐተቱ ወደ ክፍሉ ሌላ ጥግ ወሰዱኝ። አልጮህም:: አልናገርም:: ገላዬ ባለበት፣ በሙቀትና ከውስጥ በሚነሳ አውሬአዊ ጉልበት ተበታትኖ የሚሔድ መስሉኝ ነበር:: እቆምኩበት እቁነጠነጣለሁ:: ላቤ በሰራ አከላቴ ይንገዋቀዋቃል:: የጃንጋንና የአለማየሁ ጩኸት ብዙ አይሰማኝም። ዐይኖቼ ከበኩሪ ላይ አልተነሱም:: እየዋለሁ:: በስላችም አይደል:: አምሮል በመመልከቻ ኪንትም አይደል። ጎዳና ላይ ሲንሳፈፉ በሚውሉ የታዘዙ ዐይኖችም አይደል:: በከረሩ፣ ጥርስ ባወጡ ብሌኖች ነበር:: ቅኔ የለኝም:: ቀጥታ ነው:: አምሮል እያየሁ አይደለም፣ ንፋስ መውጫን እየጣልኩ ነው:: በደም ስሮቼ የሚሮጠው እንደ እሳት የቀጠነ ደም ነበር:: ሽፋሽፍቶቼ እንደ ሲሚንቶ ከረዋል:: የበኩሪን ቦግ ያለ ጨለማ ፊት በቅንድቦቼ እየቀደድኩት ነበር። ማእከሉን እየተጋፋሁ:: አውቃለሁ ለመሞት ወይም ለመኖር እየለፋሁ እንደሆን:: ልብወለዴን ሳይሆን እውነቴን ለመኖር በቁጣ ቆሜአለሁ:: ጆሮውና አንገቱ እየደማ፣ እተጋደመበት እየተንፈራፈረ ሲያቃስት......ይኼ ሲያሳድደኝ የነበረው ዓለም እጅግ ደካማና የሌሎችን ሰዎች ሕይወት እየመጠጠ፣ እየቀማ የሚኖር የኮሶ ትል መሆኑን ስረዳ......የራሴ የቀድሞ ቸልተኛነቴ......የተድሞ ትዕግስቴ አስጠላኝ......በኩሪ አስጠላኝ......የኮሶ ትሉ አስጠላኝ......ከአንጀቶቼ ወጥቶ አቧራ ላይ ሲንከባለል......ያውም በተራ የጥፊ እንቆቆ::

ኩሶው ይጮኽ ነበር......

ኩቴን ከወደቀበት አንስቼ ወጣሁ:: ቤታችን አካባቢ የበኩሪ ጩኸት የጠራቸው የመንደር ሰዎች መሰብሰብ ጀምረዋል:: የወንበሩ መደገፊያ እውጭ ጭቃ ላይ ነው:: ረግጬው ሳልፍ ወደ ውስጥ ስቦ መልሶ ወደ አየር ያወናጨፈኝ መሰለኝ:: ገላዬን ቀሎኛል:: ሰውነቴ ሁሉ የእኔ ነበር:: ሰውነቴን የሚያዘው አልነበረም::

ገነት ዘንድ ሔጄ ሱቋ ውስጥ እቀመጣለሁ::

እግሮቿን ከወደ ሁዋላ እያየሁ......ትኩስ የእርካታ ሻይ እጠጣለሁ:: ከዚያች ጠባብ ቤት ሳቋ በስሎ እንደገነፈለ አጥሚት መርካቶ ላይ ይከነበላል......

# ዕብነ በረድ

ደንግጬ ተነሳሁ:: ለምን ደንግጬ ተነሳሁ? ስለምን በድንጋጤ ፀሐይ ከምሞቅበት ኩርሲዬ ተነስቼ ቆምኩ? ስለምን ቀኝ እግሬ ስር ገኒ አስቀምጣልኝ የሔደችውን ሻይ ስደናበር ደፍቼ ዐይኖቼን በልጥጬ ውስጥ እግሮቼን ኩረኩንች እየጊጉጠኝ ተቀሰርኩ?

አንዳንድ ጉዳይ ትዝ ሲል፣ አንዳንድ ጉዳይ ሲታወስ፣ አንዳንድ በሕሊናችን ደን የጊዜ ጨለማ ለብሶ እንደ ጥቁር ሞት እየተነፈሰ የተሰወረውን ......የተጋረደበትን ቅጠል፣ ጨፈና ቀርከሃ ገፎ ችላ ያለ፣ የዘነጋ አእምሮዬ ሲያገኘው ምን ላድርግ? ጉንበስ ብዬ መሬቱን አየሁ:: ሻይው ትንሽ የሚፋጅ ቀበና ሆኖ በደረቀው መሬት እስኪዋጥ አቧራና የኮቸረ ሳር የሚንሳፈፍበት የሚጨስ ደቂቅ ኩሬ ሆኖአል:: የእግሮቼ ጣቶች ጥፍሮቻቸውን መቆረጥ ነበረባቸው?......ይሆን እንዴ? ትውስታዬ ይሆን እንዴ? ትውስታው ራሱን በየዋህነት ከፍቶ አላስደነገጠኝም:: የሆነው እንዲህ ነበር......

አንድ ለለት በትንሿ ግቢያችን ቆመን ከሚስቴ ከልጄና ከባልንጀሮቼ ጋር ፎቶ ስንነሳ የካሜራ ዐይን ላይ እንዳተኮርኩ በቀኝ ዐይኔ ቂጥ አንድ ድንጋይ ሲወድቅ አየሁ:: በቸልታ ነበር ያየሁት:: የቤተሰቤ ነገር ጠምዶኝ::......ምናልባት ማየቴ በግንዛቤ ያልታሰረ......በላላ ቸልታ የተዋጠ ነበር::

"የሰፈራችሁ ሕፃናት ድንጋይ እየወረወሩ ሊጨርሱን ነው?" ብሎ ሙስጠፋ ያላሳቀን ቀልድ ተናገረ:: ሆሆሆሆ አልን፣ ጊደኞችን ነውና እንዳጋጠመን እሱን ላለማሳፈር ለብለብ ሳቅን::

ታዲያ ተቀምጬ ሻይ ስጠጣ ከቤታችን ቆርቆሮ ላይ የሚወርደው ዝናብ መሬት እየፎገለ ከምድር ውስጥ ለተመልካች ዐይኖች ጠጠሮችን ከተሰነቀሩበት መሬት ፎግሎ እራቁታቸውን እያባበለ ሲያወጣቸው......ሉፍና ሽንብራ ሆነው:: ኑግም ሆነው:: አቾሎኒ መስለው:: ሠልፋቸውንና ትርምሳቸውን ሳጤን......ከነዚህም ትርምስ አፈንግጠው የወጡ ጠጠሮች ላይ......ከአንዱ ላይ ወይም ከሁለቱም ላይ ወይም ብዙዎች ላይ......የሻዬን ብርጭቆ ሳስቀምጥ ቂጡን ሽቅብ ገፍተው ተዳፋት ሰርተው በጉን እንዳይፈነግሉብኝ ሳስተካክል......በቀኙ ሀይኔ ቂጥ ነጭ ድንጋይ አየሁ......ይህቺ የጨረፍታ ትዕይንት በሕሊናዬ ደብቄው የምኖረውን አንድ አስደንጋጭ ልምድ ከገባበት ጨለማ እየጉተተች አወጣችው:: ነገሩ የአንጉሌን ግድግዳ ፍቆ በራሱ የድኘ ቆብ መኖሩን እንደሚያሳይ የከብሪት ዘንግ ያደርገዋል:: ብዙ ሳይቆይ አናቴ መንደድ ጀመረ:: ይመስለኛል ከተላጨው አናቴ ላይ ፍም እንደሚበቅል ጉም እንደሚነሳ::

እንዴት ይሆናል? እንዴት አምናለሁ? እንዴት ይኼን ለውነት ብሎ ሰውስ ያምነዋል? የሰማ ሰው የተገረመ ዐይኖቼ ላይ እየጮኸ "ቀጣፊ!" ቢለኝ ይፈረድበታል?



@BOOKALEM

ኀና ነጯን ድንጋይ እጠግቤ ከተደፋው የሻይ ሻሳ በዐይኔ ቂጥ ስመለከታት አእምሮዬ ዘንግቼው ወደ ነበረ ዓለም ተከፈተ......

ወሉዬውን ከቶ አምኜው እንዳልነበረ፣ እንደ ቶማስ «የጌታዬን የቆሰለ ቀዳዳ ካልነካሁ አላምንም» እንደሚል፣ ተልካሻ ገጠመኞች በሕይወቴ የጭቃ ጉዳና......በቆሰለ እርሳስ የትውስታ ብራናዬ ላይ ክትባት ሰርተው አልፈው......እንደ ባትሪ እናት ቦግ ያለ ጠባሳ......

ሕፃኑ ያለቅሳል። የግነነ እዬዬው በጀርባ በር እንደ እሳት ምገድ ይወጣል። ልማዴ ዘሎ መግባትና ድቡልቡል ለስላሳነቱን ያልሰለጡ ክንዶቼ ላይ አጋድሜ የፊቱን ግማሽ በከፈተው ክብ ቀዳዳ እሽሩሩ ማንቆርቆር ነበር። ገነት ጨጨብሳ የበላንባቸውን ሰቃዎች ታጥባለች። ኢኢታ እሰማለሁ። ልማዴ አልሳበኝም። የልጁ እሪታ መግነጢስነቱ ጠፍቶአል።

በባዶ እግሮቼ ፎቶ ወደተነሳንበት ቦታ ሔድኩ። ስነሳ ቆሜ የነበርኩበትን ቦታ ፈለግሁ። ቦታዬን ለማግኘት ፎቶግራፉ እንሺው የቆመበት ሰፍራና የዚያንን ቀን እንፃሮች አጠናሁ። ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ቆሜ የነበረበትን ቦታ አገኘሁት። ዐይኖቼን ወደ ቀኝ ጣልኩና መሬት መማተር ጀመርኩ።

እንክብካቤ ያጠረው ጓሮ ነው። ሁሉን ነገር ለተፈጥሮ የተውንላት ይመስላል። ረዥም በጋ፣ አጭር ክረምት አረንዛማ መሬት......የሣሩ ነገር ጨቅላ እናት ላይ እንደበቀለ ፀጉር ነበር። ላሽ የመታው ጓሮ። አጥሩ ጥግ ዙሪያውን በአንድ ሜትር ስፋት የበቆሎ ተከሎች፣ መስከረም ሲገባ ጠርጥረን የበላንላቸው የደረቁ የባቄላ ተክሎች፣ ሽልጦ መጋገሪያ በየጊዜው የምንመለምላቸው የሴት አኩሪዎችና ቀጥ ብለው የበቀሉ ሦስት ለጋ የዕድ ባፎች አሉበት። በሙሉ እኔ የተከልኳቸው ነበሩ። ገበሬነት ክልጂም ይሰባል ሆኖ እንደሆነ......በእያቴ።

ጠዋት ጠዋት በግራ በኩል በካናቴራ ሆኜ ጀርባዬን ለፀሐይ ሰጥቼ የልጅነት ሱሪን በግልብጥ እወጣለሁ። ማታ በስተቀኝ በኩል በሰው ቂጥ (በትክክሉ በፀሐይ) የሳመ የጅማ ወንበሬን አወጣና ጀርባዬን ለምትጠልቅ ፀሐይ ሰጥቼ መፅሐፌን እነባለሁ። ባለቤቴ የጓዳው ስራ እፍታ ሲሰጣት ልጁን አቅፋ መጥታ እጠገቤ/ጎኔ ትቀመጣለች። እጇን ጭኔ ላይ ታስቀምጣለች፣ ጉንጯን እቆነጥጣታለሁ፣ ጣቶቼ ጉንጉኗ ውስጥ ይለፋሉ—ሊያኳት። የምትጠልቀው ፀሐይ ይህቺን የኔን ውድ ፊት......ግሩን......ግር ስታስመስለው፣ የቀን ውሉዬን አወራታለሁ፣ ሳቂንና መገረሚን፣ ሀዘንና መደሰቴን ሱ እላታለሁ። ሱ ሱ! ያበጠው የጡቷ ጫጠር በልጃችን ፊት ውስጥ ይጠፋል፣ ከጨቅላው ለግላጊ ከንፈሮች ግለፊያ የጠበበው ወተት ወደግይታይ እንገቱ ይፈሳል......ቀዝቃዛ



@BOOKALEM

የእንጠጠ ንፋስ ቅንድቦቻችንን ይታከካል......ያልተበላ የእራት ጠረን ከቤቴ ይሁን ከጎረቤት እንደ ሰረገላ ከንፋሱ ጀርባ እየተሳበ ይመጣል......በክረምት በክረምት ከአሸንዳ በምባ ስር ጎራዳ በርሜል እያቆምኩ የአዲስአባን ነጭ ሰማይ እመርቃለሁ፣ በንጋት መስኮት ከፍቼ ድንግዝግዝ ባለው ጎሕ ውስጥ አዲስ ሚስጢር እንደሚጠብቅ የሮሓ መነኩሴ ተስፋ ልቤ ውስጥ እንደ እጭ ሲራባ እሰማለሁ......ዞር ብዬ በከፊል የተራቆተች ሚስቴን አያለሁ......ተልባ የመሰለ ቆዳዋ ከአንሶላችን ውስጥ እንደ ትንግርት አርፎ፣ ፊቴን አንገቷ ስር ቀብሬ እንዲህ አደርግ ነበር፡ ወዟንም እተነፍሳለሁ፣ ትልልቅ ጣቶቼ የተወጠረ እርግዝናዋ ላይ የእትብቷን ቀዳዳ በደስታ ይዘጋሉ፣ ማንም ባላቆመኝ ሊሊት ታላቅ የመሰለ ተራ ነገር አንሾካሾክላታለሁ፡ ግርጌዬ በስንፍና የወረወርኳቸው ልብወለድ ድርሰት ለመፍጠር የጫጫርኩባቸው ወረቀቶች......ለአርዕስትነት የመረጥኳቸው ሁለት ቃላት ከአንዱ የወረቀት ንጣት ላይ ቦግ ያሉ ጥቁሮች ሆነው......በትልቁ በድርብርቡ «ግራጫ ቃጭሎች» የሚሉ ሆሂያት፡፡ እሱም በእግሬ ተገፍቶ መሬት ሲወድቅ እሰማዋለሁ......በቡላው ጠዋት የቤቴ አየር ውስጥ እንደ ነጭ ጭልፊት ተገላብጦ፡፡ በዚህች ፀጥተኛ ትንሽ ቤት ውድ ገነት እግሮቿን ወገቤ ዙሪያ ታስራለች......ማሕፀኗ ውስጥ ሐሩር ይነጋል......ከእንጀራ ከንፈሮቿም ቀጭን ማሕሌት ይፈሳል......

ዐይኖቼን ወደ ቀኝ ስወረውር መድረቅ የጀመሩ ሳሮች መሐል ያቺን ነጭ ድንጋይ አየሁዋት፡፡ እሷ መሆኗን ለሰከንድ አልተጠራጠርኩም ነበር፡፡ ሳያት፣ ለአፍታ ልቤ የተሰቀለበትን ስፍራ ለቆ ወደታች (አቅጣጫውን እንኳን እርግጠኛ አይደለሁም) ወረደ፡፡ በቀስታ እየተራመድኩ ሔድኩና ድንጋይዋን አነሳሁዋት፡፡ የጠዋት ብርድ ገና አለቀቃትም ነበር፡፡ ይኼ የበለጠ በቀላሉ ከድንጋይዋ ጋር የመንፈስ ግንኙነት እንድፈጥር አደረገኝ፡፡ ድሮ በልጅነቴ ከወንዝ ዳር ሳገኛት ዕርጥብ ለስላሳና ቀዝቃዛ ነበረች፡፡ ምናልባት አጋጣሚዎች ውስጥ ያለ ዝርዝር ሴራ ይሆናል፡፡ የድንጋይዋ ቀለምና ሞላላነት የትውስታው መሠረት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስፋቷ፣ ልስላሴዋ፣ የነጭነቷ ጥልቀት፣ የድንጋይዋ ዘር፣ ሙቀቷና ቅዝቃዜዋ፣ ሸካራነቷ፣ ጠፍጣፋ መሬት ላይ የትም ያላት አቀማመጥና ግርማ፣ በፀሐይና በደመና (በምትጠልቅ ፀሐይ፣ በምትወጣ ፀሐይ፣ የዝናብ ዕለት፣ በካፊያና በዶፍ) እነዚህ ለድንጋይዋ የባህርይ ጥልቀትና፣ ለራሷ የሆነ ነፃ ስም ይሰጧታል፡፡

ድንጋይዋን እጄ መሐል ስይዛት ባይተዋርነት አልተሰማኝም፡፡ በሕሊናዬ ንፋስ መውጫ ያ ወንዝ ዳር ከነጭርቴ ቆሜአለሁ፡፡ ልቤ ረጋ ያለ ተም፣ ተም ነበር፡፡ እግሮቼ ብርድ እረግሚቸው ይንቀጠቀጣሉ፡፡ ይህቺ ድንጋይ ዕባከነ በረድ ናት፡፡ የድሮዋ ነበረች እንዴ? ወይስ የወረወርኳት የአሸዋ ድንጋይ ሰማይ ደርሳ ስትመለስ በመለኮታዊ ትኩሳት ተጠብሳ ነው? ከመሐሏ ላይ ጉድጓዳ ቤኸ መስመር ነበር፡፡

ድንጋይዋን ጨብጬ ያዝኳት። ምን እንደማደርጋት አላውቅም ነበር። መዳፌ ሰምብርት ላይ የሚመች ልስላሴ፣ ክብደትና ላቤ የረበሸው ቅዝቃዜ ነበራት። ሕፃኑ ማልቀስ አቁሟል። ገነት ልጁን ይዛው ከጊዳ ወጣች። ጠርዙ ዙሪያ ሰፊ ዳንቴል የተሰራ የናይሎን ውስጥ ልብስ ብቻ ደርባለች። የአንዱን ጡት ክብደት አያለሁ.......ጫፉ ወተት የሚበትን ለስላሳ ቋጠሮ። የእፍረቷ ጥቁረት ይታየኛል። ልጅ ወልዳም ቢሆን ወገቧ የወይዘሮ አቦሸማኔ ነው። በፀጥታ እየተራመደች መጥታ አቀፈችኝ። አገጩን ሳመችና፡

"ያዘው እስኪ፣ የምሰራው አለኝ። ምነው የደነገጠ ትመስላለህ?" አለችኝ።

"ይህቺን ድንጋይ ልወረውራት ነበር......" አልኩ እጄን ከፍቼ መዳፌ መሐል ያስቀመጥኩትን ዕብነበረድ እያሳየሁዋት።

ለምን እንዲህ አልኩ? መወርወር ፈልጌአለሁ? ለምን እወረውራለሁ? ምን አናገረኝ?

ከእጄ ላይ በፍጥነት አነሳቻትና፡ "ደስ አትልም? ሰው የሰራት ትመስላለች። ለምን ትወረውራለህ?"

"በቃ......" ትከሻዬን ነቀነቅሁ። ከንፈሮቼ ይንቀጠቀጡ ነበር ልበል?

"ዙሪያውን ሰፈር አይደለም እንዴ ያለው። ሰውና ቤት ብትመታስ?"

"ማረጋገጥ የምፈልገው ነገር አለ"

"ምን? ድንጋይ መሆኗን? ሰው ሲፈነከት የተመታው እንዴት እንደሚጮህ ለመስማት?"

ሌላ ነገር ልነግራት አልፈለኩም።

"ወደ ጐን አልወረውራትም እኮ"

"ወደ ላይስ ቢሆን......ስትመለስ አናቴን ብትመታውስ?"

ከእጇ ተቀበልኩና ከእሷ ፈቀቅ አልኩ። እውስጤ የሆነ እምነት ነበር። ሕይወት ዞር ብለን ስናየው ወፈረም ቀጠነም የሆነ አስማትና ተአምር አለው። ሁሉ ክፉም ደጉም ከውስጡ የተወሰወሰ ቶሎ ራሱን ከፍቶ የማያሳይ ተአምር አለው። ድንጋይዋ ግቢዬን ለቅቃ እንዳትወጣ አድርጌ ወደ ላይ ወረወርኳት።

ወደ ሰማይ በግምት አሥር ሜትሮች ያህል እንደተነሳች እኔና ገነት እንጋጠን እያየናት.......ጠፋች።



@BOOKALEM

"ውይ......." አለች ገነት ወደ እኔ በድንጋጤ አይታ:: ከዚያ ያኔውኑ ጆሮዋን አቁማ ድንጋይዋ ስትወድቅ ለመስማት ሞከረች:: ዐይኖቿ አተኩሩ፣ አንገቷ ተቀሰረ:: ድንጋይዋ አልተመለሰችም::

ፈገግ እያልኩ ገኒን አያታለሁ:: ቀና ብላ በፈጠጡ አይኖቿ አየችኝ::

"ይመጣል......ዛሬ አይደለም ግን" አልኳት::

"ዕውነት ነው ተሰወረ?......ወይስ ዐይኔ ነው?"

"ይመለሳል ግን ቆይቶ ነው:: ድንጋዩ ሲመለስ የሚመጣም ዕንግዳ ተአምረኛ ሰው ይኖራል......."

"እንዴት? የምን ሰው?"

"ሰው:: ተአምር ነዋ"

"አስማተኛ ነህ ምንድነህ?"

"ዐይን የለንም እንጂ ዙሪያችን አስማት ነው......ይኼ ቆንጆ ሕፃን በአስማት የመጣ አይመስልም?"

ልጁን ሳም አደረገችውና: "ይገርማል:: ወይስ አልጣልከውም:: ስትሸውደኝ ነው"

"ወደ ላይ ስትወጣ አይተሻታል አይደለም?"

ልጁን አቀበለችኝ:: ወደ ማድቤት ስትሔድ ነጭ የናይሎን ውስጥ ልብሷ እላይዋ ላይ እንደ ወተትማ ንፋስ ነው......

"ማን ሰራሽ እንዲህ አሳምሮ?" አልኳት እንድትሰማኝ ድምፄን ከፍ አድርጌ::

ፊቷን ቆቻ ዞር አድርጋ ምላሷን ለኩሸት አወጣችብኝ:: የድንጋዩን ነገር የረሳችው መሰለኝ::

ድንጋይዋን እጠብቃለሁ......የድሮ ድንጋዬን የዚያችን ቀን ዕብነ በረዴን::

ወይ ጭቃ ወይ ዕንቁ ሆና እስክትወርድ......



@BOOKALEM

## ጥበቃ ወይም ታሳቂ ፎቶ (ያቺ ቡችላ ጅራቷን በመያዝ እንዴት ተሯሯጣለች?)

ፊት ለፊት ገነት የዕርጉዝ ቀሚስ ለብሳ በሁለቱም እጆቿ ትልቅ ሆዷን አቅፋ ተቀምጣለች:: ቀሚሷ ረዥም፣ ሠፊና ባለ አበባ ነው:: ጭንቅላቷን ትንሽ ዘንበል አድርጋለች:: ጥርሶቿን ሳታሳይ እንደ ሰንቡጥ ትስቃለች:: የአንገቷ ቅላት የብርሐን ችቦ ይመስላል:: ከጀርባዋ እኔ ቆሜአለሁ:: ሁለቱንም እጆቼን ግራና ቀኝ ትከሻዋ ላይ አስቀምጬ:: ፀጉሬ ጐፍሮአል:: ምን እንዳሳቀኝ አሁን ትዝ አይለኝም እንጂ እቆምኩበት በሳቅ ፈርሻለሁ:: ከእኔ በስተግራ አለማየሁ ቀኝ እጁን እኔ ትከሻ ላይ አድርጐ በግራ እጁ በሚሪንዳ (እርማው ይታያል) መጠጥ እስከ ወገቡ የተሞላ ጠርሙስ ወደ ላይ አንስቶአል:: ሁለቱም የነጭ ሸሚዙ እጅታዎች ተጠቅልለዋል:: በስተቀኝ ጃፓን የፀሐይ መነጽር አድርጐ ክብ ፊቱ በሳቅ የበለጠ ተድቦልቡሏ:: ነጋሳ የተሳጨው የአናቱ መላጣ ገና አላደገም:: አፉን ለትልቅ ሳቅ ከፍቷል:: ባለሰንበር ካናቴራ ለብሷል:: ገነት እግር ስር የነጋሳ ትንሽ እህት ለመሳቅ ፈልጋ በማፈሯ ነው መሰል አፏን በግራ እጇ ሸፍና አንገቷን ሰብራለች:: ከእሷም ጐን ከገነት ግራ እግር ስር የነጋሳ እህት የምታሳድጋት ትንሽ ቡችላ የራሷን ጅራት ለመያዝ ትሽከረከራለች:: የፎቶው መደብ ግራጫ ነው:: ከገነትና ከአለማየሁ ፊት በስተቀር የተቀረነው ከመደቡ ጥቁርነት በቀስታ እየተሳብን የምንወጣ ይመስላል:: ጠይምነታችን ይሆናል:: ቡችላዋ ጅራቷን ለመያዝ በጣም እንደምትሯሯጥ ያስታውቃል:: ምናልባት ሁላችንን ያሳቀን የእሷ ድርጊት ይሆናል:: ለንስቅ ግን ውሻዋን አናይም:: ጃፓንን፣ ሚስቴን፣ የነጋሳ እህትንና እኔን ያሳቀን የተለያየ ጉዳይ ይሆናል:: ገነትን ያሳቃት ምናልባት እርግዝናዋ በፎቶ መቀረፁ ይሆናል:: እኔን ያሳቀኝ ፎቶግራፍ ያነሳን ሙስጠፋ ሽንቴ ወጥሮኛል እያለን እያማረረ ስላነሳን ይሆናል:: ጃፓንን ያሳቀው ነገር ለራሱም ግልጥ አልሆነለት ይሆናል:: አለማየሁን ያሳቀው የነጋሳ እህት መሬት ላይ አቀማመጧ ይሆናል:: የነጋሳ እህትን ያሳቃት ለራሷ የቀዳችውን ፋንታ አለማየሁ እየቀለደ ስለነጠቃት ይሆናል::

ከዚህ ሌላ የፎቶ ግራፉን ጠርዝ ሰብሮ ወደ ጭንቅላታችን የሚወርደውን ጉም ማናችንም አላየነውም:: ከሰፈር ማድ ቤት የመጣ ጪስ ይሁን ወይ እዚያ አካባቢ ከግቢው ውጭ ሕገ-ወጥ የሆነ ነገር እየተቀጣጠለ እንደነበረ አላውቅም:: ትዝ አይለኝም:: ፎቶውን ከብዙ ጊዜ በሁዋላ ስላየሁት ይሆናል:: ለገነት ጠርቼ ልነግራት ፈለግሁ:: መኝታ ቤት ልጇን ስለምትመግብ ልረብሻት አልፈለኩም::

ገነት ልጁን ለማጫወት ባቷን ስታጮህ እሰማለሁ::



@BOOKALEM

ምናልባት ውሻዋ ያን ጊዜ ጅራቷን ለመንከስ ታባርር የነበረው ምናልባት ጣቱን እያሾኸ ለጨዋታ፣ ለኩሸት፣ ለተንኮል ይኩረኩራት የነበረ ሰው ይኖራል (ምናልባት ጃፓን):: ፎቶው ላይ የእኔ እጆቼ ይታያሉ:: የሁላችንም እጆች ይታያሉ:: ከፎቶው ላይ ድንጋዩ ወድቆ የነበረበትን ቦታ ለማግኘት ትንሽ ባርኩ:: ሙስጠፋ ሲያነሳን ዕብነ በረዱ የወደቀበትን ቦታ አላስገባውም:: ጠረጴዛ ላይ ጥዬ ራቅ አድርጌ ሳየው ፎቶው ተራ ነበር:: እየሳቅን የተሰለፍን ሰዎች ነን:: ብዙ ሰዎች ፎቶ ሲነሱ እየሳቁ ይሰለፋሉ:: ወይም ተሰልፈው ይስቃሉ::

ጉሙ:: ጉሙ:: ጉሙ:: ምናልባት ሙስጠፋ ሲያሳጥብ አበላሽቶት ይሆን? ምናልባት ከማንኛውም ሕግ ውጪ የሆነ የማናየውና የማይገባን ጉድ ፎቶው ላይ ተቀርፆ ይሆናል::

• ፎቶው ሞልቷል::

ፎቶው ተወጥሯል::

ፎቶው አብጧል::

ፎቶው ሊፈነዳ ይቅበጠበጣል::

ይሔ ፎቶ ታላቅ ነው::

ተፈፀመ::

—— // ——



@BOOKALEM

# ሕፅን ማስታዎሻዎች/ወሽመጦች

## (1) የሱሱልታ ሴት፡

የፖሊስ ኮርሴን ስጨርስ ዕጣዩ አዲስአባ ጣለኝ፡፡ ለአዲስአባ ያልጎመዠ ወጣት አልነበረም፡፡ አንዱ ሲመቸው፣ አንዱ ዘመድ ስላለው፣ ለብዙ ብዙ ዐይነት ምክንያት፡፡ እኔ ደሞ አዲስአባን ሳውቃት፡፡

ደመወዛችን በነጠላ ኪራይ ክፍለን ሲያኖረን ስለማይችል ከነአለማየሁ ጋር ስዳበል የመጀመሪያው ዕለት ማታ «እንግዳ ማሳመጃ» ብለው በራሳቸው ወጪ ጫልቱ ቤት ራት ጋበዙኝ፡፡ ገና ስገባ ምን አየሁ? ገና ስገባ ጫልቱን አየሁ፡፡ ገና ስገባ ምንስ አሸተትኩ? ገና ስገባ የወይራ ጢስና ድፍድፍ ሸተተኝ......ወደ ውስጥ በገባሁ ቁጥር ግን በየደረጃው ቃተኛ (ያለ አንድ ቀን እንኳን ያላበላችን)፣ ክክ ወጥ፣ ጎመን ወጥ፣ ሽሮ ወጥ፣ በርበሬ......

ምን ሰማህ?

ያበበች ደራራን ዘፈን፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ጫልቱ ቤት ውስጥ የምሰማው ከር የአበበች ደራራን ነው፡፡

ዘፈኑ ምን ይባላል?

ዘፈኑ *የሰባል ነሽ* የተባለ ነው፡፡ «*የሰባል ነሽ ያባብላል ቁንጅናሽ*» ይላል የዘፈኑ የመጀመሪያ ግጥም የመጀመሪያው መስመር፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጫልቱ የሰባሌ ልጅ ትመስለኛለች፡፡

«አይደለሁም» እያለችኝ ሁሉ ትመስለኛለች፡፡

«ሱሱልታ ነኝ» ትለኛለች፡፡

«ሜዳ ካየው ምን ለየው» እላታለሁ፡፡

«ማምለጥ የለም» ልሳት ነው መሰል፡፡

## (2) ማምለጫ፡

አዲስአባ ዙሪያዋን በተራራ ተከባ ምነው በቦሌ በኩል ክፍት ሆነ? የአዲስአባ የመሬት ቅጥ ሠፋ አለ እንጂ ያው እንደ ንፋስ መውጫ ነው፡፡ ገና ከእንጦጦ ስወርድ ነው፡ «እንዲ! እንዲ!   ኸረ!» ያልኩት፡፡ በስተፀሐይ መጥለቂያ ወጨጫና ረጲ፣ እንጦጦ ጠቅላላ ከበስተሳይና ከበስተምስራቅ፤ ታዲያ በታች በኩል ይሔ የተራራ ዐውድ ሜዳ ይሆናል.......በቦሌና እንዲህ በአቃቂ በኩል፡፡ በአንዱ የፀሐይ ከሳቴ በሌላ የፀሐይ



@BOOKALEM

ዕርበት:: መሃሉ ግን......መሀሉ መሸሺያ:: አንዱ መውጫ ለማምለጫ ደል የለ ተረት:: የቦሌው በቦሌ፣ የአቃቂው ያው በባሴ ነው እሱ::

እኔ ከንፋስ መውጫ በመፈርጠጫ፤

አዲስአቤም ካዲስአባ በማምለጫ::

ታልሆነ ታዲያ በሰበታ ሳይሆን በለገሃር ለምን ሔዱ? ሐይለሥላሢ ማለቱ ነው::

## (3) ቀዳማዊ ሐይለሥላሢ ወይም......

ሐይለሥላሢ ሲወለዱ የወጣላቸው ለም ተፈሪ ይባላል:: የአንድ መልከመልካም ጠይም የሰፈር ልጅ ሥም:: ለማቸውን ያወጡላቸው አያታቸው ጉዲሳ ናቸው:: ጉዲሳ ስምና ጠባይ እንዲስተካከል በአወጣጣቸው ጦረኛ ልጅ ተፈሪ ይወጣው መስሉአቸው ነበር:: ተፈሪ ከአደንና ከጉግስ ይልቅ ሰው ማጥናት የሚቀናቸው ሆኑ:: ጉዲሳ ሕልማቸው እዚህ፣ ነገርዩው እዛ ሆነባቸው:: ከየሺ እመቤት አባት ከእሊ ጋር ሐረር ወይዘሮ ድንቄ ጠላ ቤት ሲገናኙ የሚያወሩት የተፈሪን ነገር ነበር::

«ይሄስ እንደወንዶቹም አይደል:: ተቀምጦ ማውራት የሚወድ ነው» ይሏቸዋል::

እሊ ጠላቸውን ጠጥተው ጀጎል አባድር ቤት ትናንት ያላመጡት ጫት ውል ብሎአቸው በመለሳቸት ለመነሳት ይዳዳቸዋል:: የጉዲሳ ነገር ግራ ያጋባቸዋል:: ወንድ የግድ ማደን አለበት?፣ ወንድ ለመሆን የግድ መተኮስ አለብኝ? ፊልቴራቸውን መግምገው ሲበታተኑ ባልተቋጨ ውል ነበር:: እሊ ለለ ተፈሪ ምኞት ሳለማውራት መሸሸ ይፈልጋሉ:: ለጉዲሳ ደሞ ከተፈሪ እናትና (የሺእመቤት) አባት (መኮንን) የበለጠ የልጁ የተፈሪ ወደ ፊት መሾምና ማደግ የሰዎች አስተዳዳሪ መሆን ያሳስባቸዋል:: አንድ ቀን ለአደን ወደ ጊኒር ሲወርዱ አንድ ምዕራፍ ምንገድ ተፈሪን ሸኝኝ ብለውት ተከትሉአቸው ሲሄድ የሚከተለውን አዋዩት:

«ምን ለመሆን ነው የምትመኘው?»

«ንጉሠ ነገሥት»

«የትኛው ጦረኛነትህ ነው?»

«ምንገድ ምንገድ እስ»

«አብረኸኝ ጊኒር አትወጣም?» እሉት ሲፈትሹት

«ምን ልሰራ:: የበሬ ስጋ ምን አለኝ»

«አንድ አልሞሴ እንኳን ግደል?»

ያንን ቀን ተሰናበቱትና ተፈሪ ወደ አዲስ አበባ ስለተመለሰ ከዚያ በሁዋላ ሰረኸም ጊዜ አልተገናኙም::



@BOOKALEM

ተፈሪ በስልጣናቸው እያደጉ አልጋወራሽ ሆኑ:: ጉዲሳ ይሄን ሲሰሙ ማመን ከበዳቸው:: እድሜአቸው የገፋ ቢሆንም ጦር አዝምቶ የማያውቅ አልጋ ወራሽ ምን እያደረገ እንደሆነ ለማየት ለማንም ሳይነግሩ አዲስአባ ከች ይላሉ:: አንድ የሐረር መኩዋንንት ቤት ያርፉና መምጣታቸው እንዳይነገር አስጠንቅቀው በየገበያውና በየአራዳው አልባሌ ሰው በመምሰል ስለልጅ ልጃቸው መሰለል ይጀምራሉ:: አንድ ዕለት ማታ ከአንድ ፊልተር መሸጫ አምሽተው የተፈሪን ዝናን ገናናነት ተረድተው እየተገረሙ በአራዳ መሃል ነፍጣቸውን ትከሻቸው ላይ አንግበው ወደ ማደሪያቸው ሲያዘግሙ ፊት ለፊታቸው የሚንገዳገድ አንገዳ ድምፅ የሚያሰማ ዐይናቹ· የተበለጠጠ የመሰለ ነገር ወደ እሳቸው ሲመጣ አዩ:: «ሰይጣን ነው ይሄ» አሉና ከምንገድ ሸተት ብለው ዛፍ በመከለል ጠመንጃቸውን አቀባብለው ቆሙ:: ታዲያ ግን ይሄ ነገር በአንገዳ ድምፅ እየጮኸ፣ ኡ!ኡ! እያለ አጠገባቸው ሲደርስ ሲል ውስጡ ሁለት ሰዎች እንደተቀመጡ አዩ:: ግራ ተጋብተው ገላቸው ሳሳ እንዳለ ነገርዩው ሲያልፋቸው ከላይ እስከ ታች ጭቃ አለበሳቸው:: «ዐካኪ ዘራፍ!» ብለው ቢተኩሱ የመኪናውን የፊት መስታወት በጠሱት::

ያደሩበት ቤት ደርሰው በመገረም ያጋጠማቸውን ሲነግሩአቸው: «ነገሩ መኪና ይባላል:: አውስጥ ያሉት ሰዎችም እየጋለቡዋት» ነው ይሉዋቸዋል:: ጋራሙለታ እያሉ ቢንትሌይ የሚባል እንግሊዛዊ ሰው ሰራሽ መኪና የተባለ ነገር ሐረር ይዞ ስለሚመጣ ተቀባይ ሁን ተብለው አግራቸው በዚያን ሰሞን ተገድቶ ስለነበረ ሳይዘልቁ ቀርተው ነበር:: በሁዋላም ተሽሉአቸው ሐረር ሲወጡ የድሬዳዋው ጉምሩክ አሳፊ ሸቶ ንጋቱ ስለመኪና አውርተዋቸው ነበር:: ግን እንዲህ ያለ ነገር ካልታየ እንዴት መረዳት ይቻላል?

ያዲስአባ ነገር ዞር አድርጎባቸው ለለሳቸውን አቆሙና ተፈሪን ለማየት በሰው ተመርተው ቤታቸው ይሄዳሉ:: የተፈሪ መኖሪያ ትልቅ ግቢ ነበር:: የአልጋወራሽ መኖሪያ መችም::

አጋፋሪ እየመራ ሲያስገባቸው፣ ግቢው ውስጥ ምን ቆሞ ያያሉ? ያቺ የማታዋ መኪና::

አጋፋሪውን: «ይህቺ ምንድን ናት?» ብለው ይጠይቃሉ:: ሆዳቸው ጠርጥሮአል::

«መኪና» ይላቸዋል::

«እሕም» ብለው አለፍ አሉ::

የመኪናዋ የፊት መስታወት ላይ ትልቅ ቀዳዳ አዩ:: ተደናግጠው እዳራሽ ሲገቡ የልጅ ልጃቸው ተፈሪን ጎንበስ ብለው እጅ ነሱ::

«ይህቺ ነገር ያንተ ናት ልጄ?» ይላሉ ጉዲሳ

«የቷ?»

«ይህቺ የምትጋለበዋ ነገር»



@BOOKALEM

«አዎ አዎ አባቴ፤ ትናንት አንዱ የጠገበና የፈራ ጎሽቶ ሲገለን ነበር:: ገና ሰው አልለመዳትም»

«ውይ ልጄን» አሉ ጉዲሳ በድንጋጤ::

«ሲያወጣ እንዲህ ነው» አሉ ተፈሪ ሳቅ ብለው:: ቀጠሉና: «ምንገድኛ እኮ ነው:: የሚጠጣ አምጡለት» አሉ ተፈሪ::

ጋቢያቸውን ለአጋፋሪ ሰጥተው በትከዛ: «ሰማህ ተፈሪ ጊዜው ተለውጦአል መሰለኝ»

«ተለውጦአል እንጂ አባባ»

«በል የቆርኪ ቋዋንጣ አምጥቼልሃለሁ:: አታድናትም እንጂ ትበሳታለህ» አሉ እየሳቁ::

በሁዋላ በሁዋላ ይህቺ የሐይለሥላሴ መኪና መከላከያ ሚኒስቴር ግቢ ውስጥ ነበረች አሉ:: በድሮው አይሮፕላን ማረፊያ በ1964 አካባቢ ኢግዚብሽን ተዘጋጅቶ ይህቺ መኪና ከነቀዳዳዋ ቀርባ ነበር:: መኪናዋም ጎን ላይ በትልቅ ሰሌዳ የንጉሠ ነገሥቱና የአያታቸው ስም ሳይነሳ ይሄ ከላይ የተጠቀሰው ታሪክ ተፅፎ ነበር ይላሉ:: ጠቅላላውን ገጠመኝ እንደ ትውልድ ግጥት የተገነዘበ አንድ ገብረክርስቶስ ደስታ የተባለ ሰዓሊ *አባትና ልጅ* የተሰኘ ስዕል ጉዳዩን ተመርኩዞ ስሎአል:: በዚህ ስዕል ላይ ማንነታቸው የማይለይ መኪና ውስጥ የተቀመጡ ሁለት ሰዎችና ከመኪናው በስተቀኝ ማንነታቸው ያልታወቀ ሰው ይታያሉ:: ሁለቱ ሰዎች መኪና ውስጥ የተቀመጡ ሲሆን ከመኪናው ገላ ይልቅ ጎልቶ የሚታየው በጣም የሚያበሩት ሁለቱ የፊት ለፊት መብራቶቹ ነበሩ:: በስተቀኝ በኩል ያለው ሰውዬ አንገቱን ሰብሰብ አድርጎ ከሚተኩሰው በጉልህ ከማይታየው ጠመንጃ ብርሃን ይፈልቃል:: ይሄ ብርሃን ግን ደካማና ከመኪናዋ የፊት መብራት ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ነበር:: ስዕሉ ለኢግዚብሽን ሲሰቀል ንጉሡ ገዝተውት በቤተመንግስት አስቀምጠውት እያለ የየካቲት ለውጥ ይመጣል:: ከቤተመንግስት በተለያየ መልኩ ይወጣና አዲስ አባ ማዘጋጃ ቤት በ1969 የስዕል ኢግዚብሽን ሲታይ ይሄ የገብረክርስቶስ ስዕል ስለሁዋላ ቀርነትና ስለግስጋሴ ልዩነት ያሳያል ተብሎ ይቀርባል:: በዚህ ወቅት የስዕሉ አርእስት ጠፍቶ ነበር:: የስዕል ት/ቤት አንድ ሃያሲ አርእስት ለመስጠት ሲያስብ ቆይቶ በብዙዎች ሃይ ሃይ ባይነት *ሁለት መብራቶች* ተብሎ ይሰየማል:: የሐረር ተወላጅ የሆነውን ገብረክርስቶስን አውቀዋለሁ የሚል አንድ የፖሊስ ኮሎኔል ስዕሉን ከኢግዝቢሽኑ ላይ ይገዛውና ለሥራ ጉዳይ እሱ ቢሮ ስገባ አየሁት:: ለእኔ ለአሳዋቂው ስዕሉ የሚያስፈራ ጨለማ የበዛበት መሰሉኝ ነበር:: ታዲያ ካልዋሽ ለመሆኑ ጭለማ ያልሆነበትና ያልፈራ አበሻ እስኪ እጁን ያውጣ::

ይሄንን ዕውቀት እንድከታተል የገፋፋኝ ጃፓን ስለአያቱ ያወራን ታሪክ ነበር:: የጃፓን አያት በጣም ጥቁር ሰው ይመስሉኛል:: ለጃፓን ስለ ስዕሉ ነግሬው: «እሱ ኮሎኔል ቢሮ ገብቼ እንኩዋን ሳነጋግረው ይቅርና ሳየው አልፈልግም:: ጉረኛና ባለጌ ሰው ነው» አለኝ:: ከዚህ የበለጠ ስለ ኮሎኔሉ አልነገረኝም:: ባለጌነቱን አላውቅም፣ ጉረኛ



@BOOKALEM

ግን ይመስላል:: ሲያወራ በአንድ እጁ ፀጉሩን ይዳብሳል በቀኝ እጁ ሆዱን ይዳብሳል......መልካም ቀፈት ነበረችው:: አንድ ቀን ከመስሪያቤት ግቢ ሲወጣ ሠላምታ ሰጠሁትና «ግድ የለም ሳድርስህ» ብሎኝ የመንግስት ቮልስዋገን ውስጥ ጥናኝ ብዙም ሳንሄድ ከመሬት ተነስቶ: «እጮኛዬ በጣም ውድ የሆነ ዶጅ መኪና አላት» አለኝ:: ምንም አልመለስኩለትም፣ ስሌላም ሰው ወሬውን አላስተላለፍኩለትም......እሱን ከፈለገም:: አይገርምም? የመኪናው መሪ ዘይት እንደፈሰሰበት ሁሉ ይፈልቅ ነበር:: ወይ ፀጉሩን ብዙ ቅባት ተቀብቶት ነበር ወይ በቅርብ ባስቲ ወይ ፓምቦሊና በልቶ እጁን አልታጠበም::

## (4) ፏ ፏ ይላል ዶጁ:

ዶጅ ምንድን ነው? መሃይም እኮ መሳቂያ ነው:: ለእኔ ዶጅ የሚቀነጠነጥ እንዳ ከሰቀቀት ደግሞ ማረፍ የማያውቅ ወደላ ፈረስ ይመስለኝ ነበር:: «የጠቅል አሽከር» እንደሚባለው እኔም «የዶጅ አሽከር» ለማለት ቃጥኛል:: በዘፈኗ ቅንጥ ልፊያ ያማራት የመሰለች ዱብራ (የት አውቃለሁ እቴ ተሳልፎአትስ እንደሆነ) *ይላል ዶጁ ፏ ፏ ይላል ዶጁ*......ስትል:: በስታድዮም፣ በፒያሳ፣ በየካ፣ በጉለሌ ዶጅ አሳዩኝ እያልኩ ዞርኩ::

ማግኘት አልቻልኩም::

«ታዲያ ለሌለ ነገር ይዘፈናል?» ስል

«አብዮቱ ጠርጎ ወሰደው» ይሉኛል

«እንዴት እንዴት ምን ዓይነት ሸብር ተፋፋመበት?»

«ምን ታሾፋለህ?»

«ዲኢክስ ይበልጣል ወይስ ዶጅ?»

«ካልተዘፈነለት ዶጅ ይበልጣል» አሉ

አመንኩ የባሳገር ነገር::

ግን ይሄ ግጥም ነበር አንድ አዝማሪ የቀደደው:

*እልሽሹም ዞር እሉ-ዞር እሉ መቾ ሽሹ*
*እኛስ መስሉን ነበር በጋሪ የሚሄዱ*
*ዶጅ አባረሩና በዲ-ኢክስ ነጎዱ*
*እልሽሹም ዞር እሉ-ዞር እሉ መቾ ሽሹ*

ብቻ ትንንሽ የነገር ጉጉማት፣ ትንሽ ወለም ያለች ቀብ፣ ዝንቧን እሽ እያልኩ የከተማ ወንበዴ ለጠብቅ ባርኔጣዬን ከፍ አድርጌ ግንባሬን እያከከሁ......ይጠቀጥቀኛል::



@BOOKALEM

እስመምሰል ያጠፋል ስለሚሉ ተንቦቅቡቂ ሳይሆን አይቀርም በየጥቅጣቅው መሃል በጀርጃፋ ድምጿ: *ፏ ፏ ይሳል ደፏ* እሳለሁ:: ይኼ ዘፈን ንጋት ሻይ ቤት ሁልጊዜ እንደተለኮሰ ነበር:: የደሐ ቦምቦሊኖዬን ልበሳ ስሄድ::

## (5) ቦምቦሊኖ ባለ አጭር ታሪክ:

ቦምቦሊኖ ይጣፍጣል:: ስሙም ደስ ይላል:: አዲስአባ ካሳመደችኝ አንዱ ዋና ነገር ቦምቦሊኖ ነው:: አንዳንድ አዲስ አባ አደግን የሚሉ ሰዎች «ዋጋው ከፍ አለ እንጂ ከአብዮቱ በሁዋላ የመጣው ቦምቦሊኖ ጥራት ከአብዮት በፊት ከነበረው ፓስቲ ጋር ይመሳሰላል» ሲሉ እሰማለሁ:: በፖሊስ ገንዘብ በየቀኑ ለትደፈር እንጂ አንዳንዴ እንደ ሁለቱን እበላና ከመብላቱ የበለጠ የሚያስደስተኝን ነገር እጠብቃለሁ:: የሻይ ቤት ፓስቲ ቆሻሻ ልብስ፣ ወይ ሱሪ በቀሚስ የለበሰች ቦምቦሊኖ ናት......የደሃ ቀንጆ:: ቦምቦሊኖ ጉርድ ቀሚስ አድርጋ ፀጉርዋን አብዮት አደባባይ የተሰራች ፓስቲ ናት......እስቀያሚ ሞጃ:: የቴክኒክ እርቀት የላቸውም:: የሴት እስኪትዋ ቀሚስዋ ውስጥ አልተቦረቦረም መሰለኝ:: የቦምቦሊኖ ልብ ሁልጊዜ አመልማሉ የመሰለ ነው:: የፓስቲ ልብ ውስጥ ጥቁር ቅመም፣ ያልሙዋማ ዕርድና አንዳንዴም የቅንድብ ይሁን የእናት ፀጉር አገኝ ነበር:: ቦምቦሊኖ ቀይ የተመቻት ወፍራም ሴት ትመስለኛለች:: የበለጠ የምደሰተው ስፀዳዳ ነው:: ያን ጊዜ ልዘፍንላት ያምረኛል:: ያውም በእንግሊዘኛ: *አይ ሳቭ ዩ ሞር ዛን ፓስቲ* ብዬ:: ሳይንስ እንደሚነግረኝ የበላነው ምግብ ከአስራ ስምንት ሰአቶች በሁዋላ በደነ ምድር ሆኖ ይወጣል:: ታዲያ ከአስራ ስምንት ሰዓታት በሁዋላ መፀዳጃ ቤት ሠሐን ላይ እንሳፈፍና ቆሻሻዬን እጥላለሁ:: በፈገግታም ቆሜ ዞር እላለሁ:: ወደ ኩሴ እጠቀምና «የእንጀራ እህቴን ትመስላለህ» እለዋለሁ::

ለእኔ የቦምቦሊኖ አጭር ታሪክ ይሄ ነው::

## (6) አይ ላብ ዩ ሞር ዛን አይ ነን ሰይ:

የዘመኑ ሞኝ ባገኝ ይባል የነበረ የእንግሊዘኛ ዘፈን:: ከእንግሊዘኛ ቢሉ እንግሊዘኛውን እስከሚያፈሰው ድረስ በየመንገዱ ሲያቀነቅነው የሚውል:: በሬድዮም አልቀረ:: በሬድዮማ ዘፈኑን የሚያንቸለችሉት በግብዣ:: በተለይ ሕጻናት:: ሥራ የፈታ አገር:: «እሪ እናድንቅ! እሪ አድንቁ!» ያልተባለነው አለ? «ልገልፀው ከምችለው በላይ እወድሻለሁ» ብሎ ራሱን መግለጥ የከበደው ደደብ ዘፈነና ጆሮአችን በአችፍቻፊ ምሪቅ በሰበሰ:: እነዚያ ትርቡት ሴቶች መዓዛና ሽታዬ አንድ ሰሞን መጨቃጨቃቸውን አቁመው ነጋ ጠባ ይሄን እየዘፈኑ በማለስቸት ሲገሉኝ ነበር:: እኔም መዝፈን ባልችልም ጭንቅላቴ ውስጥ ዜማው እየፈላብኝ ጣቶቼን ባጮህ አልሰምርልኝ አለ::

## (7) ጣት:

ያ ቀለበት የገባበት ጣት ደምበሽ ያለ ነበር፥



@BOOKALEM

አመልካች ጣትዋ ጥፍር ንጣት ላይ ያለው ደማቅ ጠብታ ቀይ
የጥፍር ቀለም እንጥፍጣፊ ወይስ የደረቀ ደም?
አሁን ያለውን በማየት ስለጥንቱ ማወቅ ይከብዳል::
ቢሆንም ባይሆንም ቢያጠፋንም ቢያለማንም እንጠርጥር::
ቢጎዳንም እንገምት::

## (8) አልፎ አልፎ ወደ አለፈው......፡

መቸም አንድ ሰው ሰለሰዎች ሲያወራ ፀባያቸውን ከመግለጥ ጋር አብሮ ስለአካላቸው ደዞታ በመጠኑ ቢናገር አቀራረቡን የተሟላ ያደረገዋል ተብሎ በብዙ ሰዎች ይታመናል:: እኔ አላምንም:: እኔ ለሰሰው ቁመና፣ መልክ የምናገረው ሲመችኝ ነው:: በአገራችን ይኼ ነው ተብሎ የተሰየመ የኢትዮጵያውያንን ቁንጅናና አስቀያሚነት መመዘኛ ሕግም አልወጣም:: ማለቴ ቆንጆ ማለት እንዲህ እንዲህ እንዲህ ዐይነት ሰው ነው ተብሎ:: ሰው የተለያየ ነው ልክ አጆቻችን ላይ እንዳሉ ጣቶች:: የትኛው ጣታችን ነው ቆንጆ?

### ሀ) *እንጀራ እናቴ፡*

እንጀራ እናቴ እኔ ላይ ስለምታደርገው ጉድ ሳወራ መልኳን የገለጥኩ አይመስለኝም:: አንድ ጊዜ ስለጥንዋ ያወራሁ ይመስለኛል:: ግን ይኼ ብዙ ሰው ለእንጀራ እናት እንኳዋን ቢሆንም ጨዋነት ያጉደለው የአካል ክፍል እንደጠቀስኩ ሳይገምት አይቀርም:: በወሬ በወሬ እንደለማሁትና አሁን ትዝ እንደምትለኝ እንጀራ እናቴ ቆንጆ ስትባል ነው:: መሆንም አለባት:: ምክንያቱም የወለደች ሴት አባቴ ያለ ነገር አያገባማ! የእጅ ጣቶችዋ ረዛዥም እንደነበሩ ትዝ ይለኛል:: ፀጉሯ ከርዳዳ ቢሆንም በአጭር ተጉንጉኖ ማጅራቷን የሚያልፍ ዕርዝመት ነበረው:: በመጠኑ ደባደቦ ነበረች:: ልጅዋ አለዋን ሳትመስል አትቀርም (አህቴን ማለቴ ነው) ከዚህ የበለጠ አላስታውስም:: ሁልጊዜ የምትለብሰው ሰማያዊ ቴትሮን ቀሚስ ትዝ ይለኛል::

### ለ) *ሌሊያሱ*

አሊያስ ቀጭን ቀመተ-ረዥም ነበር:: ዐይኖቹ ትላልቅ ነበሩ:: ከንፈሮቹ ትናንሽ ነበሩ:: ወንዝ ወርደን ለዋና ልብሳችንን ስናወልቅ ደረቱ ላይ ከጡቶቹ መሐል ትልቅ ጥቁር የሽታ ደሴት ነበረ:: እግረ ትልቅና ቁርጭምጭምታም ነበር:: ከዚህ በላይ......የጥርሱ የግራ የላይኛው ክራንቻ የወለቀ ነበር:: ለምን እንዲያ እንደሆነ ግን አልጠየቅሁትም::



@BOOKALEM

ሐ) *ሙስጠፋ:*

ሙስጠፋ ጢሙ ትዝ ይለኛል:: ጢሙ ትዝ የሚለኝ በዚያን ጊዜ በዕድሜ ከእኔ ከሚበልጥ ጢማም ሰው ጋር ማውራት ስለሚያኮራኝ ስለነበር ይመስለኛል:: ፊቱን ከሸፈነው ጢሙ መሐል ሲስቅ ብቅ የሚሉ ጥርሶቹ ይታወሱኛል:: ጥርሶቹ አረዝም ይሁኑ አጥር፣ ሠፊ ይሁኑ ጠባብ ግን ትዝ አይለኝም:: ትዝ የሚለኝ የሚስብ ንጣታቸው ነው:: ብዙ ጊዜ ከባንኮኒ ጀርባ ስለማየው ነበር መሰለኝ ጉበጥ ያለ ወይም አንገቱ ወደ ትከሻው ውስጥ የገባ ይመስለኛል:: ከዚህ በላይ ስለ ሙስጠፋ አላስታውስም::

መ) *አባቴ(ዱባለ)፦*

ስለጆሮው የተናገርኩ ይመስለኛል:: ሸፋፋ ነው ሲባል እሰማ ነበር:: ጠርቶ ባይገባኝም «ሸፋፋ» የሚለው ቃል......የእግር አጠማመሙ፣ አደፋፋ እንዴት ተስከቶ እንደሚሰጥ ስለማላውቅ:: ዐይኖቹ ጉረጥራጣ ነበሩ:: በተለይ ሞለጥላጫ ፀጉር ሲያስተካክልና ሲያተኩር እንዳለ ተጉልጉለው ሊወድቁ የደረሱ ይመስላሉ:: ያስፈራል:: ያስፈራል ማለቱ ዐይኖቹ ከጉድጓዶቻቸው ወጥተው ሲወድቁ ከመሐል በመቀስ እንዳይቀነጥባቸው:: ድምፁ ወፍራም እንደነበረ ትዝ ይለኛል:: ቤት ሳይገባ ገና ከአጥር ውጪ ሲያወራ ድምፁ 'እው' ሲል እሰማለሁ:: ይታወቃል:: ከዚህ በላይ ስለ እሱ አካል የማውቀው ነገር የለም:: ዝርዝር ትዝ አይለኝም::

ሠ) *ወሰን የለሽ(ወሰን)*:

ድሮም አሁንም ትዝ ስትለኝ የሚታወሰኝ ስሟ «ወሰን» ነው:: ደምበኛ ስሟ «ወሰን የለሽ» መሆኑ ትዝ ያለኝ በቅርብ ነው:: ቁመቷ ከእኔ አጠር የሚል ቀይ፣ ቀጥን ልጅ ነበረች:: ደስ የሚል ነገር አላት:: ፀጉሯ የሚያንፀባርቅ ቡናማና ሁልጊዜ የተጉነጉነ ነበር:: ቆንጆ ስትባል እኔም በተሰጣት ቅፅል ስከርኩ እንጂ ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም ነበር:: ቆንጆ ማለት ለመሆኑ ምንድን ነበር? አሁን ተለውጦአል እንዴ? ዛሬም ወሰን ቆንጆ ናት እንዴ.?......ከአሥር ከአሥራ አንድ አመታት በሁዋላ? ቁንጅና እንደዘመኑ ይለዋወጣል? የፊውዳሊዝም ቁንጅና፣ የካፒታሊዝምና የኮሚኒዝም ቁንጅና አለ እንዴ? የድሮ ሰልካካ አፍንጫ በአብዮቱ ጊዜ ደፍጣጣ ይሆናል እንዴ? የድሮ ·ደፍጣጣ አፍንጫ በአሁኑ ጊዜ ሰልካካ ይሆናል እንዴ? ስለ እሰዋ ወሬ ሰምቶ አላውቅም:: ሽፍቶች ቤታቸውን እንዳቃጠሉባቸው ሰምቻለሁ:: ሰው እንዳልሞተም ሰምቻለሁ:: ሰው አልሞተም ማለት መችም ሰው አልቆሰለም ማለት አይደለም:: ወሰን እሳት አቃጥሎአት ቡናማ ፀጉሯ ተላጭቶ ይሆናል:: እንደሚዳቋ የሚሰሯት እግሮቿ በእሳት ተጠብሰው ይሆናል:: በቃጠሎው የግንባሯ ቀይ ዳማ ቆዳ ተላልቆ ዐይኖቿ ላይ እንደ ቀለጠ ሳስቲክ ወድቆባቸው ይሆናል:: ስለ እሰዋ አሁን አላውቅም:: ምናልባት እንገናኝ ይሆናል:: ምናልባት ድሮ በተሰሙኝ ስሜቶች ዛሬ ባያት አፍር ወይ እስቅ ይሆናል::



@BOOKALEM

ረ) *አለማየሁ፡*

ድምፀ-ቀጭን ሲታሲት መልክ ያለው ነው። ለምን ሴቶች እንደሚወዱት አላውቅም። ስለትናንሽ ነገሮች ማውራት ይወዳል። ትላንት ስለበላው፣ ስለገዛው ሱሪ፣ እህቱ ስለፃፈችለት ደብዳቤ፣ የመሳሰለ። ከመኝታው በጠዋት የሚነሳው አለማየሁ፣ የምንጋራትን አንድ የፊት መስታወት በብዛት የሚጠቀምባት እሱ፤ ገላው ንፁህ ነበር። ፀጉሩ በየወሩ ለደመወዝ ዕለት ይከረከማል። ዐይኖቹ ትናንሽ ነበሩ......ሲስቅ በሸፋሽፍቶቹና በተሰበሰበ ቆዳ የሚደፈኑ። አፉ ጠባብ፣ ከንፈሮቹ ስስ፣ የእጅ ጣቶቹ ረዛዝምና ቀጭን ነበሩ። የቤታችን አጅግ ንፁህ ሰው እሱ ነበር። ስለ ማጅራቱ ምን መምሰል፣ ስለጥርሱ፣ ስለ ዐይኖቹ አቀማመጥ ለመናገር ብፈልግ የሚገርም ነው ትዝ የሚለኝ ነገር የለም።

ሰ) *ዳፓን፡*

ሁሉ ነገሩ ወፍራም። የሚናገራቸው ቃላት እንኳዋን ወፈፍራም ነበሩ። ለድብ ይቀናዋል። እናትክን፣ በስባሳ፣ ጨምላቃ፣ ንፍጣም፣ ዝባዝንኪ፣ ወንዳገረድ፣ የመሳሰሉ። ጥርሶቹ ትናንሾች ስለሆኑ ሲስቅ ሕጻን ልጅ ይመስል ነበር። እንደ ሴት ጡት አለው። ከስራ ውጪ አሁድ አሁድ ቱታ መልበስ ይወዳል። የሚያመጣቸው ሴቶች በዕድሜ የሚበልጡት ይመስለኛል። ከተናደደ ከፊቱ ዞር ማለት ያስፈልጋል። በኩረ በጣም የሚፈራው ሰው ቢኖር ዳፓንን ነበር።

ሸ) *በኩረ፡*

ግንባረ-ፈጣጣ ቀጫጫ ልጅ ነበር። አኔ ነገር ያከሳው ይመስለኛል። እንደ አኔ ያለ ልጅነት ያሳለፈ ሲሆን ይችላል ምናልባት ጨቅጫቃ ያደረገው። ሁለት የፊት ጥርሶቹ ገጠጥ ያሉ አካሄዱ ፈጠን ፈጠን ያለ ዐይነ-ልም ነበር። በኩረ......በቀጭን አጥርነቱ፣ በቀይ ሲታሲትነቱ፣ በችኩል ተቆጪነቱ ሾልኮ ያልረበሸው ዳፓንን ነው።

ቀ) *ነጋሳ፡*

በጣም ግዙፍ ሰው ወይም ልጅ ነበር። ክእኔ ይረዝማል። በመርዘሙ ይኩራል። እዚህ ቤት እንደ ሰው የተሰራነው እኔና መዝገቡ ነን ይል ነበር። ዳፓን ይኼን ጉራውን ስለማይወድ ሁልጊዜ ይሳፋዋል። አልጋ ላይ ታግሎ ከጣለው "እጀሬን ጉድ ሰራሁዋት......ረዘምኩ ስትል"። ነጋሳ አፍንጫ ስር ሁልጊዜ ትልቅ ፂም የሚያሳድግ፣ ዐይኖቹ ትናንሽ፣ ከንፈረ-ትልቅ ነበር። አሁድ ጠዋት ጠዋት ቤተክርስቲያን አይቀርም።



@BOOKALEM

ማርያምን ይወዳል:: "እዚህ ተ/ሃይማኖት ስትሔድም?......ምን አስለፋህ ልደታ ድ[
ይለዋል ጳፓን:: "ማርያም የምትጠበስ መስሎህ ነው እ" ይለዋል::

"አንተ ለዚህ ሐጢያትህ" ይለዋል......ነጋሳ::

"ፕሮቴስታንት ነው" ይላል በኩሪ::

"ማነው ፕሮቴስታንት?" ይላል ነጋሳ::

"ተወው አሺ......ልትደብቅ ፈልገህ እንደሆነ" ይለዋል በኩሪ:: ይናደዳል......ነጋሳ ይናደዳል:: "ፕሮቴስታንት አይደለሁም:: ብሆን ምናለበት" ይ[ል] በኩሪ እንዲህ ዐይነት ሥሞችን በጫወታ ለሰው መስጠት ይሞክራል:: በሚቀ[...] ቀናት ታዲያ "ያ ፕሮቴስታንት የት አለ?" እያለ መናገር ይጀምራል:: የተቀበ[...] አልነበረም:: ሁላችንም ለሐይማኖት ግድ አልነበረንም:: በዚህ በዚህ ዐይነት ጊዜ በ[...] እንዳገለልነው እያሽሙዋጠጠ ማውራት ይጀምራል:: አሽሻችሁኝ ማለት ይፈልጋል::

በ) ሌሎች:

ሌሎች ስማቸው ወይም ድርጊታቸው እዚህ ውስጥ የተጠቀሰ ባለታሪ[...] መልካቸውን ጠንቅቄ የማላስታውሳቸው ናቸው:: እያንዳንዱ ሰው የተለያየ የማስታ[...] ችሎታ አለው:: በጣም ደስተኛ ሰው የማስታወስ ችሎታው ከፍተኛ ነው፤ በ[...] የከፋው፣ የተጨነቀ ሰው የማስታወስ ችሎታው የተዳከመ ነው:: በዚህ ምክንያትም [...] ሳይሆን ፍላጎትም አለ:: ለማስታወስ የማንፈልገው ነገር ካለ አናስታውስም:: ለማስታ[...] የምንፈልገውን ነገር እናስታውሳለን:: ግን አንዳንዴ የተገላቢጦ ሲሆን ይችላል:: ለም[...] በኩረን በሕልሜም ይሁን በዕውኔ ሳስታውሰው ወይም ሲታወስ የሚገባው [...] አይደለም:: የጣጣ ፋብሪካ ወይም ራሱ ጣጣ ነበር:: ግን በግድ የሕይወታችንን [...] በተንኰሉ በመለወጥ እንድናስታውሰው ያስገድደናል:: ልክ እንደ ታላላቅ ጥሩ ሰ[...] በሕሊናችን ውስጥ በየግል ታሪካችን ውስጥ የራሱን ምዕራፍ በግድ ይከፍታ[...] ሳይለምኑት፣ ሳይጠይቁት::

«ሌሎች» ብዬ የለየምኳቸው፣ ያልፈለኳቸው፣ የረሳሁዋቸው፣ ከሕይ[...] ጠባብ ከልል ከሩቅ ውልብ ሲሉ ያየሁዋቸው ወይም እንደ ወሎዬው ለቅፅበት ያህ[...] ገብተው ረብሸውኝ የሔዱ፣ በጉዳና ላይ ደጋግሜ የማያቸውና የአዲስአበባን ከ[...] የሚወክሉልኝ ባይተዋር ሬቶች፣ አስቆቹ፣ ነፍሰገዳዮች፣ ሴቦች፣ ጉረቤቶች (ዝና[...] መንታዎቹ ወዘተ......፣ ኒንጃ፣ ጥቂት ባለሱቆች፣ የውይይት ሾፌሮችና ወያላዎች፣ [...] በደረቴዎች......እነዚህ ሁሉ «ሌሎች» ብዬ የመደብኳቸው ናቸው:: እነዚህ [...] አስፈላጊ አይደሉም ማለቴ አይደለም:: አንዳንድ ጊዜ ለቅላት ከፈረዱብን ሰዎ[...]



@BOOKALEM

ዳኖች ይልቅ የምንጠለጠልበት ተራ ገመድ አድግ አስፈሪ ሆኖ እንደሚታየን ዐይነት ሲሆን ይችላል።

ዳኖችን በድፍረት ሲናገር፣ ሲመልስላቸው ቀይቶ ያቺን ጠብቃ የተፈተለች ገመድ፣ ያቺን ቋጠሮ ሲያይ በሰቅሶ የሚፈነዳ ወንድ አለ......

## (9) ወይዘሮ ዝናሽ፡

ስመ-መልካም ናቸው። የተከፉ ሴት ቢሆኑም። ቾልተኛ አረማመዳቸውን ብንቀንስ፣ የጉንጮቻቸውን ማድያት በሆነ ሳጺስ ብናጠፋው፣ ከዐይኖቻቸው ውስጥ የሚፈልቀውን ረዝም ጩኸት ብንረሳው፣ የዘገኑ ጥርሶቻቸውን በሐረር መፋቂያ ብንልግሳቸው፣ ፈዲስ በጦርነት የሞተ ልጃቸውን ትንሣኤ ሙታን ብንሰራው፣ ወይዘሮ ዝናሽ ወዝብ ናቸው። እዚያ ሰፈር ስኖር በቅርብ የማያቸው በዓመት አንድ ጊዜ የአድባር ዕለት ብቻ ነበር። ከነዝምታቸው። የቤታችን በርና የእሳቸው ቤት በር ቀጥታ ትይዩ ነበር። እሳቸው አይታዩም፣ ግን የቤታቸውን በር (ገደድ ያለ፣ ማጠፊያዎቹ የዛጉ፣ ቀለሙ በአረንጉዋዲና በቡናማ መሃል የሆነ) ገርበብ አድርገው አውስጥ ይቀመጣሉ። ዐይኖቼ በሩን አልፈው ብዙ ጊዜ ያዩት የነበረው በቀሚሳቸው ስር የሚጤስ ወይራ የደበቁ ሴት ነበር። በዕድሰኛ ቀን ወተት የመሰለ ጢስ እንደ ሚሮን የሚያደርገው .የእሳቸውንና የእኔን መጠለያ በጠረኑ ያስረል። ይሄ ያሰቀዋረጠ የማጠንት ምስልና ጠረን አንዳንድ ነገር እንድጠይቅ አደረገኝ።

«ምነው?» ብል......ገና ሰፈር እንደ ገባሁ በአንገዳ አፍ፤

«ልጃቸው የሞተ አይመስላቸውም። ድንገት ቢመጣ ባዶ ቤት እንዳያገጥመው ብለው ነው። ዕብድ ሴት» ይሉኛል አዋቂዎች።

«ምፀ» አያሉ፣ ከንፈር መጠው።

በሰፈሬ ከላይ እስከ ታች «ምፀ» የሚጣልለት ሰው ብዛት መአት ነበር። ሰፈራችን የቀሰጠ የምፀ ፋብሪካ ነበር። የማይተፋ ዓይነት ምፀ የለም። በተለይ ዝናብ ጥሎ ያባራና ያኔውኑ ወርቅ የመሰለች ፀሐይ ስትወጣ በሠፈሬ ምንገድ ከሰሜን እስከ ደቡብ ምዕራብ ድረስ የቀሸሸ ዋልካ ሳይ ወድቀው በዝናብ እርጥበት የሚያንፀባርቁ ምፀዎች አያለሁ። የማያቸው የሽፈናቸው አቡዋራ በወጨፎ ታጥቦ በየቦዩ ስር በድካም እያብለጨለጩ ተቀምጠው ነው። ከፊሎቹ ነብ፣ ከፊሎቹ ሞላሊ፣ ከፊሎቹ እሬት ማዕዘን፣ ከፊሎቹ ኮከቢ፣ ከፊሎቹ ጥሪያንገል ቅርፅ ነበራቸው። ቀለማቸው ከገራጫ እስከ ነጭ ድረስ ነበር። በእዝነልቡናዬ ይሔ የቀለማቸው አሰሣጥ ከምፀው ንፅሕናና ቅንነት ጋር የተያያዘ ይመስለኛል። መጠናቸው አንዳንዶቹ ጠፍ፤ አንዳንዶቹ ቦሉቂ የሚያካክሉ ናቸው። ይሄ የምፀዎች ትዕይንት ለዐይኖቼ የሚከሰተው በማላውቀው ምክንያት በጠዋት ከአልጋዬ ተነስቼ በመስኮት ወደ ውጭ ሳይ ነበር......የዝናሽ ቤት ፊት ለፊት የተቆላ ካሬ የመሰሉ ምፀዎች ከቤትዋ ፊት ለፊት ምንአልባት አንድ ሜትር



@BOOKALEM

ያህል ራቅ ብለው ተከምረው አያለሁ:: በጋቢያቸው ተገንዘው የሚሄዱ ሴቶች ወደ ዝናሽ ቤት ሰረቅ አድርገው ያዩና እንደተማከሩ ሁሉ በሕብረት ግን በተራራቀ ምላሽ ከንፈሮቻቸውን ይመጣሉ......ምፀ......ምፀ......ምፀ:: ከአፋቸውም አያለሁ አረፋ የመሰሉ ብቸኛ እንክብሎች በቅለው ብዙዎቹ ግራጫ የሆኑ......በደረቶታቸው ሳይ ተንደርድረው መሬት ሳይ ሲነጥሩ፣ ነጥረውም ሲንኩዋሰሱ:: ከዐይን እንደሚርቅ ነገር እያነሱ እያነሱ ዝናሽ ደፍ ሳይ ቀድመው ሄደው ከሚጠብቁዋቸው መሰሎቻቸው ጋር ይደባለቃሉ:: ሲመሽ አንዳንዴ እቤቱ ደፍ ሳይ ተቀምጩ የቀንዋን ሶስተኛ ሲጃራዬን እየመጠጥኩ የቀን መዋለች ያዳከማቸው ሰዎች ከእኔ ብዙም ሳይርቅ ይቆሙና ከጨለማው ጋር በበረደ ገላቸው እየተሻሹ ከወሬአቸው መሃል የዝናሽ ነገር ይነሳል መሰለኝ እንደባትሪ ፋዋ ያሉ አረፋዎች ጨረቃ-ቀለም ያላቸው እንክብሎች ከሚያንሾኩዋሹኩ ከንፈሮቻቸው መሃል ይንጠባጠባሉ:: እነዚህ እንክብሎች የሚያደርጉትን እንደሚያውቁ ሁሉ ሸፐ እንደሚከተል ውሃ ተንከባለው ተንከባለው ዝናሽ ቤት ደፍ ሳይ ይሰበሰባሉ:: ሹክሹክታው ከነሰዎቹ ሲፈርስ ክምሩ ሳይ የረጉት እንክብሎች መጀመሪያ አመዳም፣ ቀጥሎ ግራጫ ይሆኑና እዚያ ቀድመው ከጠበቁአቸው ምፀዎች የሚለያቸው ነገር ይጠፋል:: ፀሐይ ሰማይ ዳዳሌብ ሳይ ተሰቅላ ምድርን እንደ ጣቃ በጨረርዋ ስትሰፋ እሑድ ቀን የዘፈን ምርጫ ፕሮግራም በሬድዮ እየሰማሁ፣ እነዝናሽ ስለ «ፈስጡት» ወንድ፣ ስላወጡት ታች ሰፈር ያለ አባወራ፣ ትናንት በህብረት ሁለት ከትፎ ስለመተሩት የመርካቶ ነጋዴ አውርተውኝ አልቆባቸው ሲሄዱ የዕለቱን የመጨረሻ ሲጃራዬን ለኩሼ አሳፊ አግዳሚውን ስመለከት መውደቅን እያለሁ::

ቆመን እንሄዳለን እያልን መውደቅን እያለሁ:: መውደቁ የረቀቀ ነበር:: መውደቁ የተቀናበረ ነበር::

ባለሰበብ ወዳቂዎች እያለሁ::

«ይሄ የዝናሽ ቤት ነው?»

«ዝናሽ የትዋ?»

«ዝናሽ»

አንድ ሰው አንዲት ሴት፣ ሦስት ሴቶች አንድ ሕፃን፣ ሁለት ወንዶችና ሌሎች ሁለት ወንዶች፣ ሦስት ቂጣም ሴቶችና ሌሎች ሦስት ሴቶች ትናንሽ ጡቶቻቸው አየር እያስገቡና እያስወጡ፣ ቀለም ያለው ጨዋታ ይጀምራሉ......ከአንዱ አፍ ቢጫ እንክብል እያለሁ፣ በምጥ እንደ ተወለደ ሁሉ ከከንፈሮቹ መሃል አሙዋልጮ ይወጣና ወደ ዝናሽ ቤት ሲያቀና:: *ይህ የውሸት አሳቢነት ነው::*

ከአንዱ አፍ ቀይ እንክብል እያለሁ:: ይሄም እንደመጀመሪያው ይጉዋዛል፣ *ይህ የመጥላት ግን ያለቡ የመምሰል* ምፀ ነው:: አረንጉዋዴም እያለሁ:: ይሄም እንደቀድሞዎቹ ይሆናል:: *ይህ የአስተቶቹ* ጠባይ ነው:: ሃምራዊም አለ:: *የደደቦች*



@BOOKALEM

*እንከብቡ፡ የሚያደርጉትን የማያውቁ፡፡ በራሳቸው ቀስል እንጨት የሚሰዱ፡፡* ብዙ ብዙ ቀለም አያለሁ፡፡ ብዙም እንከብሎች፡፡

የነዚህ ምስሎች ጀርባ ብዙ ጊዜ የዘፈን ምርጫ ፕሮግራም ነበር፡፡

*የድሬ ልጅ ነሽ የዓባይ ማዶ*
*ልቤ ተጨንቆአል አሰዋን ወዶ*

እየተባለ፡፡

*እንበሳን በጡጫ እሰው የነበረ*
*ዝሆንን በጡጫ እሰው የነበረ*
*ልቤ አንቺ ዘንድ ሲደርስ ምነው ደነበረ*

እየተባለ፡፡

የእንካሳ ምሳሳችን ሰረሰር በአቶ ሙሉቀንና በአቶ ሙሐሙድ እየታሸ፡፡ አብራካችን እሳት እየነደደበት፡፡ በሚንዓዑ አልጋዎች ሳይ፣ ከጃፓን በመጡ ትኩስ መኪናዎች ውስጥ፣ በካድሬና በፀረ-ካድሬ ቸልታ፣ ዐይናቸቸው በዙፋን በሰከረ ምሁራን፣ እግዜር የሰጠንን የትም የማይሄድ ሴት እንቆፍራለን፡፡

*እነዚህ በዝናሽ ያሸፋሉ.......*

አያለሁ እንከበሎች ቢጫቱ የሆኑ ከዝናሽ ቤት ራቅ ብለው ዕንባ ሲያልባቸው፡፡ ቀለማቸው እንደ ትንሽ ፀሐይ ውጋጋን የሚመለከተውን (በዕድሱ ካጋጠመው) እያጥበረበረ፡፡ ባለእንከብሉ ሰው ዝናሽ ቤት ይገባና ይወጣል፡፡ የሚሰሩት አይታዩኝም፡፡ እንደ ሜዳ አህያ ዝንጉርጉርም ምፀዎች አያለሁ፡፡ *እነኚህ በሰው ጉዳት የሚስቁ እነሱ ግን የሚደርስባቸው የማይመስላቸው* ናቸው፡፡ ወይም ያልደረሰባቸው የሚመስላቸው ናቸው፡፡ መልኩን ሰውጦ እንደሚመጣ ይዘነጋሉ፡፡ መዓዛን ከሳይ ያለች ጎረቤቱ «ብችል ነርስ ብሆን ደስ ይለኛል» ስትል ነበር፡፡ ፊዲስ መዝሙት ያስፈልጋታልን? እዚሁ በአጅ አዙር ዘምታ ግንባርዋን ተመታ ራስዋን ስታ የለ፡፡ ታዲያ ያለፈው ሳምንት ያወጣትን ወንድ ሰሙን «ረሳሁት» ብላ በሳቅ ፍርስ ሰምን ትላለች? ታዲያ እስዋም «ምፀ» ስትተፋ አያታለሁ፡፡ ነጥነቱ ሰየዋህነትዋ፣ ጥቁሩ ሰማይቀር መጥፋትዋ፡፡ እንከብል አያለሁ......በጉቢ በዚያ ባልሞተ ባሕሊ፡፡ ዝናሽ ፊታቸውን ብቻ ከቤታቸው በበር በኩል ብቅ አድርገው ያዩኛል፡፡ እንተያያለን፡፡ እንደ ኤሲ ይመስላሉ፡፡

በዝናሽ ውስጥ የአገሬን ትንሽ አየሁ፡፡

## (10) መንታ፡

ከዝናሽ ቤት ከፍ ብሎ ከአራት ከአምስት ቤቶች በሁዋላ መዓዛና እታዩ ይኖራሉ፡፡ መፎካከርም ይወዳሉ፡፡

በሐብት ይፎካከራሉ?



@BOOKALEM

አይችሉም:: ሐብት የላቸውም::

በዕውቀት ይፎካከራሉ?

አይሆንም:: መልፋትና መስራት ይጠይቃል::

ታዲያ በምን ይፎካከራሉ?

በወንድ::

መዓዛና ሽታዬ አያንዳንዳቸው አንዳንድ ሴት ልጆች አሉዋቸው:: የደቀሉስትን ሰውዩ እነ አስማየሁ በዐይን አስተዋውቀውኛል:: ተከለሃይማኖት ቤተክርስቲያን አጠገብ ግሮሰሪ አለው:: አሳይ ሠላም ቡና ቤት አይጠፋም:: መጀመሪያ መዓዛን ይወዳታል፣ ቢያንስ እወድሻለሁ ይላታል:: ሽታዬ መዓዛን ለመቀናናቀን (በቅናት፣ በምቀኝነት) «ወደድኩህ» ትለዋለች:: ምን ችገረው? እንደ አስማየሁ አባባል ሁለቱንም «ዱቅ ዱቅ» ያደርጋል:: አንድዋ ስትርበው በሌላዋ እየጠገበ:: አንድዋ እንደ አፕሬቲፍ ስትቀሰቅሰው ሌላዋን እንደ ጎድን ጥብስ እየበላ:: የሚያስገባው አያስወጣው:: ታዲያ ሁለቱም በጥቂት ወራት የተራራቀ ሴት ልጆች ይወልዳሉ:: ወልደው እራስ ለእራስ ሲተራረሱ ነው ራሳቸውን እንደ ሽወዱ የገባቸው::

የሁለቱም እህትማማቾች ሞራል ተያይዞ ወደቀ:: በሁዋላ ታዲያ የሠፈሩ ለግላጋ ወጣቶች መሰልጠኛ ጥንድ ተቀዋሞች ሆነዋል አሉ:: አልተመዘገብኩም::

የገረመኝ ግን .......

እነሱም ዲቃሉች እንደሆኑ ሲነገረኝ ነው::

ከሁለት እህትማማቾች ከአንድ አባት በተቀራረበ ጊዜ ከትዳር ውጭ የተወለዱ::

## (11) ቅመመንና ጥቅና፡

*ተሰገብገበን ልንበላ ተደባደበን ተሰዳደበን ተጨቃጨቀን*
*አፕሬቲፍና ጥቅና፣*
*አግዜር ጮሌው ተበሳጭቶ በሰርግማን ገደረና*
*ቅመሙም መረረን*
*ጥቅናውም ጠነዛና::*

አስማየሁ ከሴት ጋር ነበርኩ ሲል፡ «ከጥቅና ጋር ነበርኩ» ይለናል::

የሆነ ኮሚሳር ሲያስቸግረው ከሆነ ካድሬ ጋር ከተላከፈ፡ «አሁን እኔን ይነጅሰኛል እንጂ አንድ መልካም ጥቅና ብትሰጠው ሁሉን ይረሳዋል» ይላል::

ታዲያ አስማየሁ ውይይት ከበብ ላይ መፈክር ሲያሰማ ድምጹ ከፍ ይላል::

«ምነው አስማየሁ? ምነ?» ስለው::



@BOOKALEM

«መንገ ወንድ ናት አየሁ። እሰዋን አወዳስሁ፣ ሁለተኛ ከሽርዬና ከጥቅናዬ እንዳይነቅሉኝ» ይሳል፡፡

«መንገ ጥቅና ይወዳል?»

«ቆንጆ ሚስት አለችው ከዚያ በላይ ምን ይፈልጋል?»

አንድ ቀን አስራ አንድ ሰዓት ገደማ አንዲት ሴት (ወይዘሮ ዝናሽ) እዚህ ማይጨው አደባባይ አዙዋሪት ጋ በመኪና አደጋ ሞታ ደምዋ ፈሶ ሳይ አጦሰኝ። አስታወከኝ። ሁለት ቀን አልበላ አለኝ። ራቁትዋን ተዘርግታ ራስዋ ወደ ፀሐይ መውጫ፣ እግርችዋም ወደ ፀሐይ መጥለቂያ ስለፍቅረኛዋ እንደምታስብ ዓይነት ግራና ቀኝ ተዘለሳ......በዚያች ቦታ በዚያች የሕዝብ መካን የአደባባዩ ፊንፊኔ እንደ ዱቄት አሳይዋ ሳይ እየተነሰነሰ፣ እኔም እንደ ወለድኩዋት እህቴ በደም የከበደ ቀሚስዋን ስመልሰላት፣ እፍረትዋን ልጋርድላት ፊቴንም ወደ ሰማይ አዙሬ፡ «ሁሳችን ደነፋን እንዷ አንተ ጳን ኸረ አንተ ጳን ማስቂያችን ቅርብ ነው» አልኩ። ስመጀመሪያ አምሳክን አየሁ። በዚያች ሴት ደም መነጥር አምሳክን አየሁት።

ሴትዮዋ ዝናሽ ነበሩ። እግርቻቸውን መሳም ፈለግሁ። ያ መንዳቱን ሳስማሳየት የኮሪ ልብ። የአንጀት ቁስሉን ከተዘጋ ቤት ጀርባ በራሱ ቀንዲል ያጠና። ከአብራክዋ የፈሰቀቀችው ዕንቡጥ አበባ ሳይሆን የጠፋ። ባለፈችበት ምንገድ ግርማ የሴሰው ማን እንደ ፈሰፈው የማይታወቅ ምፀ።

ወድቃ ግን ሀፍረትዋን በስየታ አየናት......

ግን እንዲህ እየተናገርን፡ «እያየች አትሄድም!!?......ብቻዋን ምን እንደ ዕብድ ታወራለች?»

በልባችን ግን በስየታ እንዲህ፡ «ከዚህ የከሰለ፣ የቆሸሸ ጨርቅ ስር ምን ዐይነት ተአምር አለ? ንቀነው ያለፍነ?» እያሉ እንደሆነ ይገባኛል። ከላይ ገፅዋና ቆዳዋ የማድያት ዝገት፣ እንዳለቀ ብረት.......ከውስጥ ጨርቅዋ ሲገለጥ በስየታ የሚያደነቁር ውበት። የሚያነሆልል ልስላሴ።

ታዲያ ለአርባ ቀናች ያህል ዕንቅልፍ ዕምቢ፣ መብልም አልበላልኝ አለ። አሽቆመቆመኝ። ስራ መስራት ከበደኝ። በረሀብ ልሞት ሁሉ መስሎኝ ነበር። ለጳፓን ነገርኩትና አንድ ቦታ ወስዶ አፕሬቲፍ አጠጣኝ።

ከዚያ «ጥሩ ጥቅና ያለበት ቦታ እወስድሻለሁ» አለኝ።

ቃሉ አስፈራኝ።

ጥቅና ቃሉ አስፈራኝ። የተበላሸሁ መሰለኝ። ወጣትነቴ ያለቀ፣ ስለቴም የደለደመ......ድሮ ከነበረኝ ነው ያውም።



@BOOKALEM

ዝናሽ እንዴት መልካም ነበረች?

እንዴትስ ትሁት ነበረች?

እንዴትስ ጠፋች?

## (12ሀ) ኬማ:

የመደሻና የደማ አሳቂ ኬማ ይባላል:: አብነት ሆቴል ያጋጠመን አስተማሪያችን ራሱን በምሬት ሲያሽሙዋጥጥ መሰለኝ:: ከአብዮቱ ጀምሮ ኮሚኒስት ነኝ የሚል ነበር እሱ:: ውይይት ክበብ ውስጥ የወጣለት ሞጥሙዋጣ:: ታስሮ ከተፋታ በሁዋላ፣ የሆነ ክፍለ ጦር የዕቃ ግዢ ክፍል አላፊ ሆኖ ኪሱ በረብጣ ሞልቶ የሚውለው ከሐብታሞች ጋር ሆናለል:: ከሠራተኛው አምባገነንነት ወደ ካሽ አምባገነንነት:: በዚህ መሃል በሱ አባባል ድልድዩ ሰው(12ለ) ነው:: እሱ ኬማ ነው:: ያለቀ መደሻና ማጭድ:: ያለቀለት ኮሚኒስት::

ሰው(12ለ):--መንግስትን የሚቀናቀኑ፣ ከመንግስት ጋር ያቀነቀኑ፣ እነዚህን አቀንቃኞችና ተቀናቃኞች የተቀበሉና ያንጎራጎሩ::

## (13) ባለጋቢው:

ሁልጊዜ ይሄ ነው በማይባል ሰዓት እስከ አናቱ ጋቢ ተከናንቦ ወዲያ ወደህ የሚል ሰው ነበር::

ስሙ ደመቀ ይባላል::

እንግዲህ በአጠገቡ ሳልፍ፣ ሌሎች ባጠገቡ ሲያልፉ ተከታትለንና ተደርድረን ስናልፍ (መግተልተል) ሰዎች ሲጠሩት ሰምች ነው:: ደመቀ ሰፈራችንን ከላይ ወደታችና ግራና ቀኝ በሚቆርጥዋት ሁለት መንገዶች ላይ የሚሰራው ነገር ዕንቁላል የመሰለ ጋቢ ለብሶ በቀስታ ሲራመድ መዋል ነበር:: ዱዳሲቡ የፈረሰበት እንደሆነ መገመት አይከብድም:: ሰው ቆሞ ሲያናግር፣ ሠላምታ ለሚሰጡት ሠላምታ ሲመልስ አይቸው አላውቅም:: የሚያደርገው ነገር የተለመደ ስለሆነ በአካል እንዳለም ሳይረሳም አይቀር:: ከወዲያ ወዲህ መስቀልኛ መንገዶች ሲራመድ ታዲያ አንገቱን ሰብሮ ነበር:: ከመሃል ጉዞውን አቁሞ ወደ መሬት ጎንበስ ይልና ደቃቃ ነገር ያነሳል:: በዐይኖቹ ይመረምርና ይጥላል:: መጀመሪያ ያየሁት ጊዜ ዕቃ ጥሎ እየፈለገ መስሎኝ ነበር:: ደግሜ ሌላ ቀን ሳየው .......

እንዴ ይሄ ሰውዬ ትላንት አላየሁትም እንዴ ልክ እንዲህ ሲያደርግ?



@BOOKALEM

በሦስተኛው ቀን የታመመ ሰው ነው እልኩና ደመደምኩ:: በሁዋላ ሲበዛብኝ: «ሰማችሁኝ ደሄ ሰውዩ አብዶአል እንዴ?» ብዩ ጠየቅሁ::

«አዎ......አታየውም እንዴ?»

ከዚያ ሲገርመኝ......«ልባሲ ተበጣጥሶ፣ ተቀዳዶ ሲያልቅ ነው መርፌ ላምጣ ብሉ ከቤቱ ይወጣል» አሉኝ::

አዎ ያቺ ጣቢጦሳ፣ ቀሰመወርቅ በደንብ አድርጋ ነው የያዘችው:: ፖስታ ቤት ነው የምትሰራው:: ከርችሌ ታስሮ አምስት አመት ከሱ የባሰው ፖለቲከኛ በዘመድ አግባቢነት ተለቆ ኮሌጅ ሲገባ እሱ መርፌ ፈላጊ ሆነ::

ቀሰመወርቅ ጥሩ ልጅ ነበረች::

«ሲሲትም ይወጣል ባይገርምህ»

ከመሬት የሚያነሳው ነገር መርፌ እየመሰለው ነው::

መጀመሪያ ያየሁት ሰሞን ደንዋሳ ገሳ ነበረው:: የተመቸው እንደነበረ ያስታውቃል:: እንዲህ እያየሁት እየከሳ የጋቢው ንጣት እየቀነሰ:: ፀጉሩ ያልተበጠረና የቆሸሸ እየሆነ.......

ግን መርፌ ፍለጋውን አይረሳም::

ለዐብደቱ ታማኝ የነበረ ሰው ነው::

እሱ እየከሳ ለዐይን ሲሰወር እኔና የመሳሰልነው ወዲያ ወዲህ ወድቀን ተበታትነን:: ወይስ መርፌውን ለእኔ እየፈለገ ነው?

አንድ ቀን ትክ ብዬ መልኩን ሳየው እዚያ አብዮት አደባባይ ስዕል ሲሰቀል የወደቀውን ሰዓሊ መሰለኝ:: እህቱ የተባለችውን ልጅ ሄጄ እንዳልጠይቅ «ምን አገባህ?» የምትለኝ መስሉኝ ፈራሁ:: ወሬ ከማያመልጣቸው መንታዎቹ አንድዋን ስጠይቃት ጥርጣሬዩ ትክክል እንደሆነ አወቅሁ:: ልጁ ከከርችሌ ከወጣ በሁዋላ ስዕል ትምህርት ቤት ገብቶ ይመረቃል፤ በተመረቀ በሁለተኛ ወሩ ስዕል ሲሰቀል ይወድቃል፣ ከእሱ አገግሞ ሲነሳ አውቶቡስ ይገጨዋል:: ከዚያ በቃው::

## (14) አውቶቡስ:

ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር የሚባል ነገር ነበር:: እነዚህን ሁለት ቀለሞች ሰዎች እንዴት ለመመረጥ ቻሉ? እያልኩ በዝምታ ራሴን እጠይቃለሁ:: ለእኔ ለዘረበት መሃይሙ የመሰለኝ ነጭ ሽብር የሚያደርጉት ነጭ ልብስ ለብሰው ቀይ ሽብር የሚያደርጉት ደ'ሞ ቀይ ለብሰው ነበር:: ዕውነቱን ነው:: ከሁሉም ቡድን የሞቱትን ሳያቸው......እንዲህ ቀረብ ብዩ በደም ተነክረው የወደቁበት ሳያቸው ሁሉም በእግዚር ቡኒ ናቸው:: መልካም ቡናማም አይደል.......እንዲያው የጫጫ፣ የጠወለገ፣ ሰበገናም::



@BOOKALEM

አንዳንዱ ያው ዝጉን ነው.......መችም ሞት ምን ሌሳ ቀለም ያውቃል። አይ ኢትዮጲያ ወላዲተ-ቂል አልኩዋ። ጎረቤት ጎረቤቱን በጎረቤቱ።

ንፋስ መውጫ ብሆን ኖሮ የሆነ ዓይነት ሸብር ሳላፋፍም አልቀርም ነበር። ያደገብኝ ጥላቻ ለዚህ ዐይነት አገልግሎት ሲውል ይችል ነበር። ቅር አይለኝም ነበር። ከአባቴ ቢያስጀምረኝ ፈቃደኛ ሳልሆን እቀራለሁ? እንዲህ እርቄ ሳየው አገሬ ሰፊ፣ መልካም ሰዎችም እጅግ ብዙ ናቸው። የሚያስፈልገኝ ሸብር ሳይሆን ከፈስቅሁበት ነገረኛ ሰፍራ ሳያቀዋርጥ በየቦታው የሚያመላልሰኝ አውቶቡስ ነው።

እንዲህ ርቄ የአባቴን ክፋት ረስቼዋለሁ። እንዲህም አላሰሁ፡......

እሱ ማነው?

የት ነው ያደገው? ማነው ያሳደገው?

እንዴት አደገ? በወጣትነቱ ደስተኛ ነበርን?

ያደገው በፍቅር ነውን? ሥራውን ይወዳልን?

የሚሰራውን ያውቃልን? እነዚህን ጥያቄዎች አስተካክዬ መመለስ አልቻልኩም። እንዲህም አልኩ ለራሴ......የሚያስፈልገኝ ቀደና ነጭ ሸብር ሳይሆን አውቶቡስ ነው።

እውነቱን ነው። አያስቅም። የምፈልገው አውቶቡስ ነው።

## (15) ሲስቅ

የበኩረ ሁለቱ የፊት ጥርሶቹ ገጣጦች ነበሩ። ከሌሎቹም ይጠቁራሉ። አንድ ዕለት ጳፓንን በውፍረቱ ያበሸቀዋል--መረር ባለ ሽሙጥ።

«ስሚ ጳፓን የውፍረት መቀነሻ መድኀኒት አልሰራም ዘመዶችሽ ጳፓኖቹ?» አፋን ጠመም አንድ (የቀኙን) ዐይኑን ሸውረር አድርጎ።

«ያንተን ጥርስ መንቀያ ከሰሩ በሁዋላ ነው የሚሰሩት። የምለው ምን ያህል ሉሰኛ ብትሆን ነው ሁለት ሲጃራ ደምረህ የምታጤሰው? እ? ደሞ ጭሱ አይታይም»

ከዚያ ወዲህ ተቃልዶት አያውቅም። ወይም በቀልድ ተከልሉ ሰድቦት አያውቅም።

@BOOKALEM

መዝገቡ በዛብህ አይደለም፣ የስብእናው ማራኪነትና ሳቢነት ግን የሱን ያህል ነው፡፡ ሰብለ ገነት አይደለችም፣ አንጀት በመብላት ከሆነ ግን በሁለመናዋ ከሰብለ አትተናነስም፡፡ ነፋስ መውጫ ከዚያ በፊት በስፋት እንደማትታወቀው ማንኩሳ አይደለችም፣ ነገር ግን በመዝገቡ የተነሳ እንደማንኩሳ በልብ ተቀርጻ የማይዳፈን ጉጉት ትፈጥራለች፡፡ አዳም ረታ አዲስ ዓለማየሁ አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ በሥነጽሑፋቸው ሌላ አዲስ ትውልድ የደረሰበትን የሕይወት ምዕራፍ፣ አእምሮው የሚያሰላስለውን፣ ልቡ የሚመኘውን ራዕዩን በመሳል ግን የሚያስደስቱ፣ የአዲስ ዓለማየሁ ደቀመዝሙር ባይሆኑም የሚከሩባቸው ውብ የፈጠራ ትውፊት ታማኝ ባለአደራና፣ በዚህም የክብርና ተወዳጅነት ወራሽ ለመሆን የበቁ ደራሲ ናቸው፡፡ ግራጫ ቃጭሎች ፍቅር እስከ መቃብር አይደለም፣ ሊሆን መሞከሩም አይታሰብም፡፡ ግን እንደ ፍቅር እስከ መቃብር የኢትዮጵያን ውጥንቅጥና አስገራሚ እውነታ ሥዕል አካቷል፡፡ ከገጠር እስከ ዋናዋ ከተማ፣ ከገበሬ እስከ ወፌፌ፣ ከምሁር እስከ አስማተኛ፣ ከወታደር እስከ ቦዘኔ፣ ከታሪክ እስከ ተረት ተረት፣ ከሰቆቃ እስከ ልብ የሚተረትር የደስታ ሳቅና ሁካታ ይጋብዛል፡፡

ወርቁ ሻረው

OLand Printing Press
0921785932 A.A.

ብር 75